ለፃድረሞት ትንቋቋ

ሲድኒ ሼልደን

ሚሞሪስ ኦፍ ሚድናይት



ትርጉም፡-
ሳሙኤል ማሞ ገ/ዮሐንስ

Brought to you by:
Ethiopian Bookstore
https://t.me/etbookstore

ከዓዕረ-ሞት ትንቀንቅ

ሲድኒ ሼልደን

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልዴ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ሚሞሪስ ኦፍ ሚድ ናይት

ተርጉም
ሳሙኤል ማሞ ገ/ዮሐንስ

መታሰቢያነቷ

- ለኪሮስ ሳሙኤልና
- ለተከለማርያም ሳሙኤል ነው ።

– የአሳብ ቅብብር ያደረጉልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር አቦነህ አሸገሬ (M.A)

እና

– ሥራውን ለመጀመር ያበቁኝን አቶ ልውል አባተን ከልብ አመሰግናለው ።

የሸፋን ሥዕል
ብርሃነ ሕይወት ጌታቸው

የተርጓሚው ማስታወሻ

"አንተ በሲድኒ ሼልደን ጽሑፍ ተለክፈሃል መሰለኛ" አለኝ አንድ ወዳጅ ይህንን መጽሐፍ መጀመሬን ገና እንደተመለከተ ። ይህንን መጽሐፍ ለገኘቼ ሥራውን የጀመርኩት አንድ ከበድ ያለና ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅ የጽሑፍ ሥራ ለቁርጪ ነው ። ይህንን ያደረገኩት ለስተያየት ሰጪዩ እንዳለው በሲድኒ ሼልደን ጽሑፎች ተለክፌ ለይደለም ። ይህኛውም ተርጉሚ በሲድኒ ሼልደን ሥራ ላይ ያተኮረው የትርክተ ድር ካህኑ ሲድኒ ሼልደን በትርክተ ከሸናው የለንባቢን ስሚተ ገዝተው ድርሰተቻቸው ከሚነበቡላቸው በወንጀል ፡ በወሲብና በገንዘብ ውጣ ውረድ የሚፈጠርን የሰውን ልጅ ተንቀንቀ ዓቢይ ጉዳይ በማድረግ ከሚጽፉ ዘመናዊ ደራስያን መካከል ለንዱ በመሆኑ ብቻ ነው። በሌላ በኩል ገና በዳደነት ላይ ለሚገኘው የለገሬችን ሥነ ጽሑፍ የዚህና መሰል ዘመናዊ ደራሲያን ሥራዎች ወደለማርኛ ተመልሶ መቀረብ የሥነ ጽሑፍ ቴክኒክንም በማስተማር ረገድ መጠነኛ ለስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ብዩ ሰለምገምት ተኩረቴ በዚህ ለቀጣጫ ላይ ሊሆን ችሏል ።

ወደተነሳሁበት ፍሬ ነገር ልመለስና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀናውን ገፀ ባሕርይ ሥፍራ የያዘችዋ ወጣት ሴተ ከየት እንደመጣችና እንደተስ ወዳለችበተ ሥፍራ እንደተወሰደች ሳታውቀው ነበር ታሪኳ የሚጀምረው ። ማንነቷን ለማወቅ ከምታደርገው ጥረተ ባሻገር ለንድ የሆነ ነገር ያስጨንቃ ታል፡ ያባንናታል ፡ ሰላም ይነሳታል ፡ ልተገደል መሆኗን ይገልጽላታል ። ይህ በሀሳቢ የተፈጠረው ለስጪናቂ ነገር ማንነቷን እስካወቀችበተ ጊዜ ድረስ በሕልሟና በዓይነ ኅሊናዋ እየመጣ ይተናነቃታል ።

ወደ ታሪኩ ገባ ብዩ ለንዲቷን ለንቀጽ ላቀርብላችሁ ፡–

"……ካተሪን ለሊክሳንደር ድሮ የሰማቻቸው ድምፆች እንደገና ከጀርዋ ውስጥ ገቡ ። ሆኖም የተምታቱና የተቀራረጡ ስለነበሩ ገራ ያጋቡዋታል ። …… ድምፆቹ የሚቀሙ ለይደሉም ። ያስጪንቃሉ ፡ ያሰቃይሉ ። ……" አነፒህ ሐረጉች ከላይ የጠቀስኩትን ለባባል ያጠናከራሉ ።

ደራሲው ሲደርቪልደን ለጽሑፉ "ሚሞሪስ ኦፍ ሚድ ናይት" የሚል ርዕስ የሰጠው ቢሆንም ይህንን ርዕስ እንዳለ "የሌቱ ትውስታ" ወይም "የውድቀት ተዝታ" ብዩ ለማቀረብ አልፈለግኩም ።

ከታሪኩ በለንደኖው ክፍል ካተሪን "ሊገድለኝ እኮ ነበር ...." ስትል በተናገረችው ለባባል ዙሪያ ለብዛኖው የትርክት ድሩ ሲውጠነጠን መገኘቱን የተረዳሁ መሰለኝ ። ይህ በሕልሚም ይሁን በዓይነ ኅሊናዋ ከፊቷ ተደቅኖ የሚያስፈራራትን ነገር በበኩሌ ጸዕረ ሞት ልለው ፈለግኩ ። ያሰቃያትና ያስጨነቃትም አርሱ ነበርና ከማይታወቅ ገዳይ ጋር የተደረገውን ትግል ይበልጥ ለማንፀባረቅና ከለገራችን ለንባቢያን ግንዛቤ ለኳያ የመጽሐፉን ርዕስ "ከጸዕረ-ሞት ተንቀንቀ" ልል መረጥኩ ። ያ በለሳቧ ሲያስጨንቃት የነበረው ገዳይ በወቅቱ ይከሰትና ይተናነቃታል ። ለሳቡስ ይሳካለታል ወይስ በምኞት ይቀራል? መልሱን እኔ ከወዲሁ ከምሰጥ የተወደዳችሁ ለንባቢያን ከመጽሐፉ ብታገኙ የሚሻል መስሎኝ ከመናገር ተቆጥቢያለሁ ።

ተርጓሚው

ነሐሴ ፲፱፻፹፫

መነሻ

ኩውሉን—ሜይ 1949

"በድንገት የደረሰ አደጋ መምሰል አለበት ። አንዲህ ለማድረግ ይከብድሃል ?"

ጥያቄውን እንደስድብ ቆጠረና ደሙ ፈላ ። መንገደኛ እንጂ በመስኩ የተካነ ሰው እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አይጠየቅም ። በአሽሙር እንዲህ ብሎ ሊመልስለት ነበር :— 'የሚከብደኝ አይመስለኝም ፤ ከረጅም የፎቅ ደረጃ ላይ ወድቃ አንገቷን የተቀጨች ለማስመሰል እችላለሁ ፤ ማርሴሎስ ባለው ደናሽ አማካይነት ። ወይንም ሰክራ ፤ በገላ መታጠቢያ ገንዳዋ ውስጥ ሰጥማ እንደሞተች ለማድረግም አይሳነኝም ፤ ግስታድ ባለችው ወራጁ አማካይነት ። አሊያም ሄሮይን ከመጠን በላይ ወስዳ እንደሞተችም ለማስመሰል ይቻላል ። የተቀነባበሩላት ዘዴዎች እነኚህ ሲሆኑ ሲጋራዋን ሳታጠፋ እንቅልፍ እንደወሰዳትም ለማስመሰል አያቅተኝም ።' ፓሪስ ውስጥ በኤል ሆቴል ያለውን ሲዊድናዊውን የመረጃ ሰው አስታወሰ ። 'ከቤት ውጭ ቢሆን አይሻልም ? በመኪና ወይንም በአሮፕላን አደጋ እንድትሞት ፤ አልፎም በባሕር ውስጥ እንድትሰጥም ለማድረግም እችላለሁ ።' ሆኖም ግን ከፊትለፊቱ የተቀመጠውን ሰው በመፍራቱ አሽሙሩን ይፋ አውጥቶ ሊናገር አልቻለም ። የዚህን ሰው ብዙ አስደንጋጭ ታሪኮች ሰምቷል ። የሰማቸውን ሊያምን የቻለላቸው በርካታ ምክንያቶችም ነበሩት ።

ስለዚህ "አም ጌታዬ ማንም ሊደርስበት የማይችል ድንገተኛ አደጋ ላቀናብር እችላለሁ ።" ብቻ ነበር ያለው ። እሱን ራሱን ይህን ምስጢር የማወቁ ጉዳይ አሳስቦታል። ፀጥታ ሰፈነ ።

እራሳቸውን ከአረመኔያውያን እንግሊዞች ለመከላከል ሲሉ ቻይና ውያን በ1840 ከገነቡት የኩውሉን የግንብ ከተማ ሕንጻ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ነበሩ ። ግንቡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ፍርስርሱ ወጥቷል ። እገራው ያልሆኑ ሰዎች የሚደርሱበት ሥፍራ አይደለም ። ሰው የሚያ ርፁ፣ በእደንዛዥ ዕፅ ሱስ የተበከሉና ፣ በጉልበት ሴት የሚጻፈሩ የተደራጁ ወንጀለኞች በየስርቻው በቂ ብርሃን በሌለው ጠባቡ የኩረኮንች መንገድና የግምቡ መውጪያና መውረጃ ላይ ይተረማመሳሉ ። የአገር ጉብኚዎች ወደዚህ ሥፍራ እንዳይሄዱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ፖሊሶች እንኳ ከፈትለፈቱ ካለው ከቱንግ ታው ሱዊን ጉዳና አያልፉም ። የግንብ ከተማዋ ነዋሪዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ፣ የሽካራ ፣ የጎርናና የሰላላ ድምፅ ምስቅልቅል ፣ ከመስኩቱ በኩል እየገባ ከጆሮው ይዘልቃል ።

ሰውዬው ተጠራጣሪ ዓይኖቹን በእርጋታ ተክሎበት ያጠናዋል። በመጨረሻም "መልካም እንግዲህ ፣ የዘዴውን ጉዳይ ላንተ እተዋለሁ ።" አለ ።

"እሺ ጌታዬ ። ለመሆኑ ኢላማችን እዚሁ ኩውሉን ነው ያለችው ?"

"ለንደን ። ካተሪን ትባላለች ። ካተሪን አሌክሳንደር ።"

አንድ ሊሞሲን መኪና ሁለት ጠባቂዎችን በያዘች ሌላ መኪና ታጅባ ፂም ሻ ፁይ ሰፈር ካለው ላስካር ሮው ሕንፃ ላይ ከሚገኘው ብሉ ሀውስ ሰውዬውን አደረሰች ። በብሉ ሀውስ የሚስተናገዱት ልዩ እንግዶች ብቻ ናቸው ። የመንግሥታት መሪዎች ፣ የፊልም ኮከብ ተዋንያንና የኮርፖሬሽን ፕሬዚዳንቶች ወደዚህ ሥፍራ ተመላልሰዋል ። አስተዳደሩ በአሠራሩ ላይ በሚወስደው ጥንቃቄና በምሥጢራዊነቱ ይኩራበታል ። ከሃያ ዓመት በፊት እዚህ ትሠራ የነበረች ወጣት ስለገበያ ደንበኞቿ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥታ በማግሥቱ ምላሷ ተቆርጦ ሬሳዋ በአበርዲን ወደብ ዳር ተገኝቷል ። በብሉ ሀውስ ማንኛውም ነገር ለሽያጭ ይቀርባል ። የአሥረኛው ክፍለ ዘመን የኤሺንፓ ጥበብ ከዚህ ሥፍራ በስተቀር በሌላ ቦታ አይታወቅም ። ብሉ ሀውስ ለተከለከለ ደስታ ማኅኛ የታለመ ሥፍራ ነው ።

በአሁኑ ወቅት ሰውዬው መንትያ እህትማማቾች እንዲቀርቡለት አዟል ። እንዲን ከሌላዋ ለመለየት በፍጹም አይቻልም ። ሁለቱም ሰውነታቸው ያማረ ቆንጆነት ሲሆኑ እንቢታ የሚባል ነገር አያውቁም። ባለፈው ጊዜ መጥቶ በነበረበት ወቅት ያጋጠመውን ሁሉ አስታወሰ ።

መቀመጫ የሌለው ኩርሲ ወንበር ፣ ለስላሳው የምላሳቸውና የጣቶቻቸው ዳሰሳ ፣ ሞልቶ ተርፎ ወለሉን ያጥለቀለቀው የገላ መታጠቢያው ገንዳ ውሃ ሙቀትና በትኩስ አፋቸው ገላውን ለመዳሰስ የነበራቸው እሽቅድምድም ሁሉ ትዝ አለው ። የፍትወት ሥጋ መቀስቀሻ ምልክቱ በተጠንቀቅ ሆነ ።

"መጥተናል ጌታዬ"

ከሦስት ሰዓት በኋላ ስሜቱን አርክቶ ዝግጅቱን አጠናቀቀና ወደሞዲ ጉዳና እንዲወስደው ሊሞሲኑን መኪና አዘዘ ። በሊሞሲኑ መስኮት በኩል የማታንቀላፋውን ከተማ አሸብራቂ መብራቶች አየ ። ቻይናውያኑ ጉሞ—ላንግ—ዘጠኝ ድራጉኖች ብለው ሰይመዋቸዋል ። እና ከከተማዋ በላይ ካሉት ተራሮች ላይ እድፍጠው ደካሞችንና የተዘናጉትን ወደታች ወርደው የሚያወድሙ ድራጉኖች መስለው በሕሊናው ተሳሉ ። እሱ ግን ደካማም የተዘናጋም አልነበረም ።

ሞዲ ጉዳና ላይ ደረሱ ። ቀለሙ የለቀቀ ጥንታዊያን ሩቅ ምሥራቅ ካባና ቀሚስ ለብሶ ነጭ ፂሙን እንዠርጉ በድሮ መጻሕፍት ውስጥ ያለ ሥዕል የሚመስለው የቶይስት ቄስ ይጠባበቀው ነበር ።

"ጀው ሳን ።"

"ጀው ሳን ።"

"ጌይ ዱ ቺን ?"

"ያት—ቺን ።"

"ጀው ።"

ቄሱ ዓይኖቹን ጨፍኖ በልቡ ፀሎት አደረሰና መፀለያ የልሙጭ ጉራጅችን በውስጡ የያዘውን የእንጨት ኩባያ ቺም ነቀነቀ ። አንዱ ጉራጅ መሬት ሲወድቅ መነቅነቁን አቆመ ። ወጥታ ነገሙ ። ቶይስቱ ቄስ ወደሰንጠረዡ ዞሮ ካየ በኋላ ወደእንግዳው ተመለከተ ። በተሰባበረ እንግሊዝኛ "ከክፉ ባላንጣዎችህ ትላቀቃለህ ይሉሃል እግልክቶቹ" አለው ።

ሰውዬው በሰማው ተደስቷል ። ይሁንና ብስለቱ የቺምን ጥበብ እንደ አጉል እምነት ከመቁጠር አላገደውም ። ብልሀነቱ የሰማውን ችላ እንዲለው አድርጉታል ። ከዚህም ባሻገር ጥሩ ምልክት ይታያል ። ዛሬ የቅዱስ እጊዮስ ኩንስታንቲነስ በዓል ነው ። የልደት ቀኑ ።

“አግልክቶች በፋንግ ሹይ ፡ ባርከውሃል ።”

“ዱ ጂህ ።”

“ሁ ዋህ ።”

ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወደአቴንስ ሊመልሰው ከሆንግ ኩንግ አውሮፕላን ጣቢያ ከሚጠብቀው የግል አውሮፕላኑ ለመሳፈር ከሊሞሲን መኪናው ገብቶ ወደ ካይ ቴክ ነጉደ ።

ምዕራፍ አንድ

ኢኦኒና ፡ ግሪክ — ጁላይ ፡ 1948

ዘወትር እየጮኽች ነው ከእንቅልፍ የምትነቃው ። ሁሌ የምታየውም ሕልም ያው አንድ አይነት ነው ። በአስፈሪ ማዕበል በሚናወጥ ሐይቅ መሐል ሆና ፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ቅዝቃዜው አጥንት በሚሰብረው ውሃ ወስጥ ጭንቅላቷን ለማዝፈቅ ሊያሰጥሟት ሲታገሉ ነው ያለመችው ። ባንና ስትነቃም በላብ ተጠምቃ በፍርሐት እየተርበደበደችና ቁና ቁና እየተነፈሰች ነበር ።

ማንነቷን ጨርሳ ዘንግታለች ። የሚታወሳትም ከቶ ምንም ነገር አልነበረም ። የምትናገረው ቋንቋ እንግሊዝኛ ቢሆንም አገሯ የት እንደሆነ እንዴትስ ወደ ግሪክ መጥታ በትንሿ ካርሜላይት የሴቶች ገዳም ውስጥ እንደገባች የምታውቀው ነገር አልነበረም ።

ውሎ ሲያድርም ቅጡ የማይታወቅ ትውስታ ለቅጽበት ብቹ— ብልጭ ብሎ እያንጓጓ ወዲያው ድርግም በማለቱም ምስጡን አሰባስባ ልትጨብጥ አልተቻላትም ። ድንገት ባላሰበችውና ባልጠበቀችበት ወቅት ብቅ ብለው ያደነጋግሯታል ።

በመጀመሪያ ጥያቄዎችን አቀራርባ ነበር ። በካርሜል የሚገኙ መነኩሳት ደግና የሰው ችግር የሚገባቸው ቢሆኑም ለጥያቄዋ ምላሽ ለመስጠት እንዲናገሩ የተፈቀደላቸው ከሁሉም በዕድሜ ጠና ያሉትና ሰውነታቸው የደቀቀው የበላይዋ ሲስተር ተሬዛ ብቻ ናቸው ።

“ማን እንደሆንኩ ያውቃሉ ?”

“አላውቅም ልጂ !” አሉ ሲስተር ተሬዛ ።

“ወደዚህ ሥፍራ የመጣሁት እንዴት ነው ?”

“ከእነዚህ ተራሮች ስር ኢኦኒና የተሰኘች መንደር አለች ። ባለፈው

ዓመት ማዕበል ተነስቶ በነበረበት ወቅት በሐይቁ ላይ በትንሽ ጀልባ ውስጥ ነበርሽ ። ጀልባዋ ስትሰጥም በእግዚአብሔር ቸርነት ሁለት እህት መነኩሳት አይተውሽ ሕይወትሽን ሊያተርፉ ቻሉ ። ከዚያም ወዲህ እመጡሽ ።”

“ማን ... ከዚያ በፊት የነበርኩት የት ነው ?”

“ልጄ አዝናለሁ እኔ አላውቀውም ።”

በመልሱ ልትረካ አልቻለችም ።

“ስለ እኔ የጠየቀ ሰው የለም ? ሊፈልገኝ የሞከረስ አልነበረም ?”

ሲስተር ተሬዛ ጭንቅላታቸውን በመነቅነቅ “ማንም” አሉ ።

ከጭንቀት የተነሳ ልትሮሀ ፈለገች ። ቀጥላም “ጋዜጦች ... ስለ እኔ መጥፋት በአምዶቻቸው ላይ ያሰፈሩት ዜና ይኖር ይሆናል” አለች ።

“እንደምታውቂው ከውጭው ዓለም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንድናደርግ አይፈቀድልንም ። እግዚአብሔር ያለውን መቀበል አለብን ልጄ ። ለይቅርታው ሁሉ ልናመሰግነው ይገባናል ። በሕይወት ተርፈሻ ልና ።”

ለግግፕት የቻለችው ምላሽ ይኸንኑ ብቻ ነበር ። በመጀመሪያ ሰሞን ስለአራሷ መጨነቋ ከበሽታ ላይ ጥሏት ነበር ። ወራት እያለፉ ሲመጡ ቀስ በቀስ ጥንካሬ እያገኘችና ጤንነትዋም እየተሟላ መጣ ። ለመንቀሳቀስ ብርታት ስታገኝ መላውን ግሪክ ሺ ! የሚያደርገውን ጣፋጭ ፀሐይ እየሞቀች ፣ ነፋሻው አየር ያዘለውን የወይንና የሎሚ መአዛ እያሽተተች ፣ ውቡን የገዳም አትክልት ስትንከባከብ ቀኑን ታሳልፋለች ።

ምንም እንኳ አካባቢው ፍፁም ሰላማዊና ፀጥታ የሰፈነበት ቢሆንም የተረጋጋ መንፈስ ልታገኝ አልቻለችም ። ‘እንዲህ ጠፍቼ የትገባች ምን ሆነች ብሎ የሚያስብ ሰው ይጥፋ ?’ ብላ አሰበች ። ‘ለምን ? የፈጸምኩት በደል አለ ? ለመሆኑ ማን ነኝ ? ማን ልሆን እችላለሁ ? እረ እኔ ማን ነኝ ?’

ትውስታዎቹ ድንገት ብልጭ ይሉባታል ። አንድ ቀን ጠዋት ከእንቅልፏ ባንና ስትነሳ አንድ እርቃኑን የነበረ ሰው በአንድ ክፍል ውስጥ ልብሶችዋን ሲያወላልቅ በአዕምሮዋ ውልብ አለባት ። ነገሩ ሕልም ነው ? ወይንስ ባለፉት ጊዜያት በሕይወቷ ውስጥ የተፈጸመ እውነታ ይሆን ? ማነው ሰውዬው ? አግብታው የነበረ ሰው ይሆን ? ባልስ ነበራት ? የጋብቻ ቀለበት ደግሞ ከጣቷ ላይ የለም ። ሲስተር ተሬዛ ከሰጧት ጥቁር የመነኩሳት ልብስና ክንፉ የተዘረጋ ባለቀይ ዓይን ወርቅማ የወፍ ቅርጽ

ትንሽ የደረት አርማ በስተቀር ሌላ የግሏ የሆነ ነገር አልነበረም ።

ስም የሌላት በባዕዳን መካከል የምትኖር ባዳ ነበረች ። የሚረዳት ሰው የለ ። በከፍተኛ ጭንቀት የተወጠረው አእምሮዋ ፣ ጤነኛ ሆና ለመቆየት የሚችለው ፣ ዘግናኝ የቀድሞ ገጠመኝን ለማስታወስ እስካል ታጣ ጊዜ ድረስ ብቻ መሆኑን የሚነግራት የስነ አእምሮ ሀኪም የለም ።

ምስሎቹ በፍጥነት እየተከታተሉ መታየቱን ቀጠሉ ። አንጐሏ የተበታተኑ ቁርጥራጭ ሥዕሎችንና የመልክዓምድር ካርታዎችን በየመል ካቸው ለማገጣጠም ወደሚያገለግል ሰው ሰራሹ መሣሪያ በድንገት የተለወጠ ያክል ነበር ። ቢሆንም ቅንጭብጫቢ እይታዎቹ ስሜት ሊሰጡ አልቻሉም ። የወታደር ልብስ የለበሱ ሰዎች የሞሉበት ትልቅ የሲኒማ መቅረጫ አዳራሽ ራዕይ ውልብ ይልባታል ። ፊልም በመስራት ላይ የነበሩ ሳይሆኑ አልቀሩም ። ‘የፊልም ተዋናይ ነበርኩ ይሆን ?’ ብላ እራሷን ትጠይቅና ፣ ደግሞ በኃላፊነት ቦታ ላይ የነበረች ይመስላታል ።

ግን በምን ዓይነት የኃላፊነት ቦታ ?

አንድ ወታደር እቅፍ አበባ ያበረክትላታል ። “ለዚህ ሁሉ እራስሽ መክፈል አለብሽ” ይልና ይሰቅባታል ።

ከሁለት ምሽቶች በኋላ እንደገና ስለዚሁ ሰው ሕልም አየች ። በአውሮፕላን ማረፊያ ስትሰናበተው ከሱ በመለየቷ እየተንሰቀሰቀች ነበር ከእንቅልፏ የነቃችው ።

ከዚያ በኋላ ሰላም ልታገኝ አልቻለችም ። ይህ የሕይወቷ አካል ቁራሽ ፣ ያለፈው ኑሮዋ ክፍል እንጂ ሕልም ብቻ አይደለም ። ‘ማን እንደነበርኩ ማወቅ አለብኝ ፣ ለመሆኑ ማን ነኝ ?’

ሳይታሰብ በድንገት እኩለ ሌሊት ላይ ከሥውር ሕሊናዋ አንድ ስም ፍንትው አለባት ። “ካተሪን ። ስሜ ካተሪን አሌክሳንደር ነው ።”

ምዕራፍ ሁለት

አቴንስ ፡ ግሪክ

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ የግዛት ክልል በማንኛውም ካርታ ላይ ተከልሎ አይታወቅ እንጂ ፡ የሚያስተዳድረው ጉልት በስፋትም ሆነ በጎይል ከብዙ አገሮች የላቀ ነበር ። በዓለም ላይ ካሉት ከሁለት ወይንም ከሦስት ከማይበልጡት ታላላቅ ባለፀጋዎች መካከል አንዱ ሲሆን ፡ ተደማጭነቱና ተሰሚነቱም ያንኑ ያክል ከፍ ያለ ነበር ። የተሰጠው ማዕረግ ወይንም ሥልጣን ባይኖርም ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ፡ መኳንንቱን ፡ አምባሳደሮች ንና ነገሥታትን እንዳስፈለገው ያሽከረክራል ። ዴሚሪስ በበርካታ አገሮች ላይ መረቡን የዘረጋ የዋዛ ያልሆነ ሰው ነው ። ግርማ ሞገስ የተጎናፀፈ በብሩህና በበሳል አእምሮ የታደለ ከመሆኑ ባሻገር ሙንቻማው ደረቱ ፡ ሰፋፊ ትከሻዎቹና ዘንካታ ቁመናው በግድ እዩት — እዩት ያሰኛል። የቆዳው ንጣት የጠየመ ፡ ጠንካራ የግሪክ አፍንጫ ያለው ፡ ዓይኖቹ የጎመራ ወይራ ፍሬ የሚመሳስሉ ናቸው ። የነጣቂ ጭልፊት ፊትም ዓይነት ፊት ነው ያለው ።

ነገር ያነፈነፈ ዕለት ዴሚሪስ ጨርሶ ፎለፎል ይሆናል ። ስምንት ቋንቋዎችን አጠናቆ ያውቃል ። አንደበተ ርቱዕ ነው ። በዓለም ውስጥ የታወቁ ሥዕሎች ስብስብ አለው ። በርካታ የግል አውሮፕላኖቹ ፡ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አፓርታማዎቹ ፡ ቪላዎቹና ሕንጻዎቹ ፡ ተሰራጭተው የማይገኝበት የዓለም ክፍል የለም ። ውበት አድናቂ ከመሆኑ የተነሳ ቆንጆ ሴት አይቶ ማለፍ አይሆንለትም ። ጥሩ አፍቃሪ ነው እየተባለም በሰፊው ይነገርለታል ። ሀብት ንብረት ማካበት እንደሚሳካለት ሁሉ የሴቱም ነገር ይዋጣለታል ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አገር ወዳድ ነኝ ብሎ በመኩራራት የግል ይዞታው በሆኑት በኮላናኪና በፐሳራ ደሴት ላይ በሚገኙት ቪላዎች አናት

ላይ ሰማያዊና ነጭ ቀለም ያለው የግሪክ ሰንደቅ ዓላማ ሁሌ ያውለበልባል። የሚፈለግበትን የመንግሥት ግብር ግን አይከፍልም ። በተራ ዜጎች ላይ ለሚሠራው የአገሪቱ ሕግ ተገዥ የሚሆንበትም ምክንያት ያለ አልመሰለውም ፤ በደም ሥሩ ውስጥ የሚዘዋወረው የአግልክት ደም ነውና ።

* * *

ዴሚሪስ የሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ ከእርሱ አንድ ነገር ይፈልጋሉ ። ግማሾቹ ላቀዱት የንግድ ፕሮጀክት ገንዘብ እንዲሰጣቸው ፡ ግማሾቹ ለበጎ አድራጎት ድርጅት የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ የሚሹ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ጥላ ከለላ እንዲሆናቸው በወዳጅነት ይጠጉታል ። ዴሚሪስ ሰዎቹ ከእሱ የሚሹት ምን እንደሆነ መርምሮ ማወቁ ደስታን ይሰጠዋል ። ምክንያቱም አቀራረባቸው አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛና ግልጽ ሳይሆን በሰበብ አስባቡ ተሸፍኖ ስለሆነ ነው ። ከተጠራጣሪነቱና ነገርን ከየአቅጣጫው ከመመርመር ባሕርይው የተነሳ የሚነገረውንና የሚታየውን እንዳለ የሚቀበል አይደለም ። የሰማውን ሁሉ የማይቀበልና፡ ማንንም የሚያምን ሰው አልነበረም። የሚመራበት ፍልስፍና “ወዳጆች ህን አቅርባቸው ፡ ጠላቶችህን ግን የበለጠ አስጠጋቸው” የሚል ነው ። ዜና መዋዕሉን የሚጽፉትም ጋዜጠኞች የሚረዱት ጨዋነቱን ፡ ቀናነቱን፡ ማራኪነቱን ፡ ዘመናይነቱን በዓለም ውስጥ ካሉት ትሑት ሰዎች አንዱ የመሆኑን የላይ ላዩ ገጽታ እንጂ ነፍሰ ገዳይ ፡ የአንገት ደም ሥር ካልበጠሰ የማይረካ ገትጋታ ደመ ጥመኛ የመሆኑን አውነታ ለመጠርጠር ዕድል አልሰጣቸውም።

ይቅርታ የለሽ ፡ ጥቃቅኑን ነገር የማይረሳ ቂመኛ ነው ። ለጥንት ግሪካውያን “ዲካዮሲኒ” ማለትም “ፍትሕ” የሚለው ቃል “ኤክዲኪ ሲሳ” ማለትም “ብቀላ” ከሚለው ቃል ጋር ተጓዳኝነት አለው ። “ዴሚሪስም በነጂው ቃላት ተለክፏል ። ቀድሞ ያስቀየሙትንና ያሰቃዩትን ሁሉ አይረሳም ። ሳይታደሉ ቀርተው የእርሱን ጠላትነት ያተረፉ ሁሉ ለፈጽሙት ተግባር በመቶ እጥፍ አሳር ፍዳ ከፍለዋል ። የዴሚሪስ ተአምራዊ ጭንቅላት ለብቀላ የረቀቀ ዘዴውን በሚሸርብበት ወቅት ዒላማው የሆኑት ሰዎች ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ አያድርባቸውም ። በትእግ

ሥት ረጋ ብሎ በሰፊው እያውጠነጠነ የተወሳሰበ መረቡን ይዋልባቸ ዋል። በመጨረሻም በትብትቡ ውስጥ ያፍናቸውና ጠላቶቹን ሁሉ ሲጥ ያደርጋቸዋል ።

ተቀናቃኞቹን ለማጥፋት አሳቡን ሲያወጣና ሲያወርድ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል ። ዒላማዎቹ የሆኑትን ግለሰቦች ማንነት በሚገባ ያጠናል። ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን ደህና አድርጉ ይገመግማል ።

አንድ ቀን ዴሚሪስ በእራት ግብዣ ላይ እንዳለ አንድ የተንቀሳቃሽ ፊልም አምራች “ያ ሙልጭልጭ ግሪካዊ” እያለ ሲያማው ሰማ ። ዴሚሪስ ለጊዜው ሃሜቱን ዋጥ አድርጉ ዝም ። ከሁለት ዓመታት በኋላ ይሄው ፊልም አምራች በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀች አንዲት ተዋናይ ኩባንያው በሚቀርፀው አንድ ታላቅ ፊልም ውስጥ እንድትጫወት ኮንትራት ያስፈርማታል ። ዴሚሪስ የፊልሙ ሥራ ግማሽ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ በዝምታ ይመለከታል ። ከዚያም ተዋናይዋ የጀመረች ውን የፊልም ሥራ እንድታቋርጥ በፍቅር ያጠምድና ወደ መንሸራሸሪያ ጀልባው እንድትገባ ይጋብዛታል ። “ይህ እንግዲህ የጫጉላ ጊዜያችን መሆኑ ነው” ይላታል ዴሚሪስ ተዋናይዋን ።

ጋብቻው ሳይፈፀም መሞሸሯ ነው ። በቃ ፊልሙ ሳይሰራ ቀረ ፣ አምራቹም ከሰረ ።

ዴሚሪስ ለጊዜው ውጤት ላላስቆጠረባቸው ግን በእለምሮው ውስጥ የሸር መረብ ለዘረጋላቸው በጣት የሚቆጠሩ ተቀናቃኞች ሊጣደፍ አልፈለገም ። ግጥሚያውን በእሽናፊነት የሚወጣበትን አሳብ ማመንጨቱ ፣ ማቀዱና ተግባራዊ ማድረጉ ለዴሚሪስ እርካታን ይሰጡታል ። በአሁኑ ወቅት ፣ ሰው ሁሉ የዴሚሪስ ጠላት መሆን እንደማያዋጣ በመረዳቱ ያፈራው አዲስ ጠላት የለም ። ስለዚህ ዒላማው ያተኮረው ባለፈው ጊዜ በመንገዱ ላይ ቆመው በነበሩት ተፃራሪዎቹ ላይ ብቻ ነው ።

ይሁንና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ‘ለዲካዮሲኒ’ (ለፍትሕ) ያለው አመለካከት ሁለት ገጽታ ያለው ነው ። ለተፈፀመበት በደል ይቅርታ እንደማያደርግ ሁሉ የተደረገለትን ውለታ የሚረሳ አይደለም ። ዴሚሪስ ልጅ በነበረበት ወቅት መጠለያ ሰጥቶት የነበረ አንድ ድሃ ዓሣ አጥማጅ ሳያስበው የብዙ ዓሣ ማጥመጃ ጀልባዎች ባለቤት ሆኗል ።

ከድህነቱ የተነሳ በልጅነት ዕድሜው ፣ ምግብና ልብስ በነፃ ትሰጠው የነበረች አንድ ሴተኛ አዳሪ ፣ ድንገት ሳታውቀው የአፓርትማ ሕንፃ ባለቤት ሆናለች ። ሕንፃውን ግን እንደለገሣት ግን የምታውቀው ነገር የለም።

* * *

የዴሚሪስ አባት በፒሮዱስ ወደብ አካባቢ በመርከብ ላይ ተሸካሚ ነት ጉልበቱን ሸጦ ይተዳደር ነበር ። ዴሚሪስ አሥራ አራት ወንድሞችና እህቶች ነበሩት ። በቤታቸው ውስጥ ሆድ የሚያጠረቃ ምግብ ገበታው ላይ የቀረበበት ቀን አልነበረም ።

ከመጀመሪያውኑ አንስቶ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለንግድ ሥራ የነበረው ዝንባሌ ከፍተኛ ነበር ። ከትምህርት ሰዓት በኋላ ሰው የሚጠየፈውን የተላየየ ሥራ እያከናወነ ገንዘብ ያገኝ ነበር ። ዕድሜው አሥራ ስድስት በሆነበት ወቅት ገንዘብ ተጠራቅሞለት ነበርና ከአንድ በዕድሜ ገፋ ካለ ሸሪክ ጋር በመደቡ አካባቢ አነስተኛ የምግብ መሸጫ ኪዮስክ ከፈተ ። ገበያው ሲደራና ንግዱ ሲጧጧፍ ሸሪኩ ዴሚሪስን ካደውና ከሽርክናው አባረረው ። ዴሚሪስ ሰውየውን ለማጥፋት አሥር ዓመት ፈጀበት ። ወጣቱ በከፍተኛ የዕድገት ፍላጎት ይጨስ ጀመር ። ሌሊት በጨለማው ላይ ዓይኑን አፍጦ ‘ሀብታም እሆናለሁ ፣ ዝነኛ እሆናለሁ ፣ አንድ ቀን ስሜ በሁሉም ዘንድ ይታወቃል’ እያለ ያስባል ። ይህ ሐሳብ ብቻ ነው እሹሩሩ እያለው እንቅልፍ የሚያስወስደው ። ምኞቱ እንዴት እውን እንደሚሆን ግን አያውቅም ። ብቻ አንድ ቀን እንደሚሳካለት እርግጠኛ ነበር ።

* * *

ዴሚሪስ አሥራ ሰባተኛው የልደት በዓሉን ሲያከብር ስለሳውዲት ዓረብ የነዳጅ ዘይት በጋዜጣ ላይ የወጣውን አነበበ ። የዕድሉ በር ፣ ወለል ብሎ ሲከፈት ታየው ።

ወደ አባቱ ሄዶ “ወደ ሳውዲት ዓረብ መጓዜ ነው ። በነዳጅ ዘይት ማምረቻ ውስጥ ተቀጥሬ ልሠራ” አለ ።

“ስለነዳጅ ዘይት ማምረቻ ምን ታውቅና?”
“ምንም አላውቅም አባባ ። ወደ ፊት ልማር ነው ።”
ከአንድ ወር በኋላ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደዚያው ተጓዘ ።

* * *

ከውጭ የሚመጡ ተቀጣሪዎችን የሁለት ዓመት የሥራ ኮንትራት ውል ማስፈረም የትራንስ ኮንትኔንታል የነዳጅ ዘይት ኮርፖሬሽን ደንብ ነው ። ቢሆንም ኮንትራቱን መፈረሙ ዴሚሪስን ምንም ያህል አላሳሰበ ውም ። የወደፊት ዕድሉ እስኪሰምርለት በሳውዲት ዓረብ ውስጥ ለመቆየት አቅዷል ። ሰምቶት የነበረው ማራኪ የጥንታዊ አረቦች ጀብድ አፈታሪክ ፣ ትንግርት ያላቸው ሴቶችና አስደናቂዋ ምድር ፣ እንዲሁም ከመሬቱ ውስጥ ስለሚፈልቀው ጥቁር ወርቅ በሚያጓጓ ሁኔታ በሕሊናው ስሎ ነበር ። ደርሶ ሲያየው ግን የሚሰቀጥጥ ሆኖ ነው ያገኘው ።

በበጋው ወራት አንድ ቀን ጠዋት ዴሚሪስ በበረሃው መሐል ከሚገኘው ቀፋፊ የፉዲሊ ካምፕ ደረሰ ። በካምፑ ውስጥ ያሉ የድንጋይ ቤቶች በባራስቲስ በጥሻ በተሠሩ ጐጆዎች ተከበው ለዓይን ያስጠላሉ ። አነስተኛ ክፍያ የሚያገኙ በሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞች በሥፍራው ይሠራሉ ። አብዛኛዎቹ የሳውዲ ዜጎች ናቸው ። በአቧራማው ጥርጊያ ጐዳናዎች ላይ የሚጓዙት ሴቶች ፊት በመርገፍ ተሸፍኗል ።

ዴሚሪስ ፣ የኮርፖሬሽኑ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ የጂ ጂ ማክልንታይር ቢሮ ወደሚገኝበት ሕንፃ አመራ ።

ወጣቱ ልጅ ወደ ቢሮው እንደገባ ማክልንታይር ቀና ብሎ “ተቀጥረህ መምጣትህ ነው?” ሲል ጠየቀው ።

“አዎ ጌታዬ ።”

“ከዚህ በፊት በነዳጅ ማምረቻ መስክ ሠርተህ ታውቃለህ ልጄ?”

ዴሚሪስ ለመዋሸት ትንሽ ቃጣውና “አይ ጌታዬ” ብሎ መለሰ ።

ማክልንታየር ፈገግ አለ ። “አይዞህ ትንሽ ስትሰነብት ሥፍራውን ትወደዋለህ ። በእርግጥ ያለህበት ቦታ ከከተማ ሚሊዮን ማይል ርቆ ነው ያለው ። ደህና ምግብ አይገኝም ። የመጥረቢያ ሲላይ ለመሆን ካላሻህ በቀር ሴት ለመንካት አታስብም ። ማታ ማታማ የምታደርገው ምንም ነገር የለም ። ቢሆንም ክፍያው ጥሩ ነው ። እሺ?”

“እኔም ትምህርት ልቀስም ነው አመጣጤ” ሲል መለሰ ዴሚሪስ በትህትና ።

“እሪ? ደግ ፣ እንግዲህ በመጀመሪያ መማር የሚገባህ ምን እንደሆነ ልንገርህ ። ያለኸው በእስላሞች አገር ውስጥ ነው ። አልኮል መጠጣት ክልክል ነው ። ሲሰርቅ የተያዘ ቀኝ እጁ ይቆረጣል ። ለሁለተኛ ጊዜ ከሰረቀ ግራ እጁ ይደገማል ። ሰው ከገደልክ ደግሞ አንገትህ ይቀነጠሳል።”

“ማንንም የመግደል እቅድ የለኝም ።”

“ቆይ” አለ ማክልንታየር ኮስተር ብሎ ። “ነና እዚህ መድረስህ አይደል?”

ቅጥር ግቢው ከተለያዩ አገሮች የመጡ እንደባቢሎን ግምብ ሠራተኞች ሁሉም በየፊናው የየራሱን የተለያየ ቋንቋ የሚናገርበት ነው ። ዴሚሪስ ጥሩ የመስማት ችሎታ ያለው ሲሆን ቋንቋም ቶሎ የማወቅ ተሰጥኦ አለው ። በዚያ በረሃ ውስጥ የመንገድ ሥራና ቤት እንፃ ይካሄዳል ። የኤሌክትሪክና የስልክ መሥመር ይዘረጋል ። የዐውደ ጥናት ማካሄጃ ተቋም ፣ የምግብና የመጠጥ ማከፋፈያ ፣ የቱቦ ቀበራ ቅየሳ ፣ እንዲሁም የሕክምና ግልጋሎቶች ዝግጅት ሲከናወን ይታያል ። ሌሎችም በርካታ የተለያዩ ተግባሮች ሲከናወኑ ወጣቱ ዴሚሪስ ተመልክቷል ። ሰዎቹ በመቶ ዲግሪ ፋራናይት የሙቀት መጠን እየተቀቀሉና በዝንብ፣ በትንኝና በአቧራ እየተሰቃዩ ተግባራቸውን ያከናውናሉ ። ትኩሳትና ተቅማጥ በየጊዜው ይፈራረቅባቸዋል ። በዚህ በረሃ ውስጥ እንኳ በሰዎች ግንኙነት መካከል የደረጃ መበላለጥ አለ ። በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ነዳጅ ዘይቱ የት እንደሚገኝ ፍለጋ የሚያደርጉት ናቸው ። ከታች ያሉት የኮንስትራክሽን ሠራተኞች ሲሆኑ እነኝህም “ወዝ አልባ” በሚል ልዩ ስያሜ ይታወቃሉ። በጽሕፈት ሥራ ለተሠማሩትም “አብረቅራቂ ግሮ ጥሮ” የሚል ቅጽል ተሰጥቷል ።

በአጠቃላይ በዘይት ቁፋሮው ተግባር ላይ የተሠማሩት ማለትም የሥነ አፈር ተመራማሪዎች ፣ ቀያሾች ፣ መሐንዲሶችና የዘይት ኬሚስቶች በሙሉ አሜሪካውያን ናቸው ። ምክንያቱም ዘመናዊ የነዳጅ ዘይት ማውጫዎች መሣሪያ በዩናይትድ ስቴትስ በመፈልሰፉና አሜሪካኖች በዚህ መሣሪያ የመጠቀም ልምድ አላቸው ተብሎ ስለሚታመንበት

ነው። ወጣቱም ከተሰጠው የሥራ ድርሻ ወጣ እያለ ከእነኚህ ሰዎች ጋር ወዳጅነት ለመመሰረት ጥረት ጀመረ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አብዛኛውን ጊዜውን በእነኚህ ቆፋሪዎች አካባቢ በማሳለፍ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀርብላቸው ነበር ። ልክ ሞቃቱ እሸዋ ውሃ እንደሚመጥ ሁሉ የሚያገኛቸውን መልሶችና መረጃዎች በአእምሮው እየመጠጠ ያጠራቅማል ።

130 ሜጣ ርዝመት ያለውን በጣም ግዙፍ የመቆፈሪያ መሣሪያውን ተሸክሞ ያለውን ባለብዙ ማገር የብረት ምሰሶ የሚያንቀሳቅሱትን ባለሙያዎች ተጠጋና የቁፋሮው ተግባር ለምን በሁለት በተለያዩ መንገዶች በመከናወን ላይ እንዳለ አልገባኝም" ሲል ጠየቀ ።

ቆፋሪውም "ልጄ ፣ እንዱ ባለሽቦ መደርመሻ ሲሆን ሌላው ደግሞ ሹል ሜፍ ኖሮት በፍጥነት እየተሽከረከረ የሚቆፍረው ሮተሪ ነው ። በዛሬው ጊዜ በአብዛኛው ሮተሪ ነው የሚመረጠው ። ሁለቱም ቢሆኑ ለአገልግሎት ሲጠመዱ አጀማመራቸው ላይ ተመሳሳይነት አላቸው ።"

"ተመሳሳይነት አላቸው?"

"የባለሽቦ መደርመሻውም ሆነ ሮተሪው የሚገጠምበት ይህን የሚመስል ዴሪክ ነው ። መቼም ዴሪክ ሲሰራ አይተሃል ። ትልልቅ ሕንፃ ሲሰራ እየተሽከረከረ ከባድ ዕቃ ሲያቀብል ። እይ ፣ ግዙፍ የብረት ግማ ነው አይደል? እና ዴሪክ መተከል አለበት" አለና ቆፋሪው በጉጉት መልሱን ይጠብቅ ወደነበረው ወጣት ፊት ተመለከተ ። ቀጠለና "መሣሪያው ዴሪክ ለምን እንደተባለ እንደማታውቅ እርግጠኛ ነኝ" አለው ።

"አላውቀውም ጌታዬ ።"

"ዴሪክ በአሰራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወንጀለኞችን ይሰቅል የነበረ ሰው ስም ነው ።"

"ገባኝ ።"

"ባለሽቦ መደርመሻው ቀደምትነት አለው ። ከመቶ ዓመታት በፊት ቻይናውያን የውሃ ጉድጓድ ይቆፍሩ የነበሩት በዚህ መሣሪያ ነበር ። እጅግ በጣም ከባድ የሆነ ሹል መሣሪያ በወፍራም ሽቦ ላይ አስረው ወደ ላይ ካንጠለጠሉ በኋላ ወደ መሬት ሲለቁት ይቦድሳል ። በዛሬው ጊዜ ግን ሰማንያ አምስት በመቶው የጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ ተግባር የሚከናወነው በሮተሪ ነው ።"

"ይቅርታ ፣ የሮተሪ አቆፋፈር የሚከናወነው እንዴት ነው?"

ሰውየው ዝም ካለ በኋላ "መልካም ፣ ጉድጓድ ለመቆፈር መሬቱን ከመቅደድ ይልቅ ቀስ በቀስ ትቦረቡራለህ ። ይህን ታየለህ? በዴሪኩ መካከል በመሣሪያ አማካይነት የሚሽከረከር ከብ ብረት አለ ። ይህ ከብ ብረት ቧንቧውን ነክሶ በመያዝ እያሽከረከረ መሬት ውስጥ ያዘልቀዋል ። ከቧንቧው ሜፍ ላይ ጠንካራ የብረት ምላጭ ተሰክቷል ።"

"ይሄ ቀላል ይመስላል ።"

"እንደምታየው ቀላል ሳይሆን ውስብስብ ነው ። ቁፋሮውን በምታካሄድበት ወቅት አፈሩን ከሥር የምታስወጣበት ዘዴ መኖር አለበት ። ጉድጓዱ እንዳይደረመስ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻሃል ። በጥግና ጥግ ጋዝና ውሃ ሲመነጭ ማሸግ ይኖርብሃል ።"

"ታዲያ ያ ሁሉ ጥልቀት ሲቆፈር ሮተሪው እይዶለዱምም?"

"ልክ ነህ በሚዶለዱምበት ጊዜ መቦርቦሪያውን ሰበን እናወጣውና አዲስ ምላጭ ቧንቧው ሜፍ ላይ እጉርሰን መልሰን ወደ ጉድጓዱ እንጨምረዋለን ። እንዴት ነው ቆፋሪ ለመሆን ትለፍጋለህ እንዴ?"

"አይ ጌታዬ የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ባለቤት ለመሆን ነው የምፈልገው"

"ጎሽ! በል ፣ ወደ ሥራዬ ልመለስ ።"

አንድ ቀን ጠዋት መቆፈሪያው ከጉድጓዱ ውስጥ ሲዘተት እየ። መሣሪያውም ወደ ታች እንደመቦርቦር ፈንታ የጉድጓዱን ግድግዳ በስቶ ድንጋይ ይዞ ሲወጣ ዴሚሪስ ተመለከተ ።

"ይቅርታ እንዲህ የሚደረገው ለምንድን ነው? " ሲል ዴሚሪስ ጠየቀ።

ቆፋሪው ቀና ብሎ ቅንድቡን ጠረገና "ነዳጅ ዘይት መኖር አለመኖሩን የምንረዳው ድንጋዩን በመመርመር ነው" አለ ።

"ገባኝ።"

ሥራው በደህና ሁኔታ በመከናወን ላይ እያለ ቆፋሪዎቹ "ወደ ቀኝ በኩል መታጠፈ ነው" እያሉ ሲጮሁ ዴሚሪስ ይሰማል ። ትርጉሙ ጉድጓድ እያበጀን ነው ማለት ነው ። ዴሚሪስ ስፋታቸው ከሁለትና ሦስት ኢንች የማይበልጡ በጣም ብዙ ጉድጓዶች በየቦታው መማሳቸውን ልብ ብሏል ።

"ይቅርታ ፣ እነኚህ ደግሞ ለምን የሚሆኑ ናቸው?" ሲል ጠየቀ ወጣቱ ። "እነኚህ ተስፋ ያላቸው ጉድጓዶች ናቸው ። ከሥራቸው ምን እንዳለ ይታወቃል ። እንዲህ እነስ — እነስ አድርጎ በመቆፈር የኩባንያውን ጊዜና ገንዘብ መቆጠብ ይቻላል ።"

"ገባኝ ።"

ወጣቱ በሚያየው ነገር በመገረሙ ጥያቄ አከታተለ ።

"ይቅርታ የት ቦታ መቆፈር እንደሚገባችሁ የምታውቁት እንዴት ነው?"

"በጣም በርካታ የሆኑ የሥነ አፈር መርማሪዎች አሉን ። እነኝህም የአፈሩንና የድንጋዩን ናሙና ወስደው ጥናትና ምርምር ያካሂዳሉ ። ከዚያ በኋላ ቆፋሪዎቹ...."

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከጠዋት ጀምሮ ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ በዚያ ቃጠሎ በረሃ ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎችን ከወዲያ ወዲህ ሲያንቀሳቅስ ፣ መሣሪያዎችን ሲያፀዳዳ ፣ መርዛማ የሆነውን ጋዝ ለማቃጠል ቀንና ሌሊት ጋራው ላይ በሚንቦገቦገው እሳት አጠገብ ተሽከርካሪውን እያመላለሰ ይማስናል ።

ጂ፡ጂ ማክልንታይር ለዴሚሪስ የነገረው እውነቱን ነበር ። ምግቡ መጥፎ ነው ። ኑሮው ከባድ ነው ። ማታ ማታ የሚሠራ ምንም ነገር የለም። ከተነገረው የባሰ ሁኔታ የታየው ዴሚሪስ በመላ ሰውነቱ ቆዳ ላይ ያሉት ጥቃቅን ቀዳዳዎች ሁሉ በአሸዋ የተደፈኑ መስሎ ተሰማው ። በረሃው በረሃ ነው ። ከዚያ ለማምለጥ የሚቻልበት መንገድ የለም ። የአሸዋው ቧይት ወደ ጐጆው እየቦነነ ፣ ከልብሱ ዘልቆ ሰውነቱ ላይ እየተጣበቀ ዴሚሪስን ሊያሳብደው ይቃጣል ።

አውሎ ነፋሱ ለጉድ ነው ። አሸዋማው ውሽንፍር አእምሮ እስኪያስት ድረስ ላያቋርጥ ከወር ወር እያፍጨ ይነፍሳል ።

ዴሚሪስ በጐጆው ውስጥ ሆኖ በበሩ በኩል አሸዋማውን ቧይት እየተመለከተ "በዚህ ሁኔታ ውጭ ተወጥቶ ሥራ ይሠራል?" አለ ።

"እንዴት ተደርጎ?"

በአካባቢው ነዳጅ ዘይት የሚያመነጩ አዳዲስ ሥፍራዎች ተገኝተዋል ። በአቡ ሃድሪያህ ፣ በካቲፍና በሃራድ ፣ ነዳጅ በመፍለቁ ሠራተኞቹ

ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ሥራ በዝቶባቸዋል ። አንድ እንግሊዛዊ የሥነ አፈር ተመራማሪና ባለቤቱ በቅርቡ ተቀጥረዋል ። የሄንሪ ፓተር ዕድሜ ከስልሳ አምስት ዓመት በላይ ሲገመት ባለቤቱ ሲብል ሰላሳ አራት ዓመት ገደማ ይሆናታል ። ሲብል ፓተር ቁንጅናና የሴላት ወፍራም ስትሆን በጣም የሰለለው ድምጿ ሲሰማ ለጆሮ አይጥምም ። እንደዚያም ሆኖ በፋዲሊ አካባቢ እንደ ውብ ሴት ትቆጠራለች ። ሄንሪ ፓተር ለአዲስ የነዳጅ ዘይት ፍለጋ በየጊዜው ወደሌላ ሥፍራ ስለሚሄድ ባለቤቱ ብቻዋን የምትሆንበት ወቅት በርካታ ነበር ።

ባልና ሚስቱ ወደተሰጣቸው ቤት ሲገቡ ዕቃ ማጓጓዙን እንዲረዳ ትና እንዲያለማምዳት ዴሚሪስ ተመድቦ ነበር ።

ሲብል ፓተር "በሕይወቴ ውስጥ እንዲህ ያለ አስከፊ ቦታ አይቼ አላውቅም" ስትል ተነጫነጨች ። "ሄንሪ ሁልጊዜ በአስቸጋሪ ሥፍራ ያንከራትተኛል ። እኔም ለምን አብሬው እንደምንከረፈፍ አይገባኝም ።"

"ባለቤትዎ እኮ በጣም የተከበረ ሥራ ነው የሚያከናውነው" ሲል ዴሚሪስ ሊያረጋጋት ሞከረ ።

ማራኪውን ወጣት ትኩር ብላ አይታው "ባለቤቴ መሥራት ያለበትን ሥራ በሙሉ በቅጡ የሚፈጽም አይደለም ። የምለው ገባህ?"

በትክክል ገብቶታል ። "አልገባኝም እሜቴ" አለ ።

"ስምህ ማነው?"

"ዴሚሪስ ፣ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው እሜቴ"

"ጓደኞችህ ማን ብለው ነው የሚጠሩህ"

"ኮስታ"

"መልካም ፣ አንተና እኔ በጣም ጥሩ ጓደኛሞች ለመሆን የምንችል ይመስለኛል ኮስታ ።"

"ሁለታችን ከእነኚህ ባዕዳን ሰዎች ጋር የምንመሳሰልበት ነገር ያለ አይመስለኝም ።"

"ወደ ሥራዬ ልመለስ" አለ ዴሚሪስ ።

ሲብል ፓተር ፣ ለጥቂት ሳምንታት በሰበብ አስባቡ ወጣቱን ያስጠራው ነበር ።

"ሄንሪ እንደገና ዛሬ ጠዋት ሄደ" አለችው ። "ያንን የማይረባ ቁፋሮውን ሊያከናውን ነው የሄደው ።" ቀጠለችና በቀስታ "ስንት መቆፈር የሚገባው ነገር እቤት ውስጥ እያለ" ብላ ተናገረች ።

ዴሚሪስ ምንም መልስ አልነበረውም ። የሥነ አፈር ተመራማሪው በኩባንያው የሥልጣን ተዋረድ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው በመሆኑ ከፓተር ሚስት ጋር ተነካክቶ ከሥራው ሊፈናቀል ዴሚሪስ አልፈለገም ። እንዴት እንደሚሆን ባያውቅም ከአለታት አንድ ቀን በዚህ ሥራ አማካይነት ምኞቱ ከግብ ሊደርስለት እንደሚችል ግን እርግጠኛ ነበር ። ነዳጅ ዘይት ወደፊት ተስፋ ያለውና ታዳጊም ስለሆነ እራሱም ከዚሁ ምርት ጋር ለመቆራኘት አስቧል ። መጪው ዘመን የነዳጅ ዘይት ነው ። እና እርሱም የዚሁ አካል ለመሆን ቆርጦ ተነስቷል ።

አንድ ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ሲብል ፓተር ዴሚሪስን አስጠራችው ። አጥር ግቢውን አልፎ የቤቷን በር አንኳኳ ።

"ማዕ ።" ሲብል ሰውነቷን ወለል አድርጉ የሚያሳይ ስስ የማታ ልብስ ለብሳለች ።

"እ ... እመቤቱ ፈልገውኝ ነበር?"

"እም ፡ ና ግባ ኮስታ ። የራስጌው መብራት ተበላሽቶብኝ ነው ።"

ዴሚሪስ ወደራስጌው መብራት አመራና ብልሽቱን ለማወቅ ብድግ አድርጉ ማገላበጥ ጀመረ ። "እምፖል የለውም ... ።" ሰውነቷን ከጀርባው አንካከታ በእጇ ስታሻሽው ተሰማው ። " ሚስስ ፓተር ..."

ከንፈሯን ከከንፈሩ አጣብቃ ወደአልጋው ትገፋው ጀመር ። ከዚያ በኋላ እራሱን ሊቆጣጠር አልቻለም ።

ልብሱን አወላልቆ እውስጧ ሰጠመ ። በደስታ ብዛት ትጮሃለች ። "እንዲያ ነው! አ! አዎ! እንደሱ ነው ። አምላኬ ፡ ብዙ ጊዜኮ ሆኖኛል!"

ማሳረጊያውን ቁና ትንፋሽ እንደለቀቀች ሰውነቷ ተንዘፈዘፈ ። "አ የኔ ፍቅር እወድሃለሁ!"

ዴሚሪስ ደንግጦ ተጋድሞ ቀረ ። 'ምን ማድረጌ ነው? ፓተር ይህንን ጉዳይ ካወቀው አለቀልኝ ማለት ነው ።'

የሚያስበውን ያወቀች ይመስል "ይህቺ ጥብቅ ምስጢራችን ናት ፡ አይደል የኔ ፍቅር?" ብላ በሳቅ ተንከተከተች ።

ያቺ ምስጢር ለብዙ ወራት በዚያው ዓይነት ቀጠለች ። ዴሚሪስ ሊተዋት የሚችልበት መንገድ አልነበረም ። ባሏ ነዳጅ ዘይት ፍለጋ ለብዙ ቀናት ከሚስቱ ስለሚለይ ዴሚሪስ ከእርሷ ጋር ወሲብ ላለመፈጸም ሊያቀርብ የሚችለው ምክንያት አልታይህ ብሎታል ። ይባስ ብሎ ደግሞ ሲብል ፓተር በዴሚሪስ ፍቅር ከንፋለች ።

"በእንዲህ ዓይነቱ ሥፍራ መሥራት የማይገባህ ግሩም የሆንክ ሰው ነህ የእኔ ፍቅር ። እኔና አንተ ወደ እንግሊዝ አገር እንመለስ" አለችው ። "አገሬኮ ግሪክ ነው ።"

"ከዛሬ ወዲያ ግሪክ አይደለም" ብላ የፈረጠመውን ብልቱን ደባበሰች ።

"ከእኔ ጋር ወዳገሬ ትሄዳለህ ። ሄንሪን ፈትቼ አንተን አገባለሁ ።"

ዴሚሪስ በሽብር ተወረረ ። "ሲብል ፡ እኔ ... እኔ ገንዘብ የለኝም እኔ ..."

ዶረቱን በከንፈሯ እያሻሸች "ያ ችግር አይደለም ፡ እንዴት ገንዘብ ማግኘት እንደምትችል እኔ አውቃለሁ የእኔ ማር" አለችው ።

"ታውቂያለሽ?"

ቀና ብላ አልጋው ላይ ተቀመጠች ። "ትናንት ማታ ሄንሪ አዲስ ትልቅ የነዳጅ ዘይት ማፍለቂያ ሥፍራ ማግኘቱን ገልጦልኛል ። ባሌ በዚህ ዓይነቱ ተግባር በጣም ጉበዝ ነው ። እና በውጤቱ በጣም ተደስቷል። የግኝቱን ሪፖርት አጠናቅቆ ወደሥራው ሲሄድ ነገ ጠዋት እንዳስረክብለት እደራ ብሎኛል ። ሪፖርቱም ከእኔ ዘንድ ነው ። ልታየው ትፈልጋለህ ?"

የዴሚሪስ የልብ ትርታ ፍጥነት ጨመረ ። "አዎ እ ... እ እፈልገዋለሁ ።" ከአልጋው ወርዳ በፍጥነት ከጥግ ወደምትገኘው ጠረጴዛ ስትሄድ ተመለከታት ። ትልቅ ፖስታ እንስታ ወደአልጋው ተመለሰች ።

"ከፈተው ።"

ዴሚሪስ ትንሽ ካቅማማ በኋላ ፖስታውን ከፍቶ ከውስጥ ያለውን ወረቀት አወጣ ። ባለአምስት ገጽ ነው ። ገረፍ ገረፍ አድርጉ አንብቦ እንደጨረሰ እንደገና ወደኋላው ተመልሶ በጥንቃቄ ማንበብ ጀመረ ።

"ዘገባው ጠቃሚነት ያለው ይመስልሃል ?"

‘ዘገባው ጠቃሚነት ያለው?’ በታሪክ ውስጥ እስካሁን ከተመዘገቡት የነዳጅ ዘይት ማፍለቂያዎች ሁሉ ሊበልጥ ስለሚችለው የነዳጅ ክምችት የሚያወሳ ሪፖርት ነው ።

ዴሚሪስ ስሜቱን ደበቅ አድርጉ “እዎ ፣ ጠቃሚነት … ሊኖረው ይችላል ” አለ ።

“መልካም እንግዲህ ይኸውልህ” አለች ሲብል በደስታ ። “ይኸው አሁን ገንዘብ አግኝተናል ።”

በትካዜ “እንዲህ በቀላሉ የሆነ ነገር አይደለም” አላት ።

“ለምን አይሆንም?”

ዴሚሪስ ሊያስረዳት ሞከረ ። “ይህ የሚጠቅመው ክምችቱ ያለበትን መሬት ለመግዛት አትም ላለው ሰው ነው ። ያልገንዘብ አይሆንም። በባንክ ደብተሬ ውስጥ የተመዘገበው ሦስት መቶ ዶላር ብቻ ነው ።”

“አይ ፣ ለዚህ አትጨነቅ ። ሄንሪ ገንዘብ ስላለው ቼክ እጽፍልሃለሁ። አምስት ሺህ ዶላር አይበቃም?”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የሰማውን ለማመን አልቻለም ።

“አዎ እኔ … ምን ለማለት እንደምችል አላውቅም ።”

“ለእኛ ነው የኔ ፍቅር ለወደፊት ኑሮአችን ።” አልጋው ላይ ተቀምጦ ብዙ አሰላሰለ ።

“ሲብል ፣ ይህን ሪፖርት ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ሳትልኪው ልታቆዪው አትችዪም ?”

“እንዴታ ፣ እስከ ዓርብ ድረስ አቆየዋለሁ ። የኔ ፍቅር ፣ ይህ በቂ ጊዜ ነው?” በቀስታ ጭንቅላቱን አወዛወዘና “አዎ ፣ በቂ ጊዜ ነው ይበቃኛል” አለ።

ሲብል አምስት ሺውን ዶላር ስትሰጠው በልቡ ‘ይህ ስጦታ አይደለም ብድር ነው’ አለ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አዲሱ የነዳጅ ዘይት ክምችት ያለበትን ቦታ ገዛ ። ከጥቂት ወራት በኋላ ነዳጅ ዘይቱ መውጣት እንደጀመረ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ባንዴ ሚሊየነር ሆነ ።

ለሲብል ፖተር አምስት ሺውን ዶላር መልሶ ከፈላት ፣ አዲስ የማታ ልብስ ገዝቶ ላከላትና ወደግሪክ ተመለሰ ። ከዚያን ጊዜ በኋላ አይታው አታውቅም ።

ምዕራፍ ሦስት

በተፈጥሮ ሂደት ውስጥ የተከሰተ ማንኛውም ነገር ጨርሶ አይጠፋም የሚል አመለካከት አለ ። ከዚህ ቀደም ተሰምቶ የነበረ ድምጽና የተነገረ ቃል ሁሉ ፣ አሁንም በጊዜና በሥፍራ ተወስኖ የሚኖር ሲሆን ምናልባት አንድ ቀን በትውስታ ብቅ ይልብን ይሆናል ።

ራድዮ ከመፈልሰፉ በፊት በአካባቢያችን ያለው አየር በድምጽ ፣ በሙዚቃ በዜናና በዓለም አካባቢ በሚፈልቁ ንግግሮች የታመቀ ነው ብሎ ማን ያምን ነበር? አንድ ቀን ወዳለፈው ጊዜ ተመልሰን ሊንኮሊን ያደረጋቸውን ንግግሮች እናዳምጥ ይሆናል ፣ የቬክስፒሪን ድምፅ እንሰማ ይሆናል ፣ የተራሮች ላይ ስብከቶችን …

ካተሪን አሌክሳንደር ድሮ የሰማቻቸው ድምፆች እንደገና ከጆሮዋ ውስጥ ገቡ ። ሆኖም የተምታቱና የተቆራረጡ ስለነበሩ ግራ ያገቡዋታል ።

‘ካቲ ፣ አንቺ ልዩ ሴት መሆንሽን ታውቂያለሽ? መጀመሪያ ያየሁሽ እለት ነው ይህንን ልገነዘብ የቻልኩት ።’

‘በቃ ፣ እሀል ውሃችን አልቋል ። የምፈልገው ፍቺ ነው ። ከሌላ ሰው ፍቅር ይዞኛል …’

‘ምን ያህል እንዳስቀየምኩሽ ይገባኛል … ውሳኔውን ለአንቺ ትቻለሁ …’

‘ሊገድለኝ እኩ ነበር’

‘ማን ?’

‘ባሴ ።’

ድምፆቹ የሚቆሙ አይደሉም ። ያስጨንቃሉ ፣ ያስቃያሉ ፣ ያለፈው ሕይወቷ ትዝታዎች እንደሲኒማ በአዕምሮዋ ውስጥ በፍጥነት ይሮጣሉ ።

የሴቶቹ ገዳም ውብና ሰላም የሰፈነበት ገነት ቢሆንም በድንገት ወደ

እሥር ቤት ተለውጠባታል ። ‘ይሄ ለኔ የሚሆን ቦታ አይደለም ። ታዲያ ለኔ የሚሆነው ቦታ የት ነው?’ ለጥያቄዋ ምላሽ አልነበራትም ።

በገዳሙ ውስጥ መስተዋት የሚባል ነገር ባይኖርም ፊትን ደህና አድርጐ የሚያሳይ ኩሬ ከአትክልት ሥፍራው አጠገብ አለ ። ካተሪን በኩሬው ውስጥ መልኳን ለማየት በመፍራቷ ሆን ብላ ትርቀው ነበር ። ዛሬ ጠዋት ግን ወደኩሬው በመቅረብ ተንበርክካ ወደታች ተመለከተች ። እጅግ ውብ የሆነች ፣ የፊቷ ቆዳ በፀሐይ ሙቀት የጠየመ ፣ ሐር የመሰለ ጥቁር ፀጉር ያላት ፣ መጐሳቆሏን ግራጫማ ዓይኗ የሚናገሩላት ሴት ምስል ውሃው ላይ አየች ። ምናልባት ውሃው የህሰት ምስል አሳይቶ ይሆንን ለፈገግታ የተዘጋጀ ገራገር አፍና ከወደጫፉ በመጠኑ ቀና ያለ አፍንጫ ያላት ፣ ሰላሳ ዓመት ትንሽ ያለፋት የቆንጆ ሴት ነጸብራቅ ወደላይ ሲመለከታት አየች ። ምን ያደርጋል ታዲያ ፣ ያለፈውም ሆነ የወደፊት ማንነቷ የማይታወቅ ሴት ... ‘የሚረዳኝ ሰው ማግኘት አለብኝ ።’

ተስፋ በቆረጠ ስሜት ‘የማነጋግረው ሰው ማግኘት አለብኝ ።’ አለችና ወደ ሲስተር ተሬዛ ቢሮ ሄደች ።

“ሲስተር ...”

“እህ ፣ የኔ ልጅ”

“እ ... ህኪም ማናገር የሚያስፈልገኝ ይመስለኛል ። ማንነቴን እንዳውቅ የሚረዳኝ ሰው ማግኘት አለብኝ ።”

ሲስተር ተሬዛ ለረጅም ጊዜ ዝም ብለው ተመለከቷትና “ቁጭ በይ” አሏት ።

ካተሪን ከጥንታዊው መቀመጫ ማዶ ካለው ደረቅ ወንበር ላይ ተቀመጠች ።

ሲስተር ተሬዛ በእርጋታ “ወዳጄ ፡ ሐኪምሽ እግዚአብሔር ነው፤ እሱ እንድታውቂው የሚገባሽን ሁሉ ቀስ ብሎ ያሳውቅሻል ፤ ከእኛ ውጭ ሌላ እንግዳ ወደዚህ ገዳም ሊገባ እንደማይፈቀድለት ታውቂ የለ?”

ካተሪንን ወዲያው አንድ ትውስታ ብልጭ አለባት ። ... ይህ ነው ልትል የማትችለው ሰው በገዳሙ አትክልቶች ውስጥ ሲያነጋግራት—የሆነ ነገር ሲሰጣት ... ከዚያም እልም ሲል ።

“ይህ የእኔ መኖሪያ አይደለም ።”

“ታዲያ የት ነው ያንቺ መኖሪያ?”

“ችግሩ ይሄ አይደል? ምን አውቄ ። አንድ ለማወቅ የምፈልገው

ነገር ስላለ ነው ። እባክዎን ሲስተር ተሬዛ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፣ ቦታዬ እዚህ እንዳልሆነ ግን አውቃለሁ ።”

ሲስተር ተሬዛ ትኩር ብለው ፊቷን በጥሞና አጠኑ ።

“እሽ ከዚህ ብትለቂ ወዴት ነው የምትሄጂው?”

“አላውቀውም ።”

“ልጄ እስቲ ላስብበትና በቅርቡ እንደገና እንነጋገርበት ።”

“አመሰግናለሁ ሲስተር ።”

ካተሪን እንደወጣች ሲስተር ተሬዛ ለረዥም ጊዜ ፈዝዘው ተቀመጡ። በጣም እስቸጋሪ ከሆነ ውሳኔ ላይ መድረስ ሊኖርባቸው ነው ። በመጨረሻም ወረቀትና ብዕር አንስተው መጻፍ ጀመሩ ።

“ክቡር ጌታዬ ፣” ብለው ጀመሩ ። “እንድ ነገር ስላጋጠመኝ ላሳውቆት ብዬ ነው ። ወዳጄችን ገዳሙን ለመልቀቅ የምትፈልግ መሆኗን ስለገለጠችልኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እባክዎ ይምከሩኝ ።”

ማስታወሻውን አንዴ እንዳነበበው ወንበሩ ላይ ወደኋላ ተለጥጠ መልዕክቱ ሊያስከትል ስለሚችለው መዘዝ አውጠነጠነ ። እና ፣ ካተሪን አሌክሳንደር ከሞት ለመመለስ ትሻለች ። በጣም መጥፎ ነገር ። እርሷን ማስወገድ አለብኝ ። በጥንቃቄ ፣ በጣም ጥንቃቄ በተመላበት ዘዴ ።

የመጀመሪያው እርምጃ እርሷን ከገዳሙ ማስወጣት ነው ። ዴሚሪስ ሲስተር ተሬዛን መጐብኘት እንዳለበት ወሰነ ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ዴሚሪስ እየተሸፈረ ወደ ኢኢኒና አመራ ። ግጠሩን አጽርጦ በሚጓዝበት ወቅት ከመኪናው ውስጥ ሆኖ ስለካተሪን ያስብ ነበር ። ድሮ በመጀመሪያ ሲያገኛት ምን ያህል ቆንጆ ሴት እንደነበረች አስታወሰ ። ብሩህ አዕምሮ የነበራት ተጫዋችና መንፈሰ ጠንካራ ልጅ መሆኗ ትዝ አለው ። ግሪክ ውስጥ በመሆኗም እንዴት እንደፈነደቀች አልረሳውም ። ‘ዓለሟን አይታለች’ ሲል አሰበ ። ከዚያ በኋላ አማልክቱ በቀል ፈጸሙባት ። ካተሪን ከዴሚሪስ አውሮፕላን

አብራሪዎች አንዱን አግብታ ነበር ፤ ግን ትዳሯ ምድራዊ ሲኦል ሆነ ። ባገባች በማግሥቱ አሥር ዓመት ዕድሜ የጨመረች ይመስል ወደለች ፣ ጠጪም ሆነች ። ዴሚሪስ ቁና ተነፈሰ ። 'አይ ከስረት!'

ዴሚሪስ ሲስተር ተሬዛ ቢሮ ውስጥ ተቀምጧል ።

"ስለዚህ ጉዳይ እርስዎን በማስጨነቄ አዝናለሁ" አሉ ሲስተር ተሬዛ በትህትና ። "ሆኖም ልጅቷ መሄጃ የሌላት ስለሆነ ..."

"ደህና አድርገዋል" ሲል ዴሚሪስ አረጋጋቸው ። "ለመሆኑ ስላለፈው ሁኔታዋ የምታስታውሰው ነገር አለ?"

ሲስተር ተሬዛ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ ። "የለም ። ምስኪን ..." ብዙ መነኮሳት አትክልት ወደሚኰተኩቱበት በመስኮት አዩና "ያችው ሎት ፣ እዚያ ናት" አሉ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደ እርሳቸው ተጠግቶ በመስኮት ወደውጭ ተመለከተ ። ሦስት መነኰሳት ጀርባቸውን ሰጥተውታል ። ላፍታ ያህል እንደቆመ አንደኛዋ ዞር ስትል ፊቷን አየ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ ። በጣም ቆንጆ ነበረች ግን ያቺ ወፍራም ጐስቋላ ሴት የት ገባች?

"ከመካከል የቆመችዋ እርሷ ናት" አሉ ሲስተር ተሬዛ ።

"ልክ ነዎት" ሲል ዴሚሪስ ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። የሲስተር ተሬዛ ቃላት ራሳቸው ካላቸው እውቀት በላይ ትክክል ነበሩ ።

"ምን ላድርጋት አሁን?"

ጠንቀቅ! "እስቲ ላስብበት" አለ ዴሚሪስ ። "እንገናኛለን ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አንድ የሚወስነው ነገር አለ ። የካተሪን አሌክሳንደር መልክ እጅጉን አስገርሞታል ። እንዳለ ተቀይራለች ። 'መቼም ያቺ ሴት ናት ብሎ ለመጠራጠር የሚችል ማንም የለ' ሲል አሰበ። አሳቡ መልሶ እራሱን አሳቀው ። ያን ዕለት ማታ ለሲስተር ተሬዛ ማስታወሻ ጽፎ ላከላቸው ።

'ተአምር ነው' ስትል አሰበች ካተሪን ። 'ሕልሙ እውን ሲሆን!' ሲስተር ተሬዛ ከትንሿ ጐጆአቸው ውስጥ ፀሎት አድርሰው ሲመለሱ ወደ ካተሪን ጐራ አሉ ።

"ልጄ ሆይ ፣ አንድ የምነግርሽ ነገር አለ ።"

"ምን ነበር?"

ሲስተር ተሬዛ ቃላቶቻቸውን በጥንቃቄ በመምረጥ "የምሥራች! ለአንድ የገዳማችን ወዳጅ ስለአንቺ ሁኔታ ጽፌለት ሲረዳሽ ፈቃደኛ ሆኗል ።"

ካተሪን ልቧ በኃይል ሲመታ ተሰማት ። "ሲረዳኝ — እንዴት ?"

"እንዴት እንደሚረዳሽማ የሚነግርሽ እርሱ ነው ። ሰውዬው በጣም ደግና ሩህሩህ ሰው ነው ። ከገዳሙ መውጣትሽ ነው ።" የሰማቻቸው ቃላት በድንገተኛ ቅዝቃዜ ብርክ አስያዟት ። ልታስታው ሰው እንኳ ወዳልቻለችው እንግዳ ዓለም ልትገባ ነው ። ማን ይሆን ሊረዳት የተነሳሳው ሰው?

ሲስተር ተሬዛ "ለሰው የሚያስብ ሰው ነው ። ልታመሰግኚው ይገባል ። መኪናው ሰኞ ጠዋት እዚህ ድረስ ይመጣልሻል ።"

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት እንቅልፍ በካተሪን ዓይን ላይ ዞር አልል አለ ። ከገዳሙ ወጥቶ ወደውጭው ዓለም የመሄዱ ነገር ሲታሰባት ያስፈራታል ። እርቃኗን ያለችና ያለቀላት መስሎ ተሰማት ። "ምንነቴን አለማወቄ ይሻለኝ ይሆን? እባክህ አምላኬ ጠብቀኝ ።"

ሰኞ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ሊሞሲን መኪና ከገዳሙ ቅጥር ግቢ በር ላይ ቆመች ። ካተሪን ሌሊቱን ሳትተኛ ከፊቷ ስለተደቀነውና ስለማይታወቀው የወደፊት ሁኔታዋ ስታስብ ነበር ያነጋችው ።

ሲስተር ተሬዛ ካተሪንን ወደውጭ ዓለም እስከሚያስወጣው በር ድረስ ሸኟት ።

"እንፀልይልሻለን ። ልብ በይ ፣ ወደ እኛ ተመልሰሽ ለመምጣትም ከፈለግሽ በደስታ እንቀበልሻለን ።"

"አመሰግናለሁ ሲስተር ፣ አልረሳም ።" የካተሪን ልቦና ግን ተመልሳ እንደማትመጣ እርግጠኛ ነበር ። ካተሪን ፣ ከኢኢና እስከ አቱንስ በሚወስደው ረጅሙ መንገድ ስትጓዝ በተምታቱ አሳቦች ውስጥ ትዋኛለች ። ከገዳሙ መውጣት ልዩ ስሜት ያሳደረባት ቢሆንም ውጪው ዓለም የሆነ መጥፎ ነገር እንዳለበት ይሰማታል ። ባለፈው ሕይወቷ ውስጥ ስለተፈጸመው አሰቃቂ ነገር ትረዳ ይሆን? ሰው በሀይቅ ውስጥ ሲያሰምጣት ያየችው ተደጋጋሚ ሕልም ከዚህ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን?

ገጠሩን ዘልቀው ትንንሽ መንደሮችን ካለፉ ከቀትር በኋላ ከአቴንስ ከተማ መግቢያ ላይ ደረሱ ። ቀጥለውም ውካታ ወደበዛበት ወደመሃል ከተማው ገቡ ። ነገሩ ሁሉ ለካተሪን እንግዳና ሕልም መስሎ ቢታያትም በሌላ በኩል ደግሞ ሥፍራውን የምታውቀው ይመስላታል ። 'ከዚህ ቀደም እዚህ ነበርኩ' ስትል በግርምታ አሰበች ።

ቮፈሩ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አመራ ። ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ በጋራ ላይ ወደሚገኝ ሰፊ ርስት ደረሱ ። ረዥሙን የአጥር ፣ የብረት በርና የዘበኛ ማደሪያ ቤት እንዳለፉ በሚያማምሩ ትላልቅ ዛፎች መሐል አቋርጠው በተዋቡ በርካታ ሀውልቶች ካጌጠ ነጭ የተንጣለለ የሜዲትራኒያን ቪላ ፊት ቆሙ ።

ቮፈሩ የመኪናውን በር እንደከፈተላት ካተሪን ወረደች ። ከዋናው በር ላይ ቆሞ ሰው ይጠብቃት ነበር ።

"ካሊሜራ" "እንደምን አደርክ" የሚል ቃል ከካተሪን አፍ ሳይታወቃት አፈተለከ ።

"ካሊሜራ"

"ወዳንተ..... ወዳንተ ነበር የተላከሁት?"

"የለም ፣ አይደለሁም ። ሚስተር ዴሚሪስ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ እየጠበቁሽ ነው ።"

"ዴሚሪስ!" ይህን ስም ከዚህ ቀደም ሰምታ አታውቅም ። ለምን ሊረዳት ፈለገ ግን?

ካተሪን የእልፍኝ አሽከሩን ተከትላ ወደ ሰፈው ክብ ሕንጻ ገባች ። የጣሪያው ጉልላት በውብ ጣውላ ያማረ ነው ። በጣሊያን እብነበረድ የተነጠፈው ወለል ያብረቀርቃል ።

ሳሎኑ ትልቅ ነው ። ጣሪያው ረዝሞ ወደመሬት የተረቡ ምቹ ሶፋና ወንበሮች ክፍሉን ሞልተውታል ። ትልቅ ስዕል አንዱን ግድግዳ ሸፍኖታል ። ቤተ መጻሕፍቱ እንደደረሱ የእልፍኝ አሽከሩ ቆም አለ ።

"ሚስተር ዴሚሪስ እውስጥ እየጠበቁሽ ነው ።"

የመጻሕፍት ቤቱ ግድግዳ ነጭና ወርቅማ ቀለም ተቀብቷል ። ግድግዳውን ተጠግተው በሚገኙት መደርደሪያዎች ላይ ያሉት መጻሕፍት ሽፋን በቆዳ ተለብደው ርዕሳቸው በወርቅማ ቀለም ተጽፏል ። ከትልቅ ጠረጴዛ አጠገብ አንድ ሰው ተቀምጧል ። ካተሪን እንደገባች ቀና ብሎ አያትና ብድግ አለ ። የምታስታውሰው ነገር እንዳለ ለማወቅ ፊቷን

ለማንበብ ሞከሮ ነበር ፣ ግን ምንም አላገኘባትም ።

"እንኳን ደህና መጣሽ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እባላለሁ ። የአንቺስ ስም ማነው ?"

ጥያቄውን ያለምንም ሌላ ምክንያት የተሰነዘረ ለማስመሰል ሞከረ። 'ስሟን አስታውሳው ይሆን?'

"ካተሪን አሌክሳንደር ።"

የሰማው ያልጠበቀው በመሆኑ የስሜቱን ለውጥ ተቆጣጠረ ።

"ካተሪን አሌክሳንደር እንኳን ደህና መጣሽ ። እባክሽን ቁጭ በይ!"

ፊትለፊትዋ ካለው ጥቁር የቆዳ ሶፋ ላይ ተቀመጠ ። ከቅርብ ሆነው ሲያዩዋት ይበልጥ ታምራለች ። 'ውብ ፍጡር ናት' አለ በልቡ ። 'ደግሞ ያን ጥቁር የመነኩሳት ቀሚስ ነው የለበሰች ። ቆንጆን ግጥፋት ብልግና ነው ። ሌላው ቢቀር ደስተኛ ሆና ትሞታለች ።'

"ልት .... ልታነጋግረኝ በመፈለግህ በጣም ደስ ብሎኛል ። " አለች ካተሪን ። "ግን ለምን..."

ፈገግ አለ ። በቀላሉ ለመመሰስ ያህል "እኔ ሲስተር ተሬዛን አልፎ አልፎ እረዳቸዋለሁ ። ገዳሙ የገንዘብ ችግር ስላለበት የእቅሜን ያህል እደጉማቸዋለሁ ። አንቺን መርዳት እችል እንደሆነ ጽፈው እንደጠየቁኝም ደስ ብሎኝ እንደምሞክር አሳውቅኳቸው ።"

"መቼም በጣም...." ምን ብላ እንደምትጨርስ ግራ ተጋብታ አቋረጠች ።

"ሲስተር ተሬዛ ነግረውሃል?...የማስታወስ ችሎታ እንዳሌለኝ?"

"አዎ ፣ አንስተውልኝ ነበር መሰለኝ?"

ንግግሩን ቆም አድርጎ እንደገና "ምን ያህል ለማስታወስ ትችያለሽ ?" ብሎ ጠየቃት ።

"ስሜን አውቀዋለሁ ፣ ግን ከየት እንደመጣሁና ማን እንደሆንኩ ለይቼ አላውቅም ።" ተስፋ በተሞላበት አነጋገር "እዚህ አቴንስ ውስጥ የሚያውቀኝን ሰው አገኝ ይሆናል" አለች ።

በኮንስታንቲን ዴሚሪስ አእምሮ የማስጠንቀቂያ ደወል አንቃጨለ። ከምንም በላይ የፈለገው ይህን ነበር ። "አዎ ምናልባት ታገኚ ይሆናል" አለ በጥንቃቄ ። "ጠዋት ተገናኝተን ለምን አንወያይበትም ? እንዳጋጣሚ ሆኖ አውን ስብሰባ አለብኝ ። የመኝታ ክፍል እንዲዘጋጅልሽ አድርጌአለሁ ። ምቾት እንደሚሰጥሽ ተስፋ እደርጋለሁ ።"

“ም...ምን ብዬ እንደማመሰግንዎት አላውቅም ።”

እጁን አወዛወዘና “አስፈላጊ አይደለም ። በሚገባ እንክብካቤ ይደረግልሻል ። ልክ እቤትሽ እንዳለሽ ቁጠሪው” አላት ።

“አመሰግናለሁ ፣ ሚስተር....”

“ወዳጆቼ ኮስታ ብለው ይጠሩኛል እና አንቱታውን ተይ ።”

የእልፍኝ አሽከሩ ካተሪንን ወደ ውቡ መኝታ ክፍል ወሰዳት ። ሰፊው አልጋ ውድ የሐር ልብስ ተጐናጽፎ ተዘርግቷል ። ምቾት ያላቸው ነጭ ሶፋዎች ፣ ወንበሮች ፣ ጥንታዊ ጠረጴዛዎችና የራስጌ መብራቶች ክፍሉን አሳምረውታል ። ግድግዳው በሥዕሎች አሸብርቋል ። ረዥሙ ባለውሃ ሰማያዊ ቀለም የመስኮት መስተዋት መሸፈኛ የፀሐይ ብርሃን ሙሉ በሙሉ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከልሎታል ። ካተሪን ፣ በመስኮቱ አቆልቁላ አረንጓዴ ሰማያዊውን ባሕር ከሩቅ ለማየት ትችላለች ።

የቤት ሠራተኛው “ሚስተር ዴሚሪስ ልብስ እንድትመርጪ የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች ወደዚህ እንዲላኩ አዘዋል ፣ ደስ የሚልሽን እንድትመርጪ እንግዲህ ።”

ይሄኔ ነበር ካተሪን የመኝሐት ልብስ መልበሷን ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቀችው ።

“አመሰግናለሁ ።” በለስላሳው አልጋ ላይ ለመጠች ። በሕልም ዓለም ውስጥ ያለች መስሎ ተሰማት ። ‘ይሄ የማታውቂው ሰው ማን ይሆን ? ለምንስ እንዲህ ደግ ሆነልሽ ?’

ወዲያው ከአንድ ሰዓት በኋላ ልብስ የጫነ ትልቅ መኪና ከተፍ አለ። አንዲት የሴት ልብስ ሰፊም ወደካተሪን መኝታ ክፍል ተስተናገደች።

“ማዳም ዲማስ እባላለሁ ። እስቲ ልክሽን ልወቅ ። አንዴ ልብስሽን ታወልቂ ?”

“ምን....ምን አሉኝ ?”

“እንዴ ልብስሽን ታወልቂ ? ልብስ ለብሰሽ ልክሽን ለማወቅ ይቸግረኛል ።”

ከሰው ፊት ራቁቷን ከቆመች ምን ያህል ጊዜ ሆኗት ይሆን?

ካተሪን ዝግ ብላ እያስተዋለች ማውለቅ ጀመረች ። ከሴትዮዋ ፊት እርቃኗን እንደቆመች ማዳም ዲማስ በሰለጠነው ዓይኗ ከላይ እስከታች ቃኘቻት ። በቁመናዋ ተደነቀች ።

“ጥሩ ቅርጽ ነው ያለሽ ፣ ጥሩ ነገር ልናዘጋጅልሽ እንችላለን ።”

ሁለት ሴት ረዳቶቿ ሙታንታዎችን ፣ ሽሚዞችን ፣ ረዥምና ጉርድ ቀሚሶችንና ጫማዎችን የያዙ ሻንጣዎችን አንጠልጥለው ገቡ ።

“የምትፈልጊውን ምረጪ” አለቻት ልብስ ሰፊዋ ። “ሁሉንም ለብሰሽ ሞክሪያቸው”

ከእ... ከእነዚህ ውስጥ አንዱንም መግዛት የሚያስችል አቅም የለኝም” ብላ በፍርሃት ተናገረች ። “ገንዘብ የለኝም ።”

ሰፊዋ ሳቀች ። “የገንዘብ ችግር የለም ። ሚስተር ዴሚሪስ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ ።”

‘ግን ለምን ? ...’ ብላ አሰበች ።

ልብሶቹን ስታይ ድሮ ለብሳቸው የነበሩት ልብሶች ትዝ አሏት ። የተለያዩ ውብ ቀለማት ካሏቸው የሐር ፣ የጥጥና የሱፍ ጨርቅ የተሰፉ ናቸው ።

ሦስቱ ሴቶች በጣም ፈጣኖች ስለነበሩ ከሁለት ሰዓታት በኋላ ካተሪን በርከት ያሉ ማራኪ ልብሶች ልትመርጥ ችላለች ። የምታደርገው ግራ ገብቷት እዚያው ቁጭ ብላ ቀረች ።

‘እንግዲህ ለባብሻለሁ ።’ አለች በልቧ ። ‘ለመሆኑ ግን ምን መሄጃ ቦታ አለ?’ ግን እኮ የሚኬድበት አለ ፣ ወደ መሐል ከተማ ። ባለፈው ጊዜ ለተፈፀመባት እንቆቅልሽ መፍቻ ቁልፍ ያለው አቲንስ ውስጥ ነው ። ይሀንን አምና ተቀብላለች ። ተነስታ ቆመች። ‘አይዞሽ አንቺ እንግዳ ፍጡር ማነነትሽን ለማወቅ እንጥራለን ።’

ካተሪን ወደ አዳራሹ ብቅ እንዳለች የልፍኝ አገልጋዩ ወደ እርሷ ቀርቦ “ምን ልርዳዎ እመቤቴ?” አለ ።

“እ ... ወደ ከተማ ለመሄድ እፈልጋለሁ ። ታክሲ ልትጠራልኝ ትችላለህ?”

“ታክሲ መጥራት ምን ያስፈልጋል? ባስፈለግዎት ጊዜ እንዲጠቀ

ሙበት ሊሞሲን ተዘጋጅቷል ። ሾፌር አዘጋጅልዎታለሁ ።”

ካተሪን አቅማማችና “አመሰግናለሁ” አለች ። ወደከተማ ብትሄድ ሚስተር ዴሚሪስ ይናደድ ይሆን ? አትሂድ አላለ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሽንጣሙ ሊሞሲን የኋላ መቀመጫ ተቀምጣ ወደ አቴንስ እምብርት ተጓዘች ። ካተሪን ባየቻቸው የጥንት የሕንፃና የሀውልት ፍርስራሾች እንዲሁም በከተማው ግርግርና ሁካታ ተደነቀች ።

ሾፌሩ በኩራት መንፈስ ጣቱን ቀስሮ “ያ በአክሮፖሊስ ጫፍ ላይ የታነፀው የፓርቴኖን መቅደስ ነው” አላት ።

ካተሪን በነጭ እብነበረድ የተሠራውን ድንቅ ሕንፃ ተመለከተች ። “ለጥበብ አምላክ ለአቴና የተሠራ መቅደስ” ስትል ለእራሷ ተናገረች ።

ሾፌሩ የአባባሏን ትክክለኝነት ለመግለጽ ፈገግ አለ ። “ሚስስ ፣ የግሪክ ታሪክ ተማሪ ነሽ?” ።

የስጋት እንባ በዓይኗ አቀረረ ። “እኔ እንጃ” አለች በለሆሳስ ፣ “እኔ እንጃ ።”

ከሌላ ፍርስራሽ አጠገብ ሲያልፉ “ያ የሄሮደስ አቲከስ ትያትር ነው። እንደምታዩው የቤቱ ከፊል ግድግዳ አሁንም አልፈረሰም ። በአንድ ወቅት ትያትሩ በአንዴ ከአምስት ሺህ ተመልካቾች በላይ ያስተናግድ ነበር” አላት ።

“ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰባት” አለች ካተሪን ቀበል አድርጋ ። በፍርስራሹ መሐል ዘመናዊ የሆቴልና የቢሮ ሕንፃዎች ተቀላቅለው በየቦታው ይታያሉ ። የጥንቱና የዛሬ ድብልቅ ። ሊሞሲኗ ፣ በከተማዋ እምብርት ካለው መናፈሻ መሃል እየጋለበችና እየተብረቀረቀች ወደላይ ከሚፈሰው ሰው ሰራሽ ፏፏቴ አጠገብ አለፈች ። በመናፈሻው ውስጥ በርከት ያሉ አረንጓዴና ብርቱካንማ ቀለም ያላቸው ጠረጴዛዎች ተደርድረዋል ። ሰማያዊ ቀለም ያለው ድንኳንም ተጥሏል ።

‘ይሀንን ቦታ ቀደም ሲል አይቼዋለሁ’ አለች ካተሪን በልቧ ፣ እጇ ሲቀዘቅዝ እየተሰማት ። ‘አስደስቶኝም ነበር ።’

በመስክ ላይ ምግብና መጠጥ የሚሸጡ ትንንሽ መደብሮች በሁሉም ሕንፃዎች ላይ አሉ ለማለት ይቻላል ። በየጥግና ጥጉ ትኩስ ሰፍነጎች ይሸጣሉ ። ሐምራዊ ቀለም የተቀቡ የአበባ መሸጫ ሱቆች ገበያ ደርቷል ።

ሊሞሲኗ ከሲንታግማ አደባባይ ደረሰች ።

ከጥግ ላይ ከሚገኝ ሆቴል አጠገብ ሲያልፉ ካተሪን “እባክህ አቁምልኝ!” አለች ።

ሾፌሩ መኪናዋን ወደመንገዱ ጠርዝ አስጠጋ ። ካተሪን መተንፈስ አቃታት ። ‘ይሀንን ሆቴል አስታውሰዋለሁ ፣ አድሬበታለሁ’ አለች በልቧ።

ስትናገር ድምጿ ይንቀጠቀጥ ነበር ። “እዚህ መውረድ እፈልጋለሁ፣ ከሁለት ሰዓት በኋላ ተመልሰህ መጥተህ ብትወስደኝ ደስ ይለኛል ።”

“በደስታ !” ሾፌሩ ፈጥኖ በሩን እንደከፈተላት ካተሪን ወደ ሞቃቱ የበጋ አየር ወጣ አለች ። እግሯ ይንቀጠቀጣል ። “ሚስስ ፣ ምን ሆንሽ?” መልስ አልነበራትም ። ከገደል ጫፍ ቁልቁል ተምዘግዝጋ ከማታውቀው ነዳይ መሬት ልትፈጠፈጥ የተቃረበች መስሎ ተሰማት ።

በተጨናነቀው ሕዝብ ግፊያና ጫጫታ መሃል እየተሽሎከሎከች መራመድ ጀመረች ። በሴቶቹ ገዳም ውስጥ ካየችው ፀጥታና መገለል አኳያ አሁን ያጋጠማት ቅዠት መሰላት ። እግሯ ወደመራት ስትጓዝ በአቴንስ እንብርት ከምትገኘው ፕላክ ከተባለች ያረጀች የከተማ ክፍል ደረሰች ። የከተማዋ መንገዶች ጠባብ ፣ ጠመዝማዛና የተሸረሸሩ ናቸው ። ወደታች የሚወስደው ደረጃ ነጭ ቀለም ወደተቀቡና ያለፕላን ወደታነፁ ሻይ ቤቶችና ቡና ቤቶች የሚወስድ ሲሆን ወደዚህም ለመሄድ የግድ በአረጃ መሰላል ዚጤ ደረጃዎች ማለፍ ያስፈልጋል ። በማታውቀውና ልትቆጣጠረው በማትችለው ደመነፍሷ እየተመራች መንገዷን አገኘች ። ከተማውን ቁልቁል ለማየት ከሚቻልበት የመዝናኛ ሠገነት አጠገብ እንደደረሰች ቆም ብላ በአትኩሮት ተመለከተች ። ‘እዚያ ወንበር ላይ ተቀምጬ ነበር ። በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ የምግብና የመጠጥ ዝርዝር አቅርበውልኛል ። ሦስት ሰዎች ነበርን ።’

‘ምን ትቢያለሽ?’ ብለው ጠየቁኝና ‘መልሼም እናንተ ብታዙልኝስ? ለምግብቹ እንግዳ ስለሆንኩ የማይሆን ምግብ እንዳላዝ ብዬ ነው !’ አልኳቸው ። ‘ማቁ ። ማን እነማን ነበሩ?’

አስተናጋጁ ወደካተሪን ጠጋ አለ ። በግሪክኛ ‘ምን ልታዘዝ?’ ሲለኝ እኔም በግሪክኛ መልሼ ‘አመሰግናለሁ ምንም አልፈልግም’ አልኩ ። ቋንቋውን እንዴት ማወቅ ቻልኩ ? ግሪካዊ ነኝን?

ካተሪን የከተማውን አስጐብኚ እንደሚከተል ሰው በፍጥነት ስትንዝ ወዴት እንደምትሄድ የምታውቅ ትመስል ነበር ።

ያየችው ሁሉ የምታውቀው ሆነባት ። በሌላ በኩል ደግሞ ድፍንፍን አለባት ። 'አምላኬ!' አለች በልቧ ። 'አእምሮዬን ስቻለሁ መሰለኝ! እየቃዠሁ ነው ።'

"ትሬፍሊንካስ" የሚል ፅሑፍ ከተለጠፈበት ቡና ቤት አጠገብ አለፈች ። ከአንጐልዋ ጥግ ትውስታዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ ። እዚህ ቦታ አንዳች ነገር ተፈጽሞባታል ፤ ከባድ ነገር ። ግን ምንነቱን ለማስታወስ አልተቻላትም ።

ሰው በሚበዛበት በጠመዝማዛው ጐዳና ተጉዛ ቮኩሬስቱ ከተባለው ሥፍራ ስትደርስ ወደግራ ታጠፈች ። ብዙ የሚያማምሩ ሱቆች አየች ። 'ከእነኚህ ሱቆች ዕቃዎችን ሸምቼ ነበር' አለች በልቧ ። መንገዱን ስታቋርጥ ሰማያዊ ሴዳን መኪናም ሊገጫት ሲል ለጥቂት ተረፈች ።

በአንድ ወቅት የሰማችው ድምፅ እንቃጨለባት ። 'ግሪኮች ገና ወደአውቶሞቢል ዘመን አልደረሱም ። አሁንም በልባቸው አህያ ነጂ ናቸው ። ስለ ግሪኮች ውስጠ ሕይወት ለማወቅ ከፈለግሽ የዘመኑን የህገሪቱን ታሪክ ሳይሆን ጥንታዊውን የግሪክ ታሪክ አንብቢ ። እኛ በጥልቅ የፍቅር ስሜት ፤ በታላቅ ደስታና ሀዘን የተሞላን ነን ። ከዘመናዊው ሥልጣኔ ጋር እነኚህን እንዴት ልናዋህዳቸው እንደምንችል ገና አልተረዳንም ።'

ማነው እንዲህ ያላት?

አንድ ሰው አተኩሮ እየተመለከታት በፍጥነት ወደሷ ገሰገሰ ። አጠገቧ እንደደረሰ ቀስ አለ ። እንዳስተዋላት ከፊቱ ይነበባል ። ሰውዬው ረዥም ጠየም ያለ ነው ። ካተሪን ከዚህ ቀደም አይታው እንደማታውቅ እርግጠኛ ነበረች ። ቢሆንም…

"ሰላም" እሷን በማየቱ የተደሰተ ይመስላል ።

"በረዥሙ ወደውስጥ ተነፈሰች ። "እንተዋወቃለን?"

ሳቅ አለ "በሚገባ ።"

ካተሪን ልቧ በኃይል ሲመታ ተሰማት ። ያለውን እውነታ በመጨረሻ ልታውቀው ነው ። ግን "እኔ ማን ነኝ?" ብሎ ሕዝብ በመላበት ጐዳና ላይ ያገኙትን እንግዳ እንዴት መጠየቅ ይቻላል ።

"ለመ … ለመነጋገር እንችላለን?" ብላ ጠየቀች ካተሪን ።

"የሚሻል ይመስለኛል ።"

ካተሪን ተርበተበተች ። የተደበቀው የማንነቷ ምስጢር ይፋ ሊወጣ በመሆኑ ፍርሃት ፍርሃት አላት ። 'ማወቁ ቢቀርብኝስ? ከዚህ ቀደም ከፉ ነገር ፈፅሜ እንደሆነስ ?'

ሰውዬው ሜዳ ላይ ወደሚስተናገዱበት ሆቴል ይዟት ሄደ ። "በአጋጣሚ በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል" አላት ።

ካተሪን ምራቋን ዋጠችና "እኔም ደስ ብሎኛል" ብላ መለሰች ። የሆቴሉ አስተናጋጅ መቀመጫ ሰጣቸው ።

"ምን ለመጠጣት ትፈልጊያለሽ?" ሲል ሰውዬው ጠየቃት ።

ፅንቅላቷን ነቀነቀች ። "ምንም!"

የሚጠየቁ ብዙ ጥያቄዎች አሏት ። ከየት ይጀመር?

"በጣም ቆንጆ ነሽ" አላት ሰውዬው "የዕድል ነገር አያስገርምም?"

"በጣም እንጂ" ግራ በመጋባቷ ልትንቀጠቀጥ ምንም አልቀራትም። አየር ወደ ውስጥ በኃይል ሳበች ። "እ… ከዚህ ቀደም የት ነበር የተገናኘነው?"

ፈገግ አለ ። 'ጥያቄው አስፈላጊ ነው? የኔ ፍቅር ። ፓሪስ ወይንም ሮም ውስጥ በውድድር ሥፍራዎች ወይም በፓርቲ ላይ' እጁን ዘርግቶ እጇን ተጫናት ። "በዚህ አካባቢ ካየናቸው ሴቶች መካከል አንቺ በጣም ማራኪ ነሽ ። ስንት ነው የምታስከፍይው?"

ካተሪን ምን ማለቱ እንደሆነ ስላልገባት ትኩር ብላ አየችው ። ወዲያው ደንግጣ ብድግ አለች ።

"እንዴ ፣ ምን ነካሽ? የጠየቅሺውን ያክል እከፍ…"

ካተሪን ዞር ብላ ወደመንገዱ ሮጠች ። ከሰዋራ ሥፍራም እንደደረሰች ዝግ አለች ። የተዋረደች ስለመሰላት ዓይኗ እንባ አቀረረ ።

ከፊትለፊቷ ከምታየው ሕንፃ መስኮት ላይ "ማዳም ፒሪስ — ኮከብ ቆጣሪ" የሚል ጽሑፍ አነበበች ። ካተሪን በመጀመሪያ እርምጃዋን ቀነሰች ፣ ከዚያም ቆመች ። 'ማዳም ፒሪስን አውቃታለሁ ። ከዚህ ቀደም እዚህ ቦታ መጥቼ ነበር ።' የልብ ትርታዋ ከፍ አለ ። እስካሁን ተሰውሮባት የቆየው ምስጢሯ ገሀድ የሚወጣው ድንግዝግዝ ካለው የቤቱ መግቢያ በር እንዳለፈች መሆኑን ተሰማት ። በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ ገባች። ቤቱ በድቅድቅ ጨለማ በመዋጡ እውስጥ ያለውን ነገር ለማየት ጥቂት ጊዜ ፈጀባት ። ከዚህ በፊት ያየችው የሚመስላት ባንኩኒ ፣

ወንበሮችና ጠረጴዛዎችም ከጥግ ይታያሉ ። አስተናጋጁ ወደ እርሷ ተጠጋና በግሪክኛ ጥያቄ አቀረበላት ።

“ካሊሜራ”

“ካሊሜራ ፓው ኢነ ማዳም ፒሪስ?”

“ማዳም ፒሪስ?”

አስተናጋጁ በጥግ በኩል ያለ አንድ ባዶ ወንበር ሲያሳያት ካተሪን ሄዳ ተቀመጠች ። አኳኋኑን ሁሉ አስታወሰች ።

ፊቷ የተጨማደደ አሮጊት ጥቁር ልብስ ለብሳ ወደ ካተሪን ቀረበች ።

“ምን ልር...?” አቋርጣ በትኩረት የካተሪንን ፊት ተመለከተች ። ዓይኗ ተበለጠጠ ። “ከዚህ ቀደም ያየሁሽ ይመስለኛል ። ግን ፊትሽ...” ብላ ቁና ቁና ተነፈሰች ። “ተመልሰሽ መጣሽ!”

“ማን እንደሆንኩ ታውቂያለሽ?” አለች ካተሪን በጉጉት እየ ጠየቀች ።

አሮጊቷ አፍጥጣ በቁጣ “አላውቅም ። አንቺ ሞተሻል ፤ ውጪ ከዚህ!”

ካተሪንን እንደመዘረር ሞከራት ። ፀጉሯ ሲቆም ተሰማት ። “እባክሽ። እኔ እንዲሁ...”

“ውጪ ፣ ሚስስ ዶግላስ!”

“የግድ ማወቅ...”

አሮጊቷ አማተበችና ዞር ብላ እልም አለች ።

ካተሪን እየተንቀጠቀጠች ለትንሽ ጊዜ እዚያው ተቀምጣ ቆየችና በጥድፊያ ወደመንገድ ወጣች ። በጭንቅላቷ ውስጥ ያለውም ቃል ተከተላት ። “ሚስስ ዶግላስ!”

የጉርፍ ፉካ የተከፈተ ያህል ነበር ። በርካታ ትዕይንቶች ፣ የተያያዙ ሥዕላዊ ድርጊቶች ወደ አንጐሏ እየተከታተሉ ፈሰሱ ። ‘ሚስስ ላሪ ዶግላስ ነኝ ።’ የባልዋ ቀና መልክ ታያት ። በጣም ታፈቅረው ነበር ፤ ግን አንድ ችግር ሳይፈጠር አልቀረም ። አንድ ችግር...።

ቀጥሎ የመጣባት እይታ የእራሷ ነበር ። ሕይወቷን ለማጥፋት ሙከራ ካደረገች በኋላ በሆስፒታል ውስጥ መንቃቷ ።

ካተሪን እግሯ የማይሽከማት ስለመሰላት ፈርታ ከመሃል መንገድ ላይ ቆመች ። የተለያዩ ሥዕሎች በአእምሮዋ ውስጥ መላሱን ቀጠሉ ።

ላሪ ከሷ በመለየቱ ብዙ መጠጥ ትጠጣ ነበር ። በኋላ ግን ተመልሶ

መጣላት ። በአፓርትመንታቸው ውስጥ እንዳሉ ላሪ “እንዳስቀየምኩሽ አውቃለሁ ። እንደገና ጠባዬን ለማሻሻል እፈልጋለሁ ካቲ አፈቅርሻለሁ ። ካንቺ በቀር ሌላ ሴት ወድጄ አላውቅም ። ሌላ ዕድል እንድትሰጪኝ እፈልጋለሁ ። በድጋሚ የጫጉላ ጊዜ እንዲኖረን ወደ ሌላ ሥፍራ ብንሄድ ምን ይመስልሻል? ኢኦኒና የተባለች በጣም ውብ የሆነች ትንሽ ከተማ አውቃለሁ” ብሏት ነበር ።

በቃ! ሽብር ጀመራት ።

አሁን ወደ አእምሮዋ የመጣው ትውስታ በጣም ያስፈራል ።

ከላሪ ጋር ተራራ ጫፍ ላይ ነበሩ ። ተጥመልማዩ ግራጫማው ጉም ምንም አያሳይም ። ባልዋ ከተራራው ጫፍ አሸቅንጥሮ ሊጥላት ሲል አካባቢውን ይጐበኙ የነበሩ ቱሪስቶች ደርሰው አተረፉት ።

ከዚያ በኋላ ዋሻዎቹ ።

‘የሆቴሉ ፀሐፊ በዚህ አካባቢ ስላሉት ዋሻዎች አጫውቶኛል ። ሰዎች የጫጉላ ጊዜያቸውን ለማሳለፍ ወደዚያው እንደሚሄዱ ነግሮኛል ።’

አብረው ወደዚያው ተጓዙ እና ላሪ ወደዋሻው አስገብቷት እንድት ሞት እዚያው ጥሏት ተመለሰ ።

አስፈሪ የሆኑትንና በፍጥነት ገስግሰው በመምጣት አእምሮዋን ማስጨነቅ የጀመሩትን አሳቦች መግታት ትችል ይመስል በሁለት እጆቿ ጆሮዋን ሸፈነች ።

ከተባለችበት ሥፍራ አንስተዋት ወደሆቴሉ እንደተወሰደች ሐኪሙ የእንቅልፍ መድኃኒት ሰጣት ። እኩለ ሌሊት ላይ ከእንቅልፏ ስትነቃ ላሪና እቁባቱ ማድቤቱ ውስጥ ሆነው ሲገድሏት እቅድ ሲነድፉ በጆሮዋ ሸው አላት ።

— መቼም ማንም ሰው

— እኔ እፈጽመዋለሁ ብየሻለሁ

— ተበላሽ ። ማድረግ የሚችሉት ምንም ነገር የለም

— አሁን ፣ እንቅልፍ ወስዷት እያለ።

በዚያ አስፈሪ እውሎ ነፋስ አዘል ዝናብ ውስጥ ሮጣ መውጣቷን አስታወሰች ። እነርሱም ተከትለዋት ተቀዛፊ ጀልባ ላይ ወጣች ። ነፋሱ ጀልባዋን ወደ ተናወጠው የባሕሩ ማዕበል ገፋው ፤ ጀልባዋ መስጠም ጀመረች ። ከዚያም በኋላ ሕሊናዋን ሳተች ።

ካተሪን መሄድ ተስኗት መንገድ ዳር በተቀመጠው አግዳሚ ወንበር

ላይ ዘፍ አለች ። እንዲህ ከሆነ ቅዥት አልነበረም ማለት ነው ። በእርግጥ ባለቤቷና ዕቁባቱ ሊገድሏት ነበር ።

ከተጣለችበት ተገኝታ ወደ ገዳሙ እንደተወሰደች ሊጐበኛት ወዲያውኑ ስለመጣው እንግዳ ሰው እንደገና አሰበች ። ሰውዬው ልትበር የተዘጋጀች የወርቅማ ወፍ ልዩ አርማ ሰጥቷታል ። “ከእንግዲህ ማንም ሰው አይጐዳሽም ። ጠላቶችሽ ሞተዋል” አሁንም ፊቱን በግልጽ ልታየው አልቻለችም ።

ካተሪን ዞረባት ።

ከዚያም እንደምንም ከተቀመጠችበት ተነሳች ። ጥበቃና እንክብካቤ ወደሚያደርግላት ወደ ዩሜሪስ ሊመልሳት በመጠባበቅ ላይ ወዳለው ሹፌር በዝግታ አመራች ።

ምዕራፍ አራት

“ከቤት እንድትወጣ ለምን ፈቀዳችሁላት” ብሎ ጠየቀ ኮንስታን ቲን ዩሚሪስ ።

“ጌታዬ ይቅርታ” አለ የእልፍኝ አሽከሩ ። “እንዳትወጣ ብለው አላስጠነቀቁንም ። በዚህ ምክንያት...”

ዩሚሪስ መቆጣቱ እንዳይታወቅ ስሜቱን ተቆጣጠረ ። “ግድ የለም፤ ቶሎ ትመለስ ይሆናል ።”

“ሴላ የምታዘዘው አለ ጌታዬ?”

“የለም ።”

አሽከሩ ተመልሶ ሲሄድ ዩሚሪስ በዓይኑ ተከተለው ። ከዚያም ወደ መስኮቱ ሄዶ በእንክብካቤ የተያዘውን አትክልት አሻግሮ ተመለከተ ። ‘አይቶ የሚያስታውሳት ሰው ሊኖር በሚችልበት የአቴንስ ጐዳናዎች ላይ መታየት ለካተሪን አሌክሳንደር አደገኛ ነው ። በሕይወት እንድትኖር ዝም ብዬ ልተዋት ባለመቻሌ አዝናለሁ ። በቅድሚያ ግን — በቀሌ ። እስክበቀላት በሕይወት ትቆያለች ። ማንም ሰው ሊያውቃት ወደማይችል ሥፍራ እልካታለሁ ። ለክትትል ለንደን ምቹ ቦታ ነው ። እዚያ ቢሮዬ ውስጥ ሥራ አሰጣታለሁ ።’

ካተሪን ፣ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ወደቤቱ ስትመለስ ኮንስታን ቲን ዩሚሪስ እፊቷ ላይ ለውጥ መኖሩን ለማንበብ ችሏል ። ካተሪን ጥቁር መጋረጃ ተገልጦላት በድንገት ነፍስ የዘራች ያክል ነበር የተሰማት ። ከሐር የተሠራ የሚያምር ሙሉ ልብስ ለብሳለች ። ዩሚሪስ ቅርጿ ምን ያህል እንደተለወጠ ተገነዘበ ። ‘ቅንዝረኛ!’ አለ በልቡ ።

“ሚስተር ዩሚሪስ...”

“አቤት”

“እኔ... እኔ ማን እንደሆንኩ አውቄአለሁ ። እና.. እና ምን እንደተፈጸመብኝ ተረድቻለሁ ።”

ከፊቱ ላይ ምንም ነገር አይነበብም ። “እውነት? እስቲ ቁጭ በይና

ንገሪኝ ወዳጄ ።”

ካተሪን ስሜቷ ተቀስቅሶ ስለነበረ ለመቀመጥ አልቻለችም ። ብርክ እንደያዛት በምንጣፉ ላይ ከወዲያ ወዲህ እያለች “ባለቤቴና ኖኤሌ ሊገድሉኝ ሞክረው ነበር” አለች ። ቆም ብላ በጉጉት ዓይን ዓይኑን አየች ። “ዘባርቄ ይሆን? እ... እኔ እንጃ ምናልባት ሊሆን ይችላል።”

“ቀጥይ ወዳጄ” አለ በለሆሳስ ።

“በገዳሙ የሚገኙ መነኮሳት ናቸው ሕይወቴን ያተረፉት ። ባለቤቴ ለአንተ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር አይደል?” ብላ እቅጩን አፈረጠች ።

ዴሚሪስ እያመነታ የሚናገራቸውን ቃላት በዋንቃቄ መረጠና “እሺ” አለ ። ምን ያህል ይንገራት? “ከአውሮፕላኖቹ ነጂዎች አንዱ ነበር። ስለአንቺም ኃላፊነት ተሰማኝ ። ብቻ ...”

ቅጭም አለች ። “ግን ማን እንደሆንኩ እያወክ ዛሬ ጠዋት ፡ እንዴት ሳትነግረኝ ቀረህ?”

“ትደነግጪያለሽ ብዬ ስለሰጋሁ ነው” አለ ዴሚሪስ በለሰለሰ አነጋገር ።“አንቺ እራስሽ ብትደርሺበት ይሻላል ብዬ በማሰብም ነው።”

“ባሌስ ምን ሆነ? ያቺ...ያቺ ሴትስ? የት ነው ያሉት?”

ዴሚሪስ የካተሪንን ዓይኖች በትኩረት ተመለከተ ። “ተገደሉ ።”

ፊቷ ደም መስሎ ሲቀላ ተመለከታት ። ትንሽ ድምፅ አሰማች ። ከመቅጽበት ተዝለፈለፈችና መቆም አቅቷት ወንበር ላይ ዘፍ አለች ።

“መንግሥት ነው የረሸናቸው ካተሪን ።”

“ግን ... ለምን?”

ጥንቃቄ ። አደጋ ። “ሊገድሉሽ ስለሞከሩ ።”

ካተሪን ግንባሯን ቋጠረች ። “አልገባኝም ። መንግሥት የሚገድላቸው ለምንድነው? እኔ በሕይወት አለሁ!...”

አቋረጣት ። “ካተሪን ፡ የግሪክ ሕግ በጣም ጥብቅ ነው ። እዚህ አገር ፍትሕ ወዲያው ይገኛል ። በግልጽ ችሎት ለፍርድ ቀርበው ነው የተወሰነባቸው ። ባለቤትሽና ኖኤሌ ፖጂ ሊገድሉሽ መሞከራቸውን ብዙ ሰው ስለመሰከረባቸው ወንጀላቸው ተረጋጧ ነው ሞት የተፈረደባቸው።”

“ለማመን ያስቸግራል” አለችና ካተሪን ከተቀመጠችበት ፈዛ ቀረች ። “ነገሩ በፍርድ ቤት የታየው...”

ኮንስታንቲን ወደእርሷ ሄደና እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገ ። “ያለፈውን ከአእምሮሽ ማውጣት አለብሽ ። ክፉና አሰቃቂ ነገር

ሊፈጽሙብሽ ሞክረው ነው ዋጋቸውን ያገኙት ።” የእርካታ በሚመስል አነጋገር “አንቺና እኔ ስለወደፊቱ መወያየት ያለብን ይመስለኛል ። እቅዶች አሉሽ?”

ያለውን አልሰማችውም ። ‘ላሪ’ አለች በአሳቧ ። ‘የላሪ ፊት ቆንጆ ነው ፡ ሳቂታ ፡ የላሪ ክንዶች ፡ ድምጹም...’

“ካተሪን” አላት ።

ቀና ብላ ተመለከተችው “ይቅርታ”

“ስለወደፊቱ ኑሮሽ አስበሽ ታውቂያለሽ?”

“አላውቅም ...ምን እንደማደርግ የማውቀው ነገር የለም ። አቴንስ ውስጥ የምቆይ ይመስለኛል ።”

“አይሆንም” አለ ዴሚሪስ ጠንከር ባለ አነጋገር ። “ይሄ ጥሩ አሳብ ሊሆን አይችልም ። ደስ የማያሰኙ ትውስታዎችን ሊያመጣብሽ ይችላል ። ግሪክን እንድትለቂ አሳብ አቀርባለሁ ።”

“ግንኮ መሄጃ የለኝም ።”

“ግድየለም እኔ አስቤበታለሁ” አላት ዴሚሪስ ። “ለንደን ውስጥ ቢሮ አለኝ ። በነገራችን ላይ በአንድ ወቅት ዊሊያም ፍሬዘር ከተሰኘ ሰው ጋር ዋሽንግተን ውስጥ ሠርተሽ እንደነበረ ታስታውሽዋለሽ?”

“ዊሊያም ...?” ወዲያው አስታወሰችው ። ያ ወቅት በሕይወቷ ውስጥ ካጋጠማት አስደሳች ጊዜያቶች መካከል አንዱ ነበር ።

“እንደመሰለኝ የአስተዳደር ረዳቱ ነበርሽ ።”

“አዎ እኔ...”

“በለንደንም ተመሳሳይ ተግባር ልታከናውኚልኝ ትችያለሽ ።”

አመነታች ። “እኔ እንጃ ፡ ብድር መላሽ ላለመሆን አይደለም ግን...”

“ይገባኛል ። ትንሽ ፈጠንኩብሽ መሰለኝ?” አላት ዴሚሪስ አባባሏን የደገፈ በመምሰል ። “ስለዚህ ለማሰብ ትንሽ ጊዜ ያስፈልግሻል። በክፍልሽ ውስጥ ጥሩ እራት ተመግበሽ ለምን ስለዝርዝር ሁኔታው ጠዋት አንወያይም?”

በክፍሏ ውስጥ እራት እንድትመገብ የመጠየቁ ነገር በመጨረሻ ላይ የተከሰተለት አሳብ ነው ። ሚስቱ እንድታየው ጨርሶ አልፈለገም ።

“በጣም አሳቢ ነህ” አለችው ካተሪን ።

‘በጣም ደግ ሰው ፡ ልብሶቹም ...’

እጇን መታ መታ አደረገና ለትንሽ ጊዜ ያዝ አድርጓት ቆየ ። “ለራሴ ደስታ ብቼ ነው ።”

መኝታ ቤቷ ውስጥ እንዳለች ጠራራ የነበረችው ፀሐይ አንፀባራቂ ቀለም እየሰጠች በስማያዊው ባሕር ላይ መጥለቅ መቃረቧን የሚያሳይ ምልክት ስትፈነጥቅ ተመለከተች ። ያለፈውን ማስታወሱ ዋጋ የለውም ። ማሰብ የሚገባው ለወደፊቱ ነው ። ‘ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ስለሰጠኝ እግዚአብሔርን አመስግነዋለሁ ።’ ሕይወቷ የተንጠላጠለው በእርሱ ላይ ነው ። እርሱን ባታገኝ የምትሄድበት ምንም አማራጭ አልነበራትም ። ለንደን ውስጥ ሥራ ሰጥቷታል ። ‘ሥራውን ልቀበለው ነው?’ በሩ እንደተንኳኳ ሃሳቧ ተቋረጠ ። “እራትሽን አምጥተናል ሚስ ።”

ካተሪን ከሄደች በኋላ ሁለቱም ስላደረጉት ውይይት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ለረኾም ጊዜ ተቀምጠ አስቧል ። ኖኤል ። ዴሚሪስ በሕይወቱ ውስጥ አንዴ ብቻ ስሜቱን መቆጣጠር ተስኖት ነበር ። በኖኤሌ ፓጂ ፍቅር ከፉኛ ተጠምዶ ቅምሙ አድርጓት ነበር ። እንደ እርሷ ዓይነት ሴትም አጋጥሞት አያውቅም ። ስለ ኪነጥበብ፣ ስለሙዚቃና ስለንግድ ሥራ በደንብ አድርጋ የምታውቅ ሲሆን የሚስተካከላት ሰው ከቶ አልነበረም ። ስለኖኤሌ እንድ ለብቻው ተመዝዞ የሚደነቅ ነገር ለማውጣት ይከብደው ነበር ። ሁሌ ነገሯ የሚያጓጓና የሚያስደንቀውም ነበር ። ከማንኛውም ነገር አስበልጦ ያፈቅራታል ። እስካሁን ካጋጠሙት ሴቶች በጣም ቆንጆዋና ፍላጎቱንም የምታረካ እንስት እሷ ናት ። የመድረክ ተዋናይነት ተግባሯን አቁማ ጊዜዋን በሙሉ ከእርሱ ጋር ታሳልፍ ነበር ። ኖኤሌ ከዚህ ቀደም ተሰምቶት የማያውቀውን የስሜት ረመጥ ጭራበታለች ። ፍቅረኛው ፣ የልብ ወዳጁና ጓደኛው ነበረች ። ዴሚሪስ ከልቡ አምኗት እያለ ወደላሪ ዶግላስ በመኮብለል ከድታዋለች ። ኖኤሌንም ለሞት የዳረጋት ጥፋቷ ይሄው ነበር ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከግሪክ ባለሥልጣናት ጋር ተነጋግሮ አስከሬኗ በግል ደሴቱ ውስጥ በሚገኘው መካነ መቃብር እንዲቀበር አድርጓል ። እንዴት ዓይነት ማራኪ ቁመና እንደነበራት ያላደነቀ ሰው የለም ። እውነት ለመናገር ፣ ዴሚሪስ የቀብሯ ቦታ እዚያ እንዲሆን ያሴረው በዚያች

ውሻ መቃብር ላይ ዘወትር መረማመዱ ልዩ ደስታን ስለሚሰጠው ነው ። ከዴሚሪስ መኝታ ክፍል ውስጥ ከአልጋው ጐን ኖኤሌ አምራ ደምቃ ወደ እሱ በፈገግታ እያየች የተነሳችው ፎቶግራፍ ተቀምጧል ። በጊዜ የጠፋ የዘለዓለም ፈገግታ ።

ዓመት ቢያልፋትም ዴሚሪስ ዛሬም ስለእርሷ ማሰብን ከአእምሮው ሊያስወግድ አልቻለም ። ማንም ዶክተር አክሞ ሊያድነለት የማይችል የቆላ ቁስል ሆናበታለች ።

“ለምን ኖኤሌ፣ ለምን፣ ሁሉን ነገር ሰጥቼሽ ነበር ። አፈቅርሽ ነበር ፣ አንቺ ውሻ! በጣም ወድጄሽ ነበር ። አሁንም እወድሻለሁ ።”

እና ሌላው ላሪ ዶግላስ ነበር ። እሱም ተሰቃይቷል ። ቢሆንም ዴሚሪስ በዚያ ብቻ ሊያበቃ አልፈለገም ። ሌላ የበቀል እቅድ አልሟል ። በደንብ የታሰበበትና ሚላማውን የማይስት እቅድ ። ዶግላስ ኖኤሌን እንዳማገጠበት እርሱም በተራው የዶግላስን ሚስት አማግጦ በበቀል የመንፈስ እርካታ ሊያገኝ ነው ። ከዚያ በኋላ ካተሪንን ወደ ባሏ ይሰዳታል ።

“ኮስታ...”

ድምፁ የሚስቱ ነበር ።

ሜሊና ወደቤተ መጻሕፍቱ ገባች ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከጥንታዊ የግሪክ መላፍንታዊ ቤተሰብ የተገኘችዋን ውቧን ሜሊና ላምብሩን አግብቶ ነበር ። ሴትየዋ ረዘም ያለች ሽንቃጣና ደርባባ ናት ።

“ኮስታ ፣ እዚህ ቤት ውስጥ ያየኋት ሴት ማን ነች?” ድምጿ ያሰፈራ ነበር ።

ዋያቄዋ ወዲያው ገባው ። “ምን አልሽ? እ! የአንድ የንግድ ሽሪኬ ጓደኛ ናት” አለ ዴሚሪስ ። “ለንደን ከሚገኘው ቢሮዬ ሄዳ ልትሠራ ነው።”

“በጨረፍታ አይቻት ነበር ። የማውቃት — የማውቃት ይመስለኛል ።”

“እረ?”

“እም” ሜሊና አመነታች ። “አንተ ዘንድ ይሠራ የነበረውን አውሮፕላን ነጂ ሚስት መስላ ታየችኝ ። ቢሆንም እሷን ልትሆን አትችልም ። እነርሱ ገድለዋት የለም እንዴ?”

“እም” ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአባባሏ ተስማማ ። “ገደሏት።”

ሜሊና ተመልሳ ስትሄድ ትኩር ብሎ ተመለከታት ። ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ። ሜሊና ሞኝ አይደለችም ። ‘እርሷንኮ ማግባት አልነበረብኝም’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ‘ትልቅ ስሕተት ነው...’

ከአሥር ዓመታት በፊት የሜሊና ላምብሩና የኮንስታንቲን ዴሚሪስ መጋባት ከአቴና ጀምሮ እስከ ሪቬራና ኒው ፖርት ባለው ነጋዴና ሌላም ሕብረተሰብ ዘንድ ትልቅ አስደንጋጭ ወሬ ሆኖ ሰንብቷል ። ጋብቻውን አስገራሚ ያደረገው ሙሽሪቷ ከመዳሯ ከአንድ ወር በፊት ሌላ ሰው ለማግባት ታጭታ የነበረ መሆኑ ነው ።

ሜሊና ላምብሩም በሕጻንነቷ ወቅት ቤተሰቦቿ ፍላጐቷን እንዲ ያሟሉላት በጣሙን ታስጨንቃቸው ነበር ።

ዕድሜዋ አሥር ዓመት ሲሞላው መርከበኛ ለመሆን ምኞት አደረባት ። በወደብ ላይ ከቆመው መርከብ ላይ ለመሳፈር ስትሽሎክ ሎክ የቤተሰቡ ሹፌር አይቷት አዋርዶ ነው ወደቤት የመለሳት ። ከሁለት ዓመት በኋላ ከተዘዋዋሪ የሰርከስ ትርዒተኞች ጋር ለመክብ ለል ሞክራለች። ዕድሜዋ አሥራ ሰባት ሲሞላ ደግሞ ቁንጅናዋና ሥኖር ቁዋር የሌለው ሀብቷ ፡ እንዲሁም የሚሃሊስ ላምብሩ ሴት ልጅ መሆኗ ያኩራራት ጀመር ። ጋዜጠኞች ስለእርሷ መጻፍ ደስ ይላቸዋል። እንደተረት ውስዋ ገፀ ባሕርያት አጫዋች ባልንጀሮቿ ልዕልቶችና ልዑላን ነበሩ ። እንደዚህ ሆኖም በተአምር እንደሌሎቹ ከመበላሸት ድናለች ። ሜሊና በአሥር ዓመት ከሚበልጣት ወንድሟ ከስፒሮስ ጋር በጣም ትዋደድ ነበር። ሜሊና አሥራ ሦስት ዓመት ሲሞላት ወላጆቻቸው በጀልባ አደጋ ስለሞቱ ያሳደጋት ወንድሟ ነው ።

ሜሊና ፡ ስፒሮስ ሲንከባከባት ከመጠን እንደሚያሳልፍ ተሰምቷታል ። ሜሊና ለአቅመ ሔዋን እንደደረሰች ማን ሊመጥናት እንደሚችል ከመጨነቁም ሌላ ለጋብቻ ሊጠይቃት የሚቀርበውን ሰው ማንነት በጥንቃቄ ያጠና ነበር ። እንዳጋጣሚ ከቀረቡት መካከል አጥጋቢ መስለው የታዩት አልነበሩም ። “ጥንቃቄ ማድረግ አለብሽ” ይላታል ሁሌ ሲመክራት ። “ወጣት ፡ ሀብታምና ቆንጆ ከመሆንሽም በላይ ዝነኛም ነሽና በዓለም ውስጥ ላሉ ሀብት አሳዳጆች ዒላማ ነሽ ።”

“ብራቮ ውድ ወንድሜ ። ይሄ ሁሉ ምክርህ ዕድሜዬ ሰማንያ ዓመት ሞልቶ አርጅቼ አፍጅቼ እስክሞት ድረስ ይበቃኛል ።”

“አታስቢ ሜሊና ላንቺ የሚገባ ሰው ወደፊት ይመጣል ።”

ካውንት ቫሲሊ ማኖስ ይባላል ። ዕድሜው አርባ አምስት ገደማ ሲሆን ፡ ከተከበረ ጥንታዊ የግሪክ ቤተሰብ የወጣ የታወቀ ነጋዴ ነው ። ካውንት ቆንጆዋንና ወጣቷን ሜሊና እንዳያት ወዲያው በፍቅር ተያዘ ። ለጋብቻ ጥያቄ ያቀረበላትም እንደተዋወቁ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ነበር።

“ላንቺ የሚስማማ ሰው ነው” አላት ስፒሮስ በደስታ ። “ማኖስ የተደላደለ ከመሆኑም ሌላ በፍቅር ከንፎልሻል ።”

ሜሊና አባባሉ እምብዛም ስሜት አልሰጣትም ። “አይማርከኝም ስፒሮስ! በተገናኘን ቁጥር ስለንግድ ነው የሚያወራው ። ንግድ፡ ንግድ ፡ ንግድ ። ለፍቅር ግምት የሚሰጥ ሰው ቢሆን ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር ።”

ወንድሟ ኩስተር ብሎ “ፍቅር ብቻውን ለጋብቻ የሚበቃ ነገር አይደለም ። ላንቺ የሚያስፈልግሽ ባል ፡ የተደላደለ የማይለዋወጥና ጊዜውን ሁሉ ለአንቺ የሚሰዋ መሆን አለበት” አላት ። በመጨረሻ ሜሊና የካውንት ማኖስን ልመና እሺ እንድትል ተገደደች ።

መንፈሱ በደስታ የተነካው ካውንት “በዓለም ውስጥ ካሉት ደስተኛ ሰዎች አንዱ አደረግሽኝ” አላት ። “አዲስ ያቋቋምኩትን ኩባንያ ሜሊና ኢንተርናሽናል ብዬ ሰይሜዋለሁ ።”

የጽጌረዳ አበቦች እንደሚሻላት አስታወቀችው ። የሠርጉ ቀን ኑወሰነ ፤ ለአንድ ሺህ ሰዎች የጥሪ ወረቀት ተላከ ፤ ዝርዝር እቅዶ ° ተነደፉ ።

ከዚያ በኋላ ነበር ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሜሊና ላምብሩ ሕይ ውስጥ የገባው ።

የተገናኙትም ለእጮኛሞቹ የቀለበት በዓል ክብር ከሚደገሱት በርካታ ግብዣዎች ውስጥ ባንዱ ላይ ነበር ።

አስተናጋጅዋ አስተዋወቀቻቸው ። "ሜሊና ላምብሩ ትባላለች — ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ።"

ዴሚሪስ በትናንሽ ጥቁር ዓይኖቹ ትኩር ብሎ አያት ። "ምን ያህል ጊዜ ያቆዩሻል?" ሲል ጠየቃት ።

"ምን አሉኝ?"

"ውበት ምን እንደሆነ ለኛ ለአላፊዎቹ እንድትመሰክሪ ከገነት የተላክሽ ሳትሆኚ አትቀሪም ።"

ሜሊና ሳቅ አለች ። "በሀሰት ሰው ካቢ ነዎት ሚስተር ዴሚ ሪስ ።"

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "አንቺን በሀሰት ልካብ ማለት አይቻ ልም። የምናገራቸው ማንኛቸውም ቃላት በትክክል ማንነትሽን ሊመ ክሉ እንኳ አቅም የላቸውም ።"

በዚህን ጊዜ ካውንት ማኖስ ወደነሱ ቀርቦ ንግግራቸውን አቋረጠ ።

ያን ዕለት ሌሊት በእንቅልፍ ከመወሰዷ በፊት ሜሊና ስለዴሚ ሪስ አስባ ነበር ። ከዚህ ቀደምም ፤ ሰውዬው ሀብታም ፤ ሚስቱ የሞ ተችበት ፤ ሴት አሽቃባጭና ጨካኝ ነጋዴ ነው እየተባለ ሲወራበት ሰምታለች ።

'እንኳን ከእርሱ ጋር ድሮ አልተነካካሁ' አለች ሜሊና በአ ሳቧ። አማልክቱ ይስቁ ነበር ።

ግብዣው በተደረገ በማግስቱ የሜሊና የልፍኝ አሽከር ቁርስ ወደምትመገብበት ክፍል ገባ ። "የሚስተር ዴሚሪስ ሹፌር አንድ ጥቅል ዕቃ አምጥቶልሻል ሚስ ላምብሩ ።"

"እስቲ ወዲህ አምጣው ።"

'መስሎታል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሀብቱ የሚስበኝ ይመስ ለዋል ። ምናለ ታዲያ በገዛ እጁ የሚያበሳጨውን ነገር እያዘጋጀ ነው። የፈለገውን ነገር ቢልክ...ለምን የከበረ ዕንቁ ወይንም ፣ ወይ ንም እጅግ ውድ የሆነ ጥንታዊ ቅርስ አይሆንም...አውኑኑ መልሼ ነው የምልክለት።'

ታኮው ትንሽና ሞላላ ሲሆን ባማረ ሁኔታ ተጠቅልሏል ። ምን እንደሆነ ለማወቅ በመጓጓት ሜሊና ጥቅሉን ፈታችው ። በውስጡ ያለው ካርድ ላይ "የላኩልሽ የምትወጂው ስለመሰለኝ ነው ፣ ኮንስታ ንቲን ።" የሚል ተጽፏል ።

ስጦታው በቆዳ የተጠረዘ በኒኮስ ካዛንዛኪስ የተጻፈ ቶዳ ራባ የተሰኘ መጽሐፍ ነው ። ሜሊና ይህን ደራሲ እንደምትወድ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

ሜሊና ትሕትና የተሞላበት ምስጋና ጻፈችና አሰላሰለች ። 'እን ዲህ ነው እንግዲህ ።'

በሚቀጥለው ቀን ሌላ ጥቅል መጣ ። የአውኑ ደግሞ በምትወ ደው ሙዚቃ ቀማሪ የተደረሰ ዴሊኡስ የተሰኘ ዘፈን ያለበት ሸክላ ነው ። አብሮት ያለው ማስታወሻ "ይህንን እያዳመጥሽ ቶዳ ራባን ስታነቢ ደስ እንደሚልሽ አምናለሁ" ይላል ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ ስጦታ በየዕለቱ ጐረፈ ። የምትወደው አበባ ፣ ሽቶ ፣ ሙዚቃና ፣ መጻሕፍት ተሸጉዶዱ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፍላጐቷ ምን እንደሆነ ለማጥናት ያላደረገው ጥረት አልነበ ረም ። እሷም በሚደረገው ሁሉ ከመታለል በስተቀር ምንም ለማድ ረግ አልቻለችም ።

ሜሊና ምስጋና ልታቀርብ እንደደወለች "ከዚህ የበለጠ ለአንቺ የሚሆን ባደርግ ምንኛ ደስ ይለኝ ነበር" አላት ።

'ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነቶቹን ቃላት በስንቶቹ ሴቶች ጆሮ አንቆርቁሮ ይሆን?'

"ሜሊና ፣ አብረሽኝ ምሳ ልትበዪ ትችያለሽ?"

እምቢ ለማለት ፈለገችና እንደገና አሰበች ። "ከሰውዬው ጋር ምሳ ብበላ ምን አጎዳለሁ ። ለኔ አሳቢዬ ነው ።"

"በጣም ጥሩ ።"

ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ምሳ ልትመገብ መዘጋጀቷን ለካው
ንት ማኖስ በገለፀችበት ወቅት ተቃውሞዋት ነበር ።

"የኔ ፍቅር ምን ያስፈልጋል? ከዚያ አደገኛ ሰውዬ ጋር የሚያግ
ባባችሁ ነገር ያለ አይመስለኝም ። እርሱ ዘንድ የምትሄጂው ለምን
ድን ነው?"

"ሳሲሊስ ፡ በየዕለቱ ጥቃቅን ስጦታዎችን ይልክልኝ ስለነበረ
ይህንኑ እንዲያቆም ልነግረው ነው ።" ሜሊና እነኚህን ቃላት እንደ
ተናገረች 'ይህንንማ በስልክ ልነግረው እችል ነበር' አለች በልቧ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፓኔፒስቲሙ ጎዳና ላይ ከሚገኘው ፍሎካ
ሬስቶራንት ፡ አስቀድሞ ቦታ እንዲያዝ አዘዘና ሜሊና ስትደርስ
ቀድሞ ጠበቃት ።

ከተቀመጠበት ተነሳ ። "መጣሽ? አሳብሽን ትቀይሪአለሽ ብዬ
ሰግቼ ነበር ።"

"ሁል ጊዜ ቃሌን እጠብቃለሁ ።"

ወደ እርሷ እየተመለከተ ፊቱን ኮስተር አደረገ ። "እኔም ቃሌን
የምጠብቅ ሰው ነኝ ። አገባሻለሁ ።"

ሜሊና በከፊል በደስታ ፡ በከፊል በንዴት ተውጣ ጭንቅላቷን
ነቀነቀች ። "ሚስተር ዴሚሪስ ፡ ሌላ ሰው ለማግባትኮ ታጭቻለሁ።"

"ማኖስን?" የማጥላላት ዓይነት ምልክት በእጁ አሳያት ።

"እርሱ ለአንቺ የሚስማማሽ ሰው አይደለም ።"

"እረ ። ለምን ይሆን?"

"ስለ እርሱ በደንብ አጣርቻለሁ ። ቦቤተሰባቸው ውስጥ የጎኽ
ነት በሽታ አለ ። የደም ሥር በሽታም አለበት ። ብሩሰልስ ውስ
ጥም ሕገወጥ ወሲብ ፈጽመሐል ተብሎ በፖሊሶች እየተፈለገ ነው።
በዚህ ላይ አደገኛ የሆነ የቱኒስ ኳስ ተጫዋች ነው ።"

ሜሊና ሳቋን ልታቆም አልቻለችም ። "አንተስ?" ብላ ጠየቀ
ችው ።

"እኔ ቱኒስ አልጫወትም ።"

"ገባኝ ፡ ታዲያ አንተን ማግባት ያለብኝ ለዚህ ነዋ!"

"አይደለም ። እኔን የምታገቢው እስካሁን በዓለም ላይ ከነበ

ሩት ሴቶች ሁሉ ይልቅ በጣም ደስተኛ ሴት ስለማደርግሽ ነው ።"

"ሚስተር ዴሚሪስ..."

እጁን እጇ ላይ ጫነና "ኮስታ" አለ ።

እጇን ከእጁ ሥር ስባ አወጣች ። "ሚስተር ዴሚሪስ ፡ ዛሬ
እዚህ የመጣሁት በየጊዜው የምትልክልኝን የስጦታ በረከት እንድታ
ቆም ልነግርህ ነው ። ሁለተኛ ላይህ ፈቃደኛ አይደለሁም ።"

ረዘም ላለ ጊዜ ትኩር ብሎ አያትና "እርግጠኛ ነኝ ጨክኝ
ሴት እንዳልሆንሽ ።"

"እንዳልሆንኩ እተማመናለሁ ።"

ፈገግ አለና "ጥሩ ፡ ስለዚህ ልቤን አታቆስዪውም" ሲል ተና
ገረ ።

"ልብህ ያንን ያህል በቀላሉ ለመቁሰል እጠራጠራለሁ ። ሰፊ
ልምድ ያለህ ይመስለኛል ።"

"ያማ ካንቺ ጋር ከመተዋወቁ በፊት ነበር ። ስለአንቺ ለረ
ዥም ጊዜ ሳልም እንደነበረ ታውቂያለሽ?"

ሜሊና ከት ብላ ሳቀች ።

"የምሬን ነው ። በዕድሜ ወጣትበነበርኩ ጊዜ ስለ ላም
ብሩ ቤተሰቦች አነብ ነበር ። ያኔ አንቺ ሀብታም እኔም መናጢ ይሀ
ነበርኩ ። ምንም አልነበረኝም ። የምኖረው ከእጅ ወደአፍ በሆነ
ሥራ ነበር ። አባቴ በፒራኡስ ወደብ ላይ የሚሠራ ተሸካሚ ነበር ።
አሥራ አራት ወንድሞችና እህቶች ነበሩኝ ። እና የምንፈልገውን
ለማግኘት ሁሌ ትንቅንቅ ማድረግ ነበረብን ።"

አነጋገሩ በጣም ነካት ። "እና አሁን ሀብታም ነህ?"

"አዎ ፡ ግን ገና መንካት ከሚገባኝ ጣራ አልደረስኩም ።"

"ረሀብ ይርበኝ ነበር ። አሁንም ይርበኛል ።"

እውነትን ከዓይኑ ውስጥ ለማንበብ ችላለች ። "እንዴት...እን
ዴት አድርገህ ነው የተነሳኸው?"

"በእውነት ለማወቅ ትፈልጊያለሽ?"

ሜሊና ሳታውቀው ከአፏ አምልጦ "በእውነት ለማወቅ እፈል
ጋለሁ" አለች ።"

"አሥራ ሰባት ዓመት እንደሞላኝ ለአንድ የነዳጅ ኩባንያ ለመ
ሥራት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተቀጥሬ ሄድኩ ። ደስ የሚል

አልነበረም። አንድ ቀን ማታ በትልቅ የነዳጅ ኩባንያ ውስጥ ከሚ ሠራ ወጣት የሥነ አፈር ተመራማሪ ጋር እራት ተመግቤ ነበር ። እኔ ስቴክ ሥጋ እንዲቀርብልኝ ሳዝ እርሱ ሾርባ ብቻ ነበር የጠ ጣው። ስቴክ ሥጋ ለምን አላዘዝክም ብዬ ስጠይቀው የመንጋጋ ጥርስ ስለሌለኝና ለማስተከልም ስለማልችል ነው ብሎ መለሰልኝ ። ሰው ሰራሽ የመንጋጋ ጥርስ እንዲገዛ ሃምሳ ዶላር ሰጠሁት ። ከወር በኋላ እኩለ ሌሊት ላይ ስልክ ደውሎ አዲስ የነዳጅ ዘይት ክምችት ማግኘቱን ገለጠልኝ ። ስለጉዳዩ ለአሠሪውም አልገለጠም ነበር ። በነገታው ከየቦታው ገንዘብ ተበዳድሬ ነዳጁ ተገኝበት የተባለውን መሬት ገዛሁ ። በዓለም ውስጥ ከፍተኛው የነዳጅ ዘይት ክምችት የሚገኝበት ሆኖ ተገኘ ።”

ሜሊና በጣም አጓጊ የሆነውን ንግግሩን በጥሞና ታዳምጥ ነበር።

“መነሻዬ ይሄ ነው ። የነዳጅ ዘይት ማጓጓዣ ስላስፈለገኝ ብዙ መርከቦች ገዛሁ ። ከዚያ ማጣሪያ ፣ ቀጥሎ አውሮፕላን ።” ነቅነቅ አለ ። “እንዲያ እያለ ሄደ ።”

ስለስቴክ ሥጋው የነገራት ታሪክ ሐሰት መሆኑን ተጋብተው ብዙ ጊዜ አስከቆዩ ጊዜ ድረስ ሜሊና አላወቀችም ነበር ።

ሜሊና ላምብሩ ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ደግሞ ለመገናኘት ምንም ፍላጐት አልነበራትም ። ዴሚሪስ ሆነ ብሎ በተቀናበረ ፣ ግን አጋጣሚ መስሎ በሚታይ ሁኔታ ሜሊና በምትገኝበት ፓርቲ ፣ ትያትርና የበጎ አድራጐት ድርጅት ስብሰባ ላይ ይገኛል ። ባየችው ቁጥር የሰውዬው የመስህብ ኃይል ጉድ እያረጋት መሆኑ ይሰማታል። ከሱ ሌላ በተለይ ቫሲሊስ ማኖስ ምን ያህል እንዳስጠላት ለማመን ፈራች ።

ሜሊና ላምብሩ የጀርመኖችን ሥዕል በጣም ትወዳለች ። በብ ሩሌዬል የተሳለው ሃንተርስ ኢን ዘ ስኖው የተሰኘው ሥዕል ገበያ ላይ ሲውል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቀድሟት ገዝቶ በስጦታ መልክ ላከላት ።

ሜሊና ፍላጐቷን ቀድሞ የማወቅ ረቂቅ ችሎታውን በጣም አደነቀች ። “እንዲህ ዓይነት ውድ ስጦታ ከአንተ መቀበል አልች ልም” ስትል ተቃውሞዋን ገለጸችለት ።

“እ! ስጦታኮ አይደለም ብድር ነው ። ዛሬ ከኔ ጋር እራት በመብላት ትከፍይኛለሽ ።”

በመጨረሻ ተስማማች ። ሰውዬው ሊቋቋሙት የሚችሉት አይ ደለም ። ከሳምንት በኋላ ሜሊና ለካውንት ማኖስ የገባቸውን የጋ ብቻ ቃል ኪዳን አፈረሰች ።

ሜሊና ስለዚሁ ውሳኔዋ ለወንድሟ ስትነግረው ከው አለ ።

“በእግዚአብሔር ለምን?” ብሎ ጠየቃት ስፒሮስ ። “ግን ለምን?”

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ስለማገባ!”

በጣም ተረበሸና “አብደሻል ልበል? ዴሚሪስን ልታገቢው አትች ይም ። ሰውዬው ጭራቅ ነው ፤ ያጠፋሻል ። ምናልባት ....”

“ስለእርሱ ያለህ አመለካከት የተሳሳተ ነው ። ስፒሮስ በጣም ጥሩ ሰው ነው ። ደግሞ ተዋደናል ። .....”

“ተዋዳችሁ ሞታችኋል” አለ በማሽሟጠጥ ። “አንድ ጥቅም ይኖረዋል እንጂ ለፍቅር ብሎ እይደለም። ከዚህ ቀደም ሴቶችን ምን ያደርግ እንደነበር ታውቂያለሽ? እርሱ ...”

“ያ ያለፈ ታሪክ ነው ስፒሮስ ፤ ሚስቱ ለመሆን ወስኛለሁ ።”

እህቱን ከጋብቻው ለማከላከል ሊያደርግ የሚችለው ምንም ነገር አልነበረም ።

ከአንድ ወር በኋላ ሜሊና ላምብሩና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተጋቡ ።

በመጀመሪያ ሲታይ ትዳራቸው የተዋጣላት ይመስል ነበር ። ኮንስታንቲንም አስደሳች ፣ ትሁት ፣ አንጀት የሚበላና የጋለ የፍቅር ስሜት ያለው ፍቅረኛ ነበር ። ያልታሰበ አስደሳች ስጦታዎች በማቅረብና ለሽርሽር ብርቅ ወደሆኑ ሥፍራዎች ይዟት በመሄድ ያስደስታታል ።

በጫጉላ ጊዜያቸው የመጀመሪያዋ ምሽት “የመጀመሪያዋ ሚስቴ ልጅ ልትወልድልኝ አልቻለችም ነበር ። አሁን ግን ብዙ ወንድ ልጆች ይኖሩናል” አላት ።

“ሴት ልጅስ አያስፈልገንም?” ብላ በሽሙጥ ጠየቀችው ።

“ደስ ካለሽ ዋሩ ። ግን መጀመሪያ ወንድ ልጅ ።”

ሜሊና ቅሪት መያዟን ስታውቅ ኮንስታንቲን በጣም ነበር የፈነደቀው ።

“ይተካኛል ። ግዛቴን ይወርሳል” አለ በደስታ ።

በሦስተኛው ወር ሜሊናን አስወረዳት ። ይህ ሲፈጸም ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከግሪክ ውጭ ነበረ ። ከሄደበት ሥፍራ ተመልሶ ነገሩን ሲሰማ እብድ ሆነ ።

“ምንድን ነው ያደረግሽው?” ሲል ጮኸባት ። “እንዴት ሊያስወር ድሽ ቻለ?”

“ኮስታ ፣ እኔ ……”

“ግድየለሽ ነበርሽ ማለት ነው ።”

“በፍፁም ፣ እምልልሃለሁ ….”

አየር በኃይል ወደ ውስጥ ሳበና “መልካም ፡ የሆነው ሆኗል ። ሌላ ወንድ ልጅ ይኖረናል” አላት ።

“እኔ ….እኔ አልችልም” አለች ዓይኑን ማየት እያፈረች ።

“ምንድንነው የምትዪው?”

“በአፕራሲዮን ማኅፀኔን ስለዘጉት ከእንግዲህ ልወልድ አልች ልም።”

እዚያው እቆመበት እንደበረዶ ቀዘቀዘና የኋሊት ዞሮ ቃል ሳይተነ ፍስ ውልት አለ ።

ከዚያች ደቂቃ አንስቶ የሜሊና ሕይወት ምድራዊ ሲኦል ሆነባት ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሚስቱ ሆን ብላ ጽንሱን ያስወጣች መስሎት ጨርሶ ዘንትና ሌሎች ሴቶችን ማባረር ጀመረ ።

ለሜሊና ውርደቱ በይበልጥ እንዲሰማት ያደረገው ባሏ ከሌሎች ሴቶች ጋር ያለው ግንኙነት ይፋ እንዲወጣ የሚያደርገው ጥረትና ይኸው ተግባሩ ይሰጠው የነበረው እርካታ ነው ። ከፊልም ተዋናዮች ፣ ከአፔራ ዘፋኞች ፣ ከጓደኞቹ ሚስቶች ጋር በግልጽ ይማግጥ ነበር ። ፍቅረኞቹን በቺአስ አካባቢ ወዳለው የግል ደሴቱ ፣ ወደ መንሸራሸሪያ ጀልባውና የሕዝብ መዝናኛ ሥፍራዎች ይዟቸው ይሄዳል ። ይህንኑ የማተራመስ ተግባሩን ጋዜጦች በደስታ ያራግቡለታል ።

በአንድ የታወቀ ባንከኛ ቤት በእራት ላይ ተገኝተው ነበር ።

“አንተና ሜሊና መምጣት አለባችሁ” ባንከኛው ስላለው ነበር ባለቤቱን ይዞ የመጣው ። “በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የቻይናውያን ምግብ መስራት የሚችል የወጥ ቤት ቀጥሬያለሁ ።”

ለግብዣው የተጠሩት ሰዎች ታላላቅና ዝነኛ የተባሉት ነበሩ ። የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች ፡ የፖለቲካ ሰዎችና ባለኢንዱስትሪዎች ተገኝተዋል ። በእርግጥ ምግቡ በጣም ቆንጆ ነበር ። የዓሣ ሾርባ ፡ ከተፈልቃቂ ዓሣ የተሠራ ሳምቡሳ ፡ የአሳማ ሥጋ ፡ የጌኪንግ ዳኪዬ ፡ የጮድን ጥብስ ፡ ከአንቁላልና ሥጋ የተዘጋጀ ጥብስና ሌሎችም በርካታ ምግቦችን ወጥ ቤቱ አቅርቧል ።

ሜሊና ከደጋሹ ጎን ስትቀመጥ ባልዋ ደግሞ ከደጋሿ ጎን ነበር የተቀመጠው ። ከዴሚሪስ በስተቀኝ መልከ ቀና የሆነች የፊልም ተዋናይ ተቀምጣለች ። ዴሚሪስ ሰዎች አዩኝ ብሎ ሳይጨነቅ ተዋናይዋን ማሽኮርመም ጀመረ ። ከተዋናይዋ ጋር ይለዋወጣቸው ከነበሩት ቃላት ጥቂቱ ሜሊና ጆሮ ገቡ ።

“የፊልም ሥራሽን እንደጨረስሽ በጀልባዬ እንድንንሸራሸር ጋብ ዠሻለሁ ። በጣም ደስ የሚያሰኝ የእረፍት ጊዜ ይኖርሻል ። እስከዳልማቲ ያን የባሕር ጠረፍ ድረስ አብረን እንንሸራሸራለን ። ….”

ሜሊና ለነገሩ ጆሮዋን ላለመስጠት ሞክራ ነበር ፡ ግን አልቻለችም። ዴሚሪስም ድምጹን ለመቀነስ ጥረት አላሳየም ። “ወደ ጥሳራ ሄደሽ ታውቂያለሽ ወይ? ከሌሎች ሥፍራዎች የተለየች ደስ የምታሰኝ ደሴት ናት። በጣም ትወጂያታለሽ ።” ሜሊና ተጠቅልላ ጠረጴዛው ሥር ብትገባ ደስ ባላት ነበር ። ሆኖም ከዚህ የሚብሰውም ሊመጣ አይደል!

የጮድን አጥንቱን ግጠው እንደጨረሱ በጮድንዳ የብር ሳህን ፍራፍሬ መዘር ጀመረ ።

አስተናባሪዎቹ ፍራፍሬውን ለወጣቷ የፊልም ተዋናይ እንዳቀረቡ ዴሚሪስ “ይህ ለአንቺ የሚያስፈልግ አይደለም” ሲል ፈገግ እያለ እጇን ወደ ላይ አነሳ ። ጣቶቿን በተራ እየላሰ ወጡን ሲያደርቅላት ተጋባዦቹ ሁሉ በመገረም ተመለከቱት ።

ሜሊና ብድግ ብላ ወደ ጋባዦ ባንከኛ ዞር አለች ። “ይቅርታ አድርግልኝ እራስ …. እራስ ምታት አሞኛል ።”

ከግብዣ አዳራሹ ውልቅ ስትል ተጋባዦች አዩዋት ። ዴሚሪስ ያን ዕለትም ሆነ በሚቀጥለው ቀን ፣ ማታ ወደቤት አልሄደም ።

ስቲሮስ ያን ዕለት ምሽት የተፈጸመውን ድርጊት ሲሰማ ሰውነቱ ተለዋወጠ ። “እባክሽ ፍቀጅልኝ” አላት ወንድሟ ። “ይህን የውሻ ልጅ ልግደለው ።”

“ወዶ አይደለም” አለች ሜሊና ለባሏ ስትከላከል ። “ተፈጥሮው ነው ።”

“ተፈጥሮው ነው ትያለሽ? ከብትነት ነው እንጂ ፣ እሱን ማስወገድ አለብሽ ። ለምን አትፈቺውም?”

ይሄ ሜሊና ዴሚሪስ ለረዥም ጊዜያት በብቸኝነት በምታሳልፋቸው ምሽቶች ደጋግማ ለእራሷ የምታቀርበው ጥያቄ ነው ። ምላሿ ዞሮ ዞሮ አንድ ዓይነት ይሆንባታል ። “እወደዋለሁ ።”

ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ይቅርታ ጠይቃ ወደ ክፍሏ የገባችው ሠራተኛ ካተሪንን ከእንቅልፏ ቀሰቀሰቻት ።

“እንደምን አደርሽ ፣ ሚስ ...”

ካተሪን ዓይኗን ገልጣ ግራ በመጋባት ዙሪያዋን ቃኘች ። በገዳሙ ውስጥ ካለች ጠባብ ክፍል ውስጥ ሳይሆን በጣም በተዋበ የመኝታ ክፍል ውስጥ ነው ያለችው ።

ትውስታዋ እየተፍለቀለቀ መጣ ። ‘ወደ አቴንስ ያደረገችው ጉዞ ... አንቺ ካተሪን ዶግላስ ነሽ... የተገደሉት በመንግሥት ነው ...’

“ሚስ ...”

“አቤት?”

“ሚስተር ዴሚሪስ ከበረንዳው ላይ አብረሻቸው ቁርስ እንድታደርጊ ጋብዘውሻል ።”

ካተሪን በእንቅልፍ ልቧ ሠራተኛዋን ትኩር ብላ ተመለከተች ። አንጐሏ በመተረማመስ እስከሌሊቱ አሥር ሰዓት ድረስ እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይኗ አልዞረም ነበር ።

“አመሰግናለሁ ፣ እንደምመጣ ለሚስተር ዴሚሪስ ንገሪልኝ ።”

ከሃያ ደቂቃ በኋላ የእልፍኝ አሽከሩ ለባሕሩ ትይዩ ወደሆነው ሰፊ በረንዳ መርቶ ወሰዳት ። በረንዳው የታጠረበት የድንጋይ ግንብ አጭር በመሆኑ ከሃያ ጫማ ከማይበልጥ ርቀት ላይ ያለውን አትክልት አሻግሮ መመልከት ይቻላል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተቀምጦ ጠበቃት ። ካተሪን

ወደሱ ስትራመድ አተኩሮ አያት ። ልብ የሚነካ የዋህነት ከፊቷ ይነበባል። ይህ የዋህነቷን ሊወስድ ፣ የግሉ ሊያደርግ ነው ። ራቁቷን አልጋ ላይ ስትታይ ምን ልትመስል እንደምትችል እያሰበ ኖኤሌንና ላሪን ዳግመኛ ለመቅጣት እንዴት ሊረዳው እንደሚችል ታየው ። ዴሚሪስ ከተቀመጠበት ተነሳ ።

“እንደምን አደርሽ? ሳይነጋ ከእንቅልፍሽ ስለቀሰቀስኩሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደቢሮ መሄድ ስላለብኝ ካንቺ ጋር ትንሽ ለማውራት ጊዜ እንዲኖረን ብዬ ነው በሌሊት ያስጠራሁሽ ።”

“ደስ ይለኛል” አለች ካተሪን ። ከፊትለፊቱ ካለው ወንበር ላይ ከእብነበረድ ከተሠራው ጠረጴዛ አጠገብ ከባሕሩ ትይዩ የማለዳዋ ዝምበር ብቅ ብላ ብዙ ሺህ ጨረሮቿን ከባህሩ ላይ ታዘንባለች ።

“ምን ዓይነት ቁርስ ትፈልጊያለሽ?”

ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። “አልራበኝም ።”

“ቡናስ?”

“እሺ አመሰግናለሁ ።”

የእልፍኝ አሽከሩ በስኒ ቡና ቀዳላት ።

“መልካም ፣ ካተሪን” ሲል ዴሚሪስ ንግግሩን ጀመረ ። “ስለትና ነቱ ጭውውታችን አስበሽበታል?”

ካተሪን ሌሊቱን በሙሉ ስለዚሁ ጉዳይ እንጂ ስለሌላ ነገር አላሰበችም ። በአቴንስ ውስጥ የቀራት ምንም ነገር የለም ። ሌላ መሄጃ ሥፍራም የላትም ። ‘ወደገዳሙ እንደሆነ ተመልሼ አልሄድ!’ አለች በልቧ። ለንደን በሚገኘው ቢሮው ውስጥ እንድትሠራ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያቀረበው ጥያቄ ቸል የሚባልም አይደለም ። ‘እንዲያውም የሚያጓጓ ነው’ አለች በልቧ ። ‘የአዲስ ሕይወት መጀመሪያ ሊሆን ይችላል ።’

“አዎ” አለች ካተሪን ። “አስቤበታለሁ ።”

“እና ?”

“ል — ልሞክረው እፈልጋለሁ ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በውስጡ የተሰማውን የእፎይታ መንፈስ ለማመቅ ሞከረ ። “ጐሽ በጣም ደስ አለኝ ። ለመሆኑ ከዚህ በፊት ለንደን ሄደሽ ነበር?”

“አይ ፣ ያንን ሥፍራ — የማውቀው አይመስለኝም ።” ‘ለምንድ

ነው ግን የማላውቀው?' አእምሮዋ ውስጥ ከሚጉላሉት ነገሮች አኳያ ፍርሃት አድሮባታል ። 'ስንትስ ተጨማሪ አዳዲስ ነገሮች ይከሰቱልኝ ይሆን?'

"በዓለም ውስጥ በሥልጣኔ በጣም ከገፉ ከተሞች መካከል የቀረች ልን አንዷ ለንደን ናት ። "እርግጠኛ ነኝ በጣም ትወጂያታለሽ ።" አለ ዴሚሪስ ።

ካተሪን እንደማመንታት አለች ። "ሚስተር ዴሚሪስ ለእኔ ብለው ይህን ያህል የሚቸገሩት ለምንድነው?"

"ኃላፊነት ስለሚሰማኝ ነው" ለንግግሩ ፋታ ሰጠና "ባለቤትሽን ከኖኤሌ ፓጂ ጋር ያስተዋወቅኩ እኔ ነበርኩ ።" አላት ።

"አሃ" አለች ካተሪን በለሆሳስ ። 'ኖኤሌ ፓጂ ።' ይህን ስም ስትሰማ አንድ ነገር ሰውነቷን ወረራት ። 'አንደኛው ለሌላኛው ሲል ነው ሁለቱም የሞቱት ። ላሪ በጣም ሳያፈቅራት አልቀረም ።'

ካተሪን ሌሊቱን ሙሉ አእምሮዋን ያስጨንቅ ስለነበረው ጉዳይ ልትጠይቀው ፈለገች ። "እንዴት .... እንዴት ነበር አገዳደላቸው?"

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ። "በተኳሽ ቡድን ጥይት ተደብድበው ።"

"ውይ" አለች ። የጥይቷ እርሳስ የላሪን ሥጋ በጣጥሳ ወደ ውስጥ ስትሰምጥ ታየቻት ። በአንድ ወቅት በጣም ትወደው የነበረውን ሰው ገላ ጥይቷ ስትበጣጥሰው ማስታወሱ ዘገነናት ። ጥያቄውን ማቅረቢ መልሶ ፀፀታት ።

"እስቲ ትንሽ ምክር ልስጥሽ ። ስላለፈው አታስቢ ትርፉ ጉዳት ብቻ ነው ። ያለፈውን ሁሉ ከኋላሽ መወርወር ይገባሻል ።"

ካተሪን ባነሰ ድምፅ "እውነትዎን ነው ። እሞክራለሁ ።" አለች ።

"መልካም ፣ ዛሬ ጠዋት ወደ ለንደን የሚበር አውሮፕላን አለ ። በቶሎ ልትዘጋጂ ትችያለሽ?" ሲል ጠየቃት ።

ካተሪን ከላሪ ጋር ለመጓዝ ዝግጅት ስታደርግ ፣ ዕቃ ስትጠቀልል ይሰፍንባት የነበረውን ጉጉት አስታወሰች ።

አሁን ግን አብሯት የሚጓዝ ሰው የለም ፣ ዕሚጠቀለልም ዕቃ በጣም ጥቂት ነው ፣ በአጠቃላይ ሰፊ ዝግጅት የሚጠይቅ የጐላ ነገር የለም ። "አዎ በቶሎ መዘጋጀት እችላለሁ" አለች ።

"እጅግ በጣም ጥሩ ። በነገራችን ላይ" አለ ዴሚሪስ እግረ

መንገዱን። "አሁን የማስታወስ ችሎታሽ ተመልሷል ። ምናልባት ልትገናኚው የምታስቢውና ጤነኛ መሆንሽንም ልትገልጪለት የምትፈልጊው ወዳጅ ካለ?"

ዊልያም ፍሬዘር የሚል ስም በድንገት ብልጭ አለባት ። ካለፈው ሕይወቷ የሚታወሳትና አሁን በዓለም ላይ የሚገኝ እርሱ ብቻ ነው ። ሆኖም በአሁኑ ደረጃ ልትገናኘው ዝግጁ አይደለችም ። 'ስረጋጋ ፣ እንደገና መሥራት ስጀምር ነው የምገናኘው' ስትል አሰበች ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መልሷን እስኪሰማ በጥሞና ተመለከታት ።

"የለም" አለች ካተሪን "ማንም የለም ።"

እንዲህ በማለቷ የዊልያም ፍሬዘርን ሕይወት እንዳተረፈች ግን አታውቅም ።

"ፓስፖርት እንዲዘጋጅልሽ አደርጋለሁ" አለና አንድ ፖስታ ሰጣት ። "ይህ የቅድሚያ ደመወዝሽ ነው ። ስለመኖሪያሽም መጨነቅ አይገባም ። ኩባንያው ለንደን ውስጥ ቤቶች ስላሉት እዚያ ውስጥ ትቀመጪያለሽ ።" አስገረማት ። "ከመጠን በላይ ደግ ነዎት ።"

እጁን ጨበጥ አድርጐ ያዘ ። "ወደፊት ትረጂያለሽ እኔ..." ለማለት የፈለገውን ቀየረ ።"ባሃማስ ውስጥ 'በጥንቃቄ ያዛት' የሚል መጣበት ። 'በዝግታ፡ አስደንግጠህ ልታስበረግጋት አይገባም' ያቋረጠውን ለመጨረስ ። "... ጥሩ ወዳጅሽ ልሆን እንደምችል ።"

"በጣም ጥሩ ወዳጅ ነዎት ።"

ዴሚሪስም ፈገግ አለ ። 'ቆይ!'

ከሁለት ሰዓት በኋላ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሮልስ ሮይስ መኪናው ውስጥ በስተኋላ አስቀመጣትና ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ወሰዳት ።

"ለንደንን ተደሰቺበት" አላት ። "በየጊዜው እደውልልሻለሁ ።"

ከመኪናው ካወረዳት ፣ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ዴሚሪስ ወደለንደን ስልክ ደወለ ።

"በመንገድ ላይ ነች ።"

ምዕራፍ አምስት

አውሮፕላኑ ከሄሌኒኮን አውሮፕላን ጣቢያ የሚነሳው ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ነው ። በሀዋከር ስዲለይ አይሮፕላን ውስጥ ብቸኛ ተሳፋሪ መሆኗ ካተሪንን በጣም አስገርሟታል ። በመካከለኛው ዕድሜ ላይ የሚገኘው መልከ መልካሙ ግሪካዊ የአውሮፕላኑ ዋና አብራሪ ፓንቴሊስ ካተሪን በምቾት መቀመጧንና የወንበሩን መታጠቂያ ማሰሯን አረጋገጠ።

"ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አውሮፕላኑ ከመሬት ይለቃል" አላት ።

"አመሰግናለሁ ።"

ዋና አብራሪው ፡ ረዳቱ ወዳለበት ክፍል ሲገባ እንዳየች ልቧ በድንገት በ;ንይል መምታት ጀመረ ። ይህን አውሮፕላን ላሪ ያበረው ነበር። በዚህ በተቀመጥኩበት መቀመጫ ለይ ኖኤሌ ፓጂ ተቀምጣ ይሆን? ከመቅጽበት የማጥወልወል ስሜት ተሰማት ። ብሽ አለባት ። ዓይኗን ከድና በ;ንይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። 'አለቀ ደቀቀ' አለች በአሳቢ። 'ዴሚሪስ የተናገረው ልክ ነው ፡ ያ ያለፈ ነገር ነው እና የሚለውጠው ምንም ነገር የለም ።'

የሞተሩን ጩኸት እንደሰማች ዓይኗን ገለጠች ። አውሮፕላኑ አኩብኩቦ እንደተንሳፈፈ ወደሰሜናዊ ምዕራብ በማምራት ጉዞውን ወደ ለንደን ቀጠለ ። 'ላሪ በዚህ አውሮፕላን የበረረው ስንት ጊዜ ይሆን ?' "ላሪ" የሚለው ስም ባሳደረባት ስሜት ተሸበረች ። በትውስታውም ተብረከረከች ። ሊረሳ የማይቻል ግሩም የሆነ መከረኛ ትዝታ ...

—

ጊዜው የ1940 ሰመር ወቅት ነበር ። አሜሪካ ወደጦርነቱ ውስጥ ከመግባቷ በፊት መሆኑ ነው ። ካተሪን ከኖርዝ ዌስተርን ዩኒቨርስቲ እንደተመረቀች ወዲያው ሥራ ለመጀመር ከቺካጐ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ሄደች ።

የመኝታ ክፍል ደባሏ "ሥራ ከፈለግሽ ክፍት የሥራ ቦታ እንዳለ ሰምቻለሁ ። ትላንት ማታ ፓርቲ ላይ ያገኘኋት አንዲት ልጅ ሥራዋን ለቃ ወደ ቴክሳስ እንደምትመለስ ገልጻልኛለች ። ቤል ፍሬዘር ነው የቀጠራት። በመንግሥት ጽ/ቤት የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሃላፊ ነው ። ወደዚያ ሄደሽ ሌሎቹን ተወዳዳሪዎችሽን በማሸነፍ ሥራውን ልታገኚ ትችያለሽ" አለቻት ።

ካተሪን ተጣድፋ ወደተባለው ሥፍራ ተጓዘች ። ፍሬዘር ከሚገኝበት ቢሮ የመስተንግዶ ክፍል ብዙ ተወዳዳሪዎች ተኮልኩለው አየች ። 'ሰድሱን የማገኝ አይመስለኝም' ስትል አሰበች ። የውስጠኛው ቢሮ በር እንደተከፈተ ዊልያም ፍሬዘር ወጣ ። ረዘም ያለ ፡ ወርቅማ ፀጉር ያለው ፡ የዓይኑ ብሌን ወደ ብሩህ ሰማያዊነት የሚያደላ ፡ የፈረጠመ መንጋጋ ያለው ዓይነ—ግቡ ሰው ነው ።

ለአስተናጋጅዋ "የላይፍ መጽሔት አንድ ቅጅ እፈልጋለሁ ። ከሦስት ወይም ከአራት ሳምንት በፊት የወጣውን እትም ። በሽፋኑ ላይ የስታሊን ፎቶግራፍ አለበት ።" አላት ።

"እንዲመጣ አዛለሁ ሚስተር ፍሬዘር" ብላ መለሰች አስተናጋጅዋ።

"ሳሊ ፡ ሴናተር በራሁ በስልክ መሥመር ላይ ስላሉ ከዚያ እትም ላይ እንዴን አንቀጽ ላንብላቸው እፈልጋለሁ ። መጽሔቱን በሁለት ደቂቃ ውስጥ ልታገኚልኝ ይገባል ።" ተመልሶ ወደቢሮው ገብቶ በሩን ዘጋ ።

አመልካቾቹ እርስ በእርስ እየተያዩ ትከሻቸውን ይነቀንቃሉ ።

ካተሪን እዚያው ቆማ አሰበች ። ዞራም ከቢሮው ወጣች ። ከተወዳዳሪ ሴቶቹ መካከል አንዷ "ጐሽ ፡ አንድ ተፎካካሪ ተቀነሰ" ስትል ካተሪን ሰማቻት ።

ከሦስት ደቂቃዎች በኋላ ካተሪን በሽፋኑ ላይ የስታሊን ፎቶግራፍ ያለበትን የላይፍ መጽሔት አንድ ኮፒ ይዛ ተመለሰችና ለአስተናጋጅዋ ሰጠች ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወደ ዊልያም ፍሬዘር ቢሮ ተጠርታ ገብታ ቁጭ አለች ።

"መጽሔቱን አንዳመጣሽው ሳሊ ነገረችኝ ።"

"አዎ ጌታዬ"

“ከወጣ ሦስት ሳምንት ያለፈውን መጽሔት በቦርሳሽ ውስጥ ይዘሽው እንደማትዞሪ መቼም እርግጠኛ ነኝ ።”

“በቦርሳዬ ውስጥ አልነበረም ጌታዬ”

“ታዲያ እንዴት በፍጥነት ልታገኚው ቻልሽ ?”

“ወጥቼ ወደፀጉር አስተካካይ ቤት ሄድኩ ። ፀጉር አስተካካዮችና የጥርስ ሐኪሞች ዘንድ ብዙ ጊዜ የቆየ መጽሔት ይገኛል ።”

“ለሁሉም ነገር እንዲሁ ፈጣን የማሰብ ችሎታ አለሽ ?”

“የለኝም ጌታዬ”

“እስቲ እናየዋለን” አላት ዊልያም ፍሬዘር ። ተቀጠረች ።

ካተሪን ከፍሬዘር ጋር መሥራቱ በጣም ደስ አሰኛት ። ሰውዬው ወንደላጤ ሲሆን ከሰዎች ጋር ጥሩ የመግባባት ችሎታ ያለውና ሀብታም ነው ። በዚህም የተነሳ በዋሽንግተን ውስጥ ከብዙ ሰዎች ጋር ይተዋወቃል። የታይም መጽሔትም “የዓመቱ ብቃት ያለው ወንደላጤ” ብሎ ታል ።

ካተሪን ከዊልያም ፍሬዘር ጋር መሥራት በጀመረች በስድስተኛው ወር ሁለቱም በፍቅር አበዱ ።

ካተሪን በመኝታ ቤቱ ውስጥ ፣ “አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ ፤ ድንግል ነኝ” አለችው ። ፍሬዘር በመገረም ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። “የማይመስል ነገር ! ዋሽንግተን ከተማ ውስጥ ያለች አንዲቷ ድንግል እንዴት ልታጋጥመኝ ትችላለች ?”

አንድ ቀን ዊልያም ፍሬዘር ካተሪንን እንዲህ አላት፡— “ለአየር ኃይል ተቀጣሪዎች መመልመያ የሚሆን ፊልም ሆሊውድ ውስጥ በኤም ጂ ኤም እስቱዲዮ ስለሚቀረጽ መሥሪያ ቤታችን ሥራውን እንዲከታተል ተጠይቀናል ። እኔ ለንደን ስለምሄድ አንቺ የዚህን ሃላፊነት እንድትወስጂ እፈልጋለሁ ።”

“እኔ እንዴት ብዬ ፣ እኔኮ በፎቶግራፍ ማንሻ ውስጥ ፊልም ማጉረስ እንኳን አልችልም ። ስለማሰልጠኛ ፊልም አሠራር ምን የማውቀው ነገር አለ ?”

ፍሬዘር ኮስተር አለ ። “ማንኛውም ሰው የሚያውቀውን ያህል

ታውቂያለሽ ። የሚያሳስብሽ ነገር የለም ። የፊልም አዘጋጅ አላቸው ። አላን ቤንጃሚን ይባላል ። ሠራዊቱ ከሲቪሉ ወገን ተዋንያን ለመምረጥ ሃሣብ አለው ።”

“ለምን ?”

“ወታደሮች የወታደርን ገፀ—ባሕርይ ወክለው ቢጫወቱ ትወናው ተጓማኒነት አይኖረውም ብለው በመገመታቸው ይመስለኛል ።”

“ይሄ ወታደራዊ አመለካከት ይመስላል”

ካተሪን የማሰልጠኛውን የፊልም ቀረፃ ለመከታተል ወደ ሆሊውድ በረረች ።

የድምፅ ማቀናበሪያው መድረክ የወታደር መለዮዎችን አንጋደው በለበሱ ሰዎች ተሞልቷል ።

“ይቅርታ” አለችው ካተሪን አጠገቧ ያልፍ የነበረውን ሰው ። “ሚስተር አላን ቤንጃሚን እዚህ ይገኝ ይሆን ?”

“ትንሹ ያሥር አለቃ ?” በጣቱ አመለከተ ። “ያው እዚያ ።”

ካተሪን ዞር እንዳለች ክንዱ ላይ የአሥር አለቃ ምልክት የለጠፈ ኩስማና ሰው አየች ። የአሥር አለቃው የጀኔራልን ኮከብ በደረደረው ሰው ላይ ይጮህበታል ።

“የማይረባ የተዋናይ መልማይ ሁሉ ያለህን እርሳው ። እኔ ስለጀኔራሎች አብጠርጥሬ ነው የማውቀው ። ማንም እንዲህ አድርግ እንዳለኝ አልፈልግም ።” በቅፌታ እጁን በማወራጨት “ሁሉም አለቃ ልሁን ባይ ነው ። ተራ ሆኖ ለመሥራት የሚፈልግ የለም” አላት ።

“ይቅርታ” አለች ካተሪን ። “ካተሪን አሌክሳንደር እባላለሁ ።”

“ተመስገን አምላኬ” አላት አጭሩ ሰውዬ ። “በይ ሥራውን ተረከቢኝ ። ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኝ ነበር ! ዬርቦርን ሳለሁ በዓመት ሦስት ሺህ አምስት መቶ ዶላር እየተከፈለኝ የጠረጴዛና የመቀመጫ ንግድ የማስታወቂያ መጽሔቶች አዘጋጅ ሆኜ እሰራ ነበር ። ከዚያ በወታደራዊ መገናኛ ክፍል ባልደረባነት መልምለውኝ ለማሠልጠኛ ፊልም የሚሆን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ላኩኝ ። እኔ ስለፊልም አቅርቦት ሆነ ዝግጅት ምን የማውቀው ነገር አለ ? ይሄ የአንቺ ተግባር ነው ።” ካተሪንን ካለችበት ትቷት ተጣድፎ ወደበሩ ገሠገሠ ።

ከወደፀጉሩ የሸበተ ሹራብ የለበሰ ቀጭን ሰው ወደርሷ ቀርቦ የመገረም ፈገግታ አሳያት ። “እንድረዳሽ የምትፈልጊው ነገር አለ ?”

“የምፈልገው ተአምር እንዲወርድልኝ ነው” አለች ካተሪን ። “የፊልሙን ሥራ ሰበላይነት እንድመራ ተልኬአለሁ ። ግን እንዴት እንደሚሠራ የማውቀው ነገር የለም ።”

ፈገግ አለ ። “እንኳን ወደሆሊውድ በደህና መጣሽ ። ቶም አብሪን እባላለሁ ። ረዳት የፊልሙ አዘጋጅ ነኝ ።”

“ይህንን ፊልም ለማዘጋጀት የምትችል ይመስልሃል ?”

ከንፈሩ ሲንቀሳቀስ እየች ። “እሞክራለሁ ። ከዊሊ ዋይለር ጋር ስድስት ፊልሞች ሠርቻለሁ ። የሚፈራውን ያህል አሰቸጋሪ አይደለም ። ትንሽ ቅንብር ነው የሚያስፈልገው ፤ ጽሑፉና መቸቱ ተጠናቀዋል ።”

ካተሪን ወደ ድምፅ ቅንብሩ መድረክ ተመለከተች ። “ከእነኚህ የወታደር አልባሳት ውስጥ አንዳንዶቹ የተስተካከሉ እይደሉም ። የተሻለ ነገር ለማድረግ እንሞክር እስቲ !”

አብሪን ጭንቅላቱን በማወዛወዝ ተስማማ ። “ትክክል ነሽ” አላት ።

ካተሪንና አብሪን ወደተዋንያኑ ሄዱ ።

በሰፊ መድረክ ላይ የሚሰማው ጫጫታ ጆሮን ያደነቁራል ።

“ጫጫታውን እናቁም ጐበዝ” አለ አብሪን ትዕዛዝ በተመላበት አነጋገር ። “የምታዩዋት ሚስ አሌክሳንደር ትባላለች ። እዚህ የሚካሄደውን ሥራ በበላይነት የምትመራና የምትቆጣጠር እርሷ ናት ።”

ካተሪን “እስቲ በደንብ እንድናያችሁ አንዴ ተሠለፉ” አለች ።

አብሪን በወጣገባ መሥመር አሰለፋቸው ። ካተሪን ሳቅና ሹክሹክታ እንደሰማች ተናዳ ዞር አለች ። አንድ ዩኒፎርም የለበሰ ተዋናይ ለትዕዛዙ ደንታ ሳይኖረው ከጥግ ቆሞ ልጃገረዶችን እያሳቀ ይበቃል ። የሰውዬው ሁኔታ ካተሪንን አበሳጫት ።

“ይቅርታ ፣ አንዴ ወዲህ ትመጣልን ?”

ዞር ብሎ በግዴለሽነት “እኔን ነው ?”

“አዎ ፣ ሥራውን ቶሎ ለመጀመር እንፈልጋለን ።”

ሰውዬው ከመጠን በላይ መልከ መልካም ነው ። ረዥምና ቁመናው ያማረ ሲሆን የሚያማምሩ ዓይኖቹ ብሌን ጠቆር ያለ ሆኖ ፣ ፀጉሩ ጥቁር ሰማያዊ ነው ። የደንብ ልብሱ ተስማምቶታል ። በትከሻው ላይ

የሻምበልነት ምልክት ይታያል ። ደረቱ ላይ የተንጠለጠሉት ሜዳሊያዎች ያብረቀርቃሉ ። ካተሪን አተኩራ አየቻው ። “እነኚህ ሜዳሊያዎች ...”

“ይህን ያህል የሚማርኩ ናቸው ?” የፌዝ አነጋገር ነበር ።

“ብታወልቃቸው ይሻላል”

“ለምን ? ለፊልሙ የበለጠ ድምቀት ይሰጠዋል ብዬ ስላሰብኩ ነው ያደረግኩት ።”

“አንድ የዘነጋኸው ነገር አለ ። አሜሪካ እስካሁን ድረስ በጦርነት ረመጥ ውስጥ አለመግባቷን ረስተሃል ። ታዲያ ይህን ሜዳሊያ የተሸለምከው በመዝናኛ በዓልዋ ላይ ነው ?”

“እዚህ ላይ ልክ ነሽ ። ይህን ልብ አላልኩም ነበር ። እሺ ከላዩ ትንሽ አነሳለታለሁ ።”

“ሁሉንም አውልቃቸው” አለች ካተሪን በቁጣ ።

የጠዋቱ የፊልም ቀረፃ ሥራ ተጠናቆ ካተሪን በስቱዲዮው አካባቢ ባለው ካፌቴሪያ ውስጥ ቁጭ ብላ ምሳዋን እየተመገበ ወደ እርሷ ቀርቦ “ዛሬ ጠዋት ሥራዬ እንዴት እንደነበረ ልጠይቅሽ ብዬ ነው የመጣሁት ። አተዋወኔ ተዓማኒነት ነበረው ?” አላት ።

ሥነ ሥርዓቱ አስፈራት ። “አንተን ደስ የሚልህ ያንን የደንብ ልብስ ለብሰህ ልጃገረዶች አጠገብ መንጐራደድ ብቻ መሰለኝ ። ለመሆኑ ወታደር ለመሆን አስበህ ታውቃለህ ? ።”

ደንገጥ አለ ። “በናይት ለመሞት ? ሥራ የሞኞች ነው ።”

ካተሪን በንዴት ገነፈለች ። “ቅሌታም ትመስለኛለህ !”

“ለምን ?”

“ለምን እንደሆነ አላውቅም ለምን እንደሆነ ልገልፅልህ አልችልም !”

“ለምን አትሞከሪም ? ዛሬ እራት ጋብዘሽኝ ለምን አትነግሪኝም ። እቤትሽ ልምጣ ። ለመሆኑ ምግብ የማብሰል ሙያ አለሽ ?”

“ከእንግዲህ ወደሥራ ቦታ ተመልሰህ ለመምጣት አታስብ” አለችው ካተሪን ። “ዛሬ ጠዋት ለሠራኸው ሥራ ክፍያ ሚስተር አብሪን ቼክ እንዲልክልህ እንግረዋለሁ ። ለመሆኑ ስምህ ማነው ?”

“ዶግላስ ፡ ላሪ ዶግላስ ።”

ወጣቱ ተዋናይ ያሳያት የብልግና ጠባይ ካተሪንን ቢያሳስባትም ቅሬታዋን ለመርሳት ወሰነች ። ሆኖም ባላወቀችው ምክንያት ጉብሉን ከአእምሮዋ ለማውጣት ተሳናት ።

ካተሪን ወደ ዋሽንግተን እንደተመለሰች ዊልያም ፍሬዘር "እንዴት ናፍቄሽ ነበር መሰለሽ? ስለ አንቺ ብዙ ሳስብ ነበር ። ትወጂኛለሽ?" አላት ።

"በጣም አድርጌ ነዋ ቢል !"

"እኔም እወድሻለሁ ። ዛሬ ማታ አብረን ወጥተን ለምን አንደሰትም ?"

ካተሪን ያን ዕለት ምሽት ቢል ለጋብቻ እንደሚጠይቃት አስቀድማ አውቃለች ።

ልዩ ወደሆነው የጀፈርሰን ክለብ ሄዱ ። እራት በመብላት ላይ ሳሉ ላሪ ዶግላስ የአየር ኃይል የደንብ ልብሱን ለብሶ ፣ ሜዳሊያዎቹን ደርድሮ ብቅ አለ ። ወደነሱ ሲያመራ ካተሪን ዓይኗን ማመን ተሳናት ። ለእሷ ሰላምታ ሳይሰጥ ፍሬዘርን ነበር የጨበጠው ።

ቢል ፍሬዘር ከተቀመጠበት ተነሳና "ካቲ ፣ ተዋወቁ ። ሻምበል ሎውሬንስ ዶግላስ ይባላል ። ላሪ ፣ እሷም ሚስ አሌክሳንደር ካተሪን ትባላለች ። ላሪ የሮያል አየር ኃይል አብራሪ ነው ። የአሜሪካ የጦር አውሮፕላን ቡድን መሪም ነበር ። ልጆቻችንን ለጦርነቱ ለማዘጋጀት ዋሽንግተን ውስጥ የጦር ሠፈር እንዲያቋቁም ኃላፊነቱን የወሰደ እሱ ነው ።"

ያረጀ ፊልም ወደኋላ እንደሚውጠነጠን ሁሉ ካተሪን በሃሣቧ ወደኋላ ተመልሳ ሜዳሊያዎች እንዲያወልቅ ስታዘዙና እርሱም በፈገግታ ሲታዘዛት ታወሳት ። ያሳየችው ንቀትና "ፈሪ" ብላ በተዘዋዋሪ የሰደበችው አሳፈራት ። ተጠቅልላ ጠረጴዛ ሥር ብትገባ አትጠላም ነበር ።

በሚቀጥለው ቀን ላሪ ዶግላስ ካተሪን ቢሮ ስልክ ደወለ ። ልታነጋግረው ግን ፈቃደኛ አልሆነችም ። ሥራዋን ጨርሳ ስትወጣ እውጭ ቆሞ ጠበቃት ። ሜዳሊያዎቹን አውልቆ የምክትል መቶ አለቃ

ልብስ ለብሷል ።

ፈገግ እያለ ተጠጋት ። "አሁንሳ ፡ እንዲህ አይሻልም ?" ብሎ ጠየቃት ።

ካተሪን ትኩር ብላ አየችው ። "አግባ ... አግባብ ያልሆነውን የደንብ ልብስ መልበሱ ከሕግ ውጪ አያሰኝም ?"

"እኔ እንጃ ። ይሄ ሁሉ በጎላፊነት የሚመለከተው አንቺን መስሎኝ ።"

ትኩር ብላ እንዳየችው አንድ ልብ የሚሰውር ነገር እንዳለው ተሰማት ። ሊቋቋሙት የማይችሉት ማግኔታዊ ስበት ከውስጡ ይፈልቃል ።

"ከእኔ የምትፈልገው ምንድር ነው ?"

"ሁሉንም ። የምፈልገው አንቺን ነው ።"

ወደ አፓርትመንቱ ሄዱና ፍቅር ሠሩ ። ያልገመተችውን ልዩ እርካታና ደስታ ነበር ካተሪን ያገኘችው ። ተያይዘ በፍቅር ልዩ ዓለም ውስጥ መንጐድ ። ምልዐተ ዓለምን የሚነቀንቅ ምትሐት ውስጥ መስጠም ፣ ማለቂያ የሌለው ጥልቅ ፍንደቃን የሚያስከትል ፍንዳታ ፤ ሰውነትን ከሚያነካክትና ከሚያደቅ ረሾም ጉዞ ደርሶ መልስ ። ከመጨረሻ ደረስኩ ሲባል እንደገና ወደ መጀመሪያው መመለስ ። እንዳይሄድ ባት፡ ስሜቱ እንዳይደክምባት ከተኛበት ተጠመጠመችበት ።

ከአምስት ሰዓት በኋላ በሚሪላንድ ጋብቻቸውን ፈጸሙ ።

አዲሱን ሕይወቷን ለመጀመር በአይሮፕላን ወደለንደን ስትጓዝ ካተሪን እንዲህ እያለች ታስብ ነበር፡ በጣም ደስተኛ እንኳን ነበር ። ታዲያ ምን አበላሽው? የፍቅር ፊልሞችና የፍቅር ዘፈኖች ፡ ስለፍቅር የሚያወሳው ነገር ፍፃሜው ያማረ ፡ ፍቅርና የጦር መሣሪያ የታጠቀ ወታደር እንደማይሞት አስመስለው በማታለል ኡስምነውናል ። የጀምስን የሚያስደስት ሕይወት እንዳየን ስቴዎርት እና ዶና ሪድ በእውነትም ደስ የሚል ኑሮ የሚኖሩ ናቸው ብለን ተቀብለናል ። "አንድ ማታ እንዲህ ሆነ" የሚለው ፊልም እንዳለቀም ከለርክ ጋብልና ካልውዳት ከልበርት ለዘለዓለም በፍቅር እንደሚቆዩ ገመትን ። "የሕይወታቸን ቆንጆው ዘመናት" በሚለው ፊልም ውስጥ ፍሬድሪክ ማርች ከሚርና ሎይ ጋር ሲታረቅ እንባችንን አፍሰናል ። በሬቤካ ፊልምም ውስጥ ጀአን ሮንቴን በሎሬንስ ኦሊቨር እቅፍ ውስጥ ሳለች ደስታ ለማግኘት አልተጠራጠርንም ነበር ። ግን ይሄ ሁሉ ውሸት ነው ። ሁሉም ውሸት ። ዘፈኖቹስ ቢሆኑ እወድሻለሁ ለዘለዓለም ። እስከ ዘለዓለም መውደድን በምን ይለኩታል ? መስፈርት አብጅተውለታል ? የውቅያኖስ ጥልቀቱ ምን ያህል ነው? እስቲ ኽርሺንግ በርሊን ምን ማለቱ ይሆን ? አንድ ጫማ ርቀት ? ወይንስ ሁለት ጫማ ርቀት እንዲባል ፈልጐ ነው ? ... መሄዱ ነው ። ሰማንያዬ እንዲቀደድ እፈልጋለሁ ። ምን ማለትሽ ነው ? ይልቅስ ቱዝሽን ተራራ ላይ ለሽርሽር እንውጣ ። እንተ ፡ ያ ሴሊትና ሙዚቃ ። የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ባጠገባችን ያለውን ዋሻ ስለሚመስለው ዋሻ

አሜወተኝ ... ስሜቴን ስለነካህ ነው የምወድህ ። ማንም ቢሆን ... እውን እንቅልፍ ላይ እያለች ። ፍቅርዬ እዚሁ ሁኚ ። አብረን ሙዚቃ ሰማን ፣ ሲኒማ አየን ። ሕይወትን በትክክል ያሳዩን ይመስል። ባሌ ላይ ከፍተኛ እምነት ነበረኝ ። አውን ሌላ ሰው ማመን እችላለሁ ? ግን ምን አድርጌው ነው እንዶዚያ ሊያርደኝ የፈለገው ።"

"ሚስ አሌክሳንደር ..."

ካተሪን በብሹፓ ውስጥ ሆና በድንጋጤ ቀና አለች ።

አውሮፕላን ነጂው ከአጠገቧ ቆሟል ። "በሰላም ደርሰናል ። እንኳን በደህና ወደለንደን ገባሽ ።"

በአውሮፕላን ማረፊያው ሊሞሲን መኪና ቆሞ ካተሪንን ይጠብቃል ። ሹፌሩም "ሚስ አሌክሳንደር ሻንጣሽንም እኔው እይዝልሻለሁ ። ስሜ አልፍሬድ ይባላል ፣ በቀጥታ ወደቪላሽ ለመሄድ ትፈልጊያለሽ ?" ብሎ ጠየቃት ።

'ቪላዬ!' "መልካም ይሻላል ።"

ካተሪን ተመቻችታ ተቀመጠች ። ያጋጠማትን ሁሉ ለማመን አስቸግሯታል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የግል አውሮፕላን ለብቻዋ መድቦላት መኖሪያ ቤትም አዘጋጅቶላታል ። የመጨረሻው ደግ ሰው ነው፤ ወይንም...። ሌላ አማራጭ ስላልነበረው ነው ። 'የለም ፣ የለም ፣ በዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ደግ ሰው ስለሆነ ለእሱ ያለኝን አድናቆትና ምስጋናዬን የምገልጽበት አንድ አመቺ ዘዴ መፈለግ ይኖርብኛል ።' አለች ።

በኤሊዛቤት ጐዳና ላይ ከሚገኘው የኢቶን አደባባይ አካባቢ ያለው ቪላ በጣም ምቾት አለው ። እውስጥ ሲገባ እንደሳሎን የሚያገለግለው ሰፊው አዳራሽ በፎቴና በወንበሮች ያጌጠ ነው ። የሳሎኑ ግድግዳ እንደመስታወት በሚያብረቀርቁ ውድ ድንጋዮች የተሠራ ነው ። ውብ የሆነ ባለጌጥ መብራትም ቁጋጠልጥሎ ይታያል ። ቤቱ የተሟላ ቤተመጻሕፍት ፣ ምግብ የተትረፈረፈበት ኩሺና ፣ በጣም ያማሩና የተዋቡ ሦስት መኝታ ክፍሎችና የሠራተኛ መኖሪያ ቤት አካትቷል ።

ካተሪን ወደቤቱ ገና እንደደረሰች ጥቁር ልብስ የለበሰች አንዲት ዕድሜዋ ወደ አርባው የሚገመት ሴት ከበሩ ላይ ሆና ሰላምታ አቀረበች ላት ። "እንደምን ዋልሽ ሚስ አሌክሳንደር ። እና እባላለሁ ። የቤት ሠራተኛሽ ነኝ ።"

'የቤት ሠራተኛዬ?' ካተሪን ሁሉንም ነገር በእርጋታ መቀበል ጀመረች ።

"እንደምን አለሽ?"

ሾፈሩ የካተሪንን ሻንጣዎች መኝታ ቤቷ ውስጥ አስገባ ። "ሊሞሲኑን በፈለግሽ ጊዜ ልትጠቀሚበት ትችያለሽ" አላት ። "ወደቢሮ ለመሄድ ዝግጁ ስትሆኚ ለእና ንገሪያትና መጥቼ እወስድሻለሁ ።"

'ሊሞሲኑን በፈለግኩ ጊዜ መጠቀም እችላለሁ ። በሚገባ ።' "አመሰግናለሁ!" አለች ።

"ሻንጣሽን ከፍቼ ልብሶችሽን ላደራጅ ነው ። ሌላም የምትፈልጊው ነገር ካለ ንገሪኝ" አለቻት እና ።

"ለጊዜው ምንም አልፈልግም።" እውነቷን ነበር ።

እና ልብሶቹን ከሻንጣዎቹ ውስጥ አውጥታ እስክትጨርስ ካተሪን ቪላውን ተዟዙራ ጐበኘች ። ወደመኝታ ቤቷም እንደገባች ዴሚሪስ የገዛላትን የተዋቡ ልብሶች ተመልክታ 'ይህ መቼም ሕልም መሆን አለበት ።' ብላ አሰበች ። 'የምታየውን ሁሉ ለማመን ተሳናት ። ከአርባ ስምንት ሰዓታት በፊት በሴቶቹ ገዳም ውስጥ የሮዝ አበቦችን ውሀ ታጠጣ እንዳልነበረ ሁሉ አሁን ደግሞ የልዕልት ኑሮ ትኖራለች ። 'ሥራው ምን ዓይነት ይሆን' ብላ አሰበች ። ደግ ሰው ስለሆነ በደንብ እሠራለሁ ። ጨርሶ አላሳፍረውም ።' አለች በልቧ ። ድካም ተሰምቷት ከምቹው አልጋ ላይ ጋደም አለች ። 'እስቲ ትንሽ ልረፍ' ብላ ዓይኗን ከደነች ።

ውሃ ሲበላት ሲል የድረሱልኝ ጩኸት አስተጋባች ። ላሪ እየዋኘ አጠገቧ ደርሶ ወደውስጥ ደፈቃት ። በጨለማ ዋሻ ውስጥ ነች ። የሌሊት ወፎች ፀጉሯን ለመንጨት ይሞክራሉ ፣ በዚያ አስቀያሚ ክንፋቸው ፊቷን ያጮላሉ ። ካተሪን በድንጋጤ ከእንቅልፏ ነቅታ አልጋዋ ላይ በመቀመጥ መንዘፍዘፍ ጀመረች ።

እራሷን ለማረጋጋት ብላ አየር ወደውስጥ ሳበች ። 'አብቅቷል' አለች በአሳቧ ። 'ያከትማል ። ያ ትላንት ነው ። አሁን ደግሞ ዛሬ ነው ። ማንም ሰው ሊጐዳኝ አይችልም ። ማንም ሰው ።'

ጩኸቷ ከመኝታ ክፍሏ አልፎ ለቤት ሠራተኛዋ ለአናም ተሰማት ። ፈዘኸቱ አንዳበቃ ሁኔታውን ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለማሳወቅ አና ወደ ሳሎኑ ገብታ ስልክ አነሳች ።

ሄሌኒክ የንግድ ኮርፖሬሽን የሚገኘው ከፒካዴሊ ራቅ ብሎ ፣ በ217 የቦንድ ጐዳና ላይ በሚገኘው ፣ በቅርቡ ወደቢሮነት በተለወጠው አሮጌው የመንግሥት ሕንፃ ውስጥ ነው ። የሕንፃው የውጭ ክፍል በጣም የተዋበ የአርኪቴክት ውጤት ሲሆን ዓይን የሚስብና ልብ ደንገጥ የሚያደርግም ነው ።

ካተሪን ወደዚህ ሥፍራ ስትደርስ የቢሮ ሠራተኞቹ ተሰብስበው እርሷን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ ። ጥቂት ሰዎች ሊቀበሏት ተሰልፈው ከበሩ ላይ ቆመዋል ።

“እንኳን ደህና መጣሽ ፣ ሚስ አሌክሳንደር ። ኤቬሊን ኬይ እባላለሁ። እነኚህም ካርል ... ታከር... ማቲው... ጄኒ...”

ስሞቹና ፊቶች በዙባት ።

“ጤና ይስጥልኝ ።”

“ቢሮሽ ተዘጋጅቷል ። ወደዚያው ልውሰድሽ?”

“አመሰግናለሁ ።”

የእንግዳ መቀበያው ክፍል በሚያማምሩ ወንበሮች ተሞልቷል ። ምንጣፍ በተነጠፈበት ረዥም ኮሪዶር በኩል አልፈው በቆዳ መቀመጫ ዎች ወዳማረ ሰፊ ቢሮ ገቡ ።

“ይህ ያንቺ ነው ።”

“በጣም ደስ ይላል” አለች ድምጿን ዝቅ አድርጋ ።

በጠረጴዛው ላይ ትኩስ አበቦች አየች ።

“ከሚስተር ዴሚሪስ የተላከ”

‘በጣም የሚያስብልኝ ሰው ነው’ አለች በልቧ ።

ቢሮውን አዙራ ያስጐበኘቻት ኤቬሊን ኬይ ፣ ደልዳላ ሰውነትና ድንቡሽቡሽ ፊት ኖሯት በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ጠባየ ሸጋ ሴት ናት ።

“ለመልመድ ጥቂት ቀናት ይወስድብሽ ይሆናል ፣ ሥራው ግን በጣም ቀላል ነው ። ቢሆንም ለዚያ ሁሉ የዴሚሪስ የሥራ መስክ የነርቭ ማዕከሎቹ እኛ ነን ማለት ይቻላል ። ከመላ ዓለም የሚመጡ ሪፖርቶችን አቀነባብረን አቴንስ ወደሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት እናስተላልፋለን። እኔ የቢሮው ኃላፊና ሥራ አስኪያጅ ስሆን አንቺ ደግሞ የእኔ ረዳት ትሆኝያለሽ” አለቻት ኬይ ።

‘አሃ’ አለች ካተሪን በአሳቧ ። ‘እና የሥራ አስኪያጅ ረዳት ሆንኩኝ

ማለት ነው?’ ካተሪን ከእርሷ ምን እንደሚጠበቅ አታውቅም ። ደግሞ ሁሉም የሕልም ዓለም ይመስላታል ። የግል አውሮፕላን ፣ ሊሞሲን መኪና ፣ ያማረ ቪላ ፣ የቤት ሠራተኛ...

“ዊም ቫንዲን ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያለው የሒሳብ ሠራተኛችን ነው ። ወጪና ገቢውን በዋናው የሂሣብ ማጠናቀሪያ መዘርዝር ላይ የሚያሰፍረው በጭንቅላቱ አያሰላ ነው ። አንጐሉ ከብዙዎቹ የሒሳብ ማስሊያ መሣሪያዎች በበለጠ ፍጥነት ይሠራል ። ወደቢሮው ልውሰድሽና ተዋወቂው ።”

በኮሪዶሩ አልፈው ከአዳራሹ ቀጥሎ ከጥግ ካለው ቢሮ ደረሱ ። ኤቬሊን ሳታንኳኳ የቢሮውን በር ከፈተች ።

“ዊም ፣ ከአዲሷ ረዳቱ ጋር ተዋወቁ ።”

ካተሪን ቆማ ቀረች ። ዊን ቫንዲን በመጀመሪያዎቹ የሰላሳ ዕድሜ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን ቀጠን ብሎ ቾል ያለ አገጭ ያለው ፈዛዛ መሳይ ሰው ነው ። ጐንበስ ብሎ እግሩን እያየ ነበር ።

“ዊም ፣ ዊም! ከካተሪን አሌክሳንደር ጋር ተዋወቁ”

ቀና አለና በማይጨበጥ ፍጥነት መናገር ጀመረ — “የመጀመሪያው ካተሪን የሚል ስም የማርታ ስኮውሮንካ ስም ነበር ። በ1684 የተወለደችው ይህች ሴት በሩሲያኖች ተማርካ የቤት ሠራተኛ ሆነች ። ቀዳማዊ ፒተርን አግብታ ከ1725 እስከ 1727 የመጀመሪያዋ የሩሲያ ንግሥት ሆነች ። የጀርመን ልውል ልጅ የነበረችው ታላቋ ካተሪን ደግሞ በ1729 ተወለደች ። ኋላ በ1762 ንጉሥ ፒተርን አገባችና እርሱን በማስገደል ዙፋኑን ወሰደች ። በእርሷ አገዛዝ ወቅት ሥላንድ በሦስት ተከፍላ ነበር ። ከቱርኮች ጋር የተካሄደ ጦርነትም መርታለች ። ...” ንግግሩ ሳያቋርጥ እንደፈጠኑ ይወርድ ነበር ።

ካተሪን ፈዝዛ ቀረች ። “... የሚገርም ነው ።” የሚለውን ቃል እንደምንም ለመናገር ተሳካላት ። ዊም ቫንዲን ተመልሶ አቀረቀረ ። ኤቬሊን “ዊም ዓይናፋር ነው” አለቻት ።

‘ዓይናፋር’ አለች ካተሪን በልቧ ። “የሚያስገርም ፍጡር ነው ። ልዩ የሆነ ብሩህ አእምሮ ያለው ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አቴንስ ውስጥ በአጊኡ ጀሮንዳ ጐዳና ላይ

በሚገኘው ቢሮው ውስጥ ተቀምጦ አልፍሬድ ከለንደን በስልክ የሚያስተላልፍለትን ሪፖርት ያዳምጣል ።

“ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ሚስ አሌክሳንደርን ከአውሮፕላን እንደወረደች በቀጥታ ወደማረፍያዋ ነው የወሰድኳት ። እርሷንም ባዘዙኝ መሰረት ሌላ ቦታ ለመሄድ ትፈልግ እንደሆነ ጠይቂያት ነበር ። የትም ለመሄድ እንዳልፈለገች ነገረችኝ ።”

“ሌላ የምትተዋወቀው ሰው የለም ማለት ነው?”

“አይ ፣ ጌታዬ ። ምናልባት ካረፈችበት ቤት ሆና የስልክ ግንኙነት የምታደርግ ካልሆነ በቀር እስካሁን ምንም የለም ።”

እና ፣ የቤት ሠራተኛዋ የሆነውን ነገር ሁሉ ስለምትነግረው ኩንስታንቲን ዴሚሪስ ብዙም አልተጨነቀበትም ። በሰማው ሪፖርት ረክቶ ስልኩን ዘጋው ። ለጊዜው አደጋ የምታስከትል መስሎ ባይታየውም በዓይነ ቁራኛ ክትትል እንዲደረግባት አዟል ። በማታውቀው ዓለም ውስጥ ብቻዋን ትዋኛለች ። ከአጋጋኗና ከረዳቷ ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ በቀር ምንም የላትም ። ‘ወደለንደን ለመጓዝ በቶሎ መዘጋጀት አለብኝ’ አለ ዴሚሪስ ደስታ እየተሰማው ። ‘ባስቸኳይ ።’

ካተሪን አሌክሳንደር አዲሱ ሥራዋ የሚያስደስታት ሆኖ አግኝታዋለች ። በርካታ ሪፖርቶች በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ድርጅቶች በየዕለቱ ይጐርፋሉ ። ኢንዲያና ከሚገኘው የብረት ኢንዱስትሪ የተላከ የማስጫኛ ክፍያ ሰነድ ፣ ኢጣሊያ ካለው የአውቶሞቢል ኢንዱስትሪ የመጣ የአዲት ሪፖርት ፣ አውስትራሊያ ከሚገኝ የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ፣ ከወርቅ ማዕድናትና ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች የመጡ በርካታ የሽያጭ ዘገባዎችን የመሳሰሉት ። ካተሪን ይህን ሁሉ ሰብስባ በቀጥታ ለዊም ቫንዴን ትልካለች ። ሪፖርቶቹን ሁሉ ወዲያው ያነባቸውና እንደ ኮምፒዩተር በሚሠራው ሜንቅላቱ ሸምድዶ በማውጠንጠን ኩባንያውን የገጠመውን የትርፍና የኪሳራ ስሌት በቃሉ ያወጣል ።

ካተሪን ከሥራ ባልደረቦቿ ጋር በመተዋወቋና የምትሰራበት የሕንጻ ውበት ደስ አሰኛት ።

በተለይም ስለሕንጻው የተሰማትን ባንድ ወቅት ዊም ባለበት ለኤቪሊን ኬይ አንስታ ስትናገር ዊምም “ይህ ሕንጻ የመንግሥት

የጉምሩክ ቢሮ ነበር ። በ1721 የሕንጻው ዲዛይን የተነደፈው ሰር ክሪስቶፈር ሬን በተባለ ሰው ነበር ። ክለንደን የእሳት አደጋ ወዲህ ክሪስቶፈር ሬን የሃምሳ አብያተ ክርስቲያናትን ዲዛይን ነድፏል ። ከእነኚህም መካከል የቅዱስ ጳውሎስ ፣ የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ብራይድ አብያተ ክርስቲያናት ጥቂቶቹ ናቸው ። የሮያል ባንክንና የቡኪንግሃም ሃውስን ዲዛይን አቅዶ በ1723 ከዚህ ዓለም በሞት በመለየት በቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን መካነ መቃብር ተቀበረ ። ይህም ቤት በ1907 ወደመንግሥት ቢሮነት ተለውጦ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት መንግሥት የአየር ድብደባ መከላከያ ጣቢያ ሆኗል ብሎ አወጀ ።”

ለቦምብ የማይበገረው የአየር ድብደባ መከላከያው ሥፍራ በጠንካራው የብረት በር በኩል ታልፎ ከምድር ቤቱ ቀጥሎ ይገኛል ። ካተሪን ጠንካራውን ምሽግ አየችው ። የሂትለር አውሮፕላኖች ቦንብ እንደበረዶ በሚያዘንቡበት ወቅት በዚህ ምሽግ ውስጥ መጠለያ ይዘው የነበሩት የብሪታንያ ወንዶች ፣ ሴቶችና ሕጻናት በጎሊናዋ ታዩዋት ።

ምድር ቤቱም ቢሆን ውስጥ ለውስጥ ረዥም ሆኖ የሕንጻውን ያህል ስፋት አለው ። ሕንጻውን በሙሉ የሚያሞቅ ትልቅ ማሞቂያ ያለው እዚህ ውስጥ ነው ። ከዚህም ሌላ የኤሌትሮኒክና የስልክ መሣሪያዎችንም ይዟል። ማሞቂያው እራሱ ችግር ፈጣሪ ነው ። ብዙ ጊዜ እንዲጠግኑት ካተሪን ባለሙያዎችን አስመጥታ አስመርምረዋለች ። ግን የሚመጣው ሁሉ ነካ – ነካ አድርጎት ተሠርቷል ብሎ ይሄዳል ።

“በጣም አደገኛ ነው ማለት ነው” አለች ካተሪን “የመፈንዳት አዝማሚያ ይኖረው ይሆን?”

“አትጨነቂ ሚስ ፣ አይዞሽ አይፈነዳም ። እዚሁያለውን የአደጋ ጊዜ መቆጣጠሪያ ታይዋለሽ? ጥሩ ፣ ቦይለሩ ድንገት ከሞቀ እንኳ በውስጡ ያለውን እንፋሎት ወደውጭ ይለቅና ያቀዘቅዘዋል ። ችግር አይኖርም ።”

ለንደን ከተማ ውስጥ ቅዳሜና እሁድ የአስደናቂ ቲያትሮች ፣ የአስደሳች የባሌት ዳንሶችና ድንቅ የሙዚቃ ዝግጅቶች ሥዕላዊ ማስታወቂያዎች ይለጠፋሉ ። እንደነሃቻርድስና ፎይሌስ የመሳሰሉ ግሩም የመጻሕፍት መደብሮች አሉ ። በርካታ ሙዚየሞች ፣ የብርቅ ዕቃ መደብሮችና ሬስቶራንቶች በብዛት ይገኛሉ ። ካተሪን ወደ ሴሲል ኮርት ሄዳ የድንጋይና የብረት ላይ ጽሑፎች የሚሸጡበትን መደብር ጐበኘች ። ከሃሮድስ ፣ ከፎርትነም ፣ ከማሶን ፣ ከማርክና ከስፔንሰር መደብሮች

የተለያዩ ዕቃዎችን ገዛች ። እሁድም ወደላቮይ ሄዳ ሻይ ጠጣች ።

በየጊዜው ፣ ልታስወግዳቸው የማትችላቸው አሳቦች በካተሪን አእምሮ ውስጥ መጉላላት ቀጠሉ ። ስለላሪ እንድታስብና እንድታስታውስ የሚያስገድዷት ብዙ ነገሮች ነበሩ ። ድምፅ፣...ቃላት....የአነጋገር ዘይቤ. ... ሙዚቃ ። 'አይሆንም ያለፈው አልፏል ። ጠቃሚው የወደፊቱ ነው' ትላለች በአሳቧ ። በየዕለቱም ጠንካራ እየሆነች ሄደች ።

ካተሪንና ኤቬሊን ኬዬ ጓደኛሞች ሆኑ ። አንዳንዴም አብረው ወጣ ይላሉ ። አንድ እሁድም በቴምስ ገላጣ ሥፍራ የሥዕል ኤግዚቢሽን አዩ ። አቅራቢዎቹ በዕድሜ የገፉና ወጣት ሰዓሊያን ሲሆኑ ሥዕሎቻቸውን ሜዳው ላይ ደርድረው ነበር ለሕዝብ ያቀረቡት ። እነኚህ ሰዎች የጋራ የሆነ ነገር አላቸው ። ሁሉም ሥራዎቻቸው ተንቆባቸው በቋሚ ኤግዚቢሽን ውስጥ ለማሳየት ተቀባይነትን ያጡ ናቸው ። ሥዕሎቹ የሚረቡ አልነበሩም ። ካተሪን ለሰዎቹ ሀዘን ተሰምቷት አንዱን ሥዕል ገዛች ።

"የት ልታስቀምጪው ነው?" ስትል ኤቬሊን ጠየቀቻት ።

"ማሞቂያው ከሚገኝበት ክፍል ውስጥ" አለች ካተሪን ።

በለንደን ጐዳናዎች ላይ ሲጓዙ የመንገድ ዳር ሰዓሊዎች አጋጠሙዋቸው ። ሰዓሊዎቹ የተለያዩ ቀለም ባሏቸው ጠመኔዎች በእግረኛው መንገድ ላይ ሥዕሎችን ይስላሉ ። አንዳንዶቹ ሥራዎች ግሩም ናቸው ። በአጠገባቸው የሚያልፍ ሰው ሁሉ ቆም እያለ ሥዕሎቹን ያደንቅና ለሰዓሊዎቹ ጥቂት ሳንቲሞች ይጥልላቸዋል ። አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ካተሪን ምሣዋን ተመግባ ስትመለስ በጠመኔ ውብ የሆነ የመሬት አቀማመጥ ሲስል የነበረውን ሽማግሌ ለማየት ቆም አለች ። ሰርቶ ሊጨርስ ሲል ዝናብ መጥቶ ሥዕሉን ሲያጥበው ሽማግሌው ቆሞ የሥራውን መበላሸት ይመለከት ነበር ። 'ይህ ልክ እንዳለፈው ሕይወቱ ነው' ስትል ካተሪን አሰበች ።

ኤቬሊን ካተሪንን ወደ ሼፐርድ የዕቃ መደብር ይዛት ሄደች ። "መቼም ሥፍራውን ስታይው እንደምትወጂው እርግጠኛ ነኝ ።" ብላ ነበር ኤቬሊን ቃል የገባችላት ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ።

በእርግጥም ደስ የሚያሰኝ ነበር ። የሦስት መቶ ዓመታት ዕድሜ ያለው የቲዲ ዶልስ ሬስቶራንት ፣ የጦር መሣሪያ መሸጫ ፣ የቁንጅና ሳሎን፣ ዳቦ ቤት ፣ የብርቅ ዕቃዎች መደብር እንዲሁም ባለሁለትና ሦስት ፎቅ መኖሪያ ቤቶች ይገኝበታል ።

በአንዳንድ ሱቆች ላይ የተለጠፉ ስሞች ግራ የሚያጋቡ ናቸው ። አንዱ "ሄለን" ይልና ከሥሩ "የፈረንሣይኛ ትምህርት" የሚል ተጽፎበታል ። ሌላው "ሮሲ" ብሎ ዝቅ ይልና "ግሪክኛ እዚህ እናስተምራለን" ይላል ።

"ይህ የማስተማሪያ አካባቢ ነው?" ካተሪን ስትል ጠየቀች ።

ኤቬሊን ከት ብላ ሳቀች ። "ነገሩማ ይመስላል ። ብቻ እነኚህ ልጃገረዶች የሚያስተምሩት በሌላው ትምህርት ቤት የሚያስተምሩትን ትምህርት ዓይነት አይደለም ።"

ካተሪን ግራ ገብቷት ስታያት ኤቬሊን ከት ብላ ሳቀች ።

ካተሪን ብዙውን ጊዜ ብቻዋን ብትሆንም ብቸኝነት እንዳይሰማት እራሷን ሁሌ በሥራ ትጠምዳለች ። ባለፈው ሕይወቷ ያለአግባብ የባከነውን ጊዜ ለማሟላት የምትጥር ትመስላለች ። እያንዳንዱን ቀን በፀጋና በደስታ ነው የምትቀበለው ። ስላለፈውም ሆነ ስለወደፊቱ ላለመጨነቅ ወስናለች ። የዊንድሶርን ግንብ ፣ የካንተርበሪን ካቴድራልና የሃምቶንን ፍርድ ቤት በየተራ ጐብኝታለች ። ቅዳሜና እሁድ ሲመጣ ወደ ገጠር ወጣ ብላ አነስተኛ ሆቴል ውስጥ ከተዝናናች በኋላ ለመናፈስ ረጅም ጉዞ ታደርጋለች ።

"ሕይወቴ እንደሆነ ተርፏል" ትላለች እራሷን ስታጽናና ። "ማንም ሰውኮ ደስተኛ ሆኖ አልተፈጠረም ። ማንም ሰው ፣ ሰው ሁሉ ፣ የእራሱን መደሰቻ እራሱ መፍጠር ይኖርበታል ። ዛሬ ወጣትና ጤናማ ነኝ ። ወደፊት ደግሞ ብሩህ ዕድል ይጠብቀኛል ።"

ሰኖ ወደሥራዋ ትመለሳለች ። ከኤቬሊን ፣ ከሌሎቹ ሴቶችና ከዊም ዌንዴንም ትገናኛለች ።

ዊም ዌንዴን እንደተአምር የሚታይ ፍጡር ነው ።

ካተሪንን ከዚህ በፊት እንደእርሱ ዓይነት ሰው አጋጥሟት አያውቅም ። በዚያች ቢሮ ውስጥ ሃያ ሠራተኞች ይገኛሉ ። ዌንዴን የሒሳብ

መጣሪያ ሳይጠቀም የእያንዳንዱን ሠራተኛ የደመወዝ መጠን ፣ የኢንሹራንስ ቁጥሩን ፣ እንዲሁም ተቀናናሽ ሂሳቦችን በቃሉ ያውቃል ። የኩባንያው ሪኮርድ በፋይል የሚያዝ ቢሆንም እርሱ ሁሉንም በአእምሮው ይይዛል ። የየወሩን የገንዘብ ፍሴት በቃሉ ከማወቁ ሌላ ያሁኑን ወር ካለፈው ወር ጋርና አልፎ ተርፎም ከአምስት ዓመት በፊት ሥራ ሲጀምር ከነበረው ሂሳብ ጋር በቃሉ ማወዳደር ይችላል ።

ዊም ቫንዴን ከዚህ በፊት ያየውን ፣ የሰማውንና ያነበበውን ሁሉ የሚረሳ አይደለም ። የዕውቀት አድማሱ ድምበር የለውም ። ሆኖም ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነትና ቅርበት ደካማ ነው ።

ካተሪን ስለዊም ከኤቬሊን ጋር ስታወራ “እኔኮ የዊም ባሕሪይ ጨርሶ አይገባኝም” አለቻት ።

“ዊምኮ ከማናችንም የተለየ ልዩ ሰው ነው” አለች ኤቬሊኒ ።” ይህንን ባሕሪውን እንዳለ መቀበል አለብሽ ። እርሱን ደስ የሚያሰኙት ቁጥሮች ብቻ ናቸው ። ስለሰዎች ደንታ ያለው አይመስለኝም ።”

“ጓደኞች አሉት?”

“የሉትም ።”

“ከልጃገረድ ጋር ወጥቶ ያውቃል?”

“አይመስለኝም ።”

ዊም ብቸኛና ከሌሎች የተገለለ በመሆኑ ካተሪንን ተሰማት ። የእራሷ ወገን አድርጋም ቆጠረችው ።

የዊም የዕውቀት አድማስ ካተሪንን በጣም አስደንቋታል ። አንድ ቀን ጠዋት የጆሮ ሕመም ተሰማት ።

ዊም ጉርሃን ባለ ድምፅ “ይህ የአየር ጠባይ ሕመሙን ያብሰዋል ። ስለዚህ የጆሮ ሐኪም ብታናግሪ ጥሩ ይመስለኛል” አላት ።

“አመሰግናለሁ ዊም ...”

“የጆሮ ክፍሎች” አለ ዊም እንደ ዳዊት እያምበለበለ ። “የጆሮ ክፍሎች ተቀባይ ገንዳ ፣ የጆሮ ታምቡር ፣ ጥምጥሚ ፣ መሀከለኛ ጆሮ ፣ ወዶሺት ፣ ወስፊት ፣ ሌብቾዊ ቦይ ፣ ወጭኛ ቦይ ፣ ክብ መስኩት ፣ እዩስቻት ቦይ ፣ ስሚታዊ ነርቭ ፣ እርካቢት ፣ እዝን ናቸው ።” ብሎ ዞሮ ወጣ ።

በሌላ ቀን ካተሪንና ኤቬሊን ዊምን ይዘው በአካባቢው ወደሚገኘው ራምስ ሄድ ወደተባለው አነስተኛ ሆቴል ወስደው ምሳ ጋበዙት ። ከሆቴሉ ጓሮ ጥቂት ሰዎች ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የዳርት ቁጥር

እየወጉ ይጫወታሉ ።

“ዊም ስፖርት ትወዳለህ?” ስትል ካተሪን ጠየቀችው ። “የቤሲቦል ጨዋታስ አይተህ ታውቃለህ?”

“ቤሲቦል” አለ ዊም “የቤሲቦል ኳስ ዙሪያ ስፋት ዘጠኝ ኢንች ከሩብ ነው ። ኳሱ የተሠራው ከሱፍ ክር ሲሆን ክሩ የተጠመጠመው በጠንካራ ላስቲክ ላይ ነው ። የኳሱ የውጭ አካልም የተሸፈነው በነጭ ቆዳ ነው ። ኳሲን ለመለጋት የሚያገለግለው እንጨት ስፋት ከሦስት ኢንች ከሩብ የማይበልጥ ፣ ርዝመቱ 42 ኢንች የሆነ ነው ።”

‘መጠኑንም ጭምር ያውቃል’ ብላ ተገረመች ካተሪን በአሳቢ ። ‘ግን ጨዋታውን በአካል ለመጫወት ፍላጎትና ስሜት ያለው አይመስለኝም ።’

“በስፖርት ጨዋታ ተካፍለህ ታውቃለህ? ለምሳሌ በቅርጫት ኳስ”

“የቅርጫት ኳስ ጨዋታ ሊካሄድ የሚችለው በጣውላ ወይም በአስፋልት ወለል ላይ ነው ። ኳሱ የተሸፈነው በቆዳ ሲሆን የኳሱ ዙሪያ ስፋት ሰላሳ አንድ ኢንች ነው ። ከኳሱ ውስጥ የላስቲክ ፊኛ አለ ። ከፊኛው ውስጥ ያለው የታመቀው የአየር ክብደት አሥራ ሦስት ፓውንድ ይመዝናል ። የኳሱም ክብደት በአጠቃላይ ከሃያ እስከ ሃያ ሁለት አውንዝ ይሆናል ። በ1891 የቅርጫት ኳስን የፈለሰፈው ጄምስ ናኢስሚዝ ይባላል።”

ካተሪን ለጥያቄዋ ምላሽ አገኘች ።

* * *

አንዳንድ ጊዜ ከዊም ጋር መሄድ በሰው ፊት ያሳፍራል ። አንድ እሑድ ቀን ካተሪንና ኤቬሊን ዊምን ይዘው ወደ ሜኢዴንሂድ እንደሄዱ ርቧቸው ምሳ ለመብላት ወደ ሬስቶራንት ገቡ ። አሳላፊው ወደተቀመጡበት ሥፍራ መጣና “ዛሬ ለምሳ የሚሆን ትኩስ የቀፎ ዓሣ አለን!” አላቸው ።

ካተሪን ወደዊም ዞር አለችና “የቀፎ ዓሣ ትወዳለህ?” አለችው ። ዊምም ሲመልስ፡- “የቀፎ ዓሣ ዓይነት፡- ረዥም ቀፎ ዓሣ ፡ አለትማው የሰሜን አሜሪካ ቀፎ ዓሣ ፡ ክብ ቀፎ ዓሣ ፡ ባለስለት ቀፎ ዓሣ ፡ እንዲሁም ደማም ቀፎ ዓሣ ናቸው ።”

አሳላፊው ትኩር ብሎ "የሚፈልጉትን ቢያዙ ጌታዬ ?" አለው ።
"ቀፎ ዓሣ አልወድም" አለ ዊም መልሶ ።

ካተሪን አብሯት የሚሠሩትን ሠራተኞች ሁሉ ወደደቻቸው ። ላዒምም ያላት ፍቅር ልዩ ነበር ። ከግምቷ በላይ ብልሀና ብሩህ አእምሮ ያለው ሆኖ አይተዋለች ። ሆኖም ብቸኛና የተገለለ ነው ።

ካተሪን አንድ ቀን ኤቬሊንን "ዊም የተደላደለ ኑሮ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችል ይመስልሻል ? ለፍቅር ተምበርክኮ ለማግባትስ ያስብ ይሆን?" ብላ ጠየቀቻት ።

ኤቬሊን በትካዜ "ነግሬሽ ነበር ፤ ሰውዬው ውስጣዊ ስሜት የሚባል ነገር አልተፈጠረበትም ። ከማንም ጋር ልብ ለልብ ሊገጥም አይቻለውም ።"

የተናገረችውን ካተሪን አልተቀበለቻትም ። ከአንዴ ሁለቴ የፍላጎት ፣ የፍቅርና የመሳቅ ብልጭታዎችን ከዊም ፊት ላይ አንብባለች ። የሚቻላትን ሁሉ ልትረዳው ፈለገች ። ግን ግምቷ ልክ ነው ወይንስ የተሳሳተ ?

አንድ ቀን የቢሮው ሠራተኞች በሳቮይ በሚደረግ ግብዣ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ደረሳቸው ።

ካተሪን ወደዊም ቢሮ ገባችና "ዊም ዳንስ ትወዳለህ ?" ብላ ጠየቀችው ።

ትኩር ብሎ አያት ። "ዳንስ ለመደነስ በመጀመሪያ ኖታዎቹ ..." አለና እንደልማዱ ተነተነው ። ከሙዚቃ ኖቶች አደራደር ጀምሮ በየትኛው ሙዚቃ ምን ዓይነት ዳንስ እንደሚደነስ ፣ ሰውዬው ወይንም ሴትዮዋ መጀመሪያ የሚያንቀሳቅሱትን እግር ፣ የሚከተሉትን አቅጣጫ አዘነበላት።

ካተሪን የምትናገረው ጠፍቷት ተገትራ ቀረች ። "ዝርዝሩን ሁሉ ያውቃል ፤ ምን ያደርጋል ታዲያ ትርጉሙን አያውቅ ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስልክ ደወለ ። በጣም መሽቶ ስለነበረ ካተሪን ለመተኛት እየተዘጋጀች ነው ።

"እንዳልረበሽኩሽ እርግጠኛ የሆንኩ ይመስለኛል ። ኮስታ ነኝ ።"

"አይ ፣ አልረበሹኝም ..." ድምፁን በመስማቷ ደስ አላት ። ምክሩን

ለመጠየቅም ሆነ በአጠቃላይ ከእርሱ ጋር ለመወያየት ለረዥም ጊዜ አልቻለችም ነበር ። እውነቱን ለመናገር ያለፈውን ታሪኳን በሙሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ በዓለም ውስጥ ያለ እርሱ ብቻ ነው ። የቅርብ ወዳጇ የደወለላት መስሎ ተሰማት ።

"ካተሪን ስለአንቺ ሳስብ ነበር ። ለንደን ብቸኝነት እንዲሰማሽ የሚያደርግ ሥፍራ ይሆናል የሚል ስጋት አስጨነቀኝ ። በተለይም እዚያ የምታውቂውም ሰው ባለመኖሩ ። "

"አንዳንዴ ብቸኝነት ይሰማኛል" ብላ ካተሪን እውነቱን ነገረችው። "ቢሆንም እንዳይሰማኝ እየጣርኩ ነው ። እርስዎ ያሉኝን ለማስታወስ እየሞከርኩ ነኝ ። ስላለፈው እየረሳሁ ፣ ለወደፊቱ እኖራለሁ ።"

"ልክ ነሽ ስለወደፊቱ ለመወያየት ነገ ወደለንደን እመጣለሁ ። እራት አብረን ብንበላስ?"

"እጅግ በጣም ደስ ይለኛል" አለች ካተሪን በጉጉት ። ስትመኘው የነበረ ነው ። ምን ያህል ባለውለታዋ እንደሆነ ለመናገር መልካም አጋጣሚ ነው ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የስልኩን እጀታ መልሶ ሲያስቀምጥ ፈገግ አለ ።

'የቼዝ ጨዋታው እንግዲህ ተጀመረ' ሲል ለእራሱ ተናገረ ።

በሪትዝ ሆቴል እራት በሉ ። የምግብ አዳራሹ ውብና ያማረ ሲሆን ምግቡም በጣም ጣፋጭ ነበር ። ካተሪን ግን ስለዚህ ሁሉ ደንታ ሳይኖራት፡ ትኩረቷ ፣ አሳቧና አድናቆቷ ከፊት ለፊት ከተቀመጠው ጋባኒ ላይ ነበር ። ብዙ ልትነግረው ያሰበቻቸው ነገሮች ነበሩ ።

"ግሩም የቢሮ ሠራተኞች አሉዎት ።" አለችው ካተሪን ። "ዊምም አስደናቂ ፍጡር ነው ። ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ሰው አይቼ አላውቅም። ..."

ዴሚሪስ የምትናገረውን ነገር አላዳመጣትም ። እያጠናት ነው ። ምን ያህል ቆንጆና ተወዳጅ እንደነበረች አስታወሰ ። 'እንዳስቸኩላት አያስፈልግም' ሲል ዴሚሪስ በሀሳቡ ወሰነ ። 'ጨዋታውን ቀስ እያልኩ እየተጫወትኩ በድል አድራጊነት እፈጽማለሁ ። ኖኤሌ ፣ ይህ ሁሉ የሚደረገው ለአንቺና ለፍቅረኛሽ ተብሎ ነው ።'

"ለንደን ብዙ ይቆያሉ ?" ስትል ካተሪን ጠየቀችው ።"

"ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ብቻ ። አንድ የማከናውነው ሥራ

አለኝ ሥ” በእውነት የሚያከናውነው ነገር አለውን? ይህንን ሁሉ በስልክ መጨረስ እንደሚችል ያውቃል ። ግን አመጣጡ ካተሪን የበለጠ እ?ዮትቀርበውና ስሜቷ ለእርሱ ሙሉ በሙሉ ተገዥ እንዲሆን ዘመቻ ለ° ድረግ ነው ። ወደፊቷ ቀረብ አለ ። “ካተሪን በሳውዲት ዓረብ የነዳጅ ነምችት ሥፍራዎች ስለሰራውባቸው ጊዜያት አጫውቼሻለሁ ...?” ብሎ ጠየቃት ።

ዴሚሪስ ካተሪንን በሚቀጥለውም ምሽት እራት ጋበዛት ።

“በቢሮው ውስጥ ምን ያህል ቀልጣፋ ሥራ እንደምታከናውኚ ኤቬሊን አጫውታኛለች ። የደሞዝ ጭማሪ ላደርግልሽ ነው ።”

“ከዚህ በፊትም ብዙ ውለታ ውለውልኝ የለ? ...” ካተሪን ጭማሪውን መቃወሚ ነበር ።

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ የውስጥ ዓይኗን አየ ። “ምን ያህል ውለታ ዋይ ሰው ልሆን እንደምችል አታውቂም!”

ካተሪን በአነጋገሯ መልሳ አፈረች ።

‘ሰውዬው በቃ ደግ ነው ።’ አለች በአሳቧ ። ‘ሌላ ነገር ማሰብ አይገባኝም ።’

በሚቀጥለው ቀን ዴሚሪስ ወደግሪክ ለመመለስ ተነሳ ። “ካተሪን ፣ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ አብረን ብንሄድስ?”

“እሺ”

ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ሰው ሆኖ አግኝታዋለች ። አስደናቂና ብልህ ከመሆኑ ሌላ እንደሚያስብላት በመረዳቷም ተታልላለች ።

አውሮፕላን ማረፊያው እንደደረሱ ዴሚሪስ ለስለስ አድርጎ ጉንጯ ላይ ሳማት ።

“አብረን የበለጠ ጊዜ ብናሳልፍ ደስ ባለኝ ነበር ኩተሪን” አላት ።

“እኔም እንዲሁ ። እመሰግናለሁ ኮስታ” ብላ መለሰች ።

እዚያው ቆማ አውሮፕላኑ መራቱን እስኪጨልቅ ተመለከተች ‘ልዩ ሰው ነው’ አለች በአሳቧ ። ‘ከሱ ተለይቶ መኖር ይከብዳል ።’

ምዕራፍ ስድስት

ኮንስታንቲን ዴሚሪስና ያርሳው ስፒሮስ ላምብሩ በመወዳጀታቸው ያልተደነቀ ሰው የለም ።

ስፒሮስ ላምብሩ ልክ እንደ ዴሚሪስ በጣም ሀብታምና ተሰሚነት ያለው ሰው ነው ። ዴሚሪስ በዓለም ላይ ትልቅ የሆነው የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ባለቤት ሲሆን የላምብሩ የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ከዴሚሪስ በመጠኑ አነስ ያለ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተለያዩ በርካታ የጋዜጦች ማሳተሚያና የአየር መንገድ ድርጅቶች ፣ የነዳጅ ማውጫ ሥፍራዎች ፣ የብረት ፋብሪካዎችና የወርቅ ማዕድናትም ባለቤት ነው ። ስፒሮስ ላምብሩም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ፣ የባንኮች ፣ የበርካታ ኢንዱስትሪዎችና የኬሚካል ማምረቻ ተቋሞች ባለቤት ነው ። ሁለቱም ወዳጅ የሚመስሉ ተፎካካሪዎች ሲሆኑ ከዚህ በይበልጥ ደግሞ የቅርብ ዛደኞችም ሆነዋል ።

“ነገሩ አያስደንቅም!” ይላሉ ብዙ ሰዎች ። “በዓለም ውስጥ ያሉ ሁለቱ ታላላቅ ሰዎች ወዳጆች ሲሆኑ ።” ላይ ላዩን ላላየ ግን ሁለቱም የመጨረሻ ጠላቶች ናቸው ። አንዱ ሌልኛውን ይንቃል ። ስፒሮስ ላምብሩ 100 ጫማ ርዝመት ባለው የመንሸራሸሪያ ጀልባ የተንዘ እንደሆን ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ወዲያውኑ 150 ጫማ ርዝመት ያለው ፣ በውስጡ የመዋኛ ስፍራ ሞሮት 13 ሠራተኞች የሚሰሩበትና ሁለት ትናንሽ ፈጣን ጀልባዎችን የተሸከመ ባለ አራት ሞተር ተመሳሳይ መርከብ ይገዛል ።

የስፒሮስ ላምብሩ የዕቃ መጫኛ መርከቦች ቁጥር 12 ደርሶ የዕቃ መጫን አቅማቸውም ወደ 200.000 ቶን ከፍ ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ያሉትን የጭነት መርከቦች ቁጥር ወደ 23 አሳድጓል ። እነኚህም መርከቦች የሚይዙት 630.000 ዕቃ ነበር ። ስፒሮስ ላምብሩ ለውድድር የሚሆኑ ፈረሶች እንደገዛ ዴሚሪስም የበለጠ ፈጣን ጋላቢ የሆኑ ፈረሶችን

አለኝ ሥ” በእውነት የሚያከናውነው ነገር አለውን? ይህንን ሁሉ በስልክ መጨረስ እንደሚችል ያውቃል ። ግን አመጣጡ ካተሪን የበለጠ እ'ሮትቀርበውና ስሜቷ ለእርሱ ሙሉ በሙሉ ተገዥ እንዲሆን ዘመቻ ለ° ድረግ ነው ። ወደፊቷ ቀረብ አለ ። “ካተሪን በሳውዲት ዓረብ የነዳጅ ኮምችት ሥፍራዎች ስለሰራሁባቸው ጊዜያት አጫውቼሻለሁ ...?” ብሎ ጠየቃት ።

ዴሚሪስ ካተሪንን በሚቀጥለውም ምሽት እራት ጋበዛት ።

“በቢሮው ውስጥ ምን ያህል ቀልጣፋ ሥራ እንደምታከናውኚ ኤቪሊን አጫውታኛለች ። የደሞዝ ጭማሪ ላደርግልሽ ነው ።”

“ከዚህ በፊትም ብዙ ውለታ ውለውልኝ የለ? ...” ካተሪን ጭማሪውን መቃወሟ ነበር ።

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ የውስጥ ዓይኗን አየ ። “ምን ያህል ውለታ ዋይ ሰው ልሆን እንደምችል አታውቂም!”

ካተሪን በአነጋገሯ መልሳ አፈረች ።

‘ሰውዬው በቃ ደግ ነው ።’ አለች በአሳቧ ። ‘ሌላ ነገር ማሰብ አይገባኝም ።’

በሚቀጥለው ቀን ዴሚሪስ ወደግሪክ ለመመለስ ተነሳ ። “ካተሪን ፣ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ አብረን ብንሄድስ?”

“እሺ”

ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ሰው ሆኖ አግኝታዋለች ። አስደናቂና ብልህ ከመሆኑ ሌላ እንደሚያስብላት በመረዳቷም ተታልላለች ።

አውሮፕላን ማረፊያው እንደደረሱ ዴሚሪስ ለስለስ አድርጎ ጉንጯ ላይ ሳማት ።

“አብረን የበለጠ ጊዜ ብናሳልፍ ደስ ባለኝ ነበር ካተሪን” አላት ።

“እኔም እንዲሁ ። እመሰግናለሁ ኮስታ” ብላ መለሰች ።

እዚያው ቆማ አውሮፕላኑ መሬቱን እስኪለቅ ተመለከተች ‘ልዩ ሰው ነው’ አለች በአሳቧ ። ‘ከሱ ተለይቶ መኖር ይከብዳል ።’

ምዕራፍ ስድስት

ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ጆርላው ስፒሮስ ላምብሩ በመወዳጀታቸው ያልተደነቀ ሰው የለም ።

ስፒሮስ ላምብሩ ልከ እንደ ዴሚሪስ በጣም ሀብታምና ተሰሚነት ያለው ሰው ነው ። ዴሚሪስ በዓለም ላይ ትልቅ የሆነው የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ባለቤት ሲሆን የላምብሩ የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ከዴሚሪስ በመጠኑ አነስ ያለ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተለያዩ በርካታ የጋዜጦች ማሳተሚያና የአየር መንገድ ድርጅቶች ፣ የነዳጅ ማውጫ ሥፍራዎች ፣ የብረት ፋብሪካዎችና የወርቅ ማዕድናትም ባለቤት ነው ። ስፒሮስ ላምብሩም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ፣ የባንኮች ፣ የበርካታ ኢንዱስትሪዎችና የኬሚካል ማምረቻ ተቋሞች ባለቤት ነው ። ሁለቱም ወዳጅ የሚመስሉ ተፎካካሪዎች ሲሆኑ ከዚህ በይበልጥ ደግሞ የቅርብ ጓደኞችም ሆነዋል ።

“ነገሩ አያስደንቅም?” ይላሉ ብዙ ሰዎች ። “በዓለም ውስጥ ያሉ ሁለቱ ታላላቅ ሰዎች ወዳጆች ሲሆኑ ።” ላይ ላዩን ላላየ ግን ሁለቱም የመጨረሻ ጠላቶች ናቸው ። አንዱ ሌልኛውን ይንቃል ። ስፒሮስ ላምብሩ 100 ጫማ ርዝመት ባለው የመንሸራሸሪያ ጀልባ የተንዘ እንደሆነ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ወዲያውኑ 150 ጫማ ርዝመት ያለው ፣ በውስጡ የመዋኛ ስፍራ ሄሮት 13 ሠራተኞች የሚሰሩበትና ሁለት ትናንሽ ፈጣን ጀልባዎችን የተሸከመ ባለ አራት ሞተር ተመሳሳይ መርከብ ይገዛል ።

የስፒሮስ ላምብሩ የዕቃ መጫኛ መርከቦች ቁጥር 12 ደርሶ የዕቃ መጫን አቅማቸውም ወደ 200,000 ቶን ከፍ ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ያሉትን የሞኒት መርከቦች ቁጥር ወደ 23 አሳድጓል ። እነዚህም መርከቦች የሚይዙት 650,000 ዕቃ ነበር ። ስፒሮስ ላምብሩ ለውድድር የሚሆኑ ፈረሶች እንደገዛ ዴሚሪስም የበለጠ ፈጣን ጋላቢ የሆኑ ፈረሶችን

አስመጥቶ የሁለቱም ፈረሶች በተወዳደሩበት አሸናፊ ሆነ። ሁለቱም ዘወትር ይገናኛሉ ። በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ በኮሚቴ አባልነት፡ በተለያዩ ኮርፖሬሽኖች በቦርድ አባልነት ሲሰሩ በቤተሰብ ስብሰባዎችና ግብዣዎች ላይም አልፎ አልፎ ይገጣጠማሉ።

የሁለቱም ጠባይና ባሕሪይ ተቃራኒ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከትቢያ ተነስቶ በእራሱ ጥረት እዚህ ሥፍራ የደረሰ ሲሆን ስፒሮስ ላምብሩ ቀድሞም የመሳፍንት ወገን ነው ። የላምብሩ ቁመና ያማረ አለባበሱም ሽክ ያለ ነው ። በባሕሪውም ጥንታዊና መሳፍንታዊ ተፅዕኖ ያለበት ይመስላል ። በዘር ግንዱም በአንድ ወቅት የግሪክ ነገሥታት ከነበሩ ከባቫሪያ አቶዎች ወገን ነው ። ግሪክ ውስጥ የሕዝብ አመጽ ተነስቶ በነበረበት ወቅት ጥቂት ባለሥልጣናት በንግድ ፡ በመርከብ ሥራና በመሬት ይዞታ ዘርፍ ሀብት ለማካበት ዕድል ገጥሟቸው ነበር ። ከእነኚህም መካከል የስፒሮስ ላምብሩ አባት አንደኛው ስለነበረ ስፒሮስ ላምብሩም የአባቱን ንብረት ወርሶ ነው ሀብታም ሊሆን የበቃው ።

የስፒሮስ ላምብሩና የኮንስታንቲን ዴሚሪስ የዩስሙላ ጓደኝነት ለብዙ ዓመታት ቆየ ። ሆኖም በመጨረሻ ላይ ዴሚሪስ ያለውን ደረጃ ይዞ ለመቀጠል ባለው ጽኑ ፍላጐት ፡ ላምብሩ ደግሞ ዴሚሪስ በእህቱ ሜሊና ላይ ለሚፈጽመው በደል አንድ ቀን መጠፋፋታቸው እንደማይቀር ጠንቅቀው ያውቃሉ ።

ስፒሮስ ላምብሩ በአጉል እምነት የሚያመልክ ሰው ነው ። በሕይወቱ ውስጥ ያጋጠመውን ጥሩ ዕድል ያደንቃል ፡ በዚህም የተነሳ አማልክቱን ማሳዘን አይፈልግም ። ዘወትር ኮከብ ቆጣሪዎች ዘንድ ይመላለሳል ። አጭበርብረውት እንደሆነም ወዲያው ያውቅባቸዋል ። ከነሱ መሃከል የሚያምነው አንዷን ኮኮብ ቆጣሪ ነው ። ከዚህ ቀደም የእህቱ ሜሊና ፅንስ እንደሚጨናገፍ ፡ ትዳራቸውም ምን ሊመስል እንደሚችልና ሌሎች ሌሎች የተፈጸሙትን ነገሮች ተንብያ ይዘላታል ። የምትኖረው በአቴንስ ውስጥ ነው ። ማዳም ፒሪስ ትባላለች ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአጊኡ ጌሮንዳ ከሚገኘው ቢሮው ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት መድረሱን እንደልማድ አድርጐ ወስዶታል ። ተቀናቃኞቹ አርፍደው ቢሮአቸው ሲደርሱ ዴሚሪስ በመላ ዓለም ከሚገኙ ወኪሎቹ ጋር በርካታ ሥራዎችን አከናውኖ ይቆያቸዋል ።

ከዴሚሪስ ቢሮ ተቀምጦ ብዙ ነገር ይታያል ። የአቴንስ ከተማ በመስኮት በኩል ወለል ብላ ትታያለች የቢሮው ወለል የጥቁር ድንጋይ ንጣፍ ነው ። መቀመጫዎቹ በቆዳ የተሸፈኑ የብረት ወንበሮች ሲሆኑ በቢሮው ግድግዳ ላይ የተለያዩ ሥዕሎች ተንጠልጥለዋል ። ከብረት የተሠራ ሰፊ የመስተዋት ጠረጴዛ በቢሮው መሐል ቆሟል ። ከጠረጴዛው ላይ የታላቁ አሌክሳንደር ምስል ከፈረያብረቀርቅ ድንጋይ ተቀርጾ ተቀምጧል። ከሥሩ "አሌክሳድሮስ ፡ የሰው ልጆች ጠባቂ" የሚል ተጽፎበታል።

ያን ዕለት ጠዋት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ልክ ከቢሮው እንደደረሰ የግል ስልኩ ጠራ ። የዚያችን ስልክ ቁጥር የሚያውቁ ሰዎች በጣም የተወሰኑ ናቸው ።

ዴሚሪስ ስልኩን አነሳ ። "ካሊሜራ" የላምብሩ የግል ፀሐፊ የኒኮስ ቬሪቶስ የፍርሃት ድምፅ ነበር ።

"ስለረበሽኩዎ ይቅርታ ያድርጉልኝ ሚስተር ዴሚሪስ ። አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮች ካሉ ደውልልኝ ስላሉኝ ይህንኑ ...."

"እሺ ምንድን ነው ?"

"ሚስተር ላምብሩ ፡ አውሮራ ኢንተርናሽናል ኩባንያን ለመግዛት ይፈልጋሉ ። ኩባንያው በኒውዮርክ የገበያ ምንዛሪ መዝገብ ውስጥ ሰፍሯል ። ሚስተር ላምብሩ አንድ በሥራ አስኪያጆች ቦርድ ውስጥ ያለ ወዳጅ አላቸው ። እሱም ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖችን ለማምረት ታላቅ የመንግሥት ኮንትራት ለኩባንያው ሊሰጥ እንደሆነ ነግሮዋቸዋል ። እሁን የምንግሮት ጥብቅ ምስጢር ነው ። ነገሩ ይፋ ሲወጣ የኩባንያው የአክሲዮን ክፍያ ያድጋል ። ...."

"እኔ በአክሲዮን ክፍያ ንግድ ውስጥ ለመግባት ፍላጎት የለኝም" አለ ዴሚሪስ ኮስተር ብሎ ። "በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ልትነግረኝ ካልሆነ በቀር ሁለተኛ አትደውልልኝ ።"

"አዝናለሁ ሚስተር ዴሚሪስ እኔማ ..."

ዴሚሪስም ስልኩን ዘጋው ።

ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት የዴሚሪስ ረዳት የሆነው ጂአኒስ ቻሮስ ወደቢሮው ሲገባ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ካቀረቀረበት ቀና አለ ። "በኒውዮርክ የገበያ ምንዛሪ ውስጥ አንድ አውሮራ ኢንተርናሽናል

የሚባል ኩባንያ አለ ። ኩባንያው በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር ምርመራ እየተካሄደበት መሆኑን ለጋዜጦቻችን ሁሉ አስታውቅ ። ዜናው የተገኘው ስማቸውን ካልገለጹ ምንጮች መሆኑን ጋዜጦቹ እንዲያስፍሩ ይነገራቸው ። የኩባንያው የአክሲዮን ዋጋ በጣም ዝቅ እስኪል ድረስ ጋዜጦቹ ያለማቋረጥ በኩባንያው ላይ እንዲረባረቡ እፈልጋለሁ ። ኩባንያውን ሙሉ በሙሉ እስክንቆጣጠር አክሲዮኖቹን መግዛት ቀጥሉ ።"

"እሺ ጌታዬ ይኸው ብቻ ነው ?"

"አይደለም ። ኩባንያውን በሙሉ ከተቆጣጠርን በኋላ ነገሩ ያልተረጋገጠና ያልተጨበጠ ሐሜት መሆኑን ጋዜጦች እንደደረሱበት ይጻፉ ። እሣ ፥ እም ፥ ስፒሮስ ላምብሩ አክስዮኖቹን የገዛውም በኩባንያው ውስጥ ያለ ሰው ምስጢሩን አውጥቶ ስለነገረው መሆኑንም የኒውዮርክ የገበያ ምንዛሪ ማዕከል እንዲያውቀው ይደረግ ።"

ጂአኒስ ቻሮስ በትህትና "ግን እኮ ሚስተር ዴሚሪስ ፥ እንዲህ ዓይነቱ ነገር በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እንደወንጀል ይቆጠራል" አለው።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፈገግ አለ ። "እኔም አውቃለሁ ።"

ስፒሮስ ላምብሩ ከሲንታግማ አደባባይ አንድ ማይል ያህል ራቅ ብሎ በሚገኘው ቢሮው ውስጥ ተቀምጠ የዕለት ተግባሩን ያከናውናል ። ቢሮው ሰውዬው ምን ዓይነት ዕቃዎችን እንደሚወድ በሚገባ ያንፀባርቃል ። የሚታዩት ሁሉ ከውድ ነገር የተሠሩ ሲሆን ከአጣሊያና ከፈረንሣይ ተገዝተው የመጡ መሆናቸው ይታወቃል ። በአራቱ ግዕዘናት ከሚገኙ ግድግዳዎች ሦስቱ በፈረንሣይ ሰዓሊያን በተሠሩ ሥዕሎች ተሸፍነዋል ። አራተኛው ግድግዳ ላይ የቤልጅግ የሥራ ውጤት ተስቅሏል ። ከቢሮው መግቢያ በር ላይ "ላምብሩና ሽሪኩቹ" የሚል ጽሑፍ ተለጥፏል ። ሆኖም ሽሪክ የለውም ። ስፒሮስ ላምብሩ ይህንን የተሳካና ሰፊ የንግድ መስክ ከአባቱ የወረሰ ቢሆንም ባለፉት ዓመታት ባካሄደው ጥረት ድርጅቱ በመላው ዓለም የታወቀ እንዲሆን ለማድረግ ችሏል ።

ስፒሮስ ላምብሩ ደስተኛ ሰው መሆን ነበረበት ። በጣም ሀብታምና የተዋጣለት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ሲሆን የተሟላ ጤንነትም ያለው ነው ። ሆኖም ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሕይወት እስካለ ድረስ ጨርሶ

ደስተኛ ሊሆን አልቻለም ። የእህቱ ባል የቆላ ቁስል ሆኖበታል ። ቢሆንም ላምብሩ በጣም አድርጉ ይንቀዋል ። ዴሚሪስ ዘዴኛና ብልሃተኛ ቢሆንም ሞራል የሌለው ወሮበላ አድርጉ ይቆጥረዋል ። ዴሚሪስ ሜሊናን ስለማይንከባከባት ይጠላዋል ። ከዚህ ባሻገር ለሁለቱ ሰዎች የመረረ ጥላቻ ሌላ ምክንያትም አለ ።

ነገሩ የተጀመረው ከአሥር ዓመት በፊት ስፒሮስ ላምብሩና እህቱ አብረው ምሣ ከበሉ በኋላ ነው ። ሜሊና ወንድሟ እንደዚያን ቀን ተደስቶ አይታ አታውቅም ።

"ሜሊና ፥ በዓለም ላይ በእያንዳንዷ ቀን የሚያልቀውን ነዳጅ ያህል ለማምረት ሺህ ዓመታት እንደሚፈጅ ታውቂያለሽ?" ሲል እህቱን ጠየቃት ።

"አላውቅም ስፒሮስ ።"

"ወደፊት ለነዳጅ ዘይት የሚኖረው ፍላጐት ከፍተኛ ይሆናል ። እና በቂ የሆነ የመጓጓዣ መርከብ የለም ።"

"ታዲያ አንተ መርከብ ልታስገነባ አሰብክ?"

ፊንቅላቱን በአዎንታ ነቀነቀና "ተራውን ሳይሆን ከሁሉም የሚበልጥ ግዙፍ የነዳጅ ማጓጓዣ መርከቦች ለማሳነፅ ነው ሃሣቤ ። ካሁኖቹ የእጥፍ እጥፍ የመያዝ አቅም ያላቸው" አላት በተሰፋ በተመላ አንደበት ። "ይህንኑ ሳሰላስል ብዙ ወራት አሳልፌአለሁ ። ልብ ብለሽ አዳምጪኝ ። አሁን ባለው ሁኔታ አንድ ጋሎን ድፍድፍ ቤንዚን ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ ወደ ምሥራቃዊ የዩናይትድ ስቴትስ የባሕር ጠረፍ ለማድረስ ሰባት ሳንቲም ይከፈላል ። እኔ ለማሠራት ባቀድኩዋቸው ግዙፍ መርከቦች ግን አንዱን ጋሎን በሦስት ሳንቲም ብቻ ለማንቀሳቀስ ይቻላል ። የምልሽ ይገባሻል?"

"ስፒሮስ ፥ እንደዚህ ያለ መርከብ ለማሠራት የሚያስችል ገንዘብ ከየት ታገኛለህ?"

ሳቅ አለና "እዚህ ላይ አይደል የእቅዱ ውበት! እኔ ከኪሴ የማወጣው ገንዘብ የለም ።"

"ምን?"

ከወረቀቱው ላይ ተደገፈና "የትላልቅ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎችን ባለቤቶች ለማነጋገር በሚቀጥለው ወር ወደ አሜሪካ እሄዳለሁ ። በእነኚህ መርከቦች አማካይነት እስከ አሁን ያንቀሳቀሱበት ዋጋ በግማሽ

ነዳጃቸውን ላንጉዝላቸው እችላለሁ ።" አላት ።

"ግን...እስካሁን ምንም ግዙፍ መርከቦች የሉህም ።"

ፈገግታው ወደ መኮሳተር ተቀየረ ። "የሉኝም ግን አሁን የረዥም ጊዜ የኮንትራት ውል ከነዳጅ ኩባንያዎቹ ጋር ከተፈራረምኩ ለመርከቦቹ መሥሪያ የሚያስፈልገኝን ገንዘብ ባንኮች ያበድሩኛል ። ምን ይመስል ሻል?"

"ብሩህ አእምሮ ያለህ ነህ ። ግሩም እቅድ ነው ።"

ሜሊና በወንድሟ ሃሣብ በጣም ከመደሰቷ የተነሳ ያንኑ ዕለት ምሽት እራት እንደቀረበ እቅዱን ለባለቤቷ ለዴሚሪስ አጫወተችው ።

በዝርዝር አስረድታው ስትጨርስ "አሳቡ በጣም ግሩምና ድንቅ አይደለምን?" ስትል ጠየቀችው ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለአጭር ጊዜ ዝም አለ ። "ወንድምሽ ሕልም እያለመ መሰለኝ ። እቅዱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አይመስለኝም !"

ሜሊና በመገረም "ለምን ኮስታ?" ስትል መልሳ ጠየቀች ።

"ምክንያቱም ከጥንቸል አእምሮ የፈለቀ እቅድ ነው ። በመጀመሪያ ደረጃ የነዳጅ ተፈላጊነት ያን ያህል ነው ። ስለዚህ እርሱ የሚያልማቸው የግዙፍ መርከቦች ባዶዋቸውን ይጓዛሉ ማለት ነው ። በሁለተኛ ደረጃ የነዳጅ ኩባንያዎቹ ከዚህ በፊት ባልታዩና ባልተፈተኑ ግዙፍ መርከቦች አምነው ነዳጃቸውን አያጓጉዙም ። በሦስተኛ ደረጃ እርሱ ብድር የሚጠይቃቸው ባንኮች ስቀውበት ነው ከቢሮዋቸው የሚያስወጡት ።"

ሜሊና እንደመበሳጨት ብላ ፊቷን አጠቆረች ። "ስፒሮስ ግን በሙሉ ተስፋ ተነሳስቷል ። ስለዚህ ጉዳይ አንተ ብታዋየው ምናለ?"

ዴሚሪስ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "ተይው እያለመ ይደሰት ሜሊና ። እኔና አንቺ ስላደረግነው ውይይትም እንዲያውቅ ባይደረግ መልካም ነው" ሲል መለሰላት ።

"እሺ ኮስታ ፣ አንተው እንዳልክ !"

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ግዙፍ የነዳጅ ማጓጓዣ መርከቦችን ስለማሠራት ለመወያየት ጉዞውን ወደዩናይትድ ስቴትስ ቀጠለ ። አንድ የሚያውቀው ነገር ቢኖር ዩናይትድ ስቴትስ ካላት

የነዳጅ ክምችት ውጭና ሶቪዬት ኅብረትና ወዳጆቿ ከሚቆጣጠሩት ይዞታ ሌላ በመላው ዓለም የሚገኘው ነዳጅ ዘይት በሰባት ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር ብቻ ያለ መሆኑን ነው ። እነርሱም በኒው ጀርሴይ የሚገኘው ስታንዳርድ የነዳጅ ኩባንያ ፣ በካሊፎርኒያ ያለው ስታንዳርድ የነዳጅ ኩባንያ ፣ ገልፍ ኦይል የተሰኘው የቴክሳስ ኩባንያ ፣ ሮያል ዳች ሼልና አንግሎ ኢራንያን ኩባንያዎች ናቸው ። ከእነኚህ መካከል የአንደኞቸውን እሺታ ቢያገኝ ሌሎቹ የዚህኑ ፈለግ እንደሚከተሉ እርግጠኛ ነበር ።

* * *

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በመጀመሪያ የጐበኘው በኒው ጀርሴይ የሚገኘውን የስታንዳርድ አይል ዋና ጽሕፈት ቤት ነው ። የኩባንያው አራተኛ ምክትል ፕሬዚዳንት ከሆነው አቄን ኩርቲስ ቀጠሮ ወሰደ ።

"ምን ልርዳህ ሚስተር ዴሚሪስ?"

"ለኩባንያችሁ ትልቅ የገንዘብ ጥቅም ይሰጣል የምለው አዲስ አሳብ አለኝ ።"

"አም ይህንን በስልክ ጠቅሰህልኛል ?" አለና ኩርቲስ ሰዓቱን ተመለከተ ። "ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደስብሰባ የምገባ ስለሆነ ሐሳብህን በአጭሩ ብታስረዳኝ..."

"በጣም አሳጥረዋለሁ ። እንድ ጋሎን ድፍድፍ ቤንዚን ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ ወደምሥራቃዊው የዩናይትድ ስቴትስ የባሕር ጠረፍ ለማድረስ ሰባት ሳንቲም ትከፍላላችሁ ።"

"አም ትክክል ነው ።"

"ይህንኑ ነዳጅ ዘይት በሦስት ሳንቲም ለማጓጓዝ የሚቻልበት ዋስትና ብሰጣችሁ ምን ትላለህ?"

ኩርቲስ በመደነቅ ሳቅ አለ ። "ግን እንዲህ ዓይነቱን ተአምር እንዴት ለመፈጸም ትችላለህ?" ብሎ መልሶ ጠየቀው ።

ዴሚሪስ ቀስ ባለ አነጋገር "የአሁኑ የነዳጅ ማጓጓዣ መርከቦች በአንዴ መያዝ የሚችሉትን እጥፍ ነዳጅ መያዝ የሚችሉ ግዙፍ መርከቦች በመሥራት ። ነዳጅ ዘይታችሁን ከመሬት ለማውጣት ከሚፈጅ ባችሁ ጊዜ ባነሰ ፍጥነት ሁሉንም አጓጉዤ ከዚህ ማድረስ እችላለሁ ።"

ኩርቲስ ትኩር ብሎ እያየው ፊቱን ያጠና ነበር ። "ትላልቅ የማንንሣ መርከቦች ከየት ታገኛለህ?"

"እራሴ ልሠራቸው ነው ።"

"አዝናለሁ ፡ በዚህ ላይ ገንዘባችንን የማፍሰስ ፍላጐት የለንም..."

ዴሚሪስ አቋረጠው ። "እናንተ ምንም ገንዘብ አታወጡም ። ከእናንተ የምጠይቀው ነገር ቢኖር አውን ነዳጅ ዘይታችሁን ከምታመላል ሱበት ዋጋ በግማሽ ያነሰ እንዳንገዝላችሁ የሚያስችል የረዥም ጊዜ የኮንትራት ውል እንድትፈርሙልኝ ብቻ ነው ። ላሰብኩት ሥራ የሚረዳኝ ገንዘብ ከባንክ አገኛለሁ ።"

በመካከላቸው ለረዥም ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ። አዌን ኩርቲስ በመሳል ጉሮሮውን ጠረገ ። "ወደፎቅ እንውጣና ከጥሬዚዳንታችን ጋር ባገናኝህ የተሻለ ይመስለኛል ።"

ይህ እንግዲህ የመጀመሪያው እርምጃ ነው ። ሌሎች የነዳጅ ኩባንያዎችም በኮንስታንቲን ዴሚሪስ አዳዲስ ግዙፍ መርከቦች ነዳጃቸውን ለመጫን ጓጉ ። ስፒሮስ ላምብሩ የተሸረበበትን ተንኰል ኋላ እንደተረዳ ምንም ለማድረግ አልቻለም ። ነገሩ ከቁጥጥር ውጪ ሆኗል ። ወደዩናይትድ ስቴትስ በርሮ ከአንዳንድ አነስተኛ ኩባንያዎች ጋር በግዙፍ መርከብ ነዳጅ ማጓጓዝ ስለሚችልበት ሁኔታ ስምምነት ተፈራርሞ ነበር ። ግን የገበያውን እኖታ ዴሚሪስ አስቀድሞ ገቦበታል ።

"በእርግጥ ባልሽ ነው" አለ ላምብሩ በንዴት ። "ግን አንድ ቀን ለዚህ ለፈጸመው በደል ዋጋውን እንደሚሰጠው በመሐላ አረጋግጥልሻለሁ ።"

ሜሊና ስለተፈጸመው ነገር አዘነች ። ወንድሟንም አሳልፋ የሸጠችው መሆኑ ተሰማት ።

ስለጉዳዩ አንስታ ከባለቤቷ ጋር አተካራ በገጠመች ጊዜ ሰውነቷ ይንቀጠቀጥ ነበር ። "ሜሊና እኔ ምን ላድርግ ? እነርሱ ወደኔ መጡ እንጂ እኔ ወደነሱ አልሄድኩ ። እንዴት እምቢ ልበላቸው ታዲያ?"

ውይይቱም በዚሁ አበቃ ።

ዴሚሪስ ሜሊናን እንዴት እንደሚያጐሳቁላት ወንድሟ ላምብሩ ሲያስብ በሥራው መስክ ከተፈጸመበት በደል የበለጠ ጎሊናውን ያቆስለዋል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቅጥ ያጣ ቅንዝረኛ ነው የሚለው ላምብሩ ፡ ሁኔታውን ችላ ለማለት ሞክሮም ነበር ። በእርግጥ ወንድ አንዳንዴም መደሰት አለበት ። ቢሆንም ዴሚሪስ የሚያሳየው አይናውጣ ሴሰኛነት አሳፋሪነቱ ለሜሊና ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው የላምብሩ ቤተሰቦች ነው ። ዴሚሪስ ፡ ኖኤሌ ፖጂ ከተባለችው የፊልም ተዋናይ ጋር የጀመረው መጣጥፍ ቤተሰቡን መሳቂያ መሳለቂያ አድርጐት ሰንብቷል ። ብዙዎቹ ጋዜጦች እንደ ዓቢይ ዜና በዓምዶቻቸው ላይ አስፍረውታል ። 'አንድ ቀን' አለ ስፒሮስ ላምብሩ በአሳቡ ። 'አንድ ቀን ...'

ረዳቱ ኒኮስ ቬሪቶስ ወደላምብሩ ቢሮ ገባ ። ቬሪቶስ በዚህ ሥራ ላለፉት አሥራ አምስት ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል ። በሥራው ቀልጣፋ ሲሆን የፈጠራ ችሎታው ግን ደካማ ነው ። ስለወደፊቱ የሚያስብ አይደለም ። ወርቃማ ፀጉር እያለው መልክ መልካምነቱ ጉልቶ አይታይም ። በሁለቱ ዋርሳዎች መካከል የተፈጠረው ቅራኔ ቬሪቶስ ላሰበው ነገር ተፈጻሚነት ጥሩ አጋጣሚን ፈጥሮለታል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአሸናፊነት እንዲያበቃ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል። ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም ጥብቅ የሆኑ ምስጢሮችን ለዴሚሪስ አሳልፎ በመስጠት በምትኩ ወሮታ ይጠብቅ ነበር ።

ቬሪቶስ ወደላምብሩ ጠጋ አለና "ይቅርታ ፡ ሚስተር ቶኒ ሪዞሊ ሊያነጋግርዎ ውጭ እየጠበቀ ነው ።"

ላምብሩ ቀና አለ ። "እሺ አስገባው"

ቶኒ ሪዞሊ በአርባው አጋማሽ ዕድሜ ክልል ውስጥ ነው ። ጥሩ ቁመና ፡ ጥቁር ፀጉር ፡ ሰልካካ አፍንጫ አለው ። በደንብ የሰለጠነ ቦክሰኛ ይመስላል ። ውድ የሆኑ ሱፍ ልብስና ብጫ የሐር ሽሚዝ ለብሷል ። ለስላሳ የቆዳ ጫማ አጥልቋል ። በዝግታ የሚናገር ትሑት ነው ። ይሁንና አደገኛ የሚያስመስለው የሆነ ነገር ይታይበታል ።

"ጤና ይስጥልኝ ሚስተር ላምብሩ"

"ተቀመጥ ሚስተር ሪዞሊ"

ሪዞሊ ወንበር ሳበ ።

“ምን ልርዳህ?”

“መልካም ፡ ቅድም ለሚስተር ቬሪቶስ እንዳስረዳሁት አንድ የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ለመከናተር ፈልጌ ነበር ። በማርሴሊስ ፋብሪካ እንዳለኝ ታውቃለህ አይደል? የተወሰኑ ከባድ ማሽነሪዎችን ወደዩናይትድ ስቴትስ ለማጓጓዝ እፈልጋለሁ ። እኔና አንተ ለመስማማት የምንችል ከሆነ ወደፊትም ብዙ ሥራዎችን ላመጣልህ እችላለሁ ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ወደኋላው ተለጥጦ ከፊትለፊቱ ያለውን ሰው በትኩረት ያጠናል ።

“አንተ እንዲጫንልህ የፈለከው ዕቃ ይሄ ብቻ ነው? ሚስተር ሪዞሊ ።”

ቶኒ ሪዞሊ ግንባሩን ኮስተር በማድረግ “ምን አልክ ? አልገባኝም ።”

“የገባህ ይመስለኛል” አለው ላምብሩ ። “መርከቤ ለአንተ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም ።”

“ለምን ? ምንድነው የምትናገረው?”

“ስለሱስኛ እንክብሎች ማለቴ ነው ሚስተር ሪዞሊ ። አንተ ሱስ የሚያሲዙ እንክብሎች ነጋዴ ነህ ።”

የሪዞሊ ዓይኖች ጠበቡ ።“እብድነህ መሰለኝ ! ብዙ ሐሜቶች ስትሰማ ቆይተሃል ማለት ነው ።”

ነገሩ ከሐሜትም በላይ ነው ። ስፒሮስ ላምብሩ ስለሰውዬው ደህና አድርጎ አጥንቷል ። ቶኒ ሪዞሊ በአውሮጳ ውስጥ ዕፅ የሚያሲዙ እንክብሎች በሥውር ከሚነግዱ እውቅ ሰዎች መካከል አንዱ ነው ። ቶኒ ሪዞሊ የማፊያ አባል ነው ። ዛሬ ግን እንኳን ድርጅቱ ቃሉም ጭምር እየጠፋ በመምጣቱ ዕቃውን ለማጓጓዝ ችግር አጋጥሞታል ። ከላምብሩ ጋር የተለየ ስምምነት ለማድረግ የጓጓውም ለዚሁ ነበር ።

“ሌላ ቦታ መሄድ ያለብህ ይመስለኛል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ዓይኑ እንደፈዘዘ እዚያው እተቀመጠበት ትኩር ብሎ ላምብሩን እያየ ቀረ ። በመጨረሻም ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “መልካም” ሲል ከኪሱ አድራሻው የተፃፈበትን ካርድ አውጥቶ ላምብሩ ጠረጴዛ ላይ ወረወረ ። “አሳብህን የምትቀይር ከሆነ በዚህ አድራሻ ልታገኘኝ ትችላለህ ።” ተነስቶ ቆም ካለ በኋላ ወጥቶ ሄደ ።

ስፒሮስ ላምብሩ ካርዱን አንስቶ ሲያነብ “አንቶኒ ሪዞሊ አስመጪና ላኪ” የሚል ተጽፎበታል ። ዝቅ ብሎ በአቴንስ የሚገኝ

የአንድ ሆቴል አድራሻና የስልክ ቁጥር ሠፍሯል ።

ኒኮስ ቬሪቶስ በዚያው ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ዓይኑን አፍጥጦ የሁለቱንም ውይይት በጥሞና ይከታተል ነበር ። ቶኒ ሪዞሊ ወጥቶ ሲሄድ “በእርግጥ የሱስ…”

“አዎ ፡ ሚስተር ሪዞሊ ሄሮይን ይነግዳል ። ባንዱ መርከብ ላይ እንኳን ሞኒንስት ብንገኝ መንግሥት መርከቦቻችንን በሙሉ ከትራንስፖርቱ የንግድ ዓለም ያግድብናል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ከላምብሩ ቢሮ የወጣው በጣም ተበሳጭቶ ነው ። ‘ያ ደደብ ግሪክ እንደአንድ ገልቱ ገበሬ አደረገኝ አይደል! ስለሱስ አስያዥ መድኃኒቶቹ እንዴት ለማወቅ ቻለ? ወይኔ! ይህን አሥር ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ትልቅ ጭነት እንዴት አድርጌ ነው ኒውዮርክ ለማድረስ የምችለው ? የሚከታተሉን ኃይሎች ደግሞ በመላ አቴንስ ውስጥ ተሰራጭተው አስጨንቀውናል ። ወደ ሲሲሊ ስልክ መደወል አለብኝ ’ አለ በአሳቡ ።

ቶኒ ሪዞሊ ከዚህ በፊት ለጭነት ጠይቆ እምቢ ያለው የለም ። እዚህም እምቢ እባላለሁ ብሎ ፍፁም አልጠረጠረም ። እራሱን ዘለዓለም እንደአሸናፊ ነበር የሚቆጥረው ።

ያደገው ኒውዮርክ ውስጥ ከማንሃታን በስተምዕራብ በኤይትዝ ጐዳናና በሀድሰን ወንዝ መካከል በምትገኘው ሄልስ ኪችን በምትባል ሥፍራ ነው ። በስተሰሜንና በስተደቡብ በቱዌንቲ ስርድና ፡ ፊፍቲ ናይንዝ ጐዳናዎች ትዋሰናለች ። ሄልስ ኪችን በከተማ መሐል የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት ለማለት ይቻላል ። በቡድን በቡድን የተደራጁ ፡ ጐጥርስ ፡ ፓርሎር ሞብ ፡ ጐነላስ ፡ ሮድስ ጋንግ የሚል ስያሜ ለእራሳቸው የሰጡ ዱርዬዎች የበላይነት የሰፈነባት ናት ። በከተማዋ ውስጥ በመቶ ዶላር ውል ሰው ማስገደል ይቻላል ።

በሄልስ ኪችን የሚገኙ ነዋሪዎች ፅዳት በሌላቸው ቤቶች የሚኖሩ ሲሆኑ በአይጥ በቅማልና በሌሎች ተባዮች የተወረሩ ናቸው ። የገላ መታጠቢያ ሥፍራዎች የሉባትም ። ወጣቶች ገላቸውን የሚታጠቡት ከሀድሰን ወንዝ ዳርቻ ሆነው ነው ። ከፋብሪካ ተለቆ በሄልስ ኪችን ጐዳናዎች ሥር በቱቦ የሚጓዘው ቆሻሻ ፡ ሞተው የጠነቡ እንስሳት ፡ አካላቸው የፈረሰ ድመቶች ፡ የሸተቱ ውሾች ሁሉ ተጠራርገው የሚገቡት ከዚሁ ወንዝ ውስጥ ነው ።

በከተማዋ ጐዳናዎች ላይ ልዩ ልዩ ትዕይንቶች ሳያቋርጡ ይታያሉ ። እሳት ተነስቶ የእሳት አደጋ መኪና ሲሯሯጥ… ቤት ጣሪያ ላይ ዱርዬዎች ሲደባደቡ … የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ሲፈጸም… ከመንገዱ ዳር ኳስ ሲጠለዝ … ደንብሮ የሮጠ ፈረስ ለመያዝ ሲሮጥ ፡ ተባርሮ ማባረር…ተኩስ …ሕፃናት በመኪና መንገድ በቤቶች ጣሪያ ላይና አነስተኛ ሜዳዎች ሲሯሯጡ…። ኖርዝ ሪቨር እየፏሸ ሲፈስ ፡ በመንገድ ዳር ሲፀዳዱ ። ቶኒ ሪዞሊ ያደገው እንግዲህ በዚህ ዓይነት አካባቢ ነው ።

* * *

ቶኒ ሪዞሊን ዘወትር ትዝ የሚለው ነገር በከተማዋ ጐዳና ላይ ሲሄድ ተመትቶ መውደቁና የወተት መግዣ ገንዘቡን መዘረፉ ነው ። ያኔ የሰባት ዓመት ልጅ ነበረ ። ጠንቆቹ ታላላቆቹ ነበሩ ። ወደትምህርት ቤት በሚወስደው ጐዳና ተቆጣጣሪ እንደሌለው ሁሉ የትምህርት ቤት ግቢውም የጠብ መድረክ ነበር ። ሪዞሊ ዕድሜው አሥራ አምስት ዓመት ሲሞላው ሰውነቱ ፈረጠመ ፡ ለድብድብ የሚያበቃ ጥሩ ስልትም ቀሰመ ። መደባደብ ደስ ያሰኘዋል ። ብዙ ጊዜም አሸናፊ መሆኑ የበላይነት ስሜት እንዲሰማው አድርጐታል ። እርሱና ጓደኞቹ ብዙ ጊዜ በስቲልማን ጀምናዝየም የቦክስ ግጥሚያ ያሳያሉ ።

ብዙ ተመልካች ወደጀምናዚየሙ እየጐረፈ ለሚደግፈው ተሳቻሽ ድጋፍ ይሰጣል ። ፍራንክ ኮስቴሎ ፡ ጆ አዶኒስና ለኪ ሉቺያኖ በወር አንዴ ወይም ሁለቴ ወደጀምናዚየሙ እየሄዱ ግጥሚያውን ይመለከቱ ነበር ። ወጣቶቹ የሚያሳዩት የቦክስ ግጥሚያ ይማርካቸዋል ። በእነኚህ ውድድሮች ውስጥ ቶኒ ሪዞሊ ብዙ ጊዜ በማሸነፉ ተመልካቹ እየወደደውና እያደነቀው መጣ ።

አንድ ቀን ሪዞሊ በመቀየሪያ ክፍል ውስጥ ልብሱን ሲቀይር ፍራንክ ኮስቴሎና ለኪ ሉቺያኖ የሚያደርጉትን ውይይት በጨረፍታ ሰማ ።

“ጨጨው ልጅ የወርቅ ማዕድን ነው ።” አለ ሊቺያኖ ።

“ባለፈው ሳምንት በእርሱ ስም ተወራርጄ አምስት ሺህ ዶላር በላሁ”

“ከሉአ ዶሜኒክ ጋር ሲጋጠም እርሱ ያሸንፋል ብለህ ልትወራረድ ነው?”

“ያለጥርጥር ። ከአሥር ሰው ጋር በብዙ ሺህ ዶላር እወራረዳለሁ ። ምን ነካህ ሪዞሊ ያሸንፋል ።”

የንግግሩ ትርጉም ለቶኒ ሪዞሊ ግልፅ አልነበረም ። ወደታላቅ ወንድሙ ጂኖ በመሄድ የሰማውን ነገር አጫወተው ።

“የክርስቶስ ያለህሎ” አለ ወንድሙ በመገረም ። “ሰዎቹ በትልቅ ገንዘብ በአንተ ላይ እየተወራረዱ ነው ።”

“ግን ለምን፣ እኔ ፕሮፌሺናል አይደለሁም ።”

ጂኖ ለአፍታ ጊዜ አሰበ ። “በውድድሩ ተሸንፈህ አታውቅም አይደል ቶኒ?”

“በፍጹም”

“ምናልባት በፊት በመጠነኛ ገንዘብ ይሆናል የተወራረዱብህ ። በኋላ የአንተን ውጤት ሲያዩ በከፍተኛ ገንዘብ መወራረድ ጀመሩ ።”

“ታዲያ ለኔ ምን ይጠቅመኛል?” አለ ወጣቱ ልጅ ።

ጂኖ እጁን ያዝ አደረገ ። “ይጠቅምህ ይሆናል ። ሁለታችንንም ይጠቅመናል ። ብትሰማኝ ይሻላል አንተ ጉርባ…”

* * *

ከሉአ ዶሜኒክ ጋር የተደረገው የቦክስ ውድድር የተካሄደው በስቲልማን ጀምናዚዬም ውስጥ ዓርብ ዕለት ከሰዓት በኋላ ነበር ። ውድድሩን ለመመልከት እንፍራንክ ኮስቴሎ ፡ ጆ አዶኒስ ፡ አልበርት አናስቴዚያ ፡ ሉኪ ሉቺያኖና ሜዬሮ ላንስኪ ተገኝተዋል ። ሁሉም የወጣቶቹ የእርስ በእርስ አቦቃቀስ ስልት እርካታን ሰጥቷቸዋል ። የበለጠ ያስደሰታቸው ደግሞ ከዚህ ውድድር ብዙ ገንዘብ ለማግኘት መቻላቸው ነው ።

የሉአ ዶሜኒክ ዕድሜ አሥራ ሰባት ዓመት ሲሆን ከቶኒ በአንድ ዓመት ይበልጣል ። በክብደቱም ከቶኒ ሪዞሊ በአምስት ፓውንድ ይልቃል። ሆኖም የቶኒ ሪዞሊን የአቦቃቀስ ስልትና ጥበብ ዶሜኒክ ሊቋቋመው አልቻለም ።

ውድድሩ አምስት ዙር ነበረው ። በመጀመሪያው ወጣቱ ቶኒ በቀላሉ አሸነፈ ። በሁለተኛውም ዙር ተመሳሳይ ውጤት አገኘ ። በሦስተኛውም እንዲሁ ። ተወራራጆቹ ከአሁኑ ገንዘባቸውን መቁጠር ጀምረዋል ።

"ልጄ ወደፊት የዓለም ቻምፒዮን ሊሆን በሚችልበት ደረጃ እየተመነደገ ነው" አለ ሉኪ ሉቺያኖ ድምፁን ከፍ አድርጉ ። "እርሱ ያሸንፋል ብለህ በምን ያህል ተወራረድክ?"

"አሥር ሺህ ዶላር" አለ ፍራንክ ኮስቴሎ ። "ጥሩ ውጤት የማገኘው አሥራ አምስት ለአንድ ሲሆን ነው ። ልጄ እንደሆነ እስካሁን ጥሩ ስም አግኝቷል። ምን ዓይነት መጥፎ ነገር እንደሚጠብቀው ዙር አጋማሽ ላይ ሉአ ዶመኒክ ቶኒ ሪዞሊን ዘረረው ። አጫዋቹ መቁጠር ጀመረ .... በስጋት ከው ያሉትን ተመልካቾች እየተመለከተ ።

"ተነስና ቁም አንተ አህያ !" አለና ጆ አዶኒስ ጮኸ ። "ተነስና ተፎቀስ !"

መቁጠሩ ቀጠለ ። ቀስ ባለ ጉዞ ቆጠራው አሥር ሞላ ። ቶኒ ሪዞሊ ሕሊናውን ስቶ ተዘርሯል ።

"የውሻ ልጅ ፡ ምን ዓይነት መጥፎ ምት ናት!"

ሰዎቹ ኪሣራቸውን መደመር ጀመሩ ። በቀላሉ የማይገመት ገንዘብ ተበልተዋል ። ጂኖ ፡ ቶኒ ሪዞሊን ተሸክሞ ወደአንዱ የማረፊያ ክፍል ወሰደው ። ዓይኔን የገለጥኩ እንደሆነ ሰዎቹ ደህና መሆኔን አውቀው አደጋ ያደርሱብኛል በሚል ፍርሀት ቶኒ ዓይኑን እንደከደነ ቀረ ።

በሰላም እቤቱ መድረሱን ካረጋገጠ በኋላ ነው መዝናናት የጀመረው።

"ሠራንላቸው !" አለ ወንድምዬው በደስታ ስሜት ። "ምን ያህል ገንዘብ እንዳገኘን ታውቃለህ? ወደ አንድ ሺህ ዶላር የሚጠጋ ።"

"እኔ አልገባኝም ። እኔ ..."

"ከእነርሱው ጋር ከነበረ አራጣ አበዳሪ ገንዘብ ተበደርኩና ዶሚኒክን ደግፌ በመወራረድ አሥራ አምስት በአንድ ውጤት አሸነፍኩ ። አሁን ሀብታም ሆነናል ።"

"ካወቁ አይናደዱብንም ?" ሲል ቶኒ ጠየቀ ።

ጂኖ ሳቅ አለ ። "ሊያውቁ አይችሉም ።"

በሚቀጥለው ቀን ቶኒ ሪዞሊ ከትምህርት ቤቱ ሲወጣ መታጠፊያ ኩርባው ላይ አንዲት ጥቁር ሊሞሲን መኪና ቆማ ጠበቀችው ። ሉኪ ሉቺያኖ ከኋላ መቀመጫ ላይ ተቀምጧል ። በእጅ ምልክት ወደመኪናው ጠራው ። "ግባ።"

የቶኒ ሪዞሊ ልብ በኃይል መምታት ጀመረች ። "አልችልም ሚስተር ሉቺያኖ ፡ እዘገያለሁ ..."

"ግባ ብየሃለሁ ።"

ቶኒ ሪዞሊ ከሊሞሲኑ ውስጥ ገባ ። ሉኪ ሉቺያኖ ሾፌሩን "ዙሪያ ውን ንዳ" ብሎ አዘዘው ።

እግዚአብሔር ይመስገንና ራቅ ወዳለ ቦታ አልተወሰደም ።

ሉቺያኖ ወደልጁ ዞር አለ ። "አውቀህ ተሸነፍክ አይደል ?" አለው በቀጥታ ። ሪዞሊ ደንገጥ አለና "አይደለም ጌታዬ ፡ እኔ ..."

"ልታታልለኝ አትሞክር ። ከውድድሩ ምን ያህል ገንዘብ አገኘህ?"

"ምንም ሚስተር ሉቺያኖ ። እኔ ..."

"ደግሜ ልጠይቅህ ። ተሸናፊ በመሆን ምን ያህል ገንዘብ አገኘህ ?"

ልጁ ትንሽ አመነታና "አንድ ሺህ ዶላር" ብሎ መለሰ ።

ሉኪ ሉቺያኖ ከት ብሎ ሳቀ ። "አነስተኛ ገንዘብ ናት ። እኔ እንኳ የገመትኩት ... በነገራችን ላይ ስንት ዓመትህ ነው ?"

"አሥራ ስድስት ።"

"ለአሥራ ስድስት ዓመት ጉረምሳ ያን ያህል ገንዘብ በቂው ነው ። ለእኔና ለጓደኞቹ ብዙ ገንዘብ ልታስገኝ እንደምትችል ታውቃለህ ?"

"አዝናለሁ ። እኔ ..."

"እርሳው ። አንተ ብሩህ ተስፋ ያለህ ልጅ ነህ ። ከፊትህም ጥሩ ዕድል ይጠብቅሃል ።"

"አመሰግናለሁ።"

"እኔ ያወቅሁትን ለማንም አላወራም ። ጓደኞቹ ቢሰሙ ድራሽህን ነበር የሚያጠፉት ።"

"ሰኞ መጥተህ እንድታነጋግረኝ እፈልጋለሁ ። እኔና አንተ ወደፊት ብዙ የምንሰራቸው ነገሮች አሉ ።"

ከሳምንት በኋላ ቶኒ ሪዞሊ ከሉኪ ሉቺያኖ ጋር መሥራት ጀመረ ። በመጀመሪያ ሪዞሊ ዝቅተኛ ሥራ ላይ ነበር የተመደበው ። ቀስ በቀስም ውሳኔ ሰጭ ከመሆን ደረጃ ደረሰ ። ወጣቱ ብሩህ አእምሮ ያለውና ፈጣን በመሆኑ ሉቺያኖ የሚያሠማራውን ቡድን እየመራ የተሳካ ውጤት ያስገኝ ነበር ።

ሉኪ ሉቺያኖ በወንጀል ተከሶ ወደወህኒ ቤት ሲላክ ቶኒ ሪዞሊ እርሱን ተክቶ የሉቺያኖን ድርጊት መምራቱን ቀጠለ ።

ጓደኛሞቹ ቁማር ይጫወታሉ ፣ አራጣ ያበድራሉ ፣ በሴተኛ አዳሪዎች ይነግዳሉ ፣ በሕገወጥ መንገድ ትርፍ የሚያስገኝ ማንኛውንም ነገር ያከናውናሉ ። ሱስ የሚያስይዙ ዕፆች የመነገዱ ነጥብ ተነስቶ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል ። ሆኖም አንዳንዶቹ የቡድኑ አባሎች ይህንን ሥራ ለማከናወን አጥብቀው በመጠየቃቸው በግል ሊያካሄዱ እንደሚችሉ ተፈቅዶላቸዋል ።

አሳቡ በቶኒ ሪዞሊ ተደጋፊነትን አግኝቷል ። ሆኖም በሱስ አስያዥ ንግድ ውስጥ የተሠማሩት ሰዎች አሠራር የተዝረከረከ በመሆኑ ሁሉም ጉዳውን በየፊናው እንዳያሽከረክር ትክክለኛ አመራር ማግኘት እንዳለባቸው ተረድተዋል ።

ይህን በሚመለከትም ከአንድ ውሳኔ ላይ ተደረሰ ።

ቶኒ ሪዞሊ ማንኛውንም ነገር ከመጀመሩ በፊት ጥናት ያካሄዳል ። ሥራውን የጀመረው ስለሄሮይን የተፃፉትን ጽሁፎች በደንብ አንብቦ በቂ እውቀት ከሰበሰበ በኋላ ነው ።

ፈጣን በሆነ ሂደት ሱስ የሚያሲዘው ሄሮይን ከሌሎቹ ዓይነቶች በይበልጥ ተፈላጊ እየሆነ መጥቷል ። ማሪዋናና ኮኬይን ከፍተኛ የማደንዘዝ ችሎታ ቢኖራቸውም ሄሮይን ልዩ ስሜትን ፈጥሮ በተለየ ዓለም ውስጥ በማንሳፈፍ ረገድ ይበልጣቸዋል ። ሲወሰድ አያሳምምም ፣ ችግር አያስከትልም ፣ ጥንቃቄ ማድረግም አያሻም ። በሄሮይን ሱስ የተያዙ ሰዎች ለመግዛት ሲሉ ንብረታቸውን ሁሉ ይሸጣሉ ፣ መሸመቻ ለማግኘት የሚቻላቸውን ሁሉ ይዘርፋሉ ። አሰቃቂ ወንጀሎችን ይፈጽማሉ ። ለእነርሱ ሄሮይን ሃይማኖታቸው ነው ፤ ሄሮይን እስትንፋሳቸውም ነው ።

ሄሮይን የሚሠራበትን ዕፅ በብዛት ከሚያበቅሉት አገሮች መካከል ቱርክ አንዷ ናት ።

ጓደኛማቾቹ በቱርክ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል ። ሪዞሊ የቡድኑ አባል የሆነውን ፔቴ ሉካን አነጋግሯል ።

“እንግዲህ እኔም እጄን ላስገባበት ነው” አለ ሪዞሊ ። “የማደርገው ነገር ሁሉ ለቡድኔ ጥቅም እንደሆነ ግን እንድታውቀው እፈልጋለሁ ።”

“ቶኒ አንተ ጥሩ ልጅ ነህ ።”

“አንዳንድ ነገሮችን ለመመልከት ወደቱርክ ለመሄድ እፈልጋለሁ።

ጉዞውን ልታዘጋጅልኝ ትችላለህ ?”

በዕድሜ ጠና ያለው ሰውዬ ትንሽ አመነታ ። “መልዕክት አስተላልፋለሁ ። ግን ቶኒ እነርሱ እንደእኛ አይደሉም ። ግብረገብ ጨርሶ የላቸውም። እንስሶች ሆነዋል ለማለት ይቻላል ። የሚጠራጠሩህ ከሆነ ወዲያውኑ ይገድሉሃል ።”

“በጣም እጠነቀቃለሁ ።”

“ይሻልሃል ።”

ከሁለት ሳምንታት በኋላ ቶኒ ሪዞሊ ወደ ቱርክ መንገዱን ቀጥሏል ።

የተጓዘው ወደ ኢዝሚር ፣ አፍዮንና ኤስኪሲሂር ነው ። እነኚህ ሥፍራዎች ለሄሮይን መሥሪያ የሚያገለግል ተክል የሚበቅልባቸው ቦታዎች ናቸው ። በመጀመሪያ ሰዎቹ ሪዞሊን የተቀበሉት በትልቅ ጥርጣሬ ነበር ። እርሱ የማይታወቅ ባዳ ነው ፤ እነርሱ ደግሞ እንግዳ ሰው ማየትን ልቦናቸው አይፈቅድም ።

“አብረን የምናከናውናቸው ብዙ ሥራዎች ይኖሩናል” አለ ሪዞሊ ። “የተከሉን እርሻ ለመጐብኘት እፈልጋለሁ።”

ተጠያቂዎቹ ግራ ተጋቡ ። “ስለምትጠይቀን የተክል እርሻ ምንም የምናውቀው ነገር የለም ። ጊዜህን ከምትገድል ወደመጣህበት ብትመለስ ይሻላል ።”

ሪዞሊ ግን ተስፋ አልቆረጠም ። ብዙ የሰልክ ጥሪዎች ተካሄዱ ፣ ግልጽ ባልሆኑ ልዩ ምልክትና ቃላትም የቴሌግራሞች ልውውጥ ተደረገ። በመጨረሻ ቱርክን ከሶሪያ ጋር በሚያዋስነው ድንበር አካባቢ የሚገኘውን የእርሻ ቦታ እንዲጐበኝ ተፈቀደለት ። እርሻው የሚካሄደው በአካባቢው ካሉት ባለርስት ባላባቶች አንዱ በሆነውና በካሬላ ነው ።

“እኔ አልገባኝም” አለ ቶኒ ። “ከዚህ አበባ እንዴት አድርጋችሁ ሄሮይን ትሠራላችሁ ?”

ነጭ ረዥም የሥራ ኮት የለበሰ አንድ ሳይንቲስት ስለአዘገጃጀቱ ሲያስረዳው “ሚስተር ሪዞሊ ዝግጅቱ ብዙ ደረጃዎች አሉት ። ሄሮይን የሚገኘው ከኦፒየም ሲሆን ኦፒዬምን ለመፍጠር ደግሞ ሞርፊንንና አሴቲክ አሲድን ማዋሃድ ያስፈልጋል ። ሄሮይን የሚሠራበት ተክልም ፓፓቨር ሶምኒፈረም ተብሎ ይጠራል ። ይህም ሲተረጐም እንቅልፍ ሰጪ አበባ ማለት ነው ። ኦፒዬምም ስያሜውን ያገኘው ኦፓስ ከሚለው የግሪክ ቃል ነው ። በግሪክኛ ኦፓስ ማለት ጭማቂ ማለት እንደሆነ

ይነገራል ።”

“ገባኝ።”

የማምረት ተግባሩ በሚከናወንበት ወቅት ቶኒ ተጠርቶ የካፊላን ዋና የእርሻ ቦታ እንዲጐበኝ ተደረገ ። እያንዳንዱ የካፊላ ቤተሰብ በቱርክ ቋንቋ ‘ሲዝጊ ኪካክ’ የሚሉትን ፣ የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ለሰው ገላ መቁረጫ የሚጠቀሙበትን ቢላዋ የመሰለ ጩቤ ይይዛል ። ይህም ጩቤ ተክሉን በትክክል የሚፈልጉበት ቦታ ለመቁረጥ ይረዳቸዋል ። ካፊላ ስለሁኔታው ሲያስረዳ “ተክሉ እንደደረሰ በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ መቆረጥ አለበት” ብሎ ተናገረ ።

በቤተሰቡ ውስጥ ዘጠኝ ሰዎች ይገኛሉ ። እያንዳንዱ ስው የተክሉ አበባ ፣ ጊዜው ሳያልፍበት በወቅቱ እንዲሰባሰብ ለማድረግ ሳይታክት ይሠራል ። በአካባቢው ያለው አየር ከተክሉ በሚወጣው ልዩ ሽታ የተበከለ ነው ። ሽታውም የመጫጫን ስሜትን በሰውነት ላይ ይፈጥራል ።

ሪዞሊ የለከረ መሰለው ። “ጥንቃቄ አድርግ” አለው ካፊላ ። “እንቅልፍ እንዳይዝህ ። በዚህ ሁኔታህ እርሻው ላይ እንቅልፍ ወስዶህ ከተጋደምክ ሁለተኛ ተመልሰህ አትነቃም ።”

የተክሉ ቆረጣ በሚከናወንበት የሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ በእርሻው አካባቢ ያሉ የቤቶች በሮችና መስኮቶች ጥርቅም ተደርገው መዘጋት ይኖርባቸዋል ።

የተቆረጠው የተክሉ አናት ተሰብስቦ ከእርሻው ላይ ከተነሳ በኋላ የሚያጣብቀው ነጭ ሙጫ መሰል ነገር ወደሞርፊነት ፣ ከዚያም ወደሄሮይን ሲለወጥ ሪዞሊ በጥሞና ተመለከተ ። ሥራውም የሚከናወነው በላቦራቷር ውስጥ ነው ።

“እንዲህ ነው ለካ !” አለ ሪዞሊ ።

ካፊላ በአሉታ ጭንቅላቱን ነቀነቀና “እንዲህ ብቻ አይደለም ጓዴ ። ይህ ገና የመጀመሪያው ነው ። ሄሮይኑን መጭመቅ ቀላሉ ተግባር ነው ። አስቸጋሪው ሳይያዙ ወደሚፈለገው ሥፍራ ማጓጓዙ ነው ።”

ቶኒ ሪዞሊን አንድ የተለየ ስሜት ሰውነቱን ወረረው ። አሁን የሱን ችሎታ የሚጠይቀውን ሃላፊነት ሊረከብ ነው ። እስካሁን እዚህ ግቡ በማይባሉ ዱርዬዎች ነው ሲካሄድ የነበረው ። ፕሮፌሽናል ሰው ሥራው እንዴት ሊካሄድ እንደሚችል ሊያሳያቸው ነው ።

“እንዴት ነው የምታጓጉዙት ?”

“ብዙ ዘዴዎች አሉ ። በሞንት መኪና ፣ በአውቶቡስ ፣ በባቡር ፣ በመኪና ፣ በበቅሎ ፣ በግመል ...”

“በግመል ?”

“ሄሮይኑን በቆርቆሮ እሽገን በግመል ሆድ ውስጥ በመቅበር ኬላዎችን እናሻግር ነበር ። የኬላ ዘቦች የብረት መመርመሪያ መጠቀም ሲጀምሩ ደግሞ ቆርቆሮውን በላስቲክ ከረጢት ተካን ። በጉዞአችን መጨረሻ ላይ ግመሎቹን እንገድላለን ። ችግሩ ፣ አንዳንድ ጊዜ የፕላስቲኩ ከረጢት በግመሎቹ ሆድ ውስጥ ፈንድቶ ያሰክራቸውና ኬላ ላይ ሲደርሱ ግማሾቹ ቀጥ ብለው ይቆማሉ ፤ በዱላ ቢመቱ አይንቀሳቀሱም ። በዚህም የተነሳ በዘቦቹ የመያዝ አደጋ ያጋጥማል ።”

“የትኛውን የጉዞ መሥመር ነው የምትጠቀሙት ?”

“ባብዛኛው የምንጠቀምባቸው መሥመሮች አሌፓ ፣ ቤይሩት ፣ ስታንቡልና ማርሴለስ ናቸው ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ከስታንቡል ወደግሪክ ይጓዙና በሲሲሊ አድርገው የአትላንቲክ ውቅያኖስን ያቋርጣሉ ።”

“ስለትብብርህ አመሰግናለሁ” አለ ሪዞሊ ። “ለጓዶቼ እነግራቸዋለሁ ። ሌላ እንድታደርግልኝ የምፈልገው ነገር አለ ።”

“እሺ ።”

“በሚቀጥለው ጉዞህ አብሬ ብጓዝስ ?”

ለረዥም ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ። “እደነኛ ሊሆንብህ ይችላል።”

“እስቲ ዕድሌን ልሞክር ።”

ቶኒ ሪዞሊ ፣ በሚቀጥለው ቀን ከሰዓት በኋላ ከአንድ ግዙፍ ፣ ሪዛም ሰው እንዲተዋወቅ ተደረገ ። “የአፍዮኑ ሙስጠፋ ይባላል ። በቱርክ ቋንቋ አፍዮን ማለት እጥየም ማለት ነው ። ሙስጠፋ አደንዛዥ ዕፆችን ደብቆ ድንበር የማሻገር ጥበብ ከተካኑት ሰዎቻችን መካከል አንዱ ነው ።”

“እዎ ጥበበኛ መሆን ያስፈልጋል ።” አለ ሙስጠፋ በለሆሳስ ።

“ብዙ አደጋ ሊያጋጥም ይችላል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ፈገግ አለ ። “የሚያስገኘው ጥቅምም ከሚያጋጥመው አደጋ ይበልጣል አይደል ?”

ሙስጠፋ ጀነን ብሎ መለሰ ። “አንተ የምታወራው ስለገንዘብ ነው። ለእኛ አጢየም ከገንዘብ የበለጠ አዝመራ ነው ። ስለዚህ ተክል ያልታወቀ አንድ ምስጢር አለ ። ተክሉ ምግብንም ሊተካ የሚችል ነው ። ከዕፁ

የሚወጣው ነጩ ፈሳሽ በትንሹ ቢወሰድ እንደ መድኃኒትነት የሚያገለግል የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ። በእፍ ወይም በቆዳ ተወስዶ የሆድ መረበሽን ፣ ጉንፋንን ፣ ትኩሳትን ፣ የተለያዩ ሕመሞችን ፣ ወለምታዎችን ይፈውሳል ። ሆኖም ጥንቃቄ መወሰድ አለበት ። ከበዛ ጠቅላላ ሰውነትን ማደንዘዙ ብቻ ሳይሆን ብልትን ለዘለዓለም ያከላሻል ፤ ዘር አልባ አድርጉም ያስቀራል ። በቁርክ ውስጥ ደግሞ ከመኮላሸት የበለጠ የሚያሳፍር ነገር የለም ።

“ልክ ነህ ።”

እኩለ ሌሊት ላይ ከአፍዮን ጉዞ ተጀመረ ። ገበሬዎች በመሥመር ገብተው ከሙስጠፋ ጋር በድቅድቅ ጨለማው ውስጥ መንገዱን ተያይዘ ውታል ። በቅሎዎቹ እስከአፍ ጢማቸው ነው አፒየሙን የተጫኑት ። ሰባቱ የተሸከሙት ሞኑት በጠቅላላው 350 ኪሎ ግራም ይመዝናል ። ከአፒየሙ የሚወጣው የተለየ ሽታ በቅሎዎቹ ያለፉበትን አካባቢ ሁሉ ያውደዋል ። የሞኑቱን ደህንነት እንዲጠብቁ በሙስጠፋ የተቀጠሩት አጃቢ ገበሬዎች የጦር መሣሪያ አሟልተው ታጥቀዋል ።

“በዛሬ ጊዜ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋል” አለ ሙስጠፋ ለሪዞሊ። “ኢንተርፖልና ሌሎችም የፖሊስ ኃይሎች እያሳደዱን ነው ። በድሮ ጊዜ ቀላል ነበር ። በገጠርና በከተማ መሃል ጥቁር ቀለም በተቀባ ሳጥን በይፋ እናጓጉዝ ነበረ ። በጉዳናዎች ላይ ስናልፍ ሌሎች ሰዎችም ሆኑ ፖሊሶች ቆባቸውን እያነሱ የአፒየሙን ሬሣ እጅ ሲነሱ መመልከቱ ያስቀን ነበር ።”

አፍዮን በቁርክ ምዕራባዊ ክፍል ከሱልጣን ተራራ ሥር የተቆርቆረ ረና ከሌሎች ክፍላተ ሀገራት ታላላቅ ከተሞች ጋር መገናኛ የሌለው ኋላቀር ክፍለ ሀገር ነው ።

“ያለንበት ተራራና ሸንተረር ለሥራችን በጣም ምቹ ነው” አለ ሙስጠፋ ። “በቀላሉ ልንገኝ አንችልም ።”

በቅሎዎቹ ጭር ባለው ቁልቁለትና አቀበት ላይ በዝግታ እየተጓዙ ከሦስት ቀን በኋላ ከሶሪያ ድንበር ላይ ተደረሰ ። እዚያም ጥቁር ልብስ የለበሰች ሴት አገኙ ። ባዶ የስንዴ ዱቄት ጆንያ የተጫነ ፈረስ እየነዳች ወደእነርሱ መጣች ። ከጠንካራ ቃጫ የተሠራ 200 ሜግ ርዝመት ያለው ገመድ ከፈረሱ የከርቻ ጫፍ ላይ ታስሯር ሌላውን ጫፍ ሙስጠፋና አምራ

አምስት ጓዶቹ ባንዳንድ እጃቸው ይዘውታል ። በሌላ እጃቸው ደግሞ አምስት ፓውንድ የሚመዝን አፒየም በጆንያ አንጠልጥለው አጉንብ ሰው በደፈጣ ይጓዛሉ ። ሴትዮዋና ፈረሱ ፣ የተቀበረው ፀረ ሰው ፈንጂ እንዳይፈነዳ ጥንቃቄ እያደረጉ የበግ መንጋ ተነድቶበት የነበረውን ቀጭን መንገድ እየተከተሉ ከሕገወጥ ነጋዴዎቹ ፊት ፊት ይጓዛሉ ። በፈረሱ የተወጠረው ገመድ ላልቶ መሬት ከነካ ከፊት ለፊትነጭ ለባሾች ወይም ወታደሮች አሉ የማለት ምልክት ነው ። በአጋጣሚ ሴትዮዋ ብትያዝ እንኳ ሕገወጦቹ በቀላሉ ድንበሩን ተሻግረው ሊያመልጡ ይችላሉ ።

በፀረ ሰው ፈንጂ የታጠረውን የኪሊስን ድንበር መቆጣጠሪያ ኬላ አለፉ ። ይህን በወታደሮች ጥብቅ ቁጥጥር ሥር ያለውን ኬላ እንደተሻገሩ ሦስት ማይል ስፋት ወዳለው ነፃ ክልል ደርሰው ከሚጠብቋቸው የሶሪያ ኮንትሮባንዲስቶች ጋር ተገናኙ ። ሁሉም የአፒየሙን ሽክም አውርደው ተቀባዮቻቸው ያመጡላቸውን ራኪ መጠጥ እየተቀባበሉ ጠጡ ። አፒየሙ ሲመዘን ፣ ሲገለበጥ ፣ ሲታሠርና ከሶሪያ ከመጡ አህዮች ላይ ሲጫን ሪዞሊ ቆሞ ይመለከት ነበር ። ሥራው ተጠናቀቀ ።

‘መልካም እንግዲህ’ አለ ሪዞሊ በአሳቡ ። ‘አሁን ደግሞ ታይላንድ ያሉ ልጆች እንዴት እንደሚሠሩ እንይ ።’

የሚቀጥለው የሪዞሊ ጉዞ ወደ ባንኮክ ነው ። ታማኝነቱ እንደተረጋገጠ ከታይ የዓሣ ማስገሪያ ጀልባዎች አንዷ ላይ እንዲሳፈር ተፈቀደለት። በላስቲክ ተጠቅልሎ በባዶ ነጭ ጋዝ ቆርቆሮ ውስጥ የተወረፈ አደንዛዥ ዕፅ በጀልባዎቹ ላይ ተጭኗል ። ጀልባዎቹ ሆንግ ኮንግ ሲደርሱ ቆርቆሮዎቹ ሊማና ላድሮን ደሴት አካባቢ ጥልቀት ከሌለው ውሃ ውስጥ በተርታ ይወረወራሉ ። የሆንግ ኮንግ ዓሣ አጥማጆችም በቆርቆሮዎቹ ሜፍ ላይ ያሉትን ቀለበቶች በመንጠቆአቸው እየነከሱ በቀላሉ ወደ ውጭ ያወጧቸዋል ። “ይኸም መጥፎ አይደለም” አለ ሪዞሊ ። “ቢሆንም ከዚህ የተሻለ መንገድ መኖር አለበት ።”

አብቃዮቹ ሄሮይንን ‘ፈ’ ወይም ‘ፈረስ’ ይሉታል ። ለቶኒ ሪዞሊ ግን ሄሮይን ወርቅ ነው ። ከዚህ ምርት የሚገኘው ትርፍ ለሰሚ ያስደንግጣል ። የአፒየምን ተክል የሚያበቅሉ ገበሬዎች አሥሩን ኪሎ በሦስት መቶ ዶላር ይሸጡታል ። አሥሩ ኪሎ ሄሮይንም በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ

ላይ በሚሸጥበት ወቅት ግን ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ዶላር ከፍ ይላል ።

‘ቀላል ነው’ አለ ሪዞሊ በአሳቡ ። ‘ካሬላ እውነቱን ነው ። ሳይያዙ ኬላዎቹን ማላለፉ ላይ ነው ቁምነገሩ ።’

ይህ እንግዲህ ከአሥር ዓመታት በፊት ሲጀመር የነበረ ሁኔታ ነው። አሁን ግን ከዚያን ጊዜ በበለጠ አስቸጋሪ ሆኗል ። ኢንተርፖል ግለትም ዓለም አቀፍ የፖሊስ ኃይል በአደንዛዥ ዕፅ ነጋዴዎች ላይ የሚደረገውን ከትትል ቅድሚያ ሰጥቶታል ። የአደንዛዥ ዕፆች መተላለፊያ ናቸው ተብለው ከሚገመቱ ወደቦች የሚነሱ መርከቦች ትንሽ ጥርጣሬ ካሳደሩ እንዲቆሙ ተደርገው በጥብቅ ይፈተሻሉ ። ሪዞሊ ወደስፔርስ ላምብሩ የመጣውም ይህን ስጋት ለማስወገድ ነበር ። የላምብሩ መርከቦች ፈፅሞ በዚህ ነገር አይጠረጠሩም ። ፖሊሶች መርከቦቹን ፈትሸው አያውቁም ። ምን ይደረግ ታዲያ ሪዞሊን እምቢ ብሎ መለሰው ። ‘ሴላ ዘዴ እፈልጋለሁ’ አለ ተኒ ሪዞሊ በአሳቡ ። ‘ቶሎ ብፈልግ ይሻለኛል ።’

“ካተሪን – ረበሽኩሽ እንዴ?”

ጊዜው እኩለ ሌሊት ነው ። “የለም አልረበሽከኝም ኮስታ ፤ ድምፅህን መስማቴ ራሱ ያስደስተኛል ።”

“ሁሉም ነገር በደህና ሁኔታ እየተካሄደ ነው ?”

“እም – ለአንተ ምስጋና ይግባህና በሥራዬ እየተደሰትኩ ነኝ ።”

“መልካም ፤ በቅርቡ ወደለንደን ስለምመጣ እንገናኛለን ።”

‘ተጠንቀቅ ። እትፍጠን’ የሚል ማስጠንቀቂያ በአእምሮው ብልጭ አለ ።

“ካንቺ ጋር ስለኩባንያው ሠራተኞች መነጋገር እፈልጋለሁ ።”

“ጥሩ ።”

“በይ ደህና እደሪ ።”

“ደህና እደር ።”

በስልክ እንዲህ አለችው ፦ “ኮስታ ፤ ምን ብዬ እንደማመሰግንህ አላውቅም ። ጌጣጌጡ በጣም ቆንጆ ነው ። ግን ይህን ያህል መጨነቅ ...”

“አነስተኛ ስጦታ ናት ካተሪን ። ኤቪሊኒን ምን ያህል እየረዳሽት እንደሆነ ከእርሷ ሰምቻለሁ ። የአድናቆት መግለጫዬ ናት ።”

‘በጣም ቀላል ነገር ’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ‘አነስተኛ ስጦታና የታላት ድለላ ።’

‘ቆይቶ እኔና ባለቤቴ እንፋታለን ። ከዚያም የብቸኛ ኑሮ ። መጀመሪያ የሌለው የትዳር ጭቅጭቅ ከፍቶ ወደ ግል ደሴት በግል መዝናኛ መርከብ ለሽርሽር መንጉድ ። እንዲህ ያለው እቅድ ሳይሳካ ቀርቶ አያውቅም ። በተለይ ይህኛው በጣም አስደሳች ይሆናል’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ‘ምክንያቱም ውጤቱ ከሌላው ጊዜ ለየት ያለ ይሆናል ። መሞቷ ነው ።’

ለናፖሊዮን ቾታስ ስልክ ደወለ ። የሕግ ባለሙያው ዴሚሪስ ስለደወለለት ደስ ብሎታል ። “ብዙ ጊዜ ሆነን ኮስታ ። ሥራ ደህና ነው ?”

“ደህና ነው ። አንድ የምትረዳኝ ነገር አለ ።”

“በደስታ ።”

“ኖኤሌ ፓጂ ራፊና ውስጥ ትንሽ ቪላ ነበራት ፡ ቤቱን በሌላ ሰው ስም እንድትገዛልኝ እፈልጋለሁ ።”

“ችግር የለም ። አንዱን የሕግ ባለሙያ ሠራተኛዬን ጠርቼ እነግረዋለሁ...

“ጉዳዩን እራስህ እንድትከታተለው እፈልጋለሁ ።”

ለትንሽ ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ። “በጣም ጥሩ እኔው እከታተለዋለሁ ።”

“እመሰግናለሁ ።”

ናፖሊዮን ቾታስ ስልኩ ላይ እፍጥመ ቀረ ። ቪላው ኖኤሌ ፓጂና ላሪ ዶግላስ የፍቅር ጊዜያቸውን እየተዝናኑ ያሳልፉበት የነበረ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቤቱን የፈለገው ለምን ይሆን ?

ምዕራፍ ሰባት

በአቴንስ ከተማ ውስጥ የሚገኘው የአርሳኪዮን ፍርድ ቤት ግራጫማው የድንጋይ ሕንጻ በጣም ትልቅ ነው ። ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ የዩኒቨርስቲና የስትራይን ጉዳናዎችን ብዙ ቦታ አካብቦ ይዟል ። በሕንጻው ውስጥ ከሚገኙት 30 ችሎቶች መካከል የወንጀል ክስ የሚታይባቸው ሦስቱ ብቻ ናቸው ። የእነኚህም ችሎቶች ቁጥር 21 ፣ 30 እና 33 ነው ።

የአናስታሺያ ሳቫላስን በነፍስ ግድያ ወንጀል መከሰስ ለመከታተል ቁጥሩ በዛ ያለ ሕዝብ በመምጣቱ ጉዳይዋ በቁጥር 33 ችሎት ውስጥ እንዲታይ ተደረገ ። ክፍሉ 40 ሜማ ስፋትና 300 ሜማ ርዝመት አለው ። መቀመጫዎቹ በሦስት ረድፍ የተደረደሩ ሲሆኑ በእያንዳንዱ መቀመጫ መካከል የስድስት ሜማ ርቀት አለ ። በእያንዳንዱ ረድፍም ዘጠኝ አግዳሚ ወንበሮች ተደርድረዋል ። ፊት ለፊት ሦስቱ ዳኞች የሚሰየሙበት ከፍ ያለ ሥፍራ አለ ።

ከዳኞቹ ፊት ለፊት ምስክሮች ቆመው ቃል የሚሰጡበት ቦታም ተዘጋጅቷል ። ራቅ ብለው በግድግዳው ጥግ ከተራ ሰዎች ተመርጠው የፍርድ አሳብ የሚሰጡ የ10 ሰዎች መቀመጫ ሥፍራም ይታያል ። ከተከሳሹ ማቆሚያ ሳጥን ፊት ለፊት የጠበቃው መቆሚያ ቦታም ይገኛል።

የግድያ ወንጀሉ ክስ እራሱ በጣም አስደናቂ ጉዳይ ሆኖ መሰንበቱ ብቻ ሳይሆን ለተከሳሾቹ የቆመው ጠበቃ ናፖሊዮን ቾታስ በዓለም ውስጥ በወንጀል ክስ ጥብቅና የታወቀ መሆኑም ሞምር ነው ። ቾታስ ባለፉት ጊዜያት በጣም አስደናቂ ውጤቶችን ያስመዘገበ ሰው ነው ። የሚጠይቀውም ክፍያ ወደ ሚሊዮን ዶላር አካባቢ እንደሚጠጋ ሲናፈስ ይሰማል ። ናፖሊዮን ቾታስ ቀጠን ያለ ኮስማና ሲሆን ኮስታራ ነው ። በአለባበስ ረገድ እራሱን የማይጠብቅ ቢሆንም ዝርክርክ መሳይነቱ በሰዎች እምነት

ላይ ምንም ተፅዕኖ አያደርግም ። በጣም የሚያስደንቅ ብልህና አርቆ አስተዋይ ነውና ።

ናፖሊዮን ቾታስ ፣ የወንጀል ክስ የተመሰረተባት ሴትዮ ጠበቃ ሆኖ በመቅረቡ ዜና ማሰራጫዎች በጉዳዩ ላይ አስተያየቶችንና ትችቶችን ሰንዝረዋል ። በአንድ በኩል ሊረታ የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቾታስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚረታበት ወቅት መቃረቡ በብዙዎቹ ተወስቷል ።

ሕግ አስከባሪው ፒተር ዲሞኒዲስና ቾታስ ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ከችሎት ቀርበው ተፋልመዋል ። የቾታስ የክርክር ስልትና ጥበብ ዲሞኒዲስን የሚያስደንቀው ቢሆንም ይህንኑ እምነቱን ይፋ አያወጣ ውም። ይሁንና የአሁን ክርክር ዲሞኒዲስን ብዙም እንደማያስጨንቀው አውቋል ። እስካሁን ከቀረቡት የወንጀል ክሶች መካከል ቶሎ ውሳኔ የሚሰጥበት ቀላል ነገር ቢኖር የአናስታሺያ ጉዳይ ነው ። ወንጀሉ ግልጽ ወጥቶ ይታያል ። የተዋበችዋ ወጣት አናስታሺያ ሳቫላስ በሰላሳ ዓመት ታላቋ የሆነውን ባለፀጋ ጆርጅ ሳቫላስን አግብታ ነበር ። አናስታሺያ ዮሴፍ ፓፓስ ከተባለው ወጣት ሾፌራቸው ጋር አንሶላ በመጋፈፍ ባሏ ሊፈታት እንደዛተባትና እንዲሁም ከውርስ ኑዛዜ ሰነድ ስሟን እንደፋቀ ምስክሮች ተናግረዋል ። ግድያው በተፈጸመበት ማታ የቤት ሠራተኞቹን አሰናብታ ለባሏ እራሷ እራት አሠናዳች ። ጆርጅ ሳቫላስን ኃይለኛ ጉንፋን ይዞት ስለነበር በእራት ላይ በጣም አሳለው ። ሚስቱ የሳል መድኃኒቱን ብልቃጥ አመጣችለትና ሳቫላስ ከመድኃኒቱ ላይ ጠጥቶ ወዲያውኑ ሞተ ።

ያለቀለት ክስ ።

ተመልካቹ ሕዝብ ገና በጠዋቱ ችሎት ቁጥር 33ን ሞልቶታል ። አናስታሺያ ሳቫላስ ጥቁር ጉርድ ቀሚስና ሸሚዝ ለብሳ ከተከሳሽ ወንበር ላይ ተቀምጣለች ። ምንም ዓይነት ጌጣጌጥ ያላጠለቀች ሲሆን ፊቷንም እምብዛም አልተኳኳለችም ።

ሕግ አስከባሪው ፒተር ዲሞኒዲስ ለፍርድ ቤቱ ክሱን አሰማ ።

“ክቡራትና ክቡራን ፣ ለወንጀል ክስ ውሳኔ ለማግኘት እንዳንድ ጊዜ ከሦስት እስከ አራት ወራት ይፈጃል ። ይህ ጉዳይ ግን ያን ያህል ጊዜ ይወስዳል የሚል ሥጋት እንዲያሳድርባችሁ አይገባም ። የሚቀርበውን ክስ መረጃ በምታዩበትና በምትሰሙበት ወቅት ፣ እርግጠኛ ነኝ የእንደኛ

ደረጃ የነፍስ ግድያ መሆኑን በተጨባጭ ትገነዘባላችሁ ። ተከሳሽ ፣ ከቤተሰቡ ሾፈር ጋር ስትግግጥ ባሏ ደርሶባት እንደሚፈታት ስላስፈራራት እንደገደለችው በሕግ ተረጋግጧል ። ተከሳሽዋ የባልዋን ደም በከንቱ ለማፍሰስ ምክንያት እድልና አመቺ ሁኔታ እንዳለ ይረጋገጣል ። አመሰግናለሁ ።”

ወደመቀመጫው ተመለሰ ።

የመሐል ዳኛው ወደ ቾታስ ዞር አሉ ። “የተከሳሽ ጠበቃ የመከላከያ መግለጫውን ለመሰጠት ዝግጁ ነው ?” ሲሉ ጠየቁ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ቀስ ብሎ ከተቀመጠበት ተነሳ ። “አዎ ፣ የተከበሩ ዳኛ” አለና የፍርድ አሳብ እንዲሰጡ የተመረጡት አሥሩ ሰዎች ወደተቀመጡበት ሄዶ ቆመ ። ዝቅ ባለ ድምጽ “በሕይወቴ ባሳለፍኳቸው ዓመታት ከተረዳኋቸው ጉዳዮች አንዱ ግንዎ ሰው ለረዥም ጊዜያት መጥፎ ባሕሪውን ሰውሮት ሊኖር አለመቻሉን ነው ። ውሎ አድሮ ይከሰታል ። አንድ ባለቅኔ በአንድ ወቅት ዓይን የነፍስ መስኮት ነው ሲል ተናግሮ ነበር ። በአባባሉ ትክክለኛነት አምናለሁ ። ክቡራትና ክቡራን ፣ የተከሳሿን ዓይን እያንዳንዳችሁ በትኩረት እንድትመለከቱልኝ እጠይቃለሁ ። ይህች ሴት ሰው እስከ መግደል የሚያደርሳት ጭካኔ በልቦናዋ ስለመኖሩ የሚያንፀባርቅ ምንም ነገር አይነበብባትም ።” ናፖሊዮን ቾታስ ሌላም ተጨማሪ ነገር ለመናገር ያሰብ ይመስል አመነታና ዞሮ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ ።

ፒተር ዲሞኒዲስ ክሱ በእርሱ ረቺነት መፈጸሙ ተሰማውና በጣም ደስ አለው ። ‘ክርስቶስ ! ይህ በሕይወቴ ውስጥ ከሰማሁት ደካማ የመከራከሪያ ነጥብ በጣም የዘቀጠው ነው ። ሽማግሌው አሁንስ ተረታ’ አለ በልቡ ።

“ሕግ አስከባሪው የአንደኛ ምስክሩን ቃል ለማሰማት ተዘጋጅቷል?”

“አዎ ክቡር ፍርድ ቤት ። ሮዛ ሊኮርጉስ በመጀመሪያ የምስክርነት ቃሏን እንድትሰጥ እጠይቃለሁ ። ”

በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኝና ሰውነቷ ግዙፍ የሆነ ሴት ከተመልካቹ መካከል ተነስታ ወደፊት ለፊት መጥታ ቃለ መሐላ ፈጸመች። “ሚስስ ሊኮርጉስ ሥራሽ ምንድን ነው ?”

“የቤት ሠራተኛ ነኝ .....” ድምጿ ይቆራረጥ ነበር ። “የሚስተር

ሳቫላስ የቤት ሠራተኛ ሆኜም ሠርቻለሁ ።”

“ለሚስተር ጆርጅ ሳቫላስ ?”

“አዎ ጌታዬ ።”

“ለሚስተር ሳቫላስ ለምን ያህል ጊዜ ሠርተሻል ?”

“ለሃያ አምስት ዓመታት”

“ያማ ረዥም ጊዜ ነው ። አሠሪሽን ትወጂው ነበር?”

“ቅዱስ ሰው ነበሩ ።”

“ከቀድሞ ሚስቱ ጋር ሳለም ለሚስተር ሳቫላስ ትሠሪ ነበር ?”

“አዎ ጌታዬ ። በሚስቱ ቀብር ላይም ነበርኩ ።”

“ስምም ነበሩ?”

“በጣም እንጂ ይዋደዱ ነበር ።” በተያቂና መልሱ መካከል ናፖሊዮን ቾታስ ተታውሞ ያቀርባል ብሎ በመገመት ፒተር ዲሞኒዲስ ዞር ብሎ አየው ። ቾታስ ግን በአሳብ ተመስጦ መቀመጫው ላይ ፀጥ ብሎ ተቀምጧል ።

ፒተር ዲሞኒዲስ ጥያቄውን ቀጠለ ።

“ሚስተር ሳቫላስ ሁለተኛዋ ሚስቱን አናስታሺያ ሳቫላስን ሲያገባ ከእርሱ ዘንድ ትሠሪ ነበር?”

“አዎ ጌታዬ ሠራተኛው ነበርኩ ።”

“ባልና ሚስቱ ደስተኞች ነበሩ ለማለት ይቻላል?” ካለ በኋላ ዞር ብሎ ናፖሊዮን ቾታስን ተመለከተ ። አሁንም ምንም የተቃውሞ ምልክት አላየበትም ።

“ደስተኞች? አይ ጌታዬ ። እንደውሻና ድመት ዘወትር ይጣሉ ነበር።”

“በጥላቸው ወቅት ልብ ያልሺውን ነገር ልትነግሪን ትችያለሽ?”

“ሲጨቃጨቁ ፣ ትልቁን ቤት ሲያተራምሱ ፣ ግንም የሚሰማቸው ነው ።”

“ጭቅጭቅ እንጂ ዱላ አልነበረም ለማለት ይቻላል? ማለትም ሚስተር ሳቫላስ ሚስቱን ደብድቧት አያውቅም?”

“ዱላማ ነበር ። ግን ነነሩ የተገላቢጦሽ ነው ። እሜቴ ናቸው ባላቸውን ይደበድቡ የነበር ። ሚስተር ሳቫላስ በዕድሜውም ሽምገል ያሉ ስውነታቸውም የደከመ ስለነበረ ምን ጉልበት ነበራቸው ?”

“ሚስስ ሳቫላስ ባሏን ስትደበድብ አይተሻል ማለት ነው?”

"ከአንዴም ሁለቴ" ወደ አናስታሺያ ሳቫላስ ተመለከተችና የደስታ ስሜት ወረራት ።

"ሚስስ ሊኮርጉስ ፣ ሚስተር ሳቫላስ በሞተበት ምሽት በቤቱ ውስጥ የነበረው ሠራተኛ ማነው?"

"ማንኛችንም አልነበርንም ።"

ፒተር ዲሞኒዴስ በሁኔታው መደነቁን ለማሳወቅና ሌሎችም ይህንኑ እንዲያውቁለት ለማድረግ "ማለትም በጣም ትልቅ ነው ባልሺው በዚያ ቤት ውስጥ አንድ ሠራተኛ አልነበረም? ሚስተር ሳቫላስ የወጥ ቤት ሠራተኛ አልቀጠረም ··· ወይም የልፍኝ አሽከር ···?"

"ቀጥሮ ነበር ጌታዬ ሁሉም ነበሩት ። ሆኖም ማዳም ያን ዕለት ምሽት ለባልዋ እሷ ራሷ እራት እንደምታዘጋጅለት ነግራን ሁላችንንም አሰናበተችን ። የጫጉላ ጊዜዋን ዳግመኛ ማክበሯ መሆኑ ነው ።" የመጨረሻ ገለፃው በምፀት ነበር ።

"እሃ ፣ ሚስስ ሳቫላስ ሁሉንም አባረረቻቸው ማለት ነዋ?"

ተቃውሞ ያቀርብ እንደሆን አሁን ወደናፖሊዮን ቾታስ የተመለከቱት የመሐል ዳኛው ናቸው ። ሆኖም ጠበቃው ምንም ሳይንቀሳቀስ ከተቀመጠበት ቀረ ።

የመሐል ዳኛው ወደዲሞኒዴስ ዞረው "ሕግ አስከባሪው መሪ ጥያቄዎችን ለምስክሯ ባያቀርብ ጥሩ ነው" አሉ ።

"ይቅርታ የተከበረው ፍርድ ቤት ፣ አስተካክዬ ላቅርብ ።"

ዲሞኒዴስ ወደሊኮርጉስ ጠጋ አለና "አንቺ የምትዪው የቤቱ ሠራተኞች በሥራ ላይ መቆየት በነበረባቸው በዚያች ምሽት ሚስስ ሳቫላስ ከባለቤቷ ጋር ብቻዋን ለመቆየት ፈልጋ አባረረቻቸው ነው?"

"አዎ ጌታዬ ምስኪኑ ሰውዬ በጎይለኛ ጉንፋን ሲሰቃይም ነበር።"

"ሚስስ ሳቫላስ ከዚህ ቀደም ለባለቤቷ እራት አዘጋጅታ ታውቃለች?"

ሚስስ ሊኮርጉስ አፍንጫዋን አጣሩች ። "እርሷ ? በጭራሽ ጌታዬ በፍጹም እንዲት ነባር ነክታ አታውቅም ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ቁጭ ብሎ ይታዘባል ።

"አመሰግናለሁ ሚስስ ሊኮርጉስ ፣ ጠቃሚ ሐሳቦችን ሰጥተሻል" አለ ሕግ አስከባሪው ።

ፒተር ዲሞኒዴስ ወደ ቾታስ ዞር አለ ። እርካታውን ለመደበቅም

በጣም ይጥራል። የሚስስ ሊኮርጉስ የምስክርነት ቃል በሽንጉው ላይ ጉልህ ተጽእኖ ሊያደርግ ይችላል ። ተመልካቾች ተከሳሿን በመጥፎ ዓይን መመልከት ጀምረዋል ። የተከሳሿ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርብ እንደሆነ ተብሎ ምስክሯ እንድትቆይ ተጠየቀች ።

ናፖሊዮን ቾታስ ቀና አለ ። "ምን አሉ፣ ምንም ጥያቄ የለኝም ።"

የመሐል ዳኛው በጣም ተገረሙ ። "ሚስተር ቾታስ ··· ለዚህች ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ የለህም?"

ናፖሊዮን ቾታስ ቆመ ። "የለኝም ክቡር ጌታዬ ። ፍጹም ሐቀኛ ሴት ትመስለኛለች ።" ተመልሶ ተቀመጠ ።

ፒተር ዲሞኒዴስ የዛሬውን ጥሩ አጋጣሚ ሊያምነው አልቻለም ። 'አምላኬ !' አለ በልቡ ። 'ትንሽ እንኳ የመፈራገጥ ምልክት አላሳየም ። ሽማግሌው አልቆለታል ።' ዲሞኒዴስ ቾታስን እንደሚረታ ከወዲሁ አውቋል ።

የመሐል ዳኛው ወደሕግ አስከባሪው ዞር አሉና "ሁለተኛው ምስክር ይቅረብ" ብለው አዘዙ ።

"ጀሴፍ ፓፓስ ወደዚህ ቅረብ ።"

ከቁመቱ ረዘም ያለና መልከ መልካም ባለጥቁር ፀጉር ሰው ከሕዝቡ መካከል ተነስቶ ለምስክሮች ወደተዘጋጀው ሥፍራ መጣ ። ቃለ መሐላም ፈጸመ ።

ፒተር ዲሞኒዴስ ጥያቄውን ጀመረ ።

"ሚስተር ፓፓስ ፣ ሥራህ ምን እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ ብትገልጥ?"

"ሾፌር ነኝ ።"

"አሁን ተቀጥረህ ትሠራለህ?"

"አልሠራም ።"

"ግን እስከቅርብ ጊዜ ተቀጥረህ ትሠራ ነበር ። ማለትም ጆርጅ ሳቫላስ እስኪሞት ድረስ በሥራ ላይ ነበርክ አይደል?"

"አዎ ትክክል ነው ።"

"ከሳቫላስ ቤተሰብ ጋር ለምን ያህል ጊዜ ሠርተሃል?"

"ከዓመት በላይ ።"

"ሥራው ጥሩ ነበር?"

ጀሴፍ ፓፓስ በአንድ ዓይኑ ቾታስን እያየ ከዚህ መዓት እንዲያወጣው ይጠብቅ ነበር ። ፀጥታ ሰፈነ ።

"ሥራው ተስማምቶህ ነበር ፡ ሚስተር ፓፓስ?"

"ደህና ነበር መሰለኝ"

"ጥሩ ደመወዝ ይከፈልህ ነበር?"

"አዎ"

"ታድያ ሥራው ደህና ብቻ ሳይሆን በጣም ጥሩ ነው አትልም? ግለት ሌላ ተጨማሪ ጥቅም አልነበረውም? ዘወትር ከሚስስ ሳቫላስ ጋርስ ወሲብ አትፈጽምም ነበር?"

ጆሴፍ ፓፓስ አውንም እርዳታ ፍለጋ ወደናፖሊዮን ቾታስ ተመለከተ ። ሆኖም ምንም አላገኘም ።

"እኔ ... አዎ ጌታዬ ይመስለኛል ።"

ፒተር ዲሞኒዲስ ቆጣ አለና "ይመስልሀል? ቃለ መሐላ ፈጽመሃል እኮ ። አብረሃት ተኝተህ ታወቃለህ ወይስ አታውቅም?"

ፓፓስ እየተሸኮረመመ "አዎ ግንኙነት ነበረን" አለ ።

"ባለቤቷ ቀጥሮ እያሠራህ ፡ ጥሩ ደሞዝ እየከፈለህ እንዲሁም ውብ መኖሪያ ሰጥቶህ?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"በሹልክታ ከሚስቱ ጋር የፍትወት ግንኙነት እያደርግክ የሚስተር ሳቫላስን ገንዘብ ስትቀበል አይቀፍህም ነበር?"

"የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቻ አልነበረም"

ፒተር ዲሞኒዲስ ወተመዱን በጥንቃቄ እያዘጋጀ "የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቻ አልነበረም? እንዲህ ስትል ምን ማለትህ ነው? አባባልህ ግልጽ አልሆነልኝም ።"

"ማለቴ እኔና አናስታሺያ ለመጋባትም አቅደን ነበር ።"

በችሎቱ ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ ተገርሞ ሲያጉረመርም የፍርድ አሳብ ሰጪዎች ወደተከሳሿ ይመለከቱ ነበር ።

"የጋብቻ አሳቡን ያቀረብከው አንተ ነህ ወይንስ ሚስስ ሳቫላስ?"

"ሁለታችንም ፈልገነው ነበር ።"

"መጀመሪያ አሳብ ያቀረበው ማነው?"

"እንደሚመስለኝ እርሷ ናት" አለና አናስታሺያ ሳቫላስን ከተቀመጠችበት ተንጠራርቶ አያት ። እሷ ግን ለእይታው ፍንክች አላለችም ።

"በእውነት ለመናገር ሚስተር ፓፓስ ግራ ገብቶኛል ። በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንጋባለን ብለህ ገምተህ ነበር? ሚስስ ሳቫላስ እንደሆነ ባል ነበራት ። በእርጅና ምክንያት ይሞታል ብለህ? ይህ እስኪሆን የመጠበቅ አቅድ ነበረህ? ወይስ አንድ የሆነ አደጋ ቢፈጠር ብለህ? በትክክል በአእምሮህ ውስጥ የነበረው አሳብ የትኛው ነው?"

ጥያቄው በጣም አደገኛ በመሆኑ ሕግ አስከባሪውና ሦስቱም ዳኞች የተቃውሞ ቁጣ ከናፖሊዮን ቾታስ ይሰነዘራል ብለው ጠበቁ ። ሆኖም የተከሳሿ ጠበቃ አውንም ፈዞ ተቀምጧል ። እንዲህ መሆኑ አናስታሺያ ሳቫላስንም ጭምር አሳስቧታል ።

ፒተር ዲሞኒዲስ ያገኘውን ቀዳዳ የበለጠ ለማስፋት "ጥያቄዬን አልመለስክልኝም ሚስተር ፓፓስ" አለ ።

ዮሴፍ ፓፓስ እየተቁነጠነጠ ወደጠያቂው ዞር አለ ። "ትዝ አይለኝም "

ፒተር ዲሞኒዲስ ድምጹን እያሰላ መጣ ።

"በል እኔ ትዝ እንዲልህ ልርዳህ ። እንቅፋት እንዳይሆንባት ሚስስ ሳቫላስ ባሏን ልትገድለው አቀደች ። ባለቤቷ ከኑዛዜው ውስጥ ስሟን ለመሰረዝ መወሰኑን አውቃ ነበር ። እርሷ ..."

"ተቃውሞ !" ቃሉ የተወረወረው ከናፖሊዮን ቾታስ ሳይሆን ከመሐል ዳኛው ነበር ። "ለምስክሩ የቀረበው ጥያቄ ግምታዊ ምላሽን የሚጋብዝ ነው ።" ጠበቃው ዝም በማለቱ ተገርመው የመሐል ዳኛው ናፖሊዮን ቾታስን እዩት ። ሊያሸልበው ይመስል ዓይኑ ሊከደን የተቃረበ ሰው ቾታስ አግዳሚውን ወንበር ወደኋላ ተደግፎ ተዝናንቶ ተቀምጧል ። "ይቅርታ ክቡር ጌታዬ" አለ ሕግ አስከባሪው ። የተጠየቀውን በተከከል ስለሚያውቅ ግምታዊ ምላሽ እንደማይሰጠው ያውቅ ነበር ። ፒተር ዲሞኒዲስ ወደቾታስ ዞር አለና "ምስክሩ ይሸውልህ" አለው ።

ናፖሊዮን ቾታስ ከተቀመጠበት ተነሳና "እመሰግናለሁ ሚስተር ዲሞኒዲስ ጥያቄ የለኝም " አለ ።

ሦስቱ ዳኞች በጣም ተገርመው እርስ በእርስ ተያዩ ።

ከሦስቱ አንደኛው "ሚስተር ቾታስ ለዚህ ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ ለማቅረብ ያለህ ዕድል አውን ብቻ መሆኑን ታውቃለህ ?"

ናፖሊዮን ቾታስ በአምንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "አዎ ጌታዬ"

"የሰጠውን የምስክርነት ቃል በሚመለከት ጥያቄ ልታቀርብለት እትሻም ?"

ናፖሊዮን ቾታስ እጁን አወዛወዘ ።

“የለኝም ክቡር ጌታዬ ።”

ዳኛው ፈገግ አሉ ። “መልካም ፣ ሕግ አስከባሪው የሚቀጥለው ምስክሩን ሊያቀርብ ይችላል ።”

ተከታዩ ምስክር ሚሃሊስ ሃሪቶኒደስ ይባላል ። ሰውዬው መልከ መልካም ቢሆንም ዕድሜው ወደስልሳው ገደማ ነው ።

ሃሪቶኒደስ ቃለ መሐላውን እንደፈጸመ ሕግ አስከባሪው ጥያቄዎችን ያቀርብለት ጀመር ። “ሥራህ ምን እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ ልትገልጽ ትችላለህ ?”

“አዎ ጌታዬ ፣ የሆቴል አስተዳዳሪ ነኝ።”

“የሆቴሉስ ስም ?”

“አርጕስ”

“ሆቴሉ የሚገኘው የት ነው ?”

“በኮርፋ”

“በዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች በሆቴልህ አርፈው የነበሩ ካሉ እንድትነግረኝ ነው ሚስተር ሃሪቶኒደስ ።”

ሃሪቶኒደስ ዙሪያውን ተመለከተ ። “አዎ ጌታዬ ፣ እርሱና እርሷ ።”

“ምስክሩ ወደ ዮሴፍ ፓፓስና ወደ አናስታሺያ ሳቫላስ ማመልከቱ በደንብ ተረጋግጦ ይመዝገብልኝ ።” ወደምስክሩ መልሶ ዞረና “በሆቴልህ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ሠፍረዋል ?”

“አዎ ጌታዬ ። ብዙ ጊዜ መጥተዋል ።”

“እና ሌሊቱን አብረው በአንድ ክፍል ውስጥ ያሳልፉ ነበር ?”

“አዎ ጌታዬ ። ብዙ ጊዜ ቅዳሜና እሁድ ይመጡ ነበር ።”

“አመሰግናለሁ ሚስተር ሃሪቶኒደስ” አለና ዞር ብሎ ወደናፖሊዮን ቾታስ በመመልከት “ምስክሩ ይሽውልህ” አለው ።

“ጥያቄ የለኝም ።”

የመሐል ዳኛው የግራና የቀኝ ዳኞችን ተራ በተራ ካዩ በኋላ ሦስቱም ለጥቂት ጊዜ ተንሾካሾኩ ።

የመሐል ዳኛው ወደናፖሊዮን ቾታስ እየተመለከቱ “ለዚህኛውም ምስክር ምንም ጥያቄ የለህም ሚስተር ቾታስ?”

“ምንም ፡ ክቡር ጌታዬ የምስክሩ ቃል ትክክል ነው ። ሆቴሉ በጣም ጥሩ ስለሆነ እኔም አርፌበት ነበር ።”

ዳኛው ናፖሊዮን ቾታስን ረዘም ላለ ጊዜ ትኩር ብለው አዩትና ወደ ሕግ አስከባሪው ተመለሱ ። “የሚቀጥለው ምስክር ሊቀርብ ይችላል” አሉ ።

ቀጥሎ የተጠራው ዶክተር ቫሲሊስ ፍራንጂስኮስ ነው ።

ክቁመቱ ረዘም ያለ ፣ ደንዳና ቁመና ያለው ሰው ተነሳና ወደምስክሮች መቆሚያ ሳጥን ገባ ። ቃለ መሐላም ፈጸመ ።

“ዶክተር ፍራንጂስኮስ ፡ በምን ዓይነት የሕክምና ሥራ ላይ እንደተሰማራህ ለፍርድ ቤቱ ብትገልጽ ?”

“የጠቅላላ ሕክምና ዶክተር”

“ይህ ሥራ ከቤተሰብ ዶክተርነት ጋር እኩል ደረጃ አለው ?”

“ሙያውና ደረጃው ያው አንድ ነው ፣ መጠሪያው ተለያየ እንጂ ።”

“ዶክተር ፡ በሥራ ላይ የቆየኸው ለምን ያህል ጊዜ ነው ?”

“ለሰላሳ ዓመታት ያህል”

“የሕክምና ፍቃድ በመንግሥት ተሰጥቶሃል ?”

“እንዴታ”

“ዶክተር ፍራንጂስኮስ ፡ ጆርጅ ሳቫላስን ታከመው ነበር ?”

“አዎ ነበረ ።”

“ለምን ያህል ጊዜ ?”

“ከአሥር ዓመታት በላይ ።”

“ሚስተር ሳቫላስን ልዩ የሆነ በሽታ ይዞት አክመኸው ታውቃለህ?”

“አዎ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደእኔ የመጣው የደም ብዛት ሕመም በያዘው ጊዜ ነበር ።”

“ሕክምና አደረግክለት ?”

“አዎ”

“ከዚያ በኋላስ አግኝተኸው ታውቃለህ ?”

“አዎ ። አንዴ ብሮንካይተስ ፡ ሌላ ጊዜ የጉበት በሽታ ይዞት አክሜዋለሁ። ከዚህ የከፋ በሽታ ግን አጋጥሞት አያውቅም ።”

“ለመጨረሻ ጊዜ ሚስተር ሳቫላስ አንተ ዘንድ የመጣው መቼ ነው?”

“ባለፈው ዓመት በዲሴምበር ወር”

“ከመሞቱ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ማለት ነው ?”

"ትክክል ነው ።"

"ወደቢሮህ መጥቶ ያውቃል ዶክተር ?"

"አይ ፣ እኔ ነኝ እቤቱ እሄድ የነበረው ።"

"ብዙ ጊዜ እቤት ትደውል ነበር ?

"የለም ብዙ ጊዜ አልደውልም ።"

"ለዚህ በሽታ ግን ትደውል ነበር ?"

"እዎ"

"ለምን ?"

ዶክተሩ ትንሽ አመነታና "ወደቢሮዬ ለመምጣት የሚችልበት ሁኔታ ላይ አልነበረም ።"

"ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነበር ?"

"ቁስል ነበረበት ። ጕድኑ ላይ መፀጠጥና መቀጥቀጥ ደርሶበት ነበር።"

"አደጋ አጋጥሞት ነው ?"

ዶክተር ፍራንጂስኮስ አሁንም ላለመናገር ትንሽ አመነታ ። "የለም ባለቤቱ እንደደበደበችው ነው የነገረኝ ።"

በፍርድ ቤቱ ውስጥ የነበረው ሕዝብ ሳቁን ለቀቀው ።

የመሐል ዳኛው ቆጣ አሉ ። "ሚስተር ቾታስ ፣ በዚህኛው ምስክር ላይም ተቃውሞ የለህም ?" አሉ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ደንግጦ ቀና አለ ። "አመሰግናለሁ ። ከቡር ጌታዬ፡ ተቃውሞ አለኝ" ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ተናገረ ።

ቢሆንም ነገሩ ፈሩን ለቆ ከተበላሸ ቆይቷል ። የፍርድ አሳብ አቅራቢዎቹም ተከሳሽዋን የበለጠ በክፉ ዓይን መመልከት ጀምረዋል ።

"አመሰግናለሁ ዶክተር ፍራንጂስኮ ተጨማሪ ጥያቄ የለኝም" አለና ፒተር ዲሞኒዲስ ወደቾታስ ዞር በማለት "ምስክሩ ይሽውልህ" አለ።

"ጥያቄ የለኝም ።"

ከዚያ በኋላ የብዙ ምስክሮች ቃል ተሰማ ። አንዲት የቤት ሠራተኛ ሚስስ ሳቫላስ ወደሾፈሩ መኖሪያ ቤት ብዙ ጊዜ ስትሄድ ማየቷን ...

የእልፍኝ አሽከሩ ፣ ጆርጅ ሳቫላስ ሚስቱን ለመፍታት ሲያስፈራራትና ኑዛዜውን ለመቀየር ማሰቡን ሲናገር መስማቱን ፣ ጕረቤቶች በባልና ሚስቱ መካከል የነበረውን ጭቅጭቅ ማዳመጣቸውን ...

ይህ ሁሉ ሆኖ አሁንም ናፖሊዮን ቾታስ ለማንም ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ አላቀረበም ።

መረቡ ፈጣን በሆነ ሂደት በአናስታሺያ ሳቫላስ እየተጠመጠመባት ነው ።

ፒተር ዲሞኒዲስ አሸናፊ መሆኑ እየታየው በደስታ እየተውከነከነ ተዝናንቷል ። የፍርዱን ውጤት ጋዜጦች በአምዶቻቸው ላይ ሲያሰፍሩም በአሳቡ ሕሊናው ይታየዋል ። ይህ ጉዳይ የግድያ ወንጀል ክስ ከቀረበባቸው ወንጀሎች ሁሉ በቶሎ ውሳኔ የሚያገኝ ሊሆን ነው ። 'በጉዳዩ ላይ ዛሬም ውሳኔ ሊሰጥ ይችል ይሆናል' አለ በአሳቡ ። 'ታላቁ ናፖሊዮን ቾታስ ተሸናፊ ነው ።'

"ቀጥሎ ሚስተር ኒኮ ሜንታኪስ ቀርበው እንዲመሰክሩ እጠይቃለሁ ።"

ሜንታኪስ ቀጠን ያለና ታማኝ መሳይ ወጣት ነው ። በእርጋታና ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ነው የሚናገረው ።

"ሚስተር ሜንታኪስ ፣ ሥራህ ምን እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ ብትገልጥ ?"

"እሺ ጌታዬ ፣ በተንከባካቢ ማሳደጊያ ክፍል ነው የምሠራው"

"ሕጻናት ታሳድጋለህ ?"

"አይደለም ጌታዬ እንደዚያ ዓይነቱ ማሳደጊያ አይደለም ። እኛ ዘንድ ዛፎች ፣ አበቦችና የተለያዩ ዕፅዋት ናቸው ያሉት ።"

"አሃ ገባኝ ። ተክሎችን የሚያበቅል ልዩ ባለሙያ ነሃ !"

"ትክክል ። በዚህ ሥራ ላይ ለረዥም ጊዜ ቆይቻለሁ ።"

"እንደሚመስለኝ ፣ አንዱ ሥራህ ለሽያጭ የምታቀርባቸው ተክሎች ጤነኛ መሆናቸውንም ማረጋገጥ ነው ።"

"አዎ ጌታዬ ። ለተክሎቹ ከፍተኛ ጥንቃቄ እናደርጋለን ። የተበላሹትን ለደንበኞቻችን አንሸጥም ። ብዙዎቹ ገዥዎቻችን ቋሚ ደንበኞቻችን ናቸው ።"

"በዚህ አባባልህ ደንበኞች አዘውትረው ይመጣሉ ማለትህ ነው ?"

"በትክክል ጌታዬ" አለ ኩራት በተመላው አነጋገር ። "በጣም ጥሩ

አገልግሎትም እንሰጣለን ።”

“ሚስተር ሜንታኪስ ፡ ሚስስ ሳቫላስ ከቋሚ ደንበኞችህ መካከል አንዷ ነበረች ?”

“አዎ ጌታዬ ። ሚስስ ሳቫላስ ተክሎችና አበቦች ትወዳለች ።”

የመሐል ዳኛው ትዕግሥታቸው አለቀ ። “ሚስተር ዴሞኒዴስ ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት አለው ብሎ ፍርድ ቤቱ አያምንም፡ ወደሌላ ነጥብ ብትሄድ ። ወይም ...”

“ክቡር ጌታዬ ፡ ምስክሩ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ ጠቃሚ ነጥቦችን ሊያቀርብ ስለሚችል ፍርድ ቤቱ ቢያስጨርሰኝ ።”

የመሐል ዳኛው ናፖሊዮን ቾታስን ተመለከቱና “ሚስተር ቾታስ በዚህ ጥያቄ ላይ ተቃውሞ አለህ ?”

ናፖሊዮን ቾታስ ብድግ አለና በድንጋጤ “ምን አሉ ? የለም ፡ ጥያቄ የለኝም ክቡር ጌታዬ” ብሎ መለሰ ።

ዳኛው ተስፋ በቆረጠ አመለካከት ለጥቂት ጊዜ አዩትና ወደ ፒተር ዴሞኒዴስ ዞር አሉ ። “መልካም ፡ ልትቀጥል ትችላለህ ።”

“ሚስተር ሜንታኪስ ፡ ሚስስ ሳቫላስ በዲሴምበር ውስጥ አንድ ቀን ወዳንተ መጥታ የገዛቻቸው ተክሎች ችግር እንደነበረባቸው ገልጻልህ ለች?”

“አዎ ጌታዬ ነግራኛለች ።”

“በግልጽ ለመናገር ያህል ፡ ተባዮች ተክሎቿን እያበላሹባት መሆኑን ነግራሃለች ?”

“አዎ ጌታዬ ነግራኛለች ።”

“ለተባዮች ማጥፊያ የሚሆን መድኃኒት እንድትሰጣት አልጠየቀች ህም ?”

“አዎ ጠይቃኛለች”

“የጠየቀችህ ምን እንደነበር ለፍርድ ቤቱ ብትገልጥ ።”

“የሸጥኩላት አንቲሞኒ ነው ።”

“ምን እንደሆነ ብትነግረን ?”

“ከአርሴኒክ ጋር የሚመሳሰል መርዝ ነው ።”

ተመልካቹ ውካታ አሰማ ።

የመሐል ዳኛው መዶሻውን እንስተው ጠረጴዛውን መታ መታ አደረጉ ።

“ሌላ ሟጫታ ብሰማ ሁላችሁም እንድትወጡ ትዕዛዝ አሰጣለሁ ።” ወደ ፒተር ዴሞኒዴስ መለስ አሉ ። “ጥያቄህን መቀጠል ትችላለህ”

“እና አንቲሞኒ ሸጠህላታል ?”

“አዎ ጌታዬ ።”

“መርዙ ሊገድል ይችላል ብለህ ትገምታለህ ? ከአርሴኒክ ጋር ስታወዳድረው ?”

“አዎ ጌታዬ ሊገድል ይችላል ።”

“ማንኛውንም መርዛማ ነገር ስትሸጥ በሕጉ መሠረት ሽያጩን በመዝገብህ ውስጥ ታሰፍረዋለህ ?”

“አዎ ጌታዬ”

“መዝገቡን አምጥተኸዋል ሚስተር ሜንታኪስ ?”

“አዎ” አለና መዝገቡን ለፒተር ዴሞኒዴስ አስረከበ ።

ሕግ አስከባሪው ዳኞቹ ወደተቀመጡበት ሄደ ። “የተከበራችሁ ዳኞች ፡ ይህ መዝገብ እንደኤግዚቢት ‘ሀ’ ተደርጐ እንዲመዘገብልኝ እጠይቃለሁ ።” ወደ ምስክሩ ዞር “ተጨማሪ ጥያቄ የለኝም” ካለ በኋላ ወደ ናፖሊዮን ቾታስ ተመለከተ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ጭንቅላቱን በአሉታ ነቀነቀ ።

“ጥያቄ የለኝም ።”

ፒተር ዴሞኒዴስ ወደ ውስጥ በንይል ተነፈሰ ። የማስረጃ ናዳውን ማዝነቢያ ጊዜው አሁን ነው ። “ኤግዚቢት ‘ለ’ን ለማቅረብ እፈልጋለሁ” አለና ወደ ፍርድ ቤቱ በር ዞር ብሎ በሩ አጠገብ የቆመውን ዘብ “እባክህ ወዲህ አምጣልኝ” አለ ።

ዘቡ ተጣድፎ ወጣና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በማቅረቢያ ሳሕን ላይ የተቀመጠ የሳል መድኃኒት ብልቃጥ ይዞ ተመለሰ ።

ብልቃጡ በመጠኑ ጉድኗል ። ዘቡ ብልቃጡን ለሕግ አስከባሪው ሲሰጠው ተመልካቹ በነገሩ ተደንቆ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር ። ፒተር ዴሞኒዴስ ብልቃጡን ከፍርድ አሳብ ሰጪዎቹ አሥሩ ሰዎች ፊት ካለው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ ።

“ክቡራትና ክቡራን ፡ ሕይወት የጠፋበት መርዝ ይሄውላችሁ ። ጀርጅ ሳቫላስን የገደለው ይህ ነው ። ሚስተር ሳቫላስ በሞተበት ምሽት ሚስስ ሳቫላስ ያጠጣችው የሳል መድኃኒት የአንቲሞኒ መርዝ ይህ ነው ። እንደምታዩት ብልቃጡ ጉዶሎ ነው ። ሚቹ ከላዩ ላይ ትንሽ እንደተጉ

ነጪ ነው ወዲያው ከሃያ ደቂቃ በኋላ የሞተው ።”

ናፖሊዮን ቾታስ ብድግ አለና በድፍረት “ተቃውሞ ! ሟቹ የጠጣው ከዚህ ብልቃጥ ውስጥ ለመሆኑ የሕግ አስከባሪው የሚያረጋግጥ በት ምንም መረጃ የለውም” ሲል ተናገረ ።

ፒተር ዲሞኒዲስ የተጠመደለትን ወጥመድ ለማክሸፍ “ባሏ በሞተ በት ምሽት የሳል መድኃኒት ነው ብላ መርዙን እንደሰጠችው ሚስስ ሳቫላስ እራሷ አምናለች ። ዛሬ እዚህ ፍርድ ቤት እስከቀረበ ድረስ ብልቃጡ በፖሊስ እጅ በሳጥን ውስጥ ተቆልፎ ተይዞ ቆይቷል ። ጆርጅ ሳቫላስ በአንቲሞኒ መርዝ መሞቱንም የሐኪም ምርመራ አረጋግጧል ። ይህ የሳል መድኃኒት ብልቃጥ የተሞላው በአንቲሞኒ መርዝ ነው ።” አለና ናፖሊዮን ቾታስን አፍጥጦ ተመለከተው ።

ናፖሊዮን ቾታስ እራሱን ነቀነቀና “በእርግጥ እንዲህ ከሆነማ እርግጥ ነው ማለት ነው” አለ ።

ፒተር ዲሞኒዲስ በድል አድራጊነት መንፈስ “ ምን ጥርጥር አለው? አመሰግናለሁ ሚስተር ቾታስ ። በበኩሌ ጨርሻለሁ” አለ ።

የመሐል ዳኛው ወደ ናፖሊዮን ቾታስ ዞር ብለው “ጠበቃው የውሳኔ አሳብ ለማቅረብ ተዘጋጅቷል ?” ብለው ጠየቁ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ተነስቶ ቆመና “አዎ ክቡር ጌታዬ” አለ ። ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆመና ወደፊት ተራመደ ። የፍርድ አሳብ እንዲሰጡ ከተሰየሙት አሥሩ ሰዎች ፊት ለመናገር የፈለገው ነገር የጠፋበት ይመስል እራሱን አከክ—አከክ አደረገ ። በኋላም ረጋ ብሎ ቃላትን እየመረጠ መናገር ጀመረ ። “ምናልባት ለምስክሮቹ መስቀለኛ ጥያቄዎች አለማቅረቤ አንዳንዶቻችሁን ላያስደንቅ የቀረ አይመስለኝም ። እውነቱን ለመናገር ሚስተር ዲሞኒዲስ አብዛኛውን ጥያቄ በማቅረብ ጥሩ ተግባር በማከናወኑ የኔ ተጨማሪ ጥያቄ ማቅረብ አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም ።”

‘ሞኙ እኔኑ ደግፎ እየተከራከረልኝ ነው’ አለ ፒተር ዲሞኒዲስ በልቡ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ዞር ብሎ የሳል መድኃኒቱን ብልቃጥ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተና እንደገና ወደ አሥሮቹ ሰዎች ዞረ ። “ምስክሮቹ ሁሉ የተናገሩት እውነት ይመስላል ። ግን የተናገሩት ሁሉ በተጨባጭ መረጃ የተደገፈ ነው ? ለማለት የፈለግኩት ...” ሞንቅላቱን ነቀነቀ ።

“መልካም ፡ ምስክሮቹ ከዘረዘሩት ብዙ አሳብ አንድ ፍሬ ነገር ብቻ ግውጣት ይቻላል ። በመልኳ የተዋበች አንዲት ወጣት ሴት የወሲብ ፍላጐቷን ሊያረካላት የማይችል ሽማግሌ አገባች ።” ወደ ዮሴፍ ፓፓስ ዞር አለና ሞንቅላቱን አወዛወዘ ። “እና ሊያረካት የሚችል ወጣት አገኘች። ይህንን ሁሉ ጋዜጦችም ነግረውን ነበር እኮ ። የእነኚህ ሰዎች ግንኙነት ምስጢር አልነበረም ፡ መላ ዓለም ያውቀዋል ። በዓለም ላይ ያሉ መደዴ መጽሔቶች እንኳ ሳይቀሩ ስለዚህ ጉዳይ በዓምዶቻቸው አስፍረዋል ። ምናልባት ይህን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እኔና እናንተ ላንቀበል እንችል ይሆናል ፡ አናስታሲያ ሳቫላስ ግን የተከሰሰችው በዚህ አይደለም። ከቡራትና ከቡራን ፡ ግንኛዋንም ወጣት ሴት የሚሰማት የወሲብ ፍላጐት ስላላት አይደለም ተከሳ ፍርድ ቤት የቀረበችው ። የተከሰሰችው በግድያ ወንጀል ነው ።” አለና ብልቃጡን የወደደው ይመስል እንደገና ዞር ብሎ አየው ።

‘እስቲ ይለፍልፍ’ አለ ፒተር ዲሞኒዲስ በአሳቡ ። ቀና አለና በፍርድ ቤቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ሰዓት ተመለከተ ። ስድስት ሰዓት ሊል የቀረው አምስት ደቂቃ ነው ። ዳኞቹ ሁልጊዜ ስድስት ሰዓት ሲሞላ ችሎቱን ለፅሪፍት ይዘጋሉ ። ‘ተላላው ሽሜ እንደሆነ የውሳኔ አሳቡን እስከ ስድስት ሰዓት አቅርቦ አይጨርስ’ አለ እንደገና በአሳቡ ። ፒተር ዳኞቹ ከፅሪፍት እስኪመለሱ እንኳ ለመጠበቅ ትዕግሥት አልነበረውም ። ‘ግን እኔ እርሱን የምፈራው ለምንድን ነው ?’ ሲል ፒተር ዲሞኒዲስ ተገረመ ።

ናፖሊዮን ቾታስ እየተንጐራደደ ንግግሩን ቀጠለ ።“ እስቲ መረጃውን አብረን እንመርምረው ። የሚስስ ሳቫላስ ተክሎች በተባይ ስለተበከሉባት የተባይ ማጥፊያ ለማግኘት ወደ ሚስተር ሜንታኪስ ሄደች። የተክል ባለሙያውም እንቲሞኒ እንድትጠቀም መከራት ። እርሷም ምክሩን ተቀበለች ። ያንን ታዲያ የማድያ ወንጀል ነው ትሉታላችሁ ? እኔ አልለውም ። ስለዚሁም ጉዳይ የቤት ሠራተኛዋን የምስክርነት ቃል ሰምተናል ።

ሚስስ ሳቫላስ ያን ዕለት ምሽት የቤት ሠራተኛዟን ያሰናበተችው ከባሏ ጋር የሚጉላ ወቅት እንዲሆንላቸው ለእርሱ እራት ለማዘጋጀት አስባ ነው ። እዚህ ላይ አንድ የሚታየኝ ነገር አለ ። ምናልባት ሠራተኛዋ

ከሚስተር ሳቫላስ ጋር የፍቅር ግንኙነት ሊኖራት ይችል ይሆናል ። አንድ ጥልቅ ስሜት ወይም ፍላጐት ከውስጥ ሳይኖራት ለአንድ ሰው ለሃያ አምስት ዓመታት በተከታታይ የምትሠራበት ምክንያት አይኖርም ። በዚህም የተነሳ አናስታሺያ ሳቫላስን ትጠላታለች ለማለት እንችላለን ። ይህንንም ከአነጋገሯ ለማወቅ ትችላላችሁ" ሲል ጥሮሮውን ጠረገ ።

"ተከሳሿ ባሏን በጣም ትወደው ስለነበር ትዳሯ እንዳይፈርስ ትጥራለች እንበል ። ከዚህ በላይ አንዲት ሴት ለወንድ ፍቅሯን የምታሳየው እንዴት ነው ? አንዱ መንገድ እንደሚመስለኝ ምግብ በማዘጋጀት ነው ። ይህ የፍቅር መግለጫ ምልክት አይደለም ነው የምትሉት ? እኔ በበኩሌ ነው እላለሁ ።" አለና አሁንም ዞር ብሎ ብልቃጡን ተመለከተ ። "ሌላው መግለጫ መንገድ ደግሞ ባልዬው በሚታመምበት ወቅት እንክብካቤ ማድረግ አይደለምን ? በበሽታ ጊዜ አለመራቅ !"

በግርግዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት ስድስት ሊል አንድ ደቂቃ መቅረቱን ያመለክታል ።

"ክቡራትና ክቡራን ፣ ፍርድ ቤቱ ገና ሥራውን እንደጀመረ የዚህችን ሴት ፊት እንድትመለከቱ ጠይቄአችሁ ነበር ። ፊቷ የነፍሰ ገዳይ ፊት አይመስልም ። ዓይኖቿም የነፍሰ ገዳይ ዓይን አይደሉም ።"

አሥሩ ሰዎች ተከሳሿን ሲመለከቱ ፒተር ዲሞኒዲስ ትኩር ብሎ ያያቸው ነበር ። እንዲህ ዓይነቱን የጥላቻ አመለካከት ከእነዚህ ሰዎች ፊት ላይ ተመልክቶ አያውቅም ። አሁን የሰዎቹን ስሜት እየተቆጣጠረ መምጣቱ ገባው ።

"ሕጉ በጣም ግልጽ ያለ ነው ክቡራትና ክቡራን ። ወንጀለኛው ጥፋተኛ ሆኖ የሚገኘው የተከሳሽ ጥፋተኝነት ሲረጋገጥ መሆኑን የተከበሩ ዳኞች ሊገልጹላችሁ ይችላሉ ። ሳይረጋገጥ የሚወሰን ነገር የለም ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ንግግሩን ቀጥሎ በመሐል እንደገና አሳለውና ከኪሱ መሐረብ አውጥቶ አፉን ሸፈነ ። የሳሉ መድኃኒት ከሸንጐው አጠገብ ወደተቀመጠበት ጠረጴዛ ሄደ ።

"በጥሞና ብትመለከቱት ሕግ አስከባሪው ያቀረበው ተጨባጭ ማስረጃ የለም ። ሚስስ ሳቫላስ ለባለቤቷ ሰጠች ከሚባለው ከዚህ መድኃኒት በቀር በእውነት ለመናገር ምንም አላማኝ ነገር አልቀረበም ።"

ተናግሮ እንደጨረሰ ሳል አጣደፈው ። ሳያውቀው የሳል መድኃኒቱን አንስቶ ወደአፉ በማቅረብ ጠጣው ። በፍርድ ቤቱ ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ በድንጋጤ አፍጥጦ አየው ። ተመልካቹ ተሸበረ ። ፍርድ ቤቱም በውካታ ተዋጠ ።

የመሐል ዳኛው በመገረም "ሚስተር ቾታስ ..." አሉ ።

ናፖሊዮን ቾታስ አንደገና መድኃኒቱን ተጐነጨው ። "ክቡር ጌታዬ ሕግ አስከባሪው በፍርድ ቤቱ እየቀለደ ነው ። ጆርጅ ሳቫላስ የተገደለው በዚህች ሴት እጅ አይደለም ። የመከላከያ አላቤን በዚህ አጠቃልላለሁ ።"

ሰዓቱ ልክ ስድስት ሰዓት መሆኑን በደወል አበሰረ ። ዘቡም ፈጠን ባለ እርምጃ ወደ መሐል ዳኛው ጆሮ ተጠግቶ እንሾካሾከ ።

የመሐል ዳኛው በመዶሻ ጠረጴዛውን መታ መታ አደረጉ ። "ሥነ ሥርዓት ፡ ሥነ ሥርዓት ፡ አሁን የእረፍት መውጪያ ጊዜ ነው ። ሽንጐዎችም ተሰናብተዋል ። ከውሳኔ ነጥብ ላይ ደርሰው ይመለሳሉ ። ፍርድ ቤቱም በስምንት ሰዓት ሥራውን ይጀምራል ።" አሉ ።

ፒተር ዲሞኒዲስ እዚያው በቆመበት ፈዘ ቀረ ። ብልቃጡ ተቀይሮ ይሆን ? ግን እንዴት ሊሆን ይችላል ? በኤግዚቢትነት በደንብ ሲጠበቅ የነበረ ነው ። ምናልባት አስከሬኑን የመረመሩት ሰዎች የተሳሳተ ውጤት ልከው ይሆን ? ዲሞኒዲስ ረዳቱን ሊያነጋግር ዞር ብሎ ሲመለስ ናፖሊዮን ቾታስን በዓይን ፈልጎ አጣው ። እርሱ የለም ወጥቶ ሄዷል ።

በስምንት ሰዓት ችሎቱ እንደገና ሲሰየም የሽንጐው አባላት አንድ በአንድ ገብተው ወንበራቸው ላይ ተቀመጡ ። ናፖሊዮን ቾታስ ግን የት እንደደረሰ አልታወቀም ።

'ያ የውሻ ልጅ ሳይሞት አልቀረም' አለ ፒተር ዲሞኒዲስ በአሳቡ ።

ስለእርሱው በማውጠንጠን ላይ እያለ ናፖሊዮን ቾታስ ብቅ አለ ። በተመልካቹ መሐል አልፎ ወደመቀመጫው ሲጓዝ ሁሉም ሰው ትኩር ብሎ እንደጉድ ተመለከተው ።

የመሐል ዳኛው "የተከበራችሁ የሽንጐ አባላት ከውሳኔ ላይ ደረሳችሁ ?" ብለው ጠየቁ ። የሽንጐው ሰብሰቢ ተነሳና "አዎ ደርሰናል ክቡር ጌታዬ ። ተከሳሿ ጥፋተኛ ሆና አላገኘናትም ።"

በክፍሉ ውስጥ የነበረው ተመልካች ጭብጨባውን አቀለጠው ።

የፒተር ዲሞኒዲስ ፊት ደም ለበሰ ። 'ይህ ደደብ እንደገና ጉድ እደረገኝ አይደል?' አለ በልቡ ። ቀና ብሎ ሲያየው ናፖሊዮን ቾታስ በፈገግታ ይመለከተው ነበር ።

ምዕራፍ ስምንት

ትሪትሲስ እና ትሪትሲስ በግሪክ ውስጥ እጅግ የታወቀ የሕግ ተቋም ነው። ይህንን ተቋም በመጀመሪያ የቆረቆሩት ሰዎች ከለቀቁ ረዥም ጊዜ ሆኗቸዋል ። ባሁኑ ወቅት በባለቤትነት የሚያካሄደው ናፖሊዮን ቾታስ ነው ። ከቾታስ ጋር አብረው የሚሠሩ ሌሎች ሸሪኮች ቢኖሩም ከሁሉም የላቀ አሳቢ ጭንቅላት ያለው እሱ ነው ።

ከበርቴዎች የግድያ ወንጀል ሲመሰረትባቸው የሚርጡት ወደናፖሊዮን ቾታስ ነው ። በጣም ጥሩ ስምና አስደናቂ ሪኮርድ አለው ። ለከባድ የወንጀል ክሶች የተከሳሽ ጠበቃ ሆኖ በቆመባቸው ጊዜያት ቾታስ ተረትቶ አያውቅም ። በቅርቡ ውሳኔ ያገኘው የአናስታሺያ ሳቫላስ የክስ ጉዳይ በመላ ዓለም ጋዜጦች በሰፊው ተጽፏል ። በግያሻግ ሁኔታ የነፍስ ግድያ ወንጀል ነው በማለት ሰው ሁሉ ጥብቅና ሊቆም የፈራውን ጉዳይ ቾታስ ደፍሮ በመቀበል ረትቷል ። ሕይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ የደንበኛውን ሕይወት ከማትረፍ ሌላ አማራጭ አልነበረውም ።

በሚገድል መርዝ ተሞልቷል የተባለውን ብልቃጥ አንስቶ ሲጉነጭ የሸንጉ አባላት እንዴት ይመለከቱት እንደነበር አስታወሰና ሳቅ አፈነው ። የውሳኔ አሳቡንም ለፍ/ቤቱ ለማቅረብ ሲነሳ ሊጠቀም የሚችልበትን የጊዜ ርዝመት በሚገባ አስልቷል ። ልክ ስድስት ሰዓት ሲሆን አሳቡን አጠቃሎ እንደሚጨርስ ያውቅ ነበር ። ከዚህ ቀደምም ውስብስብ ጉዳዮችን የሚያስቋጨው በተመሳሳይ ብልሃት ነው ። ችሎቱን በስድስት ሰዓት ባያሳርፉትና ምናልባት ትንሽ ቢረዝም ኖሮ ምን ይፈጠር እንደነበረ ሲያስብ ይዘገንነዋል ።

ሕይወቱን አደጋ ላይ የሚጥል ድንገተኛ ክስተት ነበር ። ለዕረፍት ከተበተኑ በኋላ ጋዜጠኞች ጥያቄ ሊያቀርቡለት መተላለፊያውን ሲዘጉ ቾታስ እየተጣደፈ ገሠገሠ ።

“ሚስተር ቾታስ የሳል መድኃኒቱ ያልተመረዘ መሆኑን እንዴት አወቅክ ...?

“ልታስረዳን ትችላለህ ፣ ስለ ...?”

“ብልቃጡ ተተይሯል ብለህ ትገምታለህ ...?

“አናስታሺያ ሳቫላስ ...?”

“እባካችሁ ጌቶቼ ። በቅድሚያ ለተፈጥሮ ጥሪ መልስ መስጠት አለብኝ። ጥያቄያችሁን በኋላ ብመልስ ደስ ይለኛል ። ”

በመተላለፊያው ጥግ ላይ ወደሚገኘው የወንዶች መፀዳጃ በፍጥነት ገሰገሰ ። በመፀዳጃው በር ላይ “ተበላሽቷል ” የሚል ጽሑፍ ተለጥፎ አየ።

ከጋዜጠኞች አንዱ “ወደሌላ የወንዶች መፀዳጃ ብትሄድ ይሻላል” አለው ። ናፖሊዮን ቾታስ ሳቅ አለ ። “መታገስ የምችል አይመስለኝም ።” በሩን በርግዶ ወደውስጥ ገባና ቆለፈው ።

እንድ የሕክምና ቡድን ተዘጋጅቶ ይጠብቀው ነበር ። ዶክተሩ “በጣም ስጋት አድሮብኝ ነበር ። የአንቲሞኒ መርዝ በሰውነት ውስጥ በፍጥነት ነው የሚሰራጨው ።” ሪዳቱን ጠራ ። “ሆዱን ቶሎ እጠበው”

“እሺ ዶክተር ።”

ዶክተሩ ወደናፖሊዮን ቾታስ ዞር አለ ፣ “በጀርባህ ተኛ በጣም አስጊ ነገር ነው ።”

“ታዲያ ምን ላድርግ አማራጭ አልነበረኝም” አለና ናፖሊዮን ቾታስ ሳቀ ።

“ደግሞ የፈለገውን ብሆን ግድ የለኝም ።”

ናፖሊዮን ቾታስ የአናስታሺያ ሳቫላስን ሕይወት በማትረፉ የተከፈለው አንድ ሚሊዮን ዶላር ነበር ። ገንዘቡ ስዊዝ ባንክ በስሙ ገቢ ተደርጎለታል ። ቾታስ አቴንስ ውስጥ በኮሎናሪ የመኖሪያ ሰፈር ቤተመንግሥት የመሰለ ቤት ፣ በኮርፉ ደሴት ላይ አንድ ቪላ ፣ እንዲሁም ፓሪስ ውስጥ በፎች ጉዳና ላይ አንድ አፓርታማ አለው ።

በጥቅሉ ሲታይ ናፖሊዮን ቾታስ በኑሮው የሚደሰትበት አጥጋቢ ምክንያት አለው ። አንድ አክል ብቻ ነበር የማይለየው ።

ስሙ ፍሬደሪክ ስታቭሮስ የተሰኘ ሲሆን የትሪትሲስና ትሪትሲስ ድርጅት አዲስ ባልደረባ ሆነ ። በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች ዘወትር ስለስታቭሮስ ቅሬታ ያሰሙ ነበር ።

"ከየት መጥቶ ከናፖሊዮን እኩል ይሆናል? ይህን በመሰለ ተቋማችን ውስጥ ሊሰራ የሚገባው ዓይነት ሰው አይደለም ..."

"ስታቭሮስ ጉዳዬን አበላሽብኝ ። የማይረባ ደደብ"

"ስታቭሮስ ትናንት በፍርድ ቤት ያደረገውን ሰምታችኋል? ዳኛ ውኮ ከፍርድ ቤቱ ሊያባርሩት ነበር ።"

"ምን ዓይነት ነገር ነው? ይሄ ስታቭሮስ የሚባለውን ለምን አታባርረውም? ስማችንን አጐደፈ እንጂ የጠቀመን ነገር የለም ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ይህን ሁሉ ያውቃል ። ላባርረው አልችልም ብሎ እውነቱን ሊነግራቸው ከቃጣ በኋላ መልሶ "እስቲ ዕድል እንስጠው ስታቭሮስ ይሻሻል ይሆናል" አለ ።

የሥራ ጓደኞቹ ሁሉ የሚያገኙት ምላሽ ይሄው ነበር ።

* * *

አንድ ፈላስፋ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሏል ። "ስትመኝ ጥንቃቄ አድርግ ፣ ታገኘው ይሆናልና !"

የትሪትሲስና ትሪትሲስ የቅርብ ጊዜ አባል የሆነው ፍሬደሪክ ስታቭሮስ የተመኘውን ቢያገኝም ደስተኛ አልነበረም ። ምግብ የማይበላ ለት ሲሆን እንቅልፍም አይተኛም ፣ ሰውነቱም ይከሳል ።

"ሐኪም ዘንድ መሄድ አለብህ ፍሬደሪክ" አለችው ሚስቱ ። "ሳትታመም አልቀረህም"

"አልሄድም ። ፋይዳ ... ፋይዳ የለውም ።"

ያጋጠመውን ችግር ማንም ሀኪም ሊያቃልልለት እንደማይችል ያውቃል ። በሽታው የጎሊና ወቀሳ ነው ።

ፍሬደሪክ ስታቭሮስ የጋለ የሥራ ስሜት ያለው ፣ ወጣት ፣ ንጊ ፣ ብዙ የሚመኝና የጎልዮ ኑሮ የሚጓጓው ሰው ነው ። ለብዙ ዓመታት በአቴንስ ጉሮኖዋማ መንደር ሞርንቱስ ቢሮ ከፍቶ ለችግረኞች በነፃ ጥብቅና ይቆም ነበር ። ከናፖሊዮን ቾታስ ጋር ሲገናኝ ሕይወቱ በአንዲት ምሽት ተቀየረች ።

ከአንድ ዓመት በፊት ላሪ ዶግላስና ኖኤሌ ፖጂ የዶግላስን ሚስት ካተሪንን ገድላችኋል ተብለው ተከሰው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ስታቭሮስ

ለላሪ ዶግላስ ጥብቅና ቆሞ ነበር ። ዝነኛው ነጋዴ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ናፖሊዮን ቾታስን ቀጥሮ ለቀድሞው አቁባቱ ለኖኤሌ ፖጂ ጥብቅና አቆመ ። ስታቭሮስ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቾታስ የሁለቱን ጥብቅና በበላይነት መምራቱ ደስ አሰኝቶታል ። በብልሁ የሕግ አዋቂ ላይ ሙሉ እምነት ነበረው ። "ቾታስ በችሎት ላይ ሲከራከር ባየሺው !" ይላት ነበር ባለቤቱን ። "የሰውዬው ችሎታ ተዓምር ነው ። አንድ ቀን የድርጅቱ አባል ብሆን እንዴት ደስ ይለኝ ነበር። "

ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታየ ወደመጨረሻው ላይ ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ ። ናፖሊዮን ቾታስ ፈገግ እያለ ኖኤሌ ፖጂን ፣ ላሪ ዶግላስንና ፍሬዴሪክ ስታቭሮስን ወደ ልዩ ክፍል ይዟቸው ገባ ።

ቾታስ ስታቭሮስን እንዲህ አለው ፦ "ከዳኞቹ ጋር በምስጢር ተነጋግሬያለሁ ። ተከሳሾቹ ቃላቸውን ቀይረው ጥፋታቸውን ካመኑ አምስት ዓመት ብቻ እንደሚበይኑባቸው ዳኞቹ ገልጠውልኛል ። ከአምስቱ ዓመት ውስጥ አራቱ ዓመት በቆይታ ይተላለፋል ። ይህም ማለት ደግሞ ተከሳሾቹ ከስድስት ወራት በላይ አይታሰሩም ማለት ነው ።" ወደላሪ ዞር አለ ። "ሚስተር ላሪ ፣ አሜሪካዊ በመሆንህ አንተ ከአገር ትባረራለህ ። ሁለተኛ ወደግሪክ እንድትመለስ አይፈቀድልህም" አለው።

ኖኤሌ ፖጂና ላሪ ዶግላስን የሰጣቸው ተስፋ አጓጓቸውና ቃላቸውን ቀይረው ጥፋተኛነታቸውን አመኑ ። ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ተከሳሾቹና ጠበቆቻቸው ከፊት ለፊት እንደቆሙ የመሐል ዳኛው የሚከተለውን ውሳኔ አነበቡ ። "የግድያ ወንጀል መፈጸሙን ካላረጋገጡ በስተቀር የግሪክ ፍርድ ቤቶች የሞት ቅጣት በይነው አያውቁም ። በእውነት ለመናገር ተከሳሾቹ ወደጉዳዩ ማለቂያ ላይ ቃላቸውን ቀይረው ጥፋታቸውን በማመናቸው እኔና የሥራ ጓደኞቼን በጣም አስደንቆናል ... ሁለቱ ተከሳሾች ማለትም ኖኤሌ ፖጂና ሎውረንስ ዶግላስ ዘጠና ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጥይት ተደብድበው እንዲቀጡ የሞት ፍርድ ወስንንባቸዋል ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ተከሳሾቹን እንዳታለላቸው ስታቭሮስ የተረዳው ይሄኔ ነበር ። ሁለቱም በስውር የተስማሙት ምንም ነገር የለም ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለኖኤሌ ፖጂ ጥብቅና ቾታስን ቀጥሮ ሲያቆመው እንዲያድናት ሳይሆን እንዲያስፈርድባት ነበር። እንዲህ አድርጎ ነው የቀድሞ የክንዳቸውን ሴት ዴሚሪስ የተበቀለው ። ስታቭሮስ ግን በማያ

ቀው ነገር የሴረኞች መሣሪያ ሆነ ።

'ይህ ሲፈጸም ዝም ብዬ አላይም' አለ ስታቭሮስ በአሳቡ ። 'ቾታስ ምን እንደሰራ ለመሐል ዳኛው ሄጂ እነግራቸውና ውሳኔውን አስገለብጣ ለሁ'

ወዲያው ናፖሊዮን ቾታስ ስታቭሮስ ወደነበረበት መጣና "ነገ ነፃ ከሆንክ ለምን አብረን ምሳ አንበላም ፍሬዴሪክ! ከሌሎች የሥራ ጓደኞቼም ጋር እንድትተዋወቅ እፈልጋለሁ ። ..."

ከአራት ሳምንታት በኋላ ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ በስመ ጥር የትሪትሲስና ትሪትሲስ ድርጅት ባለሙሉ መብት አባል ሆነ ። ሰፊ ቢሮና ጥሩ ደመወዝም ተሰጠው ። ለሰይጣን ነፍሱን ሸጦ ነው ከዚህ የገባው ። ያገኘው ክፍያና ለክፍያው የፈጸመውን ተግባር ሲያወዳድረው ያሳብደዋል ። ሁልጊዜ በአሳቡ 'በእንዲህ ዓይነት ልዘልቅ አልችልም' የሚል ወቀሳ ይመጣበታል ። የደረሰበት ከፍተኛ የሀሊና ቁስል በቀላሉ ሊሽር አልቻለም ። 'እኔኮ ነፍሰ ገዳይ ነኝ' ይላል ሁሌ ለእራሱ ። ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ከረጅም ጊዜ የኅሊና ጭቅጭቅ በኋላ ከአንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ።

አንድ ቀን ማልዶ ወደናፖሊዮን ቾታስ ቢሮ ገባና "ሊዮን ..." አለ።

"የፈጣሪ ያለህ ፣ ምነው ተጎሳቆልክ" አለው ናፖሊዮን መልሶ ። "ለምን የአጭር ጊዜ ዕረፍት ወስደህ አታርፍም ፍሬዴሪክ?"

ስታቭሮስ ፣ ለችግሩ መፍትሔው ይህ እንዳልሆነ ያውቀዋል ።

"ሊዮን ፣ ላደረግክልኝ ውለታ ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ ። ግን እኔ ... እዚህ ልቀይ አልችልም ።" ቾታስ በመገረም ወደእርሱ ተመለከተ ። "ምንድነው የምትለው? ሥራውን እንደሆነ በደንብ እያካሄድከው ነው ።"

"የለም ፣ ሰውነቴ በጭንቀት ተበታትኗል ።"

"በጭንቀት! ግን ምን እንደሚያስጨንቅህ አልገባኝም!"

ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ትኩር ብሎ አየው ። "ያ ... ያ እኔና አንተ በኖኤሌ ፖጂና በላሪ ዶግላስ ላይ የፈጸምነው ነገር ... አንተስ ምንም የኅሊና ፀፀት አይሰማህም!"

የቾታስ ዓይኖች እየጠበቡ መው ። ጠንቀቅ ። "ፍሬዴሪክ አንዳንዴ ፍትህኮ በተለያዩ ዘዴዎች ይገኛል" ቾታስ ፈገግታ አሳየ ። "ዝም ብለህ ነው ምንም የሚያስፀፅት ነገር የለም ፣ ተከሳሾቹ ጥፋተኞች ነበሩ ።"

"ጥፋተኞች ነን ያሰኘናቸው እኛ ነን ። አታለልናቸው ። ይህንን እያስታወስኩ ልኖር አልችልም ። ሥራውን መልቀቄን እያሳወቅሁህ

ነው። እዚህም የምቆየው እስከወሩ መጨረሻ ነው ።"

"የሥራ መልቀቂያህን አልቀበልም" አለ ቾታስ ከንቸር ባለ አነጋገር ። "እኔ እንደነገርኩህ ለምን አታደርግም! ... ዕረፍት ውሰድና ...!"

"የማውቀውን በኅሊናዬ አምቄ እዚህ ሥፍራ በተደላችነት ልሠራ አልችልም ። በጣም አዝናለሁ ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ትኩር ብሎ ያጠናው ጀመር ። "ወደፊት ለመሥራት ያቀድከው ነገር አለ! መልካም ፣ ዕድልህ እንዳይበላሽ እወቅ ... ሕይወትህን"

"የለም ሕይወቴን ማትረፌ ነው ።"

"ስለዚህ በቁርጥ ከውሳኔ ደርሰሃል ማለት ነዋ !"

"አዎ ፣ አዝናለሁ ሊዮን ። ግን ስጋት አይደርብህ ። ስለዚህ ጉዳይ ለማንም አልናገርም ። ማለቴ ስለተፈጸመው ነገር ።" ወደኋላው ዞሮ ከቢሮው ወጥቶ ሄደ ።

ናፖሊዮን ቾታስ በአሳብ ባሕር ውስጥ ገብቶ እየዋኘ ለረዥም ጊዜ እዚያው ተቀምጠ ቀረ ። በመጨረሻም ከአንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ። ስልኩን አነሳና ደወለ ። "ሚስተር ዴሚሪስን ዛሬ ከሰዓት በኋላ ላገኘው እንደምፈልግ ልትነግርልኝ ትችላለህ! በጣም አስቸኳይ ነው በለው ።"

* * *

ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ 10 ሰዓት ላይ ናፖሊዮን ቾታስ ከዚንስታን ቲን ዴሚሪስ ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ነበር ።

"ችግሩ ምንድነው ሊዮን!" አለና ዴሚሪስ ጠየቀ ።

"ችግር እንኳ ላይሆን ይችላል " አለ ቾታስ በጥንቃቄ ። "ሆኖም ፍሬደሪክ ስታቭሮስ ዛሬ ጠዋት ሊያነጋግረኝ ቢሮዬ መጥቶ እንደነበረ አንተን ማሳወቁ አስፈላጊ ስለመሰለኝ ነው ። ተቋሜን ለመልቀቅ መወሰኑን ገልጦልኛል ።"

"ስታቭሮስ የላሪ ዶግላስ ጠበቃ የነበረው! እና !"

"ሕሊናው እያስጨነቀው መሰለኝ"

ከባድ ፀጥታ ሰፈነ ።

"ገባኝ"

"ለማንም እንደማይነግር ቃል ገብቶልኛል ... ያን ዕለት በፍርድ ቤት ስለተፈጸመው ሁኔታ "

"ታምነዋለህ?"

"አዎ ፣ በእርግጥ አምነዋለሁ ፣ ኮስታ ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፈገግ አለ ። "መልካም ስለዚህ ምንም የሚያሳስበን ነገር የለማ?"

ናፖሊዮን ቾታስ ትልቅ ሞነት የተራገፈለት ይመስል ቀለል አለው። ተነስቶ ቆመ ። "ያለ አልመሰለኝም ። እንድታውቀው ብቻ ነው የነገርኩህ ።"

"መንገርህማ ትክክል ነው ። በሚቀጥለው ሳምንት ከእኔ ጋር እራት ለመብላት ጊዜ አለህ?"

"እንዴታ !"

"ስልክ እደውልልህና እንቃጠራለን ።"

"አመሰግናለሁ ኮስታ ።"

ዓርብ ከሰዓት በኋላ በአቴንስ መሃል ከተማ በሚኖኘው ጥንታዊው የካፕ ኒካሪአ ቤተክርስቲያን ፀጥታና ሰላም ሰፍኖበታል ። ከመቅደሱ ጥግ ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ከፋዘር ኮንስታንቲኑ ፊት ተንበርክኳል ። ቄሱ ከስታቭሮስ ጭንቅላት ላይ ጨርቅ ጣል አድርገዋል ።

"አባቴ ኃጢአት ሠርቻለሁ ። በደለኛ ነኝ ።"

"ሰውኮ አስቸጋሪ ፍጡር ነው ልጄ ። ምንጊዜም እራሱን እንደንፁህ አድርጉ ነው የሚያየው ። የሠራኽው ኃጢአት ምንድነው ?"

"ነፍሰ ገዳይ ነኝ"

"በእጅህ ሕይወት ጠፍቷል ?"

"አዎ አባቴ ፣ እንዴት ከኃጢአቴ እንደምነጻ እንጂልኝ !"

"እግዚአብሔር ያውቃል ። እርሱኑ እንጠይቀዋለን ።"

"ከግብዝነትና ከስስታምነት የተነሳ እራሴን ለጥፋት አሳልፌ የሰጠሁት እኔው ነኝ ። ኃጢአት የሰራሁት ከዓመት በፊት ነው ። በግድያ ወንጀል ለተከሰሰ ሰው ጥብቅና ቆሜ ነበር ። ጉዳዩ በትክክለኛ ሁኔታ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ እያለ ናፖሊዮን ቾታስ ..."

ግማሽ ሰዓት ቆይቶ ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ከቤተክርስቲያኑ ሲወጣ የተለየ ሰው ሆኖ ተሰማው ። ከባድ የሆነ ሸክም ከትከሻው ላይ

የተራገፈለት ያክል ነበር ። በጥንታዊ የንስሐ ሥነ ሥርአት መንጻቱ ታወቀው ። ለቄሱ ኃጢአቱን ዘክዝኮ ነግሮአቸዋል ።

ከፍርድ ቤቱ ብያኔ ወዲህ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሟላ ሰው የመሆን ስሜት በውስጡ አድሯል ።

"አዲስ ሕይወት እጀምራለሁ ። ወደሌላ ከተማ እሄድና በአዲስ መንፈስ ሌላ ሥራ እከናውናለሁ ። ከዚህ ቀደም የፈጸምኩትን መጥፎ ተግባር የሚከስ በጉ ነገር አደርጋለሁ ። አመሰግናለሁ አባቴ ተጨማሪ ዕድል ስለሰጡኝ ።"

ጨልሟል ። የኤርሞስ አደባባይ ጭር ብሏል ። ከመንገዱም መጠምዘዣ ላይ እንደደረሰ የትራፊክ መብራቱ ለእግረኛው አረንጓዴ መብራት ሲያበራ ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ መንገዱን ማቋረጥ ጀመረ። ከመሐል ሲደርስ ኃይለኛ መብራት ያበራች ጥቁር ሊሞሲን መኪና እየበረረች ወደእርሱ አቅጣጫ መጣች ። ስታቭሮስ ደንግጦ ዞር አለና መኪናዋን አያት ። ከመንገዱ ዘሎ ለመውጣት አልቻለም ። እንደመብረቅ የሚጮህ ድምፅ ተሰማ ። ስታቭሮስ አካሉ ተፈጥፍጦ ሲበታተን ተሰማው፣ ላፍታ ያህልም ሕመም ተሰማው ። ከዚያ ድቅድቅ ጨለማ ሰፈነ።

ናፖሊዮን ቾታስ ሁልጊዜ ከእንቅልፉ የሚነቃው ማልዶ ነው ። ከዕለቱ የሥራ ጫና ጋር ከመተናነቁ በፊት ጠዋት ጠዋት ብቻውን መሆን ደስ ይለዋል ። ሁልጊዜ ቁርሱን ለብቻው እየተመገበ የዕለቱን ጋዜጦች ማንበብ ይወዳል ። በዚያች ቀን ጠዋት ብዙ ዓይንን የሚስቡ ዜናዎች ከጋዜጣው ላይ ሰፍረዋል ። ጠቅላይ ሚኒስትር ቴሚስ ቶክልስ ሶፋሊስ የአምስት ፓርቲዎች ጥምር ካቢኔ አቋቁመዋል ። 'የደስታ መግለጫ መላክ አለብኝ' ሲል አሰበ ቾታስ ። የቻይና ኮሙኒስት ጦር ከያንግቲዝ ወንዝ ዳርቻ መድረሳቸው ተነግሮ ነበር ። ሃሪ ትሩማንና አልቤን ባርክሌይ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ቃለ መሐላ ፈጽመዋል ። ናፖሊዮን ቾታስ ሁለተኛውን ገጽ ገልጦ ማንበብ ሲጀምር ከውብ ቀረ ። ዓይኑ ያረፈበት ጽሑፍ እንዲህ ይላል ፦

"ሚስተር ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ የተሰኘ የታዋቂው የትሪትሲስና

ትሪትሲስ ተቋም ባልደረባ ከካፒኒካሪአ ቤተክርስቲያን ሲወጣ ገጭታው ባመለጠች አንዲት መኪና እደጋ ሕይወቱ አለፈ ። የዓይን ምስክሮች መኪናዋ ታርጋ የሌላት ጥቁር ሊሞሲን መሆኗን ገልፀዋል ። በኖኤሌ ፖጂና በላሪ ዶግላስ ላይ ተከፍቶ በነበረው የግድያ ወንጀል ክስ ሚስተር ስታቭሮስ ለላሪ ዶግላስ ጥብቅና ቆሞ የነበረ ዝነኛ ሰው ነው ...”

ናፖሊዮን ችታስ ማንበብ አቆመ ። ቁርሱን ረሳውና እተቀመጠበት ረዞ ቀረ ። አደጋ ። ‘እውነት አደጋ ነው ?’ አለ በልቡ ። ቀደም ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ምንም የሚያሳስብ ነገር እንደሌለ ገልጦለት ነበር። ግን ብዙ ሰዎች ዴሚሪስ ላይ ላዩን በሚያሳያቸው ገጽታ ይታለላሉ ።

ችታስ ስልኩን አንስቶ ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሲደውል ፀሐፊዋም አገናኘችው ።

“የዛሬ ጠዋት ጋዜጦችን አንብበሃል?” ብሎ ችታስ ጠየቀ ።

“የለም አላነበብኩም ፤ ምነው?”

“ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ሞተ እኮ”

“ምን ?” አለ እንደመደንገጥ ብሎ ።

“ምንድነው የምትናገረው ?”

“በመኪና ትላንትና ማታ ተገጭቶ ሞተ ። መኪናዋ አምልጣለች ። ”

“አቤት አምላኬ ! በጣም የሚያሳዝን ነው ። ሊአን ፥ ቮፈራን ይዘውታል?”

“እስካሁን አልተያዘም ።”

“ክትትሉን እንዲያፋጥኑት በፖሊሶቹ ላይ ግፊት ማድረግ ይኖርብኛል ። በዛሬ ጊዜኮ ምንም አልሆንም ማለት አይቻልም ። በነገራችን ላይ ሐሙስ አብረን እራት ብንበላ ይመችሃል?”

“መልካም”

“ጥብቅ ቀጠሮ ነው ።”

ናፖሊዮን ችታስ የሰውን ንግግር አብጠርጥሮ የመረዳት ችሎታ አለው ። “ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በእደጋው አዝኗል ። በስታቭሮስ ግድያ ውስጥ እጁ የለበትም” ሲል ደመደመ ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ናፖሊዮን ችታስ መኪናውን እየነዳ ቢሮው ከሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ወስዶ አቆማት ። ከመኪናው ወርዶ ወደ አሳንሰሩ እንዳመራ አንድ ወጣት ጨለምለም ካለ ሥፍራ ብቅ

አለበት።

“ክብሪት አለህ ?”

የችታስ እእምሮ የማስጠንቀቂያ ደወል ደወለ ። ወጣቱ በመኪና ማቆሚያው ሥፍራ ታይቶ የማይታወቅ ነው ።

“አዎ” አለና ችታስ ባንጠለጠለው ቦርሳ ከመቅጽበት ሰውዬውን ፊቱ ላይ መታው ።

ወጣቱ በሲቃ ጮኸ ። “አንተ የውሻ ልጅ !” አለና ከኪሱ ውስጥ ድምጽ የሌለው ሽጉጥ አወጣ ።

“እንዴ ! አንተ ሰው ምን እያደረግህ ነው ?” እያለ የደንብ ልብስ የለበሰ ዘብ ወደ እነርሱ ገሠገሠ ። እንግዳው ወጣት እንደማመንታት ካለ በኋላ ወደበሩ ሮጠ ። ዘቡም ከችታስ አጠገብ ደረሰ ። “ደህና ነህ ሚስተር ችታስ ?”

“እ...አዎ” የናፖሊዮን ችታስ ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ አለ ። “ደህና ነኝ ።”

“ምን ሲያደርግ አገኘኸው ?”

“ምን አውቄ ?” አለ ናፖሊዮን ችታስ በርጋታ ።

“አጋጣሚ ሊሆን ይችላል” አለ ችታስ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ።

“ምናልባት ሰውዬው ስርቆት ሊፈጽም አስቦ ይሆናል ። ግን ሰዎችን ለመዝረፍ ድምጽ የሌለው ሽጉጥ መያዝ አያስፈልግም ። የለም ፥ ሆነ ብሎ ሊገድለኝ ነው የመጣው ።” ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የፍሬዴሪክ ስታቭሮስን መገደል ሲሰማ የደነገጠ እንደመሰለ ሁሉ ይህኛውም ቢነገረው የደነገጠ እንደሚመስል ችታስ ተንብዮዋል ። ‘መጠርጠር ነበረብኝ’ አለ ችታስ በአሳቡ ። ‘ዴሚሪስ የሚጠነቀቅ ሰው ነው ። የሚያከናውነውን ተግባር በግላጭ የሚፈጽም አይደለም ።’

የናፖሊዮን ችታስ ፀሐፊ ድምጽ ከኢንተርኮሙ ውስጥ ተሰማ ። “ሚስተር ችታስ በሰላሳ ደቂቃ ውስጥ ፍርድ ቤት መገኘት አለብህ ።”

ዛሬ አንድን የግድያ ወንጀል ክስ የውሳኔ አሳብ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት ነው ። ሆኖም ችታስ በመደንገጡ ወደፍርድ ቤት ለመሄድ አልፈለገም ። “ለዳኛው ደውዬና መታመሜን ንገሪያቸው ። አንድ የሥራ ባልደረባዬ እኔን ተክቶ እንዲገኝ አድርጊ ። የስልክ ጥሪ ይብቃ ።”

ከጠረጴዛው ኪስ ውስጥ ቴፕሪኮርደር አወጣና ተቀምጦ በሀሳብ

ተዋጠ ። ከዚያም መናገር ጀመረ ።

ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ናፖሊዮን ቾታስ አንድ ፖስታ እንደያዘ ወደ ሕግ አስከባሪው መደፒተር ዲሞኒዴስ ቢሮ ገባ ። ፀሐፊዋ በአንዴ አወቀችው ።

"እንደምን ዋልክ ሚስተር ቾታስ ምን ልርዳህ ?"

"ሚስተር ዲሞኒዴስን ለማነጋገር እፈልጋለሁ ።"

"አሁን ስብሰባ ላይ ነው ። ቀጠሮ አለህ ?"

"የለኝም ግን ለአስቸኳይ ጉዳይ እንደምፈልገው ንገሪልኝ ።"

"እሺ እንግረዋለሁ ።"

ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ናፖሊዮን ቾታስ ወደሕግ አስከባሪው ቢሮ ተስተናገደ ።

"መልካም" አለ ዲሞኒዴስ ። "እነሆ መሐመድ ወደ ተራራው መጣ። ምን ልርዳህ እላክህ ? ነው ወይስ የምንደራደርበት ነገር ተገኘ ?"

"አይ ፡ የመጣሁት ለማል ጉዳይ ነው ፒተር።"

"ተቀመጥ ሊዮን ።"

እንደተቀመጡ ቾታስ እንዲህ አለው ፡ "አንድ የታሸገ ፖስታ አንተ ዘንድ ለማስቀመጥ እፈልጋለሁ ። የሚከፈተው በአደጋ የሞትኩ እንደሆን ብቻ ነው ።"

ፒተር ዲሞኒዴስ ነገሩ ገርሞት በትኩረት ይመለከተው ነበር ። "አደጋ ይደርስብኛል የሚል ስጋት አለህ ?"

"ሊደርስብኝ ይችላል ።"

"አሃ ! ምናልባት ውለታ ቢስ ከሆኑት ደንበኞችህ አንዳቸው ።"

"ማንም ይሁን ማን እሱን እንተወው ። የማምነው ሰው አንተ ብቻ ነህ ። በቀላሉ ሊገኝ በማይችል ጥብቅ ሥፍራ ልታኖርልኝ ትችላለህ ?"

"በሚገባ ።" አለና ወደእሱ ተጠጋ ። "የተሸበርክ ትመስላለህሳ ?"

"አዎ ተሸብሬአለሁ ።"

"ጽሕፈት ቤቱ ጥበቃ እንዲያደርግልህ ትፈልጋለህ? ሁሉ የማይል ይህ ፖሊስ ልመድብልህ እችላለሁ ።"

ቾታስ ፖስታውን አቀበለው ። "የምፈልገው ጥበቃ ለዚህ ብቻ ነው።"

"መልካም ፡ ግን በእርግጥ ጥበቃ አያስፈልግህም ?"

"አያስፈልገኝም ።" ከተቀመጠበት ተነስቶ ጨበጠው ። "ታላቅ ውለታ ነው ያደረግህልኝ ።"

ፒተር ዲሞኒዴስ ሳቅ አለ ። "ተማመንብኝ ።"

ከአንድ ሰዓት በኋላ የደንብ ልብስ የለበሰ ተላላኪ ከሄሌኒክ የንግድ ኮርፖሬሽን ደረሰና ወደአንዲ ፀሐፊ ተጠጋ ።

"ለሚስተር ዴሚሪስ የሚሰጥ ዕቃ አምጥቼ ነበር ።"

"እኔ ፊርማ እቀበለዋለሁ ።"

"ለሚስተር ዴሚሪስ በእጅ እንድሰጥ ነው የታዘዝኩት ።"

"እዝናለሁ ሥራ ስለያዘ ላጷርጠው አልችልም ። ለመሆኑ ዕቃው የተላከው ከየት ነው ?"

"ከናፖሊዮን ቾታስ"

"እዚህ እኔ ዘንድ ለምን አትተወውም ?"

"ልተወው አልችልም እመቤቴ !"

የኢንተርኮሙን መጥሪያ ሜን አለችና "ይቅርታ ሚስተር ዴሚሪስ አንድ መልእክተኛ ከሚስተር ቾታስ የተላከ ዕቃ አምጥቷል ።" ተቀብለሺው አምጪልኛ ኤሬኒ" አለ የዴሚሪስ ድምፅ ።

"ለአንተ በእጅ እንዲሰጥ የታዘዘ ነው ።" ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ። "እብረሽው ነይ"

ኢሬኒና መልእክተኛው ወደ ቢሮው ገቡ ።

"ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እርስዎ ነዎት ?"

"አዎ"

"እባክዎ እዚህ ላይ መተማመኛ ይፈርሙልኝ ?"

ዴሚሪስ በእንድ ቁራጭ ወረቀት ላይ ፊርማውን አኖረ ። መልእክተኛውም ፖስታውን ከዴሚሪስ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና "አመሰግናለሁ" አለ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መልዕክተኛውና ፀሐፊው ወጥተው ሲሄዱ ዓይኑ ተከተላቸው ። ምን ይሆን ? ብሎ እራሱን ከጠየቀ በኋላ ፖስታውን ትንሽ ጊዜ አገላብጦ አየውና ከፈተው ። እውስጡ ቴፕ ሪኮርደርና የቴፕ ክር አገኘ ። ምን እንደሆነ ለማወቅ ንጉቶ የቴፕሪኮርደሩን ማጫወቻ ተጭኖ ማዳመጥ ጀመረ ።

የሚሰማው የናፖሊዮን ቾታስ ድምፅ ነው ።

"ውድ ኮስታ ፣ ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ያቺን ምስጢራችንን የማውጣት ፍላጐት እንዳልነበረው ብታምን ኖሮ ሁሉም ነገር እንዲህ ባልከበደ ነበር ። ስለዚያ መጥፎ ድርጊት ከማንም ጋር ለመወያየት ሀሣብ እንደሌለኝ ባለማመንህ ቅሬታ ተሰምቶኛል ። በምስኪኑ ስታቭሮስ ግድያ ሚራ ውስጥ እጅህ እንዳለበት የሚያመለክቱኝ ብዙ ምክንያቶች አሉ ። አሁንም እኔን የመግደል እቅድ እንዳለህ ተረድቻለሁ ። ሕይወትህ የምታንገህን ያህል የእኔም እንዲሁ ስለምታንገኝ ተከታዩ ዓላማህ ለመሆን ፈቃደኛ አለመሆኔን በትሕትና እገልጽልሃለሁ ። ... ለዚሁም ጥንቃቄ ስል በኖኤል ፒጀና በላሪ ዶግላስ ክስ ወቅት እኔና አንተ የተጫወትናቸውን ሚናዎች በዝርዝር ገልሠ በመጻፍ በታሸገ ፖስታ ውስጥ አድርጌ ለሕግ አስከባሪው አስረክቤያለሁ ። ፖስታውም በአደጋ ሕይወቴ ስታልፍ ብቻ እንዲከፈት በመናዘዜ ፣ ዓዴ ሆይ ፣ ያንተ ደህንነት ዋስትና የሚያገኘው ከኔ ደህና መሆን ጋር ተያይዞ ነውና አስብበት ።"

ቴፑ አበቃ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እዚያው ቁጭ ብሎ ጣራ ጣራውን እያየ ቀረ።

ናፖሊዮን ቾታስ ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ወደቢሮው ሲመለስ ፍርሃቱ ለቆታል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በጣም እደነኛ የመሆኑን ያህል የረቀቀ ዘዴኛም ነው ። እርሱን የሚያጋልጥ ሁኔታ ያለ መስሎ ከተሰማው ግንንም ሰው ለመጉዳት እጁን አይዘረጋም ። 'እርሱ ለእርምጃ ተነሳስቶ ነበር' አለ ቾታስ በአሳቡ ። 'እኔም ገትቼዋለሁ ።' ፈገግ አለ ። "ለሐሙስም እራት ግብዣ ሌላ ብልሃት ማውጣት ይኖርብኛል" ሲል ለእራሱ ተናገረ ።

በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ፡ የባሏን ሁለት ዕቁባቶች ስለ ገደለችዋ ሴት ክስ ዝግጅት ሲያደርግ ሥራ በዝቶበት ነበር ። ቾታስ መስቀለኛ ጥያቄዎችን ለመንደፍ ከእንቅልፉ ማልዶ ይነሳና አምሽቶ ይተኛል ።

ረቡዕ ዕለት ማታ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ቢሮው ውስጥ ሲሠራ ቆየና መኪና እየነዳ ወደቤቱ ሄደ ። ከቤቱ ሲደርስ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ሆኗል ።

የእልፍኝ አሽከሩ እጅ ነሳው ። "ሚስተር ቾታስ የምትፈልገው ነገር አለ ? የራበህ ከሆነ ምግብ ላዘጋጅ እችላለሁ ወይንም ...?"

"አይ ፣ ግድየለም ተኛ ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ወደመኝታ ቤቱ ገባ ። ስለክሱ ለአንድ ሰዓት ያህል ሲያሰላስል ቆይቶ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ላይ እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ። ሕልምም አለመ ።

በሕልሙ ፍርድ ቤት ውስጥ ለአንድ ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርባል ። ምስክሩም በድንገት የራሱን ልብስ መቀዳደድ ይጀምራል ። "ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?" ብሎ ቾታስ ጠየቀው ።

"በእሳት እየጋየሁኝ ነው ።"

ቾታስ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ዞር ብሎ ሲመለከት ሁሉም ልብሳቸውን ያወልቃሉ ።

ወደዳኛው መለስ አለና "ክቡር ጌታዬ ፣ እኔ ይህንን እታወግለሁ ..." አለ ።

ዳኛውም ካባቸውን ማውለቅ ጀመሩ ። "በጣም ይወጠቃል" አሉት እርሳቸውም ። "እዚህ በጣም ይሞቃል ፣ ሜጫታውም በዝቷል ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ዓይኑን ገለጠ ። የመኝታ ቤቱ ከውጭ በኩል በእሳት ተያይዞ የእሳቱ ነበልባል ይታያል ። ከፍሱ በሞስ እየታፈነ ነው ።

ናፖሊዮንን እንቅልፉ ሙሉ በሙሉ እንደለቀቀው ተነስቶ ተቀመጠ ። "ቤቱ በእሳት ተያይዞ እንዴት የአደጋ ጊዜ ምልክቱ አልሠሽም?"

የተጨጨፈው እሳት መዝጊያውን ገንድሶ ጣለው ። ጭሱ እያፈነው ቾታስ ወደመስኮቱ ተነስቶ ሮጠ ። መስኮቱን ለመክፈት ብዙ ቢታገልም በጥብቅ ተቀርቅሮ ኖሮ እምቢ አለው ። ጭሱ የበለጠ ቤቱን እያፈነው ለመተንፈስ ከማያስችልበት ደረጃ ደረሰ ። ምንም የማምለጫ መንገድ አልነበረም ።

በእሳት የተበላው ጣራም መደርመስ ጀመረ ። ግድግዳውም እየተሰነጣጠቀ ቾታስ ላይ ወደቀበት ። በጋይል ሪችፎ ። ወጉሩና የሌሊት ልብሱ በእሳት ተያይዟል ። ዓይኑን ጨፈነና መስኮቱን ሰብሮ ለመውጣት በጋይል ተንደረደረ ። በመስኮቱ ኾልኮ ወደታች እየተንጨረጨረ ስልሳ ጫማ ርቀት ባለው መሬት ላይ ተፈጠፈጠ ።

በሚቀጥለው ቀን የሕግ አስከባሪው ግልዶ ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቤት ደረሰ ። ሠራተኛው ዴሚሪስ ወደሚገኝበት ወደጥናት ክፍሉ አስገባቸው ። “እንደምን አደርክ ፒተር” አለ ዴሚሪስ ። “በመምጣትህ አመሰግናለሁ ። ያንን አመጣኸው ?”

“አዎ ጌታዬ” አለና ናፖሊዮን ቾታስ በአደራ መልክ ሰጥቶት የነበረውን የታሸገ ፖስታ ሰጠው ። “ይህ እርሶ ዘንድ እንዲቆይ ይፈልጉ እንደሆነ ብዬ ነው ።”

“በጣም አስበህልኛል ፒተር ። ቁርስ ይቅረብልህ !”

“ኤፋሪስቶ ፣ ደስ ይለኛል ሚስተር ዴሚሪስ ።”

“ኮስታ ብለህ ጥራኝ ። ለብዙ ጊዜ ዓይኔን ጥዬብህ ቆይቻለሁ ። ፒተር ለወደፊት ጥሩ ዕድል እንደሚኖርህ እገምታለሁ ። በድርጅቴ ውስጥ ለአንተ የሚስማማ የሥራ ቦታ አግኝቼልሃለሁ ። ፈቃደኛ ነህ ?”

ፒተር ዲሞኒዲስ ፈገግ አለ ። “አዎ ኮስታ በጣም ደስ ይለኛል ።”

“ጥሩ ፣ በቁርስ ላይ እንወያይበታለን ።”

ምዕራፍ ዘጠኝ

ለንደን

ካተሪንና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሳምንት አንዴ በስልክ ይገናኛሉ ፡ ይህም እንደልማድ ሆኗል ። ስጦታ በየጊዜው ይልክላታል ፡ ተታውሞዋን ስታሰማ ለሥራዋ አድናቆት ለመግለጽ የሚሰጣት አነስተኛ ስጦታ መሆኑን ይነግራታል ። የባክስተርን ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ መያዝሽን ኤቪሊን ነግራኛለች ወይም ያፈለቅሽው አሳብ በግጓጭ ተግባራችን ላይ ብዙ ገንዘብ ከመከፈል እንዳዳነን ከኤቪሊን ሰምቻለሁ ይላታል ። እውነትም ካተሪን ሥራዋን በጥሩ ሁኔታ በግ ከናወኗ ኩራት ተሰምቷታል ። በቢሮው ውስጥ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ብዙ ነገሮች ለማሻሻል ሞክራለች ።

የድሮው የሥራ ችሎታዋን መልሳ አግኝታዋለች ። እርሷ ከመጣች ወዲህ የቢሮው ሥራ መቀላጠፉን ተረድታለች ።

“እኩራብሻለሁ ” አላት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ።

ካተሪንም ሞቅ አላት ። ‘ምን ዓይነት ለሰው የሚያስብ ደግ ሰው ነው ።’

‘አሁን ሥራዬን የምጀምርበት ወቅት ነው’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ስታቭሮስና ቾታስ በዘዴ ተወግደዋል ። ካለፈው ድርጊቶቹ ጋር ግንኙነት ያላት ካተሪን ብቻ ናት ። በዚህ በኩል ያለው አደጋ መጠነኛ ቢሆንም ቾታስ ከዚህ በፊት ተገንዝቦት እንደነበረው ፡ ዴሚሪስ ቀላሉን ነገር ቸል የሚል አይደለም ። ‘የግድ መሄድ ስለሚኖርባት አዝናለሁ’ አለ ዴሚሪስ በሀሣቡ። ‘በጣም ቆንጆ ናት። ግን በመጀመሪያ ራፊና ያለው ቪላ ።’

ቪላውን ገዛው ። ካተሪንን ወደዚያው ወስዷት ላሪ ዶግላስ ከናኤሉ ጋር እንዳደረገው እሱም ከእርሷ ጋር ወሲብ ሊፈፅም ነው። ከዚያም በኋላ...

ካተሪን ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለፈውን ሕይወቷን እያስታወሰችው መጣች ። የፍሬደሪክ ስታቭሮስና የናፖሊዮን ችታስ መሞት በለን ደን ታይምስ ጋዜጣ ላይ ተጽፎ አነበበች ። ስሞቹ የላሪ ዶግላስና የናኤሉ ፓጂ ጠበቆች መሆናቸውን ለየላት እንጂ ምንም ትኩረቷን አልሳበም ።

ያን ዕለት ግን እንደገና ሕልም አለመች ።

አንድ ቀን ጠዋት ካተሪን ሰጣም ያስደነገጣትን ዜና ከጋዜጣ አነበበች ።

"የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት ሃሪ ትሩማን ረዳት ዊልያም ፍሬዘር ከብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር አዲስ የንግድ ስምምነት ለመፈራረም ስለሚቻልበት ለመወያየት ለንደን ገቡ ።"

ምንም ሳትናገር ጋዜጣውን መልሳ አስቀመጠችው ።'ዊልያም ፍሬዘር' አለች በልቧ ። ሰውዬው በሕይወቷ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የነበረው ነው ። 'ባልተወው ናሮ ኑሮዬ እንዴት ይሆን ነበር ?'

ወንበሯ ላይ እንደተቀመጠች በፈገግታ ጋዜጣውን ተመለከ ተች። ዊልያም ፍሬዘር በጣም ከምትወዳቸው ሰዎች መካከል አንዱ ነበር ። ስለእርሱ ስታስታውስ ልዩ ደስታና ፍቅር ተሰማት ። 'ደ ግሞ እዚሁ ለንደን ውስጥ ነው የሚገኘው ። ሄጄ ማነጋገር አለብ ኝ' ስትል አሰበች ። በጋዜጣው ላይ እንደተጠቀሰው የሠፈረው በክ ላሪጅ ሆቴል ነው ።

ካተሪን ስልክ አንስታ ወደ ሆቴሉ ስትደውል እጇ ይንቀጠቀጥ ነበር ። ያለፈው ሁሉ ተመልሶ ከፊቷ በመደቀን ዛሬም በመፈፀም ላይ ያለ መሰላት ። ፍሬዘርን ለማግኘት መነሳቷ ልዩ የደስታ ስሜት በውስጧ ፈጠረ ። 'ድምፄን ሲሰማ ምን ይል ይሆን? እንደገና ሲያየ ኝስ?'

የስልኩ አገናኝ "እንደምን አደሩ ፣ ክላሪጅ ሆቴል" አለች ።

ካተሪን በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰችና "እባክዎትን ሚስተር ዊል ያም ፍሬዘርን ነበር ።"

"ይቅርታ እመቤት ፣ ሚስተር ነው ወይስ ሚሲስ ፍሬዘርን ነው ያሉት?"

ካተሪን ግጅራቷን የተመታች ይመስል ከው አለች ። 'ምን ዓይነቷ ሞኝ ነኝ ። መጀመሪያውም ስለዚህ ማሰቤ! መቼም እስካሁን ሊያገባ ይችላል' ስትል ራሷን ታዘበች ።

"ማዳም..."

"እ...ግድ የለም ይቅር አመሰግናለሁ ።" ቀስ ብላ ስልኩን ዘጋች ።

'ተንከርፍፈያለሁ ። ከእንግዲህ አለቀለት ኮስታ እውነቱን ነበር። ያለፈው ነገር እንዳለፈ ሆኖ ይቅር ።'

ብቸኝነት ጨው እንደነካው ብረት ውሎ አድሮ ይመዘምዛል ። ሰው ደስታውን ፣ ድሉንና ሕመሙን የሚካፈልለት መሰል ፍጡር ይሻል ። ካተሪን በግታውቀው እንግዳ ዓለም ውስጥ የምትገኝ ስት ሆን ሌሎች የወንድና የሴት ጓደኛሞች ሲደሰቱ ታያለች ፣ ፍቅረኞች ሲሳሳቁ ትሰማለች ። እንደዚያም ሆኖ በዕድሏ ላለማዘን ደግሞ ቆር ጣለች ።

'በዚህ ዓለም ውስጥ ብቸኛዋ ሴት እኔ ብቻ አይደለሁም ። አልሞትኩም! በሕይወት አለሁ!' እያለች እሯሷን ታፅናናለች ።

በለንደን ውስጥ የሚሠራ ነገር አይጠፋም ። የለንደን ሲኒማ ቤቶች በአሜሪካ ፍልሞች የተሞሉ በመሆናቸው ካተሪን በየጊዜው እነኚህን ግየቱ ያረካታል ። 'ዘሬዘርስ ኤጅ' እና 'ዘኪንግ አፍ ሲአም' የተባሉትን አይታለች ። 'ጂንትልማንስ አግሪሜንት' የሚ ረብሽ ፊልም ሲሆን ኬሪ ግራንድ በ'ዘባችለር ኤንድ ዘቦቢ ሶክሰር' ውስጥ ቆንጆ አድርጉ ተውኗል ።

ካተሪን በአልበርት ሆል ሙዚቃ አዳምጣለች ፣ በላድለርስ ዌል የባሌት ዳንስ ተመልክታለች ። ወደስትራትፎርድ አፖን አቮን ሄዳም አንቶኒ ኩዌል በተሚንግ ኦፍ ዘ ሽሩ ተውኔት ውስጥ ሲሰራ፣ ሲር ሎሬንስ ኦሊቭር በሪቻርድ ተውኔት ውስጥ ሲተውን አይታለች።

እንዲያም ሆና ሙሉ ደስታ አታገኝም ነበር ። ኋላ ላይ ኪርክ ሪናል ድስ መጣ ።

ቢሮዋ ውስጥ ተቀምጣ እንዳለች ከቁመቱ ረዘም ያለ መልከ መልካም ሰው ከእርሷ ዘንድ ደረሰ ። "ኪርክ ሪናልድስ እባላለሁ ። እስካሁን የት ነበርሽ?" አላት ።

"ምን አልከኝ?"

"ስጠብቅሽኩ ነበር ።"

ነገሩ እንግዲህ እንደዚህ ነበር የተጀመረው ።

አሜሪካዊው ኪርክ ሪናልድስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተጠቃለ ሉት የኮንስታንቲን ዲሚሪስ ንግድ ኩባንያ ጠበቃ ነው ። በአስተሳ ሰቡ ጥብቅ አስተዋይ የሆነና ዕድሜውም በአርባዎቹ ውስጥ የሚገ መት ነው ።

ካተሪን ስለኪርክ ሪናልድስ ለኤቪሊን ስታወራ ፣ "ስለእርሱ ደስ የሚለኝ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ሴትነቱ እንዲሰማኝ ያደርገ ኛል ። እንደዚያ ዓይነት ስሜት ሳይመጣብኝ ብዙ ጊዜ ሆኖታል" አለቻት።

"እንጃ" አለች ኤቪሊን ። "አንቺን ብሆን ጥንቃቄ አደርጋለሁ ። ለሁሉም ነገር አትቸኩዪ!"

"እሱስ አልቸኩልም" ብላ ካተሪን ቃል ገባችላት ።

ኪርክ ሪናልድስ ካተሪንን በለንደን ውስጥ አንሸራሸራት ። ከመቶ ዓመታት በፊት የወንጀለኞች ጉዳይ ይታይበት ወደነበረው ጥንታዊ ግምብ በመሄድ ሰው ሰራሽ ፀጉርና የቡና ቤት አስተናባሪ ልብስ የለበሱ መልከ ጥፉ ሰዎችን እያለፉ በችሎቱ አዳራሽ ውስጥ ተንጐራደዱ ። በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፈለ ዘመን የተሠራው ንም የኒውጌት ወህኒ ቤት ከውጭ ጐበኙ ። ከወህኒ ቤቱ ፊት ለፊት ሰፋ ብሎ የሚታየው መንገድ ብዙም ሳያስኬድ ጠበብ ብሎ ይታ ያል ።

"ይህ ያልተለመደ እንግዳ ነገር ነው" አለች ካተሪን ። "መንገ ዱን ለምን በዚህ ዓይነት እንደሠሩት ገርሞኛል ።"

"ሰፋ ያለው ብዙ ተመልካች እንዲይዝላቸው ታስቦ ነው ። የሞት ቅጣት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች በሕዝብ ፊት የሚረሽኑት እዚሁ ሥፍራ ነው ።"

ካተሪን ደንገጥ አለች ። አባባሉ የእርሷንም ቁስል ነካካው ።

አንድ ቀን ምሽት ኪርክ ሪናልድስ ካተሪንን በፒርስ አድርጐ ወደ ኢስት ኢንዲያዶክ ጐዳና ወሰዳት ።

"ከቅርብ ጊዜ በፊት እዚህ ላይ ፖሊሶች መንታ ሆነው ነበር የሚጓዙት" አላት ። "ወንጀለኞች የሚሰቀሉት እዚሁ ነው ።"

አካባቢው ጨለማና አስፈሪ ስለነበረ ካተሪን ስጋት አደረባት።

ከቱምስ ወንዝ ላይ በተሠራው የእንግሊዝ ጥንታዊ አነስተኛ የዊትቢ ሆቴል ፎቅ ላይ ሆነው ወደ ባሕር የሚገሰግሱትን መርከ ቦች እያለፉ ቁልቁል የሚበሩትን ጀልባዎች እየተመለከቱ እራታቸ ውን በሉ።

ካተሪን ከሌላ ሥፍራ ልዩነት ያላቸውን የለንደን ሆቴሎች ስያሚ ትወደዋለች ። በሌላ ምሽት ደግሞ በሲቲ ጐዳና ላይ የሚገኘ ውን ዘኢግል የተሰኘውን ውብ ሕንፃ ጐበኙ ።

"ሕፃን በነበርሽበት ወቅት ስለዚህ ሥፍራ መዝሙር ሳትዘምሪ እንዳልቀረሽ እርግጠኛ ነኝ" አላት ኪርክ ።

ካተሪን ትኩር ብላ አየችውና "መዘመር ቀርቶ ስለሥፍራውም ሰምቼ አላውቅም ።"

"ሰምተሻል እንጂ ። ዘኢግል የሚባለው ይህ ሥፍራ የድሮ የሕፃናት ግጥሞች ምንጭ ነው ።"

"የምን የሕፃናት ግጥም?"

ከብዙ ዓመታት በፊት የሲቲ ጐዳና የልብስ ሰፊዎች መናኸ ሪያ ነበር ። ቅዳሜና እሁድ ልብስ ሰፊዎች የገንዘብ እጥረት ስለሚያ ጋጥማቸው ካውያቸውንና ሌሎች የሥራ መሣሪያዎቻቸውን በአራጣ አስይዘው ደመወዛቸው ሲደርስ ያስለቅቃሉ ። ይህን በሚመለከት አንድ ሰው እንዲህ እንዲህ ሲል ግጥም ጽፎ ነበር —

"እላይ እታች በጐዳናው
ወጣ ገባ በኢግልም
እንዲያ ነበር ገንዘብ ሲሄድ

እንደ ጥይት ሽው አልም ።”

ካተሪን ከት ብላ ሳቀች ። “ይህንን እንዴት ለማወቅ ቻልክ?”

“የሕግ ባለሙያዎች ሁሉንም ነገር እንዲያውቁ ይጠበቅባቸዋል ። ግን የማላውቀው አንድ ነገር አለ ። የበረዶ ላይ ሽርተቴ መቻል አለመቻልሽን እርግጠኛ አይደለሁም ።”

“አልችልም ። ለምን...?”

ወዲያውኑ ኮስተር አለ ። “ወደ ቅዱስ ሞሪዝ መሄዴ ነው ። እዚያ ጉበዝ የሆነ የበረዶ ሽርተቴ መምህር አለ ። አብረሺኝ ልት ሄጂ ትቺያለሽ ካተሪን?”

ጥያቄው የተለየ ስሜትን ፈጠረባት ። ኪርክም ምላሽዋን ይጠብቅ ነበር ።

“እኔ...እኔ እንጃ ኪርክ”

“ለወደፊት ታስቢበታለሽ?”

“አዎ” አለች ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ ፤ ከላሪ ጋር መተኛት ምን ያህል ደስታ ይሰጣት እንደነበር አስታወሰች ። ሁለተኛ እንደዚያ ዓይነት ስሜት ይኖረኛል ብላ አትገምትም ። “እሺ አስብበታለሁ ።”

ካተሪን ኪርክን ከዊም ጋር ለማስተዋወቅ ወሰነች ።

ሁለቱም ተያይዘው ወደዊም ቤት በመጓዝ እራት ሊጋብዙት ወሰዱት ። በዚያች ምሽት አንዲት ጊዜ እንኳ ዊም ቀና ብሎ በትኩረት ኪርክ ሪኖልድስን አላየውም ። በአካሉ እንጂ በሀሳቡ ከእነርሱ ጋር አልነበረም ። ኪርክ ወደካተሪን ሲያይ ካተሪን በምልክት “አንጋግረው” አለችው ።

ክርኪ በአምንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀና ወደዊም ዞር አለ ።

“ለንደንን ወደድከው ዊም?”

“ደህና ነው”

“በጣም የምትወደው ከተማ አለ?”

“የለም ።”

“በመደበኛ ሥራህ ትደሰታለህ?”

“ደህና ነው ።”

ኪርክ ወደካተሪን ዞር አለና ጭንቅላቱን ነቅንቆ ትከሻውንም

ከፍ ዝቅ አደረገ ። ካተሪን አውንም በምልክት “እባክህ” ብላ ተማፀነችው ።

ኪርክ ስቆ አውንም ወደዊም ዞር አለ ። “በሚመጣው አውድ ጉልፍ ልጫወት አስቤያለሁ ። ከኔ ጋር አትጫወትም?”

ዊም ድርደራውን ጀመረ ። “የጉልፍ መምቻና የብረት አናት ክፍል ፡ መግፊያ ማሺ ፡ ማሺ ብረት ማሺ አካፋ ማሺንብሊክ ንብሊክ አጭሩ ንብሊክ እና ፑተር ናቸው ። የእንጨት አናት ያለው መምቻ ክፍሎች ደግሞ መግፊያ ማንኪት እና ባፊ ናቸው ።”

ኪርክ ሪኖልድስ ፈገግ አለ ። “በጣም ጉበዝ ተጫዋች ሳትሆን አትቀርም።”

“ተጫውቶ አያውቅም” አለች ካተሪን ። “ዊም ብዙ...ያውቃል ። ሒሣብን በተመለከተ የማይሰራው ምንም ነገር የለም ።”

ኪርክ ሪኖልድስን እዚህ ላይ በቅቶታል ። ምሽቱን ከካተሪን ጋር ብቻ ተደስቶ ለማሳለፍ ተስፋ አድርጉ ነበር እንጂ ይህን ጅል ታመጣብኛለች ብሎ አላሰበም ነበር ።

ኪርክ በግድ ፈገግ አለ ። “እውነት?” “ሲል ወደዊም ዞር ብሎ በቅን ልቦና ፡ “የ59ን ደግሞ ርቢ ታውቃለህ?” ሲል ጠየቀ ።

ዊም ለሰላሣ ሴኮንድ ያህል ሲያሰላ በፀጥታ ቁጭ ብሎ ቆየና ኪርክ ለመናገር ትንሽ ሲቀረው “576 ፡460 ፡ 752 ፡ 303 ፡ 423 ፡ 488” ብሎ መለሰ ።

“የክርስቶስ ያለህ!” አለ ኪርክ ። “ግን መልሱ እውነት ልክ ነው?”

“አዎ” አለ ዊም በኩራት ። “ትክክል ነው ።”

ካተሪን ወደዊም ዞር አለችና ዊም ፤ “የ6√24 ፡ 137፡ 585 ን መልስ ታውቃለህ?” ብላ ጠየቀችው ።

ዊም ጭንቀት ሳይታይበት ሲያሰላ ሁለቱም በዝምታ አዩት ። ከሃያ አምስት ሴኮንድ በኋላ መለሰ ፡ “አሥራ ሰባት ሆኖ ቀሪው አሥራ ስድስት ነው ።

“ለማመን አልችልም” አለ ኪርክ ።

“እመን” አለች ካተሪን ።

ኪርክ ወደዊም ተመለከተ ። “እንዴት ነው እንዲህ የሚሆንልህ?” ዊም ተቁነጠነጠ ።

ካተሪን “ዊም ሁለት የሺህ ቤት ቁጥሮችን በሰላሳ ሴኮንድ ውስጥ አባዝቶ ማወቅ ይችላል ። ሃምሳ የስልክ ቁጥሮችን በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሽምድዶ ሊይዝ ይችላል ። አንዴ በአእምሮው ውስጥ ከከተታቸው ደግሞ ጨርሶ አይረሳቸውም ።”

ኪርክ ሪናልድስ ተገርሞ ዊም ቫንዲንን አተኩሮ ያየው ነበር።

“ቢሮዬ እንደአንተ ያለውን ሰው ሊገለገልበት ይፈልጋል።”

“እኔማ ሥራ ይዤያለሁ” አለ ዊም ።

ኪርክ ሪናልድስ ካተሪንን ወደ ቤቷ መልሶ ከመኪናው ስትወርድ “ስለ ቅዱስ ሞሪዝ አትረሺም አይደል?” ብሎ ጠየቃት ።

“የለም አይረሳኝም” አለችው መልሳ ። ‘ግን ፤ ለምን ይረሳኛል ለማለት አቃተኝ?’ አለች በሀሣቧ ።

ያንን ዕለት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ዘግይቶ ስልክ ደወለላት ። ካተሪን ስለ ኪርክ ሪናልድስ ልትነግረው ብላ ነበር ። በኋላ ግን ላለ መንገር ወሰነች ።

ምዕራፍ አሥር

አቴንስ

ቄስ ኮንስታንቲኑን አንድ ነገር በጣም አድርጉ አሳስቧቸዋል። የፍሬደሪክ ስታቭሮስን በመኪና ተገጭቶ መሞትና የመኪናውንም ማምለጥ ዜና ከጋዜጣ ላይ ካነበቡ ጀምሮ ልባቸው በጣም ተሸብሯል። ቄሱ የክህነት ሥልጣን ከተቀበሉ አንስቶ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኑዛዜዎችን ተቀብለዋል ፣ ግን የፍሬደሪክ ስታቭሮስ ኑዛዜ የማይሽር የጎሊና ቄስል አድርሶባቸዋል ።

“የሚያሳስብዎት ምንድን ነው?“ ሲላቸው ቄስ ኮንስታንቲን ዞር ብለው ከቤታቸው ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን መልክ መልካም ወጣት አዩትና “ምንም የኔ ወዳጅ” ብለው መልስ ሰጡ ።

“ታዲያ ምን ነካዎት ?”

“በጣም አዝናለሁ አንድ የንስሐ ልጄ በአውቶሞቢል አደጋ በመሞቱ ነው ።”

“ሞትማ ለሁላችንም አይቀር ።”

“አዎ ፤ ቢሆንም ሰውዬው በጣም የተጨነቀ ሰው ነበረ ።”

“ማለት አዕምሮው ተቃውሷል ነው የሚሉት?”

“አይ ፤ አንድ ጥብቅ ምስጢር ነበረው ። ይህንኑ አምቆ ይዞ ለማቆየት ተቸግሮ ነው ።”

“ምን ዓይነት ምስጢር?”

ቄሱ ኮስተር ብለው ወደ ወጣቱ ዞሩና “ታውቃለህ አይደል? በንስሐ መልክ የተነገረኝን ምስጢር ሌላ ቦታ ማባከን የለብኝም ።”

“አይ ከእኔ የሚደብቁት ምስጢር የለም ብዬ ነው ።”

“እርሱማ የለም ፤ ጂኦርጂአስ ፤ ግን ...”

“ያም ሆነ ይህ ሰውዬው ሞቷል ። ታዲያ ምስጢሩን መደበቅ ምን ለውጥ ያመጣል?”

“ምንም ፤ የእኔ ግምት ግን...” አሉና በመጨረሻ ነገሩን ዘርዝረው ለጂኦርጂአስ ላቶ አሜወቱት ።

ጂአርጂአስ ላቶ የተወለደው በአቴንስ ከተማ ውስጥ ቆሻሻማ አካባቢ ነው ተብሎ ከሚታወቀው ሠፈር ውስጥ ነው ። ዕድሜው አሥራ ሁለት ሲሆነው የለየለት ዱርዬ ሆነ ። በመጀመሪያ በአቴንስ ጉዳናዎች ላይ እየተዘዋወረ መጠጥ በመሸጥ ፣ ለቱሪስቶችም ልዩ ልዩ አገልግሎት በማበርከት ገንዘብ ያገኝ ነበር ። ጠየም ያለው ፊቱና ፈርጠም ያለ ሰውነቱ ለመላ አካሉ ውበትን ሰጥቶታል ።

የላቶ ኑሮ የተለወጠው የስፒሮስ ላምብሩ ረዳት ከሆነው ኒኮስ ቬሪቶስ ጋር ከተዋወቀ በኋላ ነው ። ሁለቱ ሰዎች በወዳጅነት ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ቬሪቶስ ላቶን በላምብሩ ድርጅት ውስጥ አስቀጠረው ። በመጀመሪያ ጂአርጂአስ ላቶ ጥያቄውን ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆንም በኋላ ተስማምቶ ሥራውን ጀመረ ። በኩባንያው ውስጥ መሥራቱ ደስታን እየሰጠው መጣ ። የኩባንያው ፖስታና መልእክት አመላላሽ ሆኖ መሥራቱ ሌሎች ሰዎችን እንዲተዋወቅና ተጨማሪ የጉርሻ ገንዘብም እንዲያገኝ ረድቶታል ። ቁስ ኮንስታንቲንንም የተዋወቃቸው ያኔ ነበር ።

ጂአርጂአስ ላቶ ያን ዕለት ከሰዓት ከቁስ ኮንስታንቲኑ ቤት ከወጣ በኋላ በአእምሮው ውስጥ ብዙ ነገር መመላለስ ጀመረ ። ቁሱ የነገሩት ምስጢር በጣም ተፈላጊና ጠቃሚ ዜና ነው ። ከዚህም እንዴት አድርጐ ገንዘብ ማግኘት እንደሚችል ያወጣ ያወርድ ጀመረ ። 'ለኒኮስ ቬሪቶስ ብነግረው ደስ ይለው ነበር ።' ግን ከዚህ የተሻለ እቅድም መጣለት ። 'ዜናውን ይዤ በቀጥታ ወደትልቁ አለቃ እሄዳለሁ' አለ ላቶ ለአራሱ ። 'ጥሩው ገንዘብ የሚገኘውም ከዚያው ነው ።'

በሚቀጥለው ቀን ላቶ ወደ ስፒሮስ ላምብሩ ፀሐፊ ቢሮ ገባ ።

መቀመጫዋ ላይ የነበረችው ፀሐፊ ቀና አለችና "እሃ፣ ዛሬስ ፖስታው ቶሎ መጣ ጂአርጂአስ" ብላ ተናገረች ።

ጂአርጂአስ ላቶ ሞንቅላቱን ነቀነቀና "አይደለም እመቤቴ ፣ ሚስተር ላምብሩን ማነጋገር ፈልጌ ነው" አላት ።

ፈገግ አለችና "የምርህን? ስለምን ጉዳይ ልታነጋግረው ፈልገህ ነው? ስለሥራ ጉዳይ የምታቀርበው አሳብ አለህ?" አለች በምፀት አነጋገር።

ላቶ ኮስተር አለና "አይደለም ፣ ከምትዪው ጋር ግንኙነት የለ

ውም ። እናቴ ልትሞት መቃረቧን ሰማሁ ። ስለዚህ እኔ...እኔ ወደዚያው መሄድ አለብኝ ። ሚስተር ላምብሩ እዚህ ቀጥሮ ያሠራኝ ስለነበረ ላመሰገነው ነው ። ከአንድ ደቂቃ በላይ ጊዜ አልወስድም ። ግን ሥራ ከበዛበት..." ብሎ ወደ ኋላ ዞር ብሎ ለመሄድ ተነሳ ።

"ቆይ ፣ ቅር የሚለው አይመስለኝም ።"

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ጂአርጂአስ ላቶ ከስፒሮስ ላምብሩ ቢሮ ውስጥ ቆሞ ነበር ። እዚህ ቢሮ ውስጥ ከዚህ ቀደም ገብቶ አያውቅም ። የቢሮው ውበትና ምቾት በጣም አስደነቀው ።

"መልካም ፣ አንተ ወጣት እናትህ ልትሞት መቃረቧን በመስማቴ በጣም አዘንኩ ። ምናልባት ጥቂት ጉርሻ..."

"አመሰግናለሁ ጌታዬ ። እዚህ የመጣሁበት ምክንያት በእርግጥ ይህ አይደለም ።"

ላምብሩ ግንባሩን ኮስተር አደረገና "አልገባኝም" አለው ።

"ሚስተር ላምብሩ አንተን በጣም ይጠቅምሃል ብዬ የማስበው ተፈላጊ ወሬ አለኝ ።"

በጣም የመጓጓት ዓይነት ገጽታ ከላምብሩ ፊት ላይ ይነበብ ነበር ። "እሃ ፣ እውነትህን ነው? አሁን ትንሽ ሥራ የበዛብኝ መሰለኝ ። ምናልባት ..."

"ስለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው!" አለና እቅጩን አፈረጠ ። "በጣም ወዳጄ የሆኑ አንድ ቁስ አሉ ። ወዲያውኑ በመኪና አደጋ የተገደለ አንድ ሰው ኑዛዜውን አሰምቷቸው ነበር ። ለሰውዬው ነግሯቸው የነበረው ስለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ሚስተር ዴሚሪስ በጣም አሰቃቂ ነገር ነው የሚሠራው ። በእውነት በጣም የሚዘገንን። በዚህም ጥፋቱ ወህኒ ሊወርድ ይችላል ። ግን አንተ ለመስማት የማትፈልግ ከሆነ..."

ስፒሮስ ላምብሩ ነገሩን ለመስማት በጣም ጓጓና "ቁጭ በል ...ስምህ ማነው?" አለው ።

"ላቶ ጌታዬ ፣ ጂአርጂአስ ላቶ ።"

"መልካም ፣ ላቶ ፣ እስቲ ከመጀመሪያው ጀምር ..."

የኮንስታንቲን ዴሚሪስና የሜሊና ትዳር ለብዙ ዓመታት የጭቅጭቅ መድረክ ነበር ። ሆኖም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በመሐላቸው ድብድብ ታይቶ አያውቅም ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የሜሊናን የቅርብ ጓደኛ በማውጣቱ ባልና ሚስቱን ከባሰ ብጥብጥ ላይ አድርሷል ።

“ያየሃትን ሴት ሁሉ አትምርም ማለት ነው” አለች ሜሊና በጩኸት “ሁሉንም ካልነካካህ ሞትህ ነው።”

“ይህን ክፍት አፍሺን ብትዘጊ ይሻልሻል ።”

“አፌን ልታዘጋኝ አትችልም” አለች ሜሊና በድፍረት ። “ምን ዓይነት ቅሌታም ሴሰኛ እንደሆንክ ለመላው ዓለም ላሳውቅ ነው ። ወንድሜ እውነቱን ነበር ። ተወዳዳሪ የሌለህ አረመኔ ነህ ።”

ዴሚሪስ ፊቷ ላይ በጥፊ ሲመታት ከክፍሉ ወጥታ ሮጠች ።

በሚቀጥለው ሳምንት ሌላ ጭቅጭቅ በመካከላቸው ተነሳና አሁንም እንደገና መታት ። ሜሊና ሻንጣዋን ይዛ የወንድሟ የግል ደሴት ወደሆነችው አቲኮስ በአውሮፕላን በረረች ። እዚያም ልቧ በጣም ተሰብሮ ብቻዋን ለአንድ ሳምንት ያህል ቆየች ። ቧሏ ናፈቃ ትና ለጥፋቱ የይቅርታ ምክንያት በአእምሮዋ ውስጥ መደርደር ጀመረች ።

‘ጥፋቱ የእራሴ ነው’ አለች ሜሊና በአሳቧ ። ‘ኮስታን ማና ደድ አልነበረብኝም ። የመታኝ በጣም ስለተናደደ እራሱን መቆጣጠር አቅቶት ነው ። ኮስታ በጣም ባይወደኝ ኖሮ አይመታኝም ነበር።’

እነኚህን የይቅርታ ምክንያቶች የምትደረድረው ትዳሯን ላለማ ፍረስ መሆኑን ሜሊና ወደ ኋላ ተረድታለች ። በሚቀጥለው አሁድ ወደ ቤቷ ተመለሰች ።

ዴሚሪስ ቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ተቀምጧል ።

ሜሊና ስትገባ ቀና ብሎ ተመለከታትና “እና ልትመለሺ ወሰ ንሽ?” አላት ።

“ይህኮ ቤቴ ነው ኮስታ ። አንተ ባለቤቴ ነህ ፣ ደግሞም እወ ድሃለሁ ። ግን አንድ ነገር ልንገርህ ። ሁለተኛ ሜፈን ከነካህ እገድ ልሃለሁ ።”

ዓይኗን ትኩር ብሎ ሲያይ የምሯን መሆኑ ታወቀው ።

ከዚያ በኋላ የጋብቻ ግንኙነታቸው በመጠኑ የተሻሻለ ይመስል ነበር ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስም ከንዴት እራሱን መቆጣጠር ከጀ መረ ሰንበት ብሏል ። ከሌሎች ጋር መግጠሙን ግን አላቆመም ።

ሜሊናም ይህንን ርኩስ ተግባሩን እንዲያቆም መጫኗን ተወች ። ‘ጋለሞታዎቹን ሁሉ የሚሰለችበት ቀን ይመጣል’ አለች በአሳቧ። ‘እኔ ብቻ እንደምበቃው የሚገነዘብበት ቀን ይመጣል ።’

ቅዳሜ ዕለት ምሽት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደ ውጭ ለመው ጣት የእራት ኮት ሲለብስ ሜሊና ፣ ወደ ክፍሉ ገባች ።

“የት ልትሄድ ነው?”

“ቀጠሮ አለኝ”

“ረሳህ እንዴ? ዛሬ ማታኮ ስፒሮስ ዘንድ እራት ተጋብዘናል።”

“አልረሳሁም ። ግን ከሱ የበለጠ ነገር አጋጥሞኝ ነው ።”

ሜሊና በንዴት ቆማ አየችው። “ምን እንደሆነ እንኳ አውቀዋ ለሁ ። ወደ ጋለሞታህ ልትሄድ ነው አይደል?”

“ምላስሽን ብትሰበስቢው ይሻላል ። ጨቅጫቃ ሚስት እየሆ ንሽ ነው ሜሊና” አለና በመስተዋቱ ውስጥ እራሱን መመልከት ጀመረ ።

“እንዲህ ስትሆን ዝም ብዬ አላይህም!” በሷ ላይ የሚፈፅመው በደል አልበቃ ብሎት ወንድሟን በግልፅ መስደቡ አሳርሯታል ። ስለዚህ እሱን የምትጐዳበት መንገድ ማግኘት ነበረባት ። እንድ መንገድ ብቻ ነው ያላት ። “ዛሬ ማታ ሁለታችንም እቤት መቆየት አለብን” አለችው ሜሊና ።

“እውነትሽን ነው?” አለ በሽሙጥ አኒጋገር ። “እኮ ለምን?”

“ዛሬ ቀኑ ምን እንደሆነ አታውቅም ?” ብላ ሳቀችበት ።

“አላውቅም ።”

“ልጅህን የገደልኩበት መታሰቢያ ቀን ነው ኮስታ ። ራሴ አስ ወጥቼው ነው ።”

ከው አለ ። የዓይኑ ብሌን ቀለም የበለጠ ሲጠቁር ታያት ።

“ከአንተ ሌላ ልጅ በማኅፀኔ ለመቋጠር ስላልፈለግኩም ነበር ዶክተሮቹ ማኅፀኔን እንዲዘጉት ያደረግሁኝ” ስትል ዋሸች ።

እራሱን መቆጣጠር እቃተው ። በጥፊ መታት ፣ ቀጥሎም ይቀ ጠቅጣት ጀመር ። ሜሊና እየጮኸች አምልጣው ወደሳሎኑ ሮጠች። ዴሚሪስ ተከተላት ። ከሳሎኑ መውጫ ላይ ስትደርስ ከኋላ ያዛት ።

“ስለዚህ ሥራሽ እንድልሻለሁ” ሲል እንቧረቀባት ። እንደገና ሲመታት ሜሊና ጎሊናዋን ስታ ከደረጃው ተንከባላ ወደቀች ።

ኃይለኛ ሕመም ስለተሰማት ከታች ሆና ማቃሰት ጀመረች ። “አቤት አምላኬ ፣ እባክህ እርዳኝ ። ተሰብሬአለሁ ።”

ዴሚሪስ እዚያው ቆሞ ዓይኑን እያጉረጠረጠ አያት ።

“ሠራተኛ ዶክተር እንድትጠራልሽ አዛለሁ ። ለቀጠሮዬ ዘግ ይቺ መድረስ አልፈልግም ።”

እራት ከመቅረቡ ጥቂት ቀደም ብሎ ስልክ ተደወለ ።

“ሚስተር ላምብሩ? ዶክተር ሜታክሲስ እባላለሁ ። እህትህ እንድደውልልህ ጠይቃኝ ነው ። ትንሽ አደጋ ስላጋጠማት እዚህ የግል ሆስፒታል ውስጥ ነው የምትገኘው ፣ አደጋ አጋጥሟታል ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ሜሊና ወደተኛችበት ክፍል ገባና ወደ አልጋዋ ተጠግቶ በድንጋጤ ትኩር ብሎ አያት ። ሜሊና እጇ ተሰብሯል ፣ እራሷ ላይ ትንሽ የመቀጥቀጥ ጉዳት ደርሶባታል ፣ ፊቷም ቆሳስሏል ።

ስፒሮስ ላምብሩ አንድ ቃል አሰማ ። “ኮንስታንቲን!” ሲል ድምፁ በንዴት ተንቀጠቀጠ ።

የሜሊና ዓይኖች እንባ አቀረሩ ።

“አውቆ አይደለም” ስትል ዝቅ ባለ ድምፅ ተናገረች ።

“ፈፅሞ ላጠፋው ነኝ ፣ የሕይወት መስዋዕትነት ቢጠይቅም።” ከዚህ ቀደም ስፒሮስ ላምብሩ እንዲህ ሲናደድ ታይቶ አያውቅም ።

ላምብሩ ፣ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሜሊና ላይ በሚፈጽመው ግፍ ተንገፍግፎል ። ከዚህ ድርጊቱ እሱን ለመግታት የሚቻልበት መንገድ መኖር አለበት ። ግን እንዴት? ለዚህ መልስ ሊያገኝለት አልቻለም ። ስለዚህ ምክር እንደሚያስፈልገው አወቀ ። ከዚህ ቀደም ያደርግ እንደነበረው ማዳም ፒሪስን ለማማከር አቀደ ። ምና ልባት እርሷ ልትረዳው የምትችልበት ዘዴ ይኖር ይሆናል ።

ወደ እርሷ በመሄድ ላይ እያለ ላምብሩን ስጋት ተሰማው ።‘ጓ ደኞቹ ኮከብ ቆጣሪ ዘንድ እየሄድኩ ማስጠንቀሌን ካወቁ ይስቁብኛ ል’ ሲል ተጨነቀ ። ግን ማዳም ፒሪስ ከነገረችው ውስጥ መሬት ጠብ ያለ የለም ። ‘የለም፣ ልትረዳኝ ይገባል’ አለ በአሳቡ ።

ደብዘዝ ያለ ብርሃን ካለበት ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ ከጥግ ቁጭ ብለው ነበር ። ባለፈው ጊዜ ካያት የበለጠ ያረጀች መስላ ታየችው ። ከወንበሯ ላይ ሆና አተኩራ ታየዋለች ።

“ዕርዳታ እፈልጋለሁ ማዳም ፒሪስ” አለ ላምብሩ ። ጭንቅላቷን በእምንታ አወዛወዘች ።

‘ከየት ልጀምርላት ይሆን?’ ሲል ተጨነቀ ።

“ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት ፍርድ ቤት የቀረበ የወንጀል ክስ ነበረ ። ካተሪን ዶግላስ የተባለች ሴት...”

የማዳም ፒሪስ ፊት ሲለዋወጥ አየ ። “ተው ፣ ተው” አለች ።

ስፒሮስ ላምብሩ ግራ በመጋባት ተመለከታት ። “እርሷ የተገደለችው...”

ማዳም ፒሪስ ከተቀመጠችበት ብድግ አለችና “አልሞተችም ፣ መንፈሴ ገና ወደፊት እንደምትሞት ነው የሚነግረኝ” ስትል ተናገረች ።

ስፒሮስ ላምብሩ ተምታታበት ። “ሞታ የለ እንዴ?” አለ ። “የተገደለችው በ...”

“በሕይወት ትገኛለች!”

ፈጽሞ ግራ ተጋባ ። “ልትገኝ አትችልም ።”

“ከሦስት ወራት በፊት ልታየኝ እዚህ መጥታ ነበር ። በሴቶች ገዳም ውስጥ አስቀምጠዋታል ።”

ፈዘ በዝምታ አያት ። አሁን ሁሉም ነገር ግልጽ ሆነ ። ‘በሴ ቶች ገዳም ውስጥ አስቀምጠዋታል።’ ዴሚሪስ ከሚፈጽማቸው የበጉ ተግባራት መካከል አንዱ በኢኢና ለሚገኘው የሴቶች ገዳም በየጊዜው የገንዘብ ዕርዳታ ማድረግ ነው ። ይህ ቦታ ካተሪን ዶግላስ ልትገደል የነበረበት ሥፍራ ነው ። ከኤሌክትራ ጂኦርጂአስ ያገኘው መረጃ ትክክል መሆኑን ስፒሮስ ላምብሩ አሁን ተረዳ ። ካተሪንን ገድላችኋል ብሎ ዴሚሪስ ሁለት ንፁሐን ሰዎችን በጥይት አስደ

ብድቧል ። እርሷን ግን ሴት መነኩሴዎች ደብቀዋት በሕይወቷ ትገኛለች ።

እና ፣ ላምብሩ እንዴት አድርጉ ኮንስታንቲን ዴሚሪስን እንደ ሚያጠፋ አሁን ተገንዝቧል ።

‘ቶኒ ሪዞሊ ።’

ምዕራፍ አሥራ አንድ

የቶኒ ሪዞሊ ችግሮች ተበራክተዋል ። ሁሉም ነገር እየተበላሸበት ነው ። ለተፈጸመው ነገር ተጠያቂ ባይሆንም ሽሪኮቹ እሱ ላይ እንደሚያላክኩ ያውቃል ፣ ሰዎቹ ምክንያትና ሰበብ የሚቀበሉ አይደሉም።

ጉዳዩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደረገው ነገር ቢኖር የአደንዛዥ ዕፅ አጓጓዝ የመጀመሪያ ደረጃ ሥራ በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙ ነው ። አደንዛዥ ዕፅን ደብቆ አቴንስ ውስጥ ያለ እንቅፋት በማስረግ በጊዜያዊነት ከአንድ መጋዘን ውስጥ አከማችቶታል ። ከአቴንስ ወደኒውዮርክ ለሚበር አውሮፕላን አስተናጋጅ ጉቦ ሰጥቶ ዕቃውን በሥውር ሊያወጣ ተዘጋጅቶ ነበር ። በረራው ከመጀመሩ ከሃያ አራት ሰዓት በፊት አስተናጋጁ ሰክሮ መኪና ሲያሽከረክር ተይዞ ታሰረና ከሥራውም ተባረረ ።

ቶኒ ሪዞሊ ሌላ አማራጭ ዘዴ መፈለግ ነበረበት ። ልጇን ለመጠየቅ ወደአቴንስ መጥታ የነበረችው የሰባ ዓመት አሮጊት ሣራ ሙርቼሶን ሻንጣውን ይዛለት ወደ ኒውዮርክ እንድትሄድ ጠየቃት ። አሮጊቷ በሻንጣው ውስጥ ስለነበረው ነገር ምንም የምታውቀው የላትም ።

“ለእናቴ ለመላክ ቃል ገብቼላት የነበር ስጦታ ነው” አለና ቶኒ ሪዞሊ አስረዳት ። “ይህንን ዕቃ ለማድረስ ታማኝ ነሽ ብዬ ስለገመትኩ ከዚህ ወደኒውዮርክ የሚያደርስ የአውሮፕላን ትኬት ልቆርጥልሽ አስቤአለሁ ።”

“ግድ የለም ይህማ ጨርሶ አያስፈልግም” ብላ ተቃውሞዋን ለመግለጽ ሞከረች። “እንዲሁ በነፃ ባደርስልህ ደስ ይለኛል ። ከእናትህ መኖሪያ የእኔም ቤት ብዙ አይርቅም ። ልተዋወቃት እኔም እፈልጋለሁ ።”

“እርግጠኛ ነኝ እርሷም ብታገኝሽ ደስ ይላት ነበር” አላት ቶኒ ሪዞሊ በብልጠት ። “ችግሩ እርሷም በሽተኛ ናት ። ሆኖም ሻንጣውን የሚቀበልሽ ሰው ይኖራል ።”

አሮጊቷ ለሥራው በጣም የምትስማማ ናት ። ደስ የምትል አሜሪካዊት አያት። የጉምሩክ ሠራተኞችም ቢሆኑ እንዲያ ዓይነቷ

ብድሏል ። እርሷን ግን ሴት መነኩሴዎች ደብቀዋት በሕይወቷ ትገኛለች ።

እና ፣ ሳምብሩ እንዴት አድርጐ ኮንስታንቲን ዴሚሪስን እንደ ሚያጠፋ አውን ተገንዝቧል ።

‘ቶኒ ሪዞሊ ።’

ምዕራፍ አሥራ አንድ

የቶኒ ሪዞሊ ችግሮች ተበራክተዋል ። ሁሉም ነገር እየተበላሸበት ነው ። ለተፈጸመው ነገር ተጠያቂ ባይሆንም ሽሪኮቹ እሱ ላይ እንደሚያላክኩ ያውቃል ፣ ሰዎቹ ምክንያትና ሰበብ የሚቀበሉ አይደሉም።

ጉዳዩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደረገው ነገር ቢኖር የአደንዛዥ ዕፅ አጓጓዝ የመጀመሪያ ደረጃ ሥራ በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙ ነው ። አደንዛዥ ዕፅን ደብቆ አቴንስ ውስጥ ያለ እንቅፋት በማስረግ በጊዜያዊነት ከአንድ መጋዘን ውስጥ አከማችቶታል ። ከአቴንስ ወደኒውዮርክ ለሚበር አውሮፕላን አስተናጋጅ ጉቦ ሰጥቶ ዕቃውን በሥውር ሊያወጣ ተዘጋጅቶ ነበር ። በረራው ከመጀመሩ ከሃያ አራት ሰዓት በፊት አስተናጋጁ ሰክሮ መኪና ሲያሽከረክር ተይዞ ታሰረና ከሥራውም ተባረረ ።

ቶኒ ሪዞሊ ሌላ አማራጭ ዘዴ መፈለግ ነበረበት ። ልጇን ለመጠየቅ ወደአቴንስ መጥታ የነበረችው የሰባ ዓመት አሮጊት ሣራ ሙርቼሶን ሻንጣውን ይዛለት ወደ ኒውዮርክ እንድትሄድ ጠየቃት ። አሮጊቷ በሻንጣው ውስጥ ስለነበረው ነገር ምንም የምታውቀው የላትም ።

“ለእናቴ ለመላክ ቃል ገብቼላት የነበር ስጦታ ነው” አለና ቶኒ ሪዞሊ አስረዳት ። “ይህንን ዕቃ ለማድረስ ታማኝ ነሽ ብዬ ስለገመትኩ ከዚህ ወደኒውዮርክ የሚያደርስ የአውሮፕላን ትኬት ልቆርጥልሽ አስቤአለሁ ።”

“ግድ የለም ይህማ ጨርሶ አያስፈልግም” ብላ ተቃውሞዋን ለመግለጽ ሞከረች። “እንዲሁ በነፃ ባደርስልህ ደስ ይለኛል ። ከእናትህ መኖሪያ የእኔም ቤት ብዙ አይርቅም ። ልተዋወቃት እኔም እፈልጋለሁ ።”

“እርግጠኛ ነኝ እርሷም ብታገኝሽ ደስ ይላት ነበር” አላት ቶኒ ሪዞሊ በብልጠት ። “ችግሩ እርሷም በሽተኛ ናት ። ሆኖም ሻንጣውን የሚቀበልሽ ሰው ይኖራል ።”

አሮጊቷ ለሥራው በጣም የምትስማማ ናት ። ደስ የምትል አሜሪካዊት አያት። የጉምሩክ ሠራተኞችም ቢሆኑ እንዲያ ዓይነቷ

የኮንትሮባንድ ተግባር ላይ ትሰማራለች ብለው አይጠራጠሩም ።

ማራ ሙርቼሶን በሚቀጥለው ቀን ወደ ኒውዮርክ መሄዷ ነው ።

“አውሮፕላን ማረፊያ እኔ አደርስዎታለሁ ።”

“ለምን? አመሰግናለሁ ። እንዴት ለሰው የምታስብ ወጣት ነህ? እናትህ በእንተ ልትኮራ ይገባታል ።”

“አዎ ፡ በጣም እንዋደዳለን ።” እናቱኮ ከሞቱ አሥር ዓመት አልፏቸዋል ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ሪዞሊ ወደመጋዘኑ ሄዶ ዕቃውን ለማምጣት ሲዘጋጅ ስልክ ተደወለ ።

“ሚስተር ሪዞሊ?” እንግዳ ድምፅ ነበር ።

“አቤት!”

“ዶክተር ፓትሳካ እባላለሁ ። የምደውለው ከአቴንስ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል ነው ። ሚስስ ማራ ሙርቼሶን የሚባሉ አሮጊት ትናንት ማታ አንሸራትተአቸው ወድቀው እጃቸው ስለተሰበረ እኛ ዘንድ መጥተዋል ። ምን ያህል እንዳዘኑ ደውዬ እንድነግሮት በጣም ተጨንቀው አደራ ብለውኛል ።...”

ቶኒ ሪዞሊ ተበሳጭቶ ስልኩን ወርውሮ ዘጋው ። “ሜርድ!” አለ ። ለሁለተኛ ጊዜ ተበላሸበት ። አሁን እንግዲህ ዕቃውን የሚያሻግርለት ሌላ ሰው ከየት ያምጣ?

ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርበት ሪዞሊ በደንብ ተገንዝቧል ። ከአሜሪካ የመጡ ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችን የሚከታተሉ አዳኞች ከግሪክ ባለሥልጣኖች ጋር ግንባር ፈጥረው በጋራ ከትትል ይዘዋል የሚል ወሬ ሲናፈስ ሰምቷል ። ከአቴንስ የሚያስወጡ ኬላዎች ሁሉ በዓይነ ቁራኛ እየተጠበቁ ናቸው ። መርከቦችና አውሮፕላኖች ሁልጊዜ ይፈተሻሉ ።

ይሄም አልበቃ ብሎ ሌላ ችግር ተከሰተ ። በደላላነት የሚሠራለት የታወቀው ሱሰኛ ሌባ ፡ ፖሊሶች የአደንዛዥ ዕፅ ውጤቶችና ሌላ የኮንትሮባንድ ዕቃ ይገኝባቸዋል ብለው የሚጠረጥሩአቸውን መጋዘኖች መፈተሽ መጀመራቸውን ገለጠለት ። ጫናው ተደራረበበት ። ለሽሪኮቹ የመንገሪያ ጊዜ አሁን ነው ።

ቶኒ ሪዞሊ ከሆቴሉ ወጣና በፖቲሲዮን ጐዳና በኩል ወደከተማው የስልክ ቤት አመራ ። የሆቴሉ ስልክ ይጠለፍ አይጠለፍ እርግጠኛ ስላልነበረ ከአደገኛ መዘዝ ውስጥ ሊገባ አልፈለገም ።

ቁጥር 85 ፖቲሲዮን የተሰኘው የስልክ ቤቱ ሕንጻ ከድንጋይ የተሠራ ሆኖ ቡናማ ቀለም ተቀብቷል ። ከሕንጻው ፊትለፊት በዛ ያሉ ምሰሶዎች ቆመው ይታያሉ ። ሕንጻው ላይ “አ·ቲ·አ·” የሚል ጽሑፍ ተለጥፏል ። ሪዞሊ ወደ ውስጥ ገባና ዙሪያውን በዓይኑ ቃኘ ። በጣም በርከት ያሉ ስልክ ያለባቸው አነስተኛ ጉጆዎች በየጥጉ ያሉ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በቁጥር ተለይተዋል ። መደርደሪያው የመላው ዓለም የስልክ ቁጥሮችን በያዙ ማውጫዎች ተሞልቷል ። አራት ሴቶች ከክፍሉ መሐል ተቀምጠው ከደንበኞቻቸው የጥሪ ትዕዛዝ ይቀበላሉ ። ተገልጋዩ ሕዝብ ሰልፍ ይዞ ያስመዘገበው ጥሪ እስኪያደርሰው ይጠብቃል ።

ቶኒ ሪዞሊ ወደአንዲት ሴት ተጠጋና ፡ “እንደምን አደርሽ?” አላት ።

“ምን ልርዳህ?”

“የባሕር ማዶ የስልክ ጥሪ ለማድረግ እፈልጋለሁ”

“ይቅርታ ፡ ሰላሳ ደቂቃ ያህል ያስጠብቃል ።”

“ችግር የለም ።”

“የምትፈልገውን አገርና ቁጥር ልትሰጠኝ ትችላለህ እባክህ?”

ቶኒ ሪዞሊ ትንሽ እመነታና ቁራጭ ወረቀት ለሴትዮዋ ሰጣት ። “በተዘዋዋሪ ነው የምደውለው ።”

“ስምህ?”

“ብራውን ፡ ቶም ብራውን”

“እሺ ሚስተር ብራውን ጥሪው ሲቀርብ እጠራሃለሁ ።”

“አመሰግናለሁ!”

በክፍሉ ውስጥ ካሉት አግዳሚ ወንበሮች ወደአንዱ ሄደና ተቀመጠ።

‘ዕቃውን በመኪና ውስጥ ደብቄ ድንበር እንዲያሻግርልኝ ለአንድ ፑሬር ገንዘብ መስጠት ነበረብኝ ። ግን ይህ አደገኛ ነው ። መኪኖችም ይፈተሻሉ ። ምናልባት ካገኘሁ ሌላ ...’ አለ በልቡ ።

“ሚስተር ብራውን ... ሚስተር ቶም ብራውን ...” ሪዞሊ ፡ የተጠራው ስም የእርሱ መሆኑን ባለመገንዘቡ ሁለቴ ተደግሞ ተጠራ ። የራሱ መሆኑን እንደተረዳ ተነስቶ ወደተጠራበት ሮጠ ።

“ጥሪ የተደረገለት ሰው በተዘዋዋሪ ለመክፈል ተስማምቷል ። እባክህ ወደ ቁጥር ሰባት ጉጆ ግባ ።”

“እመሰግናለሁ ። በነገራችን ላይ ቅድም የሰጠሁሽን ቁራጭ ወረቀት ልትመልሺልኝ ትችያለሽ? ቁጥሩን እንደገና እፈልገዋለሁ ።”

“በሚገባ” ወረቀቱን መልሳ ሰጠችው ። ቶኒ ሪዞሊ ወደ ቁጥር 7 ጉጆ ገብቶ በሩን ዘጋው ።

“ሄሎ”

“ቶኒ ነህ?”

“አዎ ፣ እንደምነህ ፔት?”

“እውነቱን ለመናገር ትንሽ አሳስቦናል ። ቶኒ ፣ ልጆቹ በአሁኑ ጊዜ ፓኮው ሥፍራው መድረስ እንዳለበት ነው የሚገምቱት ።”

“ትንሽ ችግር አጋጥሞኝ ነው”

“ፓኮው ተላከ?”

“አይ ፣ አውንም እዚሁ ነው”

ትንሽ ፀጥታ ሰፈነ። “ይህ ዕቃ አንዳች ነገር እንዲደርስበት አንፈልግም ቶኒ!”

“ምንም ነገር አይሆንም ። ከዚህ ለማስወጣት ሌላ ዘዴ መፈለግ ይኖርብኛል። በየቦታው ነጭ ለባሾች ፈሰዋል ።”

“የምንነጋገረው ስለ አሥር ሚሊዮን ዶላር ነውኮ ቶኒ!”።

“አውቃለሁ አታስብ አንድ ዘዴ እገኝለታለሁ”

“በል ቶሎ በል ቶኒ ። አንድ ዘዴ በፍጥነት አግኝ ።”

ስልኩ ተዘጋ ።

ቶኒ ሪዞሊ ከክፍሉ ውስጥ ሲወጣ ግራጫ ሱፍ የለበሰ ሰው አየው ። በፊት ሪዞሊ ወደአነጋገራት ሴት ተጠጋና “እመቤቴ ፣ አሁን ወጥቶ የሄደውን ሰውዬ ልብ ብለሽዋል?”

ሴትዮዋ ቀና አለችና “ምነው?” አለች ።

“የደወለውን ስልክ ቁጥር ለማወቅ እፈልጋለሁ ።”

“አዝናለሁ ፣ እንደዚያ ዓይነት መረጃ እንድንሰጥ አይፈቀድልንም።”

ሰውዬው ከኋላ ኪሱ ቦርሳ አወጣ ። የወርቅ ጋሻ ምልክት ተለጥፎበታል ። “ፖሊስ ነኝ ። ተቆጣጣሪ ቲኖ እባላለሁ ።”

አገላለጿ ወዲያው ተለወጠ ። “አዎ ፣ ቁጥር የተጻፈበትን ቁራጭ ወረቀት ሰጥቶኝ ነበር ፣ እና መልሶ ወሰደው” አለች ።

“ግን ቀረው በመዝገባችሁ ላይ አለ አይደል?”

“አዎ ሁልጊዜ እንመዘግባለን ።”

“እባክሽ ቁጥሩን ብትነግሪኝ”

“በደስታ”

የተጠየቀውን ቁጥር ቁራጭ ወረቀት ላይ ጻፈችና ለተቆጣጣሪው ሰጠችው ። ወረቀቱን አነበበው ። የእገሩ መለያ ኮድ 39 ሲሆን የከተማው ቁጥር ደግሞ 91 ነው። ኢጣሊያ ፣ ፖሌርሞ ።

“አመሰግናለሁ ። ሰውዬው የነገረሽን ስም ታስታውሺያለሽ?”

“አዎ ብራውን ነው ቶም ብራውን ።”

በስልክ ያካሄደው ውይይት ቶኒ ሪዞሊን ትንሽ አበሳጭቶታል ። ወደመታጠቢያ ቤት ለመግባት ፈለገ ። ‘የማይረባ ፔት ሉካ’ አለ በልቡ ። ከኮሉናኪ አደባባይ በስተግዶ “መፀዳጃ” የሚል ጽሑፍ አነበበ ። ወንዶችም ሴቶችም ጾታ ሳይለዩ በአንድ መግቢያ በር ገብተው እየተጋፉ ተፀዳድተው ይወጣሉ ። “እና ግሪኮች እንዲህ ሆነው ነው ስለጠንን የሚሉት?” አለ ሪዞሊ ለራሱ ። “አስፀያፊ ።”

* * *

በፓሌርሞ ተራራ ላይ ባለው ቪላ ውስጥ አራት ሰዎች ቁጭ ብለው ይወያያሉ።

“ዕቃው እስካሁን መላክ ነበረበት ፣ ፔት” አለ ከአራቱ አንደኛው በግጥረምረም ። “ችግሩ ምንድን ነው?”

“እርግጠኛ አይደለሁም ችግሩ ምናልባት እራሱ ቶኒ ሪዞሊ ሊሆን ይችላል ።”

“ከዚህ በፊት በቶኒ በኩል ችግር አጋጥሞን አያውቅም ነበር ።”

“አውቃለሁ ፣ ግን አንዳንዴ ሰዎች ስግብግብነት ይጠናወታቸዋል። ሁኔታውን የሚያጣራ ሰው ወደ አቴንስ ብንልክ የሚሻል ይመስለኛል።”

“ያሳዝናል ። ቶኒን በጣም እወደው ነበር ።”

አቴንስ ከተማ ውስጥ ፣ በቁጥር 10 የስታዲአ ጎዳና ላይ በሚገኘው የፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ ስብሰባ እየተካሄደ ነው ። በስብሰባ ክፍሉ ውስጥ የፖሊስ አዛዥ ሊቭሬሪ ዴሚትሪ ፣ ተቆጣጣሪ ቴኑና አሜሪካዊው የመቶ አለቃ ዎልት ኬሲ ተቀምጠዋል ። የመቶ አለቃ ኬሲ

በየናይትድ ስቴትስ የገንዘብ ሚኒስቴር የጉምሩክ መምሪያ ተወካይ ነው ።

"የሰማነው ነገር አለ" አለ ኬሲ ። "ማለትም ከፍተኛ ግምት ያልው የአደንዛዥ ዕፅ ሽያጭ ሊካሄድ መሆኑን ተገንዝበናል ። ዕቃው ወጥ ሊላክ የተዘጋጀው ከአቴንስ ነው ። በዚህ ጉዳይ ቶኒ ሪዞሊ አለበት ።"

ተቆጣጣሪ ቴኑ በፀጥታ ተቀምጧል ። የግሪክ የፖሊስ መምሪያ ሌላው አገር በውስጥ ጉዳያቸው ጣልቃ መግባቱ ደስ አላሰኛቸውም ። 'በተለይም አሜሪካኖች በጣም ያበዙታል ። ከመጠን በላይ በራስ ይተማመናሉ' አለ ተቆጣጣሪው በልቡ ።

የፖሊስ አዛዡ እንዲህ አለ:— "በጉዳዩ ላይ ክትትል እያደረግን ነው መቶ አለቃ ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ቶኒ ሪዞሊ ወደፖሌርሞ የስልክ ጥሪ አድርጓል ። ጥሪ የተደረገበትን ቁጥር ለማወቅ እየሞከርን ነው ። ያንን ስናውቀው ግብረ አበሮቹን እናገኛለን ።"

ከአዛዡ ጠረጴዛ ላይ ያለው ስልክ ጠራ ። "አገኘነው!" ብሎ ጥቂት አዳመጠና ፣ ከፊቱ ላይ ምንም አይነበብም ፣ መልሶ ስልኩን ዘጋው ።

"ጥሩ ዜና አለ?"

"ቁጥሩን አግኝተውታል።"

"እና?"

"ጥሪው የተደረገው በከተማ መሐል ወደሚገኝ የሕዝብ ስልክ ነው።"

"ጋምቶ !"

"የኛ ሚስተር ሪዞሊ በጣም ኢኒህ ኤክስፔኖስ ነው ።"

ኬሲ ትዕግሥቱ አልቆ "እኔ ግሪክኛ አላውቅም" አለ ።

"አዝናለሁ የመቶ አለቃ ፣ ትርጉሙ ሰውዬው ጭራው የማይያዝ ጮሌ ነው ማለት ነው ።"

"በእርሱ ላይ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ እፈልጋለሁ" አለ ኬሲ ።

'ምን ዓይነት እብሪተኛ ነው' ሲል ካሰበ በኋላ የፖሊስ አዛዡ ዴሚትሪ ወደ ተቆጣጣሪ ቴኑ ዞር አለ ። "ከዚህ የበለጠ እርምጃ ለመውሰድ ምንም ተጨባጭ ማስረጃ የለንም ። አለን እንዴ?"

"የለንም ፣ ግን ከፍተኛ ጥርጣሬ አለን ።"

አዛዥ ዴሚትሪ አሁንም ወደዎልት ኬሲ ዞሮ ፣ "በእደንዛዥ ዕፅ ንግድ የተጠረጠረውን ሰው ሁሉ ለመከታተል የሚያስችል ኃይል ያለኝ አይመስለኝም" ብሎ ተናገረ ።

"ግን ሪዞሊ እኮ..."

"መረጃ አቀባይ እንዳለን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ ሚስተር ኬሲ ። የተሻለ ፍንጭ ካገኘን ደግሞ የት አግኝተንህ እንደምናሳውቅህ እናውቃለን ።"

ዎልት ኬሲ ተስፋ ቆርጦ ትኩር ብሎ አየው ። "ጊዜ ባናባክን ጥሩ ነው ። የመርከቡ ጭነት እንዳያመልጠን" አለ ።

በራፊና የሚገኘው ቪላ ዝግጁ ነው ። ደላላው ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ እንዲህ አለው:— "ቪላውን ከእነሙሉ ዕቃው እንደገዛኸው አውቃለሁ ፤ አዳዲስ መቀመጫዎች ቢገዙስ..."

"የለም ፤ ሁሉንም ነገር እንዳለ እንዲሆን ነው የምፈልገው ።"

እምነተ ቢሷ ናኤሌና ፍቅረኛዋ ላሪ እርሱን ከድተው ሲዝናኑበት እንደነበረው እንዲቆይ ነው ፍላጎቱ ። በቤቱ ሳሎን በኩል እያለፈ 'ወሲብ የፈጸሙት እዚህ ወለሉ ላይ ይሆን? በማንበቢያ ክፍሉ ውስጥ ወይስ በኩቺናው?' ብሎ አሰበ ። ዴሚሪስ አልፎ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ። ከበስተጥግ በኩል አንድ ትልቅ አልጋ አለ ። 'ዶግላስ የኖኤሌን ራቁት ገላ የደባበሰበት ፣ የዴሚሪስን የግል ንብረት የቀማበትም በዚህ ቦታ ነው ።' ዴሚሪስ አልጋውን ትኩር ብሎ አየው ። ቀጥሎም ሌሎችን ክፍሎች ተራ በተራ ተመለከታቸው ። ከቪላው ሆኖም ለካተሪን ስልክ ደወለላት ።

"ሄሎ"

"ስለ አንቺኮ ሳስብ ነበር ።"

ሁለት እንግዶች ወደ ቶኒ ሪዞሊ በድንገት መጥተውበታል ። መምጣታቸውን ሳያሳውቁት ወደነበረበት ሆቴል ዘው በማለታቸው አንድ ችግር መኖሩን ጠርጥሯል። አልፍሬድ ማንኩሶ ግዙፍ ሲሆን ጂኖ ላቬሪ ደግሞ የበለጠ ግዙፍ ነው።

ማንኩሶ እንደደረሰ ወደዋናው ነጥብ ገባ ። "ከፔት ሉካ ተልከን ነው" አለው።

ሪዞሊ እንደወትሮው የተረጋጋ ለመምሰል ሞከረ ። "በጣም ጥሩ ፣ እንኳን ወደ አቴንስ በደህና መጣችሁ ። ታዲያ ምን ልርዳችሁ?"

“እትፎግረን እባክህ ሪዞሊ!” አለ ማንኩሶ ። “ምን ዓይነት ሥውር ጨዋታ እንደጀመርክ ፔት ለማወቅ ይፈልጋል ።”

“ሥውር ጨዋታ? ምንድነው የምትለው?”

“ትንሽ ችግር እንዳጋጠመኝ አስረድቼዋለሁ ።”

“እዚህ የመጣነውም ለዚሁ ነው ። አብረን ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ ።”

“እስቲ ቆዩኝ ወንድሞቼ” አለ ሪዞሊ አነጋገራቸውን በመቃወም ። “ዕቃውን በድብቅ ደህና ቦታ እንዲቀመጥ አድርጌአለሁ ። ምንም ከማያሰጋን ቦታ ፣ እና ...”

“ፔት ዕቃው በድብቅ ተወዝፎ እንዲቀር አይደለም የሚፈልገው ። ብዙ ገንዘብ አውጥቶበታል ።” ላቬሪ የሪዞሊን ትከሻ ጨምድዶ ወንበሩ ላይ ወረወረው። “ላስረዳህ ሪዞሊ ይህ ዕቃ በወቅቱ ኒውዮርክ ጉዳና ላይ ተሽጦ ቢሆን ኖሮ በገንዘቡ መልሶ ሌላ ተገዝቶበት እንደገና ይሸጥ ነበር ። የምልህ ይገባሀል?”

‘እነኚህን ወሮበሎች አፈር ላስግጣቸው ይሆን ?’ አለ ሪዞሊ በልቡ ። ሆኖም ድርጊቱን ቢፈጽም ጠቡ ከእነኚህ ጋር ሳይሆን ከፔት ሉካ ጋር መሆኑን ተረዳ ።

“እም ፣ ምን ማለትህ እንደሆነ ገብቶኛል” ብሎ ሪዞሊ ድምፁን ዝቅ አድርጉ ተናገረ ። “ጉዳዩ እንዳሰብነው ቀላል አልሆነ ብሎ ነው ። የግሪክ ፖሊሶች በያለበት ተሰራጭተው ጥብቅ ክትትል በማድረግ ላይ ናቸው ። ከዋሽንግተን የመጣ አሜሪካዊም አላቸው ። የእኔ እቅድ ...”

“ፔትም እቅድ አለው” ሲል ላቬሪ አቋረጠው ። “እቅዱ ምን እንደሆነ ታውቃለህ ? በሚቀጥለው ሳምንት ዕቃው እሚፈልገው ሥፍራ የማይደርስ ከሆነ አንተ እራስህ የዕቃውን ዋጋ ይዘህ እንድትመጣ አዟል ።”

“እንዴት ይሆናል ? ያንን ያህል ገንዘብ የለኝም ። እኔ ...”

“ፔትም እንደሌለህ ያውቃል ። እንተን የምናስከፍልበት ሌላ ዘዴ እንድንፈልግ ነግሮኛል ።”

ቶኒ ሪዞሊ በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰ ። “እሺ ፣ ሁሉም ነገር በቁጥጥር ሥር መሆኑን ንገሩት ።”

“መልካም ፣ እኛም በዚሁ አካባቢ ነን ። የተሰጠህ የአንድ ሳምንት ጊዜ ብቻ ነው ።”

ቶኒ ሪዞሊ ከቀትር በፊት መጠጥ ላይቀምስ ከገዛሁ ቁጥሬን ወስኖ ነበር። ሁለቱ ሰዎች ከወጡለት በኋላ ግን የባኮቻ ዊስኪ ጠርሙስ ከፈተና ሁለት ጊዜ አንደቅድቆ አጐደለው ። መጠጡ ቃሉን በቋሉ ዕውነቱን ሰደያዋቀው ገለማው ። ግን ምንም ፋይዳ አልኔበረውም ብሩ የሚሰራቅኝ ምንም ነገር የለም’ አለ በአሳቡ ። ‘ሽማግሌው አንዶት ዓንዶጎልዐጥ ይልብኛል? ልክ እንደልጄ ሆኜለት ቆይቼ ከአንዳሀ ዓየታ ሕወጦ ውልጥ እንደወሣየሰምንት ጊዜ ብቻ ይስጠኝ ? ባስቸኳይ ዕቁውን የሚያሻሽጠር ልን በቅሎ ማግኘት አለብኝ ። ወደ ካሲኖ መጫወቻ ብዙ ጭ ብሎ አገኛለሁ ።’

ያንኑ ዕለት ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ሪዞሊ ክልቲንስ ዓምሳማይል ርቀት ላይ ወደሚገኘው ሉትራኪ በተሰኘው ሥፍራ ወደሚገኘው ሥልሳዘኛ የካሲኖ መጫወቻ ሄደ ። ጨዋታውን የሚያዩ በሙሉሰል በተጨናነቀው ሕዝብ መሐል በሰፊ ክፍል ውስጥ ወዲያና ወዲህ አለ ። ከተጨዋቾቹ መካከል ብዙዎቹ ገንዘብ ተበልተዋል ። እንኚህኞቹ ጨዋታውን ዶየሚቀጥሉበት ሌላ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የተጠየቁትን ማንኛውንም ክፍያ ከመፈጸም ወደኋላ አይሉም ። ተስፋ የቆረጠ ለነሩሱ ስለማይሳሳ ነገሮ ከማድረግ አይመለስም ።

ጥቦንፈዘለሉ እንዲህ ዓይነቱን በዓይኑ ሲፈልግ ከነበረው ዘመኖቹ ጫረሴዛ አልገባ ካለው ሰው ላይ ተከለሰለ ። ቁመቱ ከቁጭ ቁመጠር ብሎ እንደሚገ የነበረው ሰውነቱ ጠፍጣፋ ሲሆን ዕድሜው በሃምሳው አካባቢ ይገመታል ። ከኪሱ መሐረብ እያወጣ ግንባሩን ይጠርጋል ። ይበልጥ እየተበሳ ቁጥር ይበልጥ ላቡ ይንቆረቆራል ።

“ነ ሀ ለልሚዴው ሥኔታ ሪዞሊን አስዳስቶት ከነ ክሩታ ከከታተለው ። ተመሳሳይ ሁኔታ ከዚህ በፊትም አጋጥሞታል ። ተቀቁሞ ከ ወጣ በኋላ ሰሞኑን ከሚሸት አራሱን አደለገዶ ክአቅሙ በላይ ዶሚጫወት ሰው ዕዛዘ ያዕው ሰው የደንበኛ ቁማርተኛ ምሳሌ ነው ።

መበላቱን ሲረዳ ወደቁማሩ ዳኞ ዞርአለና ‘እኔ ልሌላ ጨዋታ ግዴ ለማረፈም እፈል ጋለሁ’ አለ ። ገንዘቡን ሰብስቦ ለመሄድ ተነሳ ። ከኪሱ ሚገባ ። ሶሪ ጓዶ ተሰናበተ ። ሰለሙ ለዘነ ሰሌ ሚገ

አጫዋቹ ዞር አለና ወደ አለቃው ተመለከተ ።

“እሺ ስጠው ግን ይህ የመጨረሻው ይሆናል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ሰውዬው በምን ያህል ዕዳ ተይዞ እንደሆነ ለማወቅ በጣም ጓጓና አጠገቡ ቁጭ አለ ። እራሱም ጨዋታው ውስጥ ገባ ። የጨዋታው ዓይነት አክሳሪ ቢሆንም ሪዞሊ አጨዋወቱን ደህና አድርጐ ያውቀዋል ። አጠገቡ ያለው እየተበሳ ሪዞሊ እያሸነፈ መጣ ። ተበዬው ይበልጥ ተስፋ እየቆረጠ በአጨዋወቱ እየተዝረከረከ ሲመጣ ታየ ። ‘እንዴት እንደሚጫወት መላ ቅጡ ጠፍቶበታል’ አለ ሪዞሊ በልቡ ።

ሪዞሊ ረታው ። ሰውዬውም ቁጭ ብሎ ፈዞ ቀረ ።

ሌላ ተስፋ ይኖረኛል ብሎ በመገመት ቀና ብሎ ወደአጫዋቹ ተመለከተ ። “እንደገና …?” አለና ጠየቀ ።

አጫዋቹ ጭንቅላቱን በማነቃነቅ “አዝናለሁ” አለ ።

ሰውዬው ቁና እየተነፈሰ ተነስቶ ቆመ ።

ሪዞሊም እንዲሁ ከመቀመጫው ተነሳ ። “በጣም ያሳዝናል” ሲል ሐዘኔታውን ገለፀ ። “ትንሽ ዕድል ስላለችኝ ነው ። እስቲ መጠጥ ልጋብዝህ ።”

ሰውዬው ዓይኑን አቁለጨለጨና “እግዜር ይስጥህ ጌታዬ” አለ ።

‘እንግዲህ በቅሎዬን አገኘሁ’ አለ ሪዞሊ በአሳቡ ። በእርግጥ ሰውዬውን በጣም ገንዘብ አስፈልጎታል ። ዕቃውን ኒውዮርክ እንዲወስድ ወደ አሜሪካ ደርሶ መልስ የሽርሽር የነፃ ቲኬት ቢሰጠውና አንድ መቶ ዶላር ቢከፍለው ጮቤ ይረግጣል ።

“ስሜ ቶኒ ሪዞሊ ይባላል”

“ቪክቶር ኮሮንዚስ”

ሪዞሊ ኮሮንዚስን ይዞ ወደ ቡና ቤቱ አመራ ። “ምን ይምጣልህ ?”

“እኔ … አዝናለሁ ምንም ገንዘብ የለኝም ።”

ቶኒ ሪዞሊ በእጁ ምልክት የጉዳዩን ቀላልነት አስረዳው ። “ስለገንዘብ አትጨነቅ ።”

“የምጠጣው ሬስቲና ነው ።”

ሪዞሊ ወደ አሳላፊው ዞር አለና “ሺቫስ በበረዶ” ብሎ አዘዘ ።

“እዚህ የመጣኸው በጉብኝት ነው ?” ሲል ኮሮንዚስ በትሕትና ጠየቀው ።

“አዎ” ሲል ሪዞሊ መለሰ ። “በዕረፍት ላይ ነኝ ። በጣም ውብ

የሆነች አገር ናት ።”

ኮሮንዚስ ትከሻውን ነቀነቀ ። “እዎ መጥፎ አይደለም ።”

“ኑሮውን አልወደድከውም መሰለኝ ?”

“አይ ፣ ቆንጆ ነው ። ትንሽ ኑሮው ውድ ነው ። ግለቴ የሁሉም ነገር ዋጋ ጨምሯል ። በተለይ ሚስትና አራት ልጆች የምታስተዳድር ከሆነ እንደልብ ለመብላት ሚሊዬነር መሆን ያስፈልጋል።” አባባሉ መረር ያለ ነበር ።

‘ጉሽ ፣ ጉሽ ፣ ሻል ያለው መጣ’ “ለመሆኑ ቪክቶር ሥራህ ምንድነው ?” አለና ሪዞሊ ጠየቀ ።

“አቴንስ የሚገኘው የመንግሥት ሙዚዬም ኃላፊ ነኝ ።”

“ገባኝ ፣ ለመሆኑ በሙዚየሙ ፣ ውስጥ የኃላፊው ተግባር ምን ድነው ?”

ኮሮንዚስ ትንሽ ተኩራራና “ከግሪክ ተቆፍረው የሚወጡ ጥንታዊ ዕቃዎችን የምቆጣጠረውና የማስተዳድረው እኔ ነኝ” ብሎ መጠጡን ተጉነጨ ። “እዎ በእርግጥ ሁሉንም አይደለም ። ሌሎች ሙዚየሞችም አሉ ። አክሮፖሊስና ፣ ናሽናል ሙዚየም የተባሉም አሉ ። ሆኖም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ጥንታዊ ዕቃዎች ያሉት በኛ ሙዚየም ውስጥ ነው ።”

ቶኒ ሪዞሊ በሰውዬው አነጋገር ይበልጥ እየተሳበ መጣ ። “ምን ያህል ዋጋ የሚገመቱ ?”

ቪክቶር ኮሮንዚስ ዘና አለ ። “ዋጋ አልተተመነላቸውም ። ግንኛውም ቅርስ ከአገር እንዳይወጣ የሚያግድ ሕግ ስላለ የዋናዎቹ ዕቃዎች አምሳያዎች እየተሰሩ በሙዚየሙ ወስጥ ካለው መደብር ውስጥ ይሸጣሉ ።”

የሪዞሊ አእምሮ በፈጣን ሂደት መሥራት ጀመረ ። “ለካ እንደዚህ ነው ? ታዲያ አምሳያዎቹ ምን ያህል ዋናውን ይመስላሉ ?”

“አሆ ፣ ቁርጥ እንድ ናቸው ። ለይቶ ለማወቅ የሚችለው እውቅ ባለሙያ ብቻ ነው ።”

“በል ድገም” አለው ሪዞሊ ።

“አመሰግናለሁ ፣ በጣም ደግ ሰው ነህ ። እኔ እንኳን ብድር ለመመለስ የምችልበት ደረጃ ላይ ያለሁ አይደለሁም ።”

ሪዞሊ ፈገግ አለ ። “ስለዚያ ብዙም አትጨነቅ ። አንተ የምትረዳኝ ነገር ሊኖር ይችላል ። ሙዚየማችሁን ለመጐብኘት እፈልጋለሁ ። በጣም

ያንጓል ።”

“አም ያጫንልኛ ዝለሙ ኮሮንዚስ አጣባሉን ዝመጀመሩ ። ዝቅሳለም ውስጥ ካሉት በጣም ጥሩ ናቸው ። ከሚላሉጥ ሙዚየሞች መገበል አንዱ ነው ። ከጀለማከብቅ ዝስጀ ላከኮበኝ እቅደኛ ቂዚ የሚኖርሀ መቹሩው ከመሀከኛ ቸኳል ጭሰና ጋተሰም ጋለበ ። ልእክዚ ርዋ ሰውየው የተባለውን ዕቃ ከማንገዝ በላይ ሌላ ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል ቶኒ ሪዞሊ ገመተ ።

የአቴንስ የመንግሥት ሙዚየም የሚገኘው በአቴኳስ ቤተ መንግሥት ላይ ነው ። ከፊት ለፊቱ በአራት ኤለናዊ አምዶች ተደግፎ ከሕንፃው ጣሪያ የግሪክ ብንዲራ ይውለበለባል ። ግቢው ሳይ አረንጓዴ የምለል ቅርጸች ይታያሉ ። ከአዙነ ብረደዕሙ ከጌሉ ዝመጠ አዳራሽ ውስጥ በቅለዮ ጊዜያት የተገኙ ጥንታውያን ቅርሶች ተደርድረዋል ። ቅርሶቹና ሰው ሠራሽ ዕቃዎቹ በሥርዓት ተቀምጠዋል ። የወርቅ ቀንጫጮችና ዘውዶች ፣ የተለዘዉ ሥጌያጭዎችና የመሸቀጫ ማቅረቢያ ዕቅዎች ይታያሉ ። በአንዱ ማስቀመጫ ውስጥ አራት ከወርቅ የተሠሩ የመቅበሪያ ጭምብሎች ሲኖሩ በሌላው መሸጥ ደግሞ የጥንታዊ ሕውልት ፍርስራሽ ይገኛል ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ። ቶኒ ሪዞሊን እዴሱ እያዙረ ያስጐበኝ ነበር ። የእንቅልፍ አምላክ ኃውልት ከተቀመጠበት ሥፍራ ደረሱ ። “ቄንጆች የእንቅልፍ አምላክ ናት?” አለ ኮሮንዚስ በሥረንነ ድምፅ ። “የዘውዱ ተምሳሌነት የእንቅልፍ ፣ የሕልም የራእይና የሞቻ ንግሥት መሆኗን የሚያመለክት ነው ።

“የዚህ ዋጋ ምን ያህል ይገመታል ?”

ኮሮንዚስ ሳቀ ። “የሚሸጥ ቢሆን ኖሮ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ።”

“እውነትህን ነው ?”

አጭሩ አስጐብኚ የበለጠ ኩራት እየተሰማው ማስተናገዱን ቀጠለ ። ወደ አንዱ ቅርስ ጣቱን ቀሰረና “ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ530 የነበረ የኪኡሮስ ጭንቅላት ነው ... ፡ ይሄ ደግሞ ግሩም ነው ። የነገሥታት

መቃብር ካለበት ከሚሊኔ ጐሳ የአክሮፖሊስ ቤተመቅደስ ዘአሥራ ስድስቱኛው ክፍለ ዘመን ቅድመ ልደት የቲገኝ የእንጀሀይ ጐሳ የወርቅ ጭምብል ነው ። የአጋሜኖን ነው ተብሎም ይታመንበታል ።

“አትለኝም ?”

ቶኒ ሪዞሊን ወደ ሌላ ማስቀመጫ ወሰደውና ልዩ ማሰሮ አሳየው ።

“በጣም ከምወዳቸው ቅርሶች ይህ አንዱ ነው” አለ ኮሮንዚስ ። “ወላጅ ከልጅቹ ለይቶ የሚወዱ ልጅ መኖር እንደሌለበት አምናለሁ ። ግን ምን ላድርግ ከይዘ ቅርስ ጋር”

ሥዕሉ ማሰሮ ነው የሚመስለኝ” አለ ሪዞሊ ። ሥዕሉ ልክ ነህ ። ይህ ማሰሮ የተቀረጸው በክርስቶስ ልደት በኮይኔ ዘመን ወቅት ከነገሡ የነበሩ ክፍለ ነው ። በወቅቱ ኮሮማውያን በመሪነት እየዛበሩ ይጣሉ አንደነበር በቅርስ ላይ የተነደፈው ሥዕል ያመለክታል ። ከጥንት ግሪክ ባህርማዎች በመሪነት እየተጠለፉ ሮሚጣሉት ለመስዋዕት የሚቀርበው ደማቸው ያላባባ በየቦታው እንዳይረጭ ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ነበር ። ምክንያቱም ...”

“ይህስ በምን ያህል ዋጋ ይገመታል ?” ሲል ገለጸው አቋረጠበት ።

“እሥር ሚለዮን ዶላር ያህል ይመስለኛል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ግንባሩን ቋጠሮ እየረገጠ “እዚህ ?” አለ ።

“አም ማወቅ ያለብህ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1500 ዘመን የነለሞቹ ሚኖአን ጊዜ የነበረ መሆኑን ነው ።”

ቶኒ ሪዞሊ በመስተዋት ውስጥ የሚገኙትን አምሳያ ቅርሳ ቅርሶች እየተዘዋወረ ተመለከተ ። “የእንጀሀም ዋጋ እንደዚያው ነው ?”

“የለም አይደለም ። ጥንታዊ ቅርሶች ናቸው ። ውዶቹ የሚተኩ ባለመሆናቸው ስለ ጥንታዊው የግሪክ ሥልጣኔ ፍንጭ የሚሰጡን በመሆናቸው ነው ። እዚያጋ ያለውን ላሳይህ ?”

ቶኒ ኮሮንዚስን ተከትሎ ወደ ሌላ ክፍል ገባና ከጥግ ካለው ካንድ ማኅደር ፊት ቆሙ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ በጣቱ ማሰሮውን እያመለከተ “ይህ አንዱ ከፍተኛው ሀብታችን ነው ። የድምፅ ምልክቶች እንዴት እንደነበሩ ያሳያል ። መስቀል ያለበት ክብ ምልክት ‘ካ’ የሚለውን ድምፅ ያመለክታል ። የተሰረዘው ክብ ሥዕል ደግሞ ጥንታዊያን ሰዎች ምልአተ አለምን ለመግለጽ ይጠቀሙበት የነበረው ምልክት ነው ። እዚያ

ያሉት ...”

‘ግን ለዚህ ደንታ አለው ?’ አለ ሪዞሊ በልቡ ። “ለመሆኑ ስንት ያወጣል ?” ብሎ ጠየቀው ።

ኮሮንዚስ ፈገግ አለ ። “እጅግ ብዙ ሚሊዮን ።”

ቶኒ ሪዞሊ ያን ዕለት ጠዋት ከሙዚየሙ ሲወጣ በሕይወቱ አገኘው ይሆናል ብሎ ከሚያስበው በላይ የብዙ ሀብት ባለቤት እንደሚሆን ገምቷል ። ሳያስበው በወርቅ ማዕድን ላይ የሚረግመድ መሰለው ። አደንዛዥ ዕፁን ድንበር የሚያሻግርለት በቅሎ ሲፈልግ ሐብት የተከማቸበትን ግምጃ ቤት ቁልፍ አገኘ ። ከሄሮይን ንግዱ የሚገኘው ትርፍ እንድ ስድስተኛው ነበር የሚደርሰው ። ሽሪኮቹን ለማታለል መሞከሩ በእራሱ ላይ የማስፈረድ ያህል ነው። የቅርሳ ቅርሱ ጉዳይ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። አንዷን ሰርቆ በድብቅ ከግሪክ ቢያስወጣ ከሽያጩ የሚገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ የእርሱ ነው ፣ እጋራኝ ብሎ የሚያስቸገረው አይኖርም ። ሪዞሊን ያስፈነደቀውም ይኸው ነው ። ‘ማድረግ ያለብኝ’ አለ ሪዞሊ ለእራሱ ። ‘ዓላውን እንዴት ለማጥመድ እንደሚቻል ዘዴ ማዘጋጀት ነው ። የአደንዛዥን ዕፅ ድንበር ስለማሻገሩ ኋላ እጨነቃለሁ ።’

ያን ዕለት ምሽት ሪዞሊ አዲሱን ጓደኛውን ሞስትሮቭ አቴና ወደተሰኘው የግታ ክበብ ይዞት ሄደ ። በግታ ክበቡ ውስጥ ያለው መዝናኛ በጣም ዋሚያረካ ሲሆን ከዳንሱ በኋላም ሴቶችን እንደልብ ማግኘት ይቻላል ።

“ስማ ፣ ደናሾቹን እናስነሳና ትንሽ እንጨፍር” ሲል ሪዞሊ አሳብ አቀረበ ።

“እቤት ፣ ቤተሰቤ ዘንድ መሄድ አለብኝ” አለና ኮሮንዚስ ጥያቄውን ላለመቀበል ሞከረ ። “በተጨማሪም በእንዲህ ዓይነቱ ሥፍራ ለመዝናናት አቅሜ አይፈቅድልኝም ።”

“ምን ነካህ ? አንተኮ የእኔ ተጋባዥ ነህ ። እኔ ልዩ ወጪ ስላለኝ ምን ያህል አወጣለሁ ብለህ ነው ?”

አንዷ ደናሽ ከቪክቶር ኮሮንዚስ ጋር ሄዳ እንድታስተዳድረው ሪዞሊ አስፈላጊውን ሒሣብ ከፈለ ።

“አንተስ ?” ሲል ኮሮንዚስ ጠየቀ ።

“እኔ አንድ የማከናውነው ሥራ ስላለኝ እቆያለሁ ። አንተ ሂድ ፣ ሂሣቡ ሁሉ ተከፍሏል ።” አለ ቶኒ ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ቶኒ ሪዞሊ ወደሙዚየሙ ጉራ አለ ። በዛ ያሉ ያገር ጉብኚዎች በክፍሎቹ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቅርሳ ቅርሶቹን በማድነቅ ላይ እንዳሉ ሪዞሊ ተመለከተ ።

ኮሮንዚስ እንደማፈር እያለ ሪዞሊን ይዞት ወደቢሮው ገብና “እኔ ... ስለማታው ውለታህ እንዴት አድርጌ እንደማመሰግንህ አላውቅም ቶኒ ። እርሷ ... ምን ልበልህ በጣም ግሩም ነበር ።”

ሪዞሊ በፈገግታ “ታዲያ ጓደኝነት ለመቼ ነው ቪክቶር” አለው ።

ግን እንዴት አድርጌ ውለታህን እንደምመልስ አላውቅም ።”

“ውለታ ከአንተ አልጠብቅም” አለው ሪዞሊ በለሆሳስ ። “እወድህ ለሁ ፣ ጓደኛነትህን አፈቅራለሁ ። በነገራችን ላይ ዛሬ ማታ በአንድ ሆቴል ውስጥ የቁማር ጨዋታ ይኖራል ። እኔ ለመጫወት አስቤአለሁ ፣ አንተስ ፍላጐት አለህ ?”

“አመሰግናለሁ ። ደስ ይለኝ ነበር ። ግን ...” አለና ትከሻውን ነቀነቀ ። “አይመስለኝም ። ባልጫወት የሚሻል ይመስለኛል ።”

“ምን ነካህ የሚያስጨንቅህ ገንዘብ ከሆነ ስለዚያ አታስብ ። እኔ እመድብልሃለሁ ።”

ኮሮንዚስ ጭንቅላቱን ነቀነቀና “ብዙ ነገር አድርገህልኛል ። ድንገት ቢበሉኝ እንኳ መልሼ ልከፍልህ አልችልም” አለው ።

ቶኒ ሪዞሊ ሳቅ አለ ። “ትበላለህ ያለው ማነው ? ሁሉም ነገር ቀድሞ ተዘጋጅቷል ።”

“ቀድሞ ተዘጋጅቷል ? አል ... አልገባኝም ።”

ሪዞሊ በቀስታ አነጋገር “አንድ ጊዜ አቶ ዳልቶን የሚባል ጓደኛዬ እንዲሁ ይጫወት ነበር ። ብዙ ገንዘብ የነበራቸው የቁማር ጨዋታ የሚወዱ አሜሪካውያን አገር ጉብኚዎች መጡና እኔና ጓደኛዬ ደህና አድርገን አታለልናቸው ።” ኮሮንዚስ ዓይኑን አፍጥጦ ሪዞሊን አየ ። “በዘዴ በላናቸው ነው የምትለኝ ?” አለና በምላሱ ከንፈሩን አባበሰ ። “ግን ... በእንዲህ ያለ ሁኔታ ተጫውቼ አላውቅም ።”

ለሰኔ ሬዘሚ በእዚያ ጭንቅላቱን አውጣው ። "ይቀጣኛል ። ቅር የሚልህ ከሆነ ይቅር ። ከሁለት እስከ ሦስት ሺህ የሚደርሱ ዶላር በአንዴ ለማግኘት ቀላሉ ዘዴ ይህ ነው ብዬ ስለገመትኩ ነው ። እያየኸር ዝርክ ዓይነቶቹ የበለጠ ተብለጨጨ ። "ከሁለት እስከ ሦስት ሺህ የሚደርስ ዶላር ?"

"ሌላ ምክንያት ግን አለኝ ። ግን ... ግን አደጋ አያስከትልም ?" ። ቶኒ ሬዘሚ ሳቁ ። "አይ ፣ በጀበከበት ሰዓት ምንም አልሞከረውም ነበር ። እንመሰል ዘመን ከነጭ እንጀመሰል ። ለብዙ ዓመታት በእንዲህ ዓይነት "መንገድ እየተጓዘ አንድ ቀንም ተይዞ አያውቅም ።"

"ቶሮንዚስ እዚያች ቁጭ ብሎ የሬዘሚን ፀይን ፀይን እያየ ፈዞ ቀረ ። ምን ሰዎችን ሰብስቦ ለመግደል ነው ?" "እሞላት መቶ ዶላር ያህል ። ካን አንድ ነገር ልንገርህ ። በዚህ ጨዋታ ልትበላ ስለምትችል እምስላሴ ዶላር እኔ አበድርሃለሁ ። በአጋጣሚ ከተበላህም ገንዘቡን አላስከፍልህም ።"

"ለምን እንደሆነ ልንገርህ ?" "ለምን ... ለምንድን ነው ግን ይህን ሁሉ ለእኔ የምታደርገው ?" ። "ስለምን እንደሆነ ልንገርህ ?" ። ቶኒ ሬዘሚ መሰለ ። "እንዳንተ ያለ ገርና ብርቱ ሠራተኛ ፣ በተለይም በዓለም ውስጥ በታወቀ ትልቅ ሙቢዬም የሚሠራ ሰው አንቀሳኝ ፣ መንግሥት ደግሞ ይህን ሁሉ ጥሪቱህን በሚነሳ ሓለመሪዳት አነስተኛ ደሞዝ እንደሚከፍልህ ስታነዝብ ። ያንተን የቤተሰብህን ኑሮ ለመሸፈን የምታደርገው ጠብ የማይል መማሰን በጣም አድርጎ ያንገበግበኛል ። ለመሆኑ የደመወዝ ጭማሪ ካገኘህ ምን ያህል ሊጨምርልህ ይችላል ?"

"ሥራህን እንዳትወድ እንጂ ጥሩ ሥራ ነህ ። አንተ ሌላ አማራጭ ያለህ ሰው ነህ ሺህዶር ። ሣሪ ማታ ትንሽ ውሰጅ ልሞልልህ ። ጥቂት ሺህ ዶላሮች ከእኔ ውሰድና እንድፈጠው መኖር ጀምር ። ከእጅ ወደ አፍ ኑሮህን ቀጥልበት ።"

"እኔ ... እኔ እንጃ ቶኒ ። ቢቀርብኝ ..."

ቶኒ ሬዘሚ ከተቀመጠበት ተነሳ ። "ጭንቀኛህ ይገባኛል ። ምናልባት ከአንድ ወይም ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደ አቴንስ ተመልሺ ስመጣ እንገናኝ ይሆናል ። ካንተ ጋር በመተዋወቄ በጣም ደስ ብሎኛል ቪክቶር ።" ሬዘሚ ወደ በሩ አመራ ።

ኮሮንዚስ አሁን ከውሳኔ ሊደ ደረሰ ።

"ቆየኝ ፣ ማታ እመታ እብረን እንሂዳለን ።"

በወጥመዱ ውስጥ አስገብቶታል ። "አሦ ፣ የማ በጣም ጥሩ ሀሳብ ነው" አለ ቶኒ ሬዘሚ ። "እንተን መርዳቱ እራሱ ለእኔ ደስታን ይሰጠኛል ።"

ኮሮንዚስ አመሰጋገኑን በቅርቃ አድርሻልኝና ሃልከንን በትክክል ለመረዳት እፈልጋለሁ ። አምስት ሺቀውን ዶላር ከተበላሁ መልሺ እንድከፍል አልጠየቀም ማለት ነው ? ሙበበዱ ቶኒ ሬዘሚ ። ሙምክንያቱም ሰለማትበላ ነው ። ጨዋታው እንደሆነ በቅድሚያ ተጠናቅቋል ።

"ለመሆኑ የጨቅላ ልጅ ነው ?" ። ቶኒ ሬዘሚ ። "አዎን ፣ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር ነው ። ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ የሚያስመጣ ሥራ አንደሚኖርህ እገምታለሁ ። ንግድህ ምን እንደሆነ ግን አላውቅም ።"

"ቶሮንዚስ ሳቀ ። "ሃሃሃ ፣ ሃሃሃ ። ሃሃሃ ። ሃሃሃ ።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

በሦቱሉ ክፍል ውስጥ ከቶኒ ሪዞሊና ከቪክቶር ኮሮንዚስ ጉን አራት ሰዎች ተቀምጠዋል ።

“ከጓደኛዬ ከአቶ ዳልቶን ጋር ተዋወቅ” አለ ሪዞሊ ።

“ቪክቶር ኮሮንዚስ እባላለሁ ።”

ሁለቱ ሰዎች ተጨባበጡ ።

ሪዞሊ ሌሎቹን ሰዎች በዓይኑ መረመረ ። ‘እነኚህን እንግዶች ከዚህ በፊት የተዋወቅኳቸው አይመስለኝም ።’

አቶ ዳልቶን የማስተዋወቁን ተግባር አካሄደ ።

“ፔሪ ብሬስላአር ፡ የቴሮይት አገር ሰው ... ማርፊን ሴይሞር ከሠውስተን... ሳል ፕሪዚ ከኒውዮርክ ።”

ቪክቶር ኮሮንዚስ ምንም ድምፅ ሳያሰማ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ።

የኦ ቶ ዳልቶን ዕድሜ በስለሣዎቹ ውስጥ ሲሆን ቀጭንና ሽበት የወረረው ነው ። ፔሪ ብሬስላአር በዕድሜ ከዳልቶን ያነሰ ሲሆን ፊቱ ረዘም ያለና ለስላሳ ነው ። ማርፊን ሴይሞር ቀጠን ብሎ ገራገር ይመስላል ። ሳል ፕሪዚ ደግሞ እንደዛፍ የገዘፈ ሰውነት ያለው ፈርጣማ ነው ። ዓይኖቹ ትናንሾች ሲሆኑ ፊቱ ላይ ያለው ምልክት በጭቤ ተወግቶ እንደነበር ያሳያል ።

ሪዞሊ ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ስለሰዎቹ ደህና አድርጉ ለኮሮንዚስ ነግሮታል ። “እነኚህ ሰዎች ብዙ ገንዘብ አላቸው ። የቱንም ያህል በቁማር ቢከስሩ አይሰማቸውም ። ሴይሞር የኢንሹራንስ ኩባንያ ባለቤት ነው ። ብሬስላአር በመሳ ዩናይትድ ስቴትስ አውቶሞቢል ገዝተው የሚሸጡ ድርጅቶች አሉት ። ሳል ፕሪዚ በኒውዮርክ የሚገኝ የትልቅ ግሮሰር መሪ ነው ።”

አቶ ዳልቶን እንዲህ አለ ፦“መልካም እንግዲህ ፡ ወዳጆቼ ጨዋታውን እንጀምር ? ነጩ ካርታ አምስት ዶላር ፡ ሰማያዊው አሥር

ዶላር ፡ ቀዩ ሃያ ፡ ጥቁሩ ሃምሣ ዶላር ነው ። እስቲ የያዛችሁትን ገንዘብ እንመልከት ።”

ኮሮንዚስ ቶኒ ሪዞሊ ያበደረውን አምስት መቶ ዶላር መዞ አወጣ። ‘የለም አላበደረኝም ፡ ሰጠኝ እንጂ’ አለ በልቡ ። ሪዞሊን ዞር ብሎ አየውና ፈገግ አለ ። ‘ሪዞሊ ምን ዓይነት ጥሩ ጓደኛ ነው !’ አለ በሀሳቡ ።

ሌሎቹ ሰዎች ጥቅል ዶላሮችን ከኪሳቸው መዘዙ ።

ኮሮንዚስን ስጋት ገባው ። ምናልባት እንዳጋጣሚ አምስት መቶ ውን ዶላር ቢበሉበትስ ? ይብሱዋ ። ጓደኛው ቶኒ አለለት ። ምናልባት ሆኖለት በጨዋታው ካሸነፈስ ? ኮሮንዚስ በልዩ የደስታ ስሜት ተወጠረ ።

ጨዋታው ተጀመረ ።

የካርታ አከፋፋዩ እንደመረጠው ነው የሚሆነው ። መነሻ ገንዘቡ በመጀመሪያ ላይ አነስተኛ ነበር ። ጨዋታዎቹ የአምስት ካርታ መደብ ፡ ሰባት ካርታ መደብ ፡ ካርታ መሳብና እንዲሁም ዝቅተኛና ከፍተኛ ቁጥር መግጠሚያ ናቸው ።

ገና ጨዋታው በተጀመረ አካባቢ መሸናነፉ በእኩል ደረጃ ላይ ነበር። ቀስ በቀስ እጣው ወደእንዱ ወገን ማዘንበል ጀመረ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስና ቶኒ ሪዞሊ የተሳካላቸው ይመስላል ። እነርሱ ዘንድ ጥሩ ካርታዎች ሲመጡ ሌሎቹን መጥር ካርታዎች ያጋጥሟቸዋል ። ሌሎቹ ጥሩ መጫወት ሲጀምሩ እነርሱ ደግሞ የበለጠ ጨዋታ ያሳያሉ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ያጋጠመውን ቆንጆ ዕድል ለማመን አልቻለም ። ምሽቱ ግማሽደጃ ላይ ወደሁለት ሺህ ዶላር ገደማ በላ ። እንደተአምር ነበር የቆጠረው ።

“እናንተ ሰዎች በጣም ቀንቶአችኋል” አለ ማርፊን ሴይሞር ።

“ይመስላል !” አለ ብሬስላአርም ። “ነገ ሌላ ዕድል ብትሰጡን ምን ይመስላችኋል ?”

“እሺ ተማክረን እናሳውቃችኋለን” አለ ሪዞሊ ።

ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ ኮሮንዚስ በአድናቆት “ለማመን ያስቸግራል ! ሁለት ሺህ ዶላር ?” አለ ።

ሪዞሊ ሳቀ ። “አዎ ትንሽ ገንዘብ አይደለም ። ነግሬህ አልነበረም ? አቶ የማይነቃበት ምላጭ ነው ። ሰዎቹ ነገ ሊሞክሩን ከፍተኛ ጉጉት

“መጫወት ነው!” አለና ኮሮንዚስ ገለፈጠ ። “እንደቆልድ ዓሎ
ንውነ ለበሚልኮነህለወታጮሽት ቢከነዚር ኮሮንዚስ ጀስት ሽሽዶላር አሸናፊ ።
። ‹‹ይዘብያ አዴን ቃል !›› አለው ሪዘሊያ ‹‹ሚሥሪያሩን ሰይሞኛል››

“በሚሥሪቹ ልኡኔ ይዘውም ነገ መደብኛን እከሩ እንጀና ጀርማሳይጠይ
ሩቁ ኦያ ቀሩሳሚጣጣንዘበት ውበ ሊያስመልሶየሚችሉ ዕመብላቱዋል ።
ቀሃስትሥሥሥሚአለሀ?” ።

። ሥሰጥና ሰ ሰተቸርሰዘበ ንለጓ ሮ
። ነጠሰኽእጀይሳ ቶኽእማጀመሠ እንጀ?እሪቸሰ ጠሥሚዘበ ቸለሚኛ

። እመጀት ጠሥሚቸፊ

ጨዋታውን ለመጀመር እንደተቀመጡ ሳል ፕሪዚ እንዲህ አለ ፡
ሸሸሥሙ ቋሰኽሠ ።እስስቱመን ሩዘሠ።ከሣሪ ጆርሶብናል።። መደቦን ከና
፡ቁፍያፎግ።ሚገ ደሥመስሰሸኽልቲ?ሥ ። ጋዘና ሥትሰሪለ ጓያ ኒእሚጀመዘ
ጋሥኔ ሥቲ ሪዘሊሲ ትኳሥኽዘርስ በኣይሩ ጠሠሥመሠ ጋዘ ፡ ቡጀመ ሥጋዘ ሥቦበ

“በበኩሌ ግድ የለኝም” አለ ሪዘሊ ። “ወዳጀቹ እኛን ተስ ነ” መ
ጓሥ ጀእኣሠ ሥ ዘሩነ ቅኣነሥቹሙን ሸበእሥን ት”ከመነቅነቹ መስማማታችሁን
ገለጡ። ። እመጀ ልዘርሠሥ ናሥመ ጀርሪእመ ጠሠሥ ሸቅዘ ቦት ።ጋዘና
ሰርጋ ለአቀ ጨልሥን የመመኒዘቹ መኣሥኽሥ ሥኣሥ ሠሪጀነሸ ሥ ሠሪጀቦ ሥኣ ቁለሰ ።
ሳልጨሸ ሣለሸሸሥ ጀመኒዘቹ ሰለመሠ ሠ ሥሠኮ ሸሸሪጀነ ሥ ሠሪጀቦ ሥኣ ቁለሰ ።
ሣ

ቶኒ ሪዞሊ ሃሣቡን ለመቀበል የሚያመነታ መሰለ ። “በበኩሌ እንጃ” ብሎ ወደቪክቶር ኮሮንዚስ ዞር አለ ። “ምን ይመስልሃል ቪክ ቶር?”

ቪክቶር በሃሣቡ ‘ዛሬ ማታ ሃምሣ ሺህ ዶላር በኪስህ ይዘህ ለመሄድ አትፈልግም ? በዚህም ቤትና አዲስ መኪና ለመግዛት እችላለሁ ። ቢተሰቤንም ለሽርሽር እወስዳቸዋለሁ ።...ኮሮንዚስ’ በጣም ከመፈንደቁ የተነሳ ሰውነቱ ይንዘፈዘፍ ጀመር ። ሳቅ አለና “እሺ ከፍ እናድር ገው” አለ ።

“ጥሩ” አለ ሳል ፕሪዚ ። “ጥቅል ዝግ ነው የምንጫወተው ። የገንዘብ ጣሪያ አይወሰንም ።”

“ይኸው እኔ አስጥለሁ ።” አለ ብሬስላአር ። “በአምስት ሺህ ዶላር እንክፈተው ።”

ሁሉም መደቡን አስቀመጠ ።

ለቪክቶር ኮሮንዚስ ሁለት ንግሥቶች ተሰጡት ። ሌሎች ሦስት ካርታዎች ሲሰብ አንድ ሌላ ንግሥት አገኘ ።

እጁ ላይ ያለውን ካርታ አየና “በሺህ ብር ከፍ ይበል” አለ።

ማርፊን ሴይሞር ካርታዎቹን አጠና ። “እጠራና በሁለት ሺህ ዶላር ከፍ አደርገዋለሁ ።”

አቶ ዳልቶን ካርታዎቹን ጣለ ። “ይበዛብኛል ።”

“እጠራለሁ” አለ ሳል ፕሪዚ ።

ማርቪን ሴይሞር ቀጥታ ዘጋ ።

በሚቀጥለው ዙር ለቪክቶር ኮሮንዚስ ስምንት ፣ ዘጠኝ ፣ አስርና ልብ ሺባ ታደለው ፣ ሲዘጋ አንድ ካርታ ብቻ ጉደለው ። “በሺህ ዶላር ።” አለ ዳልቶን ።

“ጠርቼ በሺህ ዶላር ከፍ አደርገዋለሁ ።”

“በሌላ ሺህ ዶላር እናሳድገው” አለ ሳል ፕሪዚ ።

የኮሮንዚስ ተራ ነበር ። ሌሎች የፈለጉትን ዓይነት ካርታ ቢኖራቸ ውም በቀጥታ ዝግ እንደሚያሸንፋቸው እርግጠኛ ነበር ። አንድ ካርድ ብቻ ነው የጉደለው ።

“እጠራለሁ።” አንድ ካርታ ሳበና ሊያየው ፊርቶ ጠረጴዛው ላይ ደፍቶ አስቀመጠው ።

ብሬስላአር ካርታውን አሳየ ። ሁለት አራት ቁጥሮችና ሁለት አሥር

ቁጥሮች ።

ፕሪዚም እንዲሁ አድርጉ “ሦስት ሰባቶች” አለ ።

ሁሉም ወደ ቪክቶር ኮሮንዚስ ዞሩ ። አየር ወደ ውስጥ ሳበና ካርታ እነሳ ። ጥቁር ሆነበት ። “ከሸፈ” አለና ካርታውን በተነ ።

የገንዘቡ መደብ እየጨመረ ሄደ ። የቪክቶር ኮሮንዚስም ኪስ መነመነ። ሁኔታው በጣም ስላሳሰበው ቶኒ ሪዞሊን ቀና ብሎ አየው ።

ሪዞሊ ‘እይዞህ አያሳስብህ’ የሚል ፈገግታ አሳየው ።

ረዞሊ የሚቀጥለውን ጨዋታ ከፈተ ።

ካርታዎቹ ታደሉ ።

“አንዳንድ ሺህ ዶላር እናስይዝ”

“እኔው በተጨማሪ በሺህ ዶላር ከፍ አደርገዋለሁ” አለ ፔሪ ብሬስላአር ። ማርፊን ሴይሞር “እኔ ደግሞ በሌላ ተጨማሪ ሁለት ሺህ” አለ ።

ሳል ፕሪዚ “እናንተ ሰዎች ዝም ብላችሁ የምትደነፉ ይመስለኛል ። እስቲ መደቡን ወደአምስት ሺህ ዶላር ከፍ እናድርገው” አለ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ እስካሁን የያዘውን ካርታ በደንብ አላየም ። ‘አውቆ የመላላቱ ነገር መቼ ያበቃ ይሆን ?’ ሲል አሰበ ።

“ቪክቶር ?”

ኮሮንዚስ ካርታዎቹን ቀስ እያለ አንድ በአንድ ሲዘረዝር የመጀመሪ ያው የክ ፣ እንደገና የክ ፣ ሦስተኛውም የክ ፣ ሌላ ሺባና አሥር ሆኑለት ። ደሙ በፍጥነት ተሰራጨ ።

“እንዴት ነው ፣ ውስጥ ነህ ?”

ለራሱ ሳቀ ። አውቆ መልቀቁ አብቅቷል ማለት ነው ። ሌላ ሺባ ስቦ እንደሚዘጋ አውቋል ። አሥርን ጣለና በተረጋጋ አንደበት “እጠራለሁ” አለ ።

አቶ ዳልቶን “ሁለት እስባለሁ” ብሎ ካርታውን አጠና ። “በአንድ ሺህ ከፍ አደርገዋለሁ” አለ ።

ቶኒ ሪዞሊ በአሉታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “ይበዛብኛል” አለና ካርታውን በተነ ።

“ውስጥ ነኝ” አለ ፕሪዚ “በአምስት ሺህ ከፍ አደርገዋለሁ ።”

ማርፊን ሴይሞር ካርታውን በተነና “ወጥቻለሁ” አለ ።

በቪክቶር ኮሮንዚስና በሳል ፕሪዝ መሐል ብቻ ሆነ ትንቅንቁ።
“ተጠራለሁ?” እለና ጎደቢ ጠየቀ።
“አላ እባክዎ ሺ ኦላር ያስፈልገኛል።”
ቪክቶር ኮሮንዚስ ለሚወጋ የሚጮህለትን የቀረውን መጀብ ለማወቅ ሞነ ረ። አምስት ሺህ ዶላር ብቻ ነው ያለው። አሰበ ‘ማን የሚቀጥለውን ጨዋታ ሳሸንፍ…’ አለና ካርታውን እንደሳና እየ። በፍውም ሺዘጋበት እይችልም። መጀመሪ ሰንደጓሳው ላይ አደረጎና ሌላ ካርታ ካበ። አምሰት ቁጥር ነው። ቢሆንም ያስት የበቀ አለቁ። ካርታውን ዝረገፈና “ሦስት የኩች” አለ።
ፕሪዚ ካርታዎቹን ዘረገፈና “ሁለት ዱ” አለ። ለአራቱኛ ጊዜ መጥፎ አጋጣሚ መፈጠሩ ነው።
ጎሪሰ ካንዘቡን ሰብሰቦ ሺ ወስድ ኮሮንዚስ ከው ብሎ አየው። ገጽቹን ጎኒን ቃሳፈረው መስሎ ተሰማው። ‘ለማሸነፈ እርግጠኛ እስከሆን ድረስ ካርታውን መዘርገፍ አልነበረብኝ’ አለ በአሳቡ።
ጎሪዚ አዳይ ንዘር። “ባለሰባት መደብ። አንዳንድ ሺህ ዶላር እናስይዝ” አለ።
ቪክቶር ኮሮንዚስ ማን ተስፉ ቆርጦ ቶኒ ሪዞሊ ላይ ካይቱን አቁለጨለጨ። “እኔ የለኝም…”
“ችግር የለም” አለ ሪዞሊ ወደሌሎች ዞሮ። “ሰምቸ ቪክቶር ዛሬ ዝዘሳ ካንዘብ ይዞ እልመጣም እንጂ ብዙ እንዳለው አውቃለሁ።” እናበድረውና ጨዋታው ሲያበቃ እንተሳሰባለን” ሲል ጠየቃቸው።
ፕሪዚ “ገም በል ይኸኮ የብድር ማኅበር አይደለም። የቪክቶር ኮሮንዚስን ማንነት አናውቅም። ይክፈለን አይክፈለን እንጂች እንመ ነውን?” አለ።
“ቃሉን እመኑኝ” ሲል ቶኒ ሪዞሊ ማረጋገጫ ሰጣቸው። “ለዚህም ጽቶ ኧዋሰኛል።”
አቶ ዳልቶን እንዲህ አለ፡— “ሚስቶር ኮሮንዚስ እንደሚከፍል ቶኒ ሪዞሊ ከምነረን ይበልጣል ማለት ነው።”
ሳል ፕሪዚ ትከሻውን ነቅንቆ “መልካም እኔም እስማማለሁ” አለ። “እኔም ካይ የለኝም” አለ ፒሪ ዝሬስላጀርም በዘዙለ።
አቶ ዳልቶን ወደቪክቶር ኮሮንዚስ ዞሮ እለኖ ጭን ያህል ሞፈልጋ

ለህ?” ብሎ ጠየቀው።
“እሥር ሺህ ዶላር ስጠው” አለ ቶኒ ሪዞሊ። ኮሮንዚስ በመገረም ወደቶኒ ተመለከቱ። ኢሥር ሺህ ዶላር! ሁለት ዓመት ሙሉ ሠርቶ ካገኘው የገንዘብ መጠን በላይ ነው። ግን ሪዞሊ ያለ አንዳች ነገር ይህ ሁሉ ይሰጠው አላለም።
መደቡ ከኮሮንዚስ ፊት ቲቆሰሰ። ወዲያውጠ የዘአሥ ገለለ። ያንዘብም እየመነመነ ሄደ። ቶኒ ሪዞሊም እየተባባ መጣ። ኮሞሽኑ ብሰምንት ሰዓት ዕረፍት ሰደረጉ። ከፍንዚስ ቆኒ ፈዘሴን ዋዲሂግ ወሰዶውና “ምን አካህ?” አለው። ብድንጋጭ ሰንዳፀቅ “ኧምሰኪ! ምን ደህሌ ገንዘብ እንዶታበላዘ ታውቃለህ?” ተበሳጭ ተበደ። “ምንም ሰታስብ ቪክቶር እኔሞ ተሸውቼ የለ። ለአቶ ምልክት ሰጥቼዋለሁ። ካርታ ያመሰጠቱ ተራ ለእርሱ ሰይደርስ ደጨዋታው ውጭ ይለወጣል። ብዙ ገንዘብ እንደምንበላቸው ዱታየኛል” አለው ሪዞሊ።
ወሰኔ “ሰንዴኛ ሴላ ሃያ አምስት ሺህ ዶላር ዕጠው” አለ ሪዞሊ። ማርፉን ሰይሞር ሚኔባ ቋጠረ። “ጫዋታውን ለመቀጠል እንደሚፈልግ እርግጠኛ ነህ?”
ሪዞሊ ወደ ቪክቶር ኮሮንዚስ ዞሮ “ምርጫው ያንተ ነው” አለው። ኮሮንዚስ ትንሽ አመነታ። “ሰአቶ ምልክት ሰጥቼዋለሁ። የጨዋታው ውጤት ይለወጣል’ ብሎ ሪዞሊ የነገረውን አስታወሰ። “እሺ እሜወታ ለሁ” አለ።
“ዋሳ።” ሰሳ ናኒ ሰቲቦቡሰት ጉሩዘ ሚኖ። አሰኮ ሰሳ ሃያ አሞስት ሺህ ዶላር ሞዶብ ክፉቱ ቲቁመጣል። መያቢን እንዳየ የዕድሉ በር የተከፈተለት መስሎ ተሰማው።
አቶ ዳልቶን ካርታውን አከፋፈለ። “ሞልካም ወዳጄቼ ጨዋታው ባለአምስት ኮፍታ ሞይሳኑ ነው” አሉ። “እንግዲህ ተጫዋቾቹ አስያዙ።

ዳልቶን ለእያንዳንዱ ተጫዋች አምስት ካርታ አደለ ። ኮሮንዚስ የተሰጠውን ካርታ ለማየት አልፈለገም ። 'እስቲ ይቆይ' ሲል አሰበ ። 'ጥሩ እድል ሳይገጥመኝ አይቀርም።'

'ካርታችሁን ጣሉ ።'

ማርፊን ሴይሞር ከዳልቶን በስተቀኝ ነበር የተቀመጠው ። ካርታዎቹን "ብወጣ" ብሎ ዘረገፈ ።

የሚቀጥለው ሳል ፕሪዚ ነበር ። "ጠርቼ በሺህ ከፍ አደርገዋለሁ" አለና መደቡን ከጠረጴዛው መሃል ላይ ቆለለ ።

ፔሪ ብሬስላአር ካርታውን እይቶ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ ። "እኔም በአምስት ሺህ ከፍ አደርጋለሁ ።"

ቪክቶር ኮሮንዚስ በጨዋታው ውስጥ ለመቆየት ስድስት ሺህ ያስፈልገዋል ። በዝግታ ካርታዎቹን ሰብስቦ ዘረዘራቸው ። ያየውን ለማመን ከበደው ። ቀጥታ እንዲዘጋ ተሳስቶ ነው የመጣለት ። አምስት ስድስት ፡ ሰባት ፡ ስምንት ፡ ዘጠኝ ልብ ። ግሩም ካርታ ! ለካ ቶኒ እውነቱን ነበር የተናገረው ። በልቡ 'ተመስገን ፈጣሪ' አለና ደስታውን ለመደበቅ ሞከረ ። "በሌላ አምስት ሺህ ብር ከፍ አደርገዋለሁ" ሲል ተናገረ ። ይሄ ነዋ በጣም ሀብታም የሚያደርገው ።

ዳልቶን ካርታውን በተነና "አልሆነልኝም ፡ ያለፈኝ" አለ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስን ፈንድቅ ፈንድቅ አለው ። እጁ ውስጥ ያለው ካርታ ተሳክቶ ነው የሚጠብቀው ። ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ የቁማር ድል ሊገኝ ነው ።

ፔሪ ብሬስላአር ካርታውን አጠና ። "እሺ ጐበዝ ፡ ልጥራና በአምስት ሺህ ከፍ ላድርገው መሰለኝ ።"

እንግዲህ የቪክቶር ዕድል እንደኮሮንዚስ ምርጫ ነው ። አየር ወደውስጥ ሳበና "አየህ አይደል! በሌላ አምስት ሺህ ከፍ አድርጌዋለሁ ።" ሲል ተናገረ ። መቼም በጉጉት ተርበትብቷል ያን ሁሉ ሊዝቅ ።

ፔሪ ብሉስላአር ካርታውን ዘረዘረና በድል አድራጊነት "ሦስት ሼባዎች" አለ ።

'መዝጋቱ ነው' ሲል አሰበ ኮሮንዚስ ። በፈገግታ ተሞልቶ "ቀጥታ ዘግቻለሁ" አለና ካርታውን አስቀምጦ በጥድፊያ እጁን ወደገንዘቡ ዘረጋ።

"ተው !" አለና ሳል ፕሪዚ በዝግታ ካርታዎቹን ዘረገፈ ። "ካንተው

በላቀ ዝግ አሸንፍኩህ ። አሥር ጦር የክ ።"

የቪክቶር ኮሮንዚስ ፊት ገረጣ ። እራሱን እንደመሳት አደረገውና ልቡ በፍጥነት መምታት ጀመረ ።

"የክርስቶስ ያለህ !" አለ ቶኒ ሪዞሊ ። ሁለት ተከታታይ ቀጥታ ዝግ!" ወደ ኮሮንዚስ ዞሮ "በጣም እዝናለሁ ቪክቶር ም... ምን እንደምል አላውቅም !" ሲል ተናገረ ።

አቶ ዳልቶን በመጨረሻ እንዲህ አለ ፦"ወዳጆቼ ለዛሬው እዚሁ ላይ ቢያበቃ የሚሻል ይመስለኛል ።" ከአጠገቡ የተቀመጠውን ወረቀት እያየ ወደ ቪክቶር ኮሮንዚስ ዞር ብሎ "ስልሳ አምስት ሺህ ዶላር አለብህ" አለው ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ደንግጦ ቶኒ ሪዞሊን እያየ ቀረ ። ሪዞሊ ተሰፋ በመቁረጥ ትከሻውን ነቀነቀ ። ኮሮንዚስ መሐረብ አውጥቶ ግንባሩን መጥረግ ጀመረ ።

"ይህንን ዕዳህን እንዴት መክፈል ትፈልጋለህ?" አለና ዳልቶን ጠየቀው ። "በጥሬ ገንዘብ ወይስ በቼክ ?"

"እኔ ቼክ አልቀበልም" አለ ፕሪዚ ። ወደቪክቶር ኮሮንዚስ ተመለከተና "ጥሬ ገንዘብ ነው የምፈልገው" ብሎ ተናገረ ።

"እኔ...እኔ ..." ቃላቱ አልመጣልህ አሉት ። በፍርሃትና ድንጋጤ መንቀጥቀጥ ጀመረ ።

"ያን ... ያንን ያህል ገንዘብ የለኝም ..."

የሳል ፕሪዚ ፊት ጠቆረ ። "ምን ?" አለና አንቧረቀ ።

ቶኒ ሪዞሊ ቶሎ አለና "እስቲ ቆዩ ለጊዜው በእጁ የለም ነው ቪክቶር የሚለው ። በኋላ ሊከፍል እንደሚችል ገልጨላችሁ የለ ?"

"ቃላት ብቻ አይበቃም ሪዞሊ ። ገንዘቡ ሲከፈል ለማየት እንፈልጋለን ።"

"ይከፈልሃል" አለ ሪዞሊ በድጋሚ ማረጋገጫ ሲሰጥ ። "በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ይመጣልሃል ።"

ሳል ፕሪዝ ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሳና "ዞር በል ፡ እኔኮ የበጉ አድራጊ ድርጅት አይደለሁም ። ገንዘቡን እስከነገ ለማግኘት እፈልጋለሁ" ብሎ ተናገረ ።

"አታስብ ፡ ያመጣልሃል ።"

ለቪክቶር ኮሮንዚስ ነገሩ አንዳንዴ ሕልም ይመስለዋል ። ማምላጫ

የለውም ። ሌሎቹ እየወጡ ሲሄዱ እንኳ ሰውነቱ በድንጋጤ ዝሎ እዚያው እተቀመጠበት ፈዘዘ ። በከፍተ ውስጥ ቂኒና ኮሮንዚስ ብቻ ቀሩ ።

ኮሮንዚስ በድንጋጤ ተውጧል ። "እኔ እንዲ ያንን ያህል ገንዘብ መቼም ባሆን ለማግኘት አሳችልም ።" አለ ተስፋ በመቁረጥ ። "ንጉሡም ይቅር አላልኝም ።" ብሎ ተናገረ ።

ሪዘሊ ከኮሮንዚስ ተከፋ ላይ እጁን ጫል አደረገና "ምን ለማለት እንደምችል አላውቅም ቪክቶር ምን እንደነካህ ማወቅ አልቻልኩም ። ከሁሉ በላይ ግን ከኔ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ተበልጦሀል" ሲል ንግግሩን ቀጠለ ። "ወጪ ብቻ ነው ። ልጆችህን ልቦ ምን ቁበኒበ ሊያጽናናው ሞከረ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ሃይሎቹን ሰብስቦ ተነሳና ወዳጁን አቀፈው ። ከንፈሩን ነክሶ ደሙን ከንፈሩ ላይ ተጠማ ። ከዚያ ቀስ ብሎ ከሪዘሊ ክንድ ውስጥ ተፈታ ።

ቶኒ ሪዘሊ "ቪክቶር አንተን ብሆን በጉዳዩ አስብበት ። ሻል ቅሬቲ የጀስት ኮስቶሜትክ ሙያ ከጭንቅላት መደቆስ ይልቅ እንኳን ደህና ዘምት ይሻላል በጣም አደገኛች እንደሆኑ አምነህበት ነበር" ። ከቀናው ይህን ይችላል ? ከሌሎች ጋር ውስጥ ሰላም ፈጣሪ ሆኖ ለመኖር ምን ያደርጋል ? ከሌሎች ጋር ውስጥ ሰላም ፈጣሪ ሆኖ ለመኖር ምን ያደርጋል ?

"ከሁሉም አደገኛው እንደሆነች አሳስበህ ነበር" አለው ሪዘሊ በለሆ ሳስ። "ሰዎቹን ልኩብህ የጉልበትህን ሎሚ ሊያስፈስሰው ይችላል" ። ሁለተኛ በእግርህ እንዳትራመድ ያደርጉሃል" ። ከዓይንህ ውስጥ አሲድ እንዲጨምቁብህ ሊያስደርግ ይችላል" ። ዓይነ ሥውር ሆነህ ተቀራለህ ማለቱ ነው ። "ከዚህ ሁሉ ዘቀይ ከጓላም ተበታትሎ ሊያስነድልህም አይሳነውም ። ከቪክቶር ቅሮንዚስ ፈዛዛ ፊት ላይ ጀዙ ቀረ ። "ት... ትቀልዳለህ ልበል ?"

ጥቂት ቆልደ ቪሆንማ ደሸ ባለች ። ሁሉም ጓደኛው የእኔነው ቪክቶር ። ከሳል ፕሪዚ ዓይነት ሰው ጋር ቁመር እንድትሔዉት ማድረግ እልነበረብ ኝም ። ሰውዬው ርህሪሄ የሌለው ነፍሰ ገዳይ ነው ።

"ገንዘቡን ለማግኘት የምትችልበት ምንም መንገድ የለም ?" ኮሮንዚስ በብስጭት ከት ብሎ ሳቀ ። "እጄ የማገኘው ጭመዘዝ ቢቀበለኝ እንኳ ለማስቀደር አይበቃም ።

"መልካም ቪክቶር ። እኔ አሁን የምሰጥህ ምክር ቢኖር ከተማውን ለቀህ እንድትወጣ ነው ። ከቻልክ ከዚህ አገር ውጣ ። ፕሪዚ ሊደገኝህ ወደማይችል አካባቢ ዞር ማለት ይኖርብሃል ።"

"አልችልም" አለ ቪክቶር ኮሮንዚስ አሳቡን አለማቁዐሱን ሲገልፅ። "ሚስቲና አረተ ልጆች አሉኝ ።" ቶኒ ሪዘሊ ላይ በንዴት አፈጠጠበት ። "እንደማንሸነፍ ነግሬሻን የነበርክው እንተ ነህ ። እንዳልከኝም ።

"ልክ ነህ ። በማም አዝናለሁ ። ከዚህ ቀደምኮ በዚህ ዓይነት ዐዙ ተጠቅመን ነበር ። ምናልባት ፕሪዚ አሟባርባርን ይሠፍል ብዬ እገምታለሁ ።

የኮሮንዚስ ፊት እንደገና በተስፋ ተመላ ። "ዎሩ ። ደሙበረበረን ስለሆን እኔም አልከፍለውማ" አለ ።

"እንዲህስ ለማለት የሚከብድ ይመስለኛል ቪክቶር" አለው ሪዘሊ በእርጋታ ። "አሜበርብሪሃል ብለህ ልትወቅሰው ከቻኒሳህ ይችድልሃል ። አልከፍልህም ብለህ ከተጋተርከውም ይጠፋሃል ።"

"አዜት ፈጣሪዬ" አለ ኮሮንዚስ በማተቱም ። "ሞቻለሁ በለኛ!"

"በጣም አዝናለሁ ። ገንዘቡን ልታገኝ የምትችልበት ምንም ዘዴ የለም ? ..."

ያንን ያህል ገንዘብ ለማግኘት በእንግዲህ መቶ ዓመት መኖር አለብኝ ። ምናልባትም ሺህ ዓመት ። ያለኝ ንብረት ሁሉ በባንክ ዋስትና የተያዘ ነው ። ታዲያ ከየት አመጣለሁ ?"

በዚያች ቅፅበት በቶኒ ሪዘሊ አእምሮ ውስጥ አንዲት አሳብ ብልጭ አለችለት ። "ቆየኝ ቪክቶር ። በመዘየማችሁ ውስጥ ያሉት እንኳን ዎንታዊ ቅርሶች ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ ብለሽን አልነበረም ?"

"እም ብዬ ነበር ። ታዲያ ያ ከዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለው ?"

"ቆይ አስጨርሰኝ ። ከዋናዎቹ ተመሳሰለው የቋሠፉትም ኮፒዎች ከጀንበኞቹ ቅርሶች ጋር ይመሳሰላሉ ብለሃል ።"

"በእርግዮ ልዩነት አሳቸው ። ማንም ብልሙይሉዩርቸው ይችላል ።"

"ቆየኝ እባክህ ። ምናልባት አንዱ ቅርፅ ብቻ ሰብስቦ በዘነው አርሶን

መስሎ የተሠራው ቢተካ ምን ይመስልሃል ? ማለቴ ሙዚየሙን በጉበኘሁበት ወቅት በርካታ አገር ጉብኚዎች እየተዘዋወሩ ቅርሶቹን ሲመለከቱ አይቻለሁ ። ታዲያ ዋናውን ቅርስ ተመሳስሎ ከተሠራው ሊለዩ ይችላሉ ?”

“እይደለም ። ግን... ም...ምን ለማለት እንደፈለግክ ገባኝ ። እንደዚያ ዓይነት ተግባር ለመፈጸም ጨርሶ አላሰብም ።”

ሪዞሊ ረጋ ባለ የለሆሳስ አነጋገር “ይገባኛል ቪክቶር ። ምናልባት አንድ አነስተኛ ቅርስ ከሙዚዬሙ ቢወጣ ይሀንን ያህል አይጉዳም ብዬ ስላሰብክ ነው ። ብዙ ስብስብ እኩ ናቸው” አለው ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “የሙዚየሙ ኃላፊ ሆኜ ላለፉት ሃያ ዓመታት ስሠራ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር አስቤ አላውቅም ።”

“ይቅርታ ፣ እንዲህ ዓይነቱን አሳብ ማቅረብ አልነበረብኝም ። ግን ምን ላድርግ ሕይወትህን ያተርፋል ብዬ ስላሰብኩ ነው ።” ሪዞሊ ተንስቶ ቆመና ተንጠራራ ። “መልካም በጣም ስለመሸ ባለቤትህ የት ጠፋ ብላ ሳትጨነቅ አትቀርም” አለው ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ትኩር ብሎ አየውና “ሕይወትህን ያተርፋል አልከኝ ? እንዴት ?” ሲል ጠየቀው ።

“ግልፅ ነው ። ከእነኚያ ቅርሶች አንዱን ብትወስድና ...”

“አንዱን ብትወስድና ?”

“...ብትወስድና ... ለእኔ ብትሰጠኝ ከአገር አስወጥቼ ልሸጥልህና ያለብህን የፕሪዚ ዕዳ ልክፍልልህ እችላለሁ ። ትንሽ ጊዜ እንዲሰጥህም ላግባባው የምችል ይመስለኛል ። ከዚያ በኋላ ከመሳደድ ትገላገላለህ ። ይሀንን ሳደርግ ደግሞ ምን ያህል አደገኛ መስዋዕትነትን እንደምከፍል ለአንተ መንገር ያለብኝ አይመስለኝም ። እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ስፈጽም ከተያዝኩ ትልቅ አደጋ ይጠብቀኛል ። ግን የምለፋውም በዚህ ዓይነቱ ችግር ውስጥ ለመግባትህ ምክንያቱ እኔ ነኝ የሚል ፀፀት ስለተሰማኝ ነው ።”

“ጥሩ ጓደኛ ነህ” አለው ቪክቶር ኮሮንዚስ ። “ግንኩ እንተ መውቀስ አልችልም ። ከመጀመሪያውኑ እንደዚያ ዓይነት ጨዋታ ውስጥ መግባት አልነበረብኝም ። አንተማ እኔን ለመርዳት ስትል ነበር ።”

“እውቃለሁ ። ቢሳካልህ ኖሮ ደስ ይለኝ ነበር ። መልካም ፡ ሂደን ትንሽ እንቅልፍ ብናገኝ ጥሩ ይመስለኛል ። ነገ እንነጋገራለን ፡ ደህና

እደር ቪክቶር ።”

“ደህና እደር ቶኒ ።”

በሚቀጥለው ቀን ማልዶ ወደሙዚየሙ ስልክ ተደወለ ። “ኮሮንዚስ ነህ ?”

“አዎ”

“ሳል ፕሪዚ ነኝ ።”

“እንደምን አደርክ ሚስተር ፕሪዚ”

“የደወልኩት ስለዚያ ስልማ አምስት ሺህ ዶላር ጉዳይ ነው ። በስንት ሰዓት መጥቼ ልውሰደው ?”

ቪክቶር ኮሮንዚስን ላብ አሰመጠው ። “እኔ... እኔ አሁን ገንዘቡ የለኝም ሚስተር ፕሪዚ ።”

ፀሰልኩ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ።

“እንዴት ነው እንዲህ የምትቀልድብኝ ?”

“እየቀለድኩ አይደለም ። እኔ...”

“ታዲያ ገንዘቤን እፈልጋለኋ ! ግልጽ ነው ?”

“አዎ ጌታዬ ።”

“ሙዚየሙ የሚዘጋው በስንት ሰዓት ነው ?”

“አሥራ ሁለት ...በአሥራ ሁለት ሰዓት”

“እዚያው እመጣለሁ ። ገንዘቡን አምጣልኝ ወይም ድራሽህን አጠፋለሁ ። እውነት አልሃለሁ ከዚያ በኋላ እንደሌለህ ነው የማደርግህ ።”

ስልኩ ተዘጋ ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ እንደደነገጠ ቁጭ ብሎ ቀረ ። ለመደበቅም ፈልጐ ነበር ። ግን ወዴት ይሂድ ? ጨርሶ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት መላ ሰውነቱን ያዘረረው ። እንዲህ ባላደረግኩ ኑሮ የሚሉ የተለያዩ አሳቦች መጡበት ። ‘ግን ዕለት ማታ ወደካሲኖው ባልሄድኩ ኖሮ ፣ ቶኒ ሪዞሊን ባልተዋወቅ ት ኖሮ ፣ ሁለተኛ ቁማር አልጫወትም ብዬ ለባለቤቴ የገባሁትን ቃል ዳን በጠበቅኩ ኖሮ...’ ጭንቀቱን ከአእምሮው ለማውጣት ጭንቅላቱን ርገፈገፈ ። ‘አሁን አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ’ አለ በአሳቡ ።

በዚያች ቅጽበትም ቶኒ ሪዞሊ ወደቢሮው ገባ ። “እንደምን አደርክ ቪክቶር ።”

* * *

ሰዓቱ አሥራ ሁለት ተኩል ሆኗል ። ሠራተኞቹ በሙሉ ወደቤታቸው ሄደዋል ። ሙዚየሙ ከተዘጋ ግማሽ ሰዓት ያህሥዋል ። ቪክቶር ኮሮንዚስና ቶኒ ሪዞሊ የፊትለፊቱን በር በትኩረት ይመለከቱ ነበር ።

ኮሮንዚስ የበሊቋን እየቀጨነቀ ሙጫ ። "አሳውቅልህም ብል ምን ይደርስብኛል ? ገንዘቡን ብሬ ማታ አምጣ ቢለኝስ ምን ይውጠኛል?"

"እኔ እነግረዋለሁ" አለ ቶኒ ሪዞሊ ። "ማነጋገሩን ለእኔ ተውልኝ ።"

"እራሱ ባይመጣስ ? ምናልባትስ ዝምብሎ ... ታውቃለህ ... የሚገድለኝ ሰው ቢልክስ ? ለማንኛውም እንደዚያ ያሚያደርግ ይመስልሃል ?"

"በሞራሽ ፡ ገንዘቡን የሚያገኝ ማዘዣ ኑን እስክወቀ ድረስ እንጂ ሌላ ዓይነት ነገር አያደርግም" ብሎ ሪዞሊ አረጋጋው ።

ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ላይ ሳል ፕሪዚ መጣ ። ኮሮንዚስ ተነስና ፀራንክፍቶ አስገባው ። "እንደምን አመሸችሁ" አለ ሲገባ ።

ፕሪዚ ወደሪዞሊ አየና "እንተ ደግሞ እዘህ ምን ትሠራለህ?" ብሎ ጠየቀው ። ወደቪክቶር ኮሮንዚስ ምልክት ዘረና "ያንተ ጉዳይ መሰለኝ ።"

"ነገሩን አታክብደው" አለው ሪዞሊ ። "የሞጣህት ላማባባት ነው ።"

"ያአንቺን ማግባባት አልፈልግም" አለና ፕሪዚ ወደክሮንዚስ ተመለሰ "ባንዘቤ ይታለ?"

"የለ... የለኝም ። ግን ..."

ፕሪዚ ጉርደውን ቀንቆ ያዘ ። "ከሰሚያስለ አንተ ጉዳዩ ገንዘቤን ካሳጣኝለሁ ። አስባለሁ አንቁ ክሳዳህ ላመሬ ውርደሃለሁ ። ገብቶሃል ?"

ቶኒ ሪዞሊ "እንደ ተገባቸው ብል እንጂ ። ገንዘብህን ታገኘዋለህ" አለው ። ፕሪዚ ወደሪዞሊ ዞር አለና "ገንዘቤ እዴት ነው ሊመለስልኝ የሚችለው ?" ብሎ አፋጠጠው ።

"ለምን አይመለስልህም ? ቪክቶርን ይጠይቀው ። በእርግጥ ለገዢው ሳጋዘብ የለውም ። ግን ገንዘቡን የሚያገኙት መንገድ አለ ።"

"ገንዘቡን ይዟል አልያዘም ?"

"ይዟልም አልያዘምም" አለ ሪዞሊ ።

"ምን ዓይነት መልስ ነው ?"

ቶኒ ሪዞሊ በጣቱ በማመልከት "ገንዘቡ እዚያ አለ" አለ ።

ሳል ፕሪዚ ዞር ብሎ ክፍሉን ቃኘና "የት?" ሲል ጠየቀ ።

"እነኚያን መደርደሪያዎች ታያለህ ? በተለያዩ ቅርሳ ቅርሶች ተሞልተዋል ።"

"እም በቅርሳ ቅርሶች" አለ ኮሮንዚስም ቀበል እድርጉ ። "ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ናቸው ። የማወራልህ ስለሚሊዮን ዶላር ነው ።"

"በእውነት ?" አለና ፕሪዚ ዞር ብሎ መደርደሪያዎቹን ለማየት ሞከረ ። "እዚያ ውስጥ ተቆልፎባቸው ያሉ ቅርሶች ታዲያ ለእኔ ምን ይጠቅሙኛል ? እኔ የምፈልገው ጥሬ ገንዘብ ።"

"ጥሬ ገንዘቡ ይገኛል" አለው ሪዞሊ በቀስታ ። "እንዲያውም በኔደኛዬ ላይ ካለው ዕዳ የእጥፍ እጥፍ ያህል ። ትንሽ ጊዜ ብቻ ታጎስን ። ቪክቶር አጭበርባሪ ሰው አይደለም ። ትንሽ ጊዜ እንዲሰጠው ይፈልጋል ። ያቀደው ምን እንደሆነ ልንገርህ ። ቪክቶር ከእነኚህ ቅርሶች መካከል አንዱን ወስዶ ... ሊሸጥና ገንዘቡን እንዳገኘ ወዲያው ሊከፍልህ ነው ።"

ሳል ፕሪዚ ጭንቅላቱን ነቅነቀና "ደሰ አላለኝም ። ስለእነኚህ ቅርሳቅርሶች ደግሞ የማውቀው ምንም ነገር የለም" አለ ።

"አንተ ማወቅ ያለብህ አይመስለኝም ። ቪክቶር በዚህ በኩል በዓለም ካሉት እውቅ ባለሙያዎች መካከል አንዱ ነው ።" ቶኒ ሪዞሊ ወደአንደኛው መደርደሪያ ሂደና ጣቱን ወደአንዱ ጠቁሞ "ይህ ምን ያህል ያወጣል አልክኝ ቪክቶር ?" ሲል ጠየቀው ።

ቪክቶር ኮሮንዚስ ምሬቁን ዋጠ ። "ያቺ በአሥራ አራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ በፊት የነበረች ሃይጂአ የተሰኘች አማልክት ናት ። ማንም የቅርሳ ቅርስ ሰብሳቢ ዓይኑን ሳያሽ ዘሁለት እስከ ሦስት ሚሊዮን በሚደርሱ ገንዘብ ይገዛታል ።"

ሪዞሊ ወደሳል ፕሪዚ ዞር አለና "ያልኩት ይህንን ነው ። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባህ ?" ብሎ ተናገረ ።

ፕሪዚ ግንባሩን ቋጠረ ። አላወቅኩም ነበር ። ታዲያ ለምን ያህል ጊዜ ነው መጠበቅ ያለብኝ ?"

"በአንድ ወር ውስጥ ገንዘቡህ እጥፍ ተደርጉ ይሰጥሃል ።"

ፕሪዚ ትንሽ አሰበና ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። "እሺ ፡ ለወር ያህል

መጠበቅ ካለብኝ ግን ጭማሪ እፈልጋለሁ ። ማለቴ ወደ መቶ ሺህ ዶላር በተጨማሪ ።”

ቶኒ ሪዞሊ ወደቪክቶር ኮሮንዚስ ዞር ብሎ ተመለከተ ።

ኮሮንዚስም አባባሉን በመቀበል ጭንቅላቱን ነቀነቀ ።

“እሺ” አለ ሪዞሊ። “ባልከው ተስማምተናል ።”

ሳል ፕሪዚ ወደአጭሩ የሙዚዬም ኃላፊ ጠጋ አለ ። “ሰላሳ ቀናት እሰጥሃለሁ ። በዚህን ጊዜ ውስጥ ገንዘቤን ባትሰጠኝ ግን ሥጋህ ለውሾች ይጣላል ። ማለት የፈለግኩት በደንብ ግልጽ ሆኖልሃል ?”

ኮሮንዚስ የሰማውን ዋጥ አድርጎ “እዎ ጌታዬ!” አለ ።

“አስታውስ ...ሰላሳ ቀናት ።”

ቶኒ ሪዞሊንም እፍኖጠ ለጥቂት ጊዜ አየው ። “እንተን ግን አልወድህም ።”

ሳል ፕሪዚ ወደኋላ ዞሮ ወጥቶ ሲሄድ ዝም ብለው ያዩት ነበር ።

ኮሮንዚስ ተቀምጦ ግንባሩን እያሻሸ ቀረ ።

“አቤት እምላኬ !” አለ ። “ሊገድለኝ የመጣ መስሎኝ ነበር ። በሰላሳ ቀናት ውስጥ ገንዘቡን እግኝተን የምንሰጠው ይምስልሃል ?”

“አዎ” ሲል ቶኒ ሪዞሊ አረጋገጠለት ። “ማድረግ ያለብህ በመደርደሪያው ላይ ካሉት ቅርሶች አንዱን ብቻ አንስተህ በምትኩ አምሳያውን መተካት ነው ።”

“እንዴት አድርገህ ከአገር ልታስወጣው ትችላለህ ? የያዙህ እንደሆነኮ ወህኒ ቤት ትወርዳለህ ።”

“መች አጣሁ” አለ ቶኒ ሪዞሊ በድፍረት ። “ቢሆንም ዕድሌን መሞከር አለብኝ ። ቪክቶር ፣ ያንኑ ያህል ነው ላንተም የምጨነቀው ።”

ከአንድ ሰዓት በኋላ ቶኒ ሪዞሊ ፣ ሳል ፕሪዚ ፣ አቶ ዳልቶን ፣ ፔሪ ብራስላአርና ማርቪን ሴይሞር ዳልቶን በተከራየው የሆቴል ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለው መጠጥ ይጠጡ ነበር ።

“እንደሐር ልስልስ” አለ ሪዞሊ ጉራውን ሲነዛ ። “ያ ደደብኮ ሱሪው ላይ ሸና ።”

ሳል ፕሪዚ ሳቀ ። “አስቦካውት አይደል ?”

“እኔንም እኮ አስፈራራኸኝ” አለ ሪዞሊ ። “ልክ ደንበኛ ተዋናይ ሆነህ ነበር ።”

“እሱን በምን ተስማማችሁ?” ሲል ጠየቀ ማርፊን ሴይሞር ።

ሪዞሊ “የተስማማነው ከእነዚያ ቅርሶች አንዱን አውጥቶ ሲሰጠኝና ደብቄ ከአገር የሚወጣበትን ዘዴ ፈልጌ እንድሸጠው ነው ። ከዚያም ለእያንዳንዳችሁ ድርሻችሁን ልከፍል” ሲል ተናገረ ።

“በጣም ቆንጆ !” አለ ፔሪ ብራስላአር ። “አሳቡን ወድጂዋለሁ ።”

‘የወርቅ ማዕድን ባለቤት እንደመሆን ነው’ አለ ሪዞሊ በአሳቡ። ‘ኮሮንዚስ እንዴ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ከጀመረ ወጥመዱ ውስጥ ገባ ማለት ነው ። ከእንግዲህ ሊያመልጥ የሚችልበት ምንም ዘዴ አይኖረውም ። ሙዚየሙ ውስጥ ያለውን ሁሉ አጣርቶ እስኪያወጣ እጨምቀዋለሁ ።’

ማርፊን ሴይሞር “ለመሆኑ ዕቃውን እንዴት አድርገህ ከአገር ልታስወጣ ነው ?” ሲል ጠየቀው ።

“ዘዴ እፈልግለታለሁ” አለ ቶኒ ሪዞሊ ። “ዘዴ አገኝለታለሁ ።”

መፈለግም አለበት ። ምክንያቱም ባስቸኳይ አልፍሬዶ ማንኩሶና ጂኖ ላቬር እየተጠባበቁት ነው ።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ስታዲዩ ጎዳና ላይ በሚገኘው ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ አሰቸኳይ ስብሰባ እየተደረገ ነው ። በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ ያሉት የፖሊስ አዛዥ ዴሚትሪ ፣ ተቆጣጣሪ ቲኖ ፣ ተቆጣጣሪ ኒኮሊኖ፣ ከዩናይትድ ቴቴትስ የመጣው ምልት ኬሊና ሌሎችም በርካታ የመረጃ ሠራተኞች ናቸው ። የአሁኑ የስብሰባ መንፈስ ካለፈው ስብሰባ በጣም የተለየ ነው ።

ተቆጣጣሪ ኒኮሊኖ እንዲህ አለ፦ “የሰጠሽንን መረጃ ተከክለኛ ነት ለመቀበል አሳማኝ ምክንያት አግኝተናል ሚስተር ኬሊ ። ቶኒ ሪዞሊ ግምቱ በጣም ከፍተኛ የሆነ ሄሮይን ከአቴንስ ሸሽቱ ለማውጣት በመዘጋጀት ላይ እንዳለ የመረጃ ምንጮቻችን አሳውቀውናል ። ዕቃውን ደብቆበታል ብለን የምንጠረጥራቸውን መጋዘኖች መፈተሽ ጀምረናል።”

“ለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ሰው ተመድቧል?”

“ክትትል የሚያደርጉበትን ሰዎች ቁጥር ዛሬ ጠዋት ክፍ አድርገ ናል” አለ የፖሊሱ አዛዥ ዴሚትሪ ።

ዎልት ኬሊ “እግዜር ይረዳናል” አለ በተስፋ ።

እንዲከታተለው ተቆጣጣሪ ኒኮሊኖ ሁለት የስለላ ቡድን ቢያሰማራ በትም ቶኒ ሪዞሊ ለነገሩ ምንም ክብደት አልሰጠውም ። ከሰዓት በኋላ ሰዎች እየተከታተሉት መሆኑን ተረድቷል ። ካረፈበት ከትንሿ ሆቴል ሲወጣ አንዱ ፣ ወደ ሆቴሉ ሲመለስ ደግሞ ሌላው ሰላይ ከኋላ ኋላው በርቀት እንደሚያጅበው አውቋል ። መረጃ ሠራተኞቹ በእርግጥ ጎበዝ ሰላዮች ናቸው ። ሪዞሊ በዚህ ቅር አልተሰኘበትም ። እንዲያውም የታላቅነት ምልክት አድርጎ ወስዶታል ።

እንግዲህ መቀየስ ያለበት ስልት ሄሮይኑን እንዴት ከአቴንስ እንደሚያወጣው ብቻ ሳይሆን ዋጋው የማይታወቀውን ጥንታዊ ቅርስ ከግሪክ እንዴት እንደሚያሸሽም ጭምር ነው ። ‘አልፍሬዶ ማንኩሶና

ጂኖ ላቬሪ ጀርባዬ ላይ ተፈናጥው ወጥረው ይዘውኛል። ጎተራ ውስጥ በየቦታው ተሰማርተው በዓይነቁራኛ እየጠበቁኝ ሚፈናፈንበት ሁኔታ ውኖል ። ከዚህ ማጥ ውስጥ ለመውጣት ሰው ፈልጌ ማግኘት አለብኝ። ሌለ በአሳቡ ። በዚህ ያሞጋቀቲ ወቅት ስለቭ ብሩኔ የሚሉት ሰው ብቅ አሉ መጥቢት። ሰውዬው ባርሞ የሚገኝ የሱኅቲኛ ሞርካቲ ባለቤት ነው ። ሪዞሊ ከዚህ በፊት ከብሩኒ ጋር ብዙ ሥራዎችን አብሮ አከናውኗል ። አዲስ ነው ግን ከማሚት ይሻላል ።

* * *

በሆቴል ክፍሉ ውስጥ የሚገኘው ስልክ ለመጠለፉ ሪዞሊ እርግጠኛ ነበር ። ‘ሰደ ሚስጥራዊ ተጽዕኖ ውስጥ ነኝ’ ሚል መልዕክት ለማስመሰል ሚንቅላቱን ነቀነቀ ። “በክፍሌ ውስጥ የሚገኘው ስልክ እንኳ እንዲጠለፍ አድርጋለች ።”

“እሷ ዓቶች!” አለ ጎረቤትየው ። “እግዜር ይይላቸው ። እኔም ባለቤቴን የፈታኋት ባለፈው ዓመት ነው ። በእርግጥ መፍታት የነበረብኝ ከአሥር ዓመት በፊት ነበር ።”

“እውነትህን ነው? የሆነ ሆነና ልጠይቅህ የመጣሁት የክፍልህን የስልክ ቁጥርን ነግረኸኝ የተወሰኑ ጥቂት ጓደኞቼ በእንተ ቁጥር እንዲደውሉልኝ እንድትፈቅድልኝ ነው ። ብዙ ጥሪዎች እንደሚያናሩ አረጋግጥልሀለሁ ።”

ሰውዬው ጭንቅላቱን አወዛወዘና “ እሺ ግድ የለም!” አለ ።

ሪዞሊ ከኪሱ የመቶ ዶላር ኖት አወጣ ። “ይህ ለአንዳንድ ችግሮች ይሆንሃል” አለው ።

ሰውዬው ከንፈሩን መጠጠና “እሺ ፣ መልካም” አለው ። “ምንም ችግር ያለው አይመስለኝም ። የተቸገረ ሰው መርዳት እኔንም ደስ ይለኛል።”

“በጣም እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። የስልክ ጥሪ ሲናረኝ በሬን እንኳኳ ። ብዙውን ጊዜ እዚሁ ነኝ ።”

“እሺ ።”

* * *

በሚቀጥለው ቀን ሪዞሊ ግልዶ ተነሳና ለኢቮ ቡሩጊ ለመደወል ወደከተማው ስልክ ቤት ሄደ ። የኢጣሊያ አገር መለያ 39 ቁጥር ሲሆን የሮማ ከተማ መለያ ቁጥር ደግሞ 6 ነው ። ይህንኑ አስመዘገበ ።

“ሲኞር ብሩጊ ፣ ፐርፒኦቼሬ”

“ኖ ፣ ሲ ኢን ካሳ”

“ኳንዶ ፣ አሪቬራ?”

“ኖ ፣ ሎ ፣ ሶ”

“ግሲ ፣ ዲቻ ፣ ዲ ፣ ቺአግሬ ፣ ኢል ሲኞር ፣ ሪዞሊ ።”

ሪዞሊ እንዲደወልለት የሆቴሉን ዋና የስልክ ቁጥርና የጉሪቤቱን የክፍል ቁጥር ሰጥቶ ወደመኝታ ቤቱ ተመለሰ ። ክፍሉ በጣም አስጠልቶታል ። አንድ ሰው ከእለታት አንድ ቀን እንዳጫወተው ሆቴል በግሪክኛ “ክሴናዶቺአን” ነው ። የዚህም ፍቺ የዕቃ ማጉሪያ ወይም ማጠራቀሚያ ማለት ነው ። ‘አንዳንዴም እሥር ቤት ይመስላል’ አለ ሪዞሊ በአሳቡ ። ወንበሮቹ አስቀያሚዎች ናቸው ። አንድ ያረጀ አረንጓዴ ሶፋ ፣ የራስጌ መብራት ያለበት የተሰበረ ጠረጴዛ ፣ አንድ የመጻፊያ አነስተኛ ጠረጴዛ ከነወንበሩና አሮጌ አልጋ ናቸው ክፍሉ ውስጥ ያሉት። ሪዞሊ ፣ ከአሁን አሁን በሩ ይንኳኳ ይሆን እያለ ሁለት ቀን በሙሉ ከክፍሉ አልወጣም ነበር ። ምግቡን እንኳ እንዲያመጡለት ልጆችን ነበር የሚልከው ። ምንም

ጥሪ የለም ። ‘ኢቮ ብሩጊን ምንዋጠው?’ ሲል ራሱን ጠየቀ ።

የክትትል ቡድኑ ለተቆጣጣሪ ኒኮሊኖና ለዎልት ኬሊ ሪፖርት አቀረበ ። “ሪዞሊ ሆቴሉ ውስጥ መሽጓል ። ባለፉት አርባ ስምንት ሰዓታት ወጥቶ አልታየም ።”

“ከውስጥ ለመኖሩ እርግጠኛ ናችሁ?”

“አዎ ጌታዬ ጠራጊዎቹ ጠዋት ማታ ክፍሉን ሲያፀዱ ያዩታል ።”

“የስልክ ጥሪስ?”

“ምንም ። አሁን ምን እንድናደርግ ትፈልጋላችሁ?”

“በደንብ ተከታተሉት በቅርቡ አንድ እንቅስቃሴ ሳያደርግ አይቀርም ። ስልኩ እስካሁን ተጠልፎ መቆየቱን አረጋግጡ ።”

በሚቀጥለው ቀን የሪዞሊ መኝታ ቤት ስልክ ተደወለ ። ‘ደደብ!’ አለ ለራሱ ሪዞሊ ። በዚህ ቁጥር ሳይሆን በጎረቤት ስልክ እንዲያስጠራው ነበር መልእክት የተወለት ። ጥንቃቄ ማድረግ ነበረበት። ሪዞሊ ስልኩን አነሳ ።

“አቤት?”

“ቶኒ ሪዞሊ ነህ?” ድምጹ የኢቮ ብሩጊ አይደለም ። “ማን ልበል?”

“አንድ ቀን ለሥራ ጉዳይ ቢሮዬ መጥተህ ነበር ሚስተር ሪዞሊ ። አይሆንም ብዬ እንደመለስኩህ አስታውሳለሁ ። ምናልባት ስለጉዳዩ እንደገና ብንወያይ የተሻለ መስሎኛል ።”

ቶኒ ሪዞሊን የደስታ ስሜት ሰውነቱን ወረረው ። ‘ስፒሮስ ላምብሩ! ዲ ቃላው እንደገና ብቅ አለ ማለት ነው’ አለ በልቡ ። እንዲህ ዓይነቱን ጥሩ አጋጣሚ ለማመን አቃተው ። ‘ችግሮቼ ሁሉ ተቃለሉ ። ሄሮይኑንም ቅርሱንም በአንድነት ጭኜ የማወጣበት መንገድ አገኘሁ ።’

“አዎ ፣ ልክ ነህ ። ብንወያይበት እኔም ደስ ይለኛል ። መቼ እንገናኝ?”

“ዛሬ ከሰዓት በኋላ ልትመጣ ትችላለህ?”

በሃሳቡ ‘አሃ ፣ ከእኔ ጋር ለመዋዋል ቸኩሏል ማለት ነው ። ሀብታሞች ሲባሉኮ ሁሉም አንድ ናቸው ። በቃን ብለው አያውቁም’ አለ። “ጥሩ ግን የት?”

“እቢሮዬ ለምን አትመጣም?”

“እመጣለሁ” አለና ቶኒ ሪዞሊ በደስታ ስልኩን ዘጋ ።

በሆቴሉ መተላለፊያ ላይ ተሰፋ የቁረጠ አንድ ሰላይ ቆሞ ወደጠቅ

ላይ መምሪያው ሪፖርት ያስተላልፍ ነበር ። “ለሪዞሊ ስልክ ተደውሎለ ታል ። ሰው ቢሮ ድረስ ሄዶ ሊነጋገር ነው ። ደዋይ ስሙን አልተናገረም። ጥሪው ከየት ቦታ እንደተደረገም ለማወቅ ተቸግረናል ።”

“መልካም ፣ ከሦቱ ከወጣ በኋላ በደንብ ተከታተሉቲና ወዴት እንደሚሄድ አሳውቁኝ ።”

“እሺ ጌታዬ ።”

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ በምድር ቤት በኩል ወጥቶ ከሦቱ በስተጀርባ ወዳለችው ጠባብ መንገድ ገሰገሰ ። ሰዎች ይከታተሉት እንደሆነ ለሚጣራት ሁለት ታክሲ ቀያይሮ ወደ ስፒሮስ ላምብሩ ቢሮ ተጓዘ ።

ስፒሮስ ላምብሩ ሆስፒታል ሄዶ እህቱን ከጠየቃበት ቀን አንስቶ ሊበቀልላት ምሎ ተነስቷል ። ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ የሚገባው ቅጣት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ግን ገና በደንብ አልታየውም ። ጂአርጂአስ ላዲ ቢሮው ድረስ መጥቶ ያነገረውና ከግዳጅ ፒሪል ያሰማው አሸባሪ ዜና የዋርሰውን ጉድጓድ ለመማስ ደህና መሣሪያ እንዳሆነ ላምብሩ ተገንዝቧል ።

የላምብሩ ፀሐፊ “ሚስተር ላምብሩ ሚስተር ኢንቶኒ ሪዞሊ የሚባል ሊያነጋግርህ መጥቷል ። ቀድሞ ቀጠሮ ስላልያዘ ሊያነጋግርህ እንደማይችል ነግሬዋለሁ ።”

“አስገቢው”

“እሺ ጌታዬ ።”

ቶኒ ሪዞሊ በኩራት ደረቱን ነፍቶ ፈገግ እያለ መያቢቋ ሲገባ ስፒሮስ ላምብሩ ዝም ብሎ ይመለከተው ነበር ።

“እንኳን ደህና መጣህ ሚስተር ሪዞሊ ።”

ቶኒ ሪዞሊ ሳቅ አሳ “አመሰግናለሁ ። እና አብረን እንድንሰራ ከሙሳኔ ደርሰሃለህ?”

“አልደረስኩም”

የቶኒ ሪዞሊ ፈገግታ ከሰመ ። “ምን አልክኝ?”

“አይሆንም ነው ያልኩት ። ከአንተ ጋር ለመሥራት ምንም አቅድ የለኝም።”

ቶኒ ሪዞሊ ተገርሞ ትኩር ብሎ አየው ። “ታዲያ ለምንድነው የደወልክልኝ? በድርድር ሃሳብ የምታቀርብስ...”

“እሺ ላቅርብልህ ። በኮንስታንቲን ዴሚሪስ መርከብ ብትጠቀም ምን ይመስልሃል?”

ቶኒ ሪዞሊ መቀመጫው ላይ ደርቆ ቀረ ።

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስ? ስለምንድነው የምታወራው? እኔ በፍጹም...”

“አዎ ይፈቅዳል ። ሚስተር ዴሚሪስ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር እንደሚያደርግልህ ቃል እገባልሃለሁ ።”

“ለምን ምን ሊጠቀም?”

“ምንም”

“ታዲያ የተናገርከው ትርጉም አይሰጥማ ። ዴሚሪስ እንዲህ ዓይነቱን ስምምነት ከእኔ ጋር ለምን ይፈጽማል?”

“ጥሩ ጥያቄ ነው ።” ላምብሩ መነጋገሪያውን ተጭኖ “ቡና አስመጪልን እባክሽ” ካለ በኋላ ወደ ቶኒ ሪዞሊ ዞሮ “ቡናው ምን ዓይነት ይሁንልህ?” ሲል ጠየቀው ።

“ጠቆር ያለ — ግን ያለስኳር ።”

“ለሚስተር ሪዞሊ ጠቆር ብሎ — ያለ ስኳር ”

ፀሐፊዋ ቡናውን አቅርባ ከቢሮው እንደወጣች ላምብሩ “አንድ አጭር ነገር ልንገርህ ሚስተር ሪዞሊ”አለው ።

ቶኒ ሪዞሊ በጉጉት ተመለከተውና ‘እውጣው’ አለ በሀሳቡ ።

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያገባው እህቴን ነው ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ኖኤሌ ፖጂ የምትባል ዕቁባት ይዞ ነበር ።”

“ተዋናይዋ ናት አይደል?”

“አዎ ላሪ ዶግላስ የተባለ ሰው ትወድና ከእርሱ ጋር ትግባባለች ። ባሌን አልፈታም ያለችዋን የዶግላስን ሚስት ገድላችኋል ተብለው ዶግላስና ኖኤሌ ላይ የግድያ ወንጀል ክስ ይመሰረትባቸዋል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ናፖሊዮን ቾታስ የተባለውን ጠበቃ ለኖኤሌ ቀጥሮ ያስቆምላታል ።”

“ስለዚሁ ጉዳይ ጋዜጣ ላይ ማንበቤን አስታውሳለሁ ።”

“በጋዜጦች ያልተጠቀሱ ሌሎችም ነገሮች አሉ ። ይታይህ ፣ ውድ ዋርሳዬ ይህቺ እምነት ያጉደለችበትን ዕቁባቱን ለማትረፍ አልነበረም

ጥረቱ ፤ ሊበቀላት እንጂ ። ናፖሊዮን ቾታስን ለይምሰል ያቆመላት ወንጀለኛ መሆኗ እንዲረጋገጥባት ለማድረግ እንዲችል ነበር ። ችሎቱ ሊጠናቀቅ ትንሽ ጊዜ ሲቀረው ከዳኞቹ ጋር ስለተነጋገርኩላችሁ ጥፋታች ሁሉ እመኑ ብሎ ለተከሳሾቹ ይናገራል ። ለካ ውሸቱን ነበር ፤ ተከሳሾቹ ጥፋታቸውን ሲያምኑ የሞት ቅጣት ተፈጸመባቸው ።”

“ምናልባት ቾታስ ያሰበው...”

“እባክህ ልጨርስልህ ። የካተሪን ዶግላስ ሬሳ አልተገኘም ሚስተር ሪዞሊ ። ሬሳዋ ያልተገኘበት ምክንያት ሴትዮዋ በሕይወት ስለምትገኝ ነው። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደብቆአታል ።”

ቶኒ ሪዞሊ አውን ትኩር ብሎ አየው ። “ቆየኝ እስቲ ፤ ዴሚሪስ ሴትዮዋ በሕይወት መኖሯን እያወቀ ገዳዮቿ ዕቁባቱና ወዳጅዋ ላሪ ዶግላስ ናቸው አሰኝቶ አስረሽናቸው ነው የምትለኝ?”

“ትክክል ። የወንጀለኛ መቅጫው እንቀጽ ምን እንደሚያስበይን ባላውቅም እውነቱ ከወጣ ዋርሳዬ ለብዙ ዓመት ወህኒ ውስጥ እንደሚማቅቅ እርግጠኛ ነኝ ። ቢያንስ ቢያንስ ስሙ ይጠፋል ፤ ቅስሙ ይሰበራል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ቁጭ እንዳለ የሰማውን ነገር በጥልቀት ማሰላሰል ቀጠለ ። ግን ግራ የገባው ነገር አለ። “ሚስተር ላምብሩ ፤ ይህን ሁሉ ለምንድነው የምትነግረኝ?”

ስፒሮስ ላምብሩ ፈገግ አለ ። “ምክንያቱም የዋርሳዬ ውለታ ስላለብኝ ሄደህ እንድታገኘው ብዬ ነው ። መርከቡን ብትገለገልበት ደስ ይለዋል የሚል ግምት አድሮብኛል ።”

ምዕራፍ አሥራ አራት

ሊቆጣጠረው በማይችለው የአሳብ ማዕበል ተውጧል ። ይኸንኑ በውስጠ አእምሮው ሥሩን ተክሎ የሚያስጨንቀውን ነገር ለመርሳት አልቻለም ። የጀመረው ከአንድ ዓመት በፊት በኖኤሌ ፓጂ ላይ የበቀል ርምጃ በወሰደበት ጊዜ ነው ። በዚያም ያበቃለት መስሎት ነበር ። ኃላፊው ጊዜ ሞቶ እንደተቀበረ አድርጐ ቆጥሮታል ። ካተሪን አሌክሳንደር በድንገት እንደገና ወደሕይወቱ ተመልሳ እስከመጣች ድረስ ሥጋት የሚባል ነገር ተሰምቶት አያውቅም ነበር ። ይህ ጉዳይ ፍሬዴሪክ ስታቭሮስንና ናፖሊዮን ቾታስን እንዲያጠፋቸው አስገድዶታል ። አደገኛ በሆነ መንገድ ሊጫወቱበት ተነስተው በመጨረሻ እርሱ ረትቷቸዋል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ያስደነቀው ነገር ቢኖር ሊደርስበት ከሚችለው መዘዝ አንፃር ያንን ሁሉ ደፍሮ መፈጸሙ ነው ። የንግድ ሥራ በጣም ደስ ያሰኛል ፤ ሆኖም ከሕይወትና ከሞት ግብግብ ጋር ሲወዳደር ምኑም ከእነኚህ አይጠጋም ። ‘እኔኮ ነፍሰ ገዳይ ነኝ’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ‘እይ፣ ገዳይ አይደለሁም ግን አስገዳይ ነኝ ።’ በዚህ ተግባሩ ከማዘንና ከመፀፀት ይልቅ መኩራራት ጀመረ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስለካተሪን አሌክሳንደር እንቅስቃሴ በየሳምንቱ ዘገባ ይደርሰዋል ። እስካሁን ድረስ ሁሉም ነገር እርሱ በሚፈልገው አኳኋን እየተካሄደ ነው ። ከሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት አብሯት ከሚሰሩት ሰዎች ጋር ብቻ ተወስኗል ። እንደኤቬሊን አገላለጽ ካተሪን አንዳንዴ ከኪርክ ሬኖልድስ ጋር ትወጣለች ። ሆኖም ሬኖልድስ የዴሚሪስ ተቀጣሪ በመሆኑ ምንም ችግር ሊያስከትል አይችልም ። ‘ምስኪን ልጅ ፤ ተስፋ የቆረጠች ይመስለኛል’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ሪኖልድስም ቢሆን አሰልቺ ነው ። ስለ ሕግ ካልሆነ በቀር ሌላ ማውራት አይችልም ። እንዲህ መሆኑ ደግሞ ለሱ ጥሩ ነው ። ብቸኝነት በካተሪን ላይ መጠናከሩ ለሱ ያመቸዋል ። ‘ለዚህ ሪኖልድስን ማመስገን ይገባኛል’ አለ ዴሚሪስ ።

ካተሪን ከኪርክ ሪኖልድስ ጋር ቶሎ ቶሎ መገናኘት ጀመረች ።

ስሜታ የበለጠ ወደእርሱ እየተሳበ መጣ ። ሰውዬው መልከ መልካም ባይሆንም ሴቶችን የሚስብ ቁመና አለው ። 'የወንዶችን የውበት ልክ የተማርኩት ከላሪ ነው' ትላለች ካተሪን ለእራሷ በሐፍረት ። አባባሏ ትክክል ነው ። ውበት እንደባለቤቱ አመለካከት ነው ። ኪርክ ሪናልድስ አርቆ አሳቢና እምነት የሚጣልበት ነው ። 'ልተማመንበት የሚገባኝ ሰው ነው' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'የሚያንገበግብ ፍቅር የለኝም ። ሁለተኛም የሚኖረኝ አይመስለኝም ። ላሪ አሚጦ ወስዶታል ። አንድ ቀን ከተራራ ጫፍ ቁልቁል ወርውሮኝ በጨለማ ዋሻ ውስጥ ይጥለኛል ብዬ የማልሰጋበትን ፣ የማከብረውና የሚያከብረኝን ፣ ጥሩ አስደሳች ሕይወትን የሚያጋራውን ሰው መርጫ ለመጠጋት አሁን በቂ ብስለት አለኝ ።'

በክሪስቶፈር ፍራይ የተደረሰውን "ዘሌዲ ኢዝ ኖት ፎር በርኒን ግ"ንና "የገርትሩድ ሉሬንስን" ሰዮቴምበር ታይድ" የተባሉ ድራማዎችን ለመመልከት በተለያዩ ቀናት ወደትያትር ሄዱ ። በዳንስ ክበቦችም ተደሰቱ ። የክበቡ ኦርኬስትራ "ዘ ሰርድ ማን" እና "ላ ቪኤ ኤን ሮስ" የተሰኙ ሙዚቃዎችን አከታትሎ የሚጫወት ይመስላል ።

"በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ቅዱስ ሞሪዝ ልሄድ ነው ።" አላት ኪርክ ሮናልድስ ካተሪንን ። "አንቺስ አስበሽበታል?"

ካተሪን በሚገባ አስባበታለች ። ኪርክ ሪናልድስ በፍቅሯ እንደተያዘ አውቃለች ። 'እኔምኮ እወደዋለሁ' አለች ካተሪን በሃሳቧ ። 'ግን መውደድና ማፍቀር የተለያዩ ነገሮች ናቸው አይደል? ነው ወይንስ እኔ ስለፍቅር የማይገባኝ ደደብ ሆኛለሁ? የምፈልገው ምንድን ነው – ሌላ ላሪ? ልቤን እየበላ ሌላ ሴት እኔ ላይ የሚወድና ሊገድሉኝ የሚሞክር? ኪርክ ሪናልድስ ጥሩ ባል ሊሆን የሚችል ይመስለኛል ። ታዲያ የማመነታው ለምንድነው?'

ያን ዕለት ማታ ካተሪንና ኪርክ በማርቤል ሆቴል እራታቸውን በሉ። ከዋናው ምግብ በኋላ ተከታዩ ሲቀርብላቸው ኪርክ "ካተሪን ምናልባት ካላወቅሽው ከአንቺ ፍቅር ይዞኛል ። ላገባሽም እፈልጋለሁ" አላት ።

ደነገጠች ። "ኪርክ…" ምን ለማለት እንደፈለገች አላወቀችም ። የምሰጠው መልስ አለች ካተሪን በአሳቧ። 'ሕይወቴን ሊለውጥ የሚችል ነው። እሺ የሚል መልስ መስጠት ቀላል እየሆነ ሳለ ይህንኑ ከመናገር ያገደኝ ምንድን ነው? ሕይወቴን በሙሉ ፈሪ ሆኜ ልቀር ነው? ይህን መጥፎ ባሕሪዬን ዝም ብዬ መመልከት የለብኝም።'

"ካቲ"

"ኪርክ – ወደቅዱስ ሞሪዝ ለምን አብረን እንሄድም?"

የኪርክ ፊት ሲፈካ ታየ ። " ይህ ማለትሽ …?"

"እስቲ እናያለን ። የበረዶ ሸርተቴ ስጫወት ካየኸኝ የምታገባኝ አይመስለኝም ።"

ኪርክ ሳቀ ። "በዚህ ዓለም ላይ አንቺን ከማግባት ሊያግደኝ የሚችል ምንም ነገር አይኖርም ። ደስተኛ አንድሆን አድርገሽኛል ። ወደዚያ የምንሄደው ኖቬምበር 5 ቀን ነው ። ዕለቱም የጋይ ፋውኪ ቀን ነው ።"

"የጋይ ፋውኪ ቀን ማለት ምንድን ነው?"

"በጣም ደስ የሚያሰኝ ታሪክ አለው ። ንጉሥ ጄምስ ፀረ ካቶሊኮች የሆነ ጥብቅ ፖሊሲ ይከተል ነበር ። እና የታወቁ የሮማን ካቶሊክ እምነት ተከታዮች የእርሱን መንግሥት ለመገልበጥ ሴራ ጠነሰሱ ። ጋይ ፋውኪ የተሰኘውን ወታደር ከስፓኝ አስመጥተው ሴራውን እንዲመራ አደረጉ ። እርሱም አንድ ቶን የሚመዝን ባሩድ በሰላሳ ስድስት በርሜሎች ውስጥ ከትቶ ከብሪታንያ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ውስጥ እንዲደበቅ አደረገ ። ሴረኞቹ የመወሰኛ ምክር ቤቱን ለማፈንዳት በተዘጋጁበት ዕለት ግለጻ አንዱ ከመካከላቸው ከድቶ ምስጢሩን ሹክ አለና ሁሉም ተለቀሙ ። ጋይ ፋውኪ ላይ ከፍተኛ የድብደባ ስቃይ ቢደርስበትም ምስጢሩንም አላወጣም አለ ። የተያዙት ሁሉም ተረሸኑ ። ይህ ቀን በእንግሊዝ ውስጥ በየዓመቱ በጥቂት ሰዎች /ታስቦ ይውላል ።"

ካተሪን ጭንቅላቷን አወዛወዘችና "እንዴት ያለ የጨረገገ ቀን ነው" አለች ። ፈገግ አለና "የወደፊት ሕይወታችን ግን የጨረገገ እንደማይሆን ቃል እገባልሻለሁ" አላት ።

ወደተባለው ሥፍራ እንደነገ ሊሄዱ ማታውኑ ካተሪን ፀጉሯን ታጠበች ። ሻንጣዋን ሁለቴ እያሰረች ፈታታች ። ወደር የሌለው ደስታ

ተሰማት ። ከዚህ በፊት ያጋጠሟት የልብ ወዳጆቿ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው ። ዊሊያም ፍሬዘርና ባሏ ። 'እሁንም የልብ ወዳጅ የሚለው ቃል ይታወቅ ይሆን?' አለች ካተሪን በአሳቢ ። 'አይ አምላኬ ሳስታውሰው ልክ ብስክሌት እንደመፈናጠጥ እቆጥረዋለሁ ። አንዴ ከተለመደ ጨርሶ አይረሳም ይላሉ ። ምናልባት ከእኔ ጋር ሲተኛ አይደሰት ይሆን? እኔስ በግብረሥጋ ግንኙነት አልረካ ይሆን? ኤሞ መጨነቋን ትቼ ብተኛ የሚሻል ይመስለኛል' አለች ።

''ሚስተር ዴሚሪስ?''

''አቤት''

''ካተሪን አሌክሳንደር ዛሬ ጠዋት ወደቅዱስ ሞሪዝ ሄዳለች።''

ከትንሽ ፀጥታ በኋላ ''ወደቅዱስ ሞሪዝ?''

''አዎ ጌታዬ ።''

''ብቻዋን ናት?''

''አይደለም ጌታዬ ፣ ከኪርክ ሪኖልድስ ጋር ናት ።''

ረዘም ያለ ፀጥታ ሰፈነ ።

''አመሰግናለሁ ኤቬሊን ።''

'ከኪርክ ሪኖልድስ ጋር! ፍጹም ሊሆን አይችልም ። ከእርሱ ምን ልታገኝ! ብዙ ጊዜ ሰጠኋት ። መፍጠን ነበረብኝ ። አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል ። ዝም ብዬ ላያት ...' አለ በሐሳቡ ። ፀሐፊው የውስጥ ኢንተርኮም ደወል አሰማች ።

''ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ሚስተር ቶኒ ሪዞሊ የሚባል ሊያነጋግርህ መጥቶ እዚህ ይገኛል ። ቀጠሮ የሌለው ሲሆን...''

''ታዲያ ለምን ታስቸግሪኛለሽ!'' አለና ዴሚሪስ የመነጋገሪያውን እጀታ መልሶ አስቀመጠ ።

መነጋገሪያው እንደገና ጠራ ። ''ስለረበሽኩህ ይቅርታ ፣ ሚስተር ሪዞሊ ከሚስተር ላምብሩ መልእክት ይዤ ነው የመጣሁት ፣ በጣም ከፍተኛ ለሆነ ጉዳይ ነው ይላል።''

መልእክት! ነገሩ እንግዳ ሆነበት ። ዋርሳው እራሱ ለምን መልዕክቱን ይዞለት አልመጣም! ''በይ አስገቢው ።''

''እሺ ጌታዬ''

ቶኒ ሪዞሊ ወደኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቢሮ ገባ ። ውስጡን በአድናቆት እያየ የስፒሮስ ላምብሩ ቢሮ ከዚህ ይበልጥ እንደሚያምር ተገነዘበ ።

''አንተን በማግኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል ።''

''ሁለት ደቂቃ ብቻ እሰጥሀለሁ ።''

''ካንተ ጋር ብወያይ ይሻላል ብሎ ነው ስፒሮስ የላከኝ ።''

''በእውነት! ስለምን ይሆን የምንወያየው!''

''ብቀመጥ ቅር ይልሃል!''

''ግን ብዙ ለመቆየት የምትችል አይመስለኝም ።''

ቶኒ ሪዞሊ ፊቱን ወደዴሚሪስ እዙሮ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። ''አንድ ትልቅ ፋብሪካ አለኝ ሚስተር ዴሚሪስ ። ወደተለያዩ የዓለም ክፍላትም ዕቃዎች አንጉዛለሁ ።''

''ገባኝ ስለዚህ እንዱን መርከቤን ለመከራየት ትፈልጋለህ ማለት ነው!''

''በትክክል!''

''ታዲያ ስፒሮስ ለምን ወደእኔ ላከህ! የእርሱን መርከብ ለምን አትከራይም ነበር! በአሁኑ ጊዜ እንኳ ሥራ ፈትተው የቆሙ ሁለት መርከቦች አሉት ።''

ቶኒ ሪዞሊ ትከሻውን ነቀነቀ ። ''ይመስለኛል እኔ የምጭነውን ነገር እርሱ አልወደደውም ።''

''አልገባኝም ፣ ለመሆኑ አንተ ለመጫን የፈለግከው ምንድን ነው!''

''አደንዛዥ ዕፆች'' ሲል ቶኒ ሪዞሊ አፍርጦ ነገረው ። ''ሂሮይን።''

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ዓይኑን ማመን አቅቶት ትኩር ብሎ ሪዞሊን ይመለከተው ነበር ። ''እና እኔ...! ፖሊስ ከመጥራቴ በፊት ከዚህ ውጣልኝ ።''

ሪዞሊ በአገጩ ወደስልኩ አመለከተና ''በል ቶሎ ደውል'' አለው ።

ዴሚሪስ ስልኩን ሊያነሳ ሲል ፣ ''እኔም ላነጋግራቸው እፈልጋለሁ። ስለዚያ ስለኖኤሌ ፓጀና ስለላሪ ዶግላስ የወንጀል ክስ ሁኔታ ላስረዳቸው እሻለሁ ።''

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በድንጋጤ የበረዶ ያህል ቀዘቀዘ ። ''ምንድ ነው የምታወራው!''

“በአሁኑ ወቅት በሕይወቷ የምትገኘዋን ሴት ገድለዋል ተብለው ስለተረሸኑት ሰዎች ነው የማወራው ።”

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፊት ገረጣ ።

“ምናልባት ፖሊሶች ያንን ታሪክ ለመስማት ፍላጎት አይኖራቸው ይሆን? ካልፈለጉት ደግሞ የዜና አገልግሎት ድርጅቶች በደስታ ይቀበሉታል ። አይመስልህም? ጋዜጣው ላይ የሚጻፈው የዜና ርዕስ እንኳ ከወዲሁ በዓይነ ኅሊናዬ ይታየኛል ። ላንተስ? ኮስታ ብዬ ብጠራህ ቅር ትሰኛለህ? ስፒሮስ ጓደኞችህ ሁሉ ኮስታ ብለው እንደሚጠሩህ ነግሮኛል። እኔና አንተም እንግዲህ ጥሩ ጓደኛሞች የምንሆን ይመስለኛል ። ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? ጥሩ ጓደኛሞች ዞር ብለው አያዘነጣጠሉምና ነው ። የምናውቃት ምስጢርም እንዳትወጣ በመካከላችን ደብቀን እንይዛታለን። አይመስልህም?”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እተቀመጠበት ደርቆ ቀረ ። ሲናገር ድምጹ ይንቀጠቀጥ ነበር ። “የምትፈልገው ምንድን ነው?”

“ነገርኩህኮ ከመርከቦችህ አንዱን ለመኮናተር እፈልጋለሁ ። በእኔና በአንተ መካከል እንዲህ ዓይነት ወዳጅነት እያለ ለኮንትራቱ ምንም ክፍያ የምትጠይቀኝ አይመስለኝም ። ስምምነቱን የማይከፈልበት ውለታ ብለን ልንሰይመው እንችላለን ።”

ዴሚሪስ በኃይል ወደውስጥ አየር ሳበ ። “ይህን እንድታደርግ በፍጹም አልፈቅድልህም ። በአንደኛው መርከቤ ላይ አደንዛዥ ዕፆች ማስመጣቴ ከታወቀ መርከቦቼ ሁሉ ይወረሳሉ ።”

“እንዴት ተደርጎ? ምስጢሩ ሊወጣ አይችልም ። እኔ በማስታወቂያ አላስነግርም ። በምስጢር ነው የማከናውነው ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አመረረ ። “ትልቅ ስሕተት እየሠራህ ነው ። እኔን ልታስፈራራኝ አትችልም ። ማን እንደሆንኩ አታውቅም?”

“አውቃለሁ ። አዲሱ ሽሪኬ ነህ ። ኮስቲቲ ። እኔና አንተ ገና ለረዥም ጊዜ አብረን ልንሠራ ነው ። እምቢ ካልክ በቀጥታ ወደፖሊስና ወደጋዜጦች ሄጄ የማውቀውን ምስጢር ልዘከዝክብህ ነው ። ያኔ ስምህም ዝናህም ንብረትህም አፈር ድቤ ይገባል ።”

ለረዥም ጊዜ የቆየ አንቃራጭ ሰላም ሰፈነ ።

“ዋርሳዬ ሚስጢሩን እንዴት አወቀ?”

ሪዞሊ ሳቀ ። “ብነግርህ ምን ሊጠቅምህ? ዋናው ነገር እኔ ምስጢሩን ማወቄ ነው ። እንደፊኛ ጫን ያልኩህ ዕለት መፈንዳትህን አትጠራጠር ። ተግዘህ ወህኒ ትወርድና በቀረው የሕይወት ዘመንህ ሶፕራኖን ስትዘምር ትከርማለህ ።” ቶኒ ሪዞሊ ሰዓቱን ተመለከተ ። “በእሳችሁ! የተሰጠኝም የሁለት ደቂቃ ጊዜ ተፈጽሟል ።” አለና ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመ ። “በሽሪክነታችን መስማማትህን ፣ አለበለዚያም መቃወምህን ሰምቼ ከዚህ ክፍል ለመውጣት የስድሳ ሴኮንድ የማሰቢያ ጊዜ ልስጥህ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አሁን ካለው ዕድሜ አሥር ዓመት ከመቅፅበት ጨምሮ ያረጀ መሰለ ። ፊቱም ገረጣ ። ምስጢሩ ቢወጣ ምንም አልሆንም የሚል ቅዠት አይነካካውም ። የዜና ማሰራጫዎች ነፍሱ ሳትወጣ ነው ቆረጣጥመው የሚውጡት ፣ ጭራቅና ነፍሰ ገዳይ አድርገው ነው የሚስሉት ። የስታቭሮስና የቾታስን አሟሟትም እንደገና እንዲመረመር ያደርጉ ይሆናል ።

“የተሰጠህ ስልሳ ሴኮንድ አብቅቷል ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ።

“እሺ ይሁን!” አለ በሹክሹክታ ። “እሺ ብያለሁ ።”

ቶኒ ሪዞሊ ፈገግ ብሎ አየውና “ብልጥ ነህ” አለው ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስም ቀስ ብሎ ከተቀመጠበት ተነሳ ። “ይህኛውን ጭነት እንድታሻግር እፈቅድልሃለሁ” አለው ። “መቼና እንዴት እንደምትጭነው ለማወቅ አልሻም ። ከሰዎችህ አንዱ ከዕቃው ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል ። እስከዚህ ነው ማድረግ የምችለው ።”

“በቃ ተስማማን” አለ ቶኒ ሪዞሊ ። በአሳቡም ‘ያን ያህል ብልጥ አይደለህም ። እንዴ ሄሮይኑን ከጫንክልኝ አከተመልህ ፣ በመንጠቆዬ ተሰነግህ ማለት ነው ። ማሙሽ ኮስታ ። ከእንግዲህ በምንም ዓይነት አልለቅህም ።’ አለ ። ከሀሳቡ ወጥቶ ሪዞሊ ድምጹን ከፍ አደረገና “በእርግጥ ተስማምተናል” ሲል ተናገረ ።

ቶኒ ሪዞሊ እየፈነጠዘ ወደሆቴሉ ተመለሰ ። ‘ሎተሪ ። ፖሊሶች እንደሆነ የኮንስታንቲን ዴሚሪስን መርከብ ንክችም አያደርጉ ። የክርስቶስ ያለህ! ከአሁን በኋላ ሄሮይኔን እንደልቤ በየጊዜው ከግሪክ ወደቦች በሚነሱት መርከቦች ለመጫን እችላለሁ ። ገንዘብ መዛቅ ነው ፤ ሂሮይንና

ቅርሳቅርስ እያሻገሩ ።’ ቅርሳ ቅርስ ሲል ያሰበው መልሶ ካንጀቱ አሳቀው። ‘ቪክቶር አሳዛኝ ነህ! ግን ይቅርታ ።’

ሪዞሊ በስታዴኦ ጎዳና ወደሚገኘው የሕዝብ ስልክ ሄደና ሁለት ጥሪዎችን አደረገ ። የመጀመሪያው ጥሪ ወደ ፓሌርሞ ነው ። ፔቱ ሉካ ወዳለበት ።

“ሁለቱን ሽምቅ ዝንጀሮችህን ወደጫካ መልሰህ ከሌሎች አራዊት አደባልቃቸው ። ዕቃው ሊጓጓዝ ነው ። በመርከብ ነው የሚጫነው ።”

“ዕቃው በደህና ይዞታ ላይ እንደሚገኝ እርግጠኛ ነህ?”

ሪዞሊ ሳቀ ። “በእንግሊዝ ከሚገኘው ባንክ የበለጠ በደህና ይዞታ ላይ ይገኛል ። ስንገናኝ ስለሁኔታው አጫውትሀለሁ ። ብዙ ጥሩ ጥሩ ዜናዎችም ይዤልሀለሁ ። ከእንግዲህ ዕቃውን በየሳምንቱ ለማጓጓዝ የምንችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል ።”

“ያ እጅግ በጣም ጥሩ ነው ቶኒ ። እኔኮ ሁሌ በአንተ እተማመና ለሁ ።”

በልቡ ደግሞ ‘አንተ ዲቃላ ገደል ግባ!’ አለ ።

ሁለተኛው ጥሪ የተደረገው ለስፒሮስ ላምብሩ ነበር ። “በጣም ተሳክቷል ዋርሳህና እኔ ሽርክና ጀምረናል ።”

“እንኳን ደስ አለህ ፣ ይህን በመስማቴ በጣም ደስ ብሎኛል ሚስተር ሪዞሊ ።” ስፒሮስ ላምብሩ ስልኩን እንደዘጋ የአደንዛዥ ዕፅ ልዩ የሽምቅ ቡድንም ሊኖር ይችላል ሲል አሰበ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እኩለ ሌሊት እስኪያልፍ ድረስ እቢሮው ውስጥ እንደተቀመጠ አዲስ በገጠመው ችግር ልቡ ይቃጠላል ። በአንድ ወቅት ኖኤሌ ፓጂን ተበቅሏት ነበር ። አሁን ከመቃብር ወጥታ እያሳደደችው ነው ። የጠረጴዛውን መሳቢያ ከፈተና በፍሬም ውስጥ የተቀመጠውን የኖኤሌ ፓጂን ፎቶግራፍ ሰቦ አወጣ ። ‘እንዴት ነሽ አንች ውሻ!’ አለ በልቡ ። እግዜር በሚያውቀው በወም ቆንጆ ናት ። ‘አሁን እኔን የምታጠፊ ይመስልሻል? መልካም ፣ እናያለና! እስቲ ይሁን ።’

ምዕራፍ አሥራ አምስት

ቅዱስ ሞሪዝ ጥሩ የመደሰቻ ሥፍራ ነው ። ረዘም ባለው ተራራ ላይ የሽርተቱ መጫወቻ የበረዶ ክምር ፣ የእግር ጉዞ ማድረጊያ መንገድ ፣ የመንሸራሸሪያ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ፣ የበረዶ ላይ ጋሪዎች ፣ የፈረስ ግና ጨዋታ እና ሌሎችም በርካታ መዝናኛዎች ይገኛሉ ። ከአልፐስ ተራራ በስተደቡባዊ በኩል በስድስት ሺህ ጫማ ከፍታ አብረቅራቂዋን ሐይቅና የኢንጋዲን ሸለቆ ከቦ በሁለት ወገን ደግሞ በሴሌሪናና በፒዝኔ ኢር መካከል ሆና ያለችውን መንደር ካተሪን ስትመለከት በጣም አድርጋ ተደሰተች ።

ካተሪንና ኪርክ ሪኖልድስ ወደጥንታዊው የፓላስ ሆቴል ተጓዙ ። የሆቴሉ በረንዳዎችና መተላለፊያዎች ከተለያዩ አገሮች በመጡ ጉብኚ ዎች ተጣበዋል ።

ኪርክ ሪኖልድስ አስተናጋጅዋን “ለሚስተርና ለሚስስ ሪኖልድስ እዚህ አልጋ ተይዞ ነበር” ሲላት ካተሪን ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞረች ። ‘የጋብቻ ቀለበት ጣቱ ላይ ማድረግ ነበረብኝ’ አለች በልቧ ። በአካባቢው ያሉ ሰዎች ወደ እርሷ አይተው ምን እንደምታደርግ ያወቁባት መሰላት ።

“አዎ ሚስተር ሪኖልድስ ፣ የክፍል ቁጥራችሁ 215 ነው ።” አስተናጋጅዋ ለተላላኪው ቁልፍ ሰጠችው ። ተላላኪውም “እባክዎ ፣ በዚህ በኩል ይምጡ” አለና ወደክፍላቸው መራቸው ።

ቀለል ያሉ መቀመጫዎችና የመኝታ ቤት ዕቃዎች ወደሚገኙበት ውብ ቤት ተወሰዱ ። በመኝታ ቤቱ መስኮት በኩል ተራራዎቹ በደንብ ይታያሉ ።

ተላላኪው ከወጣ በኋላ ኪርክ ሪኖልድስ ካተሪንን እቅፍ አደረጋትና “ፍቅሬ ፣ ምን ያህል ደስተኛ እንዳደረግሽኝ ልገልጽልሽ አልችልም” አላት ።

“የበለጠ እንደማስደስትህ ተስፋ አለኝ” አለችው ካተሪን ። “እኔ … ብዙ ጊዜኮ አለፈኝ ኪርክ ።”

“አታስቢ ቀስ ብሎ ነው አላስቸኩልሽም ።”

‘በጣምኮ የሚወደድ ሰው ነው’ አለች ካተሪን በልቧ ። ‘ግን ስላለፈው ታሪኬ ባጫውተው ምን ይሰማው ይሆን?’ ስለላሪ ዶግላስ ፡ እንዲሁም ስለግድያ ወንጀሉ ክስ ወይም ከዚህ በፊት በሕይወቷ ውስጥ ስላጋጠሟት አደገኛ ነገሮች አንስታለት አታውቅም ። የበለጠ ልትቀርበው ና አካሉም ለመሆን ፈልጋለች ። ግን የማታውቀው ነገር ደግሞ አግዷታል ።

“ልብሶቻችንን ከሻንጣው ባወጣ ይሻላል” አለች ካተሪን ።

ቀስ እያለች በጣም በቀስታ ልብሶቹን ከሻንጣ እየመዘዘች ወዲያው አንድ ነገር ተገነዘበች ። ልብሶቹን ቶሎ ቶሎ እንዳታወጣ የሚያደርጋት ቀጥሎ የሚመጣውን ጉዳይ በመፍራቷ መሆኑን ተረዳች ።

ከሌላው ክፍል ሆኖ ኪርክ ይጣራ ነበር ። “ካተሪን … ”

‘አቤት አምላኬ ! ልብሳችንን እናውልቅና እንተኛ ሊለኝኮ ነው ’ አለች በልቧ ። ካተሪን ምራቋን ዋጥ አደረገችና በቀስታ ድምፅ “አቤት?” ብላ መለሰች ።

“ወጣ ብለን ለምን አካባቢውን አንጐበኝም?”

የካተሪን ጭንቀት ተቃለለላት ። “በጣም ጥሩ አሳብ ነው” አለች ። ‘ግን ምን ነክቶኛል? በዓለም ውስጥ ከሚገኙ አስደሳች ሥፍራዎች በአንደኛው አካባቢ በጣም ከሚወደኝና ደስ የሚል ሰው ጋር እገኛለሁ ። ለምን ይሆን የተረበሽኩት?’ አለች በአሳቧ ።

ሪኖልድስ ሁለ ነገሯ እንግዳ ሆኖበት “ለመሆኑ ደህና ነሽ?” ሲል ጠየቃት ።

“ደህና” አለች ካተሪን በፈገግታ ። “በጣም ደህና ነኝ ።”

“የተጨነቅሽ ትመስያለሽ ።”

“አይ ፡ እኔ … እኔ የማስበው ስለ — ስለበረዶ ላይ ሽርተቱ ነበር አደገኛ ይመስላል ።”

ሪኖልድስ ፈገግ አለ ። “አታስቢ ነገ ፡ በጣም በማያንሸራትተው በረዶ ላይ እንድትጀምሪ እናደርጋለን ። በጅ አሁን እንሂድ ።”

ሽሚዝ ለብሰው ከላይ ስስ ጃኬት ደረቡና ንውሁን አየር እየተነፈሱ ጉዟቸውን ቀጠሉ ።

ካተሪን በኃይል አየር ሳበች ። “አቤት በጣም ደስ ይላል ኪርክ ። ይህን ሥፍራ ከልቤ ወድጀዋለሁ ።”

“ገና ምኑን አይተሽ !” አለና ሳቀ ። “በበጋ ጊዜማ ከዚህ ይበልጥ በጣም ውብ ሥፍራ ይሆናል ።”

‘በጋ ሲመጣም ከእኔ ጋር ለመሆን ይፈልግ ይሆን?’ አለች በልቧ ። ወይንስ አስጠላዋለሁ? ምን ነካኝ ። መጨነቄን ብተው አይሻልም?’

የቅዱስ ሞሪዝ መንደር ማራኪ ቦታ ናት ። በሥፍራዋ ብዙ የተለያየ የዕቃ መደብሮችና ምግብ ቤቶች ከመኖራቸውም በላይ በተለይ በትልቁ የአልፕስ ተራራ አካባቢ የሚገኙት የስዊስ ቤቶች ከሩቅ ዓይንን የሚስቡ ናቸው ።

በየሱቁ ሲዘዋወሩ ካተሪን ለኤቪሊንና ለዊም የሚበረከቱ የስጦታ ዕቃዎችን ሸመተች ። ወደአንድ አነስተኛ ቡና ቤት ገቡና ወይን የገባበት አይብ በዳቦ ተመገቡ ።

ከሰዓት በኋላ ኪርክ በዳማ ፈረስ የሚጐተት የበረዶ ላይ ጋሪ ተከራይና ተጐትተው ወደ ጋራው ወጡ ።

“ደስ አይልም?” ብሎ ጠየቃት ሪኖልድስ ።

“በጣም እንጂ” ብላ ወደእርሱ ተመለከተችና እንዲህ ብላ አሰበች ። ‘ዛሬ ማታ በደንብ ላስደስትህ ነው ። እም ዛሬ ማታ ፡ ዛሬ ማታ ጥሩ አድርጌ አስደስተዋለሁ ።’

ያን ዕለት ምሽት በሆቴላቸው ውስጥ በሚገኘው ስቱቢሲ በተሰኘው ጥንታዊ ምግብ ቤት ውስጥ እራታቸውን በሉ ።

“ይህ ክፍልኮ የተሠራው በ1480 ዓ·ም ነው” አላት ኪርክ ።

“ታዲያ ምግቡን ባናዝ ይሻላላ !”

“ምን ?”

“ይቅርታ መቀለዴ ነው ።”

‘ላሪኮ ቀልዴ ወዲያው ይገባው ነበር ። ግን ስለእርሱ ምን አሳስበኝ? ስለዛሬ ማታው ለማሰብ ባለመፈለጌ ነው? ሜሪ አንቶኔት ሊገድሏት ስትወሰድ የነበራትን ስሜት ዓይነት ነው የሚሰማኝ ። ከእራት በኋላም ኬክ አልበላም’ አለች በሀሳቧ ።

ምግቡ በጣም ቆንጆ ቢሆንም ካተሪን በመረበሿ ደስ አልተሰኘችበትም ። በልተው ከጨረሱ በኋላ ሪኖልድስ እንዲህ አላት ፡— “ወደፎቅ

እንውጣ? ነገ ጠዋት በማለዳ የበረዶ ላይ ሸርተቴ እንዲያስተምሩሽ ተነጋግሬአለሁ ።”

“ጥሩ ነው ። እሺ”

ፎቁን መውጣት ሲጀምሩ የካተሪን የልብ ትርታ በኃይል ጨመረ ። ‘አሁን በቀጥታ ወደ አልጋ እንሂድ ሊለኝ ነው ። ታዲያ ለምን አይልም? እዚህ የመጣሁት ለዚሁ አይደል? የበረዶ ላይ ሸርተቴ ልጫወት ነው የመጣሁት ብዬ እራሴን አላታልልም’ አለች በአሳቧ ።

ከከፍላቸው እንደደረሱ ሪኖልድስ በሩን ከፍቶ መብራቱን አበራ ። እንደገቡ ካተሪን ሰፊውን አልጋ ትኩር ብላ አየችው ። ክፍሉን ሊሞላው ትንሽ ነው የቀረው ።

ኪርክ ዝም ብሎ ያያት ነበር ። “ካተሪን … የተጨነቅሽበት ነገር አለ?”

“ምን?” አለችና ሳቀች ። “በጭራሽ የለም ። እኔ … እኔ እንዲሁ …”

“እንዲሁ ምን ?”

ብሩህ ፈገግታ አሳየችው ። “ምንም ፣ ደህና ነኝ ።”

“በያ ልብሳችንን አወላልቀን እንተኛ ።”

“አስቀድሜ የገመትኩትን ነው የተናገረው ። ግን መናገር ነበረበት? ዝም ብለን ማድረግ አንችልም ነበር? እንዲህ እናድርግ ብሎ መናገሩ … ያስጠላል ።”

“ምን አልሺኝ?”

ካተሪን ድምጿን ከፍ አድርጋ መናገሯን አላወቀችም ነበር ። “ምንም ።”

ካተሪን ወደአልጋው ጠጋ አለች ። እስካሁን ካየቻቸው አልጋዎች ትልቁና ሰፊው ነው ። ለሚዋደዱ ፍቅረኞች የተሠራ አልጋ ይመስላል ። በጣም ለሚፋቀሩት ብቻ የተዘጋጀ ። የሚተኛበት አልጋ ሳይሆን የ …”

“የኔ ፍቅር ፣ ልብስሽን አታወልቂም?”

‘ማውለቅ አለብኝ? ከወንድ ጋር ከተኛሁ ስንት ጊዜ ሆነኝ? ከዓመት በላይ ። ያው ከባሌ ጋር’ ስትል አሰበች ።

“ካቲ …. ?”

“አቤት !” ‘ላወልቅ ነው ። አልጋ ውስጥ ስገባ ነው ። እና ላስቀይምህ ነው ። ገና ባንተ ፍቅር አልተያዝኩም ኪርክ ። ካንተ ጋር

አልተኛም’ በአሳቧ አለችና ድምጿን ከፍ አድርጋ “ኪርክ … ” ብላ ጀመረች።

በከፊል ራቁቱን ሆኖ ወደእርሷ ዞር አለ “አቤት?”

“ኪርክ ፣ እኔ … ይቅርታ አድርግልኝ ። ትጠላኛለህ ። ግን እኔ … እኔ አልችልም ። በጣም አዝናለሁ ። ማወቅ ያለብህ እኔ …”

የተስፋ መቁረጥ መንፈስ ከፊቱ ገጽታ ላይ አነበበች ። የግዱን ፈገግ አለና “ካቲ ልታገስ እንደምችል ገልጨልሻለሁ ። አሁንም ካልተዘጋጀሽ እኔ … እኔ እረዳሻለሁ ። ይህንን ትተን አሁንም እንዲሁ አብረን ጥሩ ጊዜ ልናሳልፍ እንችላለን” ሲል ተናገረ ።

በምስጋና ጉንጩን ሳም አደረገች ። “ኪርክ አመሰግናለሁ ። ምን እንደነካኝ ለራሴ አልገባሽ ብሎኛል ።”

“ምንም አልሆንሽም” ብሎ አረጋጋት ። “ችግርሽን እረዳዋለሁ ።” አቀፈትውና “አመሰግንሃለሁ ፣ አንተኮ መልአክ ነህ” አለችው ።

“በነገራችን ላይ” አለ እየሳቀ ። “እኔ ሳሎኑ ፎቴ ላይ እተኛለሁ ።”

“በፍጹም አይሆንም” አለችው ካተሪን አሳቡን ባለመቀበል ። “ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤዋ እኔ ስለሆንኩ ቢያንስ የአንተ ምቾት መጠበቁን ማረጋገጥ ይኖርብኛል ። ፎቴው ላይ እኔ እተኛለሁ ። አንተ አልጋው ላይ ሁን ።”

“ጨርሶ አይሞከርም ።”

ካተሪን ዓይኗን አፍጣ አልጋው ላይ እንደተኛች ስለኪርክ ሪኖልድስ ማሰብ ጀመረች ። ‘ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እችል ይሆን? ወይንስ ፍላጐቴን ላሪ ከውስጤ አሟጦ ወስዶታል? ይሆን ይሆናል። ደግሞ ላሪ ሊገለኝ የነበረ ሰው አይደለም?’ እንቅልፍ ወሰዳት ።

እኩለ ሌሊት ላይ ኪርክ ሪኖልድስ ጩኸት ሰምቶ ነቃ ። ተነስቶ ፎቴው ላይ እንደተቀመጠ ጩኸቱ በመቀጠሉ ወደመኝታ ቤቱ ሮጠ ።

ካተሪን ዓይኗን ጨፍና ከአልጋው ላይ ትወራጫለች ።

እየጮኸች “አይሆንም ተው ፣ ተው ፣ እባክህ ተወኝ !” ስትል ሰማት ።

ሪናልድስ ጐንበስ አለና በእጁ እቅፍ አድርጐ "ሽሽሽ" አላት ። "አይዞሽ ! አይዞሽ!"

የካተሪን ሰውነት በላብ ተጠምቋል ። ጩኸቱና ድንጋጤው እስኪቀንስላት አቅፎ ያዛት ።

"ሊያስጥሙኝ ነበር ።"

"ሕልም ነው" አላት በለሆሳሳ ። "መጥፎ ሕልም አይተሽ ነው ።"

ካተሪን ዓይኗን ገልጣ ቀና ብላ ከአልጋው ላይ ተቀመጠች ። ሰውነቷ ይንቀጠቀጥ ነበር ። "አይ ሕልም አይደለም ። ነገሩ እውነት ነው ። ሊገድሉኝ ነበር ።"

ኪርክ ተገርሞ እያያት "ማን ነው ሊገድልሽ የነበረው?" ሲል ጠየቃት ።

"ባለ ... ባለቤቴና ዕቁባቱ"

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "ካተሪን ፣ ቅዠት እኮ ነው እና ..."

"እውነቴን ነው የምነግርህ ። ሊገድሉኝ ነበር ። በዚሁ ምክንያት ተረሽነዋል ።"

የኪርክ ፊት በጥርጣሬ ተመላ ። "ካተሪን ..."

"ቀደም ብዬ ያልነገርኩህ ስለዚህ ... ስለዚህ መናገሩ ስለሚያሳም መኝ ነው ።"

እውነቷን መሆኑን አሁን ተገንዝቧል ። "ምንድን ነው የሆነው ?"

"ባሌን ላሪን ለመፍታት አልፈለግኩም ነበር ። እና እርሱ ... እርሱ ሌላ ሴት ወደደና ከርሷ ጋር ሆነው ሊገድሉኝ ወሰኑ ።"

ኪርክ አሁን ልብ ብሎ ያዳምጣት ጀመረ ። "ይህ የሆነው መቼ ነው?"

"ከአንድ ዓመት በፊት"

"ታዲያ እነርሱስ ምን ሆኑ?"

"መንግሥት ረሽናቸው ።"

"ቆዪኝ እስቲ ። አንቺን ለመግደል ስለሞከሩ ብቻ ተገደሉ ?"

"እም ።"

ሪናልድስ እንዲህ አላት ፦ "በግሪክ ሕግ በደንብ የተካንኩ አይደለሁም ፤ ግን በመግደል ሙከራ ብቻ በሰዎች ላይ የሞት ቅጣት የሚፈጸምባቸው አይመስለኝም ። አንድ የተፈጸመ ስሕተት መኖር አለበት ። አቴንስ ውስጥ የማውቀው አንድ ሕግ አስከባሪ አለ ። ነገ ጠዋት

ስልክ እደውልለትና ስለዚሁ ለማጣራት እሞክራለሁ ። ፒተር ዲሞኒዲስ ይባላል ።"

ኪርክ ሪናልድስ ከእንቅልፉ ሲነቃ ካተሪንን አያት ። 'በጣም እወዳታለሁ ፣ ባለፈው ጊዜ ምን እንደተፈጸመ ማወቅና ችግሯን መቅረፍ ይኖርብኛል' አለ በልቡ ።

ኪርክ ሪናልድስ ከፎቅ ወረደና ወደአቴንስ የስልክ ጥሪ አስመዘገበ። "በቀጥታ ፒተር ዲሞኒዲስን ለማነጋገር እፈልጋለሁ አፐሬተር ።"

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ጥሪው መልስ አገኘ ።

"ሚስተር ዲሞኒዲስ! ኪርክ ሪናልድስ እባላለሁ ። እንደምታስታውሰኝ እርግጠኛ አይደለሁም ። ግን ... "

"በደንብ አስታውስሀለሁ እንጂ ። ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ነው የምትሠራው አይደል ?"

"አዎ"

"ምን ልርዳህ ሚስተር ሪናልድስ?"

"ስላስቸገርኩህ ይቅርታ አድርግልኝ ። አንድ የሰማሁት ነገር ትንሽ ግራ ስላጋባኝ ነው የደወልኩልህ ። የግሪክን ሕግ የሚመለከት ነው ።"

"እኔ ስለግሪክ ሕግ ብዙ አውቃለሁ ብለህ?" አለ ዲሞኒዲስ በምፀት ። "ግን ያቅሜን ያክል ልረዳህ ዝግጁ ነኝ ።"

"በሕጋችሁ ላይ ለግድያ ሙከራ ወንጀል በሞት የሚያስቀጣ አንቀጽ አለ?"

ሰረኾም ጊዜ በስልኩ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። "ለምን ይህንን እንደጠየቅኸኝ ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"አንዲት ካተሪን አሌክሳደር የተባለች ሴት አብራኝ ትገኛለች ። ባለቤቷና ዕቁባቱ ሊገድሏት በመሞከራቸው ብቻ በመንግሥት እንደተገደሉ አድርጋ ገምታለች ። ታዲያ አልዋጥልኝ አለኝ ። ምን ማለቴ እንደሆነ ገብቶሃል?"

"አም" አለ ዲሞኒዲስ በአሳብ እንደተዋጠ ። "ምን ማለትህ እንደሆነ ገብቶኛል ። አሁን ያለሽው የት ነው ሚስተር ሪናልድስ?"

"በቅዱስ ሞሪዝ በሚገኘው የፓላስ ሆቴል አልጋ ይዣለሁ ።"

"እስቲ ላጣራና መልሼ ልደውልልህ ።"

“ደስ ይለኛል ። ነገሩ ምን መሰለህ እንደሚመስለኝ ሚስስ አሌክሳንደር በሃሣቧ የፈጠረችው ሳይሆን አይቀርም ። እና ጉዳዩን በደንብ አጣርቼ ከጭንቀቷ ላላቅቃት ብዬ ነው ።”

“ገብቶኛል ። ውጤቱን እንደማሳውቅህ እረጋግጥልሃለሁ ።”

የአየሩ ብሩህነትና አስደሳችነት ካተሪን ትናንት ማታ ያየችውን አስፈሪ ሕልም እንድትረሳው አድርጓታል ።

ሁለቱም ቁርሳቸውን በመንደሯ አብረው ከተመገቡ በኋላ ሪኖል ድስ እንዲህ አላት ፡— “ወደ ሽርተቱ እንሂድና በረዶው ውስጥ ትንሽ ዳክሪ ።”

ካተሪንን ወደ ጀማሪዎች ቁልቁለት ወሰዳትና የሚያለማምዳት ሰው ቀጠረላት ። መንሸራተቻ ጫማውን አጠለቀችና ተነስታ ቆመች ። እግሯን እያየች “በጣም ያስገርማል ። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን እግር ቢፈጥርብን ኖሮ አያቶቻችን ዛፎች ነበሩ ማለት ነው” አለች ።

“ምን አልሺኝ ?”

“ምንም አላልኩም ኪርክ”

የሽርተቱ አስተማሪው ፈገግ አለ ። “ምንም አታስብ. በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደ ልብሽ እንድትንሸራተቺ አደርጋለሁ ሚስስ አሌክሳንደር ። የምንጀምረው ከጀማሪዎች ቁልቁለት ከኮርቪጅሊያ ሳስ ሮንሶል ይሆ ናል።”

“በአጭር ጊዜ ስትለምጂው ታያለሽ ።” አላት ሪኖልድስ የአስተማ ሪውን አባባል በመደገፍ ።

ከርቀት ወደሚታየው የበረዶ መንሸራተቻ ሥፍራ ተመለከተና “እኔ ዛሬ በፈርክላ ግሪስቻ ላይ ነው የምንሸራተተው” አለ ።

“ጣፍጭ ሳይሆን አይቀርም ። ምግቤን ደህና አድርጌ አበስለዋለሁ ።” አለች ካተሪን ።

ሪኖልድስ ፈገግ ሳይል “በረዶ ላይ መንሸራተት እንጂ ምግብ ማብሰል እኩ አይደለም ፍቅሮዬ” አለ ።

“አሃ” አለችና ካተሪን የተናገረችው ቀልዷ መሆኑን ልታስታውቀው አፈረች ። ‘እርሱ ፊት መቀለድ አልነበረብኝም’ አለች በልቧ ።

አሰልጣኙ እንዲህ አለው “የግሪስቻ መንሸራተቻ ቁልቁለት ቀጥ ያለ ስለሆነ ከኮርቪጅሊያ ስታንዳርድ ማርገንስ ላይ ሰውነትህን ብታሚሙቅ

ይሻላል ሚስተር ሪኖልድስ?”

“በጣም ጥሩ አሳብ ። እሺ ካተሪን ፡ ለምሣ ሆቴሉ ውስጥ እንገናኝ ።”

“ጥሩ ።”

ሪኖልድስ እጁን በማወዛወዝ ተሰናበታትና ወደተባለው ሥፍራ ጉዞ ጀመረ ።

“መልካም የመዝናኛ ጊዜ እመኝልሃለሁ” አለችው ካተሪን ። “ደብዳቤ መጻፍ አትርሳ ።”

“መልካም” አለ አሰልጣኙ ። “እንግዲህ እንጀምር ።”

ካተሪን እንዳሰበችው ሳይሆን ትምህርቱ እጅግ የሚያዝናና ነው ። በመጀመሪያ ላይ ፈርታ ነበር ። እየተንሳፈፉ ወደ መንሸራተቻው አናት ወጣች ።

“ትንሽ ወደፊት ዘንበል በይና የመንሸራተቻዎቹን ጫማዎች ፊት ለፊት ቀጥ አድርጊ ።

“ለነርሱ ንገራቸዋ ። እንጮል አላቸው አይደል ። ቀጥ ይበሉ” አለች ካተሪን ።

“ጥሩ ይዘሻል ። አሁን ወደታች እንንሸራተታለን ። ጉልበትሽን እጥፍ አድርገሽው ሚዛንሽን ለመጠበቅ ሞክሪ ። አሁን ቀጥዪ !”

ወደቀች ።

“እንደገና ሞክሪ ፤ አያያዝሽ ጥሩ ነው ።”

አሁንም ወደቀች ። ደግሞም ወደቀች ። በድንገት ሚዛኗ ተስተካከለ ላት ። ክንፍ ያወጣች ያክል ነበር ቁልቁለቱን ሽው ያለችው ። በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው ። ልክ የመብረር ያህል ተሰማት ። የበረዶ ክምሩ ሲፈረፈርና ፊቷን በነፋስ ሲገርፍ ልዩ ደስታን ሰጣት ።

“ወድጂዋለሁ” አለች ካተሪን ። “ሰምች ለካ ሱስ የሚይዛቸው ለዚህ ነው፣ ወደትልቁ የሽርተቱ ገደል መቼ ነው የምዛወረው?” ።

አሰልጣኙ ሳቀ ። “ለዛሬው እዚሁ እንለማመድና ነገ ወደአለም አቀፍ መወዳደሪያ መንሸራተቻ እንሄዳለን ።”

የጠዋቱ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ አስደሳች ነበረ ።

ምግብ አዳራሹ ውስጥ ቁጭ ብላ ኪርክ ሪኖልድስን ትጠብቀው ነበር። ከበረዶ ሽርተቱው ተመልሶ ሲመጣ ጉንጩ ፍም መስሎ ፈክቷል ። ካተሪን

ወደተቀመጠችበት መጣና ከአጠገቧ ቁጭ አለ ።

"መልካም" አላት ። "እንዴት ነበር?"

"በጣም ልዩ ነው ። ትልቅ ነገር ባልሰብርም ስድስት ጊዜ ዘጭ ብያለሁ ። አንድ ነገር ግን ታውቃለህ?" አለችው በኩራት ። "ወደኋላ ላይ ደህና አድርጌ ስለተንሸራተትኩ ይመስለኛል ወደ አለም አቀፉ መወዳደሪያ ሽርተቴ ሊወስደኝ ነው ።"

ሪኖልድስ ፈገግ አለ ። "ጥሩ ።" ለፒተር ዲሞኒዲስ ስላደረገው የስልክ ጥሪ አንስቶ ሊያጫውታት ፈለገና እንደገና በጭንቀት ባሕር ውስጥ ሊጨምራት ስላልፈለገ ዝም ማለትን መረጠ ።

ከምሣ በኋላ በበረዶዋማው ጐዳና ላይ ለመንሸራሸር ወጥተው ዕቃዎችን ለመመልከት ወደ አንዳንድ መደብሮችም ጐራ አሉ ። ካተሪንን ድካም እየተሰማት መጥቷል ።

"ወደ መኝታ ክፍሌ ብመለስ ደስ ይለኛል" አለች ካተሪን ። "ትንሽ መተኛት እፈልጋለሁ ።"

"በጣም ጥሩ አሳብ ። አየሩ ትንሽ ሳሳ በማለቱ እስክትለምጂው ሊደክምሽ ይችላል ።"

"ኪርክ አንተስ ምን ልታደርግ ነው?"

ራቅ ብሎ ወደሚታየው የበረዶ ሽርተቴ መጫወቻ ተመለከተና "እኔም ግሪቻ ላይ ሽርተቴዬን እቀጥላለሁ ። ከዚህ በፊት እዚያ ተጫውቼ አላውቅም ። መቼም ሳይፈታተነኝ አይቀርም" አለ ።

"ማዶ በመግኘቱ?"

"ምን አልሺኝ?"

"ምንም ፣ ግን አስቸጋሪ ይመስላል ።"

ሪኖልድስ ጭንቅላቱን ነቀነቀና "ተፈታታኝ የሆነውም ለዚሁ ነው።"

ካተሪን እጁን ሳብ አደረገችና "ኪርክ ፣ ስሜማታው ሁኔታ በጣም አዝናለሁ ። ... ለመስተካከል እሞክራለሁ ።" ስትል ተናገረች ።

"ይህን ያህል አያስጨንቅሽ ። ወደሆቴሉ ተመለሺና ትንሽ ተኚ ።"

"እተኛለሁ ።"

ሪኖልድስ ተለይቷት ሲሄድ ካተሪን ቆም ብላ አየችውና በአሳቧ 'በጣም ጥሩ ሰው ነው ግን ከእንደኔ ዓይነቷ ደደብ ምን እንዳገናኘን እንጂለት?' አለች ።

ካተሪን ከቀትር በኋላ ባለው ጊዜ በደንብ ተኛች ። ሆኖም ምንም

ሕልም አላለመችም ። ከእንቅልፏ ስትነቃ አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ሆኗል። የኪርክ መምጫም ተቃርቧል ።

ካተሪን ተነስታ ገላዋን ታጠበችና ልብሷን ለባብሳ ስለመጪው ምሽት በአሳብ መብከንከን ጀመረች ። 'ለምሽቱ ሳይሆን' አለች በልቧ ። 'ሌሊቱን ሙሉ ተሻሽዬ ልገኝ እሞክራለሁ ።'

ወደ መስኮቱ አጠገብ ሄደችና ወደውጭ ተመለከተች ። ጨለማው ዓይን ያዝ ማድረግ ጀምሯል ።'ኪርክ መቼም በደንብ ሳይዝናና አልቀረም' አለች በልቧ ። ከሩቅ የሚታየውን የሽርተቴ ቦታ ለመመልከት ሞከረች ። 'ያ ግሪስቻ የሚባለው ሥፍራ ይሆን? መቼ ይሆን እዚያ ላይ የምንሽራተተው?'

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆነ ። ኪርክ ሪኖልድስ ግን አልተመለሰም ። ጨለማው ድቅድቅ ነው ። 'መቼም በዚህ ጨለማ ሽርተቱ ሊጫወት አይችልም' አለች ካተሪን ለእራሷ ። 'እርግጠኛ ነኝ ከታችኛው ፎቅ ቡና ቤቱ ውስጥ መጠጥ እየጠጡ ነው ።'

ወደበሩ ስትራመድ የስልክ ጥሪ ተሰማ ።

ካተሪን ፈገግ አለችና 'አልተሳሳትኩም ወዲያች ነይ ብሎ መደወሉ ነው' በማለት የስልኩን እጀታ አነሳች ። "ምነው ችግር አጋጠመህ እንዴ?" ብላ ጠየቀች ።

እንግዳ የሆነ ድምፅ "ሚስስ ሪኖልድስ?" ሲል

አይደለሁም ለማለት አስባ ነበር ፣ ሆኖም ኪርክ ያስመዘገባት በዚያ ስም መሆኑን አስታወሰች ። "አዎ ሚስስ ሪኖልድስ ነኝ ።"

"መጥፎ ዜና ላሰማሽ ነው ። ባለቤትሽ በበረዶ ሽርተቱው ሥፍራ አደጋ አጋጥሞታል ።"

"ሊሆን አይችልም አደ ... አደጋው ከባድ ነው?"

"ይመስለኛል"

"አሁን መጣሁ ። የት ነው ...?"

"ስነግርሽ በጣም እያዘንኩ ነው ሞ ... ሞቷል ሚስስ ሪኖልድስ ። ቁልቁለቱን ሲንሸራተት አንገቱ ተቀጭቶ ሕይወቱ አለፈች ።"

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

ቶኒ ሪዞሊ ከመታጠቢያ ቤቱ ራቁቷን ስትወጣ አየና 'የግሪክ ሴቶች ዳሌ ትልቅ የሚሆነው ለምንድንነው?' ሲል አሰበ ።

አልጋው ውስጥ ገብታ ወደእርሱ ጠጋ አለችና አቀፈችው ። "እኔን መርጠህ ስላመጣኸኝ ደስ ብሎኛል ፍቅሬ ። ካየሁህ ጊዜ አንስቶ በጣም ፈልጌህ ነበር ።"

ቶኒ ሪዞሊ ከት ብሎ ሊስቅ ትንሽ ነበር የቀረው ። ሴትዮዋ ስለወሲብ የሚያሳይ በርካታ ፊልሞችን ያየች ናት ።

"እውነትሽን ነው" አለ እርሱም "እኔም ልክ እንዳንቺው ተሰምቶኝ ነበር ።"

ሴትዮዋን ይዟት የመጣው ከክላሪ ጐዳና ላይ ከሚገኘው የኒውዮርክ የማታ ክበብ ውስጥ ስትዘፍን አግኝቶ ነው ። እንደ እሷ ላሉት ሴቶች ግሪኮች "ጋቭዮዚ ስኪሎ" የሚል ስያሜ ሰጥተዋል ። የዚህም ትርጉሙ "የምትጮህ ውሻ" ማለት ነው ። በክለቡ ውስጥ ከሚሠሩት ሴቶች ሌላ፥ መደበኛ መተዳደሪያ ላላቸውም ገንዘብ የከፈላቸው ሰው ወደቤቱ ይዟቸው ሊሄድ ይችላል ። ውበት የፈሰሰባት ይህችኛዋ ሄሌና ትባላለች ። ጠቆር ያለው ዓይኗ ፣ ማራኪ የሆነው ፊቷና ሞላ ያለው ሰውነቷ እዩኝ እዩኝ ይላል ። ዕድሜዋ ሃያ አራት ሲሆን ሪዞሊ ከሚፈልጋቸው ሴቶች የዕድሜ አካባቢ ትንሽ ላቅ ያለች ናት ። በአቴንስ ውስጥ ያሉትን ሴቶች ስለማያውቅ አማርጦ ለማግኘት ዕድል አላጋጠመውም ።

"ወደኸኛል ?" ብላ ጠየቀች ሄሌና በቀስታ ።

"አዎ ደስ ትይኛለሽ"

ጡቷን ግሻሽት ሲጀምር ጫፎቹ እንዶጦር ሹለው ሲደድሩ ተሰማው ። ጨበጥ ጨበጥ አደረጋቸው ።

"አዎዎ !"

"ከጭንቅላትሽ ወረድ በይ የኔ ፍቅር"

ጭንቅላቷን ነቀነቀች "እንደሱስ አላደርግም ።"

ሪዞሊ ትኩር ብሎ አያት ። "እውነትሽን ነው ?"

ፀጉሯን ይዞ ጐተታት ።

ሄሌና ጮኸች ። "ፓርካሎ !"

ሪዞሊ በጥፊ መታትና "ሌላ ድምፅ እሰሚና አንገትሽን እሰብረዋለሁ" አላት ።

ሪዞሊ ጭንቅላቷን ስቦ ጭኖቹ መሐል ከተተው ።

"እሄዳለሁ" አለች እያለቀሰች ። "በጣም ጐድተኸኛል"

ሪዞሊ ፀጉሯን እንደያዘ "ደስ ብዬሽ ነበር አይደል ?" ሲል ጠየቃት። ፀጉሯን ሲለቀው በደፈረሰው ዓይኗ ቀና ብላ አየችው ።

"መሄድ ትችያለሽ ..."

ፊቱ አስፈራት ። ሰውዬው አንድ መጥፎ ችግር ሳይደርስበት አልቀረም ። ይህንን እንዴት አላየችም ነበር ?

"የምንጣላበት ምንም ምክንያት የለም" አለችው በትሕትና ። "እኔና አንተ..."

አንገቷን አንቆ ያዘ ። "ስላነጋገርሺኝ ብቻ ገንዘብ ልሰጥሽ አልችልም ።" መልሶ ፊቷን በቡጢ መታት ። "አፍሺን ዝጊና ወደሥራሽ ሂጂ ።"

"እሺ የእኔ ፍቅር" አለች ሄሌና በልቅሶ "እሺ ብያለሁ ።"

ሪዞሊ ቶሎ የሚረካ ሰው ባለመሆኑ ውዝዋዜውን ባበቃበት ወቅት የሄሌና ሰውነት በጣም ዝሎ ነበር ። እንቅልፍ እስኪይዘው ድረስ አጠገቡ ተጋድማ ቆየችና መተኛቱን ስታረጋግጥ ከአልጋው ውስጥ ቀስ ብላ ወጥታ ልብሷን ለባበሰች ። ሕመሙ በጣም ተሰማት ። ሪዞሊ ምንም ገንዘብ አልከፈላትም ። ሄሌና ቦርሳውን ብትከፍት ደህና ገንዘብ ልትወስድ በቻለች ነበር ። ግን ደመ ነፍሷ ባዶ እጇን እንድትወጣ አሳሰባት ።

ከእንድ ሰዓት በኋላ የመኝታ ቤቱ በር ሲንኳኳ ቶኒ ሪዞሊ ከእንቅልፉ ነቃ ። ተነስቶ አልጋው ላይ ቁጭ አለና ሰዓቱን አየ ። ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ሆኗል ። ዙሪያውን ሲቃኝ ሴትዮዋ ሄዳለች ።

"ማን ልበል ?" አለ ።

“ጐረቤትህ ነኝ” አለው የተናደደ የሚመስል ድምፅ ። “ስልክ ይፈልግሃል ።”

ሪዞሊ ግንባሩን አሻሸና “መጣሁ” አለ ።

የሌሊት ልብሱን አጠለቀና ሱሪው ወደተቀመጠበት ወንበር አጠገብ ሄደ ። ቦርሳውን አውጥቶ አየው ። ገንዘቡ አልተነካም ። ‘እህ ፣ ያቺ ውሻ የዋዛ አይደለችምና !’ አለ በልቡ ። ከቦርሳው ውስጥ መቶ ዶላር አወጣና በሩን ከፈተው ።

ከጐረቤቱ ክፍል የተከራየው ሰው ፒጃማውን ለብሶ ነጠላ ጫማ እንዳደረገ ከመተላለፊያው ላይ ቆሞ ይጠብቀው ነበር ። “ስንት ሰዓት እንደሆነ ታውቃለህ ?” አለ በንዴት እነጋገር ። “ከዚህ ቀደም ስትነግረኝ...”

ሪዞሊ የመቶውን ዶላር ኖት አስጨበጠውና “በጣም አዝናለሁ ብዙ አላነጋግርም” አለ በይቅርታ ስሜት ።

ሰውዬው ምራቁን ዋጥ አደረገ ፣ ንዴቱም ተነነ ። “ምንም አይደለም። ሰው ከሌሊቱ በአሥር ሰዓት በስልክ የሚቀሰቀሰው ጉዳዩ ክብደት ያለው በመሆኑ ይሆናል ።”

ሪዞሊ ወደመኝታ ክፍሉ ገባና ስልኩን አነሳ ። “ሪዞሊ ነኝ።”

ሌላው ድምፅ “ሚስተር ሪዞሊ ችግር አጋጥሞሃል” አለው ።

“ማን ልበል ?”

“ስፒሮስ ላምብሩ እንድደውልልህ ጠይቆኝ ነው ።”

“ገባኝ” በአእምሮው የአደጋ ምልክት አንቃጨለ ። “ችግሩ ምንድር ነው ?”

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስን በተመለከተ ነው ።”

“እና ምን ሆነ ?”

“ከመርከቦቹ መሃል ትኤሌ የተባለችዋ ማርሴሊስ ክባዚን ዴ ላ ግራንዴ ጀሊኤት ወደብ ቆማለች ።”

“እና ?“

“ሚስተር ዴሚሪስ መርከቧ አቅጣጫዋን ወደ አቴንስ እንድትለውጥ ማዘዙን ደርሰንበታል ። አውድ ጠዋት እዚያ ደርሳ ማታ ጉዞዋን ትጀምራለች ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስም ከመርከቧ ላይ ይሳፈራል ።”

“ምን ?”

“ሊያመልጥ ነው ።”

“ግን እርሱና እኔኮ...”

ዴሚሪስ ከአንተ እስኪገላገል ድረስ በፑናይትድ ስቴትስ ውስጥ የመደበቅ እቅድ እንዳለው እንድነግርህ ነው ሚስተር ላምብሩ የላከኝ ።”

‘ይሄ የውሻ ልጅ ቆይ ይጠብቅ’ አለ በልቡ ። “ገባኝ ፣ ሚስተር ላምብሩን አመሰግንልኝ ። ትልቅ ባለውለታዬ መሆኑን ግለጽለት ።”

“እሪ ግድ የለም”

ሪዞሊ ስልኩን ዘጋ ።

“በደህና ነው ሚስተር ሪዞሊ ?” ሲል ጠየቀው ጐረቤትዬው ።

“ምን አልከኝ ! በጣም ደህና ነው” ብሎ መለሰ ሪዞሊ ።

ሪዞሊ ስለተደረገለት የስልክ ጥሪ ባስታወሰ ቁጥር የበለጠ ደስ እያለው መጣ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስን በቁንቅት ከአገር አስፈርጥጦ ታል ። ይህም ዴሚሪስን በቀላሉ እጁ ውስጥ የሚያስገባበትን ሁኔታ ይበልጥ አመቻችቶለታል ። ‘እሁድ ዕለት።’ እቅዶቹን ለመንደፍ ሁለት ቀናት አሉት ።

ሪዞሊ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርበት ገብቶታል ። በሄደበት ሁሉ ክትትል ይደረግበታል ። ‘እናታቸውን ፣ ቆይ እነኚህን ፊናንሶች አንድ ቀን እሰራላቸዋለሁ’ ሲል በልቡ ዛተ ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ሪዞሊ በኪፊሲያስ ጐዳና ላይ ወደሚገኘው የሕዝብ ቴሌፎን ማልዶ ሄደና ወደአቴንስ የመንግሥት ሙዚዬም ስልክ ሊደውል ቁጥሮችን አዞረ ።

ዕቃ እንደሚያይ ሰው በመደብሮቹ መስኮት አጠገብ የቆመ አንድ ሰውና ከመንገዱ ባሻገር ደግሞ ከአበባ ሻጭ ጋር የሚነጋገር ሌላ ሰው በመስታወቱ ነፀብራቅ ውስጥ ለሪዞሊ ታየው ። ሁለቱም ሰዎች በሪዞሊ ላይ ክትትል እንዲያደርጉ የተሰማሩ ናቸው። ‘መልካም ዕድል እመኝላች ኋለሁ’ አለ ሪዞሊ በልቡ ።

“የሙዚዬሙ ኃላፊ ቢሮ ነው ፣ ምን ልርዳዎት ?”

“ቪክቶር ? ቶኒ ነኝ ።”

“ችግር አለ ?” ኮሮንዚስ መደንገጡ በድምፁ ይታወቃል ።

“ምንም” አለ ሪዞሊ ሲያረጋጋው ። “ሁሉም ነገር ደህና ነው። ቪክቶር ፣ ያንቺ ጌጣ ጌጥ የበዛባትን ባለቀይ ምልክት የአበባ ማስቀመጫ

ሽክላ የምትመስለውን ቅርስ ታስታውሳታለህ ?”

“ያቺን ካ አምፖራ ?”

“አዎ ዛሬ ማታ ልወስዳት እመጣለሁ ።”

ለረኸም ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ። “ዛሬ ማታ ? እ...እንጃ ቶኒ ።” የኮሮንዚስ ድምፅ ይንቀጠቀጥ ጀመር ። “ምናልባት ችግር ከተፈጠ ረስ...”

“እሺ ፖል እንዲህ ከሆነ ተወው ። እኔኮ አንተን ለመርዳት ስል ነው። ለሳል ፕሪዚ ገንዘቡን አሳገኘሁም ብለህ አፍርጠህ ንገረውና የፈለገውን ያድርግ ...”

“አይደለም ቶኒ ቆየኝ እንጂ ። እኔ... እኔ ...” እንደገና ዝምታ ሰፈነ። “እሺ ይሁን ።”

“እርግጠኛ ነህ ቪክቶር ? ልትሰጠኝ የማትፈልግ ከሆነ በግልፅ ንገረኝና እንዲህ ዓይነት ችግር ወደማይገጥመኝ ወደዩናይትድ ስቴትስ ልሂድ ። ታውቃለህ አይደል ? እንዲህ ዓይነት ጭቅጭቅ ...”

“አይደለም ፡ እንደርሱ አይደለም እስካሁን ስታደርግልኝ የቆየኸ ውን ሁሉ አደንቃለሁ ቶኒ ። እውነቱን ነው የምልህ ከልቤ ነው የማመሰግንህ ። እሺ ዛሬ ማታ ይሁን ።”

“መልካም ፡ ሙዚዬሙ በሚዘጋበት ወቅት ዋናውን ቅርስ ተመስሎ የተሠራውን በሥፍራው ተካና ማሠሮዋን ይዘህ ውጣ ።”

“ከእዚህኮ ስንወጣ ዘቦች የያዝነውን ሁሉ ይፈትሻሉ ።”

“ይፈትሹዋ ! ዘቦቹ የቅርሳቅርስ ሊቅ ናቸው እንዴ ?”

“አይ ፡ እርሱማ አይደሉም ። ግን ...”

“ጥሩ ፡ ቪክቶር ፡ የምነግርህን ስማ ። የአምሳያው ቅርስ የተሸጠበ ትን ደረሰኝ ውሰድና ከዋናው ላይ ለጥፈህ በወረቀት ታኽሎ ፈጁምረህ ያዘው ። ገባህ?”

“አዎ ገ... ገብቶኛል ። ታዲያ የት ነው የምንገናኘው ?”

“እኔና አንተ አንገናኝም ። ከሙዚየሙ በአሥራ ሁለት ሰዓት በምትወጣበት ጊዜ አንድ ታክሲ ከሕንፃው ፊት ለፊት ቆሞ ይጠብቅሃል። ዕቃውን ያዝናና የታክሲውን ሾፌር ከግራጅዬ ብረታኘ ሆቴል እንዲያደር ስህ ንገረው ። ከዚያም ጠብቀኝ በለውና ዕቃውን ከታክሲው ውስጥ ትተህ ሆቴሉ የመጠጥ ክፍል ገብተህ መጠጥ እዘዝ ። ከዚያ በኋላም ወደ ቤትህ ሂድ ።”

“ግን ዕቃው ...”

“ስለእርሱ አታስብ ። አስፈላጊው ጥንቃቄ ይደረግለታል ።”

ቪክቶር ኮሮንዚስን ላብ አጠመቀው ። “እንዲህ ዓይነት ነገር አድርጌ አላውቅም ቶኒ ። ምንም ዓይነት ዕቃ ሰርቄ አላውቅም ። በሕይወቴ ውስጥ ...”

“እውቃለሁ” አለ ሪዞሊ በለሰለሰ አነጋገር ። “እኔምኮ እንዲሁ ነኝ። ይግባህ ቪክቶር ይህንን ሁሉ የማደርገው የገዛ ሕይወቴን ለአደጋ ዳርጌ ነው ። ደግሞ ከዚህ ውስጥ የማገኘው ጥቅም የለም ።”

የኮሮንዚስ ድምፅ እየተቆራረጠ “አንተኮ በጣም ጥሩ ዓደኛ ነህ ። ከዚህ በፊት ከነበሩኝ ዓደኞቼ እንዳንተ ያለ ጥሩ ሰው አላየሁም” አለ እጁን እያሻሸ ። “የእኔን ድርሻስ መቼ ነው የምትሰጠኝ ?”

“በአፋጣኝ ነዋ !” አለና ሪዞሊ ማረጋገጫ ሰጠው ። “አንዴ ይህንን ዓላማችንን ከጣቡ ካደረስን ምንም የሚያስጨንቅህ ነገር አይኖርም ።” ‘እኔም የሚያሳስበኝ ነገር የለም’ አለ ሪዞሊ በአሳቡ ። ‘ሁለተኛ በጭ ራሽ።’

ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ሁለት ተዘዋዋሪ መርከቦች ከፒራኡስ ወደብ ቆመው ነበር ። በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ሙዚየሙ በርከት ያሉ ጉብኚዎችን ያስተናግዳል ። ብዙውን ጊዜ የጉብኝዎች ሕይወት ምን እንደሚመስል ማወቅና ማንነታቸውን ማጥናት ለኮሮንዚስ ደስታን ይሰጠዋል ። ከጉብኚዎቹ መካከል አሜሪካውያንና እንግሊዛውያን የሚገኙ ሲሆኑ ከተለያዩ አገሮች የመጡም አሉ ። አሁን ግን ኮሮንዚስ ስለተረበሸ ስለእነኝህ ሰዎች ማሰቡ ጨርሶ ደንታ አልሰጠውም ።

እርሱ የሚፈልገው የቅርስ አምሳያ ለሽያጭ ወደተቀመጠበት መደርደሪያ ሲሄድ አካባቢው በጉብኝዎች ተጨናንቋል ። የሽያጩን ሥራ የሚያከናውኑትም ሁለቱ ሴቶች ጉብኝዎቹን ለማስተናገድ በሥራ ተወጥረዋል ።

‘ምናልባትኮ አምሳያ ዕቃዎቹ በሙሉ ሊሸጡ ይችላሉ’ አለ ኮሮንዚስ በአሳቡ ። ‘እንዲህ ከሆነስ የሪዞሊን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ላልችል ነው።’ እንደሰጋው አልሆነም ፤ በመጋዘኑ ምድር ቤት የብዙ ቅርሶች አምሳያዎች ተከማችተዋል ።

በስርቆት እንዲወጣ ቶኒ የጠየቀው ቅርስ ሙዚየሙ ካለው ከፍተ ኛና ውድ ዕቃ መካከል አንዱ ነው ። ዕቃው ከክርስቶስ ልደት በፊት

በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአገልግሎት ላይ እንደነበረ የሚነገርለት ነው ። ቪክቶር ኮሮንዚስ ይህንን ክቡር ቅርስ በእጁ የነካው ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት አሁን ካለበት መደርደሪያ አስቀምጦት ሲቆልፍበት ነው ። 'እና አሁን እኔም ልሰርቀው ነው' አለ በልቡ ኮሮንዚስ እያዘነ ። 'አምላኬ እባክህ ሰውረኝ ።'

ከሰዓት በኋላ ያለውን ጊዜ በሙሉ ፍዝዝ ብሎ የዋለው ኮሮንዚስ ስርቆቱ የሚፈጸምባትን ደቂቃ በስጋት ይጠብቃት ነበር ። ወደቢሮው ገባና በሩን ከውስጥ ቆልፎ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ትካዜውን ቀጠለ ። 'እንዴት አድርጌ ይህንን ልፈጽም ?' አለ በአሳቡ ። 'ከገባሁበት ማጥ ለመውጫ ሌላ ዘዴ መፈለግ ይኖርብኛል ። እኮ ግን ምን ?' ያንን ያህል ገንዘብ ለማስገኘት የሚችል ምንም ዓይነት ብልሃትና ዘዴ ብልጭ አልልለት አለ ። ሮፕሪዚ ንግግር ደጋግሞ አእምሮው ውስጥ አቃጨለ ። 'ያንን ገንዘብ ዛሬ ማታ ትሰጠኛለህ ፣ ወይም ወደባሕር እወረውርሃለሁ ። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባህ?' ሰውዬው ነፍሰ ገዳይ ስለሆነ ኮሮንዚስ ምንም ሌላ አማራጭ አይኖረውም ።

አሥራ ሁለት ሰዓት ሊሆን ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ ኮሮንዚስ ከቢሮው ወጣ ። አምሳያዎቹን ቅርሶች የሚሸጡት ሴቶች ዕቃዎቹ ያሉበትን መደርደሪያ መቆላለፍ ጀምረዋል ።

"ሲኞሚ !" ሲል ተጣራ ኮሮንዚስ ። "የልደት በዓሉን ለሚያከብር ለአንድ ጓደኛዬ ከዚሁ ከሙዚየሙ አንድ ስጦታ ገዝቼ ላበረክትለት አስቤአለሁ ።" ወደመደርደሪያዎቹ አካባቢ ሄደና እንደሚመርጥ ሰው ሆነ። በመደርደሪያዎቹ ውስጥ የአበባ ማስቀመጫ ዕቃዎች ፣ መጻሕፍትና ካርታዎች ይገኛሉ ። የትኛውን ልምረጥ ብሎ እንደሚያስብ ሰው ደጋግሞ አያቸው ። በመጨረሻ በጥቁር ቀለም ላይ ቀይ ተቀብቶ ወደሚታየው አምፎራ ቅርስ አመለከተ ። "ያንን የሚወደው ይመስለኛል ።"

"እንደሚወደው እርግጠኛ ነኝ" አለች ሴትዮዋ ። ከመደርደሪያው ውስጥ አወጣችና ለኮሮንዚስ ሰጠችው ።

"ደረሰኝ ልትሰጪኝ ትችያለሽ ?"

"በደንብ እንጂ ሚስተር ኮሮንዚስ ፣ በስጦታ ወረቀት እንድጠቀልል ልህ ትሻለህ?"

"አይ ግድየለም" አለ ኮሮንዚስ ቶሎ ብሎ ። "ዝም ብለሽ በወረቀት

ፓኩ ጨምሪና ስጪኝ ።

አምሳያውን ቅርስ በወረቀት ፓኮ ውስጥ ከነደረሰኙ ስትጨምር ዝም ብሎ ያያት ነበር ። "አመሰግናለሁ ።"

"ጓደኛህ ደስ የሚሰኝ ይመስለኛል ።"

"ደስ እንደሚለው ተስፋ አደርጋለሁ ።" እጁ እየተንቀጠቀጠ የወረቀት ፓኮውን ተቀበለና ወደቢሮው ገሰገሰ ።

ቢሮውን ከውስጥ ቆለፈና አርቲፊሻሉን የአበባ ማስቀመጫ ከወረቀቱ ፓኮ ውስጥ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ አኖረ ። 'አሁንም ሃሣቤን ልለውጥ እችላለሁ ፤ እስካሁን ገና ምንም ወንጀል አልፈጸምኩም' አለ በአሳቡ ። መወሰን አቅቶት አእምሮው ይዋዥቃል ። በጣም አስፈሪ የሆኑ አሳቦች እየመጡበት ግራ አጋብተውታል ። 'ባለቤቴንና ልጆቼንኮ ትቼ በመጥፋት ወደሌላ አገር መሄድ እችላለሁ ። ሕይወቴንስ ባጠፋ ምናለ በት? ፖሊስ ዘንድ ሄጄ የሕይወት ማስፈራሪያ እንደተሰነዘረብኝ ልገልጽላቸው እችላለሁ ። ግን እውነቱ በሚወጣበት ጊዜ አከተመልኝ ማለት ነው።' አለ በአሳቡ ። ከገባበት ማጥ የሚያወጣው ምንም ዘዴ አልተከሰተለትም ። የተበደረውን ገንዘብ ካልከፈለ ፕሪዚ እንደሚገድለው ያውቃል። 'እግዜር ይመስገን' አለ በልቡ ። 'ቶኒን የመሰለ ጓደኛ የሰጠኝ ። እርሱ ባይኖር እስካሁን ሟች ነበርኩ ።'

ሰዓቱን ሲመለከት የመንቀሳቀሻ ጊዜው መድረሱን ተረዳ ። ኮሮንዚስ ተነስቶ እንደቆመ እግሩ ተንቀጠቀጠ ። በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰና እራሱን መራገም ጀመረ ። በላቦት የራሰውን እጁን ሸሚዙ ላይ ጠራረገና አምሳያውን ቅርስ መልሶ ከፓኩው ውስጥ በመክተት ወደበሩ ሄደ ። የዋናው በር ዘብ ልክ አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ወጥቶ ሄዷል ። ተቀያሪው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ዙሪያውን እየተዘዋወረ ማየት ነበረበት ። ይሄኔ ከሙዚየሙ ሌላ ጫፍ ሳይደርስ አይቀርም ።

ኮሮንዚስ ከቢሮው ሲወጣ ዘበኛውን ከፊትለፊት አገኘና እንደ መሸማቀቅ አለ ።

"ይቅርታ ሚስተር ኮሮንዚስ እስካሁንኮ እዚህ መቆየትህን አላወቅኩም ።"

"አዎ ። እ ... አሁን እየወጣሁ ነው"

"ታውቃለህ" አለ ዘበኛው በአድናቆት ። "እኔኮ በአንተ እቀናለሁ።"

‘እውነቱን ብትረዳ እንዲህ አትልም’ አለ ኮሮንዚስ በልቡ ። “እውነትህን ነው ? ለምን ?”

“ስለእነኚህ ውብ ቅርሳቅርሶች ብዙ ነገር ስለምታውቅ ነዋ ! እየተዘዋወርኩ ባየኋቸው ቁጥር የጠለቀ እውቀት ባይኖረኝም የታሪክ መሠረቶች መሆናቸውን እረዳለሁ ። ምናልባት አንድ ቀን በደንብ ታስረዳኛለህ ። እኔኮ በእውነት ...”

ይህ ደደብ ተናግሮ የሚያበቃ አይመስልም ። “እሺ ፣ በደስታ አንድ ቀን አስረዳሃለሁ” አለ ኮሮንዚስ ። ከወዲያኛው ክፍል ውስጥ እውነተኛው የአበባ ማስቀመጫ ቅርስ ከመደርደሪያው ውስጥ ሆኖ ታየው ። ዘበኛውን በምክንያት ዞር ማድረግ ይኖርበታል ።

“እዚያ ... እዚያ ምድር ቤቱ ውስጥ የአደጋ ጊዜ መጥሪያው ችግር ያለበት ይመስለኛል ። ይሠራ አይሠራ እንደሆነ ሄደህ ብታይ ?”

“እሺ ፣ አያለሁ ። እዚያ ያሉት እቃዎች ዘመን በጣም ሩቅ...”

“አሁን ሄደህ ብታየውስ ? ሁሉም ነገር ደህና መሆኑን ሳላረጋግጥ ለመሄድ አልፈልግም ።”

“ልክ ነህ ሚስተር ኮሮንዚስ አሁን ሄጄ አይና እነግርሃለሁ ።”

ዘበኛው አዳራሹን አቋርጦ ወደምድር ቤቱ ሲገሰግስ ቪክቶር ኮሮንዚስ ቆሞ አየው ። ዘቡ ከዓይን ሲሰወር ቀዩ አምፑራ ወደተቀመጠበት መደርደሪያ ሄደና ከኪሱ ቁልፍ አውጥቶ ‘እንግዲህ ስርቆቱን መፈጸሚ መለሰኝ’ አለ በልቡ ። ቁልፉ ከእጁ አመለጠችና ወለሉ ላይ ወደቀች ። ‘ይህ የምን ምልክት ይሆን? እግዚአብሔር ሊነግረኝ የፈለገው ነገር ይኖር ይሆን ?’ አለ እንደገና በአሳቡ ። ላብ ከሰውነቱ ይንቆረቆራል ። ጉንበስ ብሎ ቁልፉን አነሳና የተባለችዋን ቅርስ ትኩር ብሎ አያት ። ልዩና በጣም የተዋበች ናት ። ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ጥንታውያን አባቶች በከፍተኛ ጥንቃቄ የሠሯት ትመስላለች ። ዘበኛው እውነቱን ነው፡ ዕቃው ምትክ የማይገኝለት የታሪክ ቅርስ ነው ።

ኮሮንዚስ ዓይኑን ለጥቂት ጊዜ ጨፈነና ተንገፈገፈ ። ዓይኑን ገልጦ ዙሪያውን ሲመለከት ሰው እያየው አይደለም ። መደርደሪያውን ከፈተና ቀስ ብሎ ቅርሲቷን አወጣ ። በያዘው ያወረቀት ባኮ ውስጥ ያለችውን አምሳያዋን ቅርስ አወጣና ዋናው በነበረበት ሥፍራ ተካት ።

ኮሮንዚስ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብሎ ተመራመራት ። በባለሙያ ቁርጥ አምሳያ ሆና ብትሰራም ዋናው አለመሆኗ በግልጽ እንደሚታወቅ ታየው ።

‘ምናልባት እኩ ግልፅ የሆነው ለእኔ ብቻ ነው’ አለ ኮሮንዚስ በአሳቡ ። ‘ሊለዩት የሚችሉት ጥቂት ባለሙያዎች ብቻ ናቸው። ሌላ ማንም ዋናውን ከአምሳያው ቅርስ ለይቶ ለማወቅ አይችልም ። ሆን ብሎ ወደአምሳያው ቅርሶ የሚመረምር ሰውም አይኖርም ።’ ኮሮንዚስ መደርደሪያውን መልሶ ቆለፈና እውነተኛውን ቅርስ ከደረሰኙ ጋር ከወረቀት ፓኮው ውስጥ ጨመረ ።

መሐረብ ከኪሱ አውጥቶ እጁን አባበሰ ። ያሳሰበውን ከግቡ አድርሷል ። ሰዓቱን ሲመለከት አሥራ ሁለት ከአሥር ሆኗል ። ፈጠን ማለት አለበት ። ወደመውጫ በሩ ሲጓዝ ዘበኛውም ወደእርሱ መምጣቱን አየ ።

“የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያው ምንም ብልሽት የለውም ሚስተር ኮሮንዚስ ፣ እና...”

“ጥሩ” አለ ኮሮንዚስ ። “ከዚህ በላይ ጥንቃቄ ማድረግም አንችልም።” ዘበኛው ሳቅ አለ ። “አባባልህ ትክክል ነው ። አሁን መሄድህ ነው ?”

“አዎ ፣ ደህና እደር”

“ደህና አደር ።”

ሌላው ዘበኛ ከመውጫ በሩ አጠገብ ቆሟል ። ኮሮንዚስ የያዘውን የወረቀት ፓኮ እየና በፈገግታ “የያዝከውን ዕቃ መፈተሽ አለብኝ ። ሕጉን ያወጣኸው አንተው አይደለህ?” አለው ።

“እንዴታ!” አለ ኮሮንዚስ ። ቶሎ ብሎ የያዘውን የወረቀት ፓኮም ለዘበኛው ሰጠው ።

ዘበኛው ፓኮው ውስጥ ያለውን ተመለከተና ቅርሱን አውጥቶ ደረሰኙን አነበበ ።

“ለጓደኛዬ የገዛሁት ስጦታ ነው” አለ ኮሮንዚስ ስለዕቃው ሲያስረዳ ። “ኢንጂንዬር ነው ።” በልቡ ‘ይህንን ሁሉ መቀባጠር ለምን አስፈለገኝ ! እርሱን ምን ያገባዋል ! ከወትሮው ያልተለየ ባሕርይ ማሳየት ነበረብኝ’ አለ ።

“ጥሩ” አለና ዘበኛው ቅርሱን ወደወረቀቱ ፓኮ መልሶ ከተተው። ኮሮንዚስ ዕቃው ቢሰበርስ የሚል አሳብ ብልጭ ብሎበት ነበር ።

ኮሮንዚስ ባኮውን ጉያው ስር ሸጉጠና “ካሊስፔህራ” አለ ።

ዘበኛው በሩን እየከፈተለት “ካሌስፔህራ” ሲል መለሰ ።

ኮሮንዚስ ቀዝቃዛውን የማታ አየር ወደውስጥ እየሳበና ከውስጡም ቁና ቁና አየር እያስወጣ ፥ እንደማቅለሽለሽም እያለው ጉዞውን ቀጠለ ። በእጁ የያዘው በሚሊዮን ዶላር የሚገመት ዋጋ ያለው ዕቃ ሲሆን እርሱን የሚያሳስበው የዕቃው ዋጋ አልነበረም ። በአእምሮው ውስጥ የሚተረማመሰው የሚወዳት አገሩን ግሪክን ከድቶ ከፍተኛ የታሪክ ቅርስ ሰርቆ ማንነቱ ለማይታወቅ የውጭ ዜጋ አሳልፎ መሸጡ ነው ።

በደረጃው ወደታች መውረድ ጀመረ ። ሪዞሊ ቃል እንደገባለት ከሙዚየሙ ፊት ለፊት ታክሲ ቆማ ትጠብቀው ነበር ። ኮሮንዚስ ወደታክሲው ሄዶ ከፍቶ ገባ ። "ከግራንዴ ብሪታኜ ሆቴል አድርሰኝ" አለው ሾፌሩን ።

ወደኋላ ደገፍ ብሎ ተቀመጠ ። ሲደባደብ የቆየ ይመስል ሰውነቱ የተቀጠቀጠ ያህል ነበር ። ግን በድብደባው አሸንፏል ወይንስ ተሸንፏል ?

ታክሲዋ ከግራንዴ ብሪታኜ ሆቴል ፊትለፊት ደርሳ ስትቆም ኮሮንዚስ ሾፌሩን "እዚሁ ቆየኝ" አለውና የያዘውን ውድ ዕቃ ያለበት ፓኮ ለመጨረሻ ጊዜ ተመልክቶ ከታክሲው ወርዶ ወደሆቴሉ አመራ ። ሆቴሉ አጠገብ እንደደረሰ ወደኋላ ዞር ሲል አንድ ሰው ታክሲው ውስጥ ሲገባና ሾፌሩም ታክሲዋን አስነስቶ ሲያከንፋት አየ ።

የተፈለገው ሁሉ ተከናውኗል ። 'እንዲህ ዓይነት ድርጊት ሁለተኛ አልፈጽምም' አለ ኮሮንዚስ በአሳቡ ። 'በሕይወቴ እስካለሁ ድረስ ማለቴ ነው ። ቅዠቱ እንግዲህ ያበቃ ይመስለኛል ።'

* * *

ፅሁድ ዕለት ከሰዓት በኋላ ልክ ዘጠኝ ሲሆን ቶኒ ሪዞሊ ከሆቴሉ ወጣና ወደፕላሺአ ኦምኒአ አቅጣጫ አመራ ። የለበሰው የቼኮዝሎቫኪያ ጃኬትና አረንጓዴ ሱሪ ሲሆን የመነኩሴ የሚመስል ቀይ ቆብ ጭንቅላቱ ላይ ደፍቷል ። ሁለት ሰላዮች ተከትለውታል ። ከሁለቱ አንደኛው "እነኚህን ልብሶች ከሰርከስ የገዛቸው ይመስለኛል" አለ ።

ከሜታክሳ ጉዳና ሲደርስ ሪዞሊ ታክሲ አስቆመና ገባ ። ሰላዩ በሆኪ ቶኪ ራድዮው "ተፈላጊው ወደምዕራብ አቅጣጭ በሚሄድ ታክሲ ውስጥ ገብቷል" የሚል መልእክት አስተላለፈ ።

መነጋገሪያው ውስጥ ሌላ ድምፅ "እያየነው ነው ፣ እየተከታተልነው ስለሆነ ወደሆቴሉ ተመለስ" ሲል አዘዘ ።

"እሺ ።"

ግራጫማ ቀለም ያላት ሴዳን መኪና ታክሲዋን በርቀት ተከታተለች። ታክሲዋ በሞናስቲራኪ በኩል አልፋ ወደደቡብ አቅጣጫ አመራች። በሴዳኗ መኪና ውስጥ ከሾፌሩ አጠገብ የተቀመጠው ሰላይ የራዲዮኑን መነጋገሪያ ሳብ አደረገና "ግዕከላዊ ፣ ይህ ቡድን አራት ነው። ተፈላጊው ታክሲ ውስጥ ነው ። በፊልሄሊዮን ጉዳና በኩል እየተጓዘ ነው። .... ቆየኝ ። ከፍታ ጉዳና ሲደርሱ ወደቀኝ ታጥፈዋል ። ወደፕላክ የሚሄዱ ይመስላል ። እዚያ አካባቢ ይሰወሩብን ይሆናል ። በእግር እንዲከታተለው የተዘጋጀ ኃይል አለ?"

"ትንሽ ቆይ ቡድን አራት ።" ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ራድዮው እንደገና ድምፅ አሰማ ። "ቡድን አራት ፣ የሚረዳህ ኃይል ተገኝቷል። ፕላክ ደርሶ ከታክሲው ከወረደ በእግር የሚከታተለው ሰው አለ ።"

"ካላ ! ተፈላጊው የለበሰው ቀይ ጃኬትና አረንጓዴ ሱሪ ሲሆን ቀይ ቆብ እራሱ ላይ ደፍቷል ። በቀላሉ ሊታወቅ የሚችል ነው ። ቆይ እስቲ ። ታክሲዋ ቆማለች ። አዎ ፕላካ ላይ ነው የወረደው ።"

"መረጃውን እናስተላልፋለን ። በደንብ ተወጥሯል ። ግልጽ ነው? በቃ ።"

ፕላካ ላይ ሰውዬው ከታክሲው ሲወርድ ሁለት ሰላዮች ያዩታል ።

"እነዚህን ልብሶች ከየት ይሆን የገዛቸው?" አለ አንደኛው ሰላይ ።

በሕዝብ በተጨናነቀውና ያረጀው የከተማው ክፍል ውስጥ ሲራመድ ተከታተሉት ። ለአንድ ሰዓት ያህል ያለምንም እቅድ በጉዳናዎች ላይ ከወዲያ ወዲህ መዘዋወር ቀጠለ ። በመድኃኒት ቤት በኩል አለፈና ጉራዴ፣ ጨቤ ፣ ነፍጥ ፣ ድስት ፣ ሻማ ፣ ላምባ ፣ እንዲሁም አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር ከሚሸጥበት ገበያ መሐል ገባ ።

"ምን ይሆን የሚፈልገው?"

"ምናልባት የከሰዓት በኋላ የእግር ሽርሽር ማድረጉ ይሆናል ። ቆይ እስቲ ያውልህ ሄደ ።"

ወደአጊአ ጀሮንዳ አቅጣጫ ዞሮ ወደክሲኖስ ምግብ ቤት ሲገሰግስ ተከተሉት ። ሁለቱም ሰላዮች ውጭ ቆመው የሚፈልገውን ሲያዝ ተመለከቱት ።

ሰላዮቹ አሁን እየሰለቻቸው መጥቷል ። "ብዙ ሳይቆይ ከዚህ እንደሚወጣ ተስፋ አደርጋለሁ ። እቤቴ ሄጄ ትንሽ ብተኛ ደስ ይለኛል ።"

"ተው እንጂ ነቅተህ ጠብቅ ። ከጠፋብን ኒኮሊኖ ድራሻችንን ያጠፋል ።"

"እንዴት ይጠፋብናል ትላለህ ? ሰውዬውኮ ግዙፍ ነው ።"

አንደኛው እንዲህ ሲል ሌላው ሰላይ ትኩር ብሎ ያየው ነበር ።

"ምን፣ ምንድንነው ያልከው?"

"እኔ ያልኩት ... "

"ተወው ግድ የለም" እንድ ሃሣብ ውልብ እንዳለበት ድምፁ ይገልጻል ። "ለመሆኑ ፊቱን አይተሃል?"

"አላየሁም ።"

"እኔምኮ አላየሁም ። ቲፍሎ ! እስቲ ና ።"

ሁለቱ ሰዎች ወደ ምግብ ቤቱ ገቡና ከነበረበት ጠረጴዛ አጠገብ ቆሙ ። አይተውት የማያውቁትን የእንግዳውን ሰው ፊት በጥሞና ተመለከቱ ።

ተቆጣጣሪ ኒኮሊኖ በጣም ተናዷል ። "ሪዞሊን እንዲከታተል ሦስት ቡድን አሰማርቼ እንዴት ይጠፋባችኋል?" ።

"ዓይናችንን በምን እንደጋረደ እንጂ ጌታዬ ። ወደታክሲ ሲገባ የመጀመሪያው ቡድን አይቶታል ። እና ..."

"እና ታክሲው ጠፋባችሁ ማለት ነው?"

"አየዩለም ጌታዬ ። ከታክሲው ሲወጣ አይተነዋል ። የወረደው እርሱ ነው ብለን ነበር ። የለበሰው ልብስ ከተነገረን ጋር አንድ ነው ። ሪዞሊ በታክሲው ውስጥ የተደበቀ ሌላ ተሳፋሪ አስቀምጠ ከእርሱ ጋር ልብስ ተለዋውጧል ። ስንከታተል የነበረውም እርሱን አልነበረም ።"

"ሪዞሊ በታክሲው አመለጠ ማለት ነዋ !"

"አዎ ጌታዬ ።"

"የታክሲውን ታርጋ ቁጥር ጽፋችኋል ?"

"አልጻፍንም ። አስፈላጊ አልመሰለንም ።"

"ያነኛችሁት ሰው ምን ዓይነት ነው ?"

"ሰውዬው ሪዞሊ ያረፈበት ሆቴል አስተናጋጅ ነው ። በሰው እየቀለደ መሆኑን ለአስተናጋጁ ገልጾ አንድ መቶ ዶላር ሰጠው ። ሰውዬው ከዚህ ውጪ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም ።"

ተቆጣጣሪ ኒኮሊኖ በኃይል ወደውስጥ ተነፈሰ ። "እና በእሁኑ ጊዜ

ሚስተር ሪዞሊ የት እንዳለ የሚያውቅ ማንም ሰው የለማ ?"

"አዎ ጌታዬ የሚያውቅ የለም ።"

ግሪክ ሰባት ዓቢይ ወደቦች አሏት ። እነርሱም ተሰሎንቄ ፣ ፓትራስ፣ ቮሎስ ፣ ኢጉሚኒትሳ ፣ ካቫላ ፣ አራክላዩንና ፒሮዩስ ናቸው ።

ፒሮዩስ ከአቴንስ ከተማ እምብርት በስተደቡባዊ ምዕራብ ሰባት ማይልስ ያህል ርቆ ይገኛል ። ፒሮዩስ የግሪክ ብቻ ሳይሆን እንደአውሮፓ ዓቢይ ወደብም ሆኖ ያገለግላል ። ወደቡ አራት ትላልቅ ክፍሎች ሲኖሩት ከእነኚህ ውስጥ ሦስቱ ለትላልቅ የሽርሽር ጀልባዎችና ለውቅያኖስ አቋራጭ መርከቦች የሚውሉ ናቸው ። አራተኛው የወደቡ ክፍል ሄራክልስ አገልግሎት የሚሰጠው ለፅቃ ጫኝ መርከቦች ነው ።

ቲኤሌ መልህቋን ከሄራክልስ ወደብ ጥላ ቆማለች ። ይህቺ ትልቅ የዕቃ መጫኛ መርከብ በጨለማ ውስጥ ስትታይ ለመሮጥ የተዘጋጀ እጅግ በጣም ግዙፍ የሆነ ጉማሬ መሰል አውሬ ትመስላለች ።

ቶኒ ሪዞሊ አራት ሰዎችን አስከትሎ ከወደቡ መድረክ ደረሰ ። ሪዞሊ ግዙፏን መርከብ አየና 'እሃ መጥታለችና ። እስቲ ወዳጃችን ዴሚሪስ ተሳፍሮባት እንደሆነ እንይ' አለ በአሳቡ ።

አብረውት ወደመጡት ሁለቱ ሰዎች ዞር ብሎ "ሁለታችሁ እዚሁ እንድትቆዩ እፈልጋለሁ ። ሁለታችሁ ደግሞ ከእኔ ጋር ኑ ። ማንም ሰው ከመርከቡ እንዳይወርድ ጠብቁ ።"

"እሺ ።"

ሪዞሊና ሁለቱ ሰዎች ወደቡንና መርከቡን በሚያገናኘው መሸጋገሪያ ላይ ተጓዙ ። ከመሸጋገሪያው ጫፍ እንደደረሱ አንድ መርከበኛ ወደ እነርሱ መጣና "ምን ልርዳችሁ?" ብሎ ጠየቀ ።

"ሚስተር ዴሚሪስን ለማነጋገር ነበር የመጣነው ።"

"ሚስተር ዴሚሪስ በመርከቡ ባለቤት ክፍል ውስጥ ነው ። ቀጠሮ አላችሁ?"

"አሃ የሰማሁት ልክ ነዋ !" ሪዞሊ ሳቀ ። "አዎ ቀጠሮ አለን መርከቢቱ ጉዞ የምትጀምረው በስንት ሰዓት ነው?"

"እኩለ ሌሊት ላይ ። ኑ ወደ እርሱ ልውሰዳችሁ ።"

"አመሰግናለሁ ።"

መርከበኛው ሚስተር ዴሚሪስ ያለበትን ሥፍራ ሲያሳያቸው ከፊት ፊት ሲጓዝ እነርሱም ተከተሉት ። ብዙ የመርከብ ውስጥ ክፍሎችን አለፉና መጨረሻው ላይ ሲደርሱ መርከበኛው ቆም ብሎ በሩን አንኳኳ ። ሪዞሊ ሰውዬውን ገፈተረና "እኛ እራሳችን እናንጋግረዋለን" ሲል በሩን በርግዶ ወደ ውስጥ ገባ ።

ክፍሉ ሪዞሊ ከገመተው በላይ ሰፊ ነው ። በክፍሉ ውስጥ አልጋ፣ ፎቴ ፣ ጠረጴዛና ሁለት ወንበሮች ይታያሉ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጧል ።

ቀና ብሎ ሪዞሊን ሲያየው ዴሚሪስ ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሳ ። ፊቱም ደም መሰለ ። "እዚህ ... እዚህ ምን ትሠራለህ?" ሲል ጠየቀው በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ።

"እኔና ጓደኞቼ ልንሰናበትህ ነው የመጣነው ኮስታ ።"

"እንዴት አወቅክ እኔ ...? ማለቴ እኔ ... እኔ ትመጣለህ ብዬ አልገመትኩም ነበር ።"

"እንዳልገመትክ እኔም እርግጠኛ ነበርኩ" አለ ሪዞሊ መለሰና ። ወደመርከበኛው ዞር ብሎ "አመሰግናለሁ" አለው ።

መርከበኛው ወጥቶ ሄደ ።

ሪዞሊ ወደዴሚሪስ ዞር አለ ። "ሽሪክህን ሳትሰናበት ወደውጭ ለመንዝ ታቅዳለህ እንዴ?"

ዴሚሪስ ቶሎ አለና "የለም ፣ በፍጹም ፣ እንደርሱ አይደለም ። የ... መጣሁት ፣ አንድ የማጣራው ነገር ስላለ ነው ። መርከቢቱ ጉዞ የምትጀምረው ነገ ጠዋት ነው ።" የእጁ ጣቶች መንቀጥቀጥ ጀመሩ ።

ሪዞሊ ወደዴሚሪስ ጠጋ አለ ። ለስለስ ባለ አነጋገር "ማሙሽ ኮስታ ፣ ትልቅ ስሕተት ፈጽመሃል ። ለማምለጥ መሞከርህ ምንም ዋጋ የለውም ፣ ምክንያቱም የትም ቦታ ብትሄድ ልትደበቅ አትችልም ። እኔና አንተ ቃል ተገባብተን ነበር ፣ ታስታውሳለህ? ቃል ኪዳን የሚያፈርሱ ሰዎች ምን እንደሚደርስባቸው ታውቃለህ? መጥፎ አሟሟት ይሞታሉ ፣ የከፋ አሟሟት" አለው ።

ዴሚሪስ ምራቁን ዋጥ አደረገ ። "ለብ ... ለብኝ ላነጋግርህ አንዴ ።"

ሪዞሊ ወደ ሁለቱ ሰዎች ዞር አለና "ውጪ ጠብቁኝ" አላቸው ።

ሰዎቹ ከወጡ በኋላ ሪዞሊ ወንበር ላይ ተቀመጠ ። "ባድራጉትህ በጣም ተበሳጭቻለሁ ኮስታ ።"

"እኔ እንዲህ ዓይነት ነገር አልፈልግም" አለው ዴሚሪስ ። "ገንዘብ አሰጥሃለሁ ተመኝተኸው ከማታውቀው በላይ ገንዘብ አሰጥሃለሁ ። ..."

"ስለምን ብለህ?"

"ከዚህ መርከብ እንድትወርድልኝ ።" በዴሚሪስ ፊት ላይ ትልቅ የተስፋ መቁረጥ መንፈስ ይነበባል ። "እንዲህ ልታደርግ አትችልም ። መንግሥት መርከቦቹን ሁሉ ይመርስብኛል ። ጎልውናዩ ጨርሶ ይጠፋል። እባክህ ተወኝ የፈለግከውን ሁሉ እሰጥሃለሁ ።"

ቶኒ ሪዞሊ ፈገግ አለ ። "የምፈልገውን ነገር ሁሉ አግኝቻለሁ ። ለመሆኑ ስንት መርከብ ነው ያለህ? ሃያ ? ሰላሳ ? እኔና አንተ ከእንግዲህ ሥራ ልናበዛባቸው ነው ። ከእንግዲህ ግድረግ ያለብህ አንድ ወይም ሁለት የወደብ ጣቢያዎችን መጨመር ነው ።"

"በኔ ... በኔ ላይ ምን በመፈፀም ላይ እያለህ እንደሆነ ይገባሃል?"

"እንድ ነገር ከማድረግህ በፊት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ቀደም አድርገህ ማወቅ ነበረብህ ።" ሪዞሊ ከተቀመጠበት ተነሳና "በል አሁን ናና ካርቴኑን አንጋግረው ። ከፍሎሪዳ ወደብ ወጣ አድርጉ መርከቢቱን እንዲያቆምልን መመሪያ ስጠው ።"

ዴሚሪስ አመነታ ። "እሺ ነገ ጠዋት ተመልሰህ ስትመጣ ..." አለ።

ሪዞሊ ሳቀ ። "አሁንማ ከዚህ አልንቀሳቀስም መሸዋወዱ አከተመ ። አንተ እኩለ ሌሊት ላይ ለመሸሽክ አቅደሃል ። እኔም አብሬህ ልሾልክ ነው። ሂሮይኑን አምጥተን እንጭነዋለን ። ስምንታችንን የበለጠ ለማጥበቅ ደግሞ ከመንግሥት ሙዚየም የወጣ ቅርስም እንጭናለን ። እነኚህን ዕቃዎች ደብቀህ በመርከብህ ወደዩናይትድ ስቴትስ ታስገባልኛለህ ። ልታታልለኝ በመሞከርህ መቀጣጫህ ይሄ ነው ።"

የዴሚሪስ ዓይኖች ፈጠጡ ። "ሌላ ... ሌላ ነገር የለም?" ጭንቅላቱን ነቀነቀና "ሌላ በዚህ ምትክ የማደርግልህ ነገር አይኖርም ...?"

ሪዞሊ ትከሻውን ቸብ—ቸብ አደረገና "አይዞህ የእኔ ሽሪክ በመሆንህ እንደምትደሰት አረጋግጥልሃለሁ" አለው ።

ሪዞሊ ወደ በሩ ሄዶ ከፈተው ። "መልካም ፣ መርከቡ ላይ እንጫነው" አለ ።

"የት እናስቀምጠው?" ሲሉ ጓደኞቹ ጠየቁት ።

በመርከቡ ላይ ዕቃውን ለመደበቅ የሚቻልባቸው በርካታ ሥፍራ

ምች አሉ ። ሆኖም የኮንስታንቲን ዲሚሪስ መርከብ በእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ስለማይጠረጠር ሪዞሊ ስለመደበቂያ ሥፍራ ይሆንን ያህል አልተጨነቀም ።

"በድንች ጆንያ ውስጥ ከትታችሁ በደንብ አሽጉትና ከመርከቡ የኋላ ክፍል አስገቡት ። ቅርሱንም አምጡና ለሚስተር ዲሚሪስ ስጡት ። በግሉ አስፈላጊውን እንክብካቤ ያደርግለታል ።" ዲሚሪስ ዓይኑ እንባ እንዳቀረረ ወደሪዞሊ ዞር ብሎ ተመለከተ ። "እንዲህ ቢሆን የሚያስቸግር ነገር አለ?" አለና ሪዞሊ ጠየቀው ።

ዲሚሪስ ለመናገር ፈልጐ ቃላት አጠሩት ።

"መልካም ወዳጀቼ" አለ ሪዞሊ ። "ቶሎ ቶሎ እንበል ።"

ሪዞሊ ወንበሩ ላይ ወደኋላው ተለጥጦ ተቀመጠ ። "ጥሩ ክፍል ነው ኮስታ ። እኔና ጓዶቼ ዕቃውን ይዘህ እዚህችው እንድትቆይ ልናደርግህ ነው ። ለራሳችን ሌላ ክፍል እንፈልጋለን ።"

"እመሰግናለሁ" አለ ዲሚሪስ ተስፋ በቆረጠ አነጋገር ። "በጣም ነው የማመሰግነው ።"

* * *

እኩለ ሌሊት ሲሆን ሁለት ጀልባዎች ትልቁን መርከብ ወደዋናው ባሕር እየመሩ አስገቡት ። ሂሮይኑ በመርከቡ ውስጥ ከድብቅ ሥፍራ ሲደረግ ቅርሱ ለኮንስታንቲን ዲሚሪስ ተሰጥቶታል ።

ቶኒ ሪዞሉ ከሰዎቹ መካከል አንዱን ጠራና "ወደራዲዮ ክፍሉ ሂድና መነጋገሪያውን ሽቦ በጣጥሰው ። ዲሚሪስ በራዲዮው ምንም መልእክት እንዲያስተላልፍ አልፈልግም" አለው ።

"እሺ ቶኒ"

የኮንስታንቲን ዲሚሪስ ቅስም ተሰብሯል ፤ ሆኖም ሪዞሊ እስከመ ጨረሻው ችላ ሳይለው በተጠንቀቅ ይገኛል ።

ሪዞሊ መርከቢቱ ጉዞዋን እስክትጀምር ድረስ እክል ያጋጥመኝ ይሆናል ብሎ ሰግቶ ነበር ። እንዲህ ይሳካልኛል ብሎ አልገመተም ነበር ። በዓለም ዝነኛ የሆነው ከበርቴው ኮንስታንቲን ዲሚሪስ ሽሪኩ ሆኗል ። 'ሽርክናህ ጀህነም ይግባ !' አለ ሪዞሊ በአሳቡ ። 'ሰውዬው በቁጥጥር ሥር ውሏል ። ከእንግዲህ መርከቦቹ በሙሉ ንብረቴ ናቸው ። አቀባባዮቹ

ሊያቀርቡልኝ የሚችሉትን አደንዛዥ ዕፅ እንደልቤ ልጭን እችላለሁ ። ሌሎቹ ኩንትሮባንዲስቶች ሄሮይናችንን ወደዩናይትድ ስቴትስ እንዴት አድርገን እናስገባ እያሉ ይጨነቁ ። እኔ እንደሆንኩ አሳክቼዋለሁ ። ከሙዚየሙ ውስጥ ያሉት ቅርሳ ቅርሶች ሌላው የወርቅ ማዕድኖቼ ሲሆኑ ሁሉም የግሌ ናቸው ። ሽሪኮቼ እነሱ በማያውቁት ነገር ብጠቀም ቅር አይላቸውም ።

ቶኒ ሪዞሊን እንቅልፍ እንደወሰደው ከወርቅ ስለተሰሩ መርከቦችና ቤተመንግሥት እንዲሁም ስለሸጋ አገልጋይ ኩረዳዎች ሕልም አለመ ።

ሪዞሊ ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነቃ አራቱን ጓደኞቹን ይዞ ቁርስ ሊመገብ ሄደ ። በርካታ የመርከቡ ሠራተኞች ቀደም ብለው ከቁርስ ቤቱ ገብተዋል ። አስተናባሪው እነርሱ ወዳሉበት ጠረጴዛ ተጠጋና "እንደምን አደራችሁ?" አለ ።

"ሚስተር ዲሚሪስ የታለ?" አለና ሪዞሊ ጠየቀ ። "ቁርስ አይበላም እንዴ?"

"ሚስተር ዲሚሪስ ክፍሉ ውስጥ ነው ያለው ። እንተና ጓደኞችህ የምትፈልጉት ማንኛውም ነገር እንዲቀርብላችሁ አዞናል ።"

"በጣም ጥሩ" ሪዞሊ ፈገግ አለ ። ለእኔ የብርቱካን ጭማቂ ፣ የእንቁላልና የሥጋ ጥብስ ። እናንተስ ወዳጀቼ?"

"እኛም አንተ እንዳዘዝከው ።"

ትዕዛዙን ለአስተናጋጁ ከሰጡ በኋላ ሪዞሊ ወደጓደኞቹ ዞሮ "እናንተ ልጆች ፣ ለሁሉም ነገር እርጋታ ይኑራችሁ ። መጣሪያችሁን ደግሞ ደበቅ አድርጉ ። ደጉችና ትሁቶች ሁኑ ። የሚስተር ዲሚሪስ እንግዶች መሆናችንን እንዳትረሱ" አለ ።

ያን ዕለት ዲሚሪስ በምሣም በእራትም አልመጣም ።

ሪዞሊ ሊያነጋገረው ወደክፍሉ ሄደ ።

ዲሚሪስ ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ ጠባብ በሆነችው የመርከቡ መስኮት ወደውጭ ይመለከት ነበር ። ፊቱ ገርጥቷል ፤ የደከመውም ይመስላል ።

ሪዞሊ “ሰውነትህ እንዳይደክም መብላት ይኖርብሃል ሽሪኬ ። እንድትታመምብኝ አልፈልግም ። ገና ብዙ የምንሰራው ሥራ አለ ። ወደዚህ ምግብ እንዲያመጡልህ ለአስተናባሪዎቹ ነግሬአቸዋለው” አለው።

ዴሚሪስ ብዙ አየር ወደውስጥ ሳበ ። “አልችልም—ግድ የለም ። እባክህ ውጣልኝ ።”

ሪዞሊ ሳቀና “እሺ ። ከእራት በኋላ ትንሽ ብትተኛ ይሻላል ፤ የደከመህ ትመስላለህ ።”

ሲነጋ ሪዞሊ ካፒቴኑን ለማነጋገር ሄደ ።

“ቶኒ ሪዞሊ እባላለው” አለው ንግግሩን ሲጀምር ። “የሚስተር ዴሚሪስ እንግዳ ነኝ ።”

“ አሃ ፤ አዎ ልታነጋግረኝ እንደምትመጣ ሚስተር ዴሚሪስ ነግሮኛል ። ምናልባት የጉዞ መሥመር ለውጥ ሊኖር ይችላል ብሎኛል ።”

“ትክክል ፤ ስለዚሁ እኔ አላውቅሃለሁ ። ለመሆኑ ከፍሎሪዳ የባሕር ጠረፍ አካባቢ የምንደርሰው መቼ ይመስልሃል ?”

“በግምት ከሦስት ሳምንት በኋላ ሚስተር ሪዞሊ ።”

“ጥሩ ፤ በኋላ እንገናኛለን ።”

ሪዞሊ ከዚያ ወጣና በመርከቡ ላይ መዘዋወር ጀመረ ። ይህንን ሆነ ሌሎቹን መርከቦች ከእንግዲህ እንደልቡ የሚያዝባቸው ንብረቶቹ ሆነ ዋል ። ዓለምም በቁጥጥሩ ሥር እንደሆነች ተሰምቶታል ። ከዚህ ቀደም ተሰምቶት በማያውቅ ከፍተኛ ፍንደቃ ሰውነቱ ረክቷል ።

በጉዞው ወቅት ምንም ችግር አላጋጠማቸውም ሪዞሊ ኮንስታንቲን ዴሚሪስን በየጊዜው ወደክፍሉ እየገባ ይጎበኘዋል ።

“መርከቡ ላይ ሴቶች መኖር ነበረባቸው” አለው ሪዞሊ ። እናንተ ካሪኮች ሴቶች አያስፈልጓችሁም ልበል?”

ዴሚሪስ ለጥያቄው ምላሽ አልሰጠም ።

ቀናቱ አንድ ሁለት እያሉ ወደፊት በመገስገስ ካለመብት ሥፍራ ሪዚሊን ሊያደርሱት እየታቀረቡ ናቸው ። ጉጉቱ በጣም አቅበጥብጦ ታል። ሳምንቱ አንድ ሁለት እያለ ሲከንፍ እነርሱም ወደ አሜሪካ አህጉር እየተጠጉ ሄዱ ።

ቅዳሜ ዕለት ምሽት ሪዞሊ በመርከቡ መደገፊያ ላይ ተደግፎ ወደውቅያኖሱ አሻግሮ ሲመለከት የመብረቅ ብልጭታ አየ ።

ከጓደኞቹ አንዱ ወደእርሱ መጣና “ሚስተር ሪዞሊ አስቸጋሪ የአየር ጣባይ ሳይገጥመን አልቀረም ። መቼም ጥሩ የመርከብ ተጓዥ እንደሆንክ እርግጠኛ ነኝ” አለው ።

ሪዞሊ ትከሻውን ነቀነቀና “ምንም አያስጨንቀኝም” ብሎ መለሰ ለት ።

ባሕሩ መናወጥ ጀመረ ። በግዕበሉ ግፊት መርከቡ አንዴ ባሕሩ ውስጥ እየጠለቀ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደላይ ይወጣ ነበር ።

ሪዞሊ እየተረበሸ መጣ ። ‘ለካ ጥሩ የመርከብ ተጓዥ አይደለሁም’ አለ በአሳቡ ። ‘ሆንኩ አልሆንኩ ምን ልዩነት ያመጣል?’ ሪዞሊ እንደሆነ ዓለምን ተቆጣጥሬአለሁ ብሎ ገምቷል ። በጊዜ ወደ ከፍሉ ገባና ለጥ አለ ።

ሕልምም አለመ ። በዚህኛው ሕልሙ የወርቅ መርከብና ራቁቷን ያለች ቆንጆ ልጃገረድ አላየም ። ሕልሙ በጣም አስፈሪ ነበር ። ጦርነት እየተካሄደ መድፍ ይተኮሳል ። የፈንጂ ድምፅ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው ።

ሪዞሊ ዓይኑን ገልጦ አልጋው ላይ ተቀመጠ ። ያለበት ክፍል ይወላወላል ። መረከቢቷ በግዕበል ተናውጣለች ። በመርከቡ መተላለፊያ ላይ ሰዎች መሯሯጣቸውን ከኮቴያቸው ድምፅ ለማወቅ ቻለ ። ምን አደጋ ደርሶ ይሆን?

ቶኒ ሪዞሊ ቶሎ ብሎ ከአልጋው ወረደና ወደኮሪዶሩ ወጣ ። የቆመበት ወለል ወደ አንድ አቅጣጫ ሲያዘነብል ሚዛኑን መጠበቅ ተሳነው ።

እየሮጡ በአጠገቡ ያልፉ ከነበሩት ሰዎች አንደኛውን “ምን ተፈጠረ?” አለና ጠየቀ ።

“ፍንዳታ መርከቧ በእሳት ተያይዛለች ። እየሰመጥን ነው ። ቶሎ ብለህ ወደ መርከቡ ወለል ብትወጣ ይሻላል ።”

“እየሰመጥን ነው…?” ሪዞሊ ጆሮውን ሊያምን አልቻለም ። እስካሁን ችግር አላጋጠመም ነበር ። ‘ይሁን ግድ የለም’ አለ ሪዞሊ በልቡ። ‘ይህኛው ጭነት ቢበላሽም ግድ የለኝም ። ወደፊት ብዙ መሥራት እችላለሁ ። የሁሉም ነገር ቁልፍ ዴሚሪስ ስለሆነ ሕይወቱን ማትረፍ ይኖርብኛል ። ዕርዳታ እንዲደረግልን ጥሪ እናስተላለፋለን ።’ ሲያስታው ሰው ለካ የሬድዮው ሽቦ እንዲበጣጠስ አዞ ነበር ።

ሚዛኑን ለመጠበቅ እየታገለ በመራመድ እንደምንም ከመርከቡ

ወለል ላይ ደረሰ ። ባሕሩ ፀጥ እያለ ማዕበሉም ቀለል ብሏል ።

ጨረቃዋ ወከክ ብላ ትታያለች ። ሌላ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ ፤ እንደገናም ተደገመ ።

መርከቢቱ የበለጠ ወደአንድ አቅጣጫ እያዘነበለች መጣች ። የኋለኛው የመርከቡ ክፍል በፍጥነት ባሕሩ ውስጥ እየሰጠመ ሄደ ። መርከበኞቹ የአደጋ ጊዜ ጀልባውን ለመጠቀም ሙከራ አድርገው ነበር ፤ ግን ሁሉም ነገር በፈጣን ሂደት ከቁጥጥር ውጪ ሆነ ። ዙሪያው በእሳት ተቀጣጥሏል ፤ ለመሆኑ ኮንስታንቲን ዴሚሪስስ ወዴት ይሆን?

ከዚያ ሪዞሊ ድምፅ ሰምቶ ቀና ሲል ከመርከቡ በላይ በአሥር ሜማርቀት ሄሊኮፕተር ስታንዣብብ ተመለከተ ። በሄሊኮፕተሯ መስኮት በኩል አንድ የሚያውቀውን ፊት አየና ትኩር ብሎ ሲመለከተው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሆኑን ተረዳ ። ዴሚሪስ ፈገግ ብሎ አየው ፤ በእጁም ያንን በቀላል ዋጋ የማይተመነውን ቅርስ ይዟል ። ሪዞሊ አእምሮውን ሰብሰብ አደረገና የተፈጸመውን ሁሉ እንደገና ለማስቃመስ ሞከረ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዚህ እኩለ ሌሊት እንዴት ሄሊኮፕተር ሊያገኝ ቻለ…?

ሪዞሊ ይሽኔ የተረዳው ነገር ቢኖር ውሀው እያሳሳቀው ይዞት በመሄድ ላይ መሆኑን ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከእርሱ ጋር በሽርክና ለመሥራት ምንም ፍላጐት አልነበረውም ። ከመጀመሪያውኑ ችግሩን ጠንሰሶ ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰው ያ ኬይሲ ዴሚሪስ ነው ። ዴሚሪስ ሸሽቶ ሊያመልጥ ነው ሲል ስልክ ያስደወለው ስፔሮስ ላምብሩ ሳይሆን ራሱ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ሪዞሊ ወደመርከቡ መጥቶ ከወጥመዱ እንዲገባ ያደረገውም ዴሚሪስ ነው ።

መርከቡ በውቅያኖሱ ውስጥ እየሰጠመ ሄደ ። ውሀው በመጀመሪያ እግሩን ሲያቀዘቅዘው ከዚያ ጉልበቱን ሲነካና ወደ አናቱም ሲያሻቅብ ሪዞሊን ተሰማው ። ግንም ሰው ምን እንደተፈጸመ ሊያውቅ የማይችል በት አሻራ እንኳ እንዳይቀር አድርጉ ዴሚሪስ ጠላቶቹን በሙሉ ንፍሮ አደረጋቸው ።

ሪዞሊ ቀና ብሎ ወደ ሄሊኮፕተሩ እያየ ጩኸቱን ቀጠለ ። "እባክህን ተመለስ! የፈለግከውን እሰጥሃለሁ ።" ነፋሱ ጩኸቱን ጠርጐት ሄደ ።

መርከቧ ሙሉ በሙሉ ከመስጠሟና ዓይኑ በጨውማው ውሃ ከመሸፈኑ በፊት ሪዞሊ ለመጨረሻ ጊዜ ያየው ሄሊኮፕተሯ ወደ ጨረቃው ስትምዘገዘግ ነበር ።

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ቅዱስ ሞሪዝ

ካተሪን ከመጠን በላይ ደንግጣለች ። ኪርክ ሪኖልድስ መሞቱን የብረዶ መንሸራተቻው ሥፍራ የሮንዶች አዛዥ የመቶ አለቃ ሃንስ በርግማን ሲነግራት ክፍሏ ውስጥ ፎቴ ላይ ተቀምጣ ፈዝዛ ትሰማ ነበር ። ምን ይናገር እንደነበረ ግን በውል አላጻመጠችውም ፤ መርዶው አደንዝዟታል ።

'ለኔ ወዳጅ የሚሆኑ ሁሉ ይሞታሉ' አለች በአሳቢ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ። 'በፊት ላሪ ሞተ ፥ አሁን ኪርክ ተደገመ ። ሌሎችም እንደኖኤሌ ፓጂ ፥ ናፖሊዮን ቾታስና ፍሬዴሪክ ስታቭሮስን የመሳሰሉ አልፈዋል ። ፍጻሜ የሌለው ቅዠት ።'

በአሳብ ባሕር በመዋኘት ላይ እያለች ሃንስ በርግማን ከሚወረውራቸው ቃላት መሐል እንዳንዱን ብቻ ማዳመጧን ታስታውሳለች ። "ሚሲስ ሪኖልድስ … ሚስተር ሪኖልድስ …"

ቀና አለችና በድካም አነጋገር "እኔ ሚስስ ሪኖልድስ አይደለሁም" አለች ። "ስሜ ካተሪን አሌክሳንደር ይባላል ። እኔና ኪርክ … ጓደኛማቾች ነበርን ።"

"ገባኝ ።"

ካተሪን በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። "እንዴት … እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ኪርክ እንኳ ነበዝ የበረዶ ላይ ተንሸራታች ነበር ።"

"እኔም ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ እዚህ ሸርተቴ ሲጫወት አይቼዋለሁ" በማለት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "ሚስስ አሌክሳንደር ፥ እውነቱን ለመናገር የተፈጸመው ነገር እኔንም አስገርሞኛል ። ሬሳውን ያገኘነው ቁልቁልቱ በመናዱ ባለፈው ሳምንት ተዘግቶ በነበረው የላጋልፕ የሸርተቴ መጫወቻ ሥፍራ ነው ። የተናደው በነፋስ ኃይልም ሊሆን ይችላል ። ግን በጣም አዝናለሁ ።"

ወለል ላይ ደረሰ ። ባሕሩ ፀጥ እያለ ማዕበሉም ቀለል ብሏል ።

ጨረቃዋ ወከክ ብላ ትታያለች ። ሌላ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ ፤ እንደገናም ተደገመ ።

መርከቢቱ የበለጠ ወደአንድ አቅጣጫ እያዘነበለች መጣች ። የኋለኛው የመርከቡ ክፍል በፍጥነት ባሕሩ ውስጥ እየሰጠመ ሄደ ። መርከበኞቹ የአደጋ ጊዜ ጀልባውን ለመጠቀም ሙከራ አድርገው ነበር ፤ ግን ሁሉም ነገር በፈጣን ሂደት ከቁጥጥር ውጪ ሆነ ። ዙሪያው በእሳት ተቀጣጥሏል ፤ ለመሆኑ ኮንስታንቲን ዴሚሪስስ ወዴት ይሆን?

ከዚያ ሪዞሊ ድምፅ ሰምቶ ቀና ሲል ከመርከቡ በላይ በአሥር ሜማ ርቀት ሄሊኮፕተር ስታንዣብብ ተመለከተ ። በሄሊኮፕተሯ መስኮት በኩል አንድ የሚያውቀውን ፊት አየና ትኩር ብሎ ሲመለከተው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሆኑን ተረዳ ። ዴሚሪስ ፈገግ ብሎ አየው ፤ በእጁም ያንን በቀላል ዋጋ የማይተመነውን ቅርስ ይዟል ። ሪዞሊ አእምሮውን ሰብሰብ አደረገና የተፈጸመውን ሁሉ እንደገና ለማስታወስ ሞከረ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዚህ እኩለ ሌሊት እንዴት ሄሊኮፕተር ሊያገኝ ቻለ…?

ሪዞሊ ይሽኔ የተረዳው ነገር ቢኖር ውሀው እያሳሳቀው ይዞት በመሄድ ላይ መሆኑን ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከእርሱ ጋር በሽርክና ለመሥራት ምንም ፍላጐት አልነበረውም ። ከመጀመሪያውኑ ችግሩን ጠንስሶ ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰው ያ ኬይሲ ዴሚሪስ ነው ። ዴሚሪስ ሽሽቶ ሊያመልጥ ነው ሲል ሰልክ ያስደወለው ስፔሮስ ሳምብሩ ሳይሆን ራሱ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ሪዞሊ ወደመርከቡ መጥቶ ከወጥመዱ እንዲገባ ያደረገውም ዴሚሪስ ነው ።

መርከቡ በውቅያኖሱ ውስጥ እየሰጠመ ሄደ ። ውሀው በመጀመሪያ እግሩን ሲያቀዘቅዘው ከዚያ ጉልበቱን ሲነካና ወደ አናቱም ሲያሻቅብ ሪዞሊን ተሰማው ። ማንም ሰው ምን እንደተፈጸመ ሊያውቅ የማይችል በት አሻራ እንኳ እንዳይቀር አድርጐ ዴሚሪስ ጠላቶቹን በሙሉ ንፍሮ እደረጋቸው ።

ሪዞሊ ቀና ብሎ ወደ ሄሊኮፕተሩ እያየ ጩኸቱን ቀጠለ ። "እባክህን ተመለስ! የፈለግከውን አሰጥሃለሁ ።" ነፋሱ ጩኸቱን ጠርጐት ሄደ ።

መርከቧ ሙሉ በሙሉ ከመስጠሟና ዓይኑ በጨውማው ውሃ ከመሸፈኑ በፊት ሪዞሊ ለመጨረሻ ጊዜ ያየው ሄሊኮፕተሯ ወደ ጨረቃው ስትምዘገዘግ ነበር ።

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ቅዱስ ሞሪዝ

ካተሪን ከመጠን በላይ ደንግጣለች ። ኪርክ ሪኖልድስ መሞቱን የበረዶ መንሸራተቻው ሥፍራ የሮንዶች አዛዥ የመቶ አለቃ ሃንስ በርግማን ሲነግራት ክፍሏ ውስጥ ፎቲ ላይ ተቀምጣ ፈዝዛ ትሰማ ነበር ። ምን ይናገር እንደነበረ ግን በውል አላዳመጠችውም ፤ መርዶው አደንዝዟታል ።

'ለኔ ወዳጅ የሚሆኑ ሁሉ ይሞታሉ' አለች በአሳቢ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ። 'በፊት ላሪ ሞተ ፤ አሁን ኪርክ ተደገመ ። ሌሎችም እንደኖኤሌ ፓጂ ፣ ናፖሊዮን ቾታስና ፍሬዴሪክ ስታቭሮስን የመሳሰሉ አልፈዋል ። ፍጻሜ የሌለው ቅዠት ።'

በአሳብ ባሕር በመዋኘት ላይ እያለች ሃንስ በርግማን ከሚወረውራቸው ቃላት መሐል አንዳንዱን ብቻ ማዳመጧን ታስታውሳለች ። "ሚሲስ ሪኖልድስ … ሚስተር ሪኖልድስ …"

ቀና አለችና በድካም እኔጋገር "እኔ ሚስስ ሪኖልድስ አይደለሁም" አለች ። "ስሜ ካተሪን አሌክሳንደር ይባላል ። እኔና ኪርክ … ጓደኛማቾች ነበርን ።"

"ገባኝ ።"

ካተሪን በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። "እንዴት … እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ! ኪርክ እንኳ ነበዝ የበረዶ ላይ ተንሸራታች ነበር ።"

"እኔም ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ እዚህ ሽርተቴ ሲጫወት አይቼዋለሁ" በማለት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "ሚስስ አሌክሳንደር ፣ እውነቱን ለመናገር የተፈጸመው ነገር እኔንም አስገርሞኛል ። ሬሳውን ያገኘነው ቁልቁልቱ በመናዱ ባለፈው ሳምንት ተዘግቶ በነበረው የላጋልፕ የሽርተቴ መጫወቻ ሥፍራ ነው ። የተናደው በነፋስ ኃይልም ሊሆን ይችላል ። ግን በጣም አዝናለሁ ።"

‘አዝናለሁ የሚል ቃል እንዴት ደካማና አስቀያሚ ቃል ነው’ አለች በልቧ ።

“ሚስስ አሌክሳንደር ቀብሩን በምን ዓይነት ሁኔታ እንድናካሄድ ልሽ ነው የምትፈልጊው?”

ሞትኮ ለሰው ልጅ የመጨረሻው አይደለም ። ከሞትም በኋላ የሚከናወኑ ሥነ ሥርአቶች አሉ ። የመቃብር ቦታ መምረጥና ማዘጋጀት ፣ የሬሳ ሳጥን መግዛት ፣ አበባ መሸመት ፣ ለዘመዶች ማሳወቅ ። ካተሪን መሥሀ ቃጣት ።

“ሚስስ አሌክሳንደር?”

“የግሪክ ቤተሰቦቹ እንዲያውቁት አድርግ” አለች ካተሪን ቀና ብላ።

“አመሰግናለሁ ።”

ወደ ለንደን ስትመለስ ሐዘኗ የከፋ ነበር ። ከኪርክ ጋር ወደተራራው ስትመጣ ወደ አዲስ ሕይወት የመግቢያ በር ይሆነኛል ብላ ገምታ ነበር ።

ኪርክን በጣም ጨዋና ታጋሽ ሰው ሆኖ አግኝታዋለች ። ‘አብሬው ተኝቼ ቢሆን ኖሮ ምን ነበረበት?’ አለች ካተሪን በአሳቧ ። ‘ግን ያም ቢሆን ምን ፋይዳ ሊኖረው ፣ ምን ዓይነት የተረገምኩ ገሬ ፍጡር ነኝ፣ ወደኔ የሚቀርቡትን ሁሉ የማጠፋ ሴት ።’

ወደ ለንደን እንደተመለሰች ልቧ በሐዘን በመነካቱ ወዲያውኑ ሥራ ለመግባት አልቻለችም ። ማንንም ሳታይና ሳታነጋግር እቤቷ ቁጭ አለች። የቤት ሠራተኛዋ አና ምግብ እያዘጋጀች ወደካተሪን መኝታ ቤት ብትወስድላትም ምግቡ ሳይነካ ነው የሚመለሰው ።

“አንድ ነገር መቅመስ አለብሽ ሚስስ አሌክሳንደር ።”

ስለምግብ ማሰቡ እራሱ ካተሪንን ያሳምማት ነበር ።

ካተሪን በሚቀጥለውም ቀን ባሰባት ። ደረቷ በብረት የታመቀ ይመስል መተንፈስ ተሳናት ።

‘በእንዲህ ዓይነት ልቀጥል አልችልም’ አለች ካተሪን በአሳቧ ። ‘አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል ።’

ከኤቪሊን ኬይ ጋር ተወያየች ። “ለተፈጸመው ሁሉ ጥፋተኛዋ እኔ ነኝ ።”

“የምትናገሪው ስሜት አይሰጥም ካተሪን ።”

“ስሜት እንደማይሰጥ አውቃለሁ ፣ ግን ምን ላድርግ? የጎሊና ፀፀት ይሰማኛል ። ስለዚህ ጉዳይ የማነጋግረው ሰው ያስፈልገኛል ። ምናልባት የሥነ አዕምሮ ሐኪም ባገኝ ። ...”

“እኔ የማውቀው በጣም ጥሩ የሆነ ሐኪም አለ” አለች ኤቪሊን ። “ዊምም የሚመላለሰው እርሱ ዘንድ ነው ። አላን ሃሚልተን ይባላል ። ሕይወቷን ልታጠፋ የነበረች አንዲት ጓደኛዬ የዶክተር ሃሚልተንን ሕክምና ካገኘች በኋላ በደህና ሁኔታ ላይ ትገኛለች ። ሄደሽ ልታነጋግሪው ትፈልጊያለሽ?”

‘እብደኝሽ ቢለኝስ? እውነት እብድ ሆኜ ከተገኘሁስ’ ስትል ካሰበች በኋላ “አዎ አነጋግሪው” አለቻት ለኤቪሊን በግድየለሽነት ።

“ሥራ ስለሚበዛበት እኔ ቀጠሮ እይዝልሻለሁ ።”

“አመሰግናለሁ ኤቪሊን ። ውለታ ከፋይ ያድርገኝ ።”

ካተሪን ወደዊም ቢሮ ሄደች ። ‘ስለኪርክ ለማወቅ ይፈልግ ይሆናል’ አለች በአሳቧ ።

“ዊም ኪርክ ሪኖልድስን ታስታውሳለህ? ከጥቂት ቀናት በፊት የበረዶ ሸርተቴ ሲጫወት አደጋ ደርሶበት ሞተ ።”

“አዎ ፣ በቄስት ሚኒስትር — ዜሮ ፣ አራት ፣ ሰባት ፣ አንድ” አላት ።

ካተሪን ዓይኗን አርገበገበችና “ምን?” አለችው ። ስታስታውሰው ለካ ዊም የሚናገረው የኪርክን መኖሪያ ቤት የስልክ ቁጥር ነው ።

በቃ ፣ ለዊም ሰው ግለት ያችን ታክል ብቻ ናት? በጥቂት ቁጥሮች መግለጽ? ለመሆኑ ለሰው ልጅ ምንም ስሜት የለውም? በእውነት ሰዎችን ለመውደድና ለመጥላት ወይም ሊራራላቸው ስሜት የሚባል ነገር በውስጡ አልተፈጠረበትም?

‘ምናልባት ከእኔ ሳይሻል አይቀርም’ ኣለች ካተሪን በአሳቧ ። ‘ምክንያቱም እኔን ከሚያሰቃየኝ ጭንቀት እርሱ ነፃ ነው ።’

ካተሪን ዶክተር ሃሚልተንን በሚቀጥለው ዓርብ እንድታነጋግር ኤቪሊን ቀጠሮ ያዘችላት ። ኤቪሊን ያደረገችውን ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለመንገር ፈልጋ ነበር ። ሆኖም ጉዳዩ አስፈላጊ ስላልሆነ ለምን እረብሸዋለሁ ብላ ተወች ።

የአላን ሃሚልተን ቢሮ የሚገኘው ከዊምፖል ጎዳና ላይ ነው ። ካተሪን በስጋትና በንዴት መንፈስ ለመጀመሪያው ቀጠሮዋ ተገኘች ። የሰጋችው ስለእኔ ምን ይል ይሆናል ብላ በማሰቧ ሲሆን ንዴቷ የመነጨው ደግሞ እራሷ በራሷ ለችግሯ መፍትሄ መሻት ሲገባት የማታውቀው ባዳ እንዲያቃልልላት በመተማመኗ ነበር ።

ከመስተዋት የተሠራ ክፍል ውስጥ የተቀመጠችዋ አስተናጋጅ “ሚስስ አሌክሳንደር ፣ ዶክተር ሃሚልተን እየጠበቀሽ ነው” አለቻት ።

‘እኔስ ተዘጋጅቻለሁ?’ አለች ካተሪን በአሳቧ ። መላ ሰውነቷ ተረብሿል ። ‘እዚህ ምን አደርጋለሁ? እራሱን እንደ እግዜር ለሚቆጥር ተመጻዳቂ እራሴን አሳልፌ አልሰጥም ።’

ካተሪን አስተናጋጇን እንዲህ አለቻት ← “አሳቤን ቀይሬአለሁ ። ዶክተር ማነጋገር የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም ። ቀጠሮ የተያዘበትን ሒሳብ ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ ።”

“እረ፣ እንዴ ቆዪኝ ።”

“ግን ... ”

አስተናጋጅዋ ወደዶክተሩ ቢሮ ገባች ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቢሮው በር ተከፍቶ አላን ሃሚልተን ከውስጥ ወጣ ። ዕድሜው በመጀመሪያዎቹ አርባዎች አካባቢ ሲሆን ረዘም ያለ ወርቅማ ፀጉር ያለው የዓይኑ ብሌን ወደ ሰማያዊነት ያዘነበለና ቁመናው የማይከብድ ሰው ነው ።

ካተሪንን አያትና ፈገግ አለ ። “በቃ ቀኑ የኔ ነው በይኛ” ብሎ ተናገራት ።

ካተሪን ግንባሯን ቋጠረችና “ምን ...?” ብላ ጠየቀችው ።

“ምን ያህል ጎበዝ ሐኪም እንደሆንኩ አላወቅኩም ነበር ። ገና ከማስተናበሪያ ክፍሌ ስትደርሺ በሽታሽ ይልቀቅሽ፣ ይህ ተመዝግቦ የሚያዝ ነው ።”

ካተሪን ላለመረታት “ይቅርታ ተሳስቼ ነው ። ዕርዳታ የሚያስፈል ገኝ አይመስለኝም” ስትል መለሰች ።

“ይህንን በመስማቴ ደስ ብሎኛል” አላት አላን ሃሚልተን መልሶ ። “ሁሉም በሽተኞቼ እንዲህ በሆኑልኝ ምንኛ ደስ በተሰኘሁ ። ከመጣሽ ዘንዳ ሚስስ አሌክሳንደር ፣ ለምን ወደውስጥ ገብተሽ ለትንሽ ጊዜ አብረን ቡና አንጠጣም?”

“እመሰግናለሁ ። አይ እኔ አልጠጣም ...”

“ብዙ አላቆይሽም ።”

ካተሪን እመነታችና “እሺ ፣ ለደቂቃ ያህል” ብላ ተከትላው ወደቢሮው ገባች ። ቢሮው ቀለል ያለ ገጽታ ያለው ሆኖ ከቢሮነት ይልቅ የመኖሪያ ቤት ሳሎንነት ድባብ ይታይበታል ። በግድግዳዎቹ ላይ ልብ የሚመስጡ ጥቅሶች ተሰቅለዋል ። አንዲት ቆንጆ ሴት ከሕጻን ልጇ ጋር የተነሳችው ፎቶግራፍ በጠረጴዛው ላይ ተደርጓል ።

‘መልካም እንግዲህ የተዋበ ቢሮና ጥሩ ቤተሰብ አለው ። ምን ይሁን ታዲያ?’ አለች በልቧ ።

“እባክሽ ቁጭ በይ” አላት ዶክተር ሃሚልተን ። “ቡናው በደቂቃ ውስጥ ይደርሳል ።”

“ዶክተር ጊዜህን ባልገድልብህ ጥሩ ይመስለኛል ። እኔ ...”

“ግድየለም አትጨነቂ” ብሎ በአንድ አነስተኛ ወንበር ላይ ተቀመጠና ፊቷን ያጠና ጀመር ።

“ብዙ ችግሮች ደርሰውብሻል” አላት በሀዘኔታ ።

“ምን እንደደረሰብኝ የምታውቀው ነገር ምን አለ?” አለች ካተሪን በቁጣ ።

“ኤቪሊን በቅዱስ ሞሪዝ የሆነውን ነገር አጫውታኛለች ። በጣም አዝናለሁ ።”

‘ያ የማልወደው አስጠሊ ቃል እንደገና መጣ?’ አለች በልቧ ።

“እውነት አዝነህል? ችሎታ ያለህ ሐኪም ከሆንክ አስቲ ኪርክን መልሰህ ሕይወት ዝራበት ።” ስቃይና ጭንቀቷ ፈንቅሎ መውጣት ጀምሯል ። ካተሪን እራሷን መቆጣጠር ተሳናትና እየተብረከረከች መነፍረቅ ጀመረች ።

“ተወኝ” አለች እያለቀሰች “ተወኝ ።”

አላን ሃሚልትን ሳይናገር ተቀምጦ ያያት ነበር ።

ካተሪን ልቅሶዋ እየቀነሰ ሲመጣ በሀፍረት “በጣም አዝናለሁ ፣ ይቅርታ አድርግልኝ ። አሁን መሄድ አለብኝ ።” ብላ ተነስታ ወደ ወንበሩ መራመድ ጀመረች ።

“ሚስስ አሌክሳንደር ፣ ልረዳሽ እንደምችል እርግጠኛ አይደለሁም፣ ግን ልሞክር እፈልጋለሁ ። ደግሞ የማደርገው ማንኛውም ነገር ጨርሶ የማይጎዳሽ መሆኑን ቃል እገባልሻለሁ ።”

ካተሪን እያመነታች በሩ አጠገብ ቆመች ። ዓይኗ እንባ እንዳቀረረ ዞር ብላ አየችውና “ምን እንደነካኝ አላውቅም” አለች በማንሾካሾክ ። “ጨርሶ የጠፋሁ ይመስለኛል ።”

አላን ሃሚልተን ከተቀመጠበት ተነሳና ወደቆመችበት ሄደ ። “ታዲያ ከጠፋሽበት ልናገኝሽ ለምን አንሞክርም? ይህንን ለማሳካት ደግሞ አብረን ጥረት እናድርግ ። እስቲ ቁጭ በዪና ቡናውም ደርሶ እንደሆነ ልጠይቅ ።”

ከክፍሉ ከወጣ አምስት ደቂቃ አልፎታል ። ካተሪን እዚያው በተቀመጠችበት ሆና እንዴት አድርጎ አቀዝቅዞ እንድትቆይ እንዳደረጋት ገረማት ። ሰዎችን የማብረድ ጥበብ አለው ። የማረጋጋት ችሎታ እንዳለው ከሁኔታው ይስታውቃል ።

‘ሊረዳኝ ይቻል ይሆናል’ አለች ካተሪን በአሳቧ ።

አላን ሃሚልተን ሁለት ፌንጃል ቡና ይዞ ወደቢሮው ተመለሰ ። “ወተትና ስኳር ይደረግበት?”

“የለም አመሰግናለሁ ።”

ከፊት ለፊቷ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠ ። “ጓደኛሽ የበረዶ ላይ ሽርተቴ ሲጫወት አደጋ ደርሶበት የሞተ መሰለኝ” አላት ።

ስለዚያ እንስቶ መናገር ይዘገንናታል ። “አዎ ፣ ተንዶ ከአገልግሎት ውጪ በሆነ መንሸራተቻ ሥፍራ ነው ሞቶ የተገኘው ። ኃይለኛ ንፋስ መስለኝ የናደው ።”

“በጣም የሚቀርብሽ ሰው በሞት ሲለይሽ ይህ የመጀመሪያ ጊዜሽ ነው?”

ይህንን ጥያቄ እንዴት አድርጋ ትመልስ? አይደለም ባለቤቴና ዕቁባቱ ሲገድሉኝ በመሞከራቸው ተረሽነዋል ። እኔን የቀረበ ሁሉ ይሞታል ብላ ትገረው? በጣም ይሰቀጥጣል ። ሐኪሙ ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ ለጥያቄዋ የሚያረካው መልስ ግን የላትም ። ‘ደግሞ በሕይወቴ ምን አገባው? አሁንስ ጠላሁት’ አለች በልቧ ።

አላን ሃሚልተን ከፊቷ ላይ ከፍተኛ ንዴት አነበበ ። ርዕስ ለመለወጥ ያህል “ዊም እንዴት ነው?” ብሎ ጠየቃት ።

ጥያቄው ካተሪን የነበረችበትን ሁኔታ ከመቅጽበት እንድትረሳው አደረጋት ። “ዊም? ደህና ነው ። የአንተ በሽተኛ እንደሆነ ኤቬሊን ነገረችኝ ።”

“እም”

“ባሕሪው በምን ምክንያት እንዲህ እንደሆነ ልትገልጥልኝ ትችላለህ?”

“ዊም በመጀመሪያ ወደእኔ የመጣው በየጊዜው ከሥራ በመባረሩ ነበር ። ሰውዬው የተለየ ባሕሪ ነው ያለው ። በሰው ልጅ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አለው ። ለምን እንዲህ ሊሆን እንደቻለ ለጊዜው ለማወቅ አልቻልኩም ። ግን ሰዎችን ይጠላል ። ከሰው ጋር ለመቀራረብ ችግር አለበት ።”

ካተሪን ኤቬሊን የነገረቻትን አስታወሰች ። ‘ሰውዬው ስሜት የሚባል ነገር አልተፈጠረበትም ። ከማንም ጋር ሊቀራረብ አይችልም ።’

“ግን ዊም በሒሳብ በጣም ጎበዝ ነው” አለ አላን ሃሚልተን። ንግግሩን በመቀጠል “አሁን የሚሠራው ይህን ችሎታውን ሊጠቀምበት በሚችልበት ሥፍራ ነው ።”

ካተሪን ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። “እንደርሱ ዓይነት ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም ።”

አላን ሃሚልተን ቀና አለና “ሚስስ አሌክሳንደር” አላት ። “ጎሊና የሚያቆስል ነገር እንዳጋጠመሽ አውቃለሁ ። ችግሩን ላቃልልሽ ብሞክርስ?”

“እ… እንጃ” አለች ካተሪን ። “ተስፋ የሌለው ነገር ይመስለኛል።”

“እንዲህ የምታስቢ ከሆነማ የትም ለመድረስ አንችልም ።” አላት አላን ሃሚልተን ። ልብ በሚሰርቅ ፈገግታ “ለምን ሌላ ቀጠሮ አንይዝም? ያኔ በውይይታችን ማብቂያ ላይ የምትጠዪኝ ከሆነ መገናኘታችንን እናቆማለን ።”

“ያን ያህል አልጠላህም” አለችው ካተሪን በይቅርታ ስሜት።

አላን ሃሚልተን ተነስቶ ወደጠረጴዛው ሄደና የቀጠሮ መስጫ አጀንዳውን ተመለከተ ። አጀንዳው ሙሉ ነው ።

“የሚቀጥለው ሰኞ ቢሆንስ?” አለና ጠየቃት ። “ከቀኑ በሰባት ሰዓት ።” ሰባት ሰዓት የምሳ መመገቢያ ጊዜው ሲሆን ያን ዕለት ምሳውን ሊተወው ፈልጓል ።

ካተሪን አሌክሳንደርን ካደረባት ከፍተኛ ጭንቀት ሊያላቅቃት አቅሙ የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆኗል ።

ካተሪን ለረዥም ጊዜ ቀና ብላ አየችው “እሺ ።”

“መልካም ፣ እንግዲህ በቀጠሮው ዕለት እንገናኛለን” አለና

አድራሻው ያለበትን ካርድ ሰጣት ። “ከዚያ ወዲህ ልታገኚኝ ከፈለግሽ የቢሮዬና የቤቱ ስልክ ቁጥር ካርዱ ላይ አለልሽ ። እንቅልፋም ብሆንም መቀስቀሱን አትስጊ ።”

“እመሰግናለሁ ።” አለችው ካተሪን ። “ሰኞ እመጣለሁ ።”

ካተሪን ከቢሮው ለትወጣ ዶክተር አላን ሃሚልተን ዝም ብሎ እያትና በአሳቡ ‘ሁሉ ነገሯ ተሰባሪ ይመስላል ፤ ውብ ናት ። ስለዚህ ጥንቃቄ ላደርግ ይገባኛል’ አለ ። ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ፎቶግራፍ እያየ ‘አንጂላ ምን ታስብ ይሆን’ አለ በልቡ ።

እኩለ ሌሊት ላይ የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስልክ ጠራ ። ስልኩን አንስቶ እንደሰማ በመገረም ተመላ ።

“ቲኤሌ ሰመጠች ነው የምትሰኝ? እኔ አላምንም ።”

“አዎ ሚስተር ዴሚሪስ የባሕር ጠረፍ ጠባቂው ጥቂት ስብርባሪ ነገሮችን ብቻ ነው ያገኘው ።”

“በሕይወት የተረፉ ሰዎች አሉ?”

“ማንም አልተረፈም ጌታዬ ። ሁሉም ሰጥመዋል ።”

“በጣም አሰቃቂ ነገር ። እንዴት ሊሆን እንደቻለ የሚያውቅ ሰው አለ?”

“ማንም የሚያውቅ አይመስለኝም ጌታዬ ። መረጃ ሁሉ አብሮ ከባሕሩ ሰምጧል ።

“ባሕሩ” አለ ዴሚሪስ በማጉመትመት “ምህረት የለሹ ጨካኝ ባሕር እነዚያ ሁሉ ጉብዛዝት እንዴት ሕይወታቸውን እንዳጡ ማሰቡ እራሴ ይሰቀጥጣል በሉ እደጋውን ለኢንሹራንስና ለሌሎችም ለሚመለከታቸው አሳውቁ ።”

ታሪካዊውን ቅርስ በግል የቅርስ መሰብሰቢያ ክፍሉ ውስጥ አኖረው ። አሁን እንግዲህ ዋርሳው የሚቀጣበትም ጊዜ ነው ።

ምዕራፍ አሥራ ስምንት

ስፒሮስ ላምብሩ የኮንስታንቲን ዴሚሪስን መታሰር ለመስማት በጉጉት ይቅበጠበጣል ። ሬዲዮውን ከቢሮው ውስጥ ከፍቱን ትቶ ሲያዳምጥ ይውላል ። በየዕለቱ የወጡትን ጋዜጦች በሙሉ አስመጥቶ አንብቧቸዋል። ‘እስካሁን አንድ ነገር መስማት ነበረብኝ’ አለ ላምብሩ በአሳቡ ። እስካሁን ፖሊሶች ዴሚሪስን ማሰር ነበረባቸው ። እደንዛዥ ዕፁን ዴሚሪስ እንደሚያጓጉዝለት ቶኒ ሪዞሊ ለስፒሮስ ነግሮት ፣ ስፒሮስም ስሙን ደብቆ ለአሜሪካ ጉምሩክ ነገሩን አስታውቋል ።

‘እስካሁን ሳይዙት እልቀሩም ። ታዲያ ጋዜጦቹ ዜናውን ለምን ሳያወጡት ቀሩ?’

ኢንተርኮሙ የደወል ጥሪ አሰማ ።

“ሚስተር ዴሚሪስ በሁለተኛው መሥመር ላይ ሊያነጋግርህ ይፈልጋል ።”

“ሚስተር ዴሚሪስን የሚፈልግ ሰው ነው የደወለው?”

“አይደለም ሚስተር ላምብሩ ። ስልኩን የደወለው እራሱ ሚስተር ዴሚሪስ ነው ።” ፀሐፊዋ የተናገረቻቸው ቃላት በሰውነቱ ውስጥ የቅካዜ ስሜት ረጩ ።

‘ሊሆን አይችልም!’ ላምብሩ በብስጭት የስልኩን እጀታ አነሳ ። “ኮስታ ነህ?”

“ስፒሮስ ። እንዴት ነህ ጃል?” የዴሚሪስ ድምፅ ደስተኛ ይመስል ነበር ። “ደህና ፣ ደህና ። የት የነው ያለኸው?”

“እዚሁ አቴንስ ውስጥ ነኝ ። ዛሬ ምሳ እንዴት ነው? ጊዜ ይኖርሃል?”

ላምብሩ የማይቀርበት የምሳ ቀጠሮ ነበረው ፤ ግን “አዎ ይቻላል” ሲል መለሰለት ። “ጥሩ በሰምንት ሰዓት ክበቡ ውስጥ እንገናኝ ።”

ላምብሩ እጁ እየተንቀጠቀጠ የስልኩን እጀታ መልሶ አስቀመጠው። ‘ስለ እግዜር የተሳሳትነው የቱጋ ይሆን?’ እንግዲህ የተፈጸመውን ሁሉ በቅርብ ጊዜ ሊያውቀው ነው ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሰላሳ ደቂቃዎች ያህል ስፒሮስን አስጠበቀው ። ዘግይቶ እንደመጣ ‹‹በመዘግየቴ ይቅርታ!›› አለው ።

‹‹ግድ የለም ።››

የሰሞኑ ሁኔታ በዴሚሪስ ላይ ያስከተለው ለውጥ ካለ ብሎ ስፒሮስ ላምብሩ በጥሞና አጠናው ። ምንም ለውጥ አይታይበትም ።

‹‹ርቦኛል›› አለ ዴሚሪስ በፈገግታ ። ‹‹እንተስ? እስቲ የዕለቱን የምግብ ዝርዝር እንመልከት›› አለና ዝርዝሩን በዓይኑ ቃኘው ።

‹‹እሃ ፡ ስትሪዳ ። ስፒሮስ በዓሣ እንጀምር!››

‹‹የለም አይመስለኝም›› አለ ። አሁንም ምንም ምግብ አላሰኘውም። ዴሚሪስ ተደላች ለመምሰል ሲሞክር ላምብሩን ግን ቀፎታል ።

ምግብ ካዘዙ በኋላ ‹‹ላመሰግንህ እወዳለሁ ስፒሮስ›› አለ ዴሚሪስ። ስፒሮስ ትኩር ብሎ አየው ። ‹‹ስለምን?››

‹‹ስለምን? ሚስተር ሪዞሊ የተባለውን ጥሩ ደንበኛ ስለላክልኝ ።››

ላምብሩ በምላሱ ከንፈሩን ጠረገ ። ‹‹ተ….ተገናኝታችሁ ነበር?››

‹‹ታዲያስ ወደፊት ብዙ የንግድ ሥራ አብረን ለመሥራት ተዋውለናል›› አለና ዴሚሪስ ሳቀ ። ‹‹ምን ያደርጋል ታዲያ የሚስተር ሪዞሊ ጉዳይ አበቃለት ።›› ስፒሮስ ደንገጥ አለ ። ‹‹ምን ማለትህ ነው?›› የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ድምፅ ጠንከር እያለ መጣ ። ‹‹ቶኒ ሪዞሊ ሞቷል ማለቴ ነው።››

‹‹እንዴት … ምን ሆነና?››

‹‹አደጋ አጋጠመው ስፒሮስ›› ብሎ የዋርሳውን ዓይን ትኩር ብሎ ይመለከት ነበር ። ‹‹እኔ ላይ ሽርና ደባ ለመፈጸም የሚጥር ሁሉ እንደሚደርስበት አደጋ ዓይነት ።››

‹‹እኔ ምንም … እኔን ምንም አልገባኝም ። አንተ …››

‹‹አልገባህም? አንተ ልታጠፋኝ ሞክረህ ነበር ግን አልተሳክልህም ፡ ሙከራው ቢሳካልህ ምንኛ በታደልክ ነበር?››

‹‹ስለ … ስለምን እንደምታወራ አልገባኝም ።››

‹‹አልገባህም ስፒሮስ?›› አለና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፈገግ አለ ። ‹‹በቅርቡ ይገባሃል ። መጀመሪያ ግን የማጠፋው እህትህን ነው ።››

‹‹ጓጓው ቀረበ ።››

‹‹አሃ!›› አለ ዴሚሪስ ። ‹‹በጣም ይሳፍጣል ፡ በል ብላ ።››

እንደተለያዩ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከላምብሩ ጋር ባደረገው ግንኙ

ነት ከፍተኛ እርካታ ተሰማው ። የስፒሮስ ላምብሩ ሞራል ደግሞ በጣም አድርጉ ተነክቷል ። ዴሚሪስ ፡ ላምብሩ እህቱን ምን ያህል በጣም አድርጉ እንደሚወዳት ስለሚያውቅ ሁለቱንም በጋራ ለማጥቃት ቆርጦ ተነስቷል።

ግን በቅድሚያ የሚፈጽመው ጉዳይ አለ ። የካተሪን አሌክሳንደር ጉዳይ። ከኪርክ ሞት በኋላ የተሰማትን ሞንቶት ደውላ ነግራው ነበር ።

‹‹ነገሩ … ነገሩ በጣም ያንገበግባል ።››

‹‹በጣም አዝናለሁ ካተሪን ኪርክን ምን ያህል ትወጂው እንደነበር ይገባኛል ። እደጋው ሁሉታችንንም ጥሩ ወዳጅ አሳጥቶናል ።›› ‘ስሌቴን መቀየር አለብኝ ።’ አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ‘ለራሬና ምንም ጊዜ አይኖረኝም ። በጣም መጥፎ ነገር ።’ በናኤሌ ፓጂና በላሪ ዶግላስ ላይ ከተፈጸመው ጋር ልታነካካው የምትችልና አሁን በሕይወቷ የተረችው ካተሪን ብቻ ናት ። ይህን ያህል ጊዜ በሕይወት እንድትቆይ ግድረጉም ስሕተት ነው ። እርሷ በሕይወት እስከቆየች ድረስ ዴሚሪስ የፈጸመውን ወንጀል ለማረጋገጥ ለሚፈልግ ማስረጃ ትሆነዋለች ። ከሞተች ግን ከአደጋ ነፃ ይሆናል ።

ዴሚሪስ ከጠረጴዛው ላይ ያለውን ስልክ አነሳና የሆነ ቁጥር ደወለ። ተቀባይ እንዳገኘ ‹‹በሚመጣው ሰኞ ኮውሉን ውስጥ ስለምሆን እዚያው ተገኝ›› አለና ስልኩን መልሶ ዘጋው ።

በግንብ በታጠረችው ከተማ ውስጥ በምትገኘዋ የዴሚሪስ የግል ቤት ውስጥ ሁለቱ ሰዎች ተገናኙ ። ‹‹በድንገት የደረሰ አደጋ መሆሰ አለበት ፡ እንዲህ ለማድረግ ይከብድሃል?›› ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጠየቀ ።

ተጠያቂው ጥያቄውን እንደሰድብ ነው የቆጠረው ። ደሙ ፈላ ። መንገደኛ እንጂ በመስኩ የተካነ ሰው እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አይጠየቅም ። በአሽሙር እንዲህ ብሎ ሊመልሰለት ፈልጉ ነበር ። ‘የሚከብደኝ አይመስለኝም ። ከረጅም የርቅ ደረጃ ላይ ወድቃ እንገቷን የተቀጨች ለማስመሰልም አይሳነኝም ። ግርሴሊስ ባለው ደናቸ አግካይነት ወይንም ሰክራ ፡ በገላ መታጠቢያ ገንዳዋ ውስጥ ሰጥማ እንደሞተች ለማስመሰል እችላለሁ ። በግስታድ ፡ በወራጁ አግካኝነት ፡ ወይንም ሄርይን ከመጠን

በላይ ወስዳ እንደሞተች ። ሦስቱ የተቀነባበሩ ዘዴዎች እነኚሁ ሲሆኑ ፣ ሲጋራዋን ሳታጠፋ እንቅልፍ እንደወሰዳትም ለማስመሰል ይቻላል ።' ፓሪስ ውስጥ በኤል ሆቴል ያለውን ስዊድናዊ የመረጃ ሰው አስታወሰ ። 'ክቤት ውጭ ቢሆን አይሻልም? በመኪና ወይንም በአይሮፕላን አደጋ እንድትሞት ወይንም በባሕር ውስጥ እንድትሰጥም ለማድረግ እችላለሁ።' ሆኖም ግን ከፊት ለፊቱ የተቀመጠውን ሰው በመፍራት ይህንን አላቡን አውጥቶ ሊናገር አልቻለም ። የዚህን ሰው ብዙ አስደንጋጭ ታሪኮች ሰምቷል ። የሰማቸውን ሊያምን የቻለባቸው በርካታ ምክንያቶ ችም ነበሩት ።

ስለዚህ "አም ጌታዬ ግንም ሊደርስበት የማይችል ድንገተኛ አደጋ ላቀናብር እችላለሁ" ብቻ ነበር ያለው ። ይህንን ሲናገር አንኳን 'እኔ ራሴ ምስጢሩን እንደማውቅ መቼም ይረዳል' ሲል ደንግጧል ። ከዚያ ፀዋታ ሰፈነ ። በግንብ በተከበበችው ከተማ ውስጥ ያሉት ነዋሪዎች የተዘበራረቀ ውካታ በመስኩት እየገባ ይሰማዋል ።

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ በዓይኑ መረመረው ።

"በጣም ጥሩ ፣ እንግዲህ የዘዴውን ጉዳይ ላንተ እተዋለሁ ።"

"እሺ ጌታዬ ። ለመሆኑ ዒላማዋ እዚህ ኩውሉን ነው ያለችውየ"

"ለንደን ነው ፣ ካተሪን ትባላለች ። ካተሪን አሌክሳንደር ። ለንደን ባለው ቢሮዬ ውስጥ ነው የምትሰራው ።"

"ብተዋወቃት ለሥራዬ ይረዳኛል ። ውስጡን ለማወቅ ።"

ዴሚሪስ ጥቂት ካሰበ በኋላ "አንድ የሥራ አስኪያጅ ቡድን በሚቀጥለው ሳምንት ወደለንደን ልልክ ነው ። አንተም ከእነርሱ አንዱ እንድትሆን አደርጋለሁ" አለው ። ወደሱ ቀረብ ብሎ "ተጨማሪ ነገር" ብሎ ተናገረ ።

"እሺ ጌታዬ ምን ነበር?"

"ማንም ሬሳዋን ለይቶ እንዲያውቅ አልፈልግም ።"

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስልክ ደወለ ። "እንደምን አደርሽ ካተሪን ። ዛሬ እንዴት ነሽ?"

"ደህና ፣ አመሰግናለሁ ፣ ኮስታ ።"

"ትንሽ ተሽሎሻል?"

"አም"

"ጥሩ ። ይህንን በመስማቴ በጣም ደስ ብሎኛል ። የኩባንያችን የሥራ አስኪያጆች ቡድንን ለንደን ያለው ሥራችን እንዴት እንደሚካሄድ ጥናት እንዲያደርጉ ወደዚያው ልኬአቸዋለሁ ። በደንብ ተቀብለሽያ ቸው ብታስተናግጂአቸው ደስ ይለኛል ።"

"በጣም ደስ ይለኛል ። የሚመጡት መቼ ነው?"

"ነገ ጠዋት ።"

"የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ ።"

"እንደምታደርጊ እተማመንብሻለሁ ። አመሰግናለሁ ካተሪን ።"

"ግድ የለም ።"

"ደህና ሁኚ ካተሪን ።"

ስልኩ ተቋረጠ ።

'አም እንግዲህ ተጠናቋል' አለ ዴሚሪስ በአላቡ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ወደኋላው እየተደገፈ ። ካተሪን አሌክሳንደር ከተወገደች የሚያሰጋው ምንም ነገር አይኖርም ። ከዚያ በኋላ ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ በሚስቱና በዋርሳው ላይ ያደርጋል ።

"ዛሬ ግታ ከዋናው መሥሪያ ቤት የተላኩ ከፍተኛ እንግዶች ስለሚመጡ በደንብ እንድታስተናግጂአቸው እፈልጋለሁ ።"

የባለቤቷን እንግዶች ካስተናገደች ብዙ ጊዜ ሆኗታል ። ነገሩ

ሚሊናን በጣም አስፈንድቋታል ። ምናልባት ይህ ሁኔታዎችን ይለውጥ ይሆናል ።

የዚያን ዕለቱ የእራት ግብዣ ግን ያስከተለው ለውጥ የለም ። ሰዎቹ መጡ ፣ እራታቸውን በሉ ፣ ተመልሰው ሄዱ ። ግብግቡ የተዘናጋ ነበር ።

ዴሚሪስ ሚሊናን እንደነገሩ ከእንግዶቹ ጋር አስተዋውቆ እርሱ ሊያወጋና ሊሳሳት እርሷ ሳትተነፍስ ቁጭ ብላ ታያቸው ነበር ። ኮስታ ምን ያህል ተጫዋች ሰው እንደሆነ ረስታለች ። ደስ የሚሉ ቀልዶችና ተረቶችን እየነገራቸው አልር አልርም ያሞግሳቸዋል ። እንግዶቹ በዚህ ተደስተዋል ። ከአጠገባቸው የተቀመጠውን ሰው ክቡርነት መረዳታቸውን በሚገባ አሳይተዋል ። ሚሊና የመናገር እድል አልነበራትም ። ስትጀምር ኮስታ ያቋርጣታል ። ስለዚህ ማዳመጥን መረጠች ።

'ታዲያ እዚህ ከሱ ጋር እንድገኝ ለምን ፈለገ?' አለች ሚሊና በአሳቧ። ጊዜው መሽቶ ሰዎቹ ሊሄዱ ሲሉ ዴሚሪስ "ነገ በግለጻ መደሰንደን ትበሪያለሽ ። መጠናቀቅ የሚገባቸውን ጉዳዮች ደህና አድር ገሽ እንደምታከናውኚ እርግጠኛ ነኝ" አላት ።

ሰዎቹም ሄዱ ።

በሚቀጥለው ቀን የልውሳኑ ቡድን ለንደን ገባ ። ሦስቱ የቡድን አባላት የተውጣጡት ከሦስት የተለያዩ አገሮች ነው ።

ጂሪሃሌይ ረዥምና ደልዳላ ቁመና ያለው ፣ ተግባቢ አሜሪካዊ ነው። ፀጉሩን በመጠኑ ሽበት የጀመረው ሲሆን ሬቱም ፈካ ያለ ነው ። የእጁ ስፋት ካተሪንን እጅግ አስገርሟታል ። እስከዛሬ ካየቻቸው እጆች በጣም ግዙፍ የሆኑና አንድ ነገር ለመሥራት የጓጉ ይመስል የሚቅበጠበጡ እጆች ናቸው ያሉት ።

ፈረንሳዊው ዩቬ ሬናድ በጣም ብልህ ሰው ነው ። አጠር ብሎ ፈርጠም ያለ ቀፍጣናና ተጠራጣሪ ይመስላል ። ሁሉ በአሳብ የተሞጠ መስሎ ይታያል ። 'ጠንቃቃነት' የሚለው ቃል ካተሪን አእምሮ ውስጥ ብልጭ አለ ። 'ግን ከምንድነው የሚጠነቀቀው?' ስትል ካተሪን በሃሳቧ ተደነቀች።

ሦስተኛው የልውሳኑ ቡድን አባል ኢጣሊያዊው ዲና ግቱሲ ነው። በቀላሉ የሚገባባ ተጫዋችና ቀልደኛ ሰው ነው ።

"ሚስተር ዴሚሪስ ስለእንቺ በጣም ይጨነቃል" አለ ግቱሲ ።

"በጣም የተቆሻበድኩ መስሎ ይሰማኛል ።"

"በለንደን ቆይታችን የምትንከባከቢን እንቺ መሆንሽን ገልጦል ናል ። እጺ ፣ ትንሽ ስጦታ አምተቆልሻለሁ ።" እንድ የተጠቀለለ ፓኮ ለካተሪን ሰጣት ። ከውስጡ ያለው ከሐር የተሠራ የአንገት ርጣ ነበር ።

"በጣም አመሰግናለሁ" አለች ካተሪን ።

ወደሌሎቹም ዞር ብላ "ቢሮአችሁን ላሳያችሁ" አለቻቸው ።

ከኋላቸው የዕቃ መውደቅ ድምፅ ሰሙና ዞር አሉ ። አንድ የአሥራ አምስት ዓመት ትንሽ ልጅ ከእጁ ያመለጠው ዕቃ እያሳሰበው ዝም ብሎ ቆሟል ። ሦስት ሻንጣዎችን ይዟል ። ከርደድ ያለ ቡናማ ፀጉርና አረንጓዴ ብሌን ያላቸው ብሩህ ዓይናች አሉት ።

"ስለከርስቶስ ብለህ" አለ ሬናድ ። "እንኂያን ዕቃዎች በቀንቃቂ ያዛቸው ።"

"ይቅርታ" አለ ልጁ በመርበትበት ። "ይቅርታ አድርጉልኝ ። ሻንጣዎቹን የት ላኑራቸው?"

ሬናድ በችኮላ "ዞር አድርገህ አስቀምጣቸው ፤ በኋላ እናስገባቸዋ ለን" አለው ።

ካተሪን ልጁን ትኩር ብላ ስትመለከት ኤቬሊን "በአቴንስ የቢሮ ተላላኪ ሆኖ ይሠራ ነበር ፤ አቋረጠና እዚህ አዛወርነው" አለቻት ።

"ስምህ ማነው?" ስትል ካተሪን ጠየቀች ።

"አታናስ ስታቪች ነው እመቤቴ ።" ሊያለቅስ የደረሰ ይመስል ነበር።

"ደህና አታናስ ለሻንጣዎቹ ማስቀመጫ ክፍል ከበስተጓር አለ ። እኔ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው አደርጋለሁ ።"

"አመሰግናለሁ እመቤቴ ።"

ካተሪን ወደሰዎቹ ዞር አለች ። "እዚህ ያለውን የሥራችንን ሁኔታ እንደምታጠኑ ሚስተር ዴሚሪስ ገልጦልኛል ። በሚቻለኝ ሁሉ አስፈላጊ ውን ትብብር አደርግላችኋለሁ ። የሚያስፈልጋችሁ ነገርም ካለ እንዲተር ብላችሁ አደርጋለሁ ። አሁን ጌቶቹ አብራችሁኝ ኑና ከሂምና ከሌሎች የቢሮው ሠራተኞች ጋር ላስተዋዋቃችሁ ።" በኮሪደሩ ላይ ሲንዙ ካተሪን

ቆም እያለች ከሠራተኞቹ ጋር ታስታዋውቃቸው ነበር ። በመጨረሻ ከዊም ቢሮ ደረሱ ።

“ዊም ፣ እነኚህ ከሚስተር ዴሚሪስ የተላኩ ልውካን ናቸው ። ዩቪ ሬናድ ፣ ዲና ግቱሲና ጂሪ ሃሌይ ይባላሉ ። ከግሪክ የመጡት ገና አሁን ነው ።”

ዊም ገልመጥ ብሎ አያቸው ። “የግሪክ ሕዝብ ብዛት ሰባት ሚሊዮን፣ ስድስት መቶ ሰላሣ ሺህ ብቻ ነው ።” ሰዎቹ ተገርመው እርስ በእርስ ተያዩ ።

ካተሪን ፈገግ አለች ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስትተዋወቀው በነበራት ዓይነት መደነቅ ሰዎቹ እንደተደነቁ አየች ።

“ቢሮአችሁ እንዲዘጋጅላችሁ አድርጌአለሁ” አለቻቸው ካተሪን እንግዶቹን ። “አብራችሁኝ ልትመጡ ትችላላችሁ?”

ከዊም ቢሮ ወጥተው በኮሪደሩ ላይ ሲጓዙ ጂሪ ሃሌይ እንዲህ ብሎ ጠየቃት ። “ምን ዓይነት ጉደኛ ሰው ነው፣ በጣም ጠቃሚ ሠራተኛ ነው ብሎ ሰው የነገረኝ መሰለኝ ።”

“አዎ ነው ” አለችና ካተሪን አባባሉን አረጋገጠችለት ። “ዊም የልዩ ልዩ መምሪያዎችን ሒሣብ በቃሉ አስልቶ ይዟል ።”

“እንዲህ ያለውን ሰው የድመቱ ጠባቂ አድርጌ እንኳን አልቀጥረ ውም ።” አለ ሃሌይ በንቀት ።

“ምናልባት ወደፊት የበለጠ ስታውቀው ...”

“ከዚህ በላይ ላውቀው አልፈልግም” አለ ፈረንሳዊው በቁጣ ።

“ማረፊያ ሆቴልም አዘጋጅቼላችኋለሁ” አለቻቸው ካተሪን ለልዑካኑ ። “እያንዳንዳችሁ በተለያዩ ሆቴሎች ማረፊያ እንዲያዝላችሁ የምትፈልጉ መሆኑንም ተገንዝቤአለሁ ።”

“አዎ” አለ ግቱሲ ሲመልስ ።

ካተሪን በዚህ ላይ አስተያየት ለመስጠት ፈልጋ መልሳ ተወችው ። በተለያዩ ሆቴሎች ለማረፍ መፈለጋቸውም የእርሷ ጭንቀት አይደለም ።

እያሰበ ካተሪንን በትኩረት ይመለከታታል ። ‘ከገመትኩት በላይ በጣም ቆንጆ ነች ። ይህም መሆኑ ጉዳዩን የበለጠ ያሳምረዋል ። ከዓይኗ ላይ እንደማነበው ብዙ ስቃይ የደረሰባት ትመስላለች ።’

ካተሪን ለእንግዶቹ ቢሮአቸውን አሳየቻቸው ። እንደተረጋጉ ወደቢሮዋ ተመለሰች ። በመተላለፊያው ላይ ፈረንሳዊው ልውክ በወጣቱ ላይ ሲጮህበት ሰማች ።

“ይህ የኔ ሻንጣ አይደለም ። ደደብ ፣ የእራሴ ሻንጣ ቡናማ ነው ። ቡናማ ነው የምልህ! እንግሊዝኛ ይገባሃል?”

“አዎ ጌታዬ ። ይቅርታ ጌታዬ ።” ድምፁ በፍርሃትና በድንጋጤ ይንቀጠቀጣል ።

‘ስለዚህ ጉዳይ እንድ ነገር ማድረግ አለብኝ’ አለች ካተሪን በአሳቧ።

ኤቪሊን ኬይ “ለልውካኑ እንዲደረግላቸው የምትፈልጊው ነገር ካለ ለኔ ንገሪኝ ።” አለቻት ።

“ስለ ትብብርሽ አመሰግናለሁ ኤቪሊን ። ሲያስፈልግ እነግርሻ ለሁ።”

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አታናስ ስታቪች በካተሪን ቢሮ በኩል ሲያልፍ ካተሪን “እስቲ አንዴ ና!” አለችው ።

ልጁ ሊገረፍ እንደተጠራ ሰው እየተርበተበተ “እሺ እመቤቴ” ብሎ ወደውስጥ ገባ ።

“በሩን ዝጋው ።”

“እሺ እመቤቴ ።”

“ተቀመጥ አታናስ ስምህ አታናስ ነው አይደል ?”

“አዎ እመቤቴ ።”

እንዳይፈራ ሞክራ አልሆነላትም ።

“አይዞህ አትፍራ ።”

“አልፈራሁም እመቤቴ ።”

እንዲህ በፍርሃት የሚያርደው ምን ይሆን ስትል ካተሪን አሰበች ። ስላለፈው ሕይወቱ ለማጥናትም ወሰነች ።

“አታናስ ፣ እዚህ ማንም ችግር ቢፈጥርብህ ወይም ሊፈጥርብህ ቢሞክር ወደ እኔ መጥተህ እንድትነግረኝ ፣ እሺ ?”

ምራቁን ዋጠ ። “እሺ እመቤቴ ።”

ከዚህ በፊት ሰው ቅስሙን የሰበረበት መስሎ ተሰማት ። ችግር ቢያጋጥመው ወደ እርሷ መጥቶ የመናገር ድፍረቱንም ተጠራጠረች ።

“በኋላ እንነጋገራለን” አለች ካተሪን ።

ልውሳኑ በኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ለረ ዥም ዓመታት የሰሩ መሆናቸው ስለድርጅቱ አሠራር በሰፊ እንዲያውቁ ረድቷቸዋል ። ካተሪንን ያስደነቃት የተወዳጁ ኢጣሊያኗ የዲና ግቱሲ ውኔታ ነው ። እራሱ መልሱን ግወቅ የሚሻቸውን ጥያቄዎች ካተሪንን ደጋግሞ ይጠይቃል ። ስለ ለንደኑ ቢሮ አሠራር ለግወቅ የፈለገም አይመስልም ። በእርግጥ ለመናገር ከኩባንያው አሠራር ይልቅ ስለካተሪን የግል ሕይወት ለግወቅ የሚሻ ይመስላል ።

“ባል አለሽ ?” ሲል ግቱሲ ጠየቃት ።

“የለኝም ።”

“ድሮስ አግብተሽ ነበር ?”

“አዎ ።”

“ተፋትተሽ ነው ?”

ውይይቱን በዚሁ ለመግታት “ባሌ ሞቶብኛል” አለች ።

ግቱሲ ሳቅ አለ ። “መቼም እስካሁን አፍታሪ ጓደኛ ሳይኖርሽ የሚቀር አይመስለኝም ። ምን ግለቴ አንደሆነ ገባሽ ?”

“ምን ለግለት እንደፈለግክ ገብቶኛል” ካለች በኋላ በሃሳቧ ‘እንተን ምንም የሚያገባህ ነገር የለም’ አለች ። መለሰችና “አንተስ አግብተሃል ?” ስትል ጠየቀችው ።

“ሲ ፥ ሲ ፥ ሚስትና አራት ቆንጆ ልጆች አሉኝ ። እንግዲህ ለሥራ ስለያቸው በጣም ቅር ይላቸዋል ።”

“ለሥራ ወደ ውጭ ብዙ ትጓዟራለህ ሚስተር ግቱሲ ?”

ትንሽ ቅር ተሰኝ ። “ዲና በይኝ ዲና ፥ ግቱሲ የአባቱ ስም ነው ። አዎ ለሥራ ወደውጭ ብዙ እጓዟራለሁ ።” ፈገግ አለና ይምጹን ቀነሰ ። “እንዳንዴኮ ከቦታ ቦታ መጓዝ ተጨግሪ ደስታን ያስገኛል ። ምን ግለቱ እንደሆነ ግልጽ ሆነልሽ ?”

ካተሪን በፈገግታ “አልገባኝም አለች ።”

ያን ዕለት በስድስት ሰዓት ከሩብ ላይ ካተሪን ወደ ዶክተር ሃሚልተን በቀጠሮዋ ሄደች ። የሚገርመው በተጠርዋ ቦታ ለመገኘት ያለወትሮዋ በጣም ጓጉታለች ። ባለፈው ጊዜ ልታነጋገረው በመጣችበት ወቅት ምን ያህል ተበሳጭታ እንደነበር አስታወሰች ። አሁን ግን ለችግሯ መፍትሔ

እንደምታገኝ በመተማመን ቢሮውን ከፍታ ገባች ። አስተናጋጅዋ ለምሳ ስለወጣች ወደ ዶክተሩ ቢሮ የሚያስገባው ክፍል ከፍት ነበር ። አላን ሃሚልተን ለቀጠሮው ሲጠብቃት ደረሰች ።

“ኑይ ግቢ” አለና ሰላምታ አቀረበላት ።

ካተሪን ወደቢሮው ስትገባ እንድትቀመጥ ወንበር አሳያት ።

“መልካም ፥ ሳምንቱ እንዴት አለፈ ? በጥሩ አሳለፍሺው ?”

የኪርክ ሪኖልድስ አሟሟት ከአዕምሮዋ ውስጥ ጨርሶ ሊጠፋ አልቻለም ። “አዎ ደህና ነበር ያሳለፍኩት ፥ ሥራ በዝቶብኝ ነው የሰነበትኩት” አለች ።

“ይሄማ ላንቺ ጥሩ ነው ። ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ምን ያህል ጊዜ ሰርተሻል ?”

“አራት ወር ።”

“ሥራሽን ትወጂዋለሽ ?”

“አእምሮዬን ሁልጊዜ ስለሚጠምድልኝና … ስለሌላ ነገር አንዳላ ስብ ስለሚረዳኝ እወደዋለሁ ። ሚስተር ዴሚሪስ ትልቅ ባለውለታዬ ነው። ምን ያህል እንደረዳኝ በቃላት ልገልጽ አልችል” በማለት ካተሪን ፈገግ አለች ። “ውለታውን እንዴት አድርጌ እንደምከፍለው እኔ እንጃ ። ግን እከፍለዋለሁ ።”

አላን ሃሚልተን ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “ልትነግሪኝ የምትፈልጊውን ብቻ እየመረጥሽ ንገሪኝ ።”

ፀጥታ ሰፈነ ። ጭርታውን ሰብራ “ባለቤቴ የሚስተር ዴሚሪስ አውሮፕላን ነጂ ነበር ። የ … የጀልባ አደጋ ደርሶብኝ ምንም ማስታወስ ከማልችልበት ደረጃ ደረስኩ ። የማስታወስ ችሎታዬ ቀስ በቀስ ሲመለስ ሚስተር ዴሚሪስ ይህንን ሥራ ሰጠኝ” አለችው ።

በሃሳቧም ‘የደረሰብኝን ስቃይና ሽብር እርግፍ አድርጌ እየተናገርኩ ነው ። ግን ባለቤቴ ሊገድለኝ እንደነበረ ልገልጽለት ለምን አፈርኩ ? ምናልባት የማልረባ አድርጐ ይገምተኛል በሚል ሥጋት ይሆን ?’

“ለማንኛችንም ቢሆን ስላለፈው ሕይወታችን አንስቶ ማውራት ይከብዳል ።”

ካተሪን ፀጥ ብላ በትኩረት ተመለከተችው ።

“የማስታወስ ችሎታዬ ጠፍቶ ነበር ነው ያልሺው ?”

“አዎ ።”

"የጀልባ አደጋ ደርሶብኝ ነበር ፦"

"አዎ ።" ብዙ ነገር ልትነግረው ያልፈለገች ይመስላል ፣ ከንፈሮቿ እንደኩበት ደርቀዋል ። ልንገረው አልንገረው ስትል አመነታች ። በመጨረሻም አፍረጥርጣ ነግራው እርዳታውን ለማግኘት ፈለገች ። በሌላ በኩል ደግሞ አትናገሪ የሚላት ነገር ከውስጧ አለ ።

አላን ሃሚልተን ትኩር ብሎ ስለሁኔታዋ አጠና ። "ከባልሽ ተፋትተሻል ፦"

በሀሳቧ 'አዎ ፣ ተረሽኖ ነው የሞተው' ካለች በኋላ "ባ… ባሌ … ሞቷል ።" ስትል ተነፈሰች ።

"ሚስስ አሌክሳንደር …" ንግግሩን ለመቀጠል አመነታና "ካተሪን ብዬ ብጠራሽ ቅር ትሰኚያለሽ ፦"

"አልሰኝም ።"

"እኔንም አላን ብለሽ ጥሪኝ ካተሪን ። ታዲያ የሚያስፈራሽ ምን ነገር አለ ፦"

"እንደፈራሁ በምን ገመትክ ፦"

"አልፈራሽም ፦"

"አልፈራሁም ።" ረዘም ላለ ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ።

እውነቱን ይፋ ለማውጣት በልቦናዋ አምቃ የያዘችውን በቃላት መንዘራ ለመናገረ ፈርታለች ። "ወዳጅ የሚሆኑኝ ሰዎች .. የሚሞቱ ይመስሉኛል ።"

አለመደነቁን ለማሳየት አየሞከረ "ለእነርሱ ሞት ምክንያት እኔ ነኝ ብለሽ ትገምቺያለሽ ፦"

"ነኝም—አይደለሁምም ለማለት እችላለሁ ። ብቻ እኔ እንጃ ። ግ… ግራ ገብቶኛል ።"

"በሌሎች ሰዎች ላይ ስለደረሰው ነገር በከንቱ እራሳችንን እንደጥፋተኛ እንቆጥራለን ። ባልና ሚስት የተፋቱ እንደሆነ እኛ ነን ምክንያቱ ብለው ልጆቻቸው ይገምታሉ ። አንድ ሰው ሌላውን ተራግሞ በእጋጣሚ ተረጋሚው ጎልፈተ ሕይወት ቢደርስበት ረጋሚው ለዚህ ምክንያቱ እኔ ነኝ ብሎ ያስባል ። እንዲህ ዓይነቱ እምነትና አስተሳሰብ ደግሞ ያልተለመደ አይደለም እና አንቺ …"

"ነገሩ ከዚህም የከበደ ነው ።"

"ነው ፦" አለና መልሳ እንድትናገር በጉጉት ጠበቃት ።

ቃላቶቹ ተሸጉዶጉዱ ። "ባሌ ተገደለ ። እና የእርሱም … እቁባቱ ተገደለች ። ጥብቅና የቆመለት ሁለቱ የሕግ ባለሙያዎችም ሞቱ ። እና አሁን ደግሞ …" ድምጿ እየሰለለ መጣ ። "ኪርክ ሞተ ።"

"ለእነዚህ ሁሉ አሟሟት ምክንያቷ እኔ ነኝ ብለሽ ትገምቺያለሽ ? ይህማ ልትሸከሚው ከሚገባሽ በላይ እራስሽን መጫንሽ ነው ፣ አይመስልሽም ፦"

"… ገፌ የሆንኩ እየመሰለኝ ነው ። ስለዚህም ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ለመፍጠር አስፈርቶኛል ። ልቋቋም የምችል አይመስለኝም ። አንድ ነገር …"

"ካተሪን ፣ ኃላፊነት ያለብሽ ለማን ሕይወት እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ለእራስሽ ብቻ ። ለሌላ ለማንም ሊሆን አይችልም ። የሌላውን ሰው ሕይወት ለመቆጣጠርም ሆነ አሟሟቱን ለማስቆም ጨርሶ አትቺይም ፣ የዋህ ነሽና ። ከእነርሱ ሞት ጋር አንቺን የሚያገናኝሽ ምንም ነገር የለም ። ይህ በደንብ ሊገባሽ ይገባል ።"

'የዋህ ነሽና ። ከእነርሱ ሞት ጋር አንቺን የሚያገናኝሽ ምንም ነገር የለም ።' ካተሪን ቁጭ ብላ እነዚህን ቃላት በአእምሮዋ ውስጥ አመላለሰች ። አባባሎቹን ሙሉ በሙሉ አምና ልትቀበላቸው ፈልጋለች ። ሰዎች የሞቱት በእራሳቸው ምክንያት እንጂ ሰበቧ እርሷ አይደለችም ። የኪርክም ቢሆን ድንገተኛ አደጋ ነው ።

አላን ሃሚልተን ዝም ብሎ ተቀምጦ ይመለከታታል ። ካተሪን ጣራ ጣራውን አየችና በአሳቧ 'ደግ ሰው ነው ምነው ቀደም ብዬ ባወቅሁት ኖሮ' አለች እራሷን እንደ ወንጀለኛ የቆጠረችው ካተሪን ። ጠረጴዛው ላይ ያለውን የአላን ሚስትና የልጁን ፎቶግራፍ ተመለከተች ።

"አመሰግናለሁ" አለች ካተሪን ። "የመከርከኝን ለመቀበል ጥረት አደርጋለሁ ። ከምክርህም ራሴን ለማዋሃድ እሞክራለሁ ።"

አላን ሃሚልተን ፈገግ አለ ። "አብረን አንሞክራለን ። ተመልሰሽ ትመጪያለሽ እይደል ፦"

"ምን ፦"

"ይህ ሙከራ ነው ፣ ታስታውሺ የለ ? ያኔ እኔ ዘንድ ለመምጣት ስታመነቺ የነበረውን ?"

ካተሪን ወዲያው "አዎ ተመልሼ እመጣለሁ አላን" አለችው ።

እንደወጣች አላን ሃሚልተን እዚያችው ቁጭ ብሎ ስለእርሷ

ማሰቡን ቀጠለ ። በሥራው ላይ በቆየባቸው ባለፉት ዓመታት በርካታ የሆኑ ውብ ሴት ሕመምተኞችን አክሟል ፤ አንዳንዶቹም ሊያሽኮረም ሙት ሙከራ ቢያደርጉም ሳይደለል በጠንካራ የሥነ አእምሮ ሐኪምነቱ ቆይቷል ። እንዲህ ዓይነት ንኪኪ ከሕመማን ጋር መፍጠር ከቡር የሆነ ሙያዬን ያዋርዳል ብሎ ያምናል ። እንደዚያ ማድረጉ ለሙያው ግዴታ ታማኝ አለመሆን ነው ይላል ።

የዶክተር አላን ሃሚልተን ወላጆችም በሕክምና ሥራ ውስጥ የነበሩ ናቸው ። የቀዶ ጥገና ሐኪም የነበረው አባቱ አብራው ትሠራ የነበፈችውን ነርስ አግብቶ ነው ሐሚልተን የተወለደው ። አያቱም ቢሆን የታወቀ የልብ ሐኪም እንደነበር ይነገራል ። አላን ገና በልጅነት ዕድሜው ነበር ሐኪም የመሆን ፍላጐት ያደረበት ። ጉጉቱም አንደአባቱ የቀዶ ጥገና ሐኪም ለመሆን ነበር ። በኪንግ ኮሌጅ ውስጥ በሚገኘው የሕክምና ትምህረት ቤት ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቆ ከተመረቀ በኋላ የቀዶ ጥገና ሕክምና ማጥናት ቀጠለ ።

ወጣቱ በትምህርት ከሚገኝ ዕውቀት ባሻገር የተፈጥሮ ችሎታም ነበረው ። በዚህ መሐል ሰፕቴምበር 1 ቀን 1939 የሂትለር ወታደሮች ፖላንድን ወረሩና ፈረንሳይና ብሪታንያ ወደ ጦርነቱ መግባታቸውን በይፋ አስታወቁ ። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተጀመረ ።

አላን ሃሚልተን በቀዶ ጥገና ሐኪምነት ተመዘገበ ።

ጁን 22 ቀን 1940 ፥ ለጦርነቱ ግንባር የፈጠሩት አገሮች ማለትም ጀርመንና ኢጣሊያ ፥ ፖላንድ ፥ ኖርዌይና በአካባቢው የሚገኙ አገሮችን ከወረሩ በኋላ ፈረንሳይም በጀርመን እጅ ወደቀች ። ስለዚህ ጀርመንን የመቋቋም ተግባር በብሪታንያ ጫንቃ ላይ ብቻ ወደቀ ።

በመጀመሪያ በቀን ከመቶ የማያንሱ አውሮፕላኖች ተሰልፈው በብሪታንያ ከተሞች ላይ ቦንብ አዘነቡ ። ብዙ ሳይቆይ የቦንብ ጣይ አውሮፕላኖች ቁጥር ሁለት መቶ ደረሰ ። ቀጥሎም ወደ አንድ ሺህ ከፍ አለ ። በዚሁ ሳቢያ የደረሰው እልቂት በአህዝ ተገልጾ የሚቻል አልሆነም። የቆሰሉትና የሞቱት ሰዎች በየቦታው ወድቀው ይታያሉ ። ከተማዋ በእሳት ጋየች ። ሆኖም ሂትለር ስለእንግሊዞች የነበረው ግምት በጣም የተሳሰተ ነበር ። በቦንብ ድብደባ ጭካኔው እንግሊዞች የበላይነትን

እንዲያገኙ ረድቷቸዋል ። ድብደባው እንግሊዞችን ይበልጥ ያነሳሳቸው ሲሆን ለነፃነቱ ለመሞት እያንዳንዱ የአገሪቱ ዜጋ ዝግጁ ነበረ ።

ቀንም ሆነ ሌሊት እረፍት የሚባል ነገር አልነበረም ። አላን ሃሚልተን አንዳንዴ ያለእንቅልፍ በተከታታይ ለስልሳ ሰዓታት የሚሰራባቸው ጊዜያት ነበሩ ። የሚያክምበት ድንገተኛ ክፍል በቦንብ ሲደበደብ በሽተኞቹን ወደ ሆስፒታሉ መጋዘን አንጉዞ ሥራውን ቀጠለ ። በጣም አስቸጋሪ በሆነው ሁኔታ ውስጥ አቅሙ የቻለውን ሁሉ አየሠራ የብዙ በሽተኞችን ሕይወት አተረፈ ።

በአክቶበር የቦንብ ድብደባው እየባሰበት መጥቶ ነበር ። በእንድ ወቅት የአደጋ ጊዜ ጥሪው ተሰምቶ ሕዝቡ ሁሉ ሮጦ ወደየቀበሮ ጉድጓድ ሲገባ አላን የኦፐራሲዮን ሥራ ያካሄድ ነበር ። ሥራውን አቋርጦ እንዲሸሽ ቢሞከርም በሽተኞቹን ጥዬ አልሄድም ብሎ የቀዶ ጥገናውን ሥራ ቀጠለ። ቦምቡ በአጠገቡ ፈነዳና ከአላን ጋር ይሠራ የነበረ ሐኪም "እባክህ ከዚህ እንውጣ" ብሎ ጠይቆት ነበር ።

"ቆይ እንድ ደቂቃ" አለና የቀደደውን የበሽተኛ ደረት ቀድዶ መጐርጐር ጀመረ ።

"አላን !"

ሥራውን አቁሞ ሊሄድ አልቻለም ። በአካባቢው ፈንጂ እንደበረዶ ሲዘንብ ደንታ ሳይሰጠው በኦፐራሲዮኑ ላይ ብቻ ተመስጧል ። ሕንጻው ላይ የወደቀውን ቦምብ ድምፅ እንኳ አልሰማም ነበር ።

ለሰድስት ቀናት ያህል ሕሊናውን ስቶ ሲነቃ በሌላው አካሉ ላይ ከደረሱት ጉዳቶች በተጨማሪ የቀኝ እጁ አጥንቶች መድቀቃቸውን ተረዳ። አጥንቶቹ ተጠግነው የዳነ ቢመስልም ከእንግዲህ የቀዶ ጥገና ሥራ ሊሰራ አይችልም ።

የወደፊቱ ሕይወቱ መበላሸቱን ሲያሰላስል የተነካው አእምሮው መልሶ ለመዳን የዓመት ያህል ጊዜ ፈጅቶበታል ። አንድ የማይረባ የሥነ አእምሮ ሐኪም "ስላለፈው ማዘኑን ትተህ ስለወደፊቱ ሕይወትህ ማሰብ የሚገባህ ከአሁኑ ጀምሮ ነው" አለው ።

“እኮ ምን ዓይነት ሥራ ልሥራ?” ሲል አላን ምርር ብሎ ጠየቀው።
“እስካሁን የምትሠራውን ሥራ ዓይነት ለየት ባለ ሁኔታ ።”
“አልገባኝም ።”
“አንተ ፈውስ ሰጪ ነህ አላን ። የሰዎችን አካል ታድናለህ ። በርግጥ ከእንግዲህ እንደዚያ ያለ ሥራ ለመሥራት አትችልም ። የሰዎችን አዕምሮ ማዳንም የዚያኑ ያህል በጣም ተፈላጊ ተግባር ነው ። ጥሩ የሥነ አዕምሮ ሐኪም መሆን ትችላለህ ። ብሩህ አእምሮ አለህ ። ለሰዎች አዛኝ ነህ ። እስቲ አስብበት ።”
አላን በሕይወቱ ውስጥ ከወሰናቸው ጠቃሚ ውሳኔዎች ይሄኛው ዋነኛው ነው ። በአዲሱ ሥራው በጣም ተደሰቷል ። አሳዛኝ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተስፋ የቆረጡ በሽተኞችን አክሞ መልሰው ጤነኛ አእምሮ እንዲኖራቸው ማድረግ ቀድሞ ከነበረው የበለጠ የመንፈስ እርካታ እየሰጠው ነው ። ስሙ ገንኖ ታዋቂነትንም በማግኘቱ ካለቋሚ ሕመምተኞቹ በስተቀር ለሦስት ዓመት ሌላ አዲስ በሽተኛ ለመቀበል አልቻለም ። ካተሪንን የተቀበላትም ለሌላ ሐኪም ሊያስተላልፋት ሲል ነበር ። ሆኖም የእርሷን ነገር ችላ ሊለው አልቻለም ‘ልረዳት ይገባኛል’ አለ በአሳቡ ።

ካተሪን ከአላን ሃሚልተን ጋር ከተወያየች በኋላ ወደቢሮዋ ስትመለስ ዊምን ልታነጋግር ሄደች ።
“ዛሬ ዶክተር ሃሚልተንን አነጋገርኩት” አለችው ።
“በእውነት ? ከሥነ አእምሮ ታካሚዎች በቁጥር ደረጃ ስናስቀምጥ መቶዎቹ ባል ወይም ሚስት የሞተባቸው ፣ 73ቱ በልዩ ልዩ ምክንያት የተፋቱ ፣ 65ቱ በእሥር ፣ 63 የቅርብ ዘመድ የሞተባቸው ፣ 63 ልዩ ልዩ አደጋ ወይም ሕመም የደረሰባቸው ፣ 53ቱ በትዳር ፣ 50ዎቹ ከሥራ በመባረራቸው ፣ 47ቱ …”
ዊም የሚናገረውን ካተሪን ዝም ብላ ቆማ አዳመጠች ። በአሳቧ ‘ሁሉንም ከቁጥር አንፃር ብቻ ማየቱ ምን ይመስል ይሆን ? ሰውን እንደሰው አለመቁጠርስ ? እውነተኛ ጓደኛ አለመፍጠርስ ? እኔማ አዲስ ጓደኛ አገኘሁ ። ለመሆኑ አዲሱ ጓደኛዬ ካገባ ምን ያህል ጊዜ ይሆነው ?’ አለች ።

ምዕራፍ ሃያ

አቴንስ

‘ልታጠፋኝ ሞክረህ ነበር ግን አልተሳካልህም ። ግን ሙከራው ቢሳካልህ ምንኛ ይሻልህ ነበር?’
እነኚህ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተናገራቸው ቃላት አሁንም ከስፒሮስ ላምብሩ ጆሮዎች ውስጥ ያንቃጭላሉ ። ዴሚሪስ ፉከራውን ከግቡ ለማድረስ ወደኋላ እንደማይል ላምብሩ ጠንቅቆ ያውቃል ። ‘አምላኬ ፣ የሪዞሊ ስሕተት ምኑ ላይ ይሆን ? ሁሉም በጥንቃቄ ታቅዶ ነበር ።’ ከእንግዲህ ስህተቱ ምን እንደነበረ ለማጤን ጊዜ የለም ፣ አስፈላጊው እህቱን ማስጠንቀቁ ላይ ነው ።
የላምብሩ ፀሐፊ ወደቢሮው ገባች ። “የአራት ሰዓት ቀጠሮህ አንደተጠበቀ ነው ። መልእክቱን…?”
“የለም ፣ ቀጠሮዎቼን ሁሉ ሰርዢያቸው ዛሬ ጠዋት ተመልሼ የምመጣ አይመስለኝም ።”
በስልኩ ካነጋገራት ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወደሜሊና ገሰገሰ ።

በቪላው አትክልት ውስጥ ሆና ትጠብቀው ነበር ። “ስፒሮስ ፣ በስልኩ ውስጥ ትንሽ የተበሳጨህ ትመስል ነበር ። ምን ችግር ተፈጠረ?”
“ሜነጋገር አለብን” አላትና በወይን ቅጠል ወደተከበበው አማዳሚ ወንበር ይዟት ሄደ ። ተቀምጦ ዓይን ዓይኗን እያየ ‘እንዴት ደስ የምትል ሴት ናት ። ለቀረቧት ሁሉ ደስታን አጐናፅፋለች ። የምትቀጣው ምንም ወንጀል ሳትፈጽም ነው’ ሲል አሰበ ።
“ምን ችግር እንዳጋጠመህ ለምን አትነግረኝም?”
ላምብሩ አየር ወደ ውስጥ በኃይል ሳበ ። “የምነግርሽ ነገር ሕመም የሚለቅብሽ ነው የኔ ፍቅር” አላት ።
“ማስጠንቀቂያ ነው?”

"እውነቱን ነው የምነግርሽ ። ሕይወትሽ አደጋ ላይ ነው ።"

"ምን? ማነው አደጋ የሚያደርስብኝ?"

የሚናገራቸውን ቃላት በጥንቃቄ መምረጥ ጀመረ ። "ኮስታ ሊገድልሽ ላይሞክር የሚቀር አይመስለኝም ።"

ሜሊና አፍን ከፍታ እንደፈዘዘች ቀረች ። "ትቀልዳለህ መሰል ።"

"የምሬን ነው ሜሊና"

"የኔ ፍቅር ፣ ኮስታ ብዙ ብዙ ሊሆን ቢችልም ነፍሰ ገዳይ አይደለም። በፍፁም በፍፁም..."

"ተሳስተሻል ። ከዚህ በፊት ግድያ ፈጽሟል ።"

ፊቷ እየገረጣ መጣ ። "ምንድነው የምትለው?"

"እርሱማ ግድያውን በገዛ እጆቹ አይፈጽምም ። ሰዎችን እየቀጠረ ነው የልቡን የሚያደርሰው ። ግን..."

"ላምንህ አልችልም ።"

"ካተሪን ዶግላስ የተባለችዋን ታስታውሺያለሽ?"

"ያቺ የተገደለችዋ ሴት..."

"አልተገደለችም ። አሁንም በሕይወት ትገኛለች ።"

ሜሊና ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። "እንግዲህ የምናገረው ስለሷ አይደለም ማለት ነው ። እኔ የማውቃትን... የገደሏት ሰዎች ተረሽነዋል ።"

ላምብሩ የእህቱን እጅ ሳብ አድርጉ ያዘ ። "ሜሊና አይምሰልሽ ፣ ላሪ ዶግላስና ናኤሌ ፓጂ ካተሪንን አልገደሏትም ። ፍርድ ቤት በቀረቡበት ወቅት እንኳን ዴሚሪስ ደብቆ አስቀምጧት ነበር ።"

ሜሊና በተቀመጠችበት ደርቃ ቀረች ። በፊት ሰሞን እቤቷ ውስጥ በጨረፍታ ያየቻት ሴት ትዝ አለቻት ።

ምልልሱን አስታወሰች ። 'በላሎኑ ውስጥ ያየኋት ሴት ማን ናት' ስትለው....

'የአንድ ሽሪኬ ሚስት ናት ። ለንደን በሚገኘው ቢሮዬ ተቀጥራ ልትሠራ መሄዷ ነው' ሲላት...

በጨረፍታ አይቻታለሁ ። እንዳየቻት አንድ ሰው ትዝ አላት ። 'የአውሮፕላንህ ነጂ ሚስት ትመስላለች' ስትለው 'ከቶ ሊሆን አይችልም እሷንማ ገለዋታል' ብሎ መለሰላት ።

እንደምንም ታግላ መናገር ጀመረች ። "እቤታችን ውስጥ አይቻት ነበር ስፒሮስ ። ኮስታ ስለእርሷ የነገረኝ ውሸት ነበር ።"

"ሰውዬው ንክ ነው ። ቶሎ ብለሽ ዕቃሽን ሰባስበሽ ከዚህ ሥፍራ እንድትለቂ እፈልጋለሁ ።"

አየችውና ዝቅ ባለ ድምፅ "አይሆንም ይህማ የገዛ ቤቴን ትቼ ?" አለችው ።

"ሜሊና ፣ አንድ ነገር ስትሆኚ ሐዘኑን ልቋቋመው አልችልም ።"

ድምጿ ጉርነን አለ ። "አታስብ ምንም አልሆንም ። ኮስታ ምኝ አይደለም ፣ አንድ ነገር ቢያደርገኝ አሳር ፍዳውን እንደሚያይ ይህና አድርጉ ያውቃል ።"

"ባልሽ ቢሆንም ደህና አድርገሽ ያወቅሺው አይመስለኝም ። በጣም ፈርቼልሻለሁ ።"

"ሰውዬውን እንዲት አድርጌ እንደምይዘው አውቃለሁ ስፒሮስ ።"

ትኩር ብሎ እንዳያት አሳቧን ሊያስቀይር እንደማይችል ተረዳ ። "የምትሄጂ ከሆነ እንግዲህ በማንኛውም ጊዜ ከሱ ጋር ስብቻችሁ እንዳትሆኑ ቃል ግቢልኝ ።"

የወንድሟን ጉንጭ መታ አደረገችና "ቃል ገብቼልሃለሁ" አለችው።

ሜሊና ለወንድሟ የገባችውን ቃል ለመጠበቅ ሃሣብ አልነበራትም።

ያን ዕለት ምሽት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከቤት እንደደረሰ ሜሊና ስትጠብቀው አገኛት ። ሲያያት በጭንቅላቱ ብቻ ሰላምታ ሰጣትና አልፏት ወደመኝታ ቤቱ ገባ ። ሜሊናም ተከተለችው ።

"መነጋገር ያለብን ይመስለኛል" አለች ሜሊና ።

ዴሚሪስ ሰዓቱን አየና "የሚናገረኝ ጥቂት ደቂቃ ብቻ ነው ፣ ቀጠሮ አለኝ" አላት ።

"አለህ ? ዛሬ ግን ደግሞ ልትገድለው ያቀድከው ሰው አለ?"

ፊቱን ወደእርሷ ዞር አደረገ ። "ምንድነው የምትቀባጥሪው ?"

"ዛሬ ጠዋት ስፒሮስ መጥቶ ነበር ።"

"ወንድምሽ እቤቴ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ልሰጠው ነው ።"

"ቤቱኮ የእኔም ጭምር ነው" አለች ሜሊና በልበ ሙሉነት ። " ከእርሱ ጋር ትልቅ ቁምነገር ተወያይተናል ።"

“እውነትሽን ነው? ስለምን ጉዳይ ይሆን?”

“ስለእንተ ፡ ስለካተሪን ዶግላስና ስለኖኤሌ ፓጂ ።”

በትኩረት አዳመጣት ። “ያን ያረጀ ያፈጀ ጥንታዊ ታሪክ!”

“ይመስልሃል፣ ሁለት ንጹሀን ሰዎችን እንዳስገደልክ ስፒሮስ ነግሮኛል ።”

“ስፒሮስ ሞኝ ነው”

“ሴትዮዋን እኔም እራሴ እዚህ ቤት ውስጥ አይቻታለሁ ።”

“የፈለግሺውን ብታወሪ ማንም ሊያምንሽ አይችልም ። ደግሞ ከእንግዲህ እታዪአትም ። የሚያጠፍትን ሰዎች አሰማርቻለሁ ።”

ለእራት ተገኝተው የነበሩትን ሦስቱን ሰዎች ከመቅጽበት አስታወሰች ። ‘ነገ በማለዳ ወደለንደን ትበሪያለሽ ። መጠናቀቅ የሚገባቸውን ጉዳዮች ደህና አድርገሽ እንደምታከናውኚ እርግጠኛ ነኝ’ሲል የተናገራት ትዝ አላት ።

ወደሜሊና በጣም ተጠጋና በለስላሳ እነጋገር “መቼም ታውቂያለሽ፣ የአንቺና የወንድምሽ ነገር እጅ እጅ ብሎኛል” አላት ። እጇን ያዘና በኃይል ጠመዘዛት ። “ስፒሮስ ሊያጠፋኝ ሞክሮ ነበር ፡ ቢገድለኝ ይሻለው ነበር ።” አላትና በይበልጥ እጇን ጠመዘዘ ። “ምነው ሞቶ በሆነ ብላችሁ ሁለታችሁም የምትመኙበት ጊዜ ሊመጣ ነው ።”

“ተው እያሳመምከኝ ነው እኳ ።”

“ውድ ባለቤቴ ሆይ እስካሁን የህመምን ምንነት ያወቅሽ ስላልመሰለኝ ለወደፊቱ በደንብ እንድትረጂው አደርጋለሁ ። ” አላትና እጇን ለቀቀው ።

“እፈታሻለሁ ። ደንበኛዋን እንስት ነው ያሰኘኝ ። እንዲህም ሲባል ከሕይወትሽ ውጭ የምሆን አይምሰልሽ ። ለአንቺና ለውድ ወንድምሽ ያሰብኩት ጥሩ እቅድ አለ ። አም ፡ በመጠኑም ቢሆን የተነጋገርን መሰለኝ። ይቅርታ አድርጊልኝና ወደውስጥ ገብቼ ልብሴን ልቀይር ። የቀጠርኳትን ሴት ብዙ ማስጠበቅ ተገቢ አይመስለኝም ።”

ዞር አለና ወደልብስ መቀየሪያ ክፍሉ ገባ ። የልብ ትርታዋ የጨመረው ሜሊና እዚያው ቆማ ቀረች ። ‘ስፒሮስ ለካ እውነቱን ነበር ። ሰውዬው እብድ ነው ።’

ተስፋ ብትቆርጥም ለገዛ ሕይወቷ ግድ አልነበራትም ። ‘የምኖረው ለምንድን ነው?’ አለች በአሳቢ ምርር ብሏት ። ባሏ አዋርዷታል ።

በአደባባይ ሳይቀር እየተሳደበ የፈጸመባትን ወራዳ ተግባር ሁሉ አስታወሰች ። በዚህም የተነሳ በጓደኞችዋ ዘንድ መሳቂያና መሳለቂያ ሆናለች ። ከእንግዲህ ለእራሷ መጨነቅን ትታለች ። ‘ለመሞት ዝግጁ ነኝ’ አለች በልቧ ። ‘ስፒሮስ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ግን ዝም ብዬ አልመለከትም ።’ ከዚህ ተግባሩ ግን እንዴት አድርጋ ልታድነው ትችላለች ? ስፒሮስ ኃያል ቢሆንም ባለቤቷ ደግሞ ከእርሱ የበለጠ ኃያል ነው ። ሜሊና ዝም ካለችው ባለቤቷ ያሰበውን ነገር ከማድረግ ወደኋላ እንደማይል በሚገባ አውቃለች ። ‘ያም ሆነ ይህ ልገታው ይገባኛል ። ግን እንዴት አድርጌ?...’

ምዕራፍ ሃያ አንድ

ከአቴንስ የመጡት ልዑካን ካተሪንን በሥራ ወጥረዋታል ። ከሌሎች ኩባንያ ሥራ አስኪያጆች ጋር እንዲወያዩና በለንደኑ ቢሮ የሚከናውነውን ተግባር እየተዘዋወሩ እንዲመለከቱ አድርጋለች ። ሰዎቹ በታታሪነቷና በብቃቷ በጣም ተደንቀዋል ። ስለማንኛውም የሥራ ዘርፍ ጠንቅቃ ማወቋ እርካታን ሰጥቷቸዋል ።

ካተሪን በየዕለቱ በሥራ መጠመዷ ስለችግሯ እንዳታስብ ረድቷታል ። እንግዶቹንም እያወቀቻቸው መጣች ።

ጂሪ ሃሌይ ከቤተሰቡ ውስጥ በጣም የተረገመ ልጅ ነው ። አባቱ የታወቀ የነዳጅ ዘይት ከበርቴ ሲሆን እያቱም ጻኛ ነበሩ ። ጂሪ ሃሌይ ዕድሜው ሃያ አንድ እንደሞላ የሰው ግቢ ሰብሮ በመግባት አውቶሞቢል ሰርቆና የልጃገረድ ክብረ ንፅሕና በጉልበት ደፍሮ በወጣት ጠባይ ማረሚያ ለሦስት ዓመት ታሥሮ ነበር ። ቤተሰቦቹ መጥፎ ባሕሪው ስላንገፈገፋቸው ወደአውሮጳ ላኩት ። "በኋላ እራሴን አርሜ ፡ እንደገና ልስተካከል ችያለሁ " ሲል ካተሪንን አሜውቷት ነበር ።

ዩቪ ሬናድ ኩስተር ያለ ሰው ነው ። ወላጆቹ በርቀት የዝምድና ሐረግ ላይ ለሚገኝ ዘመድ ሰጥተውት ነበር ያደገው ። "አሳዳጊዎቹ በቪቹ አካባቢ እርሻ ስለነበራቸው ከጠዋት ጀምሮ እስከግታ በእርሻው ላይ ያለዕረፍት እንደአህያ ያሠሩኝ ነበር ። ዕድሜዬ አሥራ አምስት ሲሞላ ከዚያ አምልጨ በመሄድ ፓሪስ ውስጥ እሠራ ነበር ።"

ሁሌ ደስተኛውና ፍልቅልቁ ኢጣሊያዊ ፡ ዴና ማቱሲ የተወለደው በመካከለኛው የኑር ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቤተሰቦች በሲሲሊ ውስጥ ነው ። "ዕድሜዬ አሥራ ስድስት ሲሞላ አሥር ዓመት ከምትበልጠኝና ባል ከነበራት ሴት ጋር በመኩብለል ስሕተት ፈጸምኩ ። ወይኔ ፡ ሴትዮዋ ቤሊሲማ ነበረች ።"

"ከዚያስ?" ስትል ካተሪን ጠየቀች ።

ሳቀ ። " መልሰው ወደቤት አመጡኝና ከሴትዮዋ ባል ቁጣ ሊሸሽጉኝ ወደሮም ላኩኝ ።"

ካተሪን ረገግ አለች ። "እሃ! በሚስተር ዴሚሪስ ኩባንያ ውስጥ መሥራት የጀመርከው መቼ ነው?"

የማይጨበጥ መልስ ሰጣት ። "በኋላ ላይ ነው ። ቀደም ሲል የእለት ጉርሻ የሚያስገኝልኝ ምናምንቴ ሥራ ስሠራ ነበር ።"

"እና ከዚያ ሚስትህን አገኘህት?"

የካተሪንን ዓይን እያየ "ባለቤቴ እዚህ የለችም" አላት ።

ትኩር ብሎ ተመለከታት ። አነጋገራት ፡ ስትናገር ድምጿን አዳመጠ ፡ የሽቶዋን ጠረን አሸተተ ። ስለእርሷ ሁሉንም ነገር ለማወቅ ፈለገ ። በአረማመዷ እንኳ ሳይቀር ቋምጠ እራቁቷን አልጋ ውስጥ ስትገባ ምን ትመስል ይሆን ብሎ አሰላሰለ ። ምን እንደምትመስል በቅርቡ ይረዳል ። በጣም በቅርብ ጊዜ ። ሊታገስ የሚችል አይመስልም ።

ጂሪ ሃሌይ ወደካተሪን ቢሮ ገባ ። "ትያትር ትወጂያለሽ ካተሪን?"

"ለምን ፡ አዎ እኔ...."

"ፌኒአንስ ሬንቦው የተሰኘ አዲስ ሙዚቃዊ ድራማ ተከፍቷል ። ዛሬ ማታ ላየው እፈልጋለሁ ።"

"ትኬት ላዘጋጅልህ?"

"ለብቻ መግባት ደስ አይልም ። አይመስልሽም? አንቺ ምን ሥራ አለሽ?" ካተሪን አመነታችና "ምንም !" ብላ ቅብጥብጡን እጆቹን ተመለከተች ።

“በጣም ጥሩ! ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ከሆቴል መጥተሽ ውሰጂኝ ።” እንደ ትዕዛዝ ነበር አነጋገሩ ። ወደኋላው ዞረና ከቢሮው ወጣ ።

አቀራረቡ ያልተለመደ ሆነባት ። ግልፅነትና የወዳጅነት አቀራረብ ቢያሳያትም… “እራሴን አርማለሁ” የሚለውን የዚያን ሰውዬ እነኚያን ግዙፍ እጆች ሁኔታ ጨርሳ ልትረሳ አልቻለችም ።

ጂሪ ሃሌይ በላቮይ ሆቴል መተላለፊያ ላይ ሆኖ ካተሪንን ጠራትና በኩባንያው ሊሞሲን ተሳፍረው ወደትያትር ቤቱ አመሩ ።

“ለንደን ታላቅ ከተማ ናት” አለ ጂሪ ሃሌይ ። “ወደዚህ በመጣሁ ቁጥር ደስ ይለኛል ። እዚህ ለብዙ ጊዜ ቆይተሻል?”

“ለጥቂት ወራት”

“ትውልድሽ አሜሪካ ነው”

“አዎ ፣ ቺካጐ”

“ቺካጐ ትልቅ ከተማ ሆኗል ። እዚያ በጣም ጥሩ ጊዜ አሳልፌአለሁ።”

‘የሴቶችን ክብረ ንጽሕና መድፈር!’ አለች በአሳቧ ።

ከትያትር ቤቱ ደረሱና ከተመልካቹ ጋር አብረው ተቀመጡ ። ትርዒቱ በጣም ጥሩ ቢሆንም ካተሪን አሳቧን ሰብስባ ልትከታተለው አልቻለችም ። ጂሪ ሃሌይ ጣቶቹን ከወንበሩ ፣ ከጭኑና ከጉልበቱ ጋር እያጋጨ ድምፅ በማሰማት ረብሿት ነበር ። እጆቹ አርፈው ሲቀመጡ አልቻሉም ።

ትርዒቱ ሲያልቅ ሃሌይ ወደካተሪን ዞር አለና “ በጣም ጥሩ የምሽት ጊዜ ነው ያሳለፍነው ። ለምን መኪናዋን ትተን በሃይድ መናፈሻ ውስጥ በእግር አንሽራሸርም?” ሲል ጠየቃት ።

“በጠዋት ቢሮ መግባት አለብኝ” አለችው ካተሪን መልሳ ። “ሌላ ጊዜ ቢሆን ይሻላል ።”

ሃሌይ ፊቷን ትኩር ብሎ እየተመለከተ ከአንገት በላይ ፈገግታ አሳያት ። “እንዳልሽ ፤ ወደፊት ብዙ ጊዜ አለን ።”

ዱቪ ሬናድ ሙዚዬሞችን መጐብኘት ይወዳል ። ፈረንሣዊው ካተሪንን “በዓለም ውስጥ ታላቅ ሙዚዬም የሚገኘው በፓሪስ ውስጥ ነው። ሉቪሬን አይተሻል?” ሲል ጠየቃት ።

“አላየሁም” አለች ካተሪን ። “ወደፓሪስ ሄጄ አላውቅም ።”

“አትዪኝም! አንድ ቀን መሄድ ይኖርብሻል ። ” እነኚህን ቃላት ሲናገር በአሳቡ ግን ‘እንደማትሄጂ አውቃለሁ’ አለ ። “በለንደን የሚገኙ ሙዚዬሞችን ለመጐብኘት እፈልጋለሁ ። በመጪው ቅዳሜ ጥቂቶቹን ብናያቸውስ?”

ካተሪን በሚቀጥለው ቅዳሜ የተወዘፉ የቢሮ ሥራዎችን ለማከናወን ዕቅድ ቢኖራትም ኮንስታንቲን ዲሚሪስ እንግዶቹን በደንብ እንድትንከባ ከባቸው መመሪያ ስለሰጣት “እሺ” አለች ። “ቅዳሜ ይመቸኛል ።”

ካተሪን ቀኑን ሙሉ ከፈረንሣዊው ጋር ለማሳለፍ አልፈለገችም ። ‘ሰውዬው ፊቱ የማይፈታ ፣ መከራ ላይ ያለ ነው የሚመስለው’ ስትል አሰበች ።

ቀኑ በጥሩ ሁኔታ ተጀመረ ። በመጀመሪያ ወደእንግሊዝ ሙዚዬም ሄደው ጥንታውያን ቅርሶችን እየተዘዋወሩ ጐበኙ ። በቀዳማዊት ኤልሳ ቤጥ የተፈረመውን የማግና ካርታ ሰነድ ተመለከቱ ። ከማግና ካርታ በፊት መቶ ዓመት አስቀድሞ የተደረጉ የጦርነት ስምምነቶችም በሙዚዬሙ ውስጥ ነበሩ ።

ካተሪንን ስለ ዱቪ ሬናድ አንድ ያሳሰባት ነገር አለ ። በሙዚዬሙ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ያህል ከቆዩ በኋላ ነው ነገሩን ልብ ያለችው ።

በአድሚራል ሂልሰን የተጻፈው ዘገባ የተቀመጠበትን መደርደሪያ ይመለከቱ ነበር ።

“እዚህ ውስጥ ከሚገኙት ቅርሶች መካከል ይኸኛው በጣም ግሩም ይመስለኛል” አለች ካተሪን ። “ይህ የተጻፈው አድሚራል ኒልሰን ወደጦርነቱ ከመሄዱ በፊት ነው ። አይግረምህ ፣ ሥልጣን እንዳለው እንኳን …” ዱቪ ሬናድ እንደማያዳምጣት ወዲያውኑ ተረዳች ። ስታስታውሰው በጉብኝቱ ወቅት በሙሉ ሀሣቡ በቅርሶቹ ላይ ከቶ አልነበረም ። ጉዳዩ ከጉብኝቱ አይመስልም ‘ታዲያ ሙዚዬሞችን ለመጐብኘት እፈልጋለሁ ያለኝ ለምንድነው?’ አለችና በልቧ ተደነቀች ።

ወደቪክቶሪያና አልቤርት ሙዚዬም ሄደው እዚህም ተመሳሳይ ሁኔታ ተደገመ ። ካተሪን ሁኔታውን በደንብ መከታተል ጀመረች ። ዴቪ ሬናድ ከክፍል ወደክፍል እየተዘዋወረ እንደረካ አልፎ አልፎ ቢናገርም ትኩረቱ በሚያየው ላይ ሳይሆን ውጭ እንደሆነ ይታወቅበታል ።

ጉብኝታቸውን ሲጨርሱ ካተሪን "ዌስት ሚኒስተር አቤይን ለማየት ትፈልጋለህ?" ብላ ጠየቀችው ።

ዴቪ ሬናድ ጭንቅላቱን እወዛወዘና "እንዴታ በደንብ እፈልጋለሁ" ብሎ መለሰላት ።

ወደታላቁ አቤይ ሲጓዙ እግረ መንገዳቸውን በእንግሊዝ ታሪክ ውስጥ የታወቁ ባለቅኔዎች ፣ የአገሪቱ መሪዎችና ነገሥታት አፅም ያረፈበትን ከድንጋይ የታነፀ የመቃብር ሥፍራ ተመለከቱ ።

"ተመልከት" አለች ካተሪን ። "ይህ የብራውኒንግ መቃብር ነው ።"

ሬናድ ዞሮ ተመለከተና "አሃ ፣ ብራውኒንግ!" ብሎ ጉዞውን ቀጠለ ።

ካተሪን በጥሞና ትመለከተው ነበር ። 'የሚፈልገው ምንድን ነው? ለምን ቀኑን እንዲሁ ያቃዋላል?' አለች በአሳቧ ።

ወደሆቴላቸው ለመመለስ ጉዞ እንደጀመሩ ዴቪ ሬናድ እንዲህ አላት፦ "አመሰግናለሁ ሚስስ አሌክሳንደር ። በጉብኝቱ በጣም ተደስቻለሁ ።"

'ውሸቱን ነው' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'ግን ለምን?'

"ስቶንሄንግ የተባለው በጣም አስደላች ሥፍራ ከሳልስበሪ ሜዳ አጠገብ ይገኛል ሲሉ ሰምቻለሁ ።"

"አዎ" አለች ካተሪን ።

"ታዲያ ቢቻል ለምን በሚቀጥለው ቅዳሜ አንጐበኘውም?"

'ስቶንሄንግ ከሙዚዬሙ ይልቅ ሊያስደስተው ?' ስትል አባባሉን ለመቀበል ተጠራጠረች።

ሆኖም "እሺ ጥሩ ነው" ብላ መለሰች ካተሪን ።

ዲኖ ማቱሲ ምግብና መጠጥ ማግረጥ ይወዳል ። በከተማ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን የሚጠቁም አንስተኛ መጽሐፍ ይዞ

ወደካተሪን ቢሮ ገባ ። "በለንደን ውስጥ የታወቁ ምግብ ቤቶች ዝርዝር ይዣለሁ ፤ ለመጋበዝ ትፈልጊያለሽ?"

"መልካም ፣ እኔ ..."

"ጥሩ! ዛሬ ማታ ወደኮናውት እንሄድና እራት አብረን እንበላለን ።" ካተሪን "ዛሬ ማታ እኔ..." አለችው ።

"ምክንያት አልቀበልም ። ከምሽቱ በሁለት ሰዓት መጥቼ እውስድሻለሁ ።"

ካተሪን ካመነታች በኋላ "እሺ ደህና ።" ብላ መለሰች ።

የማቱሲ ፊት ፈካ ። "በቤኔ!" አለና ቀና ብሎ ተቀመጠ ። "ለብቻ ልደሰት ቢባል አይሆንም ። አይመስልሽም?" 'አባባሉማ ትክክል ነበር ። ሲያዩትም አደገኛ ሰው አይመስልም ።' ስትል አሰበች ።

በኮናውት የበሉት እራት በጣም ጣፋጭ ነበር ። የተጠበሰ የስኮትላንድ ዓሣና ጥብስ ሥጋ ፤ በቆርኖ ዱቄትና በሥጋ የተጠበሰ እንቁላል ቀርበላቸው ተመገቡ ።

ቀጥሎ ሰላጣና አትክልት እንደቀረበላቸው ዲኖ ማቱሲ "ካተሪን ፣ ደስ የምትዪኮ ነሽ ። አሜሪካውያን ሴቶችን እወዳለሁ" አላት ።

"አሃ ፣ ባለቤትህ አሜሪካዊት ናት ?" ስትል ካተሪን በየዋህነት ጠየቀችው ። ማቱሲ ትከሻውን ነቀነቀ ። "የለም ፤ እጣፈንጋይ ናት ። ቢሆንም ይህን ያህል ችግር የምትፈጥርብኝ ሴት አይደለችም ።"

"ይህማ ላንተ ጥሩ ነው" አለች ካተሪን ።

ፈገግ አለና "በጣም ጥሩ ነው እንጂ" ሲል መለሰ ።

በመጨረሻም ፍራፍሬ እንደቀረበላቸው ዲኖ ማቱሲ እንዲህ አላት፦

" ከከተማ ወጣ ማለቱ አያስደስትሽም? መኪና ያለው ጓደኛ ስላለኝ ለሽርሽር ወጣ ብንልስ?"

ካተሪን እምቢ ልትል ስትል ከመቅጽበት ዊም ታሰባት ። ብቸኛ ስለሆነ ወደገጠር እንሽራሸር ቢባል ደስ ሳይለው አይቀርም ። "ደስ ይለኛል" አለች ካተሪን ።

"በጣም እንደሚያስደስትሽ ቃል እገባልሻለሁ ።"

"ዊም አብሮን ቢሄድ ደስ ይለኛል ።"

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "መኪናዋ አነስተኛ ናት ። እስቲ እንድትዘጋጅ አደርጋለሁ ።"

ከአቴንስ የመጡት ጉብኝዎች ፍላጐት ብዙ በመሆኑ ካተሪን ለእራሷ ጉዳይ ጊዜው እያነሰባት መጣ ። ሃሌይ ፣ ሬናድና ማቱሲ ከዊም ቫንዲን ጋር ብዙ ጊዜ ተገናኝተው ተነጋግረዋል ። ከጊዜ በኋላ በእርሱ ላይ ያላቸውም አመለካከት እየተለወጠ መምጣቱ ካተሪንን አስደስቷታል ።

“ይህን ሁሉ ያለ ሂሣብ መሣሪያ ነው የሚሠራው?” ብሎ ተደነቀ ሃሌይ ።

“እም ።”

“እንዲህ ዓይነት ፍጡር አይቼ አላውቅም ።”

የአታናስ ስታቪችም ሁኔታ ካተሪንን እያስደነቃት ነው ። እንደዚህ ወጣት ያለ ጠንካራ ሠራተኛ አይታ አታውቅም ። ጠዋት ካተሪን ወደቢሮ ስትገባ ሁልጊዜ ቀድሟት በሥራ ላይ ይገኛል ። ማታም ሁሉ ሰው ከሄደ በኋላ ዘግይቶ ይሠራል ። ሁሌ ፈገግተኛ ከመሆኑም በላይ ሰዎችንም ለማስደሰት ይጥራል ። ካተሪን ባየችው ቁጥር ተሽቆጥቋጭ ቡችላ መስሎ ይታያታል ። ባለፈው ሕይወቱ ውስጥ ሰዎች ጎሊናውን የሚያቆስል ጭቆና ያደረሱበት ይመስላል ።

ካተሪን ከአላን ሃሚልተን ጋር ስትገናኝ ስለ አታናስ ልታጫውተው ወስናለች ። ‘በእራሱ እንዲተማመን አንድ ነገር መደረግ ይኖርበታል’ አለች በአሳቧ ። ‘አላን እንደሚረዳው እርግጠኛ ነኝ ።’

“ልጁ ከአንቺ ፍቅር እንደያዘው አታውቂም?” አለቻት ኤቪሊን አንድ ቀን ።

“ምንድነው የምትዪው?”

“ስለአታናስ ነዋ የምናገረው ። የማፍቀር ሁኔታ ከዓይኑ ውስጥ አይታይሽም ? በግ እንደጠፋበት እረኛ ዓይኑን ያንከራትታል ።”

ካተሪን ሳቀች ። “አንቺ ደግሞ የማይሆን ነገር ነው የምታስቢው ።”

ሳታውቅ አታናስን “ምሣ ልጋብዝህ” አለችው ።

“ሬ–ሬስቶራንት ውስጥ?”

ካተሪን ፈገግ አለች ። “አዎ”

ፊቱ ፈካ ። “እ–እንጃ ሚስስ አሌክሳንደር ።” ያልፀዱ ልብሶቹን ተመለከተ ። “ይህንን ለብሼ ካንቺ ጋር ስታይ በሰዎች ዘንድ ላሳፍርሽ እችላለሁ ።”

“እኔ ሰዎችን የምለካው በአለባበሳቸው አይደለም” አለች ካተሪን ቅጭም ብላ ። “ቦታ እንዲያዝልን አደርጋለሁ ።”

አታናስን በሊናስ ኮርነር ሃውስ ምሣ ጋበዘችው ። ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ በአካባቢው በሚታየው ሁሉ መደነቅ ጀመረ ። “እኔ– እኔ ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነት ቦታ ተገኝቼ አላውቅም ። በጣም የሚያምር ነው ።”

ካተሪን በአነጋገሩ ተነካች ። “የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማዘዝ ትችላለህ ።”

የምግቡን ዝርዝር አነበበና ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “ሁሉም በጣም ውድ ነው ።”

ካተሪን ፈገግ አለች ። “ለዋጋው አትጨነቅ ። እኔና አንተ በጣም ሀብታም የሆነ ሰው ተቀጣሪ ነን ። ደህና ምሣ እንድንመገብ የሚፈልግ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ ።” የምትከፍልለት እርሷ መሆኗን ግን አልገለጸች ለትም ።

አታናስ የሽሪም ኮክቴል ፣ ሰላጣ ፣ የዶሮ ጥብስና የተጠበሰ ድንች እዘዘና ተመገበ ። በመጨረሻም እንዲመጣለት የጠየቀው የቸኮሌት ኬክና አይስ ክሬም ነበረ ።

ካተሪን ልጁ ሲመገብ በአድናቆት ትመለከተዋለች ። ሰውነቱ ቀጫጫ በመሆኑ “ይህንን ሁሉ የት ነው የምትከተው?” ስትል ካተሪን ጠየቀችው ።

አታናስ በሐፍረት “እኔ እንጃ ፣ ወፍሬ አላውቅም” አላት ።

“ለንደን ደስ ይለሃል አታናስ?”

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “እስካሁን ባየሁት ተደስቻለሁ ።”

“አቴንስ ውስጥ የቢሮ ተላላኪ ነበርክ?”

አሁንም ጭንቅላቱን በአዎንታ አነቃነቀ ። “አዎ የሚስተር ዴሚሪስ ተላላኪ ነበርኩ” አለ ። ንዴትና ቁጭት ይታይበታል ።

“ሥራውን ትወደው ነበር?”

“ይቅርታ አድርጊልኝና ፣ ስለዚያ ጉዳይ መነጋገሪያ ሥፍራው እዚህ አይመስለኝም ። ግን ሚስተር ዴሚሪስ ጥሩ ሰው አይደለም ። እኔ ...እኔ አልወደውም ።” ወጣቱ ልጅ የተናገረውን ነገር የሚሰማበት ሰው ያለ ይመስል ዙሪያውን ተገላምጦ ተመለከተ ። “እርሱ– ለሰው ግድ የለውም።”

ካተሪን ስለዚሁ ጉዳይ እንዲናገር ብዙ ላለመገፋፋት ፈለገች ።

“ለምን ወደ ለንደን ለመምጣት ፈለግህ አታናስ?”

ዝቅ ባለ ድምፅ የተናገረው ለካተሪን አልተሰማትም ።

“ምን አልከኝ? አልሰማሁህም ።”

“ዶክተር ለመሆን ስለምፈልግ ።”

በመገረም ትኩር ብላ አየችው ። “ዶክተር?”

“አዎ እመቤቴ የሞኝ አስተሳሰብ ሊመስልብኝ ይችል ይሆናል ።” ትንሽ አመነታና ንግግሩን ቀጠለ ። “ቤተሰቦቼ የመጡት ከመቅዶንያ ነው። ከልጅነት ጀምሮ ቱርኮች ወደመንደራችን እየመጡ ነዋሪውን ሲያሰቃዩና ሲገድሉ እንደነበር ተደጋግሞ ሲነገር እሰማለሁ ። በቱርኮች ግፍ የቆሰሉትን ወገኖቼን የሚረዱ ሐኪሞች አልነበሩም ። አሁን መንደሩ ተደምስሶ ነዋሪዎቹ ሁሉ ተፈናቅለዋል ። ለዚያ ብቻ ሳይሆን አሁንም በመላ ዓለም ብዙ የቆሰሉና እርዳታን የሚሹ በርካታ ሰዎች አሉ ። እነኚህኑ ለመርዳት እፈልጋለሁ ።” በሐፍረት ዓይኑን አቀረቀረ ። “በአነጋገሬ እብድ ነው ሳትዪኝ አትቀሪም ።”

“አልልም” አለች ካተሪን በለሆሳስ ። “በጣም ጥሩ አሳብ ይመስለኛል ። እና ወደ ለንደን የመጣኸው ስለሕክምና ልታጠና ነው?”

“አዎ እመቤቴ ቀን ቀን እየሠራሁ ማታ ማታ ለመማር እፈልጋለሁ። ዶክተር መሆን አለብኝ ብዬ ቆርጬ ተነስቻለሁ ።”

በአነጋገሩ ላሰበው ነገር ቆርጦ የተነሳ ይመስላል ። ካተሪን ሞንቅላቷን አወዛወዘች ። “ልታደርግ እንደምትችል እተማመናለሁ ። እኔና አንተ ስለዚሁ በሰፊው እንነጋገራለን ። ሊረዳህ የሚችልም ጓደኛ አለኝ ። አንድ የማውቀው ጥሩ ሆቴል አለ ፤ በሚቀጥለው ሳምንት እዚያ ምሣ እንበላለን ።”

እኩለ ሌሊት ላይ በስፔሮስ ላምብሩ ቪላ ቤት ውስጥ ቦንብ ፈነዳ ። ፍንዳታው የቪላውን የፊትለፊት ክፍል አፈራርሶ ሁለት ሠራተኞችን ገድሏል ። የሰፔሮስ ላምብሩ መኝታ ክፍልም በፍንዳታው ተደርምሷል ። ላምብሩ ከዚህ አደጋ ሊያመልጥ የቻለው እቤት ለመቆየት የነበረውን አሳብ ቀይሮ የአቴንስ ከተማ ከንቲባ ባደረጉት የእራት ግብዣ ላይ ከባለቤቱ ጋር በመገኘቱ ነው ።

በሚቀጥለው ቀን አንድ ማስታወሻ ወደ ቢሮው ተላከ ። ‘ሞት

ለካፒታሊስቶች’ ይላል ። የሄሊኒክ አብዮታዊ ፓርቲ ማህተም ሰፍሮበታል ።

“እንዲህ ዓይነት ነገር ለምን ባንተ ላይ ይፈጽማሉ?” ስትል በፍርሃት የተዋጠች ሜሊና ጠየቀችው ።

“እነርሱ አይደሉም” አለ ስፒሮስ ። “ይህንን ያደረገው ኮስታ ነው።”

“እንዲህ – እንዲህ ለማለት ምን መረጃ አለህ?”

“ማስረጃ አያስፈልገኝም ። ያገባሽውን ሰው አውንም በደንብ አላወቅሽም ማለት ነው!”

“ምን – ብቻ ፣ ምን ለማለት እንደምችል አላውቅም ።”

“ሜሊና ፣ ሰውዬው በሕይወቱ እስካለ ድረስ የሁለታችንም ሕይወት አደጋ ላይ ነው ። ካሰበው ነገር የሚገታው ምንም ነገር አይኖርም።”

“ሄደህ ጉዳዩን ለፖሊስ መንገር አትችልም ?”

“አንቺ እራስሽ ተናግረሽ ጨርሰሽዋል ። ምንም ማስረጃ የለኝም ። ፖሊሶች ሊስቁብኝም ይችላሉ ።” እጇን ሳብ አደረገና ያዛት ። “ከዚህ አካባቢ ዞር እንድትዪ እፈልጋለሁ ። እባክሽ የሚቻልሽን ያህል ርቀሽ ሂጂ ።”

ከነበረችበት ቆማ ቀረች ። በመጨረሻ ቃላት ስትወረውር ከአንድ ውሳኔ ላይ የደረሰች ትመስል ነበር ። “መልካም ስፒሮስ ፣ ማድረግ የሚገባኝን እፈጽማለሁ ።”

እቅፍ አደረጋት ። “ጥሩ ፣ ግን ብዙም አትጨነቂ ። ከዚህ አድራጐቱ የሚገታበትን ዘዴ እንፈልጋለን ።”

ሜሊና ከቀትር በኋላውን በሙሉ በመኝታ ቤቷ ውስጥ ተቀምጣ ሰለተፈጸመው ነገር ስታወጣና ስታወርድ ቆየች ። እና ባለቤቷ በፎከረው መሠረት እርሷንና ውንድሟን ለማጥፋት ቆርጦ ተነስቷል ። እጇን አጣጥፋ ልታየው አትችልም ። የእነርሱ ሕይወት አደጋ ላይ እስካለ ድረስ የካተሪን ዶግላስም መኖር በአስጊ ሁኔታ ላይ ነው ለማለት ይቻላል ። ‘ለንደን ውስጥ ሥራ ትሠራልናለች ። አስጠነቅቃታለሁ ።’ አለች ሜሊና በአሳቧ ። ‘ከዚህም የበለጠ ነገር ማድረግ ይገባኛል ። ኮስታን ማጥፋት አለብኝ ። ማንንም ሰው እንዳይጐዳ ማድረግም ይኖርብኛል ። ግን እንዴት ?’ ምላሹንም ወዲያው አገኘች ። ‘ልክ ነው ብቸኛው መንገድም ያ ብቻ ነው ። ግን እንዴት ቀደም ብሎ አልመጣልኝም ?’

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ምሥጢራዊ ማኅደር

ከካተሪን ዶግላስ ጋር የተካሄደ ውይይት ዶሴ

ካተሪን ፦ በመዘግየቴ ይቅርታ አላን ። ከቢሮዬ ልወጣ ስል ስብሰባ አጋጠመኝ ።

አላን ፦ ግድ የለም ። ከአቴንስ የመጡት ልዑካን አሁንም ለንደን ናቸው?

ካ ፦ አዎ ። በሚቀጥለው – በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሰው ሊሄዱ ያስባሉ ።

አ ፦ የሰለቸሽ ይመስለኛል ። በጣም አስቸግረውሽ ነበር እንዴ ?

ካ ፦ የለም ይህን ያህል እንኳን አልተቸገርኩም ። ግን…ግን የነሱ ነገር ግራ ግብት ብሎኛል ።

አ ፦እንዴት?

ካ ፦ በቃላት ለመግለፅ ያስቸግረኛል ። ምናልባት ከሞኝነቴ መንጭቶ ይሆናል… ሁሉም ላይ ለየት ያለ ነገር አያለሁ ።

አ ፦ አንቺን ያስቀየሙት ነገር አለ? አንቺ ላይ …

ካ ፦ የለም ። ብቻ አጣብ ውስጥ ጣሉኝ ። ትናንት ማታ እንደገና ያ አስፈሪ ቅዠት መጣብኝ ።

አ ፦ ሰው ከባሕር ሊያሰምጥሽ የሚሞክርበት ሕልም?

ካ ፦ አዎ። እንደዚያ ዓይነቱን ሕልም ደግሚ ሳላይ ቆይቼ ነበር ። ያሁኑ ደግሞ ለየት ያለ ነው ።

አ ፦ የሚለየው በምን ዓይነት ነው?

ካ ፦ ነገሩ የበለጠ …እውነታን ያዘለ ይመስላል ። በፊት ከቆመበት በመቀጠል ረዥም ሕልም ሆኗል ።

አ ፦ ሰው ሊያሰጥምሽ ከሞከረበትም አልፎ ተጨማሪ ሕልም ታየሽ?

ካ ፦ አዎ ። ሊያሰጥሙኝ ይታገላሉ ። ወዲያው ሕይወቴ ከተረፈበት ሥፍራ እራሴን አገኘሁ ።

አ ፦ በሴቶቹ ገዳም ውስጥ?

ካ ፦ እርግጠኛ አይደለሁም ። ሊሆንም ይችላል ግን የአትክልት ቦታ ውስጥ ነው ። እና አንድ ሰው ሊያነጋግረኝ መጣ ። እንደሚመስለኝ በፊትም እንደዚያ ዓይነት ሕልም አልሜአለሁ ። አሁን ግን የሰውዬውን ፊት በደንብ አይቻለሁ ።

አ ፦ ሰውዬው ማን እንደሆነ አውቀሻል?

ካ ፦አዎ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ።

አ ፦ እና በሕልምሽ ውስጥ…

ካ ፦ አላን ፣ ነገሩ ሕልም አይደለም ። እውነተኛው የማስታወስ ችሎታዬ ተመልሶ መምጣቱ ነው ። አሁን ያለኝን የወርቅ የደረት ጌጥ ሰጥቶኝ የነበረው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሆኑን አስታውሻለሁ ።

አ ፦ ውስጠ ህሊናሽ ከዚህ በፊት በእውን የተፈፀመውን ይፋ አውጥቶ እንዳሳየሽ እድርገሽ ነው የምትገምቺው? እርግጠኛ ነሽ? ያየሺው…

ካ ፦ እርግጠኛ ነኝ ያንን የደረት ጌጥ በሴቶቹ ገዳም ውስጥ የሰጠኝ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ።

አ ፦ በባሕሩ ከመስጠም የተረፍኩት መነኮሳት ደርሰውልኝ ወደገዳሙ ስለወሰዱኝ ነው ብለሽ ታምኚያለሽ?

ካ ፦ በደንብ ።

አ ፦ ካተሪን ፣ የሴቶቹ ገዳም ውስጥ እንደነበርሽ የሚያውቅ ሌላ ሰው አለ?

ካ ፦ የለም ፣ ያለ አይመስለኝም ።

አ ፦ ታዲያ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እዚያ መኖርሽን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

ካ ፦ እኔ–እኔ እንጃ ። የማስታውሰው ነገሩ ተፈጽሞ እንደነበረ ነው ። ከእንቅልፌ የነቃሁትም በፍርሃት ተውጨ ስለነበረ ሕልሙ እንደ ማስጠንቀቂያ ዓይነት ነገርም መስሎ ተሰምቶኛል ። አንድ እደገኛ ነገር ይፈጸምብኛል የሚል ስጋት አድሮብኛል ።

አ ፦ በእርግጥ ቅዠት እንደዚያ ዓይነት ሥጋት እንዲያድርብን ያደርጋል። ቅዠት የሰው ልጅ ጠላት ነው ። ዘመኑ ያለፈበት ከንቱ እምነት እንደሚያወሳው ከሌሊቱ ከአሥር ሰዓት በኋላ ነው ሰው በቅዠት የሚጨነቀው ይባላል ።

ካ ፦ ከእውነት ጋር የተያያዘ ትርጉም የላቸውም ነው የምትለው፣

አ ፦ አንዳንዴ ሊኖራቸው ይችላል ። ኮለሪጅ ሲፅፍ "ሕልም ጥላ ሳይሆን የሀዘኔና የሕይወቴ ቁም ነገር ነው" ብሏል ።

ካ ፦ እንደትልቅ ቁም ነገር አጋንኜ ተርጉሜው ይሆናል ። ብቻ ከዚህ አስፈሪ ቅዠት በስተቀር ደህና ነኝ ። አሃ ፣ ስለአንድ ሰው ላነጋግርህ እፈልጋለሁ አላን ።

አ ፦ እሺ ።

ካ ፦ አታናስ ስታሺች ይባላል ። ወደለንደን የሕክምና ትምህርት ሊከታተል የመጣ ወጣት ነው ። ሕይወቱ ወጣ ገባ የበዛበት ይመስላል ። አንድ ቀን አግኝተኸው ጥሩ ምክር ብትሰጠው ይጠቅመዋል ብዬ እገምታለሁ ።

አ ፦ ደስ ይለኛል ። ግን ግንባርሽን ለምንድነው የምትቋጥሪው?

ካ ፦ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው ።

አ ፦ ምን?

ካ ፦ የማይረባ ነገር ነው ።

አ ፦ ውስጠ ኅሊናችን ይረባል አይረባም አይልም ።

ካ ፦ በሕልሜ ሚስተር ዴሚሪስ የወርቅ የደረት ጌጡን ሲሰካልኝ…

አ ፦ እሺ?

ካ ፦ "ሊገድልሽ ነው" የሚል ድምፅ ሰማሁ ።

'ድንገተኛ አደጋ መምሰል አለበት ። ማንም ሬሳዋን ለይቶ እንዲያውቅ አልፈልግም ።' እርሷን ለመግደል ብዙ ዘዴዎች አሉ ። ካሁኑ ዝግጅት ማድረግ ሊኖርበት ነው ። አልጋው ላይ ተንጋሎ ስለአገዳደሏ ሲያሰላስል የወሲብ ፍላጐቱ ተቀሰቀሰበት ። የመጨረሻ ደረጃ እርካታውን የሚያስገኝለት ሞት ነው ። ይህም እንዴት እንደሚከናወን ወደኋላ ላይ ተገልጸላታል ። ቀላል ጉዳይ ነው ። ምስጢሩን ሊያውቅ የሚችል በሕይወት የተረፈ ላይገኝ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስንም በጣም ደስ ይለዋል ።

ምዕራፍ ሃያ ሦስት

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ መዝናኛ ቤት ከፒራኡስ ወደብ ሦስት ግዩልስ ያህል ርቆ ከባሕሩ ዳርቻ ላይ ይገኛል ። ዴሚሪስ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ላይ እዚያ እንደደረሰ መኪናውን ከጎዳናው ጥግ አቁሞ ከፈተና ወርዶ ወደቤቱ አመራ ።

እንደደረሰ በማያውቀው ሰው በሩ ተከፈተለት ።

"እንደምን አመሸህ ሚስተር ዴሚሪስ ።" ዴሚሪስ በርካታ ፖሊሶችን እቤቱ ውስጥ አየ ።

"እንዴ! እዚህ ምን ትሠራላችሁ?" ሲል ዴሚሪስ ጠየቀ ።

"እኔ የፖሊስ መቶ አለቃ ቲዮፊሉስ ነኝ ። እኔ…"

ዴሚሪስ ወደጎን ገፈተረውና ወደሳሎኑ ገባ ። ቤቱ ተመሰቃቅሏል ። ድብልቅልቁ የወጣ ትንቅንቅና ግርግር የተካሄደበት ይመስላል ። ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ተገለባብጠዋል ። ዴሚሪስ ፡ ተቀዶ ከወለሉ ላይ የተጣለውን የሚሊና ልብስ ትኩር ብሎ አየው ።

"ባለቤቴ የት ነው ያለችው? ከእርሷ ጋር እዚህ ለመገናኘት ቀጠሮ ነበረን ።"

መቶ አለቃው "እዚህ የለችም ። ቤቱ ውስጥና ውጪም የባሕር ዳርቻውን ዙሪያ ፈልገናት አላገኘናትም ። ቤቱ በሴባ ሳይመዘበር አልቀረም ።"

"እና ታዲያ ሚሊና የት ናት? እሷ ናት የደወለችላችሁ? እዚህ ነበረች እንዴ?"

"አዎ ፣ እዚህ የነበረች ይመስለናል ጌታዬ ።" አንድ መስታወቱ የተሰበረበት የሴት ሰዓት በእጁ ይዟል ። ሰዓቱም ልክ ዘጠኝ ላይ ቆሟል ። "ይህ የባለቤትህ ሰዓት ነበር ?"

"እዎ ይመስላል ።"

ከሰዓቱ ጀርባ ላይ "ለሚሊና ከአፍቅሮት ጋር የተሰጠ – ኮስታ" የሚል ጽሑፍ ሰፍሯል ።

"እዎ ነው ። ለልደት በዓሏ ያበረከትኩላት ስጦታ ነበር ።"

መርማሪ ቲዮፊሉስ ወደ ምንጣፉ አመለከተ ። "እነዚህ የደም ነጠብጣቦች ናቸው ። አሻራው እንዳያልፍበት ተጠንቅቆ መሬት ላይ የወደቀውን ጩቤ አነሳ ። የጩቤው ስለት በደም ተበክሏል ።

"ይህንን ጩቤ ከዚህ በፊት አይተህ ታውቃለህ ጌታዬ ?"

ዴሚሪስ ለአጭር ጊዜ ጩቤውን ተመለከተ ። "እንዴ! ሞታለች ልትለኝ ነው?"

"መሰለኝ ጌታዬ ። በእሽዋው ላይ የታየንን የደም ነጠብጣብ እየተከተልን ስንሄድ ከባሕሩ አጠገብ አደረሰን ።"

"አቤት አምላኬ !" አለ ዴሚሪስ።

"እንዳጋጣሚ በጩቤው ላይ የጣት አሻራ ቀርቶልናል ።"

ዴሚሪስ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ።

"እንዲያ ከሆነ ልትይዙት ትችላላችሁ ።"

"የጣት አሻራው በግኅደራችን ውስጥ ካለው ጋር ከተመሳሰለ እንያዘዋለን ። በቤቱ ውስጥ በርካታ የጣት አሻራዎች አግኝተናል ። እና እየለየን ማገናዘብ ሊኖርብን ነው ። ሚስተር ዴሚሪስ የጣት አሻራህን ልትሰጠን ትችላለህ?"

ዴሚሪስ ካመነታ በኋላ "እሺ ምንም ችግር የለም ።"

"ለዚያኛም የሃምሣ አለቃ ስጠው ።"

ዴሚሪስ የደንብ ልብስ ለብሶ የጣት አሻራ መቀበያውን ወደያዘው ፖሊስ ሄደ ። "እባክዎ ጌታዬ ፣ ጣትዎችዎን እዚህ ላይ ያኑሩት" አለውና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሥራው ተጠናቀቀ ። "እንዲሁ ለደንቡ ስንል ነው ።"

"ይገባኛል ።"

የመቶ አለቃ ቲዮፊሉስ ለዴሚሪስ ካርድ ሰጠው ። "ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ስለዚህ የምታውቀው ነገር አለ ?"

ዴሚሪስ ካርዱን ሲያይ "ካቴላኖስ የምርመራ ድርጅት—የግል ተቋም" የሚል ተጽፎበታል ። ካርዱን መልሶ ለመቶ አለቃው ሰጠው ። "የማውቀው ነገር የለም ። ግን ካርዱ ከገዳዩ ጋር የተያያዘ ነው ?"

"አላውቅም ፣ እያጣራን ነው ።"

"በጣም ጥሩ ፣ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚቻልህን ሁሉ እንድታደርግ እፈልጋለሁ ። ባለቤቴ የተናገረችው ነገር ካለም ብትነግረኝ ደስ ይለኛል ።"

የመቶ አለቃ ቲዮፊሉስ አየውና በአዎንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "እታስብ ጌታዬ ሁሉንም ነገር እናደርጋለን ።"

ሚሊና ፣ ቆንጆ ፣ ብሩህና ደስ የምታሰኘዋ ወርቅ ልጅ ። ቀደም ሲል ሁሉም ነገር አስደሳች ነበር ። ከዚያ በኋላ ግን ወንድ ልጃቸውን በመግደሏ ይቅርታ የማይደረግላት ሆነ ። የጠበቃት ሞት ብቻ ነው ።

* * *

የስልክ ጥሪው የተደረገው በሚቀጥለው ቀን ስድስት ሰዓት ላይ ነበር ። ፀሐፊው የውስጥ ስልክ ጥሪ ስታደርግለት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስብሰባ በማካሄድ ላይ ነበረ ።

"ይቅርታ ሚስተር ዴሚሪስ ..."

"እንዳታቋርጪኝ ብዬሽ አልነበረም ?"

"ነበር ጌታዬ የፖሊስ ባልደረባው ተቆጣጣሪ ላቫኖስ በስልኩ መስመር ላይ ሆኖ ነገሩ በጣም አስቸኳይ ነው ስላለኝ ነው ። ስብሰባ ላይ ስለመሆንህ እንድነግረው ..."

"ግደ የለም አንጋግረዋለሁ ።" ዴሚሪስ በስብሰባ ጠረጴዛው ዙሪያ ወደተቀመጡት ሰዎች ዞር አለ ። "ለጥቂት ጊዜ ይቅርታ አድርጉልኝ ጌቶቼ" ብሎ የስልኩን እጀታ አንስቶ "ዴሚሪስ ነኝ" አለ ።

"ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ከማዕከላዊ ጣቢያ ተቆጣጣሪ ላቫኖስ ነኝ ። ይጠቅምሃል ብለን የምንገምተው አንድ መረጃ አለን ። ወደፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለመምጣት ትችላለህ ?"

"የባለቤቴን ጉዳይ ደረሳችሁበት ?"

"በስልክ ባንነጋገር አይሻልም ?"

ዴሚሪስ ትንሽ አመነታ ። "አሁኑኑ እመጣለሁ ።" ስልኩን ዘጋና

ወደ ሰዎቹ ዞር አለ ። “አንድ አስቸኳይ ጉዳይ አጋጥሞኛል ። ለምን ወደምኀብ አዳራሹ ገብታችሁ ባቀረብኩት አሳብ ላይ አትወያዩም ? እኔም ተመልሼ በምላ ላይ እንገናኛለን ።”

በአሳቡ ተስማሙ ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ዲሚሪስ ወደ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያው ጉዞውን ቀጠለ ።

በርካታ ሰዎች በፖሊስ ኮሚሽነሩ ቢሮ ውስጥ ይጠብቁት ነበር ። ዲሚሪስ በባሕር ዳርቻ ቤቱ ውስጥ ያያቸውን ፖሊሶች አስታወሳቸው ። “... ይህ ዲልማ ይባላል ። ልዩ የሕግ አስከባሪ ነው ።”

ዲልማ ከቁመቱ አጠር ብሎ ደንደን ያለ ፣ ቅንድቡ ግጥም ያለ ፣ ተጠራጣሪ ዓይናች ያሉት ፣ ፊቱ ክብ የሆነ ሰው ነው ።

“እንዴት ሆነ ?” አለና ዲሚሪስ ጠየቀ ። “ስለ ባለቤቱ አወቃችሁ?”

ዋናው ተቆጣጣሪ እንዲህ አለ፡— “ሚስተር ዲሚሪስ በግልጽ ለመናገር ያህል አንድ በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር አጋጥሞናል ። ይህን በተመለከተ እንደምትረዳን ተስፋ እናደርጋለን ።”

“ብዙም ልረዳችሁ የምችል አይመስለኝም የሚዘገንን ነገር ነው ። ...”

“ባለቤትህን ትናንት ከሰዓት በኋላ በባሕር ዳርቻው ቤትህ ልታገኛት ቀጠሮ ሰጥተህት ነበር ?”

“ምን ? በፍጹም ። ሚስስ ዲሚሪስ ራሷ ናት ደውላ በአንድ ሰዓት እንድንገናኝ የጠየቀችኝ ።”

የሕግ አስከባሪው ዲልማ በእርጋታ “እኛንም ያምታታን ይኸው ነው። በስምንት ሰዓት ገደማ ለባለቤትህ ስልክ ደውለህ ወደባሕር ዳርቻው ቤትህ ብቻዋን ሄዳ እንድትጠብቅህ እንደነገርካት የቤት ሠራተኛህ ነግራናለች ።”

ዲሚሪስ ግንባሩን ቋጠረ ። “ተምታቶባት ነው ። ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ቤቱ ውስጥ እንድንገናኝ ደውላ የጠየቀችኝ ባለቤቱ ናት ።”

“እሺ ። እና ሠራተኛዋ ተሳስታለች ማለት ነዋ !”

“ያልጥርጥር ።”

“ባለቤትህ ወደ ባሕር ዳርቻው ቤት እንድትመጣ አንተን የጠየቀችበት ምክንያት ምን ይመስልሃል ?”

“እንድፈታት ልትጠይቀኝ ይመስለኛል ።”

“ልትፈታት ግቱድህን ለባለቤትህ ገልጸህላት ነበር ?”

“አዎ ።”

“ሚስስ ዲሚሪስ ልትፋታ እንደምትፈልግ በስልክ ስትነግርህ መስማቷን የቤት ሠራተኛዋ ነግራናለች ።”

“ሠራተኛዋ ለምትቀባጥረው ደንታ የለኝም ። ቃሌን አምናችሁ መቀበል ይኖርባችኋል ።”

“የዋና ልብስህን በባሕር ዳርቻ ቤት ውስጥ ነው የምታኖረው ?” ሲል ዋናው ተቆጣጣሪ ጠየቀ ።

“በባሕር ዳርቻ ቤት ውስጥ ? በፍጹም በባሕር ውስጥ መዋኘት ከተውኩ ዓመት አልፎኛል ። የምዋኘው በከተማ በሚገኙት ቤቶች አካባቢ በሠራኋቸው የመዋኛ ቦታዎች ነው ።”

ዋናው ተቆጣጣሪ የጠረጴዛውን መሳቢያ ከፈተና የፕላስቲክ ከረጢት አውጥቶ የዋና ልብሶችን እየመዘዘ ለዲሚሪስ አሳየ ። “እነዚህ የዋና ልብሶችህ ናቸው ሚስተር ዲሚሪስ ?”

“የእኔ ሊሆኑ ይችላሉ እዎ ይመስለኛል ።”

“ስምህ በላያቸው ተጽፏል ።”

“አዎ ። አስታውሳለሁ ፣ የእኔ ናቸው ።”

“ከባሕር ዳርቻው ቤት ውስጥ ከቱም ሳጥን ሥር ነው ያገኘናቸው ።”

“እና ! ምናልባት ከረዥም ጊዜ በፊት እዚያው ተትተው ይሆናል ። ለምን ... ?”

“ልብሶቹ በውሀ ርሰዋል ። የተካሄደው ምርመራ እንደሚያመለክተው ልብሱን ያራሰው ውሀ ቤቱ ፊት ለፊት ካለው የባሕር ውሀ ጋር አንድ ዓይነት ነው ። በልብሶቹ ላይ የሚታየው ቀያይ ነገር ደም ስለመሆኑ ተረጋግጧል ።”

ከፍሉ በጣም ይሞት ጀመር ።

“እና ሌላ ሰው ለብሶት ነበር ማለት ነው” አለ ዲሚሪስ ቆፍጠን ብሎ ። ልዩ ሕግ አስከባሪው “ለምን ብሎ ሌላ ሰው ይለብሰዋል ? ግራ

የገባንም ይሄው ነው ሚስተር ዴሚሪስ ።”

ዋና ተቆጣጣሪው ኤንቪሎፕ ከፈተና የወርቅ አዝራር አወጣ ። “እንዱ መርማሪዬ ይህንን ከምንጣፉ ሥር አገኘው ። ይህን አይተህ ታውቃለህ ?”

“አይቼ አላውቅም ።”

“ከአንደኛው ጃኬትህ ላይ የተበጠሰ ነው ። በተሰጠን ሥልጣን መሠረት ዛሬ ጠዋት ወደ ቤትህ ሄደን ቁምሳጥኑን ስንፈትሽ የአንደኛው ጃኬትህ ቁልፍ ተበጥሶ ነው ያገኘነው ። ቁልፉ የተሰፋበትም ከር ከሌላው ጋር አንድ ነው ። ጃኬቱም ከላውንደሪ የወጣው ከሳምንት በፊት መሆኑን ተረድተናል ።”

“እኔ እንጃ ...”

“ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ባለቤትህን ልትፈታ መፈለግህን እንደነገርካትና እርሷም ስለዚሁ ልታነጋግርህ እንደምትፈልግ ገልጠህልን ነበር ።”

“ትክክል ነው ።”

ከአንድ ቀን በፊት በባሕር ዳርቻው ቤት ውስጥ ለዴሚሪስ ስለተሰጠው ካርድ ተቆጣጣሪው አነሳ ። “አንዱ ባልደረባችን ዛሬ የካቴላኖስን የምርመራ ድርጅት ጎብኝቶ ነበር ።”

“እኔኮ ነግሬሃለሁ—ስለዚህ ድርጅት ሰምቼ አላውቅም ።”

“ባለቤትህ እራሷን ለማስጠበቅ ቀጥራቸው ነበር ።”

የሰማው በጣም አስደንጋጭ ሆነበት ። “ሜሊናን ? ከምን እንዲጠብቋት ?”

“ከአንተ እንዲጠብቋት ። ባለቤትህ እፈታሃለሁ እያለች ታስፈራራህ እንደነበረ የድርጅቱ ባለቤት ገልጦልናል ። አንተም በዚህ አሳቧ የምትገፋበት ከሆነ እንደምትገላት ማስጠንቀቂያ እንደሰጠህት ተረድተናል ። ሚስትህ ለምን ለጥበቃ ወደ ፖሊሶች ዘንድ እንደማትሄድ ቢጠይቃት ጉዳዩ በምስጢር መያዝ ስላለበት መሆኑን ነግራዋለች ። በይፋ እንዲታወቅ አልፈለገችም ነበር ።”

ዴሚሪስ ተነስቶ ቆመ ። “እኔ እዚህ ዝም ብዬ ተቀምጬ ይህን ሁሉ ውሸት ላዳምጥ አልችልም ። ምንም ...”

ተቆጣጣሪው የጠረጴዛ ኪሱን ሳበና ከባሕር ዳርቻ ቤቱ ውስጥ የተገኘውንና በደም የተበከለውን ጩቤ አወጣ ።

“በባሕር ዳርቻ ቤቱ ውስጥ መኮንኑ በጠየቀህ ጊዜ ጩቤውን

አይተኸው እንደማታውቅ ገልጸህለት ነበር ።”

“ትክክል ።”

“ግን በጩቤው ላይ ያለው የጣት አሻራ ያንተ ነው ።”

ዴሚሪስ ጩቤውን አተኩሮ አየ ። “የእኔ—የእኔ የጣት አሻራ ? ተሳስታችኋል ። ግምታችሁ ትክክል አይደለም ።”

አእምሮው ተበታትኖ በአሳብ መብከንከን ጀመረ ። እስካሁን በእርሱ ላይ ስለተጠናቀሩት ማስረጃዎች ማሰላሰል ጀመረ ። ‘የቤት ሠራተኛዋ እንዳለችው በስምንት ሰዓት ለሚስቱ ደውሎ ወደባሕር ዳርቻው ቤት ብቻዋን እንድትሄድ መንገሩ ... በሁለት የመዋኛ ትጥቅ ላይ የደም ነጠብጣቦች መታየታቸው ... ከጃኬቱ የተበጠሰ አዝራር ... የጣት አሻራው ያለበት ጩቤ ።’

“ይህ ሆነ ተብሎ የተቀነባበረ ስለመሆኑ እናንተ ደደቦች አይገባችሁም ?” አለና አንቧረቀባቸው ። “ሌላ ሰው የዋና ልብሶቹንና ጩቤውን ወደ ባሕር ዳርቻ ቤቱ ወስዶ ደም ቀብቶዋቸው የጃኬቱን አዝራር ደግሞ በጥሶ ...”

ልዩ ሕግ አስከባሪው አቋረጠው ። “ሚስተር ዴሚሪስ ፡ የጣት አሻራህ እንዴት በዚህ ጩቤ ላይ ሊያርፍ እንደቻለ ልታስረዳን ትችላለህ ?

“እኔ—እኔ አላውቅም ... ቆዩኝ ። አዎ አሁን አስታወስኩ ። ሜሊና የተጠቀለለ ፓኮ እንድከፍትለት ይህንን ጩቤ ሰጥታኝ ነበር ። የጣት አሻራዬም በጩቤው ላይ የተገኘው ፓኮውን ስቀድበት ነው ።”

“ጥሩ ፡ በፓኮው ውስጥ ምን ነበር ?”

“እኔ ... አላውቅም ።”

“በፓኮው ውስጥ ምን እንደነበረ አታውቅም ?”

“አዎ አላወቅኩም ። ፓኮው ታስሮበት የነበረውን ገመድ ብቻ በጥቼ ሰጠኋት ። እኔ ፊት አልከፈተችውም ።”

“በምንጣፉ ላይ ባሕሩ አጠገብ እስኪደርስ ድረስ በአሸዋው ላይ የተንጠባጠበውን ደም ሁኔታስ ልትገልጽልኝ ትችላለህ ? ...”

“እርሱማ ግልጽ ነው” አለ ዴሚሪስ ። ወዲያው “ሜሊና ራሷን ትንሽ አድምታ እኔ የገደልኳት ለማስመሰል እስከባሕሩ ድረስ ደሟን እያንጠባጠበች ሄደች ። ልፈታት በማሰቤ ልትበቀለኝ ብላ ነው እንዲህ ያደረገችው። ይሄኔ የምታስሩኝ እየመሰላት አንድ ቦታ ተደብቃ እየሳቀች ነው ። ሜሊና እንደኔው በሕይወት ትገኛለች” በማለት ተናገረ ።

ልዩ የሕግ አስከባሪው ተስፋ በቆረጠ አንጋገር እንዲህ አለ፡—
“ጌታዬ እንደምትለው ቢሆን ደስ ባለን ነበር ። አስከሬኗን ዛሬ ጠዋት ነው
ከባሕሩ ውስጥ ያወጣነው ። በጩቤ ተወግታ ከባሕሩ ሰምጣ ነው ያገኘናት
ሚስተር ዴሚሪስ ። ባለቤትህን በመግደልህ በቁጥጥር ሥር ውለሃል ።”

ምዕራፍ ሃያ አራት

መጀመሪያ ላይ ሜሊና እንዴት አድርጋ እንደምታከናውነው ምንም
አሳብ አልመጣላትም ነበር ። የምታውቀው ነገር ቢኖር ባሏ ወንድሟን
ለማጥፋት ቆርጦ መነሳቱንና ይህ እስኪሆን ደግሞ እጇን አጣጥፋ
እንደማትቀመጥ ብቻ ነበር ። ያም ሆነ ይህ ኮስታ መገታት ነበረበት ።
ለራሷ ሕይወት ጨርሳ አልተጨነቀችም ። ቀኑም ሆነ ሌሊቱ በስቃይና
በተስፋ መቁረጥ የተመላ እየሆነባት መጣ ። ይህንን ጋብቻ እንዳትፈጽም
ስጢሮስ እንዴት አስጠንቅቋት እንደነበር አስታወሰች ። ‘ዴሚሪስን
ልታገቢው አትቺዪም ። ሰውዬው የለየለት አረመኔ ነው ፣ ያጠፋሻል ።’
ወንድሟ እውነቱን ነበር ። ያኔ ምክሩን እንዳትቀበል ፍቅር አሳውሮአ
ታል ፣ አሁን ግን ባሏ መደምሰስ ይኖርበታል ። ግን እንዴት? ‘እንደኮስታ
አስቢ’ የሚል ከአእምሮዋ መነጨ ። አዎ እንደሱ አሰበች ። ምን
እንደምታደርግ ጠዋቱኑ ዝርዝር እቅድ ነድፋለች ። ከዚያ በኋላ ቀላል
ነበር ።

ሜሊና ወደውስጥ ስትገባ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጥናት ክፍሏ
ውስጥ ተቀምጦ ይሠራ ነበር ። በጠንካራ ገመድ የታሠረ ፓኮ ታቅፋለች ።
በእጇም ትልቅ ጩቤ ይዛለች ።

“ኮስታ ይህንን ገመድ ቆርጠህ ፓኮውን ልትከፍትልኝ ትችላለህ፣
እኔ አልቻልኩበትም ።”

ቀና ብሎ አያትና በመሰልቸት ስሜት “ድሮስ ልትችይበት ኖሯል?
ጩቤን ስለቱ ላይ መያዝ አግባብ እንዳልሆነ አታውቂም?” ጩቤውን
ከእጇ መንጭቆ ወሰደና ገመዱን መቁረጥ ጀመረ ።

“የቤት ሠራተኞቹ እንዲቆርጡልሽ ለምን አላደረግሺም?”

ሜሊና አልመለሰችለትም ።

ዴሚሪስ ገመዱን ቆርጦ እንዳበቃ “ይኸውልሽ!” አለና ጩቤውን
አስቀመጠው ። ሜሊናም በጥንቃቄ ስለቱን በመያዝ እንስታ ወሰደችው ።

ወደ እርሱ ተመለከተችና "ኮስታ በዚህ ዓይነት መቀጠል አንችልም ። አውንም ቢሆን እወድሃለሁ ። ስለእኔ ስሜት ሊኖርህ ይገባል ። አብረን ያሳለፍናቸውን አስደሳች ጊዜያት ታስታውሳለህ? ትዝ ይልሃል? በሜጉላ ጊዜያችን ሌሊት ..."

"ስለክርስቶስ ብለሽ" አለና ዴሚሪስ አመናጨቃት ። "አይገባሽም? አከተመ ። በቃሽኝ የኔና ያንቺ ነገር እዚህ ላይ አቆመ ። ውጪልኝ ፣ አስጠልተሽኛል ።"

ሜሊና እዚያው ቆማ አተኩራ አየችው ። በመጨረሻም በእርጋታ "መልካም እንዳልከው ይሁንልህ ።" ወደኋላዋ ዞራ ጩቤውን እንደያዘች ከክፍሉ ወጥታ ሄደች ።

"ፓኮውን ረስተሻል" አለና ዴሚሪስ ጮክ ብሎ ተናገረ ።

እርሷ ሄዳለች ።

ሜሊና ወደባልዋ የልብስ መቀየሪያ ክፍል ገብታ የቁም ሳጥኑን ከፈተችው ። በውስጡ በመቶ የሚቆጠሩ ሙሉ ልብሶች ተሰቅለዋል ። ለጃኬቶችም መስቀያ ልዩ ሥፍራ ተሰጥቷል ። ከአንደኛው ጃኬት ላይ አንድ ቁልፍ በጠሰችና ኪሷ ውስጥ ጨመረችው ።

ቀጥላ መሳቢያውን ከፍታ የባሏ ስም የተለጠፈበትን የዋና ልብስ አወጣች ። 'ቢቃ ዝግጁ ነኝ' አለች በአሳቧ ።

የካቴላኖስ የምርመራ ድርጅት የሚገኘው ከስፎክሊስ ጉዳና ጥግ በአረጀ የሸክላ ቤት ውስጥ ነው ። ሜሊና ፣ መለጥ ብሎ ትንሽ ፂም ወዳለው የድርጅቱ ባለቤት ወደ ሚስተር ካቴላኖስ ቢሮ እንድትገባ ተስተናገደች ።

"እንደምን አደርሽ ሚስስ ዴሚሪስ ፣ ምን ልርዳሽ?"

"ጥበቃ እንዲደረግልኝ እፈልጋለሁ ።"

"ምን ዓይነት ጥበቃ?"

"ከባሌ ።"

ካቴላኖስ ግንባሩን ቋጠረ ። እንድ ችግር እንዳለም ተገነዘበ ። እንዲህ ዓይነቱን ነገር አልጠበቀም ። እንደኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያለውን ሰው ማስቀየም ጅልነት ነው ።

"ፖሊስ ዘንድ ለመሄድ አላሰብሽም ነበር?"

"በፍፁም ነገሩ ይፋ እንዲወጣ አልፈልግም ። በምስጢር እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ ። ልፈታው እንደምፈልግ ስለገለፅኩለት በዚህ አላቤ የምገፋበት ከሆነ እገልሻለሁ ብሎኛል ። ወደአንተ የመጣሁትም በዚህ ምክንያት ነው ።"

"ገባኝ ። ታዲያ አውን እኔ ምን እንዳደርግልሽ ነው የምትፈልጊው?"

"ጥበቃ የሚያደርጉልኝን ሰዎች እንድትመድብልኝ ነው ።"

ካቴላኖስ ቁጭ ብሎ አጠናት ። በሃሣቡ 'በጣም ቆንጆ ሴት ናት ። ንክ ስለመሆኗ ደግሞ አልጠራጠርም' አለ ። ባለቤቷ ይጐዳታል ብሎ ለማመን በጣም ያስቸግራል ። በቤት ውስጥ የተነሳ እነስተኛ ግጭት ይሆናል ይህን ሁሉ ያሳሰባት ። ቢሆንም ከእርሷ ደህና ክፍያ ሊያገኝ ይችላል ። የሚያገኘው ገንዘብ ሊደርስበት ከሚችል አደጋ ጋር ሲመጣጠን ገንዘቡ የሚያጓጓ በመሆኑ ካቴላኖስ የተጠየቀውን ለማድረግ ወሰነ ።

"ጥሩ ነው" አለ ። "ጐበዝ ሰው ስላለኝ ለጥበቃሽ ልመድብው እችላለሁ ። መቼ እንዲጀመር ነው የምትፈልጊው?"

"ሰኞ ዕለት ።"

እውነቱን ነበር ፣ ምንም የሚያስቸኩል ነገር የለም ።

ሜሊና ዴሚሪስ ተነሳች ። "ስልክ እደውልላሃለሁ ። አድራሻህ ያለበት ካርድ አለህ?"

"አዎ ፣ አለኝ ።" ካቴላኖስ ሰሙና አድራሻው የሠፈረበትን ካርድ ሰጣትና እስከውጭ ድረስ ሸኛት ። 'የኒ እኔ ዘንድ መምጣት ለኔ ጥሩ ነው' አለ በአሳቡ ። 'ስሟ ሌሎች ደንበኞቼም የበለጠ እንዲያምኑብኝ ሊያደርግ ይችላል ።'

ሜሊና ወደቤቷ ስትመለስ ለወንድሟ ስልክ ደወለችለት ። "ስፒሮስ ጥሩ ወሬ አለኝ ።" ድምጿ በደስታ የተመላ ይመስላል ። "ኮስታ እርቅ ይፈልጋል ።"

"ምን? እሱን አላምነውም ሜሊና ። አንድ ያሰበው ተንኮል ይኖራል። እርሱ ..."

“እይደለም ፣ የምሩን ነው ። ሁለታችሁ በየጊዜው መፋተጋችሁ ምኝነት መሆኑን ተረድቷል ። በቤተሰቡ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ይፈልጋል ።”

ፀጥታ ሰፈነ ። “እኔ እንጃ ብቻ ።”

“ትንሽ ዕድል ብትሰጠው ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት በአክሮ ኮሪንዝ በሚገኘው የመዝናኛ ክበብህ ሊያገኝህ ይፈልጋል ።”

“ያ ሥፍራኮ በመኪና አራት ሰዓት ያስኬዳል ። እዚሁ ከተማ ውስጥ ለምን አንገናኝም?”

“እንግዲህ እርሱ እንዲህ አላለኝም ” ብላ ሜሊና “ግን እውነት ለሰላም ከሆነ …”

“እሺ አደርጋለሁ ። ግን ይህንን የምፈጽመው ለአንቺ ስል ነው ።”

“ለእኛ ብለህ ነው” አለችው ሜሊና ። “ደህና ሁን ስፒሮስ ።”

“ደህና ሁኚ ።”

ሜሊና ኮንስታንቲን ቢሮ ስልክ ደወለች ። ድምፁ የቁጣ ነበር ። “ምንድን ነው? እኔ ሥራ በዝቶብኛል ።”

“ስፒሮስ አሁን ስልክ ደውሎልኝ ነው ። ከአንተ ጋር እርቅ ለማውረድ ይፈልጋል ።”

አጭር የለበጣ ሳቅ ሳቀ ። “ቢያደርግ ይሻለዋል ። ያለምኩት ሁሉ ከግቡ ሲደርስ ብቻ ነው ሰላሙን ሊያገኝ የሚችለው ።”

“ከእንግዲህ ከአንተ ጋር ለመፎካከር እንደማይፈልግ ገልጾልኛል ኮስታ ። መርከቦቹን ሁሉ ሊሸጥልህ አስቧል ።”

“ለእኔ ሊሸጥልኝ … እርግጠኛ ነሽ?” በነገሩ እየተመሰጠ መምጣቱ ከድምፁ ይታወቃል ።

“አዎ ። እንደበቃው ተናግሯል ።”

“እሺ ። ሒሣቡን ተምኖ እንዲልክልኝ ንገሪው ። እና …”

“አይደለም ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት አክሮ – ኮሪንዝ ውስጥ ከአንተ ጋር ሊገናኝ ይፈልጋል ።”

“በመዝናኛ ክበቡ?”

“አዎ ። ሥፍራው ገለል ያለ ስለሆነ ሁለታችሁ ብቻችሁን ለመሆን አመቺ ነው ። ይህ ምስጢር ለማንም እንዲነገርበት አይፈልግም ።”

‘እንደሱ ይሻለዋል’ አለ ዴሚሪስ ኩራት እየተሰማው በአሳቡ ።

‘ምስጢሩ ቢሰማበት መሳቂያ መሳለቂያ ይሆናል ።’ “እሺ” አለ ዴሚሪስ። “በተባለው ሥፍራ እንደምገኝ ንገሪው ።”

ወደ አክሮ – ኮሪንዝ በመኪና የሚደረገው ጉዞ ረዘም ያለ ጠመዝማዛ ሲሆን በውቡ የገጠር ጐዳና ላይ የሚሽተው የግሬፕሱና የሎሚው መዓዛ ያውዳል ። ስፒሮስ ላምብሩ ከጥንታዊ ፍርስራሽ አጠገብ ሲያልፍ ከሩቁ የአምላክ ኢሲውሲስን መስዋዕት ማቅረቢያ ሥፍራ አየና ዴሚሪስ ትዝ አለው ።

ከመዝናኛ ክበቡ ቀድሞ የደረሰው ላምብሩ ነው ። ከአንድ ጐጆ ቤት ፊት ለፊት መኪናውን አቆመና ተቀምጦ ከዴሚሪስ ጋር ስለሚነጋገርበት ጉዳይ ማሰላሰል ጀመረ ። ኮንስታንቲን እውነት እርቅ እንዲወርድ ፈልጐ ይሆን ወይንስ ይህ ሌላው የማታለያ ዘዴው ነው? ድንገት አንድ አደጋ ቢደርስበት ሜሊና የት እንዳለ ታውቅለታለች ። ስፒሮስ ከመኪናው ውስጥ ወረደና ጭር ወዳለው ክበብ ገባ ። ክበቡ ከእንጨት የተሠራ ማራኪ ጥንታዊ ሕንፃ ነው ። ከፍታ ቦታ ላይ በመሠራቱ እዚያ ሆኖ ጥንታዊዋ የኮሪንዝ ከተማ በደንብ ትታያለች ። ስፒሮስ ልጅ በነበረበት ወቅት ከአባቱ ጋር ቅዳሜና እሁድ ወደዚህ ሥፍራ እየመጣ በአካባቢው ባለው ተራራ አውሬ ያድን ነበር ። አሁን ግን የሚያሳድደውና የሚያድነው ሌላ ነገር ነው ።

ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላም ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደረሰ ። ስፒሮስ ቀድሞት እየጠበቀው መሆኑን ሲመለከት የበለጠ ኩራት ተሰማው ። ‘አሃ ፣ ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ ሰውዬው ሽንፈቱን አምኖ ሊቀበል ነው ።’ ከመኪናው ውስጥ ወረደና ወደጐጆዋ አመራ ። ሁለቱም ሰዎች ቆመው ትኩር ብለው ይተያዩ ነበር ።

“መልካም ፣ ውድ ዋርሳዬ ሆይ” አለ ዴሚሪስ ። “በመጨረሻ ከጐዳናው ፍጻሜ ላይ ደረስን አይደል?”

"ከእንግዲህ እብደታችን እዚህ ላይ እንዲያከትም እፈልጋለሁ ኮስታ ። ከሚገባው በላይ ተጉዘናል ።"

"በሀሣብህ እጅጉኑ እስማማለሁ ። ለመሆኑ ስፒሮስ ስንት መርከብ አለህ?" ላምብሩ በአድናቆት ወደእርሱ ተመለከተ ። "ምን?"

"ስንት መርከቦች ነው ያለህ? ሁሉንም እገዛቸዋለሁ ። በእርግጥ ጥሩ ቅናሽ ታደርግልኛለህ ።"

ላምብሩ "መርከቦቼን ልትገዛ?"

"ሁሉንም ልገዛቸው ፈቃደኛ ነኝ ። ይህም በዓለም ውስጥ የመርከብ ባለቤቶች ቁንጮ እንድሆን ያስችለኛል ።

"አብደሃል መሰለኝ፣ ምን ይሆን መርከቦቼን የምሸጥ መሆኔን እንድታስብ ያደረገህ?"

ምላሹን መስጠት አሁን የዴሚሪስ ተራ ነበረ ። "እዚህም የተገናኘነው ለዚሁ መሰለኝ ፤ አይደለም እንዴ?"

"እዚህ የተገናኘነው አንተ እርቅ በመጠየቅህ ነው ።"

የዴሚሪስ ፊት ጠቆረ ። "እኔ – ማን ነው እንደርሱ ያለህ?"

"ሜሊና"

ለሁለቱም እውነቱ በአንዴ ታያቸው ። "እኔ እርቅ እንደምፈልግ ነገረችህ?"

"እኔ መርከቦቼን ለመሸጥ እንደምፈልግ ነገረችህ?"

"ይህች ደደብ ውሻ" አለ ዴሚሪስ ። "ሁለታችንን በማገናኘቷ ከአንድ ስምምነት ላይ የምንደርስ መሰሏት ነው ላምብሩ ፣ እርሷ ደግሞ ከአንተ የባሰች ጅል ናት ። የከሰዓት በኋላ ጊዜዬን በሙሉ ከአንተ ጋር በከንቱ አባክኩ ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደኋላው ዞረና በኃይል በሩን ከፍቶ ወጣ ። ስፒሮስ ላምብሩ በአሳብ ተመስጦ ዝም ብሎ ያየው ነበር ። 'ሜሊና ልትዋሸን አይገባትም ነበር ። በእኔና ባለቤቷ መካከል እርቅ ሊወርድ የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ማወቅ ነበረባት ። አሁን አይደለም፣ ጊዜው አልፏል ፤ ሁልጊዜም እንዲሁ ነው ።'

ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ላይ ሜሊና በደወል ጥሪ ሠራተኛዋን ጠራቻት ። "አንድሪአ ፣ ሻይ ልታመጪልኝ ትችያለሽ?"

"እሺ እመቤቴ ።" ሠራተኛዋ ወጣችና ከአሥር ደቂቃ በኋላ ሻይዋን በማቅረቢያ ላይ አስቀምጣ ይዛ ስትገባ እመቤቷ በስልክ ትነጋገር ነበር ። አነጋገሯ በንዴት የተመላ ይመስላል ።

"አይሆንም ኮስታ ከውሳኔ ላይ ደርሻለሁ ። አንተን ልፈታህ ወስኛለሁ ። ይህንኑ ነገር የበለጠ ውስብስብና በአደባባይም የታወቀ እንዲሆን አደርገዋለሁ ።"

በሰማችው የቲያናገጠችው ሠራተኛ ማቅረቢያውን አስቀመጠችና ዞራ ለመውጣት እርምጃ ጀመረች ። ሜሊና በእጅ ምልክት እንድትቆይ ነገረቻት ።

ሜሊናን ከሌላኛው የስልክ ጫፍ የሚያነጋግራት ሰው አልነበረም ። ብቻ በስልክ መነጋገሩን ቀጠለች ። "እንደፈለግከው ልታስፈራራኝ ትችላለህ ። አሳቤን ግን አልቀይርም ... በፍጹም ... የፈለግከውን ብትናገር ግድ የለኝም ... ኮስታ አታስፈራራኝ ... አይሆንም ... ጉዳዩ ምንድን ነው? ... እሺ ወደባሕር ዳርቻው ቤት መጥቼ ላገኝህ እችላለሁ ፤ ግን ይህ ምንም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም ። እሺ ፣ ብቻዬን እመጣለሁ ። በአንድ ሰዓት ውስጥ? ጥሩ ነው ።"

ሜሊና ቀስ ብላ ስልኩን ዘጋች ። ፊቷ ላይ ጭንቀት ይነበባል ። ወደ አንድሪያ ዞር አለችና "ከባለቤቴ ጋር ለመገናኘት ወደባሕር ዳርቻው ቤት መሄዴ ነው ። በአሥራ ሁለት ሰዓት ያልተመለስኩ እንደሆነ ለፖሊስ ስልክ እንድትደውዪ እፈልጋለሁ ።"

አንድሪያ በድንጋጤ ምራቋን ዋጠች ። "ሾፌሩ ቢያደርስሽስ?"

"የለም ፣ ሚስተር ዴሚሪስ ብቻሽን ነይ ነው ያለኝ ።"

"እሺ እመቤቴ ።"

አንድ የሚሠራ ተጨማሪ ነገር ነበረ ። የካተሪን አሌክሳንደር ሕይወት አደጋ ላይ ነው ። ለእርሷ ማስጠንቀቂያ ሊደርሳት ይገባል ። ወደቤታቸው መጥተው እራት ከበሉት ልዑካን መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል። 'ሁለተኛ ልታገኟያት አትችዪም ። የሚያጠፋት ሰው ልኬአለሁ ።' ተብሎ የተነገራት ትዝ አላት ። ሜሊና ለንደን ወደሚገኘው የባለቤቷ መሥሪያ ቤት ስልክ ደወለች ።

"ካተሪን አሌክሳንደር የምትባል አለች?"

"አሁን ለጊዜው ቢሮ ውስጥ የለችም ። ሌላ ሰው ላቅርብልዎ?"

ሜሊና አመነታች ። ለማስተላለፍ የፈለገችው መልእክት በጣም

አስቸኳይ ቢሆንም ለሌላ ሰው ለመንገር ደግሞ ማንንም አላመነችም ። መልሳ ለመደወል ደግሞ ጊዜ የላትም ። ኮስታ በቢሮው ውስጥ ስለሚገኘው ዊም ቫንዲን ስለተሰኘው ጉበዝ ሠራተኛ ሲያወራ ሰምታ ለች ።

“እባክም ሚስተር ቫንዲንን ለማነጋገር እችላለሁ?”

“አንድ ጊዜ ይጠብቁ”

የአንድ ሰው ድምፅ ከስልኩ ውስጥ ተሰማ ። “ሄሎ”

ማንነቱ በእንዴ ገብቷታል ።

“ለካተሪን አሌክሳንደር መልእክት ነበረኝ ። በጣም ከፍተኛ ጉዳይ ነው ። እባክህ መልእክቱን ልታስተላልፍልኝ ትችላለህ?”

“ካተሪን አሌክሳንደር?”

“እዎ ። ንገራት ። ሕይወቷ በአደጋ ላይ መሆኑን ንገራት ። ሰው ሊገድላት ነው ። ከአቴንስ ወደዚያ ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ ይመስለኛል ።”

“አቴንስ ...”

“አዎ”

“የአቴንስ ሕዝብ ብዛት ስምንት መቶ ሰድስት ሺህ ...”

ሜሊና ሰውዬው እንዲገባው ልታደርግ አልቻለችም ። ስልኩን መልሳ ዘጋችው ። የአቅሟን ሁሉ ሞክራለች ።

ዊም ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ስላደረገው የስልክ ውይይት ማሰላሰል ቀጠለ ። ‘አንድ ሰው ካተሪንን ሊገድላት ይፈልጋል ። በዚህ ዓመት ውስጥ በእንግሊዝ ውስጥ አንድ መቶ አሥራ አራት ግድያዎች ተፈጽመዋል ። ካተሪን የዚህን ቁጥር ወደ አንድ መቶ አሥራ አምስት ከፍ ታደርገዋለች ። ከአቴንስ ከመጡት ሰዎች መካከል አንደኛው ጂሪ ሃሌይ ፣ ዱቪ ሬናድ ፣ ዴኖ ማቱሲ ፣ ከእነኚህ አንደኛው ካተሪንን ሊገድል ነው ።’ የዊም ኮምፒዩተራዊ ጭንቅላት ስለሦስቱም ሰዎች ያለውን መረጃ አስታውሶ አሳውቆታል ። ‘የትኛው እንደሆነ አውቄዋለሁ ።’

ካተሪን ተመልሳ ስትመጣ ዊም ስለስልክ ጥሪው ምንም አልነገራ ትም ።

ግምቱ ትክክል መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ ወንጀሉ ተፈጽሞ

ለማየት ጓጉቷል ። ካተሪን ከልውካኑ አባላት ጋር ማታ ማታ በየተራ ትወጣለች ። በነጋታው ሥራ ስትገባ ምን እንደደረሰባት ለማየት ዊም ቀድሞ ይጠብቃታል ። ምንም አለመሆኗ ተስፋ አስቆርጦታል ።

‘መቼ ይሆን የታሰበውን የሚፈጽሙባት’ አለ በአሳቡ እየተገረመ ። የስልኩን መልዕክት ለእርሷ መንገር ነበረበት ። ያ ደግሞ ማታለል ነው ። የአጋጣሚን ልዩ ልዩ ድንገታዊ ክስተቶች እንዳይፈፀሙ ማገድ ተገቢ አይደለም ።

ምዕራፍ ሃያ አምስት

ወደ ባሕር ዳርቻ ቤቱ በመኪና ያደረገው የአንድ ሰዓት ጉዞ ያለፉትን ሃያ ዓመታት ትዝታዎች በሙሉ ከፊቱ ድቅን አድርጐበታል ። ሜሊናም የምታስታውሳቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ ፤ ብዙ ብዙ ትዝ የሚሉ ጊዜዎች ። መልከ መልካሙ ወጣት ኮስታ አንዴ ‘ውበት ምን እንደሆነ ለኛ ለአላፊና ጠፊ ፍጡሮች ለማስተማር ከመንግሥተ ሰማያት የተላክሽ ነሽ ። ይህ ድለላ አይደለም ። ስላንቺ የምናገረው ማንኛውም ነገር አንቺን በትክክል ሊገልጽሽ እንደማይችል…’ ያላት ፤ በግል የመንሸርሸሪያ መርከባቸው ያደርጉት የነበረው ሽርሽር ፤ በፕሳራ ያሳለፍቸው ጊዜያት … አስደሳች ስጦታዎች ይቀርቡባቸው የነበሩበት ቀናት ፤ በአልጋ ላይ ተቃቅፈው በፍቅር የተቃጠለ ወሲብ የፈጸሙባቸው ሌሊቶች ። ከዚያም ያስወረዳትና እንደአሸን የፈሉት የኮስታ ዕቁባቶች ፤ በተለይም ከኖኤል ፓጂ ጋር የነበረው ወዳጅነት ፤ የደበደባትና ያደረሰባት ውርደት። “ኮሪትሲሞን! እንጃ የምትኖሪበት ምክንያት የለም ። ለምን ሕይወትሽን አታጠፊም?” ያላት ። በመጨረሻም ስፒሮስን ለመግደል የተሰነዘረው ዛቻ ።

በተለይ ፍጻሜው ላይ ይህንን ነበር ሜሊና ልትቋቋመው ያልቻለችው።

ሜሊና ከባሕር ዳርቻው ቤት ስትደርስ ጭር ብሏል ። ሰማዩ ደመናን አዝሏል ። በጣም ቀዝቃዛ የሆነ ነፋስም ከወደ ባሕሩ ይነፍሳል ። ‘መጥፎ ገድ’ አለች በአሳቢ ።

ምቹ ወደሆነው አዝናኝ ቤት ገባ አለችና ለመጨረሻ ጊዜ ዙሪያውን ቃኘች ። ከዚያም ወንበሮቹን በሙሉ ገለባበጠች ፤ አምፖሎቹን ሰባበረች። የለበሰችውን ልብስ ቀዳድዳ ከወለሉ ላይ ጣለች ። ከመርማሪ ድርጅቱ የተሰጣትን አድራሻ ያለበትን ካርድ አውጥታ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠች ። ምንጣፉን ገለጠችና የወርቅ አዝራሩን ከሥር አኖረች ። ኮስታ ሰጥቷት የነበረውን የወርቅ ሰዓት ከእጇ ላይ አውጥታ ከሰከሰችው ።

ከመኖሪያ ቤቷ ያመጣችውን የባለቤቷን የዋና ልብስ ይዛው ወደባሕሩ ዳርቻ ተጓዘች ። ውሀ ውስጥ ነክራ መልሳ ወደቤቱ አመጣች ። በመጨረሻም ለማከናወን የቀራት አንድ ነገር ነበር ። ‘ጊዜው አሁን ነው’ አለች በአሳቢ ። በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰችና እጇታው በሽንት ቤት ወረቀት የተጠቀለለውን ጩቤ አውጥታ በትኩረት አየችው። ወሳኙ ይህኛው ነው ። ሰው የገደላት ለማስመሰል እራሷን በኃይል መውጋት ይኖርባታል ። ከዚህም በተጨማሪ ቀሪውን እቅዷን ከግቡ ለማድረስም ቀሪ ጉልበት ሊኖራት ይገባል ።

ዓይኗን ጨፈነችና ጩቤውን ሰውነቷ ውስጥ በኃይል ሰካች ። ሕመሙ እየተሰማት መጣ ። ደም እንደጉርፍ ፈሰሰ ። ሜሊና የሚደማውን ሰውነቷን እርጥብ በሆነ የዋና ሙታንታ ያዘችና ሙታንታው በደሙ ሲጨማለቅ ከቁምሳጥኑ በስተጀርባ ደበቀችው ። አሁን ያዞራት ጀመር ። ካሰበችው ነገር የተረሳ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ዙሪያውን በዓይኗ ቃኘችና እየተንገዳገደች ወደመውጫ በሩ አመራች ። ደሟን በምንጣፉ ላይ እያንጠባጠበች መጣች ።

ወደውቅያኖሱ ተጓዘች ። ደሟ በጣም ይፈላል ። በአሳብዋ ‘ካቀድኩት ግብ የምደርስ አይመስለኝም ። ኮስታ ሳያሸንፈኝ አይቀርም ። ግን መሆን የለበትም’ አለች ።

ወደውቅያኖስ ያደረገችው ጉዞ በቀላሉ የሚዘለቅ አልነበረም ። ‘አንድ ሌላ ርምጃ’ አለች በአሳቢ ። ‘አንድ ተጨማሪ ርምጃ ።’ ምድር ሰማዩ እየዞረባት ጉልበት ብታጣም እንደምንም ርምጃዋን ቀጠለች ። ዓይኗም ብዥ ስላለባት ወድቃ ተምበረከከች ። ‘እዚህ ላይ መቆም የለብኝም ።’ ተነስታ ጉዞ ቀጠለችና የውሀው ቅዝቃዜ እግሯን ተሰማት ።

ጨውማ ውሃ ቁስሏን ሲነካው ልትቋቋም የማትችለው ከፍተኛ ሕመም ተሰማትና በኃይል ጮኸች ። ‘ይህንን የማደርገው ለስፒሮስ ብዬ ነው’ አለች በአሳቢ ። ‘ውድ ስፒሮስ ።’

በርቀት ደመናው እየከበደ ወደ አድማስ ሲጓዝ ይታያል ። ደሟን እያዘራች ወደሱው መዋኘት ጀመረች ። ተአምር ታየ ። ደመናው ወርዶ ወደእርሷ መጣ ። ለስላሳው ደመና ሰውነቷን ሲነካ ፣ ገላዋን ሲያጥበውና ሲያንሳፍፋት ተሰማት ። አሁን ሕመሙ ጠፍቷል ። በጣም አስደሳች የሆነ ሰላማዊ ስሜት በውስጧ ሰፍኗል ።

‘ወደ ቤቴ መሄዴ ነው’ ስትል ሜሊና በደስታ አሰበች ። ‘በመጨረሻ ወደመኖሪያ ቤቴ መሄዴ ነው ።’

ምዕራፍ ሃያ ስድስት

“ሚስትህን በመግደልህ በቁጥጥር ሥር አውዬሃለሁ ።”

ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር በዝግታ እንቅስቃሴ የሚከናወን ይመስ ላል። የጣት አሻራው እንዲወሰድ ተደረገ ። ፎቶግራፍ ተነሳና ወደወህኒ ተላከ ። እንዲህ ዓይነት ነገር ይፈጸምበታል ብሎ ለማመን በጣም ያስቸግራል ።

“ፒተር ዲሞኒደስን አሁኑኑ ፈልግልኝ ። አሁኑኑ ላነጋግረው እንደምፈልግ ንገርልኝ ።”

“ሚስተር ዲሞኒደስ ከሥራው ታግዷል እየተመረመረ ነው ።”

“ስለዚህ የማነጋግረው ማንም ሰው የለም ማለት ነው ?” ‘ከዚህ ሥፍራ እወጣለሁ’ አለ በአሳቡ ። ‘እኔኮ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነኝ ።’

ልዩ ሕግ አስከባሪው እንዲመጣለት ጥያቄ አቀረበ ።

ዴልማ ከአንድ ሰዓት በኋላ ወደ እሥር ቤቱ መጣ ። “ልታነጋግረኝ ጥያቄ አቅርበሀ ነበር?”

“እዎ” አለ ዴሚሪስ ። “እንደገባኝ ባለቤትህ ተገደለች ብላችሁ የመዘገባችሁት ጊዜ ዘጠኝ ሰዓት ነው ።”

“ትክክል ነው ።”

“ኋላ እራስህም ሆነ ፖሊሶች እንዳታፍሩ ፣ በተባለው ሰዓት ከባሕር ዳርቻ ቤቴ አካባቢ አለመኖሬን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለኝ ።”

“ማረጋገጫውን ለማቅረብ ትችላለህ?”

“እንዴታ ምስክር አለኝ ።”

ከፖሊስ ኮሚሽነሩ ቢሮ ተቀምጠው እንዳለ ስፒሮስ ላምብሩ ደረሰ ። ዴሚሪስ ገና እንዳየው ፊቱ ፈካ ።

“ስፒሮስ ፣ እግዚአብሔር ነው ደህና ጊዜ አንተን ወዲህ ያመጣልኝ። እነኚህ ደደቦች ሜሊናን የገደልኩ መስሏቸዋል ። እንዳልገደልኳት ስለምታውቅ እባክህ ንገራቸው ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ግንባሩን ቋጠረ ። “ምን ልንገራቸው?”

“ሜሊና የተገደለችው ትናንት ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ነው ። በዘጠኝ ሰዓት ደግሞ እኔና አንተ በአክሮ ኮሪንዝ የመዝናኛ ክበብህ አብረን ነበርን ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት በፊት ከባሕር ዳርቻ ለመድረስ እንደማል ችል ደግሞ ታውቃለህ ። አብረን እንደነበርን ግለጽላቸው ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ትኩር ብሎ ተመለከተው ። “አብረን እንደነበ ርን?”

የዴሚሪስ ፊት ፍም መሰለ ። “እ … እኔና አንተ ትናንት አክሮ ኮሪንዝ በሚገኘው የመዝናኛ ክበብ ውስጥ አብረን እንደነበርን?”

“ዞሮብሃል መሰለኝ፣ ኮስታ ፣ ትናንት ከሰዓት በኋላ ብቻዬን በመኪና ከከተማ ወጥቼ ነበረ ። ውሸት ልናገርልህ አልችልም ።”

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፊት በንዴት ተወጣጠረ ። “እንዴት እንዲህ ትላለህ?” አለና የላምብሩን የኮት ኮሌታ ጭተተ ። “እውነቱን ንገራቸው!”

ስፒሮስ ላምብሩ እጁን አስለቀቀው ። “እውነቱ እህቴ መሞቷና የገደልካትም አንተ መሆንህ ነው ።”

“ውሸታም!” ሲል ዴሚሪስ ጮኸ ። “ውሸታም!” ዘሎ ላምብሩን ለማነቅ ሲንደረደር ሁለት ፖሊሶች ጣልቃ ገቡ ።

“አንተ የውሻ ልጅ ። ንፁህ ሰው መሆኔን ታውቃለህ ።”

“ንፁህነትህን የሚያረጋግጥልህ እኔ ሳልሆን ዳኛው ነው ። ጥሩ ጠበቃ የሚያስፈልግህ ይመስለኛል ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከዚህ ሁሉ ጉድ ሊያተርፈው የሚችል አንድ ሰው ብቻ እንደነበር ተገነዘበ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ።

ምዕራፍ ሃያ ሰባት

ምስጢራዊ ማኅደር

ከካተሪን ዶግላስ ጋር የተካሄደው ውይይት ዶሴ

ካ = አንድ ሰው ክፉ እንደሚያደርስበት ሰውነቱ እንደሚነግረው ታምናለህ አላን?

አ = በሳይንሳዊ አመለካከት ተቀባይነት የለውም ። እውነት ለመናገር ግን እኔም አምንበታለሁ ። ክፉ ይደርስብኛል ብለሽ ሰግተሽ ታውቂያለሽ?

ካ = አዎ ። አንድ አደጋ ያጋጥመኛል የሚል ፍርሃት አድሮብኛል ።

አ = ድሮ በሕልምሽ ያየሽው ዓይነት

ካ = አይደለም ። እንደነገርኩህ ሚስተር ዴሚሪስ ከአቴንስ ሰዎችን ወዲህ ልኳል ።

አ = አዎ ።

ካ = ሰዎቹን እንድንከባከባቸው ባዘዘኝ መሠረት ከጥቂቶቹ ጋር ቅርበት ነበረኝ ።

አ = ያስፈራራሽ አለ?

ካ = የለም ። እንደዚያ አይደለም ። ለማስረዳት ያስቸግራል ። ምንም ያደረገኝ የለም ። ግን አንድ አሰቃቂ ድርጊት ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት አለኝ ። ይህ አባባሌ ትርጉም ይሰጥሃል?

አ = ስለ ሰዎቹ ንገሪኝ ።

ካ = ፈረንሣዊው ዱቬ ሬናድ ይባላል ። ወደ ሙዚዬም እንሂድ ብሎ ፈትሮ ይይዘኛል ። እተባለው ሥፍራ ስንደርስ ደግሞ ሙዚዬሞቹን ለመጎብኘት ምንም ደንታ የሌለው ሆኖ አገኘዋለሁ ። ለምሳሌ ባለፈው ቅዳሜ ወደስቴን ሄንግ አብሬው እንድሄድ ጠይቆኝ ነበር። ከልዑካኑ አባላት ሌላው ጂሪ ሃሌይ የሚባለው አሜሪካዊ ነው ። ሰውዬው ደስ የሚል ቢሆንም ግራ የሚያጋቡ ነገሮች አይበታለሁ።

ሦስተኛውም ሰው ዲኖ ማቱሲ ይባላል ። በሚስተር ዴሚሪስ ኩባንያ ውስጥ ከፍተኛ የኃላፊነት ሥፍራ ያለው ቢሆንም እራሱ የሚያውቀውን እንዳብራራለት ይጠይቀኛል ። አብሬው በመኪና ከከተማ ውጭ እንድሄድ ጋብዞኝ ነበር ። እኔም ዊም አብሮን እንዲመጣ አስቤ ... እና ያ ለሌላ ምክንያት ሊሆን ይችላል ።

አ = እንዴት?

ካ = ዊም የተለየ ፀባይ ማሳየት ጀመረ ።

አ = እንዴት ዓይነት?

ካ = ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ወደቢሮ ስመጣ ቀድሞ ይጠብቀኛል ። ከዚህ ቀደም እንደዚያ አድርጐ አያውቅም ። እና በሚያየኝም ወቅት በቢሮው ውስጥ መገኘቴ እንደሚያናድደው ከፊቱ ላይ አነባለሁ ። ይህ ሁሉ ግራ አጋብቶኛል ። አንተስ ምን ይመስልሃል?

አ = አንዴ መክፈቻ ቁልፉን ከጨበጥሽ ምስጢሩ ይገለፅልሻል ። ሌላ ተጨማሪ ሕልሞች አይተሽ ታውቂያለሽ?

ካ = ስለኮንስታንቲን ዴሚሪስ አልሜ ነበር ፣ ግን ፍቺው ግልጽ አልሆነልኝም ።

አ = ካየሽው ውስጥ የምታስታውሺውን ንገሪኝ ።

ካ = ለምን ይህን ያህል ደግ እንደሆነልኝ ፣ ስለምንስ በለንደን ሥራና መኖሪያ እንደለገሰኝ ፣ የወርቅ የደረት ጌጡን ለምን እንደሸለመኝ እንዲያስረዳኝ ጠይቄው ነበር ።

አ = ታዲያ እርሱስ ምን አለሽ?

ካ = አላስታውሰውም ፣ የማስታውሰው ከእንቅልፌ እየጮህኩ መነሳቴን ነው ።

ዶክተር አላን ሃሚልተን ማኅደሩን በጥንቃቄ ማጥናት ቀጠለ ። በውስጠ ኅሊናዋ ተደብቆ የቀረና ካተሪንን የሚረብሻት ነገር ካለ ለይቶ ለማወቅ ጥረት አደረገ ። ስጋቷ የመነጨው እንግዶች ከአቴንስ በመምጣታቸውና ያለፈው አሰቃቂ ሕይወቷ ከአቴንስ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ እንደሆነ እርግጠኛ ነበር ። የዊምም ሁኔታ አላንን አስገርሞታል ። ሊሆን ይችላል ብላ ካተሪን በመገመቷ ነው፣ ወይንስ ዊም እንግዳ ባሕሪይ

ማሳየት ጀምሯል? ‘ዊምን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ማግኘት አለብኝ’ አለ አላን በአሳቡ ። ‘ምናልባት ቀጠሮውንም ወደዚህ ማቅረብ እችል ይሆናል ።’

አላን ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ስለካተሪን ማሰብ ቀጠለ ። ከታካሚዎቹ ጋር ልዩ ግንኙነት አለመፍጠርን መመሪያው ቢያደርግም ካተሪን ግን የተለየች ሴት ሆናበታለች ። በጣም ቆንጆና የምታጓጓ ... “ምን ማድረጌ ነው? እንዲህ ማሰብ የለብኝም ። በሌላ ነገር ላይ ባተኩር ይሻለኛል ።” ግን አእምሮው ተመልሶ ስለእርሷ ያስባል ።

ካተሪን ስለአላን ሃሚልተን ማሰቧን ከአእምሮዋ ለማስወገድ አልቻለችም ። ‘ባልጃጃል ይሻላል ። ትዳር ያለው ሰው ነው ። ታካሚዎች ሁሉ ስለሀኪማቸው ተመሳሳይ ስሜት ይኖራቸው ይሆን?’ ስትል ለእራሷ የምታወራው ጥቅም የሚሰጣት አልሆነም ። ‘ምናልባት ስለሐኪሜ ሌላ ሐኪም ማማከር ሳያስፈልገኝ አይቀርም ።’

ከሁለት ቀናተ በኋላ ተመልሳ አላንን ማነጋገር ነበረባት ። ‘ብዙ ጣጣ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ቀጠሮውን ብሰርዝ ይሻለኛል ። ግን ልቤ ብዙ ጉዳና ተራምዷል ።’ አለች ካተሪን በአሳቧ ።

ከአላን ጋር ቀጠሮ በነበራት ቀን ጠዋት ካተሪን ሽክ ብላ ወደቁንጅና ሳሎን አመራች ። ‘ከዛሬ በኋላ ዳግመኛ ስለማላየው ለአሁኑ ሽክ ብል ምንም ክፋት የለውም ።’ አለች ካተሪን ለራሷ ።

ወደቢሮው ገና እንደገባች ውሳኔዋ እንደጨው ሟሟ ። ‘ለምንድን ነው እንዲህ በጣም የሚሰበኝ? ምነው ከማግባቱ በፊት ተገናኝተን በነበረ? አእምሮዬ ደህና ሳለ ብንተዋወቅ ምንኛ ደስ ይለኝ ነበር? ለካ አእምሮዬ ጤነኛ ቢሆን ወደ እርሱ ዘንድ አልመጣም ነበር?’

“ያልሺውን በደንብ አልሰማሁትም” አላት ።

ካተሪን ድምጿን ከፍ አድርጋ መናገሯንም የተረዳችው ይኼኔ ነበር። ይህ የመጨረሻ ጉብኝቷ መሆኑን አፍርጣ ለመንገር ጊዜው አሁን

ነው ።

በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። “አላን ...” እንደገና ውሳኔዋ ተቀየረ ። በጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ፎቶግራፍ ተመለከተች ። “ካገባህ ስንት ጊዜ ይሆንሃል?”

“ካገባህ አልሺኝ?” አለና የካተሪንን ዓይን ተከተለ ። “ይህኮ የእህቴና ልጇ ፎቶግራፍ ነው ።”

ካተሪን ከፍተኛ ደስታ በመላ ሰውነቷ ሲሰራጭ ተሰማት ። “በጣም ጥሩ ነው ። ማለቴ እርሷ ... እርሷ በጣም ደስ የምትል ናት ።”

“ካተሪን ፣ አመመሽ እንዴ?”

ኪርክ ሪኖልድስም እንዲህ ብሎ ይጠይቃት ነበር ። አሰበች ። ‘ያኔማ ሲጠይቀኝ ያመኝ ነበር ፣ አሁን ግን ደህና ነኝ ።’ አላን ላቀረበላት ጥያቄ “ደህና ነኝ” ስትል መለሰችና “አላገባህም ?” ብላ ጠየቀችው ።

“የለም ፣ አላገባሁም ።”

‘አብረሽኝ እራት ልትበላ ትችላለህ? የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ቢኖረንስ? ታገባኛለህ? ብላ ከእነኚህ ሦስቱ ጥያቄዎች አንዱን እንኳ በይፋ ብትናገር የለየላት እብድ ነች እንደሚላት እርግጠኛ ነበረች ። ‘ምናልባትም እብድ ሳልሆን አልቀርም ።’

ግንባሩን ቋጥሮ ዝም ብሎ ተመለከታት ። “ካተሪን ከእንግዲህ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውይይታችንን ለመቀጠል የምንችል አይመስለኝም ። የዛሬው የመጨረሻችን ይሆናል ”

የካተሪን ልብ ሊቆም ደረሰ ። “ምነው ያስቀየምኩህ ነገር ...?”

“አይደለም ። አስቀ...አስቀይመሽኝ አይደለም ። በዚህ ዓይነቱ የሙያ ግንኙነት ሳቢያ በተፈጠረው መተዋወቅ አስታኮ ከታካሚ ጋር ልዩ ግንኙነት መፍጠር ለአንድ ሐኪም የተከለከለ ነው ።”

ዓይኗ እፍጥጦ አትኩራ አየችው ።

“ስላንቺ ፍላጎት አድሮብኛል ነው የምትለኝ?”

“እም ስጋቴ ...”

“ሙሉ በሙሉ ትክክል ነህ” አለች ካተሪን በደስታ ። “ስለዚህ ጉዳይ ዛሬ ግታ በእራት ላይ በዝርዝር እንወያይ ።”

በሶሆ እምብርት ላይ በምትገኝ አንዲት አነስተኛ የኢጣሊያን ሆቴል ውስጥ እራታቸውን በሉ ። ምግቡ መጥፎ ይሁን ጣፋጭ ለሁለቱ ምኑም አልታወቃቸውም ። አንዱ ስለሌላው በተመስጦ ሲያሰላስል ነበር ያመሹት ።

“አላን ፣ ልክ አይደለህም ። መቼም ስለእኔ ሁሉንም ነገር ታውቃለህ። ስለእራስህ ደግሞ ንገረኝ ። ከዚህ ቀደም አግብተህ እታውቅም ?” ስትል ካተሪን ጠየቀችው ።

“አላገባሁም ግን አጭቼ ነበር።”

“ታዲያ ምን ሆነ ?”

“በጦርነቱ ወቅት አንዲት አነስተኛ አፓርታማ ውስጥ አብረን እንኖር ነበር ። በቦንብ ድብደባው ሰሞን እያከምኩ ሆስፒታል አምሽቼ ወደቤቴ ስመጣ ...”

ሁኔታው ምን ያህል እየዘገነነው እንደሆን ካተሪን ከድምጹ ተረዳች።

“...ሕንጻው ወድሟል ። የቀረ ምንም ነገር አልነበረም ።”

እጇን ከእጁ ላይ አኖረች ። “በጣም አዝናለሁ ።”

“ይህንን ለመርሳት ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል ፣ ከዚያ በኋላ ለጋብቻ የምመኛት ሴት አላጋጠመችኝም ። ከዓይኖቼም ውስጥ ‘አሁንም ቢሆን’ የሚሉ ቃላት ይነበባሉ ።

የባሑን የቆሑን እያነሱ ሲያወጉ በሆቴሉ ውስጥ ለአራት ሰዓታት ያህል ተቀመጡ ። ስለትያትር ፣ ስለሕክምና ፣ ስለዓለም ሁኔታ ሲያወጉ ፣ ዋናውን ነጥብ እስካሁን አላነሱም ። በመካከላቸው አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል የተፈጠረ ይመስላል ። ሁለቱንም ይህ ስሜት ተሰምቷቸዋል ። በጉጉትና በምኞት የተወጠረ የወሲብ ፍላጎትም ክፉኛ ተቀስቅሰባቸዋል።

በመጨረሻ አላን ጉዳዩን አፍረጠረጠው ። “ካተሪን ዛሬ ጠዋት ስለሕኪምና ታካሚ ግንኙነት የተናገርኩት ነገር...”

“ስለዚሁ ሁኔታ በመኖሪያ ቤትህ ውስጥ አጫውተኝ ።”

በፍጥነትና በጉጉት ሁለቱም ልብሶቻቸውን አወላለቁ ። ካተሪን በምታወልቅበት ወቅት ከኪርክ ሪኖልድስ ጋር የነበራትን ስሜት አስታወሰች ። የአሁኑ ከዚያን ጊዜው የተለየ ነው ። ‘ልዩነቱ ብፍቅር በመያዜ ነው’ ስትል ካተሪን አሰበች ። ‘ከዚህኛው ሰውዬ ፍቅር ይዞኛል።’

አልጋው ላይ ተንጋላ ስትጠብቀው መጥቶ እቅፍ ካደረጋት በኋላ ከእንግዲህ ወደወንድ ልጠጋ አልችልም የሚለው ስጋትና ፍርሃቷ ተነነ ። አንዱ የሌላውን ገላ መጀመሪያ በቀስታ ከዚያም በኃይል እየዳሰሰና እየጨበጠ ከሰውነት ወጥተው የአውሬ ዓይነት ባሕሪይ ወደማሳየት ደረሱ ። አንዱ በሌላው ውስጥ ሰመጠ ። ከፍተኛ ደስታና እርካታ የተሰማትም ካተሪን ድምጿን ከፍ አድርጋ ጮኸች ። ‘እንደገና ሙሉ ሰው ሆኛለሁ ።’ አለች በአሳቧ ። ‘አመሰግናለሁ ።’

አልጋው ላይ ተኝተው ለረኽም ጊዜ ቆዩ ። ዳግመኛ እንዳይለያት ካተሪን ጥብቅ አድርጋ አቀፈችው ።

ለመናገር ትንፋሿ እንደተመለሰ በሚንቀጠቀጥ ድምጿ “በሽተኛን ማከሙን በደንብ ታውቅበታለህ ዶክተር” አለችው ።

ምዕራፍ ሃያ ስምንት

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሚስቱን በመግደሉ የተነሳ መታሰሩን ካተሪን በጋዜጣ ላይ እንዳነበበች በጣም ተደናግጣ ነበር ። ከቢሮዋ ስትደርስ ሁሉም ሰው ተክዞ አገኘች ።

“ዜናውን ሰማሽ ?” ስትል ኤቬሊን ጠየቀቻት ።” አሁን ምን እናድርግ ?”

“ከዚህ ቀደም በሰጠን መመሪያ መሠረት ሥራው እንዲካሄድ ማድረግ ። እርግጠኛ ነኝ በስሕተት ነው ያሰሩት ። አሁን በስልክ ላገኘው እሞክራለሁ ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ለማግኘት ግን ከቶ አልተቻለም ።

የአቴንስ ማዕከላዊ እሥር ቤት እስካሁን በቁጥጥር ሥር ካዋላቸው እሥረኞች መካከል በጣም ታዋቂው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ለዴሚሪስ ከሌሎች የተለየ እንክብካቤ እንዳይደረግለት የሚያዝ መመሪያ ከሕግ አስከባሪው ተሰጥቷል ። ዴሚሪስ የቴሌፎን ፣ የቴሌክስና ሌሎች መልእክት መለዋወጫ አገልግሎቶች ለማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብም ተቀባይነትን አላገኘም ።

ዴሚሪስ ቀንም ሆነ ሌሊት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ሜሊናን ማን ገድሏት ይሆን እያለ ሲያሰላስል ነው ።

በመጀመሪያ ላይ ፣ ሌባ የባሕር ዳርቻ ቤቱን ለመመዝበር መጥቶ ሜሊና በድንገት ስለደረሰችበት ገድሏት ይሆናል ብሎ ሲያስብ ነበር ። ፖሊሶች መረጃውን አሰባስበውበት ካቆጠጡት በኋላ ግን ሆን ተብሎ እሱን በወንጀለኛነት ለማጥመድ የተጠነሰሰበት ሤራ መሰለው ። ግን ማን እንዲህ ሊያደርግ ይችላል ? ሊያደርግ የሚችለው ስፒሮስ ላምብሩ ፣ እህቱን ከማንም በላይ ስለሚወዳት ዴሚሪስን ለመወንጀል ብሎ አይገድላትም ከሚል መደምደሚያ ደረሰ ።

የዴሚሪስ ሌላው ጥርጣሬ ከቶኒ ሪዞሊ ጋር ተሰልፈው ባሉት ወሮበሎች ላይ ነው ። ምናልባት በሪዞሊ ላይ የፈፀመውን ነገር ተረድተው በዚህ ዓይነት መንገድ የበቀል እርምጃ መውሰዳቸው ይሆናል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ይህንንም ግምት አልተቀበለውም ። ግፊያዎቹ የበቀል ርምጃ ቢመስሱ ኖሮ ፍላጻቸው የሚያተኩረው በቀጥታ በኮንስታንቲን ዴሚሪስ ላይ ነው ።

እና በጠባብ የእሥር ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ አእምሮውን እያንከራተተ ለእንቆቅልሹ መፍቻ ለማግኘት ይጥር ነበር ። ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ጥርጣሬዎች ሁሉ መቋጫ የሌላቸው መሆኑን ሲረዳ መጨረሻ ላይ አንድ አማራጭ ብቻ መኖሩን ተገነዘበ ። የሜሊና ሕይወት ያለፈው በእራሷ እጅ ነው ። ራሷን ገድላ እሱ እንደገዳይ እንዲወነጀል ብላ ነው ። ዴሚሪስ ፣ በኖኤሌ ፓጂና በላሪ ዶግላስ ላይ የፈጸማቸውን ተግባሮች አስታወሰ ። የሚያስገርመው ግን በእነርሱ ላይ የደረሰው በእርሱም ላይ መፈጸሙ ነው ። እንደነሱ ባልፈጸመው የግድያ ወንጀል ክስ ተመስርቶበታል ።

የእሥር ቤቱ ጠባቂ ከዴሚሪስ ክፍል በር ላይ ቆሟል ። “ጠበቃህ ሊያነጋግርህ መጥቷል ።”

ዴሚሪስ ተነስቶ ዘበኛውን ተከትለና ወደአንዲት አዳራሽ አመራ ። ቫሲሉኪ የተባለው የሕግ ባለሙያ ይጠብቀው ነበር ። ዕድሜው በሃምሳው አካባቢ ሲሆን የፊልም ኮከብ ተዋናይ አቋም ያለው ሽበቶ ነው። በግድያ ወንጀል ጥብቅና ጥሩ ውጤት ማስገኘቱ ቢነገርለትም ፣ አሁን ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ ይችል ይሆን ?

የእሥር ቤቱ ዘበኛ “አሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው ያላችሁ” አለና ሁለቱንም በአዳራሹ ውስጥ ትቶ ወጣ ።

“መልካም” ሲል ዴሚሪስ ንግግሩን ጀመረ ። “ከዚህ ሥፍራ መቼ ነው የምታስወጣኝ ? የማታስወጣኝ ከሆነ ለምንስ እከፍልሃለሁ ?”

“ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ጉዳዩ ያንን ያህል ቀላል አይመስለኝም ዋናው ሕግ አስከባሪ እምቢ ስላለ ...”

“ዋናው ሕግ አስከባሪ ጅል ነው ። እዚህ ሥፍራ ሊያቆዩኝ አይችሉም ። ገንዘብ በዋስትና ማስያዝስ እንዴት ይመስልሃል ? የጠየቁ ኝን ያህል ገንዘብ ማስያዝ እችላለሁ ።”

ቫሲሉኪ በንዴት ከንፈሮቹን በምላሱ አረጠበ ። “የገንዘብ ዋስትና

ተቀባይነት አላገኝም ። ሚስተር ዴሚሪስ ፖሊሶች በአንተ ላይ ያቀረቡአ ቸውን ማስረጃዎች መርምሬአለሁ ። ማስረጃዎቹ በጣም ሊጐዱን የሚችሉ ናቸው ።”

“ጐዱንም አልጐዱንም –እኔ ሚሊናን አልገደልኩም ። ከደሟ ንጹህ ነኝ ።”

ጠበቃው ምራቁን ዋጠ ። “አዎ ፣ ትክክል ነህ ፣ ትክክል ። ባለቤትህን ማን ገደላት ብለህ ታስባለህ ?”

“ማንም ። ባለቤቴ ራሷን በራሷ ነው የገደለችው ።”

ጠበቃው ትኩር ብሎ አየው ። “ይቅርታ አድርግልኝና ሚስተር ዴሚሪስ ይህ አባባልህ ጥሩ መከላከያ ሊሆንልን አይችልም ። ከዚህ የተሻለና የሚያዋጣን ጥሩ የመከላከያ አሳብ ማግኘት ይኖርብሃል ።”

ልቦናው የተሰበረው ዴሚሪስ ጠበቃው የተናገረው ነገር ትክክል መሆኑን ተረዳ ። በዓለም ላይ በየትኛውም ፍርድ ቤት በሚሰየሙ የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎች ዘንድ ይህ አባባል ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም ።

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ጠበቃው ወደ ዴሚሪስ ተመልሶ መጣ ።

“መጥፎ ዜና ነው ይዤልህ የመጣሁት ።”

ዴሚሪስ ከት ብሎ ሳቀ ። በጠባብ የእሥር ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ የሞት ቅጣት ፍርድ ሲጠባበቅ ይህ ሞኛሞኝ ደግሞ መጥፎ ዜና ይዤልህ መጣሁ ይለዋል ። አሁን ካለበት ሁኔታ የከፋ ምን ነገር ሊገጥመው ይችላል ?

“እሺ?”

“የዋርላህ ጉዳይ ነው ።”

“ስፔሮስ ? ምን ሆነ ?”

“ወደፖሊሶች ዘንድ ሄዶ ካተሪን ዶግላስ የተባለችው ሴት በሕይ ወት ትገኛለች ብሎ እንደነገራቸው የሚገልጽ መረጃ አግኝቻለሁ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እያዳመጠ አልነበረም ። ከየአቅጣጫው በመወጠሩ ካተሪንን ረስቷት ነበር ። ሴትዮዋ ወደአደባባይ ወጥታ የምታውቀውን ምስጢር ካወጣች በኖኤሌ ፓጂና በላሪ ዶግላስ ግድያ ወንጀል እንደገና ሊጠየቅ ነው ። ቀደም ሲል በእፎይ ላይ ርምጃ የሚወስድ ሰው ወደለንደን ቢልክም ተልእኮው አሁን በአጣዳፊ ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት ተረድቷል ።

ወደፊት ቀና ብሎ ተቀመጠና የጠበቃውን ክንድ መታ መታ አደረገ። “በአስቸኳይ ወደለንደን መልእክት እንድታስተላልፍልኝ እፈል ጋለሁ ።”

መልእክቱን ሁለት ጊዜ እንዳነበበ ዘወትር የኮንትራት ውል ከመፈራረሙ በፊት የወሲብ ፍላጐቱ እንደሚቀሰቀስበት ሁሉ አሁንም ተቀሰቀሰበት ። የፈጣሪን ሚና እንደመውሰድ ያህል ነው ። ማን እንደሚኖርና ማን እንደሚሞት ወስኗል ። ባለው ኃይሉና ጉልበቱ ተኩራርቷል ። ግን አንድ ችግር አለ ። ይህን ያቀደውን በአስቸኳይ የሚፈፅም ከሆነ ሌላውን ሃሣቡን ተግባራዊ ለማድረግ ጊዜ ሊያጥረው ነው ። ዘዴ መፍጠር ይኖርበታል ። በድንገት የደረሰ አደጋ እንደሚመስል ማድረግ አለበት ። ዛሬ ማታ ።

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ምስጢራዊ ሰነድ

ከዊም ቫንዲን ጋር የተካሄደ ውይይት ዶሴ

አላን = ዛሬ ምን ይሰማሃል?

ዊም = ደህና ነኝ ። እዚህ የመጣሁት በታክሲ ነው። የሾፈሩ ስም ፎናልድ ክሪስቲ ይባላል ። የታክሲው ታርጋ ቁጥር 30271 ሆኖ የሊብሬውም ቁጥር 3070 ነው ። ወደዚህ በምንመጣበት ወቅት በአጠገባችን ሰላሳ ሰባት ሮቨሮች ፣ አንድ ቤንትሌይ ፣ አሥር ጃጓሮች ፣ ስድስት አውስቲኖች ፣ አንድ ሮልስ ሮይስ መኪና ሃያ ሰባት ሞተር ብስክሌቶችና ስድስት ብስክሌቶች አልፈዋል ።

አ= ዊም ፣ የቢሮ ሥራህ አሁን እንዴት ነው ?

ዊ= ታውቃለህ ።

አ= ንገረኝ ።

ዊ= እዚያ ያሉትን ሰዎች ጠልቻቸዋለሁ ።

አ = ካተሪን አሌክሳንደርስ? ... ዊም ፣ ካተሪን አሌክሳንደርንስ? ... ዊም?

ዊ= እርሷማ ፣ ከእንግዲህ እዚያ አትሠራም ።

አ= ምን ማለትህ ነው ?

ዊ= እሷ ልትገደል ነው ።

አ= ምን? ለምን እንደዚያ አልክ ?

ዊ= እርሷ ነገረችኝ ።

አ= ካተሪን ናት እንደምትገደል የነገረችህ ?

ዊ= የለም ሌላ ።

አ= ሌላ ማን ?

ዊ= ሚስቱ ።

አ= የማን ሚስት ዊም ?

ዊ= የኮንስታንቲን ዴሚሪስ

አ= ካተሪን አሌክሳንደር ልትገደል መሆኗን እርሱ ነገረህ ?

ዊ= ሚስስ ዴሚሪስ ፣ ሚስቱ ናት ። የደወለችልኝ ከግሪክ ነው ።

አ= ካተሪንን ማን ሊገድላት ?

ዊ= ከሰዎቹ አንዱ ።

አ= ከአቴንስ ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ ማለትህ ነው ?

ዊ= አዎ ።

አ= ዊም ውይይታችንን እዚህ ላይ እናብቃ ፣ መሄድ አለብኝ ።

ዊ= እሺ ።

ምዕራፍ ሠላሳ

የሄሌኒክ የንግድ ኮርፖሬሽን ቢሮዎች የሚዘጉት በአሥራ ሁለት ሰዓት ነው ። አሥራ ሁለት ሰዓት ከመሆኑ ጥቂት ደቂቃዎች በፊት ኤቬሊንና ሌሎች ሠራተኞች ከቢሮ ወጥተው ለመሄድ ዝግጅት ያደርጉ ነበር ።

ኤቬሊን ወደ ካተሪን ቢሮ ገባች ። "ሚራክል አን ሰርቲፎርዝ ስትሪት" የተባለ ድራማ በክራቴሪያን ይታያል ። ቢጋዜጣና በሬዲዮ ተደንቋል ። ዛሬ ማታ ልታይው ትፈልጊያለሽ ?"

"አልችልም ። አመሰግናለሁ ኤቬሊን ። ወደትያትር ቤት አብሬው ለመሄድ ለጂሪ ሃሌይ ቃል ገብቼለታለሁ ።"

"ሥራ አበዙብሽ አይደል ? መልካም ጥሩ የመዝናኛ ጊዜ እንዲኖ ርሽ እመኛለሁ ።"

ሌሎች ሠራተኞች ከቢሮ ወጥተው ሲሄዱ ካተሪን ትሰማ ነበር ። በመጨረሻም ዐዋታ ሰፈነ ። ጠረጴዛዋን ለመጨረሻ ጊዜ አየችውና ሁሉም ነገር በሥርዓት መቀመጡን ካረጋገጠች በኋላ ለብሳ ፡ ቦርሳዋን ይዛ ከቢሮ ወጣች ። ደረጃውን ወርዳ ከዋናው በር አጠገብ እንደደረሰች የስልኩን ድምፅ ሰማች ። ካተሪን ተመልሼ ስልኩን ላንሳ ብላ አመነታች። ሰዓቷን ተመለከተች ። ከቃጠሮዋ የሚያዘገያት ሊሆን ነው ። ስልኩ ጥሪውን ቀጠለ ። ሮጣ ወደ ቢሮዋ ተመለሰችና ስልኩን አነሳች ። "ሃሎ" አለች ።

"ካተሪን" የደወለው አላን ሃሚልተን ነው ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ። "ስላገኘሁሽ ለፈጣሪ ክብር ምስጋና ይግባው ።"

"ችግር አለ ?"

"ሕይወትሽ አደጋ ላይ ነው ። ሰው ሊገድልሽ ነው ።"

እንደማጉመትመት አለች ። አሰቃቂው ቅዠቷ እውን እየሆነ መጥቷል ። ሰውነቷ ደነዘዘ ። "ማን ?" ።

"እኔ አላውቅም ግን ካለሽበት ሥፍራ እንድትቆይ እፈልጋለሁ ። ከቢሮው አትውጪ ። ማንንም እንዳታነጋግሪ ። አሁኑኑ መጥቼ እወስድሻ ለሁ ።"

"አላን ፡ እኔ ..."

"አታስቢ መንገድ ጀምሬአለሁ ። ቆልፈሽ ተቀመጪ ምንም አትሆኚም ።"

ስልኩ ተዘጋ ።

ካተሪን ቀስ ብላ የስልኩን እጀታ አስቀመጠች ። "አቤት አም ላኬ !"

አታናስ ከቢሮዋ ፊት ለፊት ቆሟል ። የገረጣውን የካተሪንን ፊት አንዴ ገረመመና ወደቆመችበት ተራመደ ። "ችግር አለ ሚስ አሌክሳን ደር ?"

ወደእርሱ ዞር አለች ። "የሆነ ሰው ... አንድ ሰው ሊገድለኝ ነው ።"

ቁና ቁና እየተነፈሰ "ለምን ! ማን ... ማን ነው ይህንን ለማድረግ ያሰበው ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም ።"

የውጪው በር ሲንኳኳ ሰሙ ።

አታናስ ካተሪንን ተመለከተ ። "ልክፈት ... ?"

"የለም" አለች በፍጥነት ። "ማንንም እንዳታስገባ ። ዶክተር ሃሚልተን እየመጣ ነው ።"

የፊትለፊቱ በር ደጋግሞ በኃይል ተንኳኳ ።

"ምድር ቤቱ ውስጥ ልትደበቂ ትችያለሽ" አለና አታናስ በሹክሹ ክታ ነገራት ። "እዚያ ማንም አይነካሽም ።"

በድንጋጤ መንፈስ በአዎንታ ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። "ልክ ነህ ።"

በጓሮ በኩል ዞረው ወደ ምድር ቤቱ አመሩ ።

"ዶክተር ሃሚልተን ሲመጣ የት እንደሆንኩ ንገረው ።"

"እዚያ ለብቻሽ ስትሆኚ አትፈሪም ?"

"እልፈራም" አለች ካተሪን ።

አታናስ መብራቱን አብርቶ ወደ ምድር ቤቱ በሚወስደው መው

ረድ ጀመረ ።

"እዚህ ማንም ሰው ሊያገኝሽ አይችልም ። ሊገድልሽ ስለሚፈልገው ሰውዬ ምንም አታውቂም ?" ሲል አታናስ ጠየቃት ።

ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ስለ ሕልሞቿ ያደረጉትን ውይይት አስታወሰች ። 'ሊገድልሽማ ነው ። ግን ቅዠት ነበር ያየሽው ።'

"እርግጠኛ አይደለሁም ።"

አታናስ ወደእርሷ ተመለከተና በሹክሹክታ "እኔ የማውቅ ይመስለኛል" አላት ። ካተሪን ትኩር ብላ አየችው ። "ማን ነው ?"

"እኔ ነኝ ።" ከመቅጽበት ትልቅ አውቶማቲክ ሰንጢ አወጣና ጉሮሮዋ ላይ ደገነ ።

"አታናስ ይህ የጨዋታ ጊዜ አይደለም ..."

ሰንጢው ጉሮሮዋን በኃይል ሲጫነው ይሰማት ነበር ።

"ካተሪን አፖይንትመንት ኢን ሳማራ የሚል መጽሐፍ አንብበሽ ፣ ታውቂያለሽ አታውቂም ? መልካም ፣ አሁን ሁሉም ነገር መዳረሻ አግኝቷል ። ያንቺም ያሁኑ ሁኔታ ከሞት ሊያመልጥ ወደሳማራ ሲሄድ እዚያም ሞት እንደጠበቀው ሰው ነው ። ይህ ሥፍራ ላንቺ ሳማራ መሆኑ ነው ። ካተሪን" ። የዋህ ይመስል ከነበረው ልጅ አንደበት እንደዚህ ዓይነት አስፈሪ ቃላት ሲወጡ መስማት በጣም አድርጐ ይዘገንናል ።

"አታናስ እባክህ እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ ... "

ፊቷን በጥፊ በኃይል መታት ። "ልጅ በመሆኔ ነው እንዲህ ማድረጌ ያስደነቀሽ ? አትገረሚ ብልሃተኛ ተዋናይ ስለሆንኩ ነው ። ካተሪን ልጅ አልምሰልሽ ፣ ሰላሳ ዓመቴ ነው ። ለምን ልጅ እንደምመስል ታውቂያለሽ! በሕፃንነቴ በቂ ምግብ አላገኝም ነበር ። ማታ ማታ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ የሚበላ ነገር እየሰረቅኩ ነበር ያደግሁት ።" ግድግዳ አስደግፏት ሰንጢውን ጉሮሮዋ ላይ ደግኗል ። "ልጅ በነበርኩበት ወቅት ወታደሮች እናትና አባቴን ገርፈው ሲገድሏቸው በዓይኔ አይቻለሁ ። እኔንም ደብድበው በሞት አፋፍ ላይ ጥለውኝ ነበር ።"

በኃይል እየገፈተራት ወደ ምድር ቤቱ ወሰዳት ።

"አታናስ ፣ እኔ — እኔ አንተን የሚጐዳ ነገር አድርጌ አላውቅም ። እኔ ..."

የጨቅላ ፈገግታ አሳያት ። "ይህን የማደርገው ጠልቼሽ ሳይሆን ሥራ ስለሆነ ነው ። አንቺን ብገድል ሃምሣ ሺህ ዶላር አገኛለሁ ።"

ካተሪን ልክ መጋረጃ ከፊት ለፊቷ የተጣለ ይመስል አይኖቿ በቀይ ብዥታ ተጋርደው ማየት ተሳናት ። ከፊል ሰውነቷ ደግሞ ከግርዶሹ ወጣ ብሎ እየተፈፀመባት ያለውን ድርጊት ያያል ።

"በጣም ግሩም እቅድ ነድፈልሽ ነበር ። ግን አለቃችን በጣም በመቻኮሉ ቶሎ ለፍጻሜ የሚያደርሰኝን ሌላ ዘዴ እንደምንም መፈለግ አለብን ። አይመስልሽም?"

የሰንጢው ጫፍ ስለት ጉሮሮዋን እያሳመመው መጣ ። ስለቱን ወደታች አወረደውና ከፊት ለፊት ያለውን ልብሷን ሸረከተባት ።

"ቆንጆ ነሽ" አላት ። "በጣም ደስ ትያለሽ ። ፓርቲ ልደግስ እስቤ ነበር፤ ግን ዶክተሩ ጓደኛሽ ስለሚመጣ ለዚህ ጊዜ አይኖረንም ። አይመስልሽም? መጥፎ እድል ነው ያለሽ ። እንዴት ያለ ፍቅረኛ ይወጣኝ ነበር መሰለሽ!"

ካተሪን በቆመችበት መተንፈስ አቃታት ።

አታናስ እጁን ወደኪሱ ከተተና ጠርሙስ አወጣ ። በደብዛዛው ጠርሙስ ውስጥ ቀይ ሐምራዊ ቀለም ያለው ፈሳሽ ነበረ ። "ስሊቮቪክ ጠጥተሽ ታውቂያለሽ ? ስለሚደርስብሽ አደጋ ፅዋ እናነሳለን ።" በሰንጢው ጠርሙሱን ለመክፈት ሲሞክር ካተሪን ሮጣ ለማምለጥ ቃጣት።

"በይ ቀጥይ" አለ አታናስ ተዝናንቶ ። "እስቲ ሞክሪው !"

ካተሪን ከንፈሯን መጠጠች ። "ይኸውልህ ፣ እኔ ... ገንዘቡን እሰጥሃለሁ ። እኔ ..."

ትንፋሽሽን ብተቆጥቢ አይሻልም ? አታናስ ጉንጩን ሙሉ ተጐነጨና ጠርሙሱን አቀበላት "ጠጪው ።"

"የለም እኔ አልጠጣም ..."

"ጠጪ !"

ካተሪን ተቀበለችና ትንሽ ተጐነጨች ። ጠንካራው ብራንዲ ጉሮሮዋን አቃጠላት ። አታናስ ጠርሙሱን መልሶ ተቀበላትና በኃይል ተጐነጨ ።

"ሰው ሊገድልሽ መሆኑን ለዶክተሩ ጓደኛሽ የነገረው ማነው ?"

"እኔ—እኔ አላውቅም ።"

“ግድ የለም ። ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም !” አታናስ ጣራውን ደግፎ ወደያዘው የእንጨት ምሰሶ አመለከተ ። “ወደዚያ ሂጂ ።”

ካተሪን ወደበሩ አየች ። በሰንጢው እንደገና አንገቷን ገፋ ። “ደግሜ እንድነግርሽ አትፈልጊ ።”

ካተሪን ወደ እንጨቱ ምሶሶ ሄደች ።

“አሁን ገና ጥሩ ልጅ ሆንሽ ። ተቀመጭ” አለ አታናስ ። “ወደኋላው ዞሮ ሲያይ ካተሪን ያቺን አጋጣሚ ተጠቀመች ።

ልቧ በኃይል እየመታ ወደደረጃው አቅጣጫ እግሬ አውጭኝ አለች። ሕይወቷን ለማትረፍ ነው ሩጫው ። ካሰበችበት ደርሳ ገና አንድ ደረጃ ወደ ላይ መውጣት ስትጀምር በጣም የጠነከረ እጅ እግሯን ይዞ ወደ ኋላ ጐተታት ።

“ውሻ !”

ፀጉሯን ጨምድዶ ፊቷን ወደ እራሱ ፊት አስጠጋ ።

“እንዲህ ዓይነቱን ነገር ሁለተኛ ብትሞክሪው ሁለቱንም እግሮች ሽን አሰብራቸዋለሁ ።”

ሰንጢው አሁን ብብቷ ላይ አርፏል ።

“ተንቀሳቀሺ”

አታናስ መልሶ ወደእንጨቱ ምሰሶ ወሰዳትና ከመሬት ወረወራት ።

“እዚያው ቆዪ ።”

አታናስ የካርቶን ቁልል በሲባጎ ታስሮ ወደ ተቀመጠበት አቅጣጫ ሲሄድ ካተሪን ትመለከት ነበር ። ከሲባጐው ላይ ርዝመት ያላቸው ሁለት ሲባጐዎችን ቆርጦ ወደ እርሷ ተመለሰ ።

“እጆችሽን ወደኋላሽ ምሶሶው ላይ አስደግፊ”

“አይሆንም አታናስ ። እኔ ...”

ፊቷ ላይ በቡጢ ሲመታት ዞረባት ። አታናስ ወደ እርሷ ጠጋ አለና “ሁለተኛ እምቢ እንዳትይኝ ። ጭንቅላትሽን እንዳልበረቅሰው ያልኩሽን ብትፈጽሚ ይሻልሻል ።”

ካተሪን እንደታዘዘችው እጇን ወደ ኋላ ከምሶሶው ላይ ስታስደግፍ አታናስ ከንዶቿ እስኪከረከሩ ድረስ ጠፈራት ። የደም ሥሮቿ ደም እንደልብ ማስተላለፍ ማቆማቸው ተሰማት ።

“እባክህ” አለች ። “በጣም ወጥሪህ ነው ያሰርከኝ ።”

“ጥሩ ነው” አለ እየሳቀ ። ሁለተኛውን ሲባጐ አነሳና ቁርጭምጭሚቶቿን አስሮ ተነስቶ ቆመ ። “የሚፈለገውም ይኸው ነው” አለ ። “በተሳካና በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል ።”

ከጠርሙሱ ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ተንነጨ ። “ተጨማሪ መጠጥ ትፈልጊያለሽ ?”

ካተሪን ጭንቅላቷን ነቀነቀች ።

ትከሻውን ነቀነቀ ። “እሺ ።”

ጠርሙሱን እንደገና ወደ አፉ ሲወስድ ‘ምናልባት ተሳክሮ እንቅልፍ ይይዘው ይሆናል ?’ አለች ካተሪን በአሳቧ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ።

“በቀን አንድ ሊትር ያህል እጠጣለሁ” ሲል አታናስ ጉራውን ነዛ። ባዶውን ጠርሙስ ከሲሚንቶው ወለል ላይ አስቀመጠው ። “መልካም ፣ አሁን ዋናውን ሥራ የምንጀምርበት ጊዜ ደርሷል ።”

“ምን—ምን ልታደርግ ነው ?”

“አንድ ትንሽ አደጋ ልፈጥር ነው ። ይህ ደግሞ በደንብ ታቅዶ የሚፈጸም ተግባር ነው ። ለዚህ ተግባር ዴሜሪስ ከተዋዋልነው በላይ እጥፍ እንዲከፍል እጠይቀዋለሁ ።”

‘ዴሚሪስ! እና ነገሩ ሕልም አይደለም ፣ ይህንን ሁሉ የሚያስደርገው እርሱ ነው ማለት ነው ? ግን ለምን ?’

አታናስ ማሞቂያው ወደሚገኝበት ሥፍራ ሲጓዝ ካተሪን ዝም ብላ ከመመልከት በቀር ሌላ አማራጭ አልነበራትም ። የማሞቂያውን ክዳን አነሳና ከውስጥ ያለውን የሙቀት ማመልከቻ እንዲሁም ማሞቂያው እንዲግል የሚያደርጉትን ስምንቱን ምጣዶች ተመለከተ ። የአደጋ መከላከያው ቁልፍ በቀላሉ እንዳይነካካ ከብረት በተሰራ ሽፋን ውስጥ ተደርጓል ። አታናስ አንድ ትንሽ እንጨት አነሳና በመከላከያው ቁልፍ ውስጥ በመሽነቆር ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን አደረገው ። ማሞቂያው በ150 ዲግሪ ሙቀት ላይ ተደርጎ ቆይቷል ። ካተሪን እያየችው አታናስ ማሞቂያው የመጨረሻ ደረጃ ሙቀት ወደሚሰጥበት ዘወረው ። በፈጸመው ተግባር በመርካት ዞር ብሎ ካተሪን ወዳለችበት አካባቢ መጣ።

“ይህን ማሞቂያ ለማሠራት ምን ያህል ሲያስቸግረን እንደከረመ ታስታውሺያለሽ ?” ሲል አታናስ ጠየቃት ። “መልካም ፣ ከእንግዲህ ስለሱ ብዙ ላንጨነቅ ነው ። አሁን ከናካቴው ሊፈነዳ አይደል ?” አለና

ወደ ካተሪን ተጠጋ ። “ያ የሙቀት መጠን ጠቋሚ ከአራት መቶ ዲግሪ ላይ ሲደርስ ማሞቂያው ይፈነዳል ። ከዚያ በኋላ ምን እንደሚሆን ታውቂያ ለሽ? የጋዝ ቧንቧዎቹ ይፈነዱና እሳት ይያያዛል ። ከዚያም ሕንጻው ቦምብ የፈነዳ ይመስል እንዳልነበረ ይሆናል ።”

“አንተ እብድ ነህ ። እዚህ ውስጥ እኮ ሌሎች ንጹሐን ሰዎች አሉ ። ...”

“ንጹህ የሚባል ሰው የለም ። እናንተ አሜሪካኖች በአስደሳች ፍጻሜ ታምናላችሁ ። ሞኞች ናችሁ ። አስደሳች ፍጻሜ ከቶ ሊኖር አይችልም ።” የካተሪንን እጆች ከምሰሶው የጠፈረው ሲባጐ መጥበቅ አለመጥበቁን ለማረጋገጥ ጐንበስ ብሎ ተመለከተ ። የደም አበላ ከእጆቿ ላይ ይታያል ። ገመዱ በጣም ከመጥበቁ የተነሳ አካሏን ሠርስሮታል ። አታናስ በተቀደደው ልብስ በኩል ሾልከው እፍጠው የሚታዩትን የካተሪንን ጡቶች በእጁ ደባበሰና ጐንበስ ብሎ ሳማቸው ። “በጣም አሳዛኝ ነው ፡ በቂ ጊዜ አጣን ። እንዴት ያለ ነገር እንዳመለጠሽ ባወቅሽ ።”

ወጉሯን ጨምድዶ ያዘና ከንፈሯን ሳማት ። ትንፋሹ ብራንዲ ብራንዲ ይላል ። “ደህና ሁኚ ካተሪን” አለና ተነስቶ ቆመ ።

“እባክህ ጥለሽኝ አትሂድ” ስትል ለመነች ። “እስቲ እንወያ ይና ...”

“ወደአቴንስ የሚመልሰኝ አውሮፕላን መነሻ ሰዓት ተዳርሷል ።” ደረጃውን ሲወርድ ዝም ብላ ተመለከተችው ። “ፍጻሜሽን በደንብ ለማየት እንድትችዪ መብራቱን አብርቼ እተውልሻለሁ ።” ከጥቂት ደቃቂዎች በኋላ ካተሪን የምድር ቤቱ በር ተከፍቶ ተመልሶ ከውጭ ሲቀረቀር ሰማች ። ከዚያ በኋላ ወጥታ ሰፈነ ። ለብቻዋ ናት ። ቀና አለችና የማሞቂያውን ቆጣሪ ተመለከተች ። ሙቀቱ በፍጥነት ወደላይ ይገሰግ ሳል። ከ160 ዲግሪ ወደ 170 ድግሪና ከዚያም በላይ እያሻቀበ ሄደ ። እጇን ከገመዱ ለማስለቀቅ ታገለች ። ስትታገል ገመዱ የበለጠ እየጠበቀ ሄደ ። እንደገና ቀና ብላ አየች የሙቀቱ ቆጣሪ 180 ዲግሪ ደርሶ ከዚያም በላይ እየወጣ ነው ። ምንም ማምለጫ መንገድ አልነበራትም ።

ጨርሶ ምንም ።

አላን ሃሚልተን በዊምፖል ጐዳና በኩል ቁልቁለቱን በመኪናዎች መካከል እየተሽሎከለከ ፡ የሌሎችን እሽከርካሪዎች ግልምጫና የብስጭት

ጩሩንባ እየሰማ እንደእብድ ያሽከረክራል ። ከፊት ለፊቱ ያለው መንገድ ስለተዘጋ ወደግራ ታጠፈና በፖርትላንድ በኩል ወደ አክስፎርድ ሰርከስ ገሰገሰ ። እዚህ ደግሞ የባሰ መኪናዎች በመጨናነቃቸው እንደልብ በፍጥነት መንዳት ተሳነው ።

በ217 ቦንድ ጐዳና ላይ በሚገኘው ምድር ቤት ውስጥ ያለው የማሞቂያው ቆጣሪ ከ200 ዲግሪ ላይ ደርሷል ። ምድር ቤቱ እየጋለ ነው ።

የመኪኖቹ ሁኔታ ጨርሶ አላንቀሳቅሰው አለ ። ሰዎች ወደቤታቸው ይመለሳሉ ፡ ወደ እራትና ትያትር ቤቶች ይገሰግሳሉ ። አላን ሃሚልተን ተስፋ እንደቆረጠ ከመኪናው ውስጥ ተቀምጦ ቀረ ። ‘ሲፖሊስ መደወል ነበረብኝ? ግን ምን ጥቅም ሊኖረው? አንድ የአእምሮ በሽተኛዬ ሊገድል መሆኑን ሰው ነገረኝ ብል ማን ያምነኛል? ፖሊሶቹ ሊስቁብኝ ይችላሉ። የለም—የለም ፡ ቶሎ ብዬ እርሷው ዘንድ መድረስ አለብኝ ።’ መኪኖቹ ትንሽ እየተቃለሉና መንገዱም እየተከፈተ መጣ ።

በምድር ቤቱ ውስጥ የማሞቂያው ቆጣሪ ከ300 ላይ ደርሷል ። ከፍሉ ሊቋቋሙት በማይቻል ከፍተኛ ሙቀት ተውጧል ። እጇን ከገመዱ ለማስለቀቅ እንደገና ስትሞክር የበለጠ ከንዲ ተወጠረ ።

በአክስፎርድ ጐዳና ላይ ባለው የእግረኞች መንገድ ለይ መኪናውን በፍጥነት ማሽከርከር ቀጠለ ። ሁለት አሮጊቶች እቃረጡት ። ከኋላው የትራፊክ ፖሊስ የፊሽካ ድምፅ እንዳሰማ መኪናውን አቁሞ ዕርዳታ ሊጠይቅ አስቦ ነበር ። ግን ስለጉዳዩ ለማስረዳት ጊዜ የለውም ። መንዳቱን ቀጠለ ።

ማቋረጫ ላይ አንድ ከባድ መኪና መንገድ ዘጋበት ። ሃሚልተን ትዕግሥቱ አልቆ ተነጫነጨ ። ጭንቅላቱን በመኪናዋ መስተዋት በኩል ወጣ አደረገና “ተንቀሳቀስ !” አለ ።

የከባድ መኪናው አሽከርካሪ ዞር ብሎ አየው ። “ምን ነካህ ጓዴ ፤ እሳት ውስጥ ልትገባ ነው ?”

መኪኖቹ እንደገና ተጨናነቁ ። መንገዱ ለቀቅ ሲልለት ደግሞ ወደበንድ ጐዳና በረረ ። ከአሥር ደቂቃ በላይ የማይወስደው መንገድ ግማሽ ሰዓት ያህል ፈጀበት ።

ምድር ቤቱ ውስጥ ያለው መቁጠሪያ 400 ዲግሪ ላይ ደርሷል ።

በመጨረሻ እግዜር አድሎት ሕንፃውን ከፊትለፊት ከሚያይበት ደረጃ ደረሰ ። አላን ሃሚልተን መኪናውን ወደ አንድ ኩርባ አስጠግቶ አቆመና በሩን ቶሎ ከፍቶ ወረደ ። ወደ ሕንፃው አቅጣጫ መሮጥ እንደጀመረ ደነገጠና ቀጥ ብሎ ቆመ ። ሕንፃው እንደ ትልቅ ቦምብ ሲፈነዳ መሬቱ በነይል ተንቀጠቀ ። አካባቢው በእሳት ወላፈንና በጢስ ተሞላ ።

ከዚያ በኋላ ሞት ።

ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

አታናስ ስታቪችን የወሲብ ፍላጐቱ በጣም ተቀስቅሶበታል ። የተፈራረመውን ኮንትራት በተግባር ሲፈፅም ሁልጊዜ እንዲህ ዓይነት ውስጣዊ ስሜት ያድርበታል ። ሊገድላት የተላከባትን ሴት ሲጥ ከማድረጉ በፊት ከሷ ጋር ወሲብ መፈጸምን እንደመመሪያ አድርጐ ይዞታል ። አሁን ግን ተበሳጭቷል ፤ ምክንያቱም ካተሪንን ለማሰቃየትም ሆነ አብሯት ወሲብ ለመፈጸም የሚያስችለው በቂ ጊዜ አላገኘም ። አታናስ ሰዓቱን ተመለከተ ። አሁንም ጊዜው ገና ነው ። አውሮፕላኑ የሚነሳው ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ነው ። ወደሼፐርድ የገበያ ሥፍራ በታክሲ ተጓዘና ከታክሲው ወርዶ በጐዳናዎቹ ላይ መራመድ ጀመረ ። በጐዳናዎቹ ላይ በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች ግራና ቀኝ ተሰልፈው ቆመው በዚያ የሚያልፈውን ወንድ ሁሉ ይለክፋሉ ።

‘ሰላም ፣ የእኔ ፍቅር ፣ ዛሬ ማታ ከኔ ጋር አብረህ ለማምሸት ትፈልጋለህ?’

‘ትንሽ ፓርቲ ብናደርግስ ምን ይመስልሃል?’

‘የግሪክ ዓይነቱን ትሻለህ?’

ሆኖም አንዲት ሴት እንኳ አታናስን እንዲህ አላለችውም ። አጭር የቆዳ ቀሚስ ለብሳ ረዥም ታኮ ወደተጫማችው ባለወርቅማ ፀጉር ረዥም ሴት ተጠጋ ።

“እንደምን አመሸሽ?” አለ አታናስ በትህትና ።

በሁኔታው ተገረመችና እቅልቁላ እየችው ። “ሰላም አንተ ትንሽ ልጅ ። እዚህ መምጣትህን እናትህ ታውቃለች?”

አታናስ በሐፍረት ፈገግ አለ ። “አዎ እመቤቴ ። ሥራ የማይበዛብሽ ከሆነ …” ሴተኛ አዳሪዋ ሳቀች ። “ከሆነ ምን ልታደርግ? ሥራ የማይበዛብኝ ከሆነ ምን ልታደርግ? ከዚህ በፊት ከሴት ጋር ተገናኝተህ ታውቃለህ?”

"እንዴ ፣" አለ አታናስ በለሆሳስ ። "በጣም ወድጀው ነበር ።"

"አንተኮ ጨጨ ነህ" አለችና ሳቀች ። "ብዙውን ጊዜ እንዳንተ ያሉትን ጨጨዎች እመልሳቸዋለሁ ፤ ግን ዛሬ ሥራ የለም ለመሆኑ አሥር ይዘሃል?"

"አዎ እመቤቴ ።"

"እሺ የእኔ ፍቅር እንግዲያውስ ወደፎቅ እንውጣ ።"

አታናስን መርታ ወደፎቅ አወጣችውና ከአንድ ክፍል ደረሱ ።

አታናስ ገንዘቡን ሰጣትና የሄደበትን ጉዳይ ጨርሶ ዓይኑን ሲገልጥ አብራው የነበረችው ካተሪን አለመሆኗን ተረዳ ። በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ከአንዲት አስቀያሚ ሴተኛ አዳሪ ጋር ነው ተኝቶ ያለው ። ልብሱን ለበሰና በታክሲ ተሳፍሮ ወደሆቴሉ በመሄድ ሻንጣውን ይዞ ወጣ ።

ወደአውሮፕላን ማረፊያ ጉዞ ሲጀምር ሰዓቱ ከምሽቱ ሦስት ተኩል ነበረ ። ከአውሮፕላኑ ለመድረስ በቂ ጊዜ አለው ።

ተሰልፈው ያሉ የኦሎምፒክ አየር መንገድ ተሳፋሪዎች ጥቂት ናቸው አታናስ ተሰልፎ ተራው ሲደርስ ለሠራተኛው ቲኬቱን አሳየ ። "አውሮፕላኑ በሰዓቲ ነው የሚነሳው?"

"አዎ" አለና ሠራተኛው ቲኬቱ ላይ የሠፈረውን ስም ተመከተ ። 'አታናስ ስታቪች' ይላል ። እንደገና ቀና ብሎ ወደ አታናስ ተመለከተና ዞር ብሎ አጠገቡ ቆሞ ወዳለው ሰው እይቶ ሹንቅላቱን ነቀነቀ ። ሰውዬው ወደ ቲኬት ማዕደቂያው ጠረጴዛ ተጠጋ ።

"እስቲ ትኬትህን ልየው?"

አታናስ ቲኬቱን ሰጠውና "ችግር አለ?" ሲል ጠየቀ ። ሰውዬው መለሰና "ለዚህ በረራ የተመዘገቡ ሰዎች ቁጥር የበዛ ይመስለኛል ።

አታናስ ትከሻውን ነቀነቀ ። "እሺ" አለና በልበ ሙሉነት ሰውዬውን ተከትሎ ወደቢሮ ሄደ ። ይሄኔ ዴሚሬስ ከእሥር ተለቆ ሊሆን ይችላል ። ሰውዬው ሕግ የማይገዛው ዝነኛ ሰው ነው ። ሁሉም ነገር እንደታቀደው ተከናውኗል ። የሚቀበለውን ሃምሳ ሺህ ዶላር በስዊስ ባንክ ውስጥ ከከፈታቸው የተለያዩ ደብተሮች በአንደኛው ሊያስቀምጥ ይችላል ። ከዚህ በኋላ ለዕረፍት ወደሪቪኢራ ወይም ሪኦ ይሄዳል ። በተለይ በሪኦ የሚወደው ነገር አለ ።

አታናስ ወደቢሮው ውስጥ ገባና ቆም ብሎ አፈጠጠ ። ፊቱ ገረጣ ። "ሞተሻል! ሞተሽ የለ እንዴ! ገድዬሻለሁ!" እያለ ጩኸቱን ለቀቀ ።

ከክፍሉ አውጥተው ወደተዘጋጀው የፖሊስ መኪና ሲወስዱትም አታናስ ጩኸቱን አላቆመም ነበር ። መኪናው ውስጥ ገብቶ ሲሄድ እነ አላን ሃሚልተን ያዩታል ። አላን ወደ ካተሪን ዞር አሰና "እዚህ ላይ አበቃ ፍቅሬ ፣ ከእንግዲህ ተገላግለናል" ሲል ተናገረ ።

ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

ከተቂት ሰዓታት በፊት ካተሪን እጀጀን ከገመዱ እሥራት ለማላቀቅ በምድር ቤቱ ውስጥ ብዙ ታግላለች ። በተወራጨችና በታገለች ቁጥር ገመዱም ይበልጥ ጠብቆባታል ። ጣቶቿ ደንዝዘዋል ። በማሞቂያው ላይ ያለውን ቆጣሪ አሁንም አሁንም ታይ ነበር ። ቆጣሪው ከ250 ዲግሪ ላይ ደርሷል ። 'ያ ቆጣሪ ከ400 ዲግሪ ላይ ሲደርስ ግሞቂያው ይፈነዳል ። ከዚህ ለማምለጥ አንድ ዘዴ መገኘት ይኖርበታል' አለች ካተሪን በአሳቧ ።

'ዘዴ መገኘት ይኖርበታል ።' የካተሪን ዓይን በወለሉ ላይ በተጣለው የብራንዲ ጠርሙስ ላይ አረፈ ። አተኩራ ስታየው ልቧ በኃይል መምታት ጀመረ ። 'አንድ ፅድል አለኝ' አለች በአሳቧ 'የምችል ከሆነ ።' ... ካተሪን ከታሰረችበት ምሰሶ እራሷን ለማላቀቅ ወደፊት ተንጠራራችና በእግሯ ጠርሙሱን ለመንካት ሞከረች ። ልትደርስበት አልቻለችም ። የበለጠ ስትንጠራራ የምሰሶው ስንጥር ጀርባዋን ወጋጋው ። ጠርሙሱ ከእግሯ አንድ ኢንች ያህል ርቆ ይገኛል ። የካተሪን ዓይኖች እንባ አቀረሩ። 'አንድ ጊዜ ልሞክር' አለች በአሳቧ ። 'አንዴ ብቻ ።' እንደገና ባለ በሌለ ኃይሏ ወደፊት ስትንጠራራ ፣ ስንጥሮቹ የበለጠ ጀርባዋን ወጋጉት ። አንዱ እግሯ ጠርሙሱን ነካው ። 'ጥንቃቄ ፣ ገፍቼ እንዳላርቀው' የሚል አሳብ በአእምሮዋ ብልጭ አለ ። ቀስ በቀስ የጠርሙሱን አንገት እግሯን ባሰረው ገመድ ውስጥ ከተተች ። ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ እግሯን አጠፈችና ጠርሙሱን አስጠጋች ። አሁን ጠርሙሱ ከአጠገቧ ነው ።

ቀና ብላ የማሞቂያውን ቆጣሪ ተመለከተች ፣ አሁን ከ280 ዲግሪ ደርሷል ። ከፉኛ ተደናግጣለች ። ቀስ ብላ ጠርሙሱን በእግሯ ወደኋላዋ ገፋች ። ጣቶቿ ወደ ጠርሙሱ ቢደርሱም ደንዝዘው ስለነበረ እንደምትፈልገው ሊጨብጡላት አልቻሉም ። ከእጅ ጡንቻዎቿም የሚንጠባጠበው የደም እበላ እጀጀን አርሶ እንዲያሙለጨልጭ አድርጎቸዋል ።

ምድር ቤቱ በጣም እየሞተ መጥቷል ። እንደገና ሞከረች ፣ ግን

ጠርሙሱ ተሙለጭልጮ ወደቀ ። ካተሪን ቆጣሪውን ስታየው ከ300 ዲግሪ የደረሰ ሲሆን በፍጥነት ማሻቀቡን ቀጥሏል ። ከማሞቂያው ውስጥ እንፋሎት መውጣት ጀምሯል ። እንደገና ጠርሙሱን ለመጨበጥ ሞከረች።

አም አሁንጠርሙሱን በእጇ ጨበጠች ። ጠበቅ አድርጋ ያዘችውና ምሰሶው ላይ ልትሰብረው ሞከረች ። አልተሰበረም ። ተስፋ በመቁረጥ ድምጿን ከፍ አድርጋ ጮኸች ። እንደገና ሞከረችው ፣ አሁንም ምንም ለውጥ አልተገኘም ። ቆጣሪው አሁን ከ350 ዲግሪ ላይ ደርሷል ። ካተሪን በኃይል ወደውስጥ ተነፈሰችና ባለ በሌለ ጉልበቷ እንደገና ልትሰብረው ሞከረች ። የመሰበር ድምፅ ሰማች ። 'እግዚአብሔር ይመስገን' አለችና በፍጥነት አንዱን ስባሪ አንስታ ገመዱን መገዝገዝ ጀመረች ። ጡንቻዋን ቢቆርጠውም ሕመሙን ተቋቁማ ገመዱን መበጣጠስ ቀጠለች ። ወዲያው አንዱ እጇ ተለቀቀ ። ሌላውን እጇንም እንዲሁ በመጨረሻ ፈታች ። ይኸኔ ቆጣሪው ከ380 ዲግሪ ደርሷል ። ከማሞቂያው ውስጥ እንፋሎት በኃይል ቡልቅ ቡልቅ ይላል ። ካተሪን ዘላ ተነስታ ቆመች ። አታናስ የምድር ቤቱን በር ከውጭ ዘግቶታል ። ። ከፍንዳታው በፊት ከሕንፃው ውስጥ ለማምለጥ የሚቻልበት በቂ ጊዜ የለም ።

ካተሪን ወደማሞቂያው ሮጣ የእደጋ መከላከያው እንዳይሠራ የተሸነቀረበትን እንጨት መዝዛ ስታወጣ ቆጣሪው ከ400 ዲግሪ ደርሷል።

ከውሳኔ ላይ ለመድረስ በጣም አጭር ጊዜ ነበራት ። ወደፍንዳታ መከላከያው ክፍል ሮጣ በሩን ከፍታ ዘው አለችና በኃይል ወርውራ ዘጋችው ። ቁና ቁና እየተነፈሰች ወለሉ ላይ እንደተዘረረች ከአምስት ደቂቃ በኋላ ከፍተኛ ፍንዳታ ደረሰና ከፍሉ ከፉኛ ተነቃነቀ ። በጨለማው ውስጥ ወለሉ ላይ ተኝታ ከውጭ የሚንቀለቀለውን የእሳት ወላፈን ድምፅ ትሰማ ነበር ። ምንም ጉዳት አልደረሰባትም ፣ ፍንዳታውም አልቋል ። 'የለም ። አሁንም ገና ነው' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'አሁንም ማድረግ ያለብኝ ነገር አለ ።'

የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች ከአንድ ሰዓት በኋላ ደርሰው ሊያወጧት አላን ሃሚልተንም እዚያው ነበር ። ካተሪን ሮጣ አቀፈችው ፣ እርሱም ጥብቅ አድርጐ ያዛት ።

"ካተሪን የእኔ ፍቅር ፣ በጣም ፈርቼ ነበር ፣ ለመሆኑ እንዴት ...?"

"በኋላ" አለች ካተሪን ። "አታናስ ስታቪችን ማስያዝ አለብን ።"

ምዕራፍ ሰላሳ ሦስት

በሱሴክስ በሚገኘው የአላን እህት የእርሻ ቦታ ማንንም ተጋባዥ ሳይጠሩ የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን ፈጸሙ ። ካተሪን በአላን ቢሮ ውስጥ እንዳየችው ፎቶግራፍ የአላን እህት ፍፁም ደስ የምትል ሆና አግኝታታለች ። ልጇ ወደ ትምህርት ቤት ሄዷል ። ካተሪንና አላን ቅዳሜና እሁድን እየተዝናኑ በእርሻው አካባቢ ካሳለፉ በኋላ ለጫጉላ ጊዜያቸው ወደቬኒስ በረሩ ።

ቬኒስ በመካከለኛው ዘመን ታሪኳ የታወቀች ናት ። ለመርከብና ለጀልባ መጓጓዣ ቦይ የተቆፈረላት ፣ 120 ደሴቶቿ በ400 ድልድዮች የተያያዙላት ውብ ከተማ ናት ። አላንና ካተሪን ሚስትሬ አጠገብ ከሚገኘው ማርኮፖሎ የቬኒስ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ በሞተር ጀልባ ተሳፍረው ወደፒአዛ ሳን ማርኮ አመሩ ። ከዚያም እንደደረሱ በዶጅስ ቤተመንግሥት አጠገብ ካለው የሮያል ዳኒኤሊ ሆቴል ውስጥ ክፍል ተከራዩ ።

ክፍላቸው ልዩና ውብ ሲሆን በጥንታዊ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች አጊጧል ። መኝታ ቤቱ ውስጥ ሆኖ ዋናውን ትልቅ ቦይ መመልከት ይቻላል ።

"በመጀመሪያ ምን ለማድረግ ትፈልጊያለሽ?" ሲል አላን ጠየቃት።

ካተሪን ወደእርሱ ተጠጋችና እቅፍ አደረገችው ። "እስቲ ገምት።"

ዕቃቸውን ከሻንጣቸው ያወጡት በኋላ ነው ።

ካተሪን ያለፈውን ቅዠቷንና አስፈሪ ነገሮችን እንድትረሳ ቬኒስ ፈዋሽ መድኃኒቷ ሆነች ።

ከአላን ጋር ብዙ ሥፍራ ጉብኙ ። የብዙ መቶ ዓመታት ዕድሜ ያለው የቅዱስ ማርቆስ አደባባይ ከሆቴላቸው 100 ያርድ ያህል ብቻ ርቆ ይገኛል ። የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ቤተክርስቲያንም ፣ የሥዕል ግሳያም ነው ። በግምቡና በጣሪያው ልዩ ልዩ አይነ-ግብ ሥዕሎች ተስለዋል።

ወደዶጅስ ቤተመንግሥት ገብተው በውስጡ ያሉትን ክፍሎች ጐበኙ ። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ሞት የተፈረደባቸው እሥረኞች ሊገደሉ ሲወሰዱ ከሚያልፉበት የሳይስ ድልድይ ላይ ቆመው ተመለከቱ ።

የተለያዩ ሙዚየሞችን ፣ አብያተ ክርስቲያናትንና ደሴቶችን እየተዘዋወሩ አዩ ። በሙራኖም የመስተዋት ሥራን ፣ በቡራኖ የሴቶችን የጥልፍ ሥራ ተመለከቱ ። በሞተር ጀልባ ወደቶርሴሎ ተጉዘው በአበባ ተክል በተዋበችው በሉካንዳ ሲፕሪአኒ ሆቴል ምሣ ተመገቡ ።

ካተሪን የሴቶቹን ገዳም የአትክልት ሥፍራ አስታወሰችና ምን ያህል ጠፍታና ተበላሽታ እንደነበር ተገነዘበች ። ከፊት ለፊቷ የተቀመጠውን ፍቅረኛዋን አላንን እያየች በልቧ 'እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ' አለች ።

ሜርሴሪ ፣ ቆንጆ-ቆንጆ ፣ በርካታ መደብሮች ያሉባት አካባቢ ነች። ከሩቤሉ መደብር ልብሶችን ፣ ከካሳላ መደብር ጫማዎችን ፣ ከጂአኮንዶ ካሲኒ ሱቅ ብርቅዬ ዕቃዎችን ሸማመቱ ። በኳድሪና አል ግራስታ ዴሉአና እንዲሁም በሃሪ ባር ሆቴሎች ተመገቡ ። በትልቁ ጉንዶላና በትንሽ ሳንዶሊ ታንኳዎች ተንሸራሸሩ ።

መመለሻቸው ሲቃረብ ዓርብ ዕለት መጠነኛ ዝናብ ዘነበ ፣ አውሎ ነፋስም ተነሳ ።

ካተሪንና አላን ቶሎ ብለው ወደሆቴል ክፍላቸው ተመለሱ ። ከመኝታ ቤታቸው ሆነው በመስኮት በኩል እያዩ "በመዝነቡ በጣም እዝናለሁ ሚስስ ሃሚልተን" አለ አላን እየቀለደ ። "ስለአየር ጠባዩ የሚገልፀው ወረቀት ፀሐይ እንደሚኖር ነበር የጠቆመኝ ።"

ካተሪን ፈገግ አለች ። "የምን ዝናብ? ፍቅርዬ እኔን በጣም ደስ ብሎኛል ።"

በሰማዩ ላይ ብልጭታ ታይቶ የመብረቅ ድምፅ መሰማቱ ካተሪን የማሞቂያውን ፍንዳታ እንድታስታውስ አደረጋት ።

ወደአላን ዞር አለች ። "ዛሬ የፍርድ ውሳኔ ሰጭዎቹ ፍርድ የሚሰጡበት ቀን አይደለምን?" ስትል ጠየቀችው ።

ትንሽ አመነታ ። "አዎ ፣ ነገሩን ያላነሳሁብሽ ለምን መሰለሽ ..."

"መጥፎ ነገር የማስታውስ መስሎህ ነው? ደህና ነኝ ለማወቅ ነው።"

ትኩር ብሎ እያትና ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "እሺ ።"

አላን ሬድዮኑ ወደተቀመጠበት ሥፍራ ሄዶ ሬድዮኑን ሲከፍት ካተሪን ዝም ብላ ታይ ነበር ። ሬድዮኑን ጉራጉረና ከቢቢሲ ጣቢያ ላይ መሥመሩን አቆመ ።

“ … ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዛሬ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤያቸውን አቀረቡ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስ መንግሥት ያቋቁማሉ ።” የራድዮው ድምፅ ብቅ እልም እያለ በደንብ አይሰማም ።

“ያ መብረቅ አዘል አውሎ ነፋስ ነው እክል የሚፈጥረው” አለ አላን።

የራድዮው ድምፅ እንደገና መሰማት ጀመረ ። “በአቴንስ የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ክስ ከማጠቃለያ ላይ የደረሰ ሲሆን የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የቀድሞ ውሳኔያቸውን በማጠፍ ብዙ ሰዎችን ባስገረመው ሁኔታ ፈረዱ …”

የሬድዮው ድምፅ ጠፋ ።

ካተሪን ወደ አላን ዞር አለች ። “ምን … ፍርዱ ምን ይመስልሃል?”

እቅፍ አደረጋትና “በመልካም ፍፃሜ ማመንና አለማመንሽ ይህንን ይወስነዋል” አላት ።

መዳረሻ

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፍርድ ቤት በመቅረቡ ከአምስት ቀናት በፊት ጠባቂው ዘበኛ የእሥር ቤቱን በር ከፈተለት ።

“ጠያቂ መጥቶልሃል ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቀና ብሎ አየው ። ከጠበቃው በስተቀር እስካሁን ድረስ ማንም ጎብኚ እንዲያየው አልተፈቀደም ነበር ። ፊቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉጉት አላስነበበም ። አነጂያ ውላጆች እንደተራ ወንጀለኛ ነበር የቆጠሩት ። የውስጥ ስሜቱን እሳይቶ ደስ ሊያሰኛቸው አልፈቀደም። የእሥር ቤቱን ዘብ ተከትሎ ወደ አንዲት የስብሰባ አዳራሽ አመራ ።

“እዚያ አለልህ ።”

ዴሚሪስ ከክፍሉ ውስጥ እንደገባ በተሸከርካሪው ወንበር ላይ ጎብጦ የተቀመጠ አካለ ስንኩል ሽማግሌ ተመለከተ ። ፀጉሩ እንደ በረዶ የነጣ ነው ። ፊቱ የተሰበሰበ ሳምባ ይመስላል ። የተቆለመሙ ከንፈሮቹ ፈገግታ ለማሳየት ሲሉ ያስፈራሉ ። ዴሚሪስ ጎብኚው ማን እንደሆነ ለማወቅ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም ። በድንጋጤ አመዱ ቡን አለ ።

“ያንተ ያለህ!”

“ፅፈሮት አይደለሁም” አለ ናፖሊዮን ቾታስ በጉረኒነ ድምጽ ። “ገባ በል ኮስታ!”

ዴሚሪስ በግድ መናገር ጀመረ ። “አሳቱ …”

“በመስኩት በኩል ዘልዬ ወጣሁና ወገቤ ተሰበረ ። የአሳት እደጋ ተከላከዮች ከመድረሳቸው በፊት የአልፍኝ አሽከሬ ደርሶ ገለል አደረገኝ ። በሕይወት መኖሬን እንድታውቅ አልፈለግኩም ነበር ። ከአንተ ጋር ግብግብ መግጠሙ ሰልችቶኛል ።”

“ቁን … ያኔ የተገኘውስ አስከሬን?”

“የቤቱ ጠባቂ ነው ።”

ዴሚሪስ ወንበር ላይ ዘፍ አለ ። “ሕይወትህ በመትረፉ ደስ ብሎኛል” አለ በደከመ ድምፅ ።

“ደስ ሊልህ ይገባል ። ሕይወትህን ላተርፍ ነው ።”

ዴሚሪስ በጥርጣሬ አተኩሮ አየው ።

“አንተ ልታተርፈኝ?”

“አዎ ። እኔ ጥብቅና ልቆምልህ ነው ።”

ዴሚሪስ ከት ብሎ ሳቀ ። “የምርህን ነው ... ሊዮን? ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ አሁንም እንደምኝ ትቆጥረኛለህ? ለመሆኑ ሕይወቱን ባንተ መዳፍ ውስጥ የምጥል እንዴት ሊመስልህ ቻለ?”

“ምክንያቱም ኮስታ ፣ ሕይወትህን ለማትረፍ የምችለው እኔ ብቻ ስለሆንኩ ነው ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተነሳና “አልፈልግም ለማንኛውም አመሰግናለሁ” በማለት ወደበሩ አመራ ።

“ስፒሮስ ላምብሩን አነጋግራዋለሁ ። እህቱ በተገደለችበት ሰዓት ከአንተ ጋር እንደቆየ ምስክርነቱን እንዲሰጥ አግባብቼዋለሁ ።”

ዴሚሪስ ቆም ብሎ ወደኋላው ዞረና “ለምን ብሎ ይመሰክርልኛል?” ሲል ጠየቀው።

ቾታስ ወንበሩ ውስጥ እንዳለ ወደፊት አዘመመ ። “ሕይወትክን ከማጥፋቱ ይልቅ በቁምህ ሀብትህን በሙሉ በመንጠቅ መበቀሉ የበለጠ እንደሚያረካው ሰላሳመንኩት ።”

“በጀ ።”

“እሚመሰክርልህ ከሆነ መላ ሀብትህንና ንብረትህን እንደምታስረክበው አረጋገጥኩለት ። ኩባንያዎችህን ፣ መርከቦችህን ፣ ማንኛውንም ቅርስህን ...”

“አብደህል መሰለኝ?”

“እመስልሃለሁ፣ ኮስታ እስቲ አስብበት ።”

“የእርሱ ምስክርነት ሕይወትህን ሊያተርፍ ይችላል ። ሀብትህ ከሕይወትህ ይበልጥብህል እንዴ!”

ለረኹም ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ። ዴሚሪስ ተመልሶ ተቀመጠ ። “ሜሊና በተገደለችበት ወቅት ከእርሱ ጋር እንደነበርኩ ላምብሩ ሊመሰክርልኝ ፈቃደኛ ነው!”

“አዎን ።”

“በምላሹ ከኔ የሚፈልገው ...”

“ያፈራኽውን ሁሉ እንድትሰጠው ።”

ዴሚሪስ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “አንድ ነገር ሰራሲ ማስቀረት ...”

“እትችልም ። ሙልጭህን ሊያስቀርህ ፈልጓል ። እንደበቀል የሚቆጥረውም ይህንን ነው ።”

ዴሚሪስን ያስገረመው ሌላም ነገር አለ ። “ይህን ሁሉ በማድረግ አንተስ የምታገኘው ምንድርነው ሊዮን?” ሲል ቾታስን በጭንቀት ጠየቀው ።

የቾታስ ከንፈሮች ፈገግታ ሊያሳዩ ሞክሩ ፣ ያልተሳካ ጥረት ። “ሁሉንም” ብሎ መለሰለት ።

“አ ... አልገባኝም ።”

“የሄሌኒክ ንግድ ኩባንያን ወደላምብሩ ይዞታ ከማዛወርህ በፊት የኩባንያውን ንብረት ሁሉ የእኔ ንብረት ወደሆነው ወደ አዲስ ኩባንያ ታዛውራለህ ።”

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ አየው ። “እና ላምብሩ ምንም አያገኝም ማለት ነዋ!”

ቾታስ ትከሻውን ነቀነቀ ። “አሸናፊዎች እንዳሉ ሁሉ ተሸናፊዎችም አሉ ።”

“ላምብሩ ጥርጣሬ አያድርበትም?”

“አሠራሬ ጥርጣሬ አያሳድርም ።”

“ላምብሩን በዚህ ዓይነት የምታታልለው ከሆነ እኔንም ላለማታለልህ ምን ማረጋገጫ አለኝ?”

“ቀላል ነው ውድ ኮስታ ፣ ሥጋት አይግባህ ። ኩባንያው የኔ የሚሆነው እንተ በነፃ ስትለቀቅ ብቻ መሆኑን ጠቅሰን እንፈራረማለን ። ወንጀለኛ ሆነህ ከተገኘህ እኔም ምንም አላገኝም ።”

ለመጀመሪያ ጊዜ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በጉዳዩ ተመስጦ ከተቀመጠበት ሆኖ አካለ ስንኩሉን የሕግ ባለሙያ በጥሞና ተመለከተ ። ‘እኔን ሊበቀልስ ሲል ከፍርድ ቤቱ ሊያገኝ የሚቻለውን በብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ካሳ ለማጣት ይፈልጋል! በፍጹም ያን ያህልስ ጅል አይደለም ።’ “መልካም” አለ ዴሚሪስ ። “ተስማምቻለሁ ።”

ቾታስ “ጥሩ ፣ ኮስታ አሁን ገና ሕይወትህን አተረፍክ” አለው ።

‘መች ሕይወቴን ብቻ’ አለ ዴሚሪስ በአሸናፊነት መንፈስ በልቡ ። ‘ማንም ሰው ሊያገኘው በማይችል ሥፍራ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ያህል ደብቄአለሁ ።’

ቾታስ ከስፒሮስ ላምብሩ ጋር ያደረገው ውይይት በቀላሉ ከመግባባት ላይ የተደረሰበት አይደለም ።

“መስክረህ የዚያን አረመኔ ሕይወት አትርፍለት ነው የምትለኝ? በል ከዚህ ውጣልኝ ።”

“ልትበቀለው ትፈልግ የለ?” ሲል ቾታስ ጠየቀው ።

“እየተበቀልኩትማ ነው ።”

“ነው እንዴ? ኮስታን ታውቀዋለህ! ሀብቱ ከሕይወቱ ይበልጥበታል። ብትገድለው ጣሩ ለቅጽበት ብቻ ተሰምታው ወዲያው ያልፋል ። ያለውን ሁሉ ወስደህበት በባዶ ኪሱ ከኑሮ ጋር ካጋፈጥከው ግን ከሞት በባሰ ቅጣት ቀጣኸው ማለት ነው ። አይገባህም?”

የሕግ ባለሙያው ያለው እውነትነት አለው ። እስካሁን ካጋጠሙት ሰዎች መካከል እንደዴሚሪስ ሰስታም ሰው አላየም ። “ያለውን ሀብት በሙሉ አሳልፎ ሊሰጠኝ ተሰማምቷል ነው የምትለው?”

“ሳንቲም ሳትቀር ስልህ! በየብስ ፣ በአየርና በባሕር ያሉ ይዞታዎቹ ንም ሆኑ ኩባንያዎቹን ሁሉ ።”

አባባሉ በጣም የሚያጓጓ ነው ። “እስቲ ላስብበት” ካለ በኋላ የሕግ ባለሙያው ተሽከርካሪ ወንበሩን እያሽከረከረ ከቢሮው ሲወጣ ላምብሩ ዝም ብሎ ተመለከተው ። ‘እስቲ እንዲህ ሆኖ መናር ያስመኛል!’ አለ በልቡ ።

እኩለ ሌሊት ላይ ስፒሮስ ላምብሩ ለናፖሊዮን ቾታስ ስልክ ደወለለት ። “ከውሳኔ ደርሻለሁ በሃሳብህ እስማማለሁ ።”

የዜና ማሰራጫዎች የሚያርገበግቡት ትኩስ ዜና ሆነ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ባለቤቱን በመግደሉ የወንጀል ክስ የተመሠረተበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን በእሳት አደጋ ሞቷል ተብሎ የነበረ ዝነኛ ጠበቃ በሕይወት ተገኝቶ ጥብቅና የቆመለት መሆኑ ጭምር ጉዳዩን የበለጠ አስገራሚ አድርጎታል ።

ችሎቱ የተሰየመበት ክፍል ያኔ ናኤሌ ፓጂና የላሪ ዶግላስ ክስ የታየበት ያው ክፍል ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ብዶንብ ሊታይ ከማይችልበት የተከላሽ መቀመጫ ሥር ተቀምጧል ። ክሱ ተጥሎ ናፖሊዮን ቾታስ በተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ተኮፍሷል ። የሕግ ተወካይ ሆነ

በከሳሽ ወገን የቆመው ልዩ አቃቤ ሕግ ዴልማ ነው ።

ዴልማ ለፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ የሚከተለውን ቃል አሰማ ፦

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዓለም ውስጥ በጣም ታዋቂ ከሆኑትና ተደማጭነትን ካላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ነው ። ወደርየለሽ የሆነው ሀብቱ ያሻውን ብዙ ነገር ለማድረግ አስችሎታል ። ቢሆንም አረመኔያዊ ግድያ የመፈፀምን መብት ሊያስከብርለት አልቻለም ። ማንም ቢሆን እንዲህ ዓይነት መብት አይኖረውም ።” ዞር ብሎ ወደ ዴሚሪስ ተመለከተ። “ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ታፈቅረው የነበረችውን ሚስቱን በአሰቃቂ ሁኔታ ለመግደሉ በቂ ማስረጃ በሕግ አስከባሪው በኩል ሊቀርብ ይችላል ። ይህ ማስረጃ ቀርቦላችሁ ስትሰሙ ልትሰጡት የምትችሉት ውሳኔ አንድ ብቻ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ ። ይኸውም ተከሳሹ ለተከሰሰበት ወንጀል በአንደኛ ደረጃ ጥፋተኛ መሆኑን ነው ።” ተመልሶ ወደመቀመጫው ሄደና ተቀመጠ ።

ሰብሳቢ ዳኛው ወደናፖሊዮን ቾታስ ዞር አለ ። “ተከሳሾች የመከላከያ አሳብ ለማቅረብ ተዘጋጅታችኋል?”

“አዎ ጌታዬ” አለና ቾታስ በተሽከርካሪ ወንበሩ ወደፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ተጠጋ ። አስፈሪ ፊቱንና ሽባ አካሉን ለማየት ቢጠየፉም በፊታቸው ገፅታ ላይ አዘኔታ እንደሚነበብ ተገንዝቧል ።

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተከሰሰበት ጉዳይ ሀብታምና ኃያል ስለሆነ አይደለም ። ምናልባት ወደዚህ ፍርድ ቤት ተጕትቶ የመጣው በዚያ ሰበብ ሊሆን ይችላል ። ደካሞች ምን ጊዜም ጠንካሮችን ለማንበር ከክ መከጀላቸው አይቀርም ። ሚስተር ዴሚሪስ ኃያል ባለፀጋ በመሆኑ እንደጥፋተኛ ሊታይ ይችል ይሆናል ። ግን ባለቤቱን ከመግደል ወንጀል ንፁህ መሆኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ ።”

ችሎቱ የተጀመረው በዚህ ሁኔታ ነበር ።

አቃቤ ሕጉ ዴልማ ለፖሊስ የመቶ አለቃ ቲዮፊሉስ በዳኞቹ ፊት ጥያቄ አቀረበ ።

“የመቶ አለቃ ፣ ወደዴሚሪስ የባሕር ዳርቻ ቤት ስትገባ ምን እንዳየህ ትገልጥልናለህ?”

“ወንበሮቹና ጠረጴዛዎቹ ተገለባብጠውና ቤቱ ተመሰቃቅሎ ነበር።”

“በከባድ ልፊያና ትንቅንቅ ምክንያት ይመስልሃል?”

"አዎ ጌታዬ ። ቤቱ የተዘረፈ ነበር የሚመስለው ።"

"ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ሥፍራ በደም የተጨማለቀ ጩቤ አግኝተህ ነበር አይደል?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"በጩቤው ላይ የጣት አሻራ ነበረ?"

"ትክክል ።"

"የማን የጣት አሻራ ነው?"

"የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ።"

የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ዓይን ዴሚሪስ ላይ አረፈ ።

"ቤቱን በምትፈትሽበት ወቅት ሌላ ምን አገኘህ?"

"ክቁም ሣጥኑ በስተጀርባ የዴሚሪስ አህፅሮተ ስም ያለበትን በደም የተጨማለቀ የዋና ሙታንታ ።"

"የዋና ልብሱ በቤቱ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ቆይቶ ነበር ለማለት አይቻልም?"

"አይደለም ጌታዬ ያኔ በባሕሩ ውሀ እንደረጠበ ነበር ።"

"አመሰግናለሁ ።"

ተራው የናፖሊዮን ቾታስ ነበረ ። "መርማሪ ቲዮፊሉስ ፥ ተከሳሹን በግል የማነጋገር ዕድል አግኝተህ ነበር?"

"አዎ ጌታዬ"

"ስለእርሱ ሥዕላዊ መግለጫ አስቲ ስጠን ።"

"መልካም ..." አለና መርማሪው ዴሚሪስ ወደተቀመጠበት ተንጠራርቶ እያየ "ግዙፍ ሰው ነበር ለማለት እችላለሁ ።"

"ጠንካራ ይመስል ነበር? ማለት በሰውነት አቋሙ ።"

"አዎ ።"

"ማለቴ ሚስቱን ለመግደል ያን ያህል ቤቱን የሚያመሰቃቅል አይደለማ?"

ዴልማ ተስፈንጥሮ ቆመ ። "ተቃውሞ ።"

"ተቃውሞው ይጸናል ። የተከሳሹ ጠበቃ ጠቋሚ ጥያቄዎችን ባያቀርብ ጥሩ ነው ።"

"ይቅርታ ክቡር ጌታዬ ።" ቾታስ ወደመርማሪው ተመልሶ ዞረ ። "ከሚስተር ዴሚሪስ ጋር ካደረግከው ውይይት በወሰድከው ግምት ብልህ ሰው አድርገህ ትቆጥረዋለህ?"

"አዎ ጌታዬ ። በጣም ብልህና ጉበዝ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው እንደርሱ ሀብታም ሊሆን አይችልም ።"

"ትክክል ብለሃል የመቶ አለቃ ፥ ይሁንና ይህ ሀቅ ወደሌላ ጥያቄ ይመራናል ። ታዲያ እንደ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያለ ብልህ ሰው ግድያ የፈጸመበትን ጩቤ ከእነአሻራው እንዲሁም በደም የተጨማለቀ ሙታን ታም ለማስረጃነት ትቶ ይሄዳል? ... ይህ ሞኝ የሚያከናውነው አይመስል ህም?"

"አዎ ፥ አንዳንዴ ሰዎች ወንጀል በሚፈጽሙበት ወቅት እንግዳ ነገር መስራታቸው አዲስ አይደለም ።"

"ፖሊሶች ዴሚሪስ ከሚለብሰው ጃኬት ላይ የተበጠሰ የወርቅ አዝራር አግኝተዋል ይባላል ፥ ይህ ልክ ነው?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"እና ለሚስተር ዴሚሪስ ወንጀለኛነት ዋነኛው ማስረጃ አዝራሩ ነው ። በፖሊሶቹ ግምት ሟች ቱ ነፍሷን ለማዳን ስትታገለው የበጠሰችው መሆኑ ነው?"

"ትክክል ።"

"ታዲያ አዘውትሮ ላለባበሱ የሚጨነቅ የሚስተር ዴሚሪስ ዓይነት ሰው የጃኬቱ ቁልፍ መጉደል ፊት ለፊት እየታየው ሳያስተውል ቀረ? እቤቱ ውስጥ እየለበሰውም ልብ ሳይለው ቀረ? አውልቆት ቁም ሳጥኑ ውስጥ ሲሰቅለው እንዴት መበጠሱን አያይም? የመቶ አለቃ ፥ ይህማ ተከሳሹ ጅል ብቻ ሳይሆን ዓይነስውርም ነበር ማለት ነው?"

ተከታዩ ምስክር ሚስተር ካቴላኖስ ነበር ። የግል የወንጀል መከላከያና ምርመራ ድርጅት ባለቤት የሆነው ካቴላኖስ በአለባበሱ በጣሙን ደምቋል ።

ዴልማ "የግል የምርመራ ድርጅት ባለቤት ነህ?" ሲል ጥያቄ አቀረበለት ።

"አዎ ጌታዬ ።"

"እና ሚስስ ዴሚሪስ ከመገደሏ ከጥቂት ቀናት በፊት ልታነጋግርህ መጥታ ነበር?"

"ትክክል ነው ።"

"ምን ፍለጋ ነበር?"

"ጥበቃ ። ባለቤቷን ለመፍታት በመፈለጓ ሊገድላት እንደዛተባትና በዚህም የተነሳ የኛን ጥበቃ እንደምትሻ ገልጣለች ።"

ተመልካቹ ማጉረምረም ጀመረ ።

"እና ሚስስ ዴሚሪስ ተሸብራ ነበር?"

"አዎ ተረብሻ ነበር ።"

"ድርጅትህ ከባለቤቷ እንዲጠብቃት ነዋ የቀጠረችህ "

"አዎ ጌታዬ ።"

"ይበቃኛል ፤ አመሰግናለሁ ። " ዴልማ ወደ ቾታስ ዞር አለ ። "ምስክሩ ይኸውልህ ።"

ቾታስ ወንበሩን እያሽከረከረ ወደ ምስክሩ ተጠጋና "ሚስተር ካቴላኖስ በዚህ የምርምራ ሥራ ላይ ለስንት ዓመት አገልግሎት ሰጥተሃል?" አለው ።

"ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ።"

ቾታስ ተገረመ ። "በጣም ረዥም ጊዜ ነው በሥራህ የተካንክ ሳትሆን አልቀረህም ።"

"ይመስለኛል" አለ ካቴላኖስ ጉራ እንዳይመስልበት እየሰጋ ።

"እና ችግር የገጠማቸው ሰዎችን በመርዳት በኩል ሰፊ ዕድል አለህ ማለት ነዋ!"

"ለዚህ አይደል ወደእኔ ዘንድ የሚመጡት!" አለ ካቴላኖስ ።

"እና ሚስስ ዴሚሪስ ወደአንተ ዘንድ ስትመጣ የተረበሸች ትመስል ነበር ፤ ወይንስ ...?"

"አዎ በጣም የተረበሸች ትመስል ነበር ። ደንግጣ ነበር ለማለት ይቻላል ።"

"አሃ ምክንያቱም ባለቤቴ ይገድለኛል ብላ ፈርታ ስለነበር?"

"ትክክል ።"

"ታዲያ ከቢሮህ እንደወጣች ስንት ሠራተኞችህን እንዲከተሏት አደረግህ? አንድ? ሁለት?"

"የለም ፣ የሚከተላት እንኳ አልመደብኩላትም ።"

ቾታስ ተኩሳተረ ። "ለምን ያኔውኑ እንዳልመደብክላት ሊገባኝ ግን አልቻለም ።"

"ምክንያቱም እስከሰኞ ድረስ ጥበቃችንን እንድንጀምር አልፈለገችም ነበር ።"

ቾታስ ግራ ተጋብቶ ወደእርሱ ተመለከተ ። "ሚስተር ካቴላኖስ ነገሮችን እያምታታህብኝ ነው ። ባለቤቴ ሊገድለኝ ስለሆነ በጣም ፈርቻለሁ ያለች ሴት እንዴት እስከመጪው ሰኞ ድረስ ጥበቃ እንዲደረግ ልኝ አልሻም ትላለች?"

"ይኸው ነው እንግዲህ እንዲሁ ነበር ያለችኝ ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ለእራሱ እንደሚናገር ቀስ ባለ ድምፅ "የሚስስ ዴሚሪስ ፍራቻ ምን ያህል እንደነበር መቼም እግዜር ይወቀው ።"

የዴሚሪስ የቤት አገልጋይ ለምስክርነት ቀረበች ። "በሚስስ ዴሚሪስና በባለቤቷ መካከል በስልክ የተደረገውን ውይይት በትክክል ሰምተሻል?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"ውይይቱ ምን እንደነበር ልትነግሪን ትችያለሽ?"

"ሚስስ ዴሚሪስ ባለቤቷን ልትፈታው እንደምትፈልግ ገልጻለት እርሱም ይህንኑ አሳቧን እንደማይቀበል ነግሯታል ።"

ዴልማ የፍርድ አሳብ ሰጪዎቹን ቃኘ ። "ገባኝ" ተመልሶ ወደምስክሯ አየ ። "ሌላስ የሰማሽው ነገር አለ?"

"በባሕር ዳርቻ ቤቱ በዘጠኝ ሰዓት ብቻዋን መጥታ እንድታገኘው ቀጠሮ ሰጥቷት ነበር ።"

"ብቻሽን መምጣት አለብሽ ነው ያላት?"

"አዎ ። እስክ አሥራ ሁለት ሰዓት ባትመለስ ለፖሊስ እንዳመለክትም አዛኝ ነበር ።"

የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ አስተያየት ሲለዋወጥ በግልጽ ይታይ ነበር ። ሁሉም ዞር አሉና ዴሚሪስን በትኩረት ተመለከቱት ።

"ጥያቄዬን ጨርሻለሁ ።" ዴልማ ወደ ቾታስ ዞር አለና "የተከሳሽ ጠበቃ ልትጠይቃት ትችላለህ" ሲል ተናገረ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ወንበሩን እያሽከረከረ ምስክሯ ወደ ቆመችበት ሥፍራ ተጠጋ ።

"ስምሽ አንድሪያ ነው አይደል?"

"አዎ ጌታዬ" አስቀያሚና አስፈሪ ወደሆነው ፊት ላለመመልከት ሞከረች ።

"አንድሪያ ፣ ሚስስ ዴሚሪስ ባሏን ልፈታህ እፈልጋለሁ ብላ ስትነግረውና ሚስተር ዴሚሪስም ለዚሁ ጥያቄዋ ምላሽ ለማግኘት በዘጠኝ ሰዓት ብቻዋን ወደባሕር ዳርቻው ቤት እንድትመጣ ሲጠይቃት መስማትሽን ተናግረሻል ፣ ይህ ልክ ነው?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"አንድሪያ ፣ መሐላ መፈፀምሽን አትርሺ አንድሪያ አንቺ የሰማሺው ይህንን አይደለም ።"

"አዎ ይህ ነው ጌታዬ ።"

"በክፍሉ ውስጥ ስንት ስልክ ነበር?"

"አንድ ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ወንበሩን እያሽከረከረ ወደምስክሯ ተጠጋ ። "ሌላ ስልክ አንስተሽ ሙሉ ንግግራቸውን አላዳመጥሽም ማለት ነው ።"

"እንዴት እንደዚያ አደርጋለሁ ጌታዬ?"

"እንግዲያውስ አንቺ የሰማሺው ሚስስ ዴሚሪስ የተናገረችውን ብቻ ነው ። የባሏን ንግግር ማዳመጥ ግን አይቻልሽም ነበር ።"

"እኔ ግን ስገምተው ..."

"በሌላ አነጋገር ሚስተር ዴሚሪስ ሚስቱን ሲያስፈራራ ወይም ወደባሕር ዳርቻው ቤት እንድትመጣ ሲጠይቃት አሊያም ሌላ ነገር ሲናገር በጆሮሽ አልሰማሽም ማለት ነው ። ይህንን የተናገርሺው ሚስስ ዴሚሪስ ስትናገር ስለሰማሽ ከሚስተር ዴሚሪስ ጋር ላይሆን አይቀርም በሚል ግምት ነው ።"

አንድሪያ ግራ ተጋባች ። "መልካም ፣ ነገሩ እንዳልከውም ሊሆን ይችላል ።"

"እንዳልኩት ሊሆን ይችላል ። ለመሆኑ ሚስስ ዴሚሪስ ስልክ ስታነጋግር አንቺ ክፍሉ ውስጥ የነበርሽው ለምንድን ነው?"

"ሻይ እንዳቀርብላት ጠይቃኝ ነው ።"

"እና ሻይውን አመጣሽላት?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"ጠረጴዛ ላይ ነው ያስቀመጥሺው?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"ታዲያ ለምን ከክፍሉ አልወጣሽም?"

"ሚስስ ዴሚሪስ እንድቆይ በእጇ ምልክት ስለሰጠችኝ ።"

"አንቺ እርግጠኛ ውይይቱን እንድታዳምጪ ነው? ወይንስ ውይይት መስሎ እንዲሰማሽ ለማድረግ አስባ ነው?"

"መሰለኝ ።"

ድምፁ እየጠነከረና እየቀጠነ መጣ ። "ስለዚህ በስልኩ ባለቤቷን ታናግር ፣ ወይንም ለይስሙላ ብቻዋን ትለፍልፍ የምታውቂው ነገር የለም ማለት ነዋ!" ቾታስ ወንበሩን ይበልጥ ወደ እርሷ አስጠጋ ። "ወደክፍሉ ስትገቢ ስልኩን አቋርጣ ሚስስ ዴሚሪስ አንቺን ቆዩ ማለቷን እንደእን ግዳ ነገር አትቆጥሪውም? እኔ እንደማውቀው እቤቴ ውስጥ የግል ውይይት በማድረግ ላይ ያለን ከሆነ ማንም የቤቱ ሠራተኛ ወዳለንበት ክፍል ውስጥ እንዲገባ አንፈቅድለትም ። ግልጽ ለማድረግ ያህል ያ ውይይት ጨርሶ አልተካሄደም ። ሚስስ ዴሚሪስ ማንንም አላነጋገረችም ። ሆነ ብላ ከባለቤቷ ጋር እንደምታወራ በማስመሰል በዚህች ዕለት በዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ በመረጃነት የሚያደናግር ወሞመድ አዘጋጀች ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ባለቤቱን አልገደለም ። በእርሱ ላይ የቀረቡት በጥንቃቄ የተወጠኑ ማስረጃዎች ሁሉ ሆነ ብለው የተሸረቡ ናቸው ። ማንም ብልህ ሰው ወንጀል ፈጽሞ እንዲያ ዓይነት ማስረጃ ከኋላው ሊተው አይችልም ። የሚተው ይኖራል ቢባል እንኳ እንደ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያለ ብልህ እንዲህ አያደርግም ።"

በፍርድ ቤቱ ለአሥር ቀናት ክርክር ሲካሄድ መከላከያ ሲሰማ እንዲሁም የልዩ ወንጀል ተከታታዮች ማረጋገጫ ሲቀርብና የፖሊስ ማስረጃ ሲታይ ቆየ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወንጀለኛ ላይሆን አይቀርም የሚል ግምት በአብዛኛው ሰው ዘንድ አደረ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ቦንቡን ለማፈንዳት መዘግየቱን መረጠ ። ስፒሮስ ላምብሩን በምስክር ቃል መስጫ ሳጥን ውስጥ አቆመው ። የዕለቱ ችሎት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የሂሊኒክ ንግድ ኮርፖሬሽኑና ሌሎችም

ንብረቶቹ ሁሉ ወደስፒሮስ ላምብሩ ይዞታ እንዲዛወሩ ዴሚሪስ ውል ፈርሟል ። እንድ ቀን ቀደም ብሎም እነኚህ ንብረቶቹ በምስጢር ወደናፖሊዮን ቾታስ ይዞታ ተዛውረዋል ። ይህ የንብረት ዝውውር ውል የሚፀናው ግን ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከተመሠረተበት ክስ በነፃ የተለቀቀ እንደሆነ ብቻ ነው ።

"ሚስተር ላምብሩ ፣ በአንተና በእህትህ ባለቤት በኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሃከል አለመግባባት ነበር ይባላል ፣ እውነት ነው?"

"አዎ ፣ ስምምነት አልነበረም ።"

"በሁለታችሁ መካከል መቃቃር ነበር ለማለት ይቻላል?"

ላምብሩ ወደኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተመለከተ ። "ይቻላል ። ከመቃቃርም በላይ ነበር ።"

"እህትህ በጠፋች ቀን ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በባሕር ዳርቻው ቤት አካባቢ እንዳልነበረ ለፖሊሶች ተናግረህ ነበር ። እንዲያውም በዘጠኝ ሰዓት ግለትም እህትህ ተገደለችበት በተባለው ሰዓት ዴሚሪስ በአክሮ ኮሪንዝ ካንተ ጋር እንደቆየ ነበር የገለፀው ። ፖሊሶች የአንተን ማረጋገጫ በጠየቁበት ወቅት ግን በሰዓቱ ካንተ ጋር መቆየቱን ክደህ ነበር ።"

"አዎ ክጂአለሁ ።"

"ለምን?"

ላምብሩ ለረዥም ጊዜ ዝም ብሎ ተቀምጦ ቀረ ። ከዚያም በንዴት "ዴሚሪስ እህቴን በየጊዜው እየሰደበ ፣ እያጥላላና ሌላም ውርደት እያስከተለባት ስላበሳጫት እንዲቀጣ ፈልጌ ነበር ያቀድኩት ። ወንጀል ተፈጸመ በተባለበት ሥፍራ እንዳልነበረ እንድመሰክርለት ይፈልግ ነበር። እኔ ደግሞ ልመሰክርለት አልፈለግሁም ።"

"አሁንስ?"

"በዋሾነት ልቆይ አልፈልግም ። እውነት መናገር እንዳለብኝ ተሰምቶኛል ።"

"ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ አንተና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአክሮ ኮሪንዝ አንድ ላይ ነበራችሁ?"

"አዎ እርግጠኛ ነኝ አንድ ላይ ነበርን ።"

በፍርድ ቤቱ ውስጥ ሁካታ ተሰማ ። ዴልግ ፊቱ በርበሬ እንደመሰለ ከተቀመጠበት ተነሳ ። "ክቡር ጌታዬ ፣ ተታውሞ አለኝ ..."

"ተታውሞህ ተቀባይነት የለውም ።"

ዴልግ ተመልሶ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ። ዓይኑ የፈካው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደፊት አዘንብሎ ተቀመጠ ።

"እስቲ እንዴት እንደተገናኛችሁ አጫውተን ። እንድትገናኙ አሳብ ያቀረብከው አንተ ነህ?"

"አይደለም አሳቡ የሜሊና ነበር ። ሁለታችንንም አታልላን ነው ።"

"እንዴት አድርጋ ነው ያታለለቻችሁ?"

"ሜሊና በስልክ ደወለችልኝና ባልዋ በግል መዝናኛ ክበቤ ውስጥ ለንግድ ሥራ ጉዳይ ሊያነጋግረኝ እንደሚሻ ገለጠችልኝ ። እንደገና ደግሞ ለዴሚሪስ ደውላ እኔ ላገኘው እንደምፈልግ ነገረችው ። በተባለው ሥፍራ እንደተገናኘን ሁለታችንንም የሚያወያየን ነገር አልነበረም ።"

"እና ሁለታችሁ የተገናኛችሁት ሚስስ ዴሚሪስ ሞተች በተባለው ሰዓት ነው?"

"ትክክል ።"

"እኔ ሰዓት አስይዤ እንዳስጠናሁት በመኪና ከአክሮ ኮሪንዝ እስከ ባሕር ዳርቻ ቤቱ አራት ሰዓት ይፈጃል ።" ናፖሊዮን ቾታስ ወደፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ዞር ብሎ ተመለከተ ። "ስለዚህ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዘጠኝ ሰዓት በአክሮ ኮሪንዝ ታይቶ ተመልሶ ደግሞ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት አቴንስ ውስጥ ሊገኝ በፍፁም አይችልም ። "ቾታስ ወደስፒሮስ ላምብሩ ዞር ብሎ ተመለከተ ። ቃለመሐላ ፈፅመሃል ላምብሩ ። ለዚህ ፍርድ ቤት የሰጠኸው ቃል እውነተኛ ነው?"

"አዎ ነው ። እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ።"

የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ለአራት ሰዓታት ለምክክር ቆይታ አድር ገው ተመልሰው ወደፍርድ ቤቱ ሲገቡ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በጥሞና ይመለከት ነበር ። ፊቱ ገርጥቶ በጉጉት ውሳኔውን ይጠባበቃል ። ቾታስ ግን ወደሰዎቹ እንደማየት አተኩሮ የሚያየው የኮንስታንቲን ዴሚሪስን ፊት ነው ። ያ ሁሉ የዴሚሪስ ትዕቢትና ኩራት አሁን አይታይም ። ከሞት ፊት ለፊት የቆመ ሰው ነው ።

የመሐል ዳኛው "የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎች ከውሳኔ ላይ ደረሱ?" ሲሉ ጠየቁ ።

"አዎ ደርሰናል ፣ ክቡር ጌታዬ ።" የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ሰብሳቢ

ወረቀት ይዞ ተነሳ ።

"እባክህ ውሳኔውን ለአስተናባሪው ትሰጥልኝ?"

አስተናባሪው የውሳኔውን ወረቀት ተቀበለና ለመሐል ዳኛው ሰጣቸው ። የመሐል ዳኛው ወረቀቱን አዩና ቀና ብለው "የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ አላገኙትም" ሲሉ ገለፁ ።

በፍርድ ቤቱ ውስጥ ጫጫታ በረከተ ። ግማሹ ተነስቶ ሲያጨበጭብ ሌላው ደግሞ ያተረመርማል ።

የዲሚሪስ ፊት ፈካ ። በንይል ወደውስጥ ተነፈሰና ተነስቶ ችታስ ወዳለበት ሥፍራ ሄዶ "እንዳልከው አደረግክ! ትልቅ ባለውለታዬ ነህ ።" አለው ።

ችታስ ትኩር ብሎ ዓይን ዓይኑን እያየ "እዚህ ላይ አበቃን ። እንግዲህ እኔ ስከብር አንተ ደግሞ ደህይተሃል ። በል አሁን የደስ ደስ ልበልህ ።"

ኮንስታንቲን ዲሚሪስ የችታስን ተሽከርካሪ ወንበር እየገፋ በሕዝቡና በጋዜጠኞች መካከል አልፎ ወደመኪና ማቆሚያው አመራ ። ችታስም ከፍርድ ቤቱ መግቢያ አጠገብ ወደ ቆመችው ሲዳን መኪና አመለከተ ። "መኪናዬ ያችጋና ።"

ዲሚሪስ ወንበሩን እየገፋ ወደ መኪናዋ ተጓዘ ። "ምነው ሾፌር የለህም?"

"አያስፈልገኝም ፣ እኔ ራሴ እንድነዳት ሆና በልዩ ትዕዛዝ የተሠራች ልኝ ናት ። ወደውስጥ አስገባኝ ።"

ዲሚሪስ የመኪናዋን በር ከፈተና ችታስን ተሽከሞ ከመሪው አጠገብ አስቀመጠው ። ተሽከርካሪ ወንበሩንም አጣጥፎለት ከኋላ ኮፈን ውስጥ ከከተተው በኋላ እራሱም መኪናው ውስጥ ገብቶ ከችታስ ጐን ተቀመጠ ።

"አሁንም በዓለም ውስጥ ያሉት ጠበቃዎች ቁንጮ ነህ" ሲል ኮንስታንቲን ዲሚሪስ ፈገግ አለ ።

"አዎ" አለና ናፖሊዮን ችታስ መኪናውን አስነስቶ ማሽከርከሩን ቀጠለ ። "አሁን ምን ልትሠራ አስበሃል ኮስታ?"

ዲሚሪስ በጥንቃቄ "ምን ታደርገዋለህ እንደምንም ብዬ እራሴን ለማቋቋም እሞክራለሁ" ብሎ መለሰ ። በልቡ ግን 'በመቶ ሚሊዮን ዶላር እንደገና የእራሴን ሰፊ ድርጅት አቋቁማለሁ' አለ ።

ዲሚሪስ እየሳቀ "ስፒሮስ ፣ እንዴት እንዳታለልከው ሲረዳ በጣም መበሳጨቱ ነው ።"

"ከእንግዲህ ምን ሊያደርግ ይችላል ብለህ ነው?" ሲል ማረጋገጫ ሰጠው ። "ባዶ ኩባንያ የሚያሳቅፈው ውል ነው የተፈራረመው ።"

ወደተራራው ተጓዙ ። ችታስ የፍሬን መያዣና የቤንዚን መስጫ ውን እንዲሁም ማርሽ መቀየሪያውን እየተቆጣጠረ መኪናውን ሲያሽከረክር ዲሚሪስ ይመለከት ነበር ። "ደህና አድርገህ ነው የምትነዳው ።"

"የግድ ሲሆንብህ ትማራዋለህ" አለ ችታስ ። በጠባቧ መንገድ ወደተራራው ጫፍ አሽከረከረ ።

"ወዴት ነው የምንሄደው?"

"እዚህ ጫፉ ላይ ትንሽ ቤት አለችኝ ። አንዳንድ ብርጭቆ ሽምታኝ እንጠጣና በታክሲ ወደ ከተማ እልክሃለሁ ። ታውቃለህ ኮስታ ፣ ከዚህ ቀደም ስለተፈጸሙት ነገሮች አስብ እንደነበረ ... ስለ ኖኤሌ ሞት ፣ ስለላሪ ዶግላስ ሞት ፣ እንዲሁም ስለዚያ ምስኪን ስታቭሮስ ። ግን መቼም የሦስቱም እሚሚት ከገንዘብ ጋር በተገናኘ ምክንያት ነው አትለኝም ።" ዞር ብሎ ዲሚሪስን ተመለከተው ። "ሁሉም በጥላቻ ምክንያት ነው ። በጥላቻና በፍቅር ። ኖኤሌን ትወዳት ነበር?"

"አዎ" አለ ዲሚሪስ ። "ኖኤሌን እወዳት ነበር ።"

"እኔምኮ እወዳት ነበር ግን እንደምወዳት አታውቅም ነበር አይደል?" አለ ችታስ ። ዲሚሪስ በመገረም ተመለከተው ። "አላውቅም ።"

"እንደዚያ ሆኖ እርሷን እንድትገድል ረዳሁህ ። ለዚያ ኃጢአቴ ምንጊዜም ከፀፀት አላመልጥም ። አንተስ ኮስታ?"

"ዋጋዋን ነው ያገኘችው ።"

"እኛም መጨረሻ ላይ ዋጋችንን እናገኛለን ። አንድ ያልነገርኩህ ነገር አለ ኮስታ ። የእሳቱ ጉዳይ የእሳት አደጋ ከደረሰብኝ ከዚያ ሌሊት ጀምሮ ልቋቋመው የማልችለው ሕመም ይሰማኛል ። ዶክተሮች መልሰው እንደነበርኩ ሊያደርጉኝ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም ። በመጥፎ ሁኔታ ነው ሰውነቴ ሽባ የሆነው ።" መኪናውን ለማፍጠን ማርሽ ቀየረ ። በጣም ጠባብ በሆነው ጠመዝማዛው መንገድ እየበረሩ ከተራራው ላይ ሲወጡ የኤጊአን ባሕር ከበታቻቸው ርቆ ወለል ብሎ ታየ ።

"እንደእውነቱ ከሆነ" አለ ችታስ በጐረነነ ድምፅ ። "በአሁኑ ወቅት የሚያሰቃየኝ ሕመም በሕይወት ኑር ፣ ኑር አያሰኝኝም ።" ማርሽ

ቀይሮ መኪናዋን የበለጠ አበረረ ።

"ቀስ በል" አለ ዴሚሪስ ። "ልትገለ..."

"እኔና አንተ አንድ ላይ እንዲያከትምልን ለማድረግ ወስኛለሁ ።"

በድንጋጤ የተዋጠው ዴሚሪስ ዞር ብሎ አየው ። "ምንድነው የምታወራው? ፍጥነት ቀንስ ነው የምልህ ሰውዬ ። ሁለታችንም እንዳናልቅ ።"

"ልክ ነህ" አለ ቾታስ ማርሹን እንደገና ሲለውጥ መኪናዋ ወደፊት ዘለለች ።

"እብድነህ ልበል? ሀብታም ሆነህ ሳለ ለምን ለመሞት ትፈልጋለህ?" አለ ዴሚሪስ ።

የተጠላበሱት የቾታስ ከንፈሮች ፈገግ ለማለት ሲሉ እጅግ አስፈሪ ሆኑ ።

"የለም እኔ ሀብታም አይደለሁም ። ግን ሀብታም እንደሆነ ታውቃለህ? ወዳጅህ ሲስተር ተሬዛ ። ገንዘብህን ሁሉ ኢኢኒና ለሚገኘው የሴቶች ገዳም ሰጥቻለሁ ።"

መኪናዋ ወደኩርባው አቅጣጫ ሸመጠጠች ።

"መኪናውን አቁመው" ሲል ዴሚሪስ ጮኸ ። መሪውን ከቾታስ ለመንጠቅ ቢታገል አልተቻለውም ።

"የምትፈልገውን ሁሉ እሰጥሃለሁ" አለ ዴሚሪስ በጭንቀት ። "አቁም!"

"የምፈልገውን አግኝቻለሁ" አለ ቾታስ ።

ወዲያው የተሳፈሩባት መኪና ከገደሉ ላይ ተንሳፍፋ እየተላተመች በፊትና በኋላ እየተገለባበጠች ረጅሙን የተራራ ቁልቁለት ጨርሳ ከባሕሩ ላይ ወደቀች ። የከባድ ፍንዳታ ድምፅ ተሰማ ። ከዚያም ረጭ ያለ ፀጥታ ።

ፍፃሜም ሆነ ።